የመለስ "ትሩፋቶች"

ባለቤት አልባ ከተማ

ኤርምያስ ለገሰ

የመለስ "ትሩፋቶች" ባለቤት አልባ ከተማ

YeMeles "Tirufatoch" Balebet Alba Ketema

Copyright © Ermias Legesse – 2014

የደራሲው መብት በህግ የተጠበቀ ነው - 2006

ነጻነት አሳታሚ ድርጅት

Published by Netsanet Publishing Agency

www.npabooks.com

የሽፋን ዲዛይን፣ ነጻነት አሳታሚ ድርጅት

ነጻነት አሳታሚ ድርጅት
Netsanet Publishing Agency

ጥቂት ስለጸሃፊው

አቶ ኤርሚያስ ለገሰ የኢህአዴግን ፓለቲካ የተጠጋው ገና የ20 አመት ወጣት ሆኖ በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ተማሪ እያለ ነበር። ትምህርቱን አንደጨረሰ የስራ አለም አህዱ ብሎ የጀመረው ደግሞ የዛሬዎቹን የመከላከያ ከፍተኛ መኮንኖች (አንዳንድ ጀነራሎች ጨምሮ) በማስተማር ነበር። ከእነዚህ ወታደራዊ መኮንኖች ጋር የነበረው መቀራረብ ወደ ኢህአዴግ ካድሬነት ለመሳብ በር ከፈተ። በ24 አመቱ የአዲስ አበባ ባ ምክርቤት አባልና የዞን ሁለት አስተዳደር ዘርፍ ሀላፊ ሆነ። በማስከተልም የአዲስ አበባ አማካሪ ምክር ቤት አባል እና የአቃቂ ቃሊቲ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በመሆን ተመደበ። ከምርጫ 97 በኃላ በኢህአዴግ ቢሮ የአዲስ አበባ ክንፍ ስራ አስፈጻሚ ሆነ። የምርጫ 2000 ውጤትን ተከትሎ የአዲሳስ አበባ ምክር ቤት አባል፣ የከንቲባው የፓለቲካ ጉዳዮች አማካሪና የመንግስት ዋና ተጠሪ በመሆን አገልግሏል። በመጨረሻም በማስታወሻው የተለያዩ ቦታዎች ላይ በገለጻቸው ምክንያቶች ሀገሩን ለቆ እስኪወጣ ድረስ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ሚኒስትር ዴኤታ ነበር።

አቶ ኤርሚያስ በኢህአዴግ የፓለቲካ ጉዳና በአባልነት፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ ካድሬነት ከ12 አመት በላይ ተጉዟል። በዚህም ምክንያት በፓርቲው፣ በመዲናይቷና በሀገሪቷ ወሳኝ የፓለቲካ ምእራፎች ያለፈ ሲሆን በትላልቅ ጉዳዮች ላይ መሪ ተዋናይ ነበር። በሀገር አቀፍ ደረጃ በተካሄደው ምርጫ 92፣ 97 እና 2000 በእጩነት እና አመራርነት ተሳትፏል። አዲስ አበባ ከፕሬዝዳንት አሊ አብዶ እስከ ከንቲባ ኩማ ደመቅሳ የተጓዘችበትን መንገድ አብሮ ተጉዟል። የአዲስ አበባ ቻርተር የተዘጋጀበት አላማ፣ ከረቂቅ እስከ ትግበራ የሄደበትን ሂደት ጠንቅቆ ያውቀዋል። ኢህአዴግ አሁን የያዘው ቅርጽና ግዝፈት ለማረጋገጥ በተከናወኑ ተግባራት ቀደምት ተሳታፊ ነበር።

በመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ጽህፈት ቤት በነበረው ቆይታ ደግሞ በሀገሪቷ ፓለቲካ ምህዳር እስከ አሁንም አጨቃጫቂ የሆኑ ጉዳዮች በእንድ ወይም በሌላ መልኩ ተሳታፊ ነበር። የፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ፣ የኤርትራውያን ንብረት ለመመለስ የወጣውን አዋጅ ለመጀመሪያ ጊዜ ለህዝብ ይፉ ያደረገው እሱ ነበር ። ከመንግስት ግልበጣ፣ ወደ ባለስልጣናት ግድያ ከዛም ቀቢፀ-ተስፉ የተባለውን የመንግስት መግለጫ ሲያስተጋባ የነበረው እሱ ነበር። ይህን አስመልክቶ ከአሜሪካ ኤምባሲ ጋር ያደረገው ሚስጥራዊ ውይይት በዊክሊክስ ላይ ይገኛል። በሱዳኑ ፕሬዝዳንት አማር አልበሽር ላይ የተላለፈውን የዘር ማጥፋት ውሳኔ ተከትሎ በተሰጠው ምላሽ ከአለም የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያ ስትሆን፣ ምላሹን በቪኦኤ የሰጠው ደግሞ እሱ ነበር። የኢትዮጵያ መንግስት በታሪኩ ለመጀመሪያ እና መጨረሻ ጊዜ ለአሜሪካን ውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት አመታዊ የሰብአዊ መብት ሪፓርት የተጣራ ምላሽ ሲሰጥ ሂደቱን በመምራትና መግለጫ በመስጠት ተሳትፏል። የአዲስ ነገር ጋዜጣ መዘጋት፣ የጋዜጠኞች መሰደድና በሽብርተኝነት መከሰስ ከጥንስሱ እስከ ፍጻሜው የነበረውን ሂደት በቁጭት ይገልፀዋል።

አቶ ኤርሚያስ በዚህ እድሜው ተዝቀው የማያልቁ አስደማሚ ታሪኮች ባለቤት ነው። በማስታወሻው ያቀረባቸው ፓለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ስነልቦናዊ ጉዳዮች በታሪክ ደረጃ ብቻ የሚታዩ ሳይሆን ወቅታዊውን እና የወደፊቱን የሀገሪቷን ጉዞ የሚያመላክቱ ናቸው። የጻፈውም ኢትዮጵያ የምትባለውን ትልቅ ሀገር ለመረከብ በትግል ላይ ላሉና በየትኛውም መስመር ለተሰለፉ ወጣቶች ነው። "የኢትዮጵያ ወጣቶች ሀገሪቷ ያለችበትን ተጨባጭ እውነታ ተገንዝበው የሚጓዙበት

መንገድ መስቀለኛ፣ አባጣ ጐርባጣና ጥልፍልፍ እንደሆነ መግንዘብ ይኖርባቸዋል" ይለናል። በየትኛውም መስመር ያሉ ኢትዮጵያዊ ወጣቶች እንደ ሰው የመታየት፣ የዲሞክራሲ፣ የፍትህና የነፃነት ጥማት እንዳላቸው በድናት ከማመንም አልፎ በማስታወሻው ላይ በተደጋጋሚ ይገልጻል። ከአያቶቻችን፣ ከአባቶቻችንና ወንድሞቻችን መውረስ የሚገባን በጐ ነገሮች እንዳሉ ሆነው እነሱ ያለፉባቸው የጥላቻና ቂም በቀል መንገዶች ቦታ እንደሌላቸው አጽንኦት ይሰጣል። የወደፊቷን ኢትዮጵያ በጋራ መግባባት፣ በቁጭት መንፈስ፣ ይቅርባይነት፣ የዘመናዊ አስተሳሰብ የመግንባት ጉዳይ በወጣቶች ጫንቃ ላይ የወደቀ እንደሆነ ያሳስባል።

አቶ ኤርሚያስ የሚያነሳቸው ጉዳዮች ወቅታዊና አንገብጋቢ ቢሆኑም በአንድ ማስታወሻ የሚገደብ ሆኖ አላገኘነውም። በዚህም ምክንያት ከላይ ከተጠቀሱት ውስጥ እጅግ በጣም ጥቂቶቹን ብቻ በዚህ ማስታወሻ ለማካተት ተገደናል።

በመሆኑም ይህ "የመለስ ትሩፋቶች" በተሰኘው መጽሐፍ ለማተኮር የፈለግነው የአዲስ አበባን አስር አመት ጉዞ፣ ኢህአዴግ በምርጫ 97 ምን ዘርቶ ምን እንዳጨደ እና ከምርጫ 97 በኋላ የተከናወኑ ተግባራት የአገሪቷን መጻኢ እድል ላይ ያሳረፉትን አሻራ ይሆናል። "የመለስ ትሩፋቶች" መጽሀፍ የኤፌዴሪ ህገ - መንግስትና የአዲስ አበባ ቻርተር ተቀናጅተው መዲናይቷን ነዋሪና ባለቤት አልባ አድርገዋታል ትለናለች። በአቶ በረከት የተጻፈችው "የሁለት ምርጫዎች ወግ" መጽሀፍ ለህዝብና ለታሪክ ያቀረበችው ወግ የተዛባና ከእውነት የራቁ ትንታኔዎች የቀረቡበት እንደሆነ በተጨባጭ መረጃ ታመላክታለች። ከሁሉም በላይ ነዋሪው የተነጠቀውን ከተማ ለማስመለስ ያደረገው እልህ አስጨራሽ ትግልና መስዋእትነት በታሪክ ማስታወሻነት ተመዝግቦ መቆየት እንዳለበት የፀና እምነት አላት።

ነጻነት አሳታሚ ድርጅት

ግንቦት 2006

መታሰቢያነቱ

በአምባገነኑ ስርአት ሰለባ ለሆንከው አባቴ ለገሰ ዋቅጅራ
እና ለልጆቻችሁ መስዋት በመሆን ያለጊዜያችሁ ከመሬት በታች ለዋላችሁት
እናቶቼ እቴነሽ ቸርነትና ብዙነሽ በቀለ ይሁንልኝ።

ምስጋና

በአሜሪካን ሀገር ለምትኖረው ወንድሜ ዳንኤል ለገሰ (ዶ/ር)።

የአንድነት ፓርቲ ም/ሊቀ መንበር ለነበርከው
አንዱአለም አራጌ

ምንም እንኳን ባታውቀኝ የፖለቲካ እስርኛ መሆንህን
እረዳለሁና የአንተን ስሜት ለመጋራት ከዚህ መጽሃፍ ከሚገኘው ገቢ ሃያ
በመቶውን ለሁለት ልጆችህ የተወሰኑ ወራት የትምህርት ቤት ወጪ እንዲሆን
ወስኛለሁ።

ማውጫ

እንደ መክፈቻ 1

ክፍል አንድ: የመዲናይቱ ህዳሴ አሳቢዎች ! 9
ምእራፍ አንድ 10
የህዝቦቿን ሉአላዊነት የተገፈፈች መዲና! *10*
ምእረፍ ሁለት 25
"ንቅል ካደሪ!" *25*
ምእራፍ ሶስት 32
" ስናይፐር ተኳሽ" *32*

ክፍል ሁለት: የጨፈው ግምገማ 38
ምእራፍ አራት 39
ባህታዊ የመራው የክህንቸሰ መንግስት! *39*
ምእራፍ አምስት 45
ዶንቦስኮና ሞንጀሪኖ! *45*
ምእራፍ ስድስት 58
ኢህአዴግን ከአዲሳባ ያባረረው - ምርጫ 92 ..... *58*
ምእራፍ ሰባት 76
ዘቡተሎው መሪ ! *76*
ምእራፍ ስምንት 96
"ህገ -መንግስት በጠረባ !" *96*

ክፍል ሶስት : የጥፉቱ ቅብብሎሽ: ከመመሪያ ቁጥር አንድ ወደ ሁለት ወደ*** 103
ምእራፍ ዘጠኝ 104
መመሪያ ቁጥር አንድ !! *104*
ምእራፍ አስር 113
መመሪያ ቁጥር ሁለት! *113*
ምእራፍ አስራ አንድ 119
መመሪያ ቁጥር ሶስት!! *119*

ክፍል አራት : የምርጫ 97 መባቻ 130
ምእራፍ አስራ ሁለት 131
"ከተማን በጠበር ስሌት" *131*
ምእራፍ አስራ ሶስት 141
ቆርኪው ሲለጥ *141*

ክፍል አምስት: የምርጫ 97 ክስተቶች 156
ምእራፍ አስራ አራት 157
ለምን እናሸንፋለን? *157*
ምእራፍ አስራ አምስት 162
የምርጫ 97 ዋዜማ *162*
ምእራፍ አስራ ስድስት 180
ግንቦት 6: 1997 (የጠቆረ ትዝታ) *180*
ምእራፍ አስራ ሰባት 214
ግንቦት 7 1997 ..... *214*
ምእራፍ አስራ ስምንት 224
ለምን ተሸነፍን? *224*
ምእራፍ አስራ ዘጠኝ 240
ያልተቋጨው የሬንፌኔ አጀንዳ *240*
ምእራፍ ሃያ 255
ጉንጭ አልፉው ግምገማ *255*
ምእራፍ ሃያ አንድ 278

የህዝብ መድረኮች *278*

ክፍል ስድስት: ምርጫ 2000 ..... **298**

ምእራፍ ሃያ ሁለት 299

የ2000 ምርጫ አቅጣጫዎች *299*

ምእራፍ ሃያ ሶስት 318

እውን ታሪክ ራሱን ደገመ ? *318*

ምእራፍ ሃያ አራት 341

የበቀለ ጅራፍ *341*

ክፍል ሰባት: የአርማጌዶን ጦርነት **348**

ምእራፍ ሃያ አምስት 349

የሐመሩ(ሐ) ፓለቲካ *349*

ምእራፍ ሃያ ስድስት 361

የአከራሪነት ጫካ *361*

ክፍል ስምንት: የጐበልስ ትእዛዛት ማጠንጠኛ - "THE BIG LIE THEORY" **380**

ምእራፍ ሃያ ሰባት 381

ያልሞተው አስሰት *381*

ምእራፍ ሃያ ስምንት 389

ጐብልስ በአዲሳአባ *389*

እንደ መነሻ

የካቲት 23፣ 2004። የሞት ያህል የከበደኝ ጭንቀት ድንገት ጥሎኝ ሸሸ። ውስጤ እፎይ ሲል ነፍሴ ስትረካ ታወቀኝ። አጥንቶቼን እንደ እሳት የሚጠብሰው ግለት ጋብ አለ። ከራሴ ጋር የገጠምኩት ግብግብ መልስ አገኘ። የግል ማስታወሻዬን የህዝብ ሀብት ለማድረግ ወሰንኩ። ኢህአዴግ ውስጥ እንደ መኖሬና ማደጌ መጠን ገጠመኞቼ ድርጅታዊና አገራዊ ይዘታቸው ሚዛን ስለሚደፉ።

ውሳኔዬን ተከትሎ በርካታ ተቃውሞ በዙሪያዮ ካሉ ወዳጆቼ ገጥሞኛል። ያበደ ያህል የቆጠሩኝ ጥቂት አይደሉም። እኔ የለሁበትም ያሉኝም አልታጡም። ስጋታቸው ይገባኛል። ከኢህአዴግ ጋር መላተም ከአንበሳ ጋር ስጋ የመናጠቅ ያህል ከባድ እንደሆነ አውቃለሁ።

ግን ደግሞ አንበሳውም ሆነ እኔ ስጋ እንደሆንን ግልፅ ነው፣ ስጋ የሚናጠቁ ስጋዎች። ለመቆም የመታገላችንን ያህል መውደቃችን አይቀሬ ነው። እስከንወድቅ የሚያቆመን ደግሞ በውስጣችን ያለው እውነት እንጂ እንደ ቻይና ግንብ በፕሮፓጋንዳ ብዛት የገዘፈ ስግችን አይደለም።

ሲጀመር ኢህአዲግ እራሱ በፈጠረው ባህር የሚቀዝፍ፣ መነሻው መድረሻ የሆነበት ድርጅት ነው። ይህ ባህር የራሱ የሚባሉ የቀዘፋ ሕግጋቶች አሉት። ስለነዚህ ሕግጋት አጠናቆ ለመፃፍ ቢያንስ ሶስት ጊዜ መወለድ ሊያስፈልግ ይችላል።

ሕግጋት አንድ: **እውነት የተደጋገመ ኩሸት ነው**። ከኢህአዴግ ጋር ያቆራረጠኝ ከራሴም ጋር ቅራኔ ውስጥ የዘፈቀኝ ሕግ ይህ ነበር። ለኢህአዴግ ደቀ-መዛሙርት የኩሸት ክፋቱ አለመደጋገሙ ነው። ከተደጋገመ ኩበረት የጠጠረ እውነት ይወጣዋል፣ ከአለት የደደረ የአስተሳሰብ ልዕልና ያረጋግጣል። የኩሸቱ ዋነኛ አቀንቃኝና አስተጋቢ ያደርጋል።

ማስረጃ ካስፈለገ ከመልክተ ዜናዊ አለያም ከትንቢተ ስምኦን መጠቃቀስ እችላለሁ። ለዛሬው ፅሁፌ መነሻ የሆነኝ ከነዚህ ድርሳናት አንዱ የሆነው ገድለ

ኢህአዴግ ነው። ይህ ገድል የሁለት ምርጫዎች ወግ የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል።

እኔ ብሆን ሰውዬው ተአምረ ኢህአዴግ ነበረ የምለው። መልእክተ ስምአን ወደ አቢሲኒያ ሰዎችም መጽሀፉን የሚመጥን ርእስ ይመስለኛል። በዚህ ገድል ምእራፍ ሶስት ስር አዲሳ አበባን በተመለከተ የሚመለከተውን ኢህአዴግአዊ እውነታ ሲቀለጨለጭ እናገኘዋለን፣

"*** የአዲስ አበባን የምርጫ ውጤት እየሰማን ባለንበት ሰዓት በከተማው ከተመደቡት ጓዶች አንዱ የሆነውና መልካም ስራ በመስራት በቅንነትና በታማኝነት ሲፈጋ የከረመው ጓድ በአዲስ አበባ ውጤት ተበሳጭቶ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ። የአዲስ አበባ ህዝብ ለምን ይጠላናል የሚል ጥያቄ አነሳ። ኢህአዴጎች በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ስናልፍም ቢሆን ፈተናውን ወገባችንን ጠበቅ አድርገን ማለፋችን የተለመደ ነው። ብዙውን ሰው የሚያደናግጡ ወይም የሚያሸብሩ ጉዳዩችን፣ የኢህአዴግ አባላት ሲሆን እንደ ቀላል አሊያም ጥርሳቸዉን ነክሰው ያልፉሉ እንጂ ማልቀሳቸውን የተለመደ አይደለም። የኢህአዴግ አባላት ህዝብ በአንድ ወቅት በሚያሳልፉቸው ውሳኔዎች ወይም ከእኛ የተለዩ አቋሞች በመበራገግ ይህን የመሰለ መደምደሚያ ላይ አንደርስም።እናም በቅንነቱ የሚታወቅና በጣም ታታሪ የሆነው ጓድ የነባሮችን ያህል በከባድ ፈተናዎች ውስጥ ያለፈ ስላልነበረ ያነሳው ጥርጣሬ እንደሆነ በመገንዘብ ለብቻ ወስደን ቀስ አድርገን ለማግባባት ጥረት ማድረግ ጀመርን። ህዝብ እንደማይጠላን በምርጫው አዲሳባ ላይ የተገኘው ውጤት በምንም መልክ የህዝብን ዘላቂ ስሜትና ፍላጎት እንደማያሳይ ልናስረዳው ሞከርን።ግድ የለህም ከአመት ሁለት አመት በኋላ የህዝቡን መንፈስ ታየዋለህ ብለን አጽናናነው። በእርግጥም ሁላችንም ህዝቡን ወደእኛ መልሶ መምጣት የጊዜ ጉዳይ ብቻ እንደሆነ እናምን ነበርና።" ይላል።

ከዚሁ ገድል ምዕራፍ ሶስት ድምፅ መስጠት፣ ቆጠራና ያልተገመተ የምርጫ ውጤት ከሚለው ርእስ ሳንወጣ በገፅ 104 ላይ የሚከተለው መልእክት ተፅፎ እናገኛለን፡ -

*"*** ምርጫ 97 በአዲስ አበባና በአንዳንድ ትላልቅ ከተሞች የኢህአዴግን መሸነፍ ቢያስከትልም በጠቅላላ የድምፅ ብልጫ ኢህአዴግ አሸንፎ የፌደራልና የክልል ምክር ቤቶችን አብላጫ ወንበሮች ሊቆጣጠር የቻለው በወሳኝነት በገጠር አርሶ አደሩ በሰጠው ድምፅ ነበር። የኢትዮጵያ አርሶ አደር የታደገው ግን ኢህአዴግን ብቻ አይደለም። አርሶ አደሩ እንደገና አገሩንም ታደጋት... ተቃዋሚዎች አብዛኛውን የፓርላማ መቀመጫ ቢወስዱት ኖሮ የኢትዮጵያ እጣ ፈንታ ይህን ግዜ ምን ሊሆን እንደሚችል ለመገመት አይከብድም።"*

***

በትንቢተ ሰምኦን የሁለት ምርጫዎች ወግ አሊ ሲራጅ ሳይጠቀስ ጓድ በሚል የወል ስም እንዲተካ ተደርጓል። አሊ ሲራጅ የኦህዴድ ማእከላዊ ኮሚቴና የኢሲሳባ ኢህአዴግ ከንፍ ስራ አስፈፃሚ ነበር። በአሁን ሰአት ደግሞ የኢህአዴግ የዜሮ ድምር መጫወቻ ተቋም የሆነው "መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ምዝገባና ማስተባበሪያ ኤጀንሲ" ዋና ስራ አስኪያጅ ሆኗል። በእርግጥም እንደተገለፀው አሊ የምርጫ 97 ማታ "የኢሲሳባ ህዝብ ለምን ይጠላናል?" የሚል ጥያቄ አንስቶ እንባዉን ረጭቷል። ይህ ልብ ኮርኳሪ ጥያቄ በእሱ ሳይወሰን ወደ መዲናይቱ የኢህአዴግ ካድሬና አባላት ተሸጋግሮ በየመድረኩ ህዝብ ይጠላናል የሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሶ ነበር።

ከዛም አልፎ ህዝቡን ለመበቀል እንቅስቃሴ ያካሄዱ ካድሬዎች ራሳቸውን ባጋለጡ ወቅት ድርጊቱን ለመፈፀም ያነሳሳቸው የህዝቡን ጥላቻ በማየታቸው እንደሆነ ተናግረዋል። በተለይም የህውሀት ነባር ታጋይና የኮልፌ ካድሬዎች አለቃ የነበረው ነጋ በርሔ ግለሂስ ያደረገው በዘግናኝነቱ ይታወሳል። ይህ ካድሬ የስምኦን ልጅ በመራው ግምገማ "እንባዬ የሚደርቀው አንድ ቅንጅት ስገድል ነው" በማለት በምርጫው ማግስት ሽጉጥ ይዞ ሲዞር እንደነበር በፀፀት ተውጦ ነግሮናል። ተኩሶ አለመግደሉን እሱና እግዜር ይወቀው።

የትንቢተ ሰምኦን ገድል የየዋሁ አሊ ሲራጅ ለቅሶ መንስኤ እንደ እነ ነጋ በከባድ ፈተናዎችና እሳት ተፈትኖ አለማለፉ እንደሆነ "...በቅንነቱ የሚታወቅና በጣም ታታሪ የሆነው ጓድ የነባሮችን ያህል በከባድ ፈተናዎች ወስጥ ያለፈ ስላልነበር ..." በማለት ይገልፀዋል።

ይሁን እንጂ በምርጫ 97 የህዘን ፅልማሞትና በቀል ገንፍሎ የፈሰሰው በነባሩ የኢህአዴግ ካድሬ በተለይም የህውሀት ተጋዮች ላይ ሆኖ ሳለ ለምን አሊ ተለይቶ ቀረበ?፣ ለምን አህዴድ? ... እንደ እውነቱ ከሆነ በምርጫ 97 ማግስት አራት ኪሎ ኢህአዴግ ቢሮ የሄድን ካድሬዎች የነበረውን አጋጣሚ እስከወዲያኛው አንረሳውም። የነበረው ልቅሶና ሀዘን የእናት ሞት ያህል ከባድ ነበር። የሽማግሌው ስብሀት ነጋ ዘመድ ታጋይ ፀሀይቱ የባህርዛፍ ቅጠል ነስንሳ ልቅሶ እንደተቀመጠች ዛሬም ድረስ እንደ ታሪክ ይነገራል። የስምኦን ልጅ በረከት ባደረበት ብስጭት ምክንያት ራሱን እየሳተ መውደቅ በመጀመሩ ቢሮው ውስጥ ባለች የውስጥ ክፍል መኝታ ተዘጋጅቶለት ነበር። ሁኔታው ከቁጥጥር ውጭ ሲወጣ ደግሞ የጡት አባቱ ሼህ አላሙዲን አንዴ ደቡብ አፍሪካ፣ ሌላ ጊዜ እስራኤል አመላልሰው ህይወቱን ታድገዋል።

በአጠቃላይ ግን በወቅቱ የነበረው ሁኔታ የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ካለቀ በኃላ የነበረውን የመርዶ ዜና ያስታውሰናል።

(የመርዶ ዜናው ሂደት እንደሚከተለው ነበር ።

በ1993 አጋማሽ ላይ በማዘጋጃ ቤት ትንሿ አዳራሽ ለአስቸኳይ ስብሰባ ተጠራን። ስብሰባውን የመሩት የአስተዳደሩ ካቢኔ አባል ካሊድ አብድርሀማንና ጀነራል ታደሰ ወረደ ነበሩ። አጀንዳው ደግሞ በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ወቅት የቀረበውን ሀገራዊ ጥሪ ተቀብለው ከዘመቱት የመዲናይቱ ወጣቶች ውስጥ መስዋዕት የሆኑትን ለቤተሰባቸው የምናረዳበት መመሪያ ለመቀበል ነበር። በስብሰባው መጨረሻ በጥብቅ ሚስጥር የሚያዝ የሚቾች ስም ዝርዝር ተሰጠን። እኔ አስተዳደር የሆንኩበት ዞን ሁለት ብቻ 542 ወጣቶች ተሰውተዋል።

የሞቱትን የማርዳት ሂደት የተከናወነው የሰፈር ሰራፊ ሜዳዎችን በመምረጥ (ጃንሜዳ ጨምሮ) በጅምላ ነበር፣... የከተማዋ ወጣቶች ህልፈተ ህይወት አስደንጋጭ በሆነ መልኩ መዝጉበ እየተገለጠ የተነበበበት... አዲሳባ ማቅ የለበሰችበት ቀን! በቡድን ደረት የተደለቀበት አሳዛኝ ወቅት! የጦርነት መጥፎ ገጽታ።)

በምርጫው ማግስት ደግሞ የሆነው ይህ ነበር።

"በደማችን ያገኘነውን ስልጣን በትምክህተኞች ተነጠቅን"፣ "ኢትዮጵያ አለቀላት"፣ "ኢንተርሀምዌይ በትግራይ ህዝብ ላይ ታወጀ"፣ "ሻዕቢያ በእጅ አዙር አሸነፈ"... የሚሉ አደገኛ ቃላት በእንባ ታጅቦ የተወረወረበት፣ ሴት ተጋዳሊቶች ከያሉበት ተጠራርተው በመምጣት ነጠላ አዘቅዝቀው ሙሾ ያወረዱበት፣ ዲሞብላይዝድ የኢህአዴግ ወታደሮች በየቤታቸው የደበቁትን የጦር መሳሪያ ይዘው የወጡበት አጋጣሚ።

(በነገራችን ላይ በአዲሳባ ከአስር ሺህ በላይ ዲሞብላይዝድ የሆኑ የህውሀት ታጋዮችና ከኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት በኃላ የተቀነሱ ወታደሮች ይኖራሉ። እነዚህ አካላት በተለያዩ መንግስታዊ ተቋማት ውስጥ በሲቪል ሰራተኝነት እንዲሰገሰጉ ተደርጓል። በተለይም በወረዳና ቀበሌ ፉይናንስ ጽ/ቤት፣ የሚሊሽያ ጽ/ቤት፣ የፌደራልና አዲሳአባ ፓሊስ፣ አየር መንገድ፣ ጉምሩክ፣ ውጭ ጉዳይና ደህንነት መስሪያ ቤቶች የሚጠቀሱ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪም የኤርትራውያን ንብረት የሆኑ መኖሪያ ቤቶች፣የንግድ ተቋማት፣ የመኪና መለዋወጫ ሱቆችና ጋራጦችን እንዲወርሱ ተደርጓል። ከቄራ እስከ ገፆ

ገብርኤል የተዘረጉትን ጋራጉኖችና መለዋወጫ ሱቆች "ከኤርትራውያን ወደ ትግራውያን የተደረገ ሽግሽግ" የሚል ሰያሜ እንደተሰጣቸው የአደባባይ ሚስጥር ነው። ዛሬ ፀረ ሙስና የደህንነት ባለስልጣን የነበረውን ወልደስላሴ ሲከስ "ምንጩ ያልታወቀ ንብረት" ብሎ የሚለው የኤርትራውያን ንብረት ላለማለት ተፈልጐ ነው።

በእነዚህ ዲሞቢላይዝድ ታጋዮች ቤት በነፍስ ወከፍ አንድ የጦር መሳሪያ ይገኛል። ታጋዮቹን ዲሞቢላይዝ የሚድረግ ሂደት መሳሪያ መንጠቅን አያጠቃልልም ነበር። በዚህም ምክንያት እነዚህ ታጋዮችና ተቀናሽ ወታደሮች የሲቪል ህይወት ሲጀምሩ ከነትጥቃቸው ነበር። በእነሱ እጅ ያለው የጦር መሳሪያ ቁጥር የአዲሳባ ፓሊስ ካለው በብዙ እጥፍ ይበልጣል። የጉምሩክ ባለስልጣን የነበረው ገ/ዋህድ ቤት እንደተበረበረው ሁሉ የሌላውም ቢፈተሽ ቢከፉ እንጂ የሚያንስ አይሆንም። ከዚህ አንጻር ገ/ዋህድ ተለይቶ ተጠያቂ የሚሆንበት አንዳችም ምክንያት የለም። ግራም ነፈስ ቀኝ የአዲሳባ የፀጥታ ስጋት አንዱ ምንጭ ይህ ነው።)

***

በትንቢተ ስምአን መልእክት ላይ፣ "የአዲሳባ ህዝብ አይጠላንም፣ ጠልቶንም አያውቅም" ሲል መጀመሪያ አካባቢ ከተዛባ ኢንፎርሜሽን ሊሆን ይችል እንደሆነ ተጠራጠርኩ። የስምአን ልጅን በቅርበት ከሚያውቁት ሰዎች አንዱ ስለሆንኩና ምን አይነት መረጃዎች እንደሚደርሱት ስለማውቅ ጭምር። ትንሽም ሳልቆይ ሌላ ክፍል ላይ፣ "...እኛ ኢህአዴጐች እንደ ህዝብ የምንፈራው የለንም፣ ጌታችንም ህዝባችን ነው፣ ባለፉት አመታት በጐ ነገር በመስራት ሉአላዊ የስልጣን ባለቤት የሆነውን የአገሪቱ ጌታ ለማስደሰት ጥረት አድርገናል። " የሚል ተፅፎ ሳኑብ ደነገጥኩ። እጄን በጭንቅላቴ ላይ አገኘሁት።

ስለየትኛው ኢህአዴግና ህዝብ እያወራ እንደሆነ ግራ ገባኝ። እነዚህ ህዝብ የተባሉት ውስጥ በቅርብ የማውቃቸው የአዲሳባ ነዋሪዎች ፊትለፊቴ ተደቀኑ። የአዲሳባ መከራና ብሶት ኖሬበታለሁ። ኢህአዴግ የመዲናይቱን ነዋሪዎች በመናቅና በማዋረድ የሰራውን ወንጀሎች አይቻለሁ። በከተማዋ ነዋሪዎች ላይ የተፈፀሙ ፀረ - ዲሞክራሲ ተግባሮች ተነግረው አያልቁም።

ከዲሞክራሲያዊ መብቶች ብንነሳ የአዲሳባ ህዝብ ፕሬዝዳንቱን (ከንቲባውን) በተናጠል የመምረጥ መብት የለውም። ከንቲባውና የካቢኔ አባላት ምርጫ ከመካሄዱ በፊት በኢህአዴግና እናት ድርጅቶቹ የሚመደቡ ናቸው። በዚህም ምክንያት ኢህአዴግ አዲሳባን በተቆጣጠረ ሀያ ምናምን አመታት መዲናይቱ የምትተዳደረው በምስለኔ ፕሬዝዳንቶችና ከንቲባዎች ሆኗል። እነዚህ ሹመኛ ካድሬዎች የሚፈሩትና የሚሸቆጠቆጡት ለኢህአዴግና ብሔር ድርጅቶቹ

እንጂ ለአዲሳአባ ነዋሪ አይደለም። አዲሳባ የነዋሪዎቿ ስላይደለች።

ቀጥሎ የሚመጣው የስልጣን ብልግና ነው። በዘመነ ኢህአዴግ ስልጣን የሀብት ምንጭ ሆኖ አገልግሏል፣ ከህዝብ በተዘረፈ ንብረት ብዙዎች የሀብት ማማ ላይ ተሰቅለዋል። ከቀድሞዎቹ አምባገነን መንግስታት በባሰ በአዲሳባ የመሬት ዝርፊያና ወረራ ተካሂዷል። ከመሬት ወረራው ጋር በተያያዘ ብቻ ከሀያ ቢሊዮን ብር በላይ የሚጠጋ የመዲናይቱ ህዝብ ገንዘብ ተዘርፉል። ለጆሮ የሚሰቀጥጥ ቢሆንም የህዝብ መሬት የተቸበቸበው የከተማዋን ማስተር ፕላን ሰርቆ በማውጣት ጭምር የተፈፀመ ነበር። የአሁኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ሀይለማርያም ደሳለኝ ለዚህ እማኝ ይሆናል። የፐላኑን ኮፒ ዱባይ ድረስ በመሔድ በአምስት ሚሊዮን ብር ገዝቶ ያመጣው እሱ ስለሆነ።

በየጊዜው የተቋቋመው አስተዳደር ንቅዘት በሁሉም ዘርፎች የሚታይ ነበር። በገቢ ማሰባሰብ፣ ህግን ያልተከተለ የግዥ አገልግሎት፣ የፍትህ እጦት፣ በብልሹ አሰራሮች ምክንያት ነዋሪው መንገላታት ደርሶበታል። ካድሬዎች ከቢሮአቸው ሳይወጡ ፍርደ ገምድልና አድሎአዊ በሆነ ሁኔታ ግብር ጥለዋል። በጉቦ ተጨማልቀዋል። በቢሊዮኖች ገንዘብ በማውጣት ተጠያቂነትና ግልጸኝነት በጎደለው ሁኔታ ያለ ጨረታ ግዥ የሚፈፀምበት ሁኔታ በተደጋጋሚ ታይቷል። የህገ መንግስቱ መሰረታዊ መርሆ ተጥሷል። መልእክተ ዜናዊ የዚህ አካል ነበር።

የአዲሳአባ ነዋሪ ከየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል በከፉ ሁኔታ በኑሮ ውድነት በመጠበስ ላይ ይገኛል። የኑሮ ወድነቱ የከተማ ችጋር ፈጥሯል። የከተማው ነዋሪ ድህነትና ጉስቁልና እርቃኑን መታየት ከጀመረ አመታት ተቆጥሯል።ግራ የተጋቡና መሄጃ የሌላቸው ነባሩ የአዲሳአባ ነዋሪ መዲናይቱ ሲኦል ሆናበታለች። ህዝቡ ከፊዴራል መንግስት የሰንዴ መና ጠባቂ ሆኗል። በተለይም የከተማው ነባር ነዋሪ እንኳን ስለፓለቲካ መብቱ ሊያስብ በህይወት መኖሩም ጥያቄ ውስጥ ገብቷል።

***

በትንቢተ ስምኦን መፅሀፉ ውስጥ የአዲሳባና የሀገሪቷ ትላልቅ ከተማ ነዋሪዎች በምርጫ 97 ተቃዋሚን መምረጣቸው ሀገሪቷን አደጋ ላይ ጥለው እንደነበር በወቀሳ መልክ ቀርቧል። እነዚህ የከተማ ነዋሪዎች ኢህአዴግን ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን እጣ ፉንታ አጨልመውት ነበር ብሏል። ገበሬው ባይኖር ኖሮ በከተማው ህዝብ ውሳኔ ምክንያት ኢህአዴግ ብሎም ኢትዮጵያ እንደ ሀገር የመቀጠል አጣብቂኝ ውስጥ ይገቡ እንደነበር ነግሮናል። አርሶ አደሩ ኢህአዴግን

መርጦ ሀገሩን በድጋሚ ስለታደገ ምስጋና እንደሚገባው አስገንዝቧል።

በዚህ አገላለፅ ውስጥ በርካታ ቁምነገሮችን ማንሳት ይቻላል። ከእነዚህ ውስጥ ኢህአዴግ በምርጫ 97 አሳካዋለው ብሎ ያስቀመጠው አላማና ግብ፣ የኢህአዴግና ኢትዮጵያ መግኢ እድል ተጃምለው የቀረቡበት ምክንያት፣ የኢትዮጵያ ገበሬና ከተሜ ለሀገራቸው ያነገቡት ራእይና ተግባር ተዛምዶ፣ ...

ምርጫው ፍፅም ዲሞክራሲያዊና እንከን የለሽ እንደሚሆን፣ ማንኛውም ዜጋ የመሰለውን መምረጥ እንደሚችል ፣ ውጤቱ ምንም ሆነ ምን በፀጋ መቀበልና በጋራ ለመስራት ዝግጁ መሆን እንደሚያስፈልግ፣ የምርጫውን ዲሞክራሲያዊነት የሚያደናቅፍ ስራ ሰርቶ የተገኘ ካድሬ ሀላፊነቱን ራሱ እንደሚወስድ ደጋግሞ ያስጠነቀቀው መልእክተ ዜናዊ ነበር። በመላ ሀገሪቱ ለሚገኙ አባላትና ካድሬዎች የስነ -ምግባር መመሪያውን በፕላዝማ ያሰለጠነው ደግሞ የስምአን ልጅ በረከት ነበር።ውሳኔውን ለማስተግበር ጥበቅ ክትትል የሚያደርግ ኮሚቴ በየደረጃው ተቋቁሞ ነበር። ባልተለመደ ሁኔታ በአንዳንድ የሀገሪቱ ከተሞች የተቃዋሚን ስብሰባ አደናቅፉችኃል በሚል ካድሬዎች ተቀጥተዋል። ከድርጅት ተባረዋል። የመንግስት ስራቸውን እንዲለቁ ተደርገዋል። ካድሬዎቹ የፈፀሙት አስነዋሪ ተግባር ለሌላው መቀጣጫ እንዲሆንና ኢህአዴግ በድርጅት ደረጃ ቁርጠኛ መሆኑን ለማሳየት በሚዲያ ተቋማት እንዲገለጽ ተደርጓል።

ይህንን ተከትሎ በከተማ የሚኖረው ህዝብ የፈለገውን መረጠ። በገጠር የሚኖረውም እንዲሁ። የምርጫው ውጤት የሀገሪቷን የዲሞክራሲ ጉዞ አፉጠነው እንጂ ህልውናዋን አልተፈታተነም። ከተሜው ኢትዮጵያን የማጥፉት፣ ገጠሬው ደግሞ የመታደግ ሚና ይዘው አልተንቀሳቀሱም። ይህ ለሰሚ ግራ የሚያጋባ መልእክት ነው። ባይሆን አሁን ባለንበት የስልጣኔና መረጃ ዘመን በከተማ የሚወሰዱ እርምጃዎች የገጠሩ ህዝብ በተመሳሳይ ይከተላቸዋል። የኢትዮጵያም አርሶ አደር ከዚህ ውጭ አይደለም። የመረጃ ፍሰቱ ከከተማ ወደ ገጠር፣ ከገጠር ወደ ከተማ ሁለትዮሽ የሚሆንበት አድል ለአመታት ተጠናክሮ ይቀጥላል። በመሆኑም አሁን ባለችው ኢትዮጵያ የከተሜው አፍንጫ ሲመታ የገጠሬው አይን ያለቅሳል። ገበሬው ሲራቆት ከተሜው ይራባል። አንድም ሁለትም ናቸው።

በመሆኑም የከተሜው ህዝብ ለብቻው የኢህአዴግና ኢትዮጵያ ጠላት ተደርጐ የሚወሰድበት እድል የለም። በተለይም እንደ አዲሳባ ያሉ ከተሞች አሳማኝ የሆነ ፓለቲካዊ ምክንያቶች እንዳላቸው እየታወቀ ሀላፊነት በጐደለው ሁኔታ የተገለፀውን በትክክለኛ ምስሉ ማሳየት አስፈላጊ ይሆናል።

***

የዚህ መፅሀፍ አላማ በዝች ባለቤት አልባ በሆነች ከተማ ተዛብቶ የቀረበውን ታሪክ በትክክለኛ ገፅታው ማሳየት ነው። ይህ መጽሐፉ የአዲሳባ ህዝብ ኢህአዴግን የጠላው በተጨባጭ ምክንያቶች ላይ ተመስርቶ መሆኑን በመረጃዎች ላይ በመመስረት ለማሳየት ይሞክራል። የአዲሳባና አህአድግ መፋታት ከጥላቻ በዘለለ የአይዲኦሎጂና መርህ ልዮነት መሆኑን ለመግለፅ ጥረት ያደርጋል። የዚህ ማስታወሻ ፀሀፊ ኢህአዴግ በመዲናይቱ ከሞግዚትነት ያለፈ ሚና እንደማይኖረው ለማመላከት ይሞክራል።

የስምአንን ልጅ ጨምሮ በፉካሬ ኢህአዴግ መፅሀፍ ላይ ድርሻ ያላቸው ሰዎች ከስሜት በፀዳ መልኩ እንደሚያነቡት ተስፉ አደርጋለሁ። እያዘጋጁ ባሉት ቁጥር ሁለት መልእክተ ዜናዊ ላይ ማረሚያዎችን በማድረግ እንደሚጀምሩ ምኞቴ ነው። ከእንግዲህም እውነትን ዋጋ ከማሳጣት እንደሚቆጠቡ ተስፉ አደርጋለሁ።

በዚህ ሀቅ ላይ ተመስርተው ይቅርታ የሚጠይቅ ልቦና መፍጠር ከቻሉ ደግሞ የኢትዮጵያ ትንሳኤ ይበሰራል። ይቅርታ ለእርቀ ሰላም የመጀመሪያ እርምጃ ነው... ከህሊና ቁስል ይፈውሳል፣ ራስን ያነፃል። ይቅርታ የትላንትን መጥፎ ግንኙነት ለታሪክ ትቶ ዛሬና ነገን "በለውጥ ተህድሶ ፈረስ "በጋራ ለመጓዝ በር ይከፍታል። ሁልጊዜም መኖር ያለበት ፓለቲካ ልዩነቱ እንዳለ ሆኖ!... የዚህ መፅሀፉ ግብም ይህና ይህ ብቻ ነው።

ክፍል አንድ: የመዲናይቱ ህዳሴ እሳቤዎች!

ምእራፍ አንድ

የህዝቦቿን ሉአላዊነት የተገፈፈች መዲና!

ከገራው ዘልቄ እስኪ ልነጋገር
ካለሰው ቢወዱት ምን ያደርጋል አገር?
የኔ ውብ ከተማ
ህንፃ መች ሆነና የድንጋይ ክምር
የኔ ውብ ከተማ
መንገድ መች ሆነና የድንጋይ አጥር
የኔ ውብ ከተማ የኔ ውብ አገር
የሰው ልጅ ልብ ነው
የሌለው ዳርቻ የሌለው ድንበር።
ህንፃው ምን ቢረዝም ምን ቢፀዳ ቤቱ
መንገዱ ቢሰፋ ቢንጣለል አስፉልቱ
ሰው በሰው ካልሸተተ ምንድነው ውበቱ?
የሰውን ልብ ነው።
ምን ቢነድ ከተማው ተንቦግቡገ ቢጦፍ
ቢሞላ መንገዱ በሺ ብርሀን ኩሬ
በሺ ብርሀን ገርፍ
ምን ያደርጋል ?
ምን ያሳያል?
ካለሰው ልብ ብርሀን
ያ ዘላለማዊ ነበልባል ያ ተስፋ ሻማ
ጨለማ ነው
ሁሉም ጨለማ።
(አሮማይ፣ በአሉ ግርማ)

ጥቅምት 1995 ዓ.ም÷ ÷÷÷

በሌ መንገድ የሚገኘው የኦሮሚያ ምክር ቤት (ጨፌ) ለአስቸኳይ ስብሰባ በመጡ የመዲናይቱ እና አንግዳ ካድሬዎች ተጨናንቋል። ሁሉም ጥጋጥጉን ይዞ ያወራል። አጀንዳው ስላልተነገረ ብዙዎች መላምት ይሰጣሉ። ውስጥ ያውቃሉ የተባሉት ደግሞ በየቦታው ተከበዋል።

የአዲሳባ ቻርተር ለመተግበር እንቅስቃሴዎች በመጀመራቸው ምክንያት በከተማው ብዙ ወሬዎች ተናፍሰዋል። የተወሰኑ ሚስጥሮች ሾልከው ወጥተዋል፦ የከተማው ኢህአዴግ መዋቅር እንደሚፈርስ፣የካቢኔ አባላት ፕሬዝዳንት አሊ አብዶን ጨምሮ እንደሚባረሩ፣ የሚታሰሩ ባለስልጣናት እንደተለዩ። የካድሬው ሹክሽክታና መነጋገሪያ ከዚህ አልዘለለም። ወሬ የተራበ ካድሬ! ... ሁሉ ነገር ሚስጥር በሆነበት ፓርቲ ውስጥ መኖር የመረጃ ረሀብተኛ ያደርጋል። በዛ ላይ ፀጉረ ልውጦች መታየታቸው ውጥረቱን አባብሶታል።

የአቶ አሊ ከሰልጣን መባረር ሁሉም በጉጉት የሚጠብቀው ነበር። በብዙዎች ዘንድ የአሊ አብዶ የስልጣን ወቅት "የጨለማ ዘመን" በመባል ይታወቃል። ሌጋሲዉ በህዝቡ ጫንቃ ላይ ተጣብቆ እንደከረመ መሸገር ሊታሰብ የሚችል ነው። የዘረጋው ኔትወርክ ጥፋትን በጥፋት እያረመ በማያቋርጥ የወንጀል ኡደት ዉስጥ እንዲጓዝ ያደረገ ...የጨለማ ዘመን ንጉስ!

ወደ ስብሰባው አዳራሽ እንድንገባ ተነገረ።የአዲሳአባ ፕሬዝዳንት አሊ አብዶና አባይ ፀሀዬ ወደ መድረክ ወጡ። አሊ የሰብሰባው አላማ በልማትና ፓለቲካ ስራ ያለፉትን ሁለት አመታት ለመገምገም የተጠራ መሆኑን ገለፀ። በከተማዉ የተናፈሰው ወሬ ከእውነት የራቀ እንደሆነ ፣ የጥፋት ኃይሎች እንዳሰራጩት አስረዳ (*በአሊ አብዶ መዝገብ ላይ የጥፋት ኃይሎች ተብለው ከተጠቀሱት ውስጥ ግንባር ቀደሙ ንግድ ም/ቤት ሲሆን ተከታዩ የኦርቶዶክስ ሀይማኖት ተቋም ነው።*) ...በድርጅቱ አሰራር መመሪያ መሰረት ምደባና ሽግሽግ የሚካሔደው ከግምገማ በኃላ እንደሆነ አብራራ። መድረኩን የሚመሩት እሱ ፣ ምክትል ፕሬዝዳንቱ ደሳለኝ ሸሹና አባይ ፀሀዬ እንደሚሆኑ ተናገረ።

ደሳለኝ ሸሹ ከቀናት በፊት ሶስት ጉልቻ መስርቷል። የደሳለኝን ደመቅ ያለ የጋብቻ ድግስ በልተናል። ድምቀቱን በመገምገም ስጋው ተቦጭቋል። እሱም ዋዛ አይደለም የቀረበበትን ሀሜት ወደ ጐን ትቶ ደስታውን በማራዘም ለጫጉላ ሽርሽር ባህር ማዶ ተሻግሯል። የሆዱን ሳናውቅ " ከሳምንት በህዋላ ሂሱን በሀኒ ሙን ሙድ ያወራርዳል " ብለን ተሳለቅን ። የአራዳውን ልጅ! ...ያውም የልደታ! ... ደሳለኝ ሸሹ ሸሸ! ...ሂሳቡን በሌላ ጣቢያ አወራረደ። አባባሉስ ቢሆን " የትም ተወለድ ልደታ እደግ!" አይደል።

***

"መዲናችንን አናድሳት" የሚለው ሰነድ በጨፌው ለተሰበሰብን ካድሬዎች ተበተነ። በተናጠል እንድናነብ ሙሉ ቀን ተሰጠ። ሰነዱ በከተማዋና ካድሬዎቿ ላይ ውርጅብኝ ነበር። ሰድቦ ለሰዳቢ የሚዳርግ።

መዲናይቷን በተመለከተ እንደሚከተለው ሰፍሯል፣

"በማያቋርጥ የማሽቆልቆል ጉዞ የምትገሰግስ የበሰበሰች ከተማ"፣ "በድህነት የተተበተበችና እርቃኗን የቀረች መዲና"፣ "ከበግ ጉረኖ ያልተሻሉ ቤቶች የተከማቹባት..."፣ "የአፍሪካ ማፈሪያ"... በአጠቃላይ ወደ አሳዛኝ የቁራ አሚሚት እያመራች ያለች ከተማ። አዲስ አበባ!!...

በተመሳሳይ የመዲናይቱ ካድሬዎች ላይ ግርፊያ ቀረሽ ስድብ ተጽፎአል። አንዳንዶቹ የወረዱ የመንደር ቧልቶች ናቸው፣ መረን የለቀቁ መደዴዎች...

"የሰው ሰጋ መብላት የቀረው- ማሽንክ!"፣

"ከኪሎው በላይ ወሮ የሚበላ - አንበጣ!"፣

"ተነሳ ሲሉት የሚነሳ፣ ተኛ ሲባል የሚተኛ - አድርባይ!"፣

"ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል በሚል መርህ የሚመራ—— ቀማኛ!"፣

ማሽንክ... አንበጣ... አድርባይ...ቀማኛ...

የአቶ መለስ ስድቦች።

በነበረን የምሳ ሰዓት ካድሬዎች ምን እንደተሰማቸው እርስ በራስ ይጠያየቃሉ። በአብዛኛው ተመሳሳይነት ያላቸውን አስተያየቶች ይሰጣሉ። አንደኛው ካድሬ፣ "በሠነዱ ላይ የተቀመጠው ሀቅ ቢሆንም እንደዚህ እስኪሆን ለምን ተጠበቀ?" በማለት ሲናገር ሰማሁት። ሌላኛው፣ "ይህም ቢሆን የተጠያቂነቱን አንበሳ ድርሻ ሰነዱን ያዘጋጀው ክፍል መውሰድ አለበት? እንደ አሳ ከጭንቅላታችን ገምተናል ያሉት እነሱ ናቸው። እነሱ በገመቡት እኛ ብንሸት ምን ይገርማል!" በማለት መልስ ይሰጣል። በተለይም አንዱ ካድሬ በተበሳጨ አንደበት፣

"ይህ ሰነድ የሴኔጋሉ ኘሬዝዳንትና መሀመድ ጋዳፊ አዲሳባን በተመለከተ በተለያየ መንገድ ካሰራጩት መረጃ በምን ይለያል?" በማለት ሲናገር ሰምቼ ቀልቤን ሳበው።

ካድሬው የጠቀሳቸው ፕሬዝዳንቶች የአፍሪካ መዲና መቀየር እንዳለበት ከጀርባ የጠነሰሱት በከተማዋ የታዩት ችግሮችን በመጥቀስ ነበር። በዓመቱ መጀመሪያ ወራት የውጭ ጉዳይ ምክትል ሚኒስትሩ ዶክተር ተቀዳ አለሙ የውጭ ጉዳይ ፓሊሲውን ሲያወያየን አስደማሚ በሆነ መልኩ የእነ ጋዳፊን ሸፍጥ አስረድቶናል። ዶክተር ተቀዳ በተቆጨ ስሜት፣

"አዲሳአባ ባለባት የፀጥታ፣ የመልካም አስተዳደር እጦት፣ ኋላቀርነትና አስከፊ ድህነት ምክንያት የአፍሪካ መዲናነቷን ለማጣት ተቃርባለች። ብሔራዊ ውርደታችን እዚህ ደረጃ ደርሷል" በማለት ነግሮናል። እነ ጋዳፊ የኢትዮጵያን

ታሪካዊነት አልካዱም። ቀኝ ገዥዎችን ማንበርከካቸንን በተለያዩ ወቅቶች ገልጸዋል። በተባበሩት መንግስታት ብቻችንን እንደነበርን አልዘነጉትም። ኒልሰን ማንዴላን ማሰልጠናችንን እንዲሁ።

በተለይ ጋዳፊ ከፍተኛ የአክሲዮን ባለቤት በሆነባቸው አለም አቀፍ ሚድያዎች ሳይቀር ዘመቻውን በመረጃ በማስደገፍ አጯጯፎት ነበር። በመዲናይቱ የበሰበሱ አካባቢዎችን፣ በከተማዋ የሚገኙ ሆቴሎች የብዛትና ጥራት ችግር፣ የጐዳና ተዳዳሪዎች፣ የህዝቡን የጉስቁልና ደረጃ፣ የፀጥታ ስጋት...ወዘተ የሚያሳዩ ዶክመንተሪዎች እንዲዘጋጅ ድጋፍ በማድረግ በአለም ዙሪያ እንዲታዩ አድርጓል። ጋዳፊ የአዲሳባ ጠላትም፣ ባለውለታም ነበር... ቪቫ ጋዳፊ!!

ለዚህም ነው አቶ መለስ ያቀረበው መከራከሪያ ውሀ አይቋጥርም የተባለውና ዶክተር ተቀዳ የአቶ መለስን መከራከሪያ ያጣጣለው በዚህ ምክንያት ነበር። የቀድሞ ታሪክና ወቅቱ የሚጠይቀውን ይዞ መገኘት እርስ በራስ ይመጋገባሉ። እነ ጋዳፊ አሁን ላይ ተመስርተው በከተማዋ የተበተነውን ህገ ወጥ የጦር መሳሪያና ስርአት አልበኝነት በማጣቀስ፣ "አዲሳባ የፀጥታ ስጋት አለባት" ይላሉ። አቶ መለስ ወደ ድሮ ሄዶ (ድሮን ይወድ ይመስል!)፣

"በተባበሩት መንግስታትና ፀጥታው ምክርቤት ብቻችንን ነበርን" ይላል።

እነሱ ዛሬ ላይ ሆነው፣

"አዲሳባ አለም አቀፍ ሰብሰባ ለማስተናገድ አቅም የላትም" ይላሉ።

አቶ መለስ ደግሞ ሰገሌን ጐትቶ፣

"መ.ጋቤንና ማንዴላን ያሰለጠነው ማነው ንጉሱና መንግስቱ አይደሉምን?" የሚል ምላሽ ይሰጣል። ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ እንዲሉ። ደግነቱ መሪዎቹ የአፍሪካ ናቸው!!

***

መዲናችንን እናድሳት የሚለውን ሰነድ አንብቦ የጨረሰ እንዲሄድ ስለተፈቀደ አጠገቤ ከነበረው ፍስሀ ዘሪሁን (መአሲ) ጋር ተያይዘን ወጣን። ፍስሀ የቅርብ ጓደኛዬ ነበር፣...በየጊዜው እየተገናኘን በሀገርና ግል ጉዳዮች በግልፅ እንጫወታለን። የወዳጅነት መንፈሶችን እድሜ ፣ዘርና የስልጣን እርከን አለያየውም ።በደምና አጥንት የሚያምን አይደለም። ማንኛውም ሰው ቀርቦ ሊያናግረው የሚችል ቀላል ሰው ነው። ነገሮችን ከስር መሰረቱ ገላልጦ ማየት ባህሪ አለው። ሰውን በሰውነቱ የሚመዝንና የሰዎችን ጥቃት ማየት የማይፈልግ ነበር። ከህውሀት ካድሬዎች በተለየ መልኩ አዲስ ነገሮችን ለመስማትና ለመቀበል ዝግጁ ነው...

"ተከርቸም" የሚባለው ግምገማ ገብቶ ሰለነበር ለሁለት ሳምንት አልተያየንም። ተከርቸም በኢህአዴግ ውስጥ ጫፍ የረገጠ ዝግ ስብሰባ ነው። እንደ አቶ በረከትና አባይ ፀሀዬ የመሰሉ ፕሮፌሽናል ገምጋሚዎች ይመሩታል። አጀንዳዎቹ በጥብቅ ሚስጥር ይያዛሉ፣ ተሰብሳቢዎች ከማንም ጋር ግንኙነት እንዲያደርጉ አይፈቀድም። እንደዚህ አይነት አሰራሮች በህዉሀት የተለመዱ ናቸው። በተለይ በአደጋ ጊዜ (የኢትዮ - ኤርትራ ጦርነት ውሳኔዎችን የህውሀት ስራ አስፈጻሚ ብቻ በተከርቸም እንደወሰነ ልብ ይሏል።)

ፍስሀ መአሲ አዲሳባን በንብረትነት ከተሰጣቸው ሶስት የህውሀት ነባር ታጋዮች አንዱ ነበር። ካዛንችስ በሚገኘው አዲሳባ ኢህአዴግ ጽ/ቤት በመቀመጥ። ወደ አዲሳአባ ከመዘዋወሩ በፊት በአራት ኪሎ ኢህአዴግ ቢሮ የካድሬ አሰልጣኝ ነበር። የሰልጠና ስራው በየክልሉ እየሄደ አብዮታዊ ዲሞክራሲን ማጥመቅ ነበር። የኦሮሚያ ፕሬዝዳንቱን አለማየሁ አቶምሳና የፕሮፐጋንዳ ካድሬው አበራ ሀይሉ ኮትኩቶ ያሳደጋቸው እሱ ነው ። ቅርርባቸው የወንድም ያህል ሆኗል።

የህውሀት ለሁለት መሰንጠቅ በፍስሀ ፓለቲካ ህይወት ላይ መጥፎ አሻራ አሳርፎበት ነበር። የእነተወልደ ቡድን አባል በመሆንና ስምሪት ከአባይ ፀሀዬ በመውሰድ የአዲስአባን ህውሀት አባላት በፀረ -መለስ ሲያደራጅ ከነበሩት ቀንደኛው እሱ ነበር። አፍታም ሳይቆይ ተልእኮ ሲሰጠው ከነበረው አባይ ፀሀዬ ጋር መለስን ይቅርታ ጠይቆና ንስሀ ገብቶ ተመለሰ። ፍስሀ ከመለስ በላይ አባይ ላይ ልዩ እምነት አለው። የማይጠርቁት ሚስጥር የለም። ሲርበው እንኳን ወደ አባይና የቀድሞ ሚስቱ ሞንጆሪኖ ይሄዳል... እሱ የጡት አባቱ ፣ እሷ ደግሞ እናቱ ናት።

ፍስሀ በታጋዩ ዘንድ "መአሲ" በሚል በረሀ ስሙ ይታወቃል። መአሲ ማለት በትግርኛ የለፋ ቆዳ እንደሆነና ከሲታ መሆኑን ለመግለፅ እንደተጠቀመበት አጫውቶኛል። ርግጥም አንጀቱ የታጠፈ ነው... ደቃቃ! ከራሱ አልፎ የሰው አምሮት ይዘጋል፣ ሳይበላ ይጠግባል። በውህው አካባቢ ግን አይታማም። በተለይ ቅርብ ከሚላቸው ሰዎች ጋር መጠጣትና መጫወት ይወዳል። ለዚህም ነበር ከጨፈሬ ተያይዘን የወጣነው። በዛ ላይ ተከርቸም በመሰንበቱ ቋንጣ ያልሆኑ ወሬዎች እጁ ላይ አሉ በስልክ እየተካሄደ በነበረው ግምገማ ደስተኛ እንዳልሆነ ጠቆም አድርገኖኛል። ላለማስጨነቅ ብዙ

አላነሳሁበትም። አሁን ግን ስብሰባው ስላለቀ ሊያወጋኝ እንደፈለገ ገብቶኛል።

ተያይዘን ወደ ለመድነው ሜክሲኮ ራስ ሆቴል ሔድን።

ፍስሀ ቁመናው ተዳክሟል። የመኪናውን መሪ እንኳን ማዟዟር አቅቶታል። አስር ጊዜ የቀኝ እጆቹ መሪውን ይደበድባሉ። ፊቱ ላይ የጭንቀት መስመሮች ተሰምረዋል። የተናደደበት ነገር እንዳለ ያስታውቃል። የከረመበት ግምገማ ሳይገሪብጠው አልቀረም።

ሆቴል እንደደረስን መጠጥ ብቻ አዘዘ። አጠጣጡ ከወትሮው የተለየ ሆነብኝ። ያለትንፋሽ ይጋተዋል። ለረጅም ጊዜ አቋርጦት የነበረውን ሲጋራ በየደቂቃው ይጠጣል።

ወሬ ለመጀመር፣

"ፊሽ !ግምገማው የተስማማህ ይመስላል የበለጠ ሸንቀጥ አድርገሀል።"

በሲጋራው ጭስ ቀለበት እየሰራ፣

"ልትጠፉ ነው ማለት ከብዶህ ነው?"

"ከሚጠፉት ወገን እንዳልሆንክ እያወቅኩ" ቀለድኩበት።

"ሊያጠፉኝ መጥቶ እያየሁ?"

"ማነው?"

"አዲሱ ከንቲባህ...አርከበ እቑባይ!"

"እየተወራ ያለው እውነት ነው እንዴ?" በመገረም ጠየኩት።

"ምን በሌለበት አይሸትም ሲባል አልሰማህም።"

አቋረጥኩት፣

"የሚሆን ነገር ስላልመሰለኝ ነው። እንደምታውቀው የከተማው ቻርተር ከንቲባ የሚመረጠው ከምክር ቤት አባላት ውስጥ እንደሚሆን ይደነግጋል። ምክር ቤቱ ከተቋቋመ ደግሞ ገና ሁለት ዓመት አልሞላውም።"

የሲጋራ ጭሱን እየዋጠ፣

"አንዱ ያበሳጨኝ ይህ ነው። ለመጽደቅ በተዘጋጀው አዲሱ ቻርተር ላይ ፓርላማው ምክር ቤቱን መበተን እንደሚችል ተቀምጧል። የምክር ቤቱ የአይን ቀለም ካላማረው ሰበብ ፈጥሮ ያፈርሰዋል። ይህ ፍጹም ፀረ ዲሞክራሲ ነው። የህዝቦችን ሉአላዊ መብት ይጥሳል። ከአራት ሚሊዮን በላይ የአዲሳባ ህዝብ ይመራኛል ብሎ የመረጠውን ምክር ቤት ከሌላ በታ ተመርጦ የመጣው ሲበትነው።"

ከደቂቃዎች ዝምታ በኃላ እንዲህ በማለት ጠየኩት፣

"ፊሽ! እንደዚህ ማድረጉ ለምን አስፈለገ? እንዴት ሌሎች የተሻሉ አማራጮችን ማሰብ አልተቻለም?"

"ድርጅቱ በመርህ መመራት አቁሟል። ከውስጥ ሊመጣ የሚችለውን እሳት በመፍራት የህዝብ መብት መደፍጠጥ ስራዬ አድርገሃታል።"

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የኢህአዴግ ከፍተኛ ካድሬዎች ድርጅቱ ብለው ሲጠሩ አቶ መለስ ማለታቸው ሆኗል።... የአቶ መለስ የወል ስም "ድርጅቱ" ነው። አቶ መለስ ራሱ አንድ ነገር ሲፈቅድ "ድርጅቱ ፈቅዷል" ሲከለክል ደግሞ፣ " ድርጅቱ አልፈቀደም" ይላል። (ከአለም አቀፍ ማህበረሰቡና ጋዜጠኞች በደረሰበት ጫና" በግሌ ስልጣን መልቀቅ እፈልጋለሁ፣ ነገር ግን ድርጅቱ አልፈቀደልኝም።" ማለቱን ልብ ይሏል።)

እንደገና እንዲህ በማለት ጠየኩት፣

"ስለዚህ ምክር ቤቱ ሊበተን እንደሆነ እየነገርከኝ ነው?... የኢህአዴግ አባላት ይሁን ፣ከ39 በላይ ህዝብ የመረጣቸው የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት እንዳሉበት ለምን ግምት አይገባም?"

"የምክርቤቱ ጉባዔ ተጠርቶ በክብር ይሰናበቱ የሚል ሀሳብ ቀርቦ ነበር። ድርጅቱ አልተቀበለውም። መልስ የሌላቸው ጥያቄዎች አንስተው ያጋልጡናል የሚል ፍራቻ አለው"

"ምን ጥያቄ ይኖራቸዋል?"

የእጁን ጣቶች እየቆጠረ፣

"የምክር ቤት አባላት ተጠያቂነታቸው ለህገ መንግስቱ፣ ለመረጣቸው ህዝብና ለህሊናቸው ነው" አለኝ።

"ይህ የሚሰራው ለፓርላማው ብቻ እንዳይሆን ?"

"ፓርላማ ሆነ!... ክልል ሆነ!...አዲሳባ ምን ልዩነት አለው? ... ህዝቡ ይሆነኛል ያለውን ከመረጠ ሳያቅማሙ መቀበል ነው።"

ከልብ በመነጨ ስሜት፣

"ፊሽ! ከአሊ አብዶ እንኳንም ህዝቡ ተገላገለ። በህዝብ ላይ በግድ የተጫነው ቀንበር እንደተሰበረ ይሰማኛል። እኔም እትብቴን የቀበርኩባት ቀራንዮ ሄጄ ሻማ አበራለሁ።" አልኩት።

"እኔ እያነሳው ያለሁት ከእሱ ጋር የተያያዘ አይደለም። የህዝቦች ሉአላዊነት ለምን ይጣሳል ነው የእኔ ጥያቄ። አሊ አብዶ መጀመሪያም ህዝቡ እንዳልመረጠው ድርጅቱ ያውቃል። ይህ የማይታበል ጥሬ ሀቅ ነው።"

ከደቂቃዎች ዝምታ በኃላ በድጋሚ እንዲህ በማለት ጠየኩት፣

"ረስቼው! ሊያጠፉኝ ስትል! ምን አዲስ ነገር አለ?"

"ወደ ድሬደዋ በቅርብ እኔም ምድብ ከንቲባ ሆኜ እንደምሔድ አባይ ነገረኝ። ይገርምሀል ስለድሬደዋ ምንም የማውቀው ነገር አልነበረም። ለካስ ከአዲሳአባ የባሰ መከረኛ ከተማ ናት። የፓለቲካ ቁማር ስጋት የፈጠረባት ሌላኛዋ ከተማ።"

"ለምን አንተ ተመረጥክ? በአካባቢው የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች እያሉ?"

"አህዴድና ሶህዴፓ በየኔናት ጥያቄ ተፉጠዋል። እስካሁንም ምላሽ አላገኘም። ድርጅቱ ለጊዜው ገለልተኛ ይምራት ብሎ ወስኗል።"

ቀጠለና እንዲህ ሲል ተናገረ፣

"ይገርምሀል! የድሬደዋ ህዝብ አስተዳዳሪውን መርጦ አያውቅም። ከሁለት አመት በኃላ በሚካሄደው ምርጫ (ምርጫ 97) ድሬደዋ ተዘላለች። ሁኔታዎች በድርጅቱ ቁጥጥር ስር እስኪውል ድረስ በምደባና ዙር ለማስተዳደር ተወስኗል። ለአህዴድ ቀጣይ ተረኝነት ተሰጥቶታል። በማስከተል ደግሞ ሶህዴፓ። በድሬደዋ አህዴድና ሶህዴፓ አማራን እንደ ገመድ ዘርግተው ይጓተታሉ። የሁለቱ ድርጅቶች ፍጥጫ አልተፈታም። ይህን በመመልከት ድርጅቱ ለጊዜው ገለልተኛ ይምራት ያለው። እውነቱን ንገረኝ ካልከ ደስተኛ አይደለሁም።"

"በአንድ ጀንበር ከንቲባ ሆንክ!" ዋንጫዬን ለማጋጨት አነሳሁ።

አዲስ ሲጋራ እየለኮሰ፣

"በህዝብ ላይ በግድ የተጫንኩ ያህል ይሰማኛል። በዛ ላይ በሁለት የፌደራል ከተሞች ሁለት ህዝብ ያልመረጣቸው የህውሀት ታጋዮችን ከንቲባ አድርጎ በተመሳሳይ ወቅት መመደብ አሳፋሪ ነው።" ሲል መልስ ሰጠኝ።

"የድሬ ልጅ ልትሆን ነው? ህዝቡ ቶሎ የሚያላምድ ስለሆነ ብዙ አትቸገርም።"

በሀዘኔታ ውስጥ ሆኖ እንዲህ አለኝ፣

"አንዳንድ መረጃዎች ለማጣራት ሞክሬ ነበር። ድሬ በጣም ታሳዝናለች። ታስፈራለች። የታፈነ ጩኸት አየሯን በክሎታል። ካድሬዎቿ ግራ ተጋብተዋል። ቢሮክራሲው ማመጣጠን በሚባል በሽታ ዘወትር ይናጣል። ወጣቶቿ የተስፋ እጦት ባቡር ተሳፍረዋል። አቧራ ከለበሰ ነጠላ ጫማ መላቀቅ አልቻሉም። "

ከፍስሀ ጋር በራስ ሆቴል በነበረን ቆይታ ብዙ ነገሮችን አንስተን ጣልን። ወጋችን እንደ ፔንዱለም ሆነ። ኢህአዴግን ከአዲሳባ ያባረረው ምርጫ 92፣

የካዛንችሱ ስውር መንግስት፣ ዶንቦስኮ፣ የአሊ አብዶ የጨለማው ዘመን፣ የአርከበ እቁባይ ወደ መዲናይቱ የመምጣት ሚስጥር፣ የአቶ መለስ በአንድ ድንጋይ ሶስት ወፍ ለምታት መዘጋጀት ጊዜያችንን ወሰዱ።

እኩለ ለሊት ሲቃረብ ቀሪ ወጋችንን ለይደር አቆየን። ያልፀደቀውን የከተማ ቻርተር እንዳነበው ሰጠኝ። ፍስሀ መለስ ያዘጋጀውን ረቂቅ ቻርተር "የምርጫ 92 ውጤት የፈጠረው የፍራቻ ሰነድ፣ ምርጫ 97 አሻግሮ የሚያይ ዶክመንት" እያለ በተደጋጋሚ ሲጠራው አምሽቷል። እንደሚጠጣው ቢራ እያነሳ ሲጥለው ነበር።

ጐን ለጐን "ተስፉ ድርጅት" የሚባል መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ፕሬዝዳንት ዶክተር ሀሩይ የሚመራው ኮሚቴ ተቋቁሞ ለመነሻ ያዘጋጀውን ቻርተር አይቻለሁ። በብዙ ጉዳዮች ተመችቶኝ ነበር ። በተለይም የማዘጋጃ ቤት በከፍተኛ ሙያተኛ እንዲመራ ለማድረግ የቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ቢያገኝ ኢህአዴግን የሚያስመሰግነው ነበር። ዶክተሩ ባቀረበው መሰረት ቢፀድቅ ለመዲናይቱ ስራ አስኪያጅ የሚሆን ሰው በአለም አቀፍ ደረጃ ማስታወቂያ ተለቆ በነፃ ውድድር ሙያና የቀድሞ ፕሮፉይል ላይ ያተኮረ ይሆናል። ፓለቲካና ሙያ ለየቅል ይሮጡ ነበር።

ወደ ቤቴ እየሄድኩ ድብልቅልቅ ያለ ስሜት ተሰማኝ። በአንድ በኩል ለይስሙላ አጥኝ ቡድን እየተባለ በርካታ ገንዘብ ይፈሳል፣ በሌላ በኩል ድርጅቱ የራሱን ሰርቶ ለተመረጡ ካድሬዎች ያሳውቃል።

ኢህአዴግ መጀመሪያ አካባቢ የህዝቦች መብት ያለገደብ በሚል ባዘጋጀው የሽግግር መንግስት ቻርተር አዲሳባን የክልልነት ስልጣን እንዲኖራት አድርጐ ነበር። ክልል 14 በማለት። ብዙም ሳይቆይ በህገ - መንግስቱ ላይ ኢህአዴግ በዘረጋው ዘርና ቋንቋ ላይ የተመሰረተ የክልል ስልቻ ውስጥ ማስገባት እንደማይቻል ሲያውቅ አዲሳባ የሁላችንም ናት በሚል ሒሳብ ክልልነቷን ተነጥቃ የፌደራል መንግስት ሆነች። ህገ መንግስቱ መዲናይቱን በሶስት ሰንኮፍ የምትወጋ ከተማ አደረጋት። በፌደራሉ መንግስት፣ በህዝቦቿ የነጻነት ትግልና በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት።

ርግጥም እንኩን የለሹ የኢፊዴሪ ህገ መንግስት አዲሳባን በሶስት ጦር የምትወጋ ባለቤት አልባ ከተማ አድርጓታል። ይህ የህገሪቷ የበላይ ህግ በአንድ በኩል የአዲሳአባ ህዝብ ራሱን በራሱ የማስተዳደር ሙሉ ስልጣን አለው ይላል።

በሌላ በኩል የአስተዳደሩ ተጠሪነት ለፌደራል መንግስት እንደሆነ ይደነግጋል። ይህም ፌደራል መንግስቱ በመዲናይቱ ላይ ያልተገደበ የስልጣን ባለቤት እንዲሆን ያደረገ ሆነ። ግንኙነቱም በእኩልነትና ነፃነት መርሆዎች እንዳይመራ አደረገ። በዚሁ የህገመንግስት አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ሶስት ደግሞ አሮሚያ ልዩ መብት እንዳላት ይደነግጋል። ይህም በአሮሚያ ክልልና የከተማዋ ነዋሪዎች ዘንድ መገፋፋት የፈጠረ ግንኙነት እንዲመሰረት በር ከፈተ። በአጠቃላይ መልኩ የከተማዋን ፓለቲካዊ ኢኮኖሚ የፌደራል መንግስቱና አህዴድ ጠፍረው በመያዝ ውጥንቅጡ የወጣ መስተዳድር እንዲቋቋም አደረጉ።

የህገ - መንግስቱ አንቀጽ 61 የፌዴሬሽን ምክርቤት በፌደራል መንግስቱ አባል ክልሎች በሚወክሏቸው አባላት እንደሚዋቀር ይደነግጋል። የፌዴሬሽን ምክር ቤት ህገ መንግስት ከመተርጎም በተጨማሪ የበጀት ማከፋፈያ ቀመር በመስራት ድጎማ ይሰጣል። አዲሳአባ የክልልነት ስልጣን ስለሌላት በፌዴሬሽን ምክር ቤት ልታገኝ የሚገባትን ቢያንስ አምስት ወንበር አጥታለች። ከዚህ በተጨማሪም አዲሳአባ ክልል ስላልሆነች ህጋዊ የሆነው የቀመር ስሌት ውስጥ የለችም። የምታገኘው ድጎማም የላትም። አንዳንድ ክልሎች የሰራተኛ ደሞዛቸውን ሳይቀር በፌደራሉ ድጎማ እንደሚሸፍኑ እየታወቀ አዲሳአባን መንፈግ ፍትህ የጎደለው መሆኑ አይቀርም።

የኢትዮጵያው ፌደሬሽን ምክርቤት በአለም የሌለ ስልጣን ባለቤት ነው። ይህ ዋነኛው የኢህአዴግ የዜሮ ድምር መጫወቻ ተቋም የህዝቦች ሉአላዊነት መገለጫ ተብሎ የሚነገረውን ህገ መንግስት ይተረጉማል። አባላቶቹ ደግሞ በተለየ ውድድር የሚመጡ ሳይሆን ከክልል ምክርቤት አባላት በህዝብ ብዛት የሚወከሉ ናቸው። በየክልሉ አስፈጻሚ የሆነው አካል ተገልብጦ ህግ ለማውጣትና ህገ መንግስት ለመተርጎም ወደ ፌዴሬሽን ምክርቤት ይመጣል። ይህም ሆኖ ወደ አምስት ሚሊዮን የሚጠጋው የአዲሳባ ህዝብ አንድን ህግ ወይም ውሳኔን ህገ-መንግስታዊ አሊያም ኢ-ህገ መንግስታዊ ነው ብሎ በሚወሰንበት ቦታ ወንበር የለውም።

ከህገ መንግስቱ ተቀዳ የተባለውን ቻርተር ምን እንዳካተተ ለማወቅ ጉጉት አደረብኝ። ፍስሀ በንዴት እንደገለፀው ለሌላ ድብቅ አላማ (ምርጫ 97) የተዘጋጀ ይሁን ወይንስ በተቃራኒው የመዲናይቱን ነዋሪ ያልተሸራረፈ መብት ለማክበር ?የሚል ጥያቄ ተመላለሰብኝ።

እንደሚታወቀው ቻርተር የአንድን ከተማ የወደፊት ራዕይና ግቦቿን

ለማሳካት የምታደርገውን ፓለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴ ለማሳካት የምትመራበት እሳቤዎች ፣መርሆዎችና አደረጃጀቶች የሚደነገግበት የህልውና ሰነድ ነው። የአንድን ከተማና ህዝቦቿን ህልውና የሚወሰን ቻርተር ሲዘጋጅ ደግሞ መፈፀም ያለባቸው መሰረታዊ ጉዳዮች አሉ።

በመጀመሪያ ደረጃ ቻርተሩ ሲረቀቅ የአዲሳባ ጉዳይ ያገባናል የሚሉ የህብረተሰቡ ተወካዮች ፣በተለያዩ ዘርፍ የተሰማሩ ምሁራን፣ የፓለቲካ ድርጅቶች፣ መንግስታዊ የሆኑና ያልሆኑ አደረጃጀቶች፣ የንግዱ ማህበረሰብ አመራሮች መገኘት ይኖርባቸው ነበር። ለአዲሳባ ይህ መርህ አልሰራም!

ቀጥሎ የሚመጣዉ ጉዳይ በያገባኛል ባዮች የተረቀቀው ቻርተር የከተማዋ ባለቤት ለሆነው ነዋሪ እንዲመክርበት መቅረብ ነበረበት። ከውይይቱ በኃላ ህዝቡ ሊካተቱ አሊያም ሊቀነሱ ብሎ ያመነባቸውን ቁምነገሮች በመጨመር ወይም በመቀነስ የባለቤትነት መንፈስ መፍጠር ያስፈልጋል። ይህም ቢሆን አልተደረገም። ሊደረግም አይችልም። ሂደቱ ግልፅና አሳታፊ ቢሆን በርካታ ፀረ ዲሞክራሲያዊ አንቀፆች አጣብቂኝ ውስጥ ይገባሉ። የኢህአዴግ ዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት ይጋለጣል።

ቤቱ ስደርስ ረቂቅ ቻርተሩን ገፅ በገፅ ማንበብ ጀመርኩ። በመጀመሪያዉ ገፅ ቻርተሩን ማዘጋጀት ያስፈለገበት ምክንያቶች ዘርዘር ብለው ቀርበዋል። ከእነዚህ ውስጥ ቀልቤን የሳበው አዲሳባ የኢትዮጵያ ርዕሰ ከተማ፣ የአፍሪካ ጎብረትና የተለያዩ አለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ በመሆኗ፣ የአዲሳባ ነዋሪ ራሱን በራሱ የማስተዳደር ሙሉ ስልጣኑን እንዲጠቀም ለማስቻል፣ የአዲሳባ ከተማን አደረጃጀትና አመራር ከዲሞክራሲያዊ መርሆዎችና ከመልካም አስተዳደር ስርአት መርሆዎች ለማጣጣም የሚሉት አንቀፆች ተካተዋል። ከዚህ በተጨማሪም የፓለቲካና የማዘጋጃ ቤት ሙያዊ ስራዎች ተነጣጥለው እንዲሄዱ ፣ የስራ አስኪያጅነት ምደባ በከተማ አመራር ሙያዊ ብቃት ላይ የተመሰረተ እንደሚሆን ታሳቢ መደረጉ ይገልፃል። ይህም ለከተማዋ መለወጥ ተስፋ እንድጨብጥ አደረገኝ። ጓደኛዬ ፍስሀ መአሲን ወቀስኩት። በንጋታው ልሞግተው ተዘጋጀሁ። በተቃራኒው የአቶ መለስን አርቆ አስተዋይነት በመመልከት አከበርኩት።

ቻርተሩን ዘልቄ ማንበብ ስቀጥል በዝርዝር የተጠቀሱት ቁም ነገሮች በመግቢያው ከተቀመጡት ጋር እርስ በራስ የሚደባደቡ ሆነው አገኘሁ። የከተማውን ነዋሪ መብት በመንጠቅ የአዲሳባ ምክር ቤት በፓርላማ ሊበተን

እንደሚችል ይገልፃል። የሚፈርስበት ምክንያት ደግሞ ህገ-መንግስቱን አደጋ ላይ የሚጥል ተግባር በከተማው ምክርቤት ሲፈፀም ወይም የከተማው አስተዳደር ፀጥታና ድንገተኛ ሁኔታን መቆጣጠር ሲያቅተው አንደሆነ ያትታል። ወቀሳና አክብሮቴ ተገላበጠ።

ይህ ከመዲናይቱ ህዝብ ሉአላዊነት ጋር የሚጋጭ ነው። የከተማዋ ህዝብ ሉአላዊነት ተረጋግጧል የሚባለው ነዋሪዎቿ የመጨረሻዉን የወሳኝነት ስልጣን ባለቤቶች ሲሆኑ ብቻ ነው። የህዝቦች ሉአላዊነት እየተለካ የሚሰጥ ሳይሆን ከራሱና መራጩ ህዝብ የሚመነጭ ነው። በተጨባጭ የታየው ግን የከተማው ህዝብ የሚያስተዳድሩትን ተወካዮች የሚመርጥበት ፣ ሲያሻው ደግሞ የሚሽርበት ስርአት መጣሱን ነው። አዲሳባ ማለት ዜጋ የሆኑ ነዋሪዎቿ ናቸው። እነዚህ ነዋሪዎች ባለሙሉ ስልጣንና የሉአላዊ ስልጣን ባለቤት በመሆናቸው ማንም ይህን መብት ሊነጥቃቸው አይችልም።

ወደ ሌላ ገፅ ስሸጋገር የሚያስደነግጥ ነገር አነበብኩ። የአዲሳባን ፓሊስ የሚመለከት ነበር። ቻርተሩ የአዲሳባ ፓሊስ ኮሚሽን ተጠሪነትን ለፌዴራል ፓሊስ ኮሚሽን ሰጥቷል። የከተማው ፓሊስ ኮሚሽነርና ምክትል ኮሚሽነር የሚሾሙት በከንቲባው ሳይሆን በፌዴራል ጉዳዮች ሚንስትር እንደሚሆን ይገልፃል። ይህም መዲናይቷ የእኔ የምትለው የፓሊስ ሀይል እንዳይኖራት ያደረገ ታሪካዊ ሰነድ ሆነ። አስቂኙ ነገር ለከተማው ህዝብ በቀጥታ ተጠሪ ያልሆነው ይህ ተቋም አጠቃላይ በጀቱ፣ ደሞዙን ጨምሮ የሚመድበውና የሚከፍለው የከተማው ነዋሪ ነው።

(ከምርጫ 97 ውጤት በኃላ በአዲሳባ ኢህአዴግ እንዴት ይቀጥል የሚለውን ለመወሰን ሶስት ቡድኖች ተቋቁመው ጥናት በማካሄድ የተናጠል አስተያየት አምጥተው ነበር። በአርከበ እቁባይ የሚመራው ቡድን ይህንን ጊዜ ጠብቆ እንዲፈነዳ የተዘጋጀ አንቀፅ በማጣቀስ አማራጭ ሀሳብ ይዞ መጣ።፣ ቅንጅት መዲናይቷን በተረከበ በሁለት አመት ውስጥ የተለያዩ አመፆችን በማስነሳት ፀጥታውን መቆጣጠር አልቻሉም ብለን የከተማውን ምክር ቤት በፓርላማ እንበትነው የሚል። የሚገርመው ነገር ቅንጅት ሊወነጀልበት የተዘጋጀው የፀጥታ ችግር ለእሱ ተጠሪ ካልሆነው ከፓሊስ ጋር የተያያዘ መሆኑ ነበር።)

ቻርተሩ በጥቃቅን ጉዳዮች ሳይቀር አስተዳደሩን ስልጣን ነፍጓል ።

የከተማው አስተዳደር የፌዴራል መንግስት ካልፈቀደለት በስተቀር ከሀገር ውስጥ የፋይናንስ ምንጮች መበደርም ሆነ የዋስትና ሰነዶችን በመሸጥ ሊበደር አይችልም። የአለም አቀፍ የገንዘብ ምንጮችን አፈላልጎ ቢያገኝ እንኳን የሚበደርለት ፌዴራል መንግስት ብቻ ነው። በሌላ በኩል የአዲሳባ ህዝብ አስተዳደር እንደሌሎች ክልሎች በህግ የተደነገገና በቀመር የተሰላ ድጎማ ከፌደራል መንግስት ማግኘት አይችልም ። በቻርተሩ ላይ የፌደራል መንግስት በራሱ መልካም ፍቃደኝነት ብቻ እንደአስፈላጊነቱ የፋይናንስ እገዛ ለአስተዳደሩ ሊያደርግ የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል ደንግጓል። በከተማው ከሚኖሩ ግለሰብ ነጋዴዎች እና ከተማዋ ባለቤት የሆነቻቸው ድርጅቶች የተጨማሪ እሴት ታክስ በፌደራል መንግስት ብቻ ይሰበሰባል። በመሆኑም ቻርተሩ ከተማይቷን ከገንዘብም አንፃር እግር-ከወርች በማሰር ያሽመደመደና የፌደራል ፍርፋሪ ጠባቂ እንድትሆን ያደረገ ሆነ።

በምርጫ 97 በህዝብ ፍላጐት የተመረጡት ቅንጅቶች አስተዳደሩን ቢረከቡት (እንኳንም አልተረከቡ!) እንደፈለጉ ወስነው ከተማዋ ከተዘፈቀችበት አረንቋ ሊያወጧት አይችሉም የተባለበት ሌላኛው ምክንያት ይህ ነበር። የፌዴራል መንግስቱ ከሀገር ውስጥ የፋይናንስ ተቋማት እንዲበደሩ እንደማይፈቅድላቸው ሳይታለም የተፈታ ነው። ከውጭ ተቋማት ፌዴራል እንዲበደርላቸው መጠየቅም አፍን ከማበላሸት አያልፍም። የፌደራል መንግስቱ በህግ የሚገደድበት የድጐማ ስርአት በሌለበት ሁኔታ እጁን ፈታ አድርጐ በተቃራኒው ለቆመው ከተማው አስተዳደር መና ይወረውራል ብሎ መጠበቅ ማሞ ቂሎነት ነው። አስተዳደሩ የሚያመነጨው ገቢ ደግሞ እንኳን ትላልቅ ካፒታል ፕሮጀክቶችን ሊሰራ ቀርቶ የሰራተኛ ደሞዝና መደበኛ ወጪዎችን ለመሸፈን በየአመቱ የሚንገታገት ነው።

የቻርተሩ አንቀጽ 61 ደግሞ ሌሎች አስገራሚ ቁምነገሮች ተሸክሟል። ከእነዚህ ውስጥ ንዑስ አንቀጽ አምስትና ስድስት የሚከተለውን ይደነግጋሉ፣ "የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የፌደራል መንግስት በመወከል የከተማውን አስተዳደር ስራ ይከታተላል፣ የከተማውን አቅም ግንባታ ይገነባል። የከተማው አስተዳደር ዕቅዱን፣ በጀቱንና የከተማውን አጠቃላይ ሁኔታ በተመለከተ ለፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር አመታዊና ወቅታዊ የስራ አፈጻጸም ሪፓርት ያቀርባል።"

እነዚህ አንቀጾች አቶ መለስ ምን ያህል በቁጥጥር የታመመና ለአዲሳአባ ህዝብ ያለውን ጥላቻ የሚያሳይ ነው። በከተማው ህዝብ የተመረጠ የህግ አውጭ አካል ለፌደራሉ አስፈጻሚ መስሪያ ቤት ተጠሪ የሚሆንበት ህግ

ማውጣት ንቀት ካልሆነ በስተቀር ሌላ ምን ሊሆን ይችላል?

በምርጫ 97 የነዋሪውን ይሁንታ አግኝተው የነበሩት እነ ዶክተር ብርሀኑ ነጋ የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትሩ ዶክተር ሽፈራው ጋር እየሄዱ ስለ ልማታዊ መንግስት፣ የስርአቱ አደጋዎች ስለሆኑት ጠባብነትና ትምክህት፣ ስለአበዮታዊ ዲሞክራሲ መርሆዎች፣ ስለኪራይ ሰብሳቢነት የአቅም ግንባታ ትምህርት ይወስዱ ነበር ማለት ነው? ፣ ወይንስ አቶ መለስ የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትርነት ደርቦ ይይዛል?... እነ ዶክተር ብርሀኑ በየወሩ ዶክተር ሽፈራው ጋር እየቀረቡ፣ "ከቡር ሚኒስትር! ይህን አቅደናል፣ በጀታችን ይህን ያህል ነው፣ የከተማው አጠቃላይ ሁኔታ ደግሞ ይህን ይመስላል... ክቡርነቶ የሾሙልን የፓሊስ ኮሚሽነርና ምክትል ኮሚሽነር አላሰራ አሉን። እባክዎ ይቀይሩልን!!" የሚል ተማጽኖ ያቀርቡ ነበር?

ቻርተሩ በግልጽ ቢያስቀምጥም መዘዛቸውን በመፍራት እስከ ዛሬ ድረስ ወደ ተግባር ያልተለወጡ አሉ። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ የአዲሳባ የስነ ምግባርና ፀረ - ሙስና ኮሚሽን ማቋቋም ይገኝበታል። ኮሚሽኑ የጣልቃ ገብነትና ነፃነት ችግር እንደሚያጋጥመው ቢጠበቅም በተባራሪ አግኝቶ የሚመዛቸው ክሮች ኢህአዴግን ይገለባበጥ ነበር። በመሬት ፣ግቢ፣ የግዥ አፈጻፀም፣ መንግስታዊ አሰራርን ባልተከተለ ገንዘብ አጠቃቀም ብቻ ከ ሀያ ቢሊዮን በላይ የህዝብና መንግስት ገንዘብ ተዘርፉል። ከአስር ቢሊዮን ብር በላይ የህዝብ ገንዘብ መዘረፉን ተጠሪነቱን ለአቶ መለስ ያደረገው የፌደራል ፀረ ሙስና ሲፈራ ሲቸር አጋልጧል። እንደ እውነቱ ከሆነ የተፈፀመው ሌብነትና ህግን ያልተከተለ አሰራር በገለልተኛ አካል ቢጣራ በቅድሚያ የፍርድ ቤት ሳጥን ውስጥ የምናገኛቸው አቶ መለስና አርከበ እቁባይ ይሆኑ ነበር።

በእንቅርት ላይ እንዲሉ በምርጫ 97 ማግስት በአቶ መለስ ቀጭን ትእዛዝ ቁልፍ የገቢ ማስገኛ ዘርፎች፣ የከተማዋ ውልና ማስረጃ እንዲሁም የአንድ ከተማ የደም ስር ተደርገው ከሚቆጠሩት አንዱ የሆነው ትራንስፓርት ክፍል ተቀምቷል። ከሁሉም አሳዛኙ ከከተማዋ ታሪክ ጋር ልዩ ቁርኝት ያለው አንበሳ አውቶብስ ሳይቀር ተጠሪነት ለፌደራል መንግስት ሆኗል።

ይህንን በተመለከተ ከአቶ መለስ ጋር በነበረን ሳምንታዊ ስብሰባ የመዲናይቱ ነዋሪ ቅሬታ እንዳለው ስንነግረው ባልጠበቅነው ሁኔታ የአንድ እጁን መዳፍ በሌላ እየጠበጠበ፣ "የቅንጅት ፈረሶች የሆኑትን የከተማ ታክሲዎች ከጨዋታ ውጭ ሳናደርግ ውሳኔው አይቀለበስም!" የሚል ምላሽ ሰጠን። በአቶ

መለስ ካፈርኩበት ቀናት አንዱ ሆኖ ተመዘገበ። ከዛን ቀን በኃላ ይህንን ጥያቄ ህዝቡ ምን ይላል ከሚለው ሳምንታዊ ሪፓርት ሰረዝነው። አቶ መለስ እንደዛተው ታክሲዎችን ለመተካት ያላሰለሰ ጥረት ቢያደርግም አልተሳካም። ከቅን ልቦና ያልመነጨ በመሆኑ።

በአጠቃላይ መልኩ እነ አርከበ ባቀረቡት ጥናት መሰረት ቅንጅት አዲሳባን በተረከበ በሁለት አመት ውስጥ መዲናይቱ ከተማ አቀፍ ኪሳራ (Bankruptcy) በማወጅ የድሬደዋ ተከታይ ትሆናለች። ይህንንም ተከትሎ የእነ አርከበ ቡድን አዲሳባን እንደ ነውጥ መሳሪያ በመጠቀም መሬት አንቀጥቅጥ ተቃዉሞዎችና አመፆች በጥቅም ላይ ይውላሉ። ግጭቶች በህዝቡና አስተዳደሩ በማይቆጣጠረው ፓሊስና ፀጥታ ሀይሉ መካከል ይሆናል። የህዝብና ሀብትና ንብረት ይወድማል። የሰዉ ደም እንደ ጐርፍ ይወርዳል... አስተዳደሩ የከተማዋን ፀጥታ መቆጣጠር እንዳቃተው በሰፊው ይነገራል።

ቀዩ መስመር ታለፈ በሚል አስተዳደሩ ይበተናል።

ምእረፍ ሁለት

"ንቅል ካድሬ!"

"ከየክልሉ ከተማ ቀመስ ሰው እየተፈለገ ተመልምሎ አዲስ አበባ እንዲገባ ተደረገ... በዚህም የአዲሳ አበባ ትንሳኤ ተበሰረ።"

በረከት ስምኦን (የሁለት ምርጫዎች ወግ)

እነ አርከበ ከትግራይ ወደ አዲስአባ ከመምጣታቸው ጥቂት ወራት በፊት በህውሀት ውስጥ መደናገጥ ተፈጥሮ ነበር። የህውሀት ዳግም መከፋፈል። ምክንያቱ ደግሞ በወ /ሮ አዜብና አርከበ ቡድኖች መካከል አለመግባባቶች መፈጠራቸው ነበር። መነሻው መረን የለቀቀ የጥቅም ግጭት ሲሆን አላማው የህውሀት ኢንዶውመንቶችን የመቆጣጠር ታሳቢ ያደረገ ነበር። ቡድኖቹ ይህንን ልዮነት ወደ ፊት ሳያወጡ በሌሎች ጉዳዮች ላይ መገታተር ጀመሩ። ፀቡ የተገለፀበት አግባብ ለየቅል ሆነ።

የአርከበ ቡድን የተንኮል እቅዱን በሁለት መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ አደረገ። የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነትና ህውሀት በአቶ መለስና በረከት እየተገፉ ነው በማለት።

በመጋቢት ወር 1993 ዓ.ም የህዉሀት መሰንጠቅ ምክንያቱ የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ላይ የተነሳው ልዮነት እንደሆነ፣ የአልጀርሱ ስምምነትና እሱን ተከትሎ የተሰጠው የፍርድ ቤት ውሳኔ ትግራይን ለመጉዳት የታሰበ መሆኑ፣ መለስ የትግራይን መሬት ለኤርትራ አሳልፎ መስጠቱ፣ የባድመ ጉዳይ እንዳለቀለት ውስጥ ለውስጥ አሰራጩ።

አብዛኛው የህውሀት ካድሬ አቶ መለስ በኤርትራ ጉዳይ ላይ በያዘው አቋም ደስተኛ ሰላልነበረ በአርከበ መስመር ተሰለፈ። በሰውየው ላይ ያለው እምነት እየተሸረሸረ ሄደ። ጦርነቱ ግማሽ ላይ የቆመበት ምክንያት የመለስ ተንበርካኪነት እንደሆነ መተማመን ተደረሰ። የትግራይ ህዝብም ይህንኑ ተቀብሎ አስተጋባ።

ሁለተኛው የአርከበ ዘመቻ የህውሀት ካድሬዎች ከፊዴራል ስልጣን

እየተገፉ እንደሆነ የሚገልጽ ነበር። መለስ እያስጠቃን ነው የሚለው ከመቀሌ አልፎ አዲስአባ ድረስ ተዛመተ። የመለስ ቀኝ እጅ በረከት ስምኦን ህውሀትን ወደ ገደል ገፍትሮ ሊጥላት ነው ተባለ። በህውሀት ህዋሳትና መሰረታዊ ድርጅቶች ዋነኛ መነጋገሪያው ይህ ሆነ።

አዲግራት ውስጥ የምትገኝ አንዲት የቀበሌ ህዋስ የሚኒስትሮች ውክልና ትግራይን አግሏል ብላ አቋም ትወስዳለች። መቐሌ ላይ የምትገኝ መሰረታዊ ድርጅት ከሀያ በላይ ሚኒስትሮች ባሉበት ሁኔታ ውጭ ጉዳይና ጤና ጥበቃን ብቻ ለትግራይ መስጠት ፍትሀዊ አይደለም የሚል ሪፓርት ታስተላልፉለች። የተምቤን ወረዳ ህውሀት ጽ/ቤት መለስ የራሱን ስልጣን ከሌሎች ጋር አደላድሎ ህውሀትን ገፍትሮ ጣለ በማለት አጀንዳ ቀርጻ ትነጋገራለች። ኢህአዴግ ቢሮ በፅዳት ሰራተኝነት የምትሰራ የህውሀት አባል ቢሮው በብአዴን ካድሬዎች ተወረረ ብላ ቅሬታ ታቀርባለች። እንደ እውነቱ ከሆነ የህውሀት ካድሬዎችና አባላት የስልጣንን ትርጉም በደንብ ተገንዝበዋል።

በሂደት አቶ አርከበ ይዞ ብቅ ያለው መቀሰቀሻ የካድሬውንና አባሉን ቁስል የነካ በመሆኑ ተቀባይነት አገኘ። በትግራይ ፕሮፐጋንዳና ድርጅት ተመድበው የሚሰሩ ቁልፍ ካድሬዎች ተቀላቀሉት።

ወ/ሮ አዜብ በበኩሏ አርከበና ቡድኖቹ በሙስና ተዘፍቀዋል የሚል ክስ ይዛ ብቅ አለች። አርከበ በሚስቱና ቤተሰቦቹ የያዘውን ንብረት በመረጃ አስደግፉ አራገቡች:: ላውንደሪ ቤት፣ ፉርማሲ፣ ክሊኒክ፣ ሱፐር ማርኬት፣ መስታወት ማስመጣትና መሸጥ...። በትግራይና አዲስአባ የተፈጠሩት አዳዲስ ባለሀብቶች የአርከበና ቡድኖቹ እንደሆኑ በስም ዝርዝር አሳወቀች። ስዬ በታሰረበት የሌብነት ወንጀል አርከበ እጁ እንደነበር፣ በተለይም የስዬ ወንድም ለገዛቸው በርካታ መኪናዎች ቅናሽ እንዲያገኝ ማግባባቱን የፈፀመው አርከበ መሆኑን አጋለጠች።

በወቅቱ ሁለቱም ቡድኖች "ያለ ኢኮኖሚ የበላይነት የፓለቲካ የበላይነት አይመጣም" የሚል ፓሊሲ ቀርፀው የህውሀት ባለሀብቶችን ለመፍጠር ተንቀሳቅሰዋል። በዚህ ፓሊሲ ምክንያት በአንድ ሌሊት ከሹፌርነት ወደ አስመጪና ላኪነት፣ ከገራዥ ሰራተኝነት ወደ የመኪና እቃ መለዋወጫ አስመጭነት፣ ከታጋይነት ወደ ሪልስቴት ባለቤትነት፣ ከወታደርነት ወደ ፉበሪካ ባለቤት፣ ከህውሀት ምድብተኛ ካድሬ ወደ ግል ባንክ ከፍተኛ አክሲዮን ባለድርሻነት የተቀየሩ ሰዎችን መስማት የተለመደ ነበር።

በሂደት የሀይል ሚዛኑ እያደር ወደ አርከበ ቡድን አዘነበለ። መቀሌ

የሚገኘው የህውሀት ጽ/ቤት ለሁለት ተከፈለ። የወ/ሮ አዜብ የምንጊዜም ደጋፊ የሆነውና የፕሮፓጋንዳ ሀላፊው ቴዎድሮስ ሀጐስ በአንድ በኩል ፣ እነ አርከበ በሌላ በኩል ተሰለፉ። በጽ/ቤቱ የሚያዙ አቋሞች አስደንጋጭ ሆኑ...አዲሳባ ከሚገኘው ኢህአዴግ ቢሮ ራሳቸውን አገለሉ። ከ1993 ዓ.ም ጀምሮ ለስምንት አመታት የኢህአዴግ ቢሮ ከፓርቲው መተዳደሪያ ውጭ የሶስት ብሔር ድርጅቶች ጥምረት ሆነ። ስራ አስፈፃሚውን ደግሞ ሙሉ ለሙሉ ብአዴኖች ተቆጣጠሩት።

(የቢሮው ሀላፊ በረከት ስምኦን ፣ ስልጠና ክፍሉን ታደሰ ካሳ (ጥንቅሹ)፣ የፐሬስ ክፍሉን ፍሬህይወት አያሌው፣ የውጭና ህዝብ ግንኙነቱን ሴኮቱሬ፣ የአዲሳባ ከንፍ ሀላፊ ዮሴፍ ፣አስተዳደርና ፉይናንሱን ተሰማ ድብርቱ)

ለአዲሳባ ኢህአዴግ ክንፍ ከህውሀት ውስጥ በአስፈፃሚነት የሚሰራ ወደ መዲናይቱ እንዲልኩ በተደጋጋሚ ሲጠየቁ የለንም የሚል ምላሽ ሰጡ። በምርጫ 2000 ለአዲሳባ ከንቲባና ምክትል ሊወዳደሩ የሚችሉ እጩዎችን ከማእከላዊ ኮሚቴ መልምላችሁ ላኩልን ተብለው ቢጠየቁ፣" ለፌደራል የምናዋጣው የለንም ያልን ለከተማ እንዴት ይኖረናል?" የሚል መልስ በመስጠት ከመዲናይቱም ራሳቸውን አገለሉ።

(በምርጫ 2000 ብአዴን ለከንቲባና ምክትል እንዲወዳደሩ የገቢዎች ሚኒስትሩ መላኩ ፉንታ እና ከሚዲያ ተቋማት ከፍያለው አዘዘን፣...አህዴድ ለከንቲባነት ኩማ ደመቅሳን እና ወ/ ሮ አስቴር ማሞን ፣...ወ/ ሮ አዜብ መስፍን ደግሞ ለከንቲባነት አህዴዲን አስቴር ማሞ በእጩነት አቀረቡ። አህዴዲ አስቴር ህውሀትንም ወከለች። ደኢህዴን ከፓለቲካ ጨዋነት አልተላቀቀም ተብሎ በድጋሚ ተዘለለ።)

መቀሌ በተገላቢጦሽ ህውሀት በኢህአዴግ መገለል እየተፈፀመባት እንደሆነ በሰፊው መነገር ተጀመረ። ህውሀቶች ከሌላው በተለየ የቀረበላቸውን እድል እየገፉ "ጅራፍ ራሱ ገርፎ... " እንደሚባለው ሆኑ። ከኢህአዴግ እህት ድርጅቶች ውስጥ እንደ ህውሀት አኩራፊ የለም። ምክንያቱ ደግሞ ህውሀት የተቃኘው "ሁሉን ማግኘት አሊያም ሁሉን እርግፍ አድርገ መተው ! " የሚባለው የዜሮ ድምር ፓለቲካዊ አሳቤ የተጠናወታቸው በመሆኑ ነው። ሁሉንም ቦታ ጠቅልለውና ሙጥጥ አድርገው መያዝ ይፈልጋሉ፣ ካልሆነ ደግሞ ሁሉንም ለማጣት ተግተው ይሰራሉ።

ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ የነበረው አቶ መለስ የህውሀት ካድሬዎች ጭላሽት ከመቀባት ተቆጥበው ድርድር እንዲቀመጡ አሳሰበ። ከብዙ ማንገራገር በኃላ

ጥሪውን ተቀብለው አራት ኪሎ መጡ። ግምገማው ተጀመረ።

ህውሀቶች የያዙትን ሀሳብ በአብሪት ተወጥረው መተኮስ ጀመሩ። በረከትን እንዲህ በማለት ተከራከሩት፣ "ብአዴን የህውሀትን መሰንጠቅና መዳከም እንደ ጥሩ አጋጣሚ በመውሰድ ኢህአዴግ ቢሮን በቁጥጥር ስር አውሏል ... በረከት! ጥንቅሹ!ሀላዌ!ሴኮ! ፍሬህይወት!ተሰማ!..." በረከት ብልጭ አለበት። ሲናደድ ደግሞ የሚናገረውን አያውቅም፣

"እናንተ ውስጥ ብእርና ወረቀት አጋጥሞ ሶስት ገፅ መፃፍ የሚችል ካለ የእኔን ወንበር ዛሬውኑ መውሰድ ይችላል! ይህን የተጃጃለ ክርክር ይዛችሁ ከምትመጡ ራሳችሁን ዞር ብላችሁ ብታዩ ጥሩ ነበር። ታቹን ስትርመጠመጡ ጊዜ እያለፈባችሁ ነው።"

ብሎ የስድብ ውርጅብኝ አወረደባቸው። በፈዝና የንቀት አርጩሜ ገረፋቸው።

ርግጥም በረከት ትክክል ነበር።

ከመለስና አባይ ውጭ ያሉት የህውሀት ካድሬዎች በምላሳቸው ወፍ የሚያረግፉ፣ ወደ ብእርና ወረቀት ሲመጣ ደግሞ ጨዋ ናቸው ። የንቃተ ህሊናቸው ቁልቁል እየወረደ ሄዷል። ከዘመኑ ጋር የሚራመዱ መሪዎች ማግኘት ተስኗቸዋል። ጥሎአቸው ያልሄደው ከስልጣን ጥማት የሚመነጨው ደፋርነት ብቻ ሆኗል።

አብሪታቸው ሳይፈነዳና ድርድሩ ሳይሳካ ህውሀት ከአራት ኪሎ ኢህአዴግ ቢሮ ራሱን እንዳገለለ ቀረ። የድርጅቱ ህገ ደንብ " የጽ/ቤቱ አስፈጻሚዎች ከሁሉም የብሄር ድርጅቶች የተውጣጣ ይሆናል" የሚለው ለስምንት አመታት እንደተጣሰ ቀረ።

አቶ መለስ ይቺ ባቄላ በማለት ስራውን ውስጥ ለውስጥ ጀመረ። የአርከበ ቡድንን የዝርፊያ ዶክመንቶች አሰባስቦ በጐንዮሽ እንዲደርሳቸው አደረገ። እርግጥ አቶ መለስ ለማስፈራሪያ እንጂ በሙስና አሳቦ እግረ መቅ ሊያጠልቅላቸው እንደማይፈልግ ይታወቃል። የዛ አካሔድ በነ ስዬ አብርሀ ዘመን ብዙ ዋጋ አስከፍሎታል። የህውሀት ካድሬ የእነ ስዬን ንቅዘት እያወቀና በአይኑ በብረቱ እያየ አላጋነነውም። በመቀሌ የሚገኘው ካድሬ አልፎ ሄዶ፣ "ሁላችሁም አንድ ናችሁ ፣ አንዱ ሌላውን በሌብነት ለመክሰስ የሞራል ብቃት የለውም " ብሎ እንደነበር ያስታውሳል። እናም የተለመደውን የሙስና ክስ ይዞ መምጣት የመልስ ምት እንደሚኖረው አውቋል።

ከዚህ በተጨማሪም የህውሀት ካድሬዎች ዘንድ ሌብነትን በተመለከተ

አደገኛ አመለካከትና አዝማሚያ እንዳለ ያውቃል። የህውሀት አባላት በትግራይ ክልል ሙስና ከሞላ ጐደል በቁጥጥር ስር ውሏል፣ ሌብነት የስርአቱ አደጋ አይደለም ብለው ያምናሉ። በሌላ በኩል ፌደራልና አዲስአባ ተመድቦ የሚሰራ የህውሀት ካድሬ ሰረቀ ሲባል አያጋንኑም። በእነዚህ ተቋማትና አዲሳባ መመደብ ሎተሪ እንደደረሰው ይነገራል። "እንኳን ደስ አለህ" ይባላል። ዘርፈው ሲገኙም እንደሌላው ባለስልጣን ድርሻቸውን እንደወሰዱ ይቆጠራል። ብዙዎች ከፌደራልና አዲሰአባ በዘረፉት ገንዘብ መቀሌ ላይ አፍ የሚያስከፍቱ ቪላዎችን ገንበተዋል። በተለይም በአካል ተገኝቼ ያየኃቸው ሐውልቲና ገረብ የሚባሉት አካባቢዎች የምእራቡ አለምን ህንፃዎች የሚያስንቁ ናቸው።

ሁኔታው አሳፋሪ ደረጃ ደረሰ...

የትግራይ ህዝብ ማጉተምተም ጀመረ፣ አቶ መለስ የህዝቡን ስሞታ በማየት ወደ መቀሌ ወረደ። ስብሰባው ሲጀመር ባልተጠበቀ ሁኔታ ግምገማው ተገለበጠ። ካድሬዎቹ የግምገማው አድማስ በትግራይ የሚገኙትን ብቻ ሳይሆን በሁሉም ቦታ የተመደቡትን የህውሀት ባለስልጣናት ማካተት እንደሚኖርበት ተከራከሩ። የፌደራል፣ የደህንነት፣ የፓሊስና መከላከያ ባለስልጣናት እንዲካተቱ ጠየቁ። ግምገማው በሌብነት ላይ ብቻ ከሚንጠለጠል ያለፉት ሁለት አመታት አጠቃላይ ጉዞ መመልከት ወቅታዊ እንደሆነ በተደራጀ መንገድ አሳሰቡ፣ ...የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት (ጦርነቱ የቆመበት ምክንያት፣ የአልጀርሱ ስምምነት፣ ባድመና የአለም አቀፍ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ፣ የኤርትራውያን ንብረት አመላለስ) ...የኤፈርት የፉይናንስና አዲት ሪፓርት፣ የባለስልጣናት የሀብትና ንብረት ደረጃ፣ የምደባና ሹመት ግልፀኝነት፣ ፀረ ዲሞክራሲነት በግምገማው ይካተቱ የሚል አቋም ወሰዱ።

አቶ መለስ የካድሬዎቹ አካሄድ ስለገባው መውጫ መንገድ ፈለገ። ሳይከራከር ካድሬው የያዘው አቋም አብዮታዊና የሚደገፍ እንደሆነ አስረዳ። ይህ ተራማጅ አስተሳሰብ ከህውሀት ውጭ ማንም ሊደፍረው እንደማይችል በኩራት ገለፀ። ግን ደግሞ ህውሀት የሻይ ቤት ውይይት ከበብ ስላልሆነ ያለ ቅድመ-ዝግጅት መግባት እንደሌለበት አሳወቀ። የሚደረገው ግምገማ በግልም ሆነ በድርጅት ደረጃ ተጠናክሮ የሚወጣበት እንጂ፣ ጠላቶች በድጋሚ እንዲሳለቁ እድል የሚሰጥ መሆን እንደሌለበት አብራራ። የሁለት አመቱን ጉዞው የቀጣይ አቅጣጫ የሚያሳይ ሪፓርት ፓሊት ቢሮ በቅርብ አዘጋጅቶ ግምገማው እንደሚጀመር መተማመን ተደረሰ። በተመሳሳይ ደረጃ በኢህአዴግ ደረጃና በሌሎች ብሄር ድርጅቶች ግምገማው እንደሚካሄድ ቃል ገባ። የጠዘውን ካድሬ ውሀ ቸለሰበት!

አቶ መለስ ከጓላ እየተሸረበበት መሆኑን ተገንዝቦ የአርከበን ቡድን

ከመቀሌ ጠራርጐ ማስወጣት ጊዜ የሚሰጠው እንዳልሆነ ተረዳ። ለጊዜው ባለቤት የሌላት ከተማ አጠገቡ አለች። ከተማዋን መለወጥና ካንቀላፉችበት የቀን መኝታ ማስነሳት ጊዜ የማይሰጠው አጀንዳ ሆኗል። ስለዚህም አቶ መለስ በአንድ ድንጋይ ሶስት ወፍ ለምታት አልሞ ተነሳ፡- የአፍሪካ ተቀናቃኞቹን አፍ ማዘጋት፣መዲናይቱን በልማት ማዕበል በመምታት የነዋሪውን አቅጣጫ ማስቀየር፣አርከበና የቡድኑ መሪ ካድሬዎችን ከትግራይ ጠራርጐ ማስወጣት። ለዚህ እንዲረዳ "መዲናይቱን እናድሳት" የሚል ሰነድ አዘጋጀ።

"የመዲናይቱ እናድሳት "እሳቤ የሚመነጨው ከእነዚህ ሶስት ውጫዊ ምክንያቶች እንጂ፣ ኢህአዴግ በአዲሳባ ላይ ውስጣዊ የአመለካከት ለውጥ ስላመጣ አልነበረም። የድርጅቱ "ከተማን በገጠር ስሌት" መምራት አቅጣጫ አልተቀየረም። አዳዲስ ከተሞችን መፍጠርና ማመጣጠን የሚለው ስትራቴጂ እንደነበረ ነው። ከዛም አልፎ የትምክህተኛ መከማቻ ከተሞችን ማዳከም ከሚለው ገራ ውስጥ አዲሳባ የመጀመሪያው መስመር ውስጥ የነበረች ናት።

መዲናይቱን እናድሳት የሚለውን ሰነድ ተከትሎ በአዲሳባ ከፍተኛ ንቅናቄ እንደሚቀጣጠል ታወጀ። የትራንስፎርሜሽኑ መሀንዲስ አባይ ፀሀዬ እንዲሆን ተደረገ። ድርጅቱና አባይ ከደኢህዴን በስተቀር ለሶስቱ ብሔር ድርጅቶች ከተማና ዞን መምራት የሚችሉ ካድሬዎች እንዲያዋጡ ትዕዛዝ ሰጡ። ደኢህዴን አንኳን ሊያዋጣ ቀጥ ብሎ የሚቆምበት አንድ እግር የለውም ተብሎ ተዘለለ... የፓለቲካ ጨዋ! ... ያሳፍራል።

አንዳንድ የጉራጌ ካድሬዎች ቅሬታቸውን ይዘው ወደ አለቃቸው ዶክተር ካሱ ኢላላ ቢሮ ሄደው ነበር። ዶክተሩ ለትዝብት በሚጥለው መንገድ "ስራውን የሚሰሩት መለስና አባይ ስለሆኑ ጥያቄ ማንሳቱ ተገቢ አይደለም። እነሱ ሁሌም ትክክል ናቸው!" ብሎአቸው እርፍ አለ። በእርግጥ የጉራጌ ካድሬዎች "አስጠቂው "የሚል ስያሜ አስቀድመው ስለሰጡት ብዙም በምላሹ አልተገረሙም። ከታሪክ ተጠያቂነቱ እና ለህሊና በሽታው አስቀድመው ከማዘን ውጭ...

በአጠቃላይ ግን ከሀያ ሚሊዮን በላይ የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦችን ለማስተዳደር ስልጣን የተረከበ ፓርቲ አስር ሰዎችን ለማዋጣት አቅም ያንሰዋል ሲባል በርካታ ጥያቄዎች አስነሳ፡- ደኢህዴን በካድሬነት የሰበሰበው እነማንን ነው? የደቡብ ክልል በምን አይነት ሰዎች እየተዳደረ ነው? ከአዲሳባ ህዝብ ብዛት አንዳንዴ ሁለተኛ ሌላ ጊዜ ሶስተኛ የሆነው የደቡብ ኢትዮጵያ ብሔረሰብ ለሚያነሳው ጥያቄ ምን ምላሽ ይሰጣል? በአዲሳአባ የለውጥ እንቅስቃሴ ውስጥ ደኢህዴን አልነበረበትም ተብሎ ለታሪክ ሲቀመጥ ምን ስሜት ይፈጥራል?

በረከትና ብአዴን በበኩላቸው ህላዌ ዮሴፍን ወደ መዲናይቱ አዘዋወሩ። የኋላ ደጀን እንዲሆኑት አስር የብአዴን ካድሬዎች ከአማራ ክልል እንዲመጡ ተደረገ። ህላዌ አዲሱን ከንቲባ በአይነ ቁራኛ እንዲጠብቅ መመሪያ ሰጡ። የኘሮፖጋንዳ ክፍሉን እንዲቆጣጠር አደረጉ። የህላዌ ምደባ በአማራ ልማት ማህበር (አልማ) ጋር ተያይዞ ጥያቄ አስነሱ። ባህርዳር የሚገኘው የአልማ ጽ/ቤት በአሳት ቃጠሎ ሙሉ ለሙሉ እንዲወድም ካደረጉት ውስጥ የህላዌና ታደሰ ካሳ (ጥንቅሹ) ስም በሰፊው ይነሳ ስለነበር። የማጣራቱ ሂደት ሳይጠናቅ ሁለቱም እንዲሸሹ መደረጋቸው ተቃውሞ ገጥሞት ነበር። ጥንቅሹ የባህርዳር ህዝብ አላስቀምጥ ብሎት አስቀድሞ አራት ኪሎ በሚገኘው ኢህአዴግ ቢሮ እንዲከትም ተደርጓል።ህላዌ ደግሞ ቀኑን ጠብቆ ለሚዛን ጥበቃ ወደ ትውልድ በታው መጣ።

በመሆኑም መዲናይቱን የማደስ እርምጃ በአባይ ፀሀዬ የጡት አባትነት፣ በአርከበ እቀኳይ ፊት አውራሪነት፣ በህላዌ ዮሴፍ ደጅ አዝማችነት ተጀመረ።

ምእራፍ ሶስት

"ሰናይፐር ተኳሽ"

"አባይ የቋጠረውን፣ አባይ ብቻ ይፈታዋል"
ፍስሀ ዘሪሁን (መአሲ)

የጨፈው ምክር ቤት ለመዲናይቱ ተሀድሶ ተዘጋጅቷል። አዳራሹ እስካፍንጫው ሞልቷል። ሰፊውን ከፍል በሚይዘው የመሀለኛው ቦታ የከተማው፣ በስተግራ ፌደራል፣ በቀኝ ደግሞ አዲሶቹ ካድሬዎች ተቀምጠዋል። ውጥረት ሰፍኗል።

የአዲሳባ ነባር ካድሬዎች ባነበቡት ሰነድ ደስተኛ እንዳልሆኑ ፊታቸው ያሳብቃል። ቅጥ አምባሩ የጠፉበት ፅሁፍ አበሳጭቷቸዋል። ጭፍግግ ብለዋል። ስንዴውን ከእንክርዳዱ መለየት የተሳነው ጽሁፍ በጅምላ ለመጥረግ ያሰበ መሆኑ ጉብቷቸዋል። ሊበሏት ያሰቡትን አሞራ ሆኖባቸዋል። በሹክሹክታ ያወራሉ። በተለይ በቅንነት ሲሰሩ የነበሩት ተብሰከሰከዋል። ጩኸት ሰበው ጩኸት ይተነፍሳሉ።

ርግጥም ምንም ጥሪት ያላሰባሰቡት ከተከፉይ ካድሬነት ቢባረሩ ምን ይውጣቸዋል?... ያውም በዝጉብኝ እየተጠጣ፣ በየቀኑ ታናሽና ታላቅ እየተቆረጠ። ቤተሰብም ቢሆን በሰፊው ለምዷል። ከአካባቢው በተሻለ የኑሮ ሁኔታ መኖር ጀምረዋል። ልጆች ደረጃውን የጠበቀ ትምህርት ቤት ገብተዋል።

በተቃራኒው መውደቂያ ያዘጋጅት ነባር ካድሬዎች በሰላም መሰናበት ፈልገዋል። ሰርቀው ያከማቹትን ንብረት ከኢህአዴግ ሳይጣሉ ለመብላት። አንዳንዶቹ በመሀል ከተማ በአከራይ ተከራይ ስም ነባሩን ነጋዴ አስለቅቀው የቤተሰብ ቢዝነስ ከፍተዋል። ኢትዮጵያ ሆቴል አካባቢ የቡድን ቡቲኮች ከፍተው የጥቁር ገበያ ዶላር መመንዘሪያ ያደረጉም አሉበት። በመሬት ወረራው በግንባር ቀደምትነት ተሳትፈው በሻንጣ ብር ያከማቹም አሉ። ከአንዳንድ ነጋዴዎች ጋር በመመሳጠር ግብር ቅናሽ አድርገው ኪሳቸውን የሞሉ ብዙ ናቸው። የኤርትራውያን የግል ቤትና ቢዝነስ ወደ ራሳቸውና ቤተሰባቸው ያዞሩ በርካቶች ናቸው። እነዚህን ካድሬዎች ያስፈራቸው ነገር አንድ ብቻ ነው። አስቀድሞ እንደተደረገው አዉጫጭኙ ከድርጅት አልፎ ወደ ህዝብ ከወረደ።

"ሁሉን እናውቃለን" ያለው ህዝብ የተነፈሰ እለት መጨረሻቸው የት እንደሚሆን ተገንዝበዋል። ከህዝብ የተደበቀ አንዳችም ነገር ስለሌለ።

ከፌደራል ተቋማት አሥር የህውሀት ፕሮፌሽናል ገምጋሚዎች ስብሰባውን ለማጋጋል ተመደቡ። ዘርአይ አስገዶምና ኢሳያስ ወ/ሂዮርጊስ ጠርናፊያቸው ሆኑ። ዘርአይ የኢቲቪ ስራ አስኪያጅ፣ ኢሳያስ ደግሞ የደህንነት ሹማምንት ናቸው። ካድሬዎቹ ወደ ጨፌ ሲመጡ ከድርጅቱ ስልቶች አንዱ የሆነውን "ገሎ መዳን" ለመተግበር ልዩ ተልእኮ ወስደው ነበር።

በነገራችን ላይ ከድርጅቱ የግምገማ ስልቶች በብዛት ስራ ላይ የሚውሉት "ገሎ ማዳን" እና "አድኖ መግደል" በመባል ይታወቃሉ። ሁለቱም የዜሮ ድምር መጫወቻ ቴክኒኮች ናቸው፣... አንዱን ለማዳን ሌላውን መግደል። የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ጨዋታ!

የዜሮ ድምር ጨዋታ (Zero sum game) እንደ ኢኮኖሚክስ ባሉ የማህበረሰብ ሳይንሶች ከተለመዱ ሀልዮቶች አንዱ ነው። በዚህ የጨዋታ ህግ መሰረት አንዱ ሙሉ ለሙሉ ለማሸነፍ ሌላኛው መሸነፍ፣ አንደኛው ሊያተርፍ ሌላኛው ማከሰር፣ አንዱ ሊበለፅግ ሌላኛው መደህየት ይኖርበታል። በዜሮ ድምር ጨዋታ የጋራ ድል (Win-Win) የሚባል ነገር አይሰራም። ዋነኛ ባህሪው ጥሎ ማለፍ ነው።

አቶ መለስ የዜሮ ድምር ጨዋታ መህንዲስ ነበር። መቼና በምን መልኩ እንደሚተገብረው ይቀይሳል። በአንድ ወቅት ዛሬ ወደ ጨፌ የላከውን ዘርአይ አስግዶምን በሚገባ አሟውቶታል። በህውሀት ካድሬዎች ፊት።

ታሪኩ እንደዚህ ነበር፣

በህውሐት መሰንጠቅ ተደናግጦ መሀል ላይ ከቆሙት ካድሬዎች አንዱ አባይ ፀሀዬ ነበር። የአንጃው ማዕበል ካለፈ በኃላ የፓርቲው ጉባኤ ተካሀሄደ። አባይ ፀሀዬ ለማዕከላዊ ኮሚቴ ተጠቆመ። በክፍፍሉ ወቅት አሸናፊውን አይተው በጊዜ ከተሸበለሉት አንዱ የሆነው ዘርአይ አስግዶም ለተቃውሞ እጁን ከፍ አደርገ፣

"አባይ መመረጥ የለበትም፣ የአላማ ፅናትና የራሱ አቋም የለውም!!" አለ። ቀዩ የመቀሌ አዳራሽ በሳቅ ተናወጠ።

የሚሉሽን በሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ!!

ህውሐቶች ዘርአይን የሚያውቁት እሱ አባይ ላይ በሰነዘረበት ትችት ነው። የሳቁ እንድምታ የገባው መለስ እንዲህ በማለት አከሮባት ሰራ፣ "አባይ ለፈስፉሳ እንደሆነ እናውቃለን፣ ግን ደግሞ የጀርባ አጥንቱን የሚደግፍ

የእንጨት መቀርቀሪያ ካስገባንለት ከማናችንም በላይ በወሬ ማቀባል የተሰማራ ሳይሆን የተግባር ታጋይ ነው።" አለ። ዘርአይን በመወረፍ አባይን ማዕከላዊ ኮሚቴ አስመረጠው። በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ!

አባይ ከዛን ቀን በኃላ ወገቡን ጠበቅ አርገው መስራት ቀጠለ። የእንጨት ሳይሆን የብረት መቀርቀሪያ ተገጠመለት። በሀገሪቱ ችግር በተፈጠረበት ቦታ ሁሉ አባይ አለ። ሱማሌ... ጋምቤላ... አፋር ይሯሯጣል። አባይ የሲኖዶሱም ፣ የመጂልሱም አባል እስኪመስል ድረስ ከተቋማቱ አይጠፉም።

ለገሎ ማዳን ጨፌ የተገኘው ዘርአይ አስግዶም የተወረፈው በአቶ መለስ ብቻ አይደለም። ቀዳማዊ እመቤቷም ሂሳቡን ሰጥታዋለች። እመቤት አዜብ በካድሬው ፊት፣ "ዘርአይ ማለት የራሱ ሀሣብ የሌለው፣ ተኛ ሲሉት የሚተኛ፣ ተነስ ሲሉት የሚነሳ፣ አስተላላፊ ቱቦ ነው" አለችው። እሱም ከእሷ አስከትሎ፣

"ቁልፍ ችግሬ ቱቦነትና አድርባይነት ነው" ብሎ ራሱን ወቀሰ።

"አይለመደኝም" አለ።

በድርጅቱ ማህደር እንዲሰፍር ተደረገ። ሁለት አመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ራሱን የኮነነበትን ስራ ለመስራት ተከታዮች አፍርቶ ጨፌ ተገኝቷል...አሊ አብዶን ገሎ ድርጅቱን ለማዳን።

ድመት መንኩሳ አመሏን አትረሳ።

***

ብዙሀኑ ከገጠር የመጡት አዳዲስ ካድሬዎች ግራ መጋባት ይታይባቸዋል ፣የከተማዋ አዙሪት አለቀቃቸውም። አብዛኛቹ የገጠር ከተማ አስተዳዳሪዎች ስለሆኑ አዲሳባ ውቅያኖስ ሆናባቸዋለች... ለሰው እንግዳ ላገሩ ባዳ!

በእርግጥ ድርጅቱ "ከተማን በገጠር ስሌት መምራት" ለሚለው ስትራቴጂ ማስፈጸሚያ ባያንሱም። አንዳንዶቹ በተለይም አህዴድ የላካቸው ለምን እንደመጡ እንኳን የተነገራቸው አዲስአባ ከደረሱ በኃላ ነው። አመጣጣቸውም ለየቅል ነበር። የአካባቢው ህዝብ አይናቸውን አያሳዮኝ በማለቱ በግድ የመጡ አሉ። ከሌሎች አስተዳዳሪዎች በመጣላታቸው "እስቲ ዞር ይበልልን" ተብለው በቅጣት የተመደቡ ይገኙበታል። ብአዴን መልምሎ የላካቸውም ተመሳሳይ ይዘት ነበራቸው። ከሁሉም የሚገርመው ብአዴንን ጨምሮ የመንዲ አማርኛ መናገር የማይችሉ በውስጣቸው ነበሩበት።

የከተሜ አማርኛ አለመቻል የግል ድክመት አይደለም። ግን ደግሞ ለማስተዳደር እየተዘጋጁ ያሉት ይህንን ቋንቋ ተናጋሪውን ክፍል ነው። መቼስ

ወፍ ለሚያዘንበው የመዲናይቱ ቢሮክራሲ በቱርጁማን ትእዛዝ አይሰጡ!

በጨፌ እየተካሄደ ያለው የፓለቲካ ቁማር ቀጥሏል...

ፍስሀ መአሲና አባይ እየተነጋገሩ ወደ አዳራሽ ገቡ። ፍስሀ በአይኑ ሲፈልገኝ አይቼ እጇን አሳየሁት። ተሰናብቶት ወደ እኔ መጣ።

"አባይ እምነት የምትጥልበት የግምገማ ቃል አቀባይ ስጠኝ ብሎኝ የአንተን ስም ሰጥቸዋለሁ" አለኝ። ከግራ መጋባት ሳልወጣ፣

"በኢህአዴግ ውስጥ ስኖር የግምገማ ቃል አቀባይ ሲባል ሰምቼ አላውቅም" አልኩት።

"ህዝቡ አዲሱን የእነአርከበን ቡድን እንዲደግፍ የተዘየደ ነው።"
እንዲህ በማለት ተቃወምኩት፣

"ለምን ሌላ ሰው አትፈልግም፣ አሊ በክፉ አይኑ እንደሚያየኝ እያወክ?"

"የተፈለገው ሁለት ካድሬ ነው። አሊ የራሱን ሰው መድቧል፣ አባይ በተቃራኒው ፈልጌ ጠይቆኝ ነው"

ከፍስሀ ጋር እየተጨቃጨቅን ወደ መድረክ አሊ አብዶና አባይ ፀሀዬ ወጡ። ትኩረቴን ወደ ስብሰባ መለስኩ።

አባይ ዲስኩር ጀመረ...

ቃለ-ጉባኤ እንድንይዝ እኔና ሉልሰገድ ይፍሩ መመረጣችንን ገለፀ። ሉልሰገድ በአሊ አብዶ ኔትወርክ ውስጥ ያለ ካድሬ ነበር። ለግምገማው ቃል አቀባይነት የመረጠው እሱ ነው። ሉልሰገድ የአሊ አብዶን ያህል በአባላት ይጠላል። አንዳንድ ካድሬዎች "ሻለቃ፣ የቁረጠው ፍለጠው ጌታ" ይሉታል። የካድሬነት ጥንካሬውን የሚለካው ከስራ ባባረረው ሰው ብዛት ነበር። መሸቶ በነጋ ቁጥር አስር ሰው ያባርራል። በዚህ ጉበዝናው ምክንያት በአሊ አብዶ የጨለማ ወቅት የዞን አራት ሊቀመንበር፣ በዘመነ አርከበ ደግሞ በልዩ ምደባ የአዲስ ከተማ ከንቲባ ሆነ። ቀጥሎም የአዲሳባ ኢህአዴግ ክንፍ ስራ አስፈፃሚ ተሹሞ እኛን ተቀላቀለን።

አባይ ሰነዱን በድጋሚ ቃል በቃል አብራራ። ወደ ኋላ ሄዶ የህውሐትን መከፋፈል ዋነኛ ምክንያት የቤተሰብ ገዥ መደብ (ቦናፓርቲዝም) መሆኑን በሰፊው ገለፀ። ይህ ገዥ መደብ ማዕከሉ አዲስአባ እንደነበር እና ያልተበጠሰ ኔትወርክ እንዳለው ተናገረ። ከአዲስአባ እስከ መቐለ የተዘረጋው የጥፋት ሀይል ፀረ ዲሞክራሲና ፀረ ልማት እንደነበር አስረዳ። ቫንጋርድ ፓርቲው ይህንን ሀይል ጠራርጌ ከትግራይ ቢያስወጣውም እንደ ቻይናው ኮሚንታግ ፓርቲ አዲስአባ ላይ መመሸጉን አስገነዘበ። ይህ ግምገማ ምሽጉን እንደሚደረምስ ገለፀ።

ቀጥሎ ወደ አዲሳባ አስተዳደር ችግሮች እንድንዲገባ እድሉን ለቤቱ ዘረጋ። ነባሩ የከተማ ካድሬ የተመካከረ እስኪመስል ፀጥ አለ። በተለያየ መንገድ ቢጐተጉት ቤቱን ከዝምታ ማውጣት አቃተው። ቁስቀሳው ይበልጥ ማጉረምረምን አስከተለ። ግራ ተጋባ።

ይህም ሆኖ የአባይ የተለመደ ባህሪ አልተቀየረም። ተረጋግቶ ይናገራል። እስከመጨረሻው ያዳምጣል። ግልፍተኛ አይደለም። ከአፉ የሚያወጣቸው ቃላት የተመዘኑ ናቸው። አውቆና ለክቶ ይናገራል። አይስትም። አይደበላልቅም። ከመለስ ጋር የሚለያዩት በዚህ ባህሪው ነው። የህውሀት ካድሬዎች አባይን "ስናይፐር ተኳሽ" ይሉታል። ኢላማውን አስቀድሞ በመለየት ተኩሶ የማይስት። ፍስሀ መአሲ በበኩሉ "አባይ የቋጠረውን፣ አባይ ብቻ ይፈታዋል" ይላል።

የመዲናይቱ ካድሬ በቶሎ ቀበቶውን ሊፈታ አልቻለም። ድርጅቱ ከጀርባ እየሸረበ ያለውን አውቋል። ከብዙ ውትወታ በኃላ ግምገማውን ምልዑነት ለማረጋገጥ ይቀራሉ የተባሉ ነገሮች ተነሱ። በተለይ ከዚህ ቀደም መዲናይቱን በስውር ሲያሸከረክሩ የነበሩ ካድሬዎች መገኘት እንደሚኖርባቸው አስተያየት ተሰጠ።

"ይጠሩ! ይምጡና ይገምገሙ!" የሚለው ቃል ከየአቅጣጫው ተስተጋባ። አርከበ እቁባይ የካድሬዎችን አስተያየት በመደገፍ ተናገረ። ይህ ዲስኩር ወደ አዲስአባ ከተዘዋወረ በኃላ የመጀመሪያው ሆኖ ተመዘገበ። አባይ ጥያቄው የሁሉም መሆኑን በመመልከቱ ለመወሰን ተቸገረ። ርግጥ አርከበ ሀሳቡን አጠንክሮ የገፉበት ምክንያት ገብቶታል።

በከተማው ስውር መንግስት ውስጥ የአባይ እጅ ነበረበት። ከራሱ በላይ ሲወዳት በነበረችው የቀድሞ ሚስቱ አማካኝነት። ደግነቱ ለትምህርት ውጭ ሀገር ልኳታል። የተቀረው ፍስሀ መአሲ ነው። እሱ ደግሞ ከአርከበ ጋር መስራት አልቸልም ብሎ ከምደባ ውጭ ሆኗል። በግምገማውም ተገኝቷል። አዲስአባ እየኖረ ያልተገኘው የስውር መንግስቱ የበላይ ካድሬ ተስፉማርያም ብቻ ነው። ተስፉማሪያም ከህውሐት መሰንጠቅ በኃላ የአልጋ ቁራኛ ሆኗል። እንዲመጣ የተወሰነበት በዚሁ ሁኔታ ላይ እንዳለ ነበር። ፍስሀ መአሲ ሊያመጣው ሄደ። እስከዛ የሻይ እረፍት ሆነ።

ከረፍት እንደተመለሰን ተስፉማሪያም በፍስሀ ተደግፎ ወደ አዳራሽ ገባ። ብዙ ሰው ደነገጠ። ከፊቴ ተቀምጣ የነበረችዉ ታጋይ ፀሀይቱ ባህታ እጆቿን ወደ ጭንቅላቷ ልካ ጮኸች። የአዲሳባ ሚሊሻ ጽ/ቤት ጠርናፊ እንድትሆን

ከመቀሌ ያዘዋወራት እሱ ነበር። ከኋላዋ ያሰለፈቻቸው የየወረዳዉ ሚሊሻ ሀላፊዎች እሷን ተከትለው አለቀሱ። ሀላፊዎቹ ዲሞብላይዝድ ተጋዳሊቶች ናቸው። የእሱ ቀኝ እጆች ነበሩ። በስውር መንግስቱ ውስጥ የወረዳ ሊቀመናብርትን ትእዛዝ የሚሰጡት እነሱ ነበሩ። አዲሳአባ በ28 ወረዳዎች ተዋቅራ የነበረች ሲሆን በ25 ወረዳዎች ሚሊሻ ሀላፊ የነበሩት እነዚህ የህውሀት ዲሞብላይዝድ (ዲሞራላይዝድ) ተጋዳሊቶች ነበሩ። እነዚህ ተጋዳሊቶች "ከደደቢት በረሀ ወደ ጦላይ በረሀ" በመሄድ ግማሽ እድሜያቸውን አሳልፈዋል። በመጨረሻም ባለቤት ለሌላት ከተማ ቁልፍ ካድሬ እንዲሆኑ በየወረዳው ተመደቡ። የህብረተሰቡን የአኗኗር ዘይቤ በአግባቡ ሳያጣጥሙ ነዋሪውን አቅጣጫ ሊያሲዙ መጡ። እድሜ ለተስፉማርያም።

ተስፉማርያም በቁሙ አልቋል። የጉንጮቹ አጥንቶች ቆዳውን በስተው ሊወጡ ይታገላሉ። ፀጉሩ ተኗል፣ ሲጉረጠረጡ የሚያስፈሩት አይኖቹ ተደብቀዋል፣ እጆቹ ከመሰለላቸው የተነሳ ከዘራው ከብዷቸዋል ፣ የምግብ ጉዳት እንዳጋጠመው ሰውነቱ ይመስክራል። አፈር አፈር ይሸታል። መልአከ ሞት ቀርቦታል!

አዳራሹ በሀዘን ተዋጠ።

አባይ ቤቱን አረጋግቶ ወደ ስብሰባዉ ተመለሰ። ግምገማው ካዛንችስ በሚገኘው የአዲሳባ ኢህአዴግ ቢሮ አመራር ላይ ተጀመረ። አሳዛኝ ታሪኮች ተደመጡ። በሀያ አንደኛው ክ/ዘመን ተፈፅመዋል ብሎ ለማመን የሚያስቸግሩ እውነቶች ተዘከዘኩ። ብዙዎቹን የምናውቃቸው ቢሆኑም "ከፈረሰ አፍ" መስማቱ ሌላ ትእይንት ነበር። በባህታዊ የሚመራው ሁሉን አድራጊና ፈጣሪው -የካዛንችሱ መንግስት፣... የስርአቱ መጨቆኛ ቦታ - ዶንቦስኮ፣ ... ኢህአዴግን ከመዲናይቱ ያባረረው - ምርጫ 92፣ የዘባተሎው ፕሬዝዳንትና ካቢኔው ገድሎች፣ ህገ መንግስቱን በጠረባ የመታው አዋጅ...

በመሆኑም ይህ የግምገማ ሂደትና ውጤት በመዲናይቱ ላይ የነበረውን ሁኔታ ግልጥልጥ አድርጐ ስለሚያሳይ ወደዚህ ክፍል እንሸጋገር።

***

ክፍል ሁለት: የጨፈ፡ው ግምገማ

ምእራፍ አራት

ባህታዊ የመራው የካዛንችስ መንግስት!

"የኢህአዴግ አመራሮች እጅግ ወሳኝ ጥንካሬያቸው ለህዝብ የተለየ ፍቅር፣ አክብሮትና የፀና ወገናዊነት የነበራቸውና ያላቸው መሆኑ ነው።"
በረከት ስምኦን (የሁለት ምርጫዎች ወግ)

ራሷን የተወችው ካዛንችስ የከተማውን ኢህአዴግ ጽ/ቤት ተሸከማለች። ካዛንችስ ከፒያሳው ማዘጋጃ ቤት በላይ ግዙፍ ውሳኔዎች ታሳልፉለች። ፒያሳ ሲጨልም ካዛንችስ ይነጋል። ሰራዎጅን በምሽት ትጀምራለች።

ካዛንችስ የማትሰራው የለም፣...ለመዲናይቱ ፕሬዝዳንት (ከንቲባ) ትመድባለች። ከንቲባውን ተከታ የካቢኔ አባላት ታዘጋጃለች። ፍርድ ቤት ሆና ብይን ትሰጣለች፣ ትገመድላለች። የቀረባትን ታስደስታለች፣ የራቃትን ታስለቅሳለች።

በእሷ ለሚታመኑት ሁሉ ጋሻና መከታ ትሆናቸዋለች!

ውስጥ አዋቂዎች ጉዳያቸው ፒያሳ ከተጓተተ አቆራርጠው እሷ ጋር ይመጣሉ። ለወራት የተንከራተቱበት በአንድ ቀን ያልቃል። በቀጭኑ ሽቦ ወደ ፒያሳና እንግልት ወደ ፈጠረው ተቋም መደወል ብቻ በቂ ይሆናል። ይህን ተከትሎ ለቅሬታ አቅራቢዎቹ፣

"የማዘጋጃ ቤትን አቀበት አትውጡ፣ አትውረዱ" በመባል ውሳኔው እቤት ድረስ ይላክላቸዋል። ሰዎቹም ወደ ካዛንችስ ያደረሳቸውን ካድሬ ያመሰግናሉ።

ግና! ወደ ካዛንችስ መንግስት መግቢያው መንገድ ጠባብ ነበር...
እንደ ገነት።

ማንም እንዳፈተተው መምጣት አይችልም። በቀጠሮም የማይታሰብ ነው። በር የሌላት ካዛንችስ በውስጧ ለያዘችው ስውር መንግስት ቀን ከሌት ዘብ ታቆማለች። መንግስቱን ለመጠበቅ ያቆመቻቸው ዋርድያዎች የሰው ባህሪ የሌላቸው አውሬዎች ናቸው። በየሰአቱ "ተሻግረህ ሂድ" የሚል ወፍራም ትእዛዝ

ያስተላልፉል። ትእዛዙን ያላከበረ የማርያም ጠላት ይሆናል። የታክሲ ሹፌር በሩ ላይ አቁሞ ካወረደ በቆመጥ ይደበደባል። "ማቆም አይቻልም የሚል ምልክት የለም" ብሎ ከተከራከረ አለቀለት፡- መንጃ ፍቃዱን ይቀማል፣ መቀመጫው እስኪተላ ይገረፉል... የቆመጥ ጡጫ ይዘንበበታል... ትንሽ ያጉረመረመና የመብት ጥያቄ ያነሳ ደግሞ በጠመንጃ ሰደፍ አናቱ ይቦረቀሳል...ጀርባው ይጠናል። ከእለታት በአንዱ ቀን የሆነው ግን ከህሊናዬ አይጠፉም ።

አንዲህ ነበር የሆነው፣

ስውር መንግስቱ ፅ/ቤት እየተካሔደ ያለው ስብሰባ ተራዘመ። እኩለ ለሊት ተጋመሰ። ሰለቸኝ...ንፉስ ለመውሰድ ወደ ጓሮ ሄድኩኝ። በጀርባ ያለውን መፀዳጃ ቤት ከፍቼ ስገባ ያየሁት ነገር አስደነገጠኝ። አንድ ሰው ራቁቱን ተንበርከክል። ሁለት እጆቹ ወደ ኃላ የፊጥኝ ታስረዋል። ጭንቅላቱ ተዘቅዝቆ በመፀዳጃ ቤቱ አፍ ውስጥ ተደፍቋል ። አንደኛው ዋርድያ በጐማ ውሀ ያፈስበታል። ሌላኛው ወገቡን በቆመጥ ይተለትላል። ከደፈቁት ቀና ሲያደርጉት አፉ ውስጥ ጨርቅ ተጠቅጥቋል። ውስጤን ተናነቀኝ። ምን አድርጉ እንደሆነ ጠየኳቸው።

አንደኛው ዋርድያ፣ " ሁል ጊዜ ሲሰክር አህአድግ ሌባ፣ መለስ ዘረኛ እያለ ይጮህል " አለኝ። ተበሳጭቼ "መብቱ ነው! ልቀቀው" አልኩት። አንደኛው ፊቱን ወደ እኔ አዞረ። ሲበላኝ ደረሰ። ተጨቃጨቅን። ከእነሱ ጋር ተነጋግሮ መተማመን እንደማይቻል ስገነዘብ ወደ ውስጥ ገብቼ ለፍስሀ መአሲ ነገርኩት። ተቆጥቷቸው ሰዉየውን ይቅርታ ጠይቆት አሰናበተው።

***

የካዛንችሱ መንግስት በሶስት የህውሐት ካድሬዎች ይመራ ነበር። ተሰፉ ማርያም፣ ሞንጆሪኖ፣ እና ፍስሀ መአሲ። በአጃቢነት ደሳለኝ ሸሹ፣ሊሻንና ዮሀንስ የሚባሉ የብአዴን ካድሬዎች ተመድበዋል። ተሰፉማርያም የበላይ ሹም ነበር። ህዝቡ ሳይሆን እነ ተወልደና ስዬ የቀቡት።ነዋሪው የት አውቆት? የት አይቶት ?

ተሰፉማርያም የቀደምት ህውሐት ታጋይ ነበር። ቡበረት ትግሉ ወቅት በፓለቲካ ዘርፍ ተመድቦ ህዝብ አደራጅቷል። ከደርግ ውድቀት በኋላ አዲስአባ ተሰጠችው። እንደ ግል ንብረቱ ቆጠራት። ለከተማዋ ካድሬ ይመድባል፣ ያባርራል።ሰው ያሳስራል፣ ያስፈታል። መሬት ይሰጣል፣ ይቀማል። ግብር ይጨምራል፣ ምህረት ያደርጋል። ለከተማዋ በጀት ይደለድላል፣ ይቀንሳል። መስኪድና ቤተ ክርስትያን እንዲሰራ ይፈቅዳል ፣ያስፈርሳል። ታዲያ ይህን ሁሉ የሚያደርገው በስውር ነበር። ከከተማ ካድሬዎች በአካል የምናውቀው ጥቂቶች ነበርን።ብዙሀኑ አይቶት አያውቅም። በስሙ ብቻ ይርድለታል።

በድሮ ጊዜ "ንጉሱ ምን አሉ?" ተብሎ እንደሚጠየቀው ሁሉ፣ እኛም የተስፉማርያምን ትዕዛዝ ለመስማት እናነፈንፉለን። ትዕዛዙ የንጉስ ነበር ። በተባለው ቀን የሚፈፀም።

የመዲናይቱ ካድሬዎች ተስፉማርያምን "ባህታዊው" ብለን እንጠራዋለን።በትክክልም የከተማ ያውም የመሀል ካዛንችስ መነኩሴ ነበር። በሶስት አመት ውስጥ፡ ሁለት ጫማ፣ ሱሪ፣ ጃኬትና ሸሚዝ ብቻ የነበረው። ጫማውን ሳይቀያይር አንዱን ሳምንት አንድ ልብስ ሌላ ሳምንት የተቀረውን ይለብሳል።

ከእለታት በአንዱ ቀን ጫማ ለውጦ "ባህታዊዉ ጫማ ቀየረ!" ተብሎ ለወራት የወሬ ማሟሻ ተደረገ። ይህ በሁለት ልብስ ላይ ተጣብቆ መቅረቱ በአብዮታዊነት አስቆጠረው። "ተስፉማሪያም እኮ እውነተኛ ታጋይ ነዉ! ያለ አንድ ጫማና ልብስ የለውም" ተብሎ ዝናው ከአንጦጦ እስከ ቂልንጦ ተራራ ተነገረ። ከአንፎ እስከ ለገጣፎ ሚዳ ተዘመረ። በዞንና ወረዳዎች እሱን መምሰል የሚፈልጉ ተከታዮች አፈራ። የሚዘንጥና እራሱን የሚጠብቅ እንደ ቢሮክራት ተቆጠረ። ስራ የማይችል። አንዳንዶች ሰውነታቸውን ሲያኩ እንኳን የእሱ ግልባጭ ሆኑ። ተስፉማርያም የማያቋርጥ ፎካች ነበር... አንድ እጁ ብእር ጨብጦ ሌላኛው ከብብቱና ጭኖቹ ስር የማይጠፉ።

ተስፉማርያም ምግብም ላይ ተመሳሳይ ባህሪ ነበረው። የእለት ቀለቡ እንጀራ በሽሮ ወጥ ነበር። ምግብ የሚያዘጋጅለት፣ ልብሱን የሚያጥብለትና ፀጉሩን የሚከረክመው ደሱ በርጋጋ የሚባል ሎግላጋ ጭሎ ነበረው።ደሱ ጐበዝ ነበር። ሳይታክት ሽሮ ያንደከድካል። ለውጥ ካስፈለገ ደግሞ ቲማቲም በቃሪያ ይከትፋል። ይህን ሁሉ የሚያደርገው ካዛንችስ በሚገኘው ጽ/ቤት ነበር። ምድር ላይ በምትገኘው ትንሿ አዳራሽ። ተስፉማሪያም ለመኖሪያ እንዲሆነው ትልቅ ቪላ ቢሰጠውም በብዛት አይኖርበትም። ቢሮው አልጋ ዘርግቶ ይተኛል።

ባህታዊዉ አራት ኪሎ እነ ተወልደ ወልደማርያም ጋር በመሄድ የስራ መመሪያ ይቀበላል። ከዛ ውጭ ከካዛንችስ አይወጣም። እሱና ተወልደ በብዙ ነገር ይመሳሰላሉ። የጋራ ባህሪያት አላቸው። ላባቸው አንድ የሆነ ወፎች...! አመራር ባህሪያቸው ተመሳሳይ ነበር። በእነሱ ዘመን የመንግስት ተቋማት የስራ ትዕዛዝ የሚወስዱት ከፓርቲው ጽ/ቤት ነበር። እቅድ ኢህአዴግ ቢሮ በእነ ተወልደ ተዘጋጅቶ በመመሪያ መልኩ ለእነ መለስ ይወርዳል። የእዝ ሰንሰለቱ ከድርጅት ወደ መንግስት ይፈሳል።

በዚህ መሰረት ተወልደ መለስን፣ ስለሞን ጢሞ ኩማ ደመቅሳን፣ቢተው በላይ አባተ ኪሾን፣ ተስፈማሪያም ደግሞ አሊ አብዶን የስራ ስምሪት ይሰጣሉ። አቶ መለስም ሆነ ሌሎች ካድሬዎች ድርጅቱ ካስቀመጠው ውጭ ዝንፍ አይሉም። ለሀገሬውና መዲናይቱ ህዝብ መግለጫ እንኳን ሲሰጡ የተቀመጠውን አቅጣጫ አይለቁም። ድርጅቱን የሚመሩት ለጋዜጠኛው ጥያቄ አውጥተው ይሰጡታል፣ ከአቶ መለስ ጋር ደግሞ በጋራ አቅጣጫ ያስቀምጣሉ። በድምጽ ብልጫ ከተወሰነው ውጪ አላመንኩበትም የሚባል ነገር አይሰራም። የተጻፈውን የራስ አድርጐ ከማኩበነበ ውጭ!... ከራሱ አንደበት እንደሰማነው በመጨረሻው ወቅት አቶ መለስ ወደ ህዝብ ግንኙነት ሰራተኛ ተንሸራቶ ነበር። እነ አለምሰገድ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ሄደው ሚስቱን ሲያባርሩ እንኳን ትነፍሽ አላለም። ያላመነበትን የኢትዮ ኤርትራ ጦርነት እንደ ራሱ አድርጐ የኢትዮጵያን ህዝብ ዋሽቷል።

ሁኔታዎች እየከፉ ሲሄዱ አቶ መለስ ከተሰጠው ወጣ እያለ አስቸግሮ ነበር። እነ ተወልደ እየጠሩ ቢቆጡትም አልመለስ አለ። ይህም ልዩነቱን እያሰፋው ሄደ። በተለይ ከስዬ ጋር በወረደ መልኩ መዘነጣጠል ተጀመረ። አንዱ ሌላኛውን ስም ለማጥፋት ተንቀሳቀሱ።

ስዬ አብርሀ የኢህአዴግ ቢሮ የሚሰሩ የህውሐት ምድብተኛ ካድሬዎችን በመሰብሰብ፣

"ጥጃው አስቸግሯል፣ ሻዕቢያ እንዳይደመሰስ እንቅፋት ሆኗል" ብሎ ተናገረ። ስዬ አቶ መለስ ላይ ያለውን ንቀት ለማሳየት "ጥጃው" እያለ ይጠራው ነበር።

ለሰበሰባቸው ካድሬዎች የአቶ መለስን እምቢተኝነት እንዲህ ሲል ገልጾ ነበር፣

"... ሻዕቢያ የትግራይ ጣላት ነው፣ ካልተደመሰሰ በስተቀር ትግራይ ሰላም አታገኝም ። ሻዕቢያን ከዚህ ምድር ጠራርገን እንዳናጠፋ ጥጃው አንድ ጊዜ ጦርነቱን ኢኮኖሚያችን መሸከም አይችልም ፣ ሌላ ጊዜ የኤርትራን ከቀኝ ግዛትነት ነፃ መውጣት አለም ሳይቀድመን አውጀን እንዴት ድንበሯን ዘልቀን እንገባለን የሚል ተልካሻ ምክንያት እየሰጠ ነው።"

ውጤቱ ግን በተቃራኒው ሆነ።

ጥጃ ያሉትን ለምሳ ሊጠብሱት አስበው እሱ በቆረጣ ለቁርስ አደረጋቸው!... የኢትዮጵያ ታሪክም ራሱን ደገመ። ካርል ማርክስ እንዳለው "መጀመሪያ አሳዛኝ ቀጥሎ ቧልት በሚመስል መንገድ!!" የመጀመሪያዉ ታሪክ የመንግስቱ ሀይለማርያም ነው። መንግስቱ ሊገለብጡት የነበሩትን "ለምሳ ያሰቡንን ለቁርስ አደረግናቸው" ብሎ እንደወረደ ተናገረ። አቶ መለስ ደግሞ እነ

ተወልደን ሲያሰናብት በኢህአዴግ ውስጠ ድርጅት ስብሰባ "ጃኬታቸውን እያስወለቅን ሸኘናቸው!" ብሎ ተሰብሳቢውን አስደመመ። ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ ደግሞ ሁለቱን ታሪኮች ለማዋደድ ፈልገው አቶ መለስን በዛው ስብሰባ፣

"አሁንስ መንግስቱ ሀይለማርያም መሰልከኝ!" አሉ።

በዶክተሩ አስተያየት ክፉኛ ስሜታቸው የተነካው ሚኒስትር ገነት ዘውዴ ስቅስቅ ብለው አለቀሱ። ሚኒስትር ገነትም ቢሆን ታሪክ ደጋሚ ናቸው። በሚቀጥለው ክፍል የክብርት ሚኒስትሯ የልቅሶ ጅማሪ ወግ ይቀርባል።

(ስዬ አብርሀ መለስን በምን ምክንያት "ጥጃው" እያለ እንደሚጠራ ለማወቅ ጥረት አድርጌ ነበር። በዝዋይ ህፃናት አምባ ከአሁኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ሐይለማርያም ጋር በነበረን ቆይታ የመለስን ስሜታዊ መሆንና፣ አለመስከን ለማሳየት እንደሆነ ገለፀልኝ። ጥጃው ብቻ ሳይሆን "ወዲ አለማሽ" እያለ በእናቱ ስም ሲጠራው እንደነበር ጨምሮ ነገረን። የዛኑ እለት የሐይለማርያም ንግግር ማጠቃለያ "ስዬ ባለጌ ነው!" የሚል ነበር።)

በአዲሳባ የተሰፉማርያምና አሊ አብዶ ግንኙነት ከእነመለስና ተወልደ በከፉ ሁኔታ የጌታና ሎሌ ስርአት የነገሰበት ነበር። የአሊ የእለት እንቅስቃሴ ከካዛንችስ በሪሞት ኮንትሮል ክትትል ይደረጋል። ካቢኔው ተሰፉማሪያም የወሰነውን መንግስታዊ ሰነድ አድርጎ ያፀድቃል። አቶ አሊ በአስተዳደሩ ምክር ቤት የሰጠው ምላሽ ተሰፉማርያም ቢሮው በዴክ ይከታተላል። እሱ ካለው ዘነፍ ካለ ይቆጣዋል።

በነገራችን ላይ በጨፈ ግምግማ ወቅት አብዮታዊ ሆኖ መታየት የፈለገው የመስተዳድሩ ምክትል ፕሬዝዳንት ካሊድ አብድርሀማን ለአሊ ሂስ ሲያቀርብ፣ "ተሰፉማርያምን ትፈራዋለህ። ትሰግድለታለህ" አለ።

አሊ በበኩሉ፣

"አንተም ሆንክ እኔ እንዴት አንፈራው! እንዴት አንሰግድለት፣ የሰጠን የመዲናይቱ ቁልፍ አርቴፍሻሉን ነው" በማለት ካሊድን ጨምሮ መልስ ሰጥቷል።

ተሰፉማርያም ሲወሳ የማይቀር ትዝታ አለው። በየሳምንቱ ይዘንለት የምንሄደው ሪፓርት። የመዲናይቱ ካድሬዎች ለስራው ከምናጠፉው ጊዜ በላይ ለምንጽፈው እንጨነቃለን። እሱም የአንድን ሪፓርት ጥራትና ደረጃ የሚለካው በክብደቱና ወረቀት ብዛቱ ነበር። ሪፓርቱን በእጁ መዳፍ ላይ አስቀምጦ እንደሚዛን ይለካል። በዛ ብሎ የእጁን መዳፍ ገድገድ፣ ገድገድ ካደረገው የረፓርቱ ባለቤት ስራውን በአግባቡ ሰርቷል። ምስጋና ይቸረዋል። የገጽ ቁጥር ካነሰና ቀትረ ቀላል ከሆነ ሪፓርቱን ያመጣው ካድሬ እንደ ውሻ ተሰድቦ አዲስ

ሰርተህ ና ይባላል። የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል።

የህውሀት መሰንጠቅ የተስፉማርያምን አገዛዝ እንዲያከትም አደረገው። ትልቁ ዛፍ ወደቀ። ምሳርም በዛበት። በስሙ ብቻ ሲርድ የነበረው ካድሬ የከተማዋን ችግሮች በሙሉ በእሱ ላይ ደፈደፈ። በተለይ ካሊድ አብድርህማን ላይ የቀረበው አስገራሚ ነበር። ወይዘሮ ጥጉ የምትባል የአዲሳባ ሴቶች ማህበር ፕሬዝዳንት ካሊድን እንዲህ በማለት አፉጠጠችው፣

"ትሰክራለህ፣ ትማግጣለህ... መቀሌ ለስብሰባ ይዘሀቸው ከሔድካቸው የማህበሬ አባላት ከአንዷ ጋር ተኝተህ ወሮታውን ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ በማስገባት መልሰሀል።" አለችው።

ካሊድ የቀረበለትን ሂስ ዉጦ የችግሩ ምንጭ ተስፉማርያም የፈጠረበትን ጭንቀት ለመቀነስ እንዳደረገው ተናገረ።

ባህታዊው ለወሲብ ሴሰኝነት ተጠያቂ ሆነ...

ቀን ሲገለበጥ ውሀ ወደ ላይ ይፈሳል እንዲሉ።

***

ተስፉማርያምን ለመጨረሻ ጊዜ ያየሁት ከጨፌው ግምገማ ማግሽ አመት በኋላ ከፍስሀ መአሲ ጋር ልንጠይቀው ሄደን ነበር። ፍስሀ የተጣለ ሰዉ አይረሳም። ከድሬደዋ ለስብሰባ መጥቶ ነበር ወደ ባህታዊው ቤት የሄድነው። የተንጣለለው ቪላ ቤት ክፍሎቹ በሙሉ ባዶ ናቸው። በሳሎኑ ትልቅ ጠረጴዛና አራት ወንበር ተቀምጧል። በመኝታ ቤቱ ከአልጋው ውጭ ቴሌቪዥን አለ። ቤቱ ሊባላ ደርሷል።ብዙ ሰአቱን ከአልጋው አይወርድም። እኔን አላወቀኝም። ከፍስሀ ጋር የበረሀ ትዝታዎች ተጫወቱ። ከዛ መልስ ያለውን ረስቶታል፣ አሊያም ማስታወስ አይፈልግም። ተከለ ቁመናው ጨፈ ካየሁት ብዙም አልተለወጠም። እንደተዳከመ ነው። እጆቹ አግጠው ያልደረቀ አፅም መሰለዋል። በአካል ካወኩት ጀምሮ ቤቱ እስካገኘሁት ድረስ አብራው የኖረችውን አንዲት አመል አልተዋትም። መሀል አናቱን በሌባ ጣቱ መፈተግ ፣... በዝቶባት ነው መሰል ለብቻዋ ጥቁር ብላለች።

ሲያልቅ አያምር!!

ምእራፍ አምስት

ዶንቦስኮና ሞንጆሪኖ!

"የኢህአዴግ አመራርና ታጋዮች በህዝብ ላይ የሚፈፀም ግፍና በደል አምርረው ይጠላሉ። የሚጠሉትን ግፍና በደል በፅናት ይታገላሉ።"

በረከት ስምኦን (ሁለት ምርጫዎች ወግ)

ሞንጆሪኖ አታረጅም...

ሁልጊዜም ወጣት ናት። ማንም አይቷት አስቸጋሪውን የዱርና ቆንጥር ዘመናት አሳልፋለች ብሎ ማመን አይቻለውም። ተራራን ያንቀጠቀጠች ፣ቋጥኝ የደረመሰች አትመስልም። የእጆቿ ልስላሴ ከብዙዎቹ ተጋዳሊቶች የተለየ ነው። ቃታ ሲስብ መኖሩን ረስቶታል። ሞንጆሪኖ ከአለቃዋ በተቃራኒ ዘናጭ ናት። አዲስ የወጡ የአውሮፓ ፉሽኖች አያመልጧትም። የአይን መነፅሮቿ ሳይቀር በትእዛዝ የሚሰሩ ናቸው።

የሞንጆሪኖን የበረሀ ውጣ ውረድ ማሳበቁን ማቆም ያልቻሉት የአግሮቿ ጡንቻና ተረከዟ ብቻ ናቸው። ይህ ደግሞ በብዙሀኑ ነባር ተጋዳሊቶች የሚታይ ነው። ደንዳና ጡንቻና የተሰነጣጠቀ ተረከዝ። አንዳንዶች የትግል ዘመን ለማወቅ የስንጥቁን ብዛት መቁጠር በቂ ይሆናል የሚሉ አሉ።

ሞንጆሪኖ ከተስፋማሪያም ቀጥላ ወደ አዲሳባ ኢህአዴግ ቢሮ በመዘዋወር የካዛንችሱን መንግስት ተቀላቅላለች። የፕሮፐጋንዳ ዘርፉን እንድትመራ ተሰጣት። ከማዘጋጃ ቤት ማሚት የምትባል የትግል ጓዷ ተጨመረችላት። ማሚትና ሞንጆሪኖ የአዲሳአባን ፕሮፐጋንዳ በህውሀት የበረሀ ቅኝት አተራመሱት።

በተለይም ዶንቦስኮ እየተባለ የሚጠራውን የካድሬ ማሰልጠኛ በበላይነት ተቆጣጠሩ። በላፍቶ ሳር ቤት አካባቢ በጫካና ወንዝ የተከበበው ዶንቦስኮ የስርአቱ ዋነኛ መጨቆኛ ቦታ ነበር። በመዲናይቱ ካድሬ ሆኖ ለመመደብና የመንግስት ስልጣን ላይ ለመቆየት በየጊዜው ዶንቦስኮ እየተገባ መሰልጠንና መገምገም ግዴታ ነበር። ለመጀመሪያ ዙር ለሁለት ወራት በአዳሪነት መሰልጠን የማይታለፍ ነው።

በቋሚ አሰልጣኝነት ለካዛንችሱ መንግስት ታማኝ የሆኑ ካህሳይ የሚባሉ ሞክሼዎች ተመድበዋል። ሁለቱም ነባር የህውሀት ታጋዮች ናቸው። የተመረጡትም በፕሮፌሽናል ጠርናፊነት ብቃታቸው ነበር። እነ ካህሳይ የሰው ጨጓራ ገልብጠው የማየት ስልጣን ነበራቸው።

የዶንቦስኮ ካሪኩለም የሚዘጋጀው በካዛንችስ ሲሆን ትኩረቱ በአብዮታዊ ዲሞክራሲ መርሆዎች ላይ ነበር። መስቀለኛ መንገድ ላይ ቆማ የነበረችውን ኢትዮጵያ ኢህአዴግ እንዴት እንደታደጋት ፣የበሐርና መሬት ጥያቄ፣ ዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት፣ ጠባብና ትምክህተኝነት ዋነኛ አጀንዳዎች ናቸው። ይህም ሆኖ የዶንቦስኮ በጀቱ የሚመደበው ከመንግስት ነበር። ለፓርቲ ስራ ከመንግስት ካዝና።

በየካሪኩለሙ ማጠቃለያ ላይ ሰልጣኞች የአቋም መግለጫ ያወጣሉ ። እንዲህ በማለት፣

"አንቀፅ 39 የአንድነታችን መሰረት ነው!"፣

"የመሬትና ብሔር ጥያቄ ተነጣጥለው አይታዩም!"፣

"ማእከላዊነት የዲሞክራሲያችን መገለጫ ነው!"፣

"እንደ አነግና መአድ ያሉ ድርጅቶች የጥበትና ትምክህት አቀንቃኞች ናቸው!"...

አዳር ስልጠናው ሊጠናቀቅ ሁለት ሳምንት ሲቀረው ግለሰባዊ ግምገማ ይጀመራል።... በዚህን ወቅት ሞንጆሪኖ ከኢህአዴግ ቢሮ፣ የበረሀ ጓደኛዋ ማሚት ከማዘጋጃ ቤት ይመደባሉ።

ማሚት በማዘጋጃ ቤት ሶስተኛ ሰው ስትሆን ዋና ስራዋ አሊ አብዶን መቆጣጠር ነበር። በአሊ ፊርማ የሚወጡ ደብዳቤዎች፣ ያናገራቸውን ባለጉዳዮች፣ ያደረጋቸውን የስልክ ልውውጦች በመጥለፍ ለባህታዊው ተስፋማርያም ታስተላልፉለች።

ዶንቦስኮ በታቀደ መልኩ የከተማውን ካድሬዎች ወኔ ለመስለብ የተዘጋጀ መጨቆኛ ተቋም ነበር። ካድሬዎችን አስቀድሞ በማደንዘዝ ምንም ጥያቄ እንዳያነሱ፣ የህዝቡን ብሶት ተጋርተው እንዳያስተጋቡት ከወዲሁ እንደ አባብ አናታቸውን ለመቀጥቀጥ በማሰብ የተዘጋጀ። የከተማው ካድሬዎችና የመንግስት ባለስልጣናት በፍርሀትና ስጋት እንዲሞሉ ለማድረግ፣ ፀጥ ለጥ ብለው እንዲገዙ፣ አቅመ ቢስ እንዲሆኑና የራሳቸውን ጥላ ሳይቀር እንዲጠራጠሩ ለማድረግ የተቋቋመ ተቋም። ይህን ለማስፈጸም ቅድመ ዝግጅቱ

አስቀድሞ ይጀመራል።

ሰልጣኖች ተቋመ· ከመግባታቸው· በፊት የጀርባ ታሪካቸው· ይጠናል። ይህን ጥናት የሚሰሩት የወረዳ የካድሬ አለቆች፣ የሚሊሻ ጽ/ቤት ሀላፊዎችና የሀገር ውስጥ ደህንነቶች በመቀናጀት ነበር።እጩ ሰልጣኙ ተወልዶ ያደገበት፣ የት/ቤት ደረጃውና የሰራበት ቦታዎች፣ የፓለቲካ ተሳትፎው፣ የቤተሰቦቹና ጓደኞቹ የኋላ ታሪክ፣ የሚያዘወትርበት መጠጥ ቤት፣ ዝመ·ተኝነቱ በዶሴ ይዘጋጃል· ...ለእነ ማሚትና ካህሳይ እንዲደርስ ይደረጋል።

ምርቃቱ ሁለት ሳምንት ሲቀረዉ ግምገማ ይጀመራል። ሰልጣኙ አስቀድሞ ኑዛዜውን እንዲያቀርብ እድል ይሰጠዋል። ቅንጥብጣቢ ያቀርባል። በደንብ እንዲናዘዝ እነ ማሚት ያስፈራራሉ። ከደበቃት ትንሽ ይጨምራል። አሁንም በደንብ እንዲያወጣ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል። የለኝም ይላል። እነ ማሚት አስቀድሞ የተዘጋጀውን ዶሴ በመገላለጥ አውጫጭኙን ይጀምራሉ።

ለሁሉም ሰልጣኞች ዋነኛ አውጫጭኝ ጥያቄ "የትግራይ/ህውሀት የበላይነት አለ ብለህ ታምናለህ ወይ?" የሚለው ነበር። ይህ ወሳኝ ጥያቄ ካድሬውን የስንግ በመያዝ መላወሻ እንዲያጣ የሚያደርግ ነበር። ተገምጋሚው የትግራይ የበላይነት አለ ብሎ እንደሚያምን ከገለፀ የፈለገ ንፁህ ቢሆን መጨረሻ ላይ ሻንጣውን ይሸክፉል። የበላይነት የለም ብሎ ከተናገረ ደግሞ፣ "የህብረተሰቡ ገቹ አስተሳሰብ በሆነበት ሁኔታ እንዴት የተለየ አቋም ሊኖርህ ቻለ? እየዋሸህ ነው? አድርባይ ነህ!!" ተብሎ ከግራ ከቀኝ እሳት ይወረወርበታል። ከዚህ ቁልፍ ጥያቄ ቀጥሎ ያሉትም ቢሆኑ ሰልጣኙን አጣብቂኝ የሚከቱ ነበሩ... አንቀፅ 39 የአንድነታችን መሰረት ነወይ? ወደ ኃላ ለቀሩ እና በጦርነት ለተጐዱ ክልሎች ልዩ ድጋፍ መደረጉን ትቃወማለህ ወይ? ቁልፍ ችግርህ ትምክህት ወይስ ጥበት?

እንደ እውነቱ ከሆነ ዶንቦስኮ ፃታና ዘር ሳይለይ ጨርቅ አሰጥሏል። በስልጠና ላይ እያለ ከተኛበት ዶርም በለሊት ልብሶቹን አውልቆ ወንዝ ሊገባ ሲል የተያዘ ባለስልጣን ነበረ። የምን ማስተርስ በማለት ፈረንጅ ሀገር ያገኘዉን ዲግሪ የቀዳደደም እንዲሁ።

ዶንቦስኮ ለዘመናት ተደብቀው· የነበሩ ወንጀሎችን እንዲወጣ አድርጓል። በደርግ መዋቅር ውስጥ ሆኖ አንድ ወጣት ተኩሶ የገደለ ለሊት ባሰማው ቅዠት ምክንያት እውነቱን እንዲያወጣ ተወጥሮ በመያዙ ድርጊቱን የፈፀመበት ቦታ ሂዶ አሳይቷል። ከፍለ ሀገር በሚሰራ ሰአት ሚስት አግብቶ ሁለት ልጅ ወልዶ በመጥፉት አዲሳባ ሌላ ትዳር መስርቶ የሚኖር ካድሬ

ተጋልጧል። ዶንቦስኮ ብዙ ቤቶች አፍርሷል። አራት ልጆች የወለዱ ባለትዳሮች ከዶንቦስኮ ግምገማ በኃላ ወረቀታቸው በፍርድ ቤት ቀደዋል። በግፍ ስማቸው የጠፉት በርካታ ናቸው።

የኮልፌ ወረዳ አስተዳደር የነበረችው ቆንጅየዋ ንግስቲ፣ "ሌላ የተደበቀ አመል ቢኖርብሽ እንጂ ባልሽን ፈተሽ ፣ልጆችሽን ይዘሽ ቤተሰብ ጋር አትገቢም" ተብላ አንድ ሳምንት ተገምግማለች። ዶንቦስኮ በሰላም ተመርቆ መውጣት ግመልን በመርፌ ቀዳዳ እንደሚባለው ነበር። ከምርቃቱ በኋላ እውነተኛ ስማቸው ተትቶ በወጣላቸው ቅፅል የሚታወቁ አሉ። እስቲ ስላንዳንዶቹ የጨለማው ዘመን ሰለባዎችና ተያያዥነት ያላቸው ትረካዎች እንሸጋገር።

***

በአንድ ወረዳ ላይ አስተዳደር ሆነው የሚሰሩ ሁለት የቅርብ ጓደኛሞች ነበሩ። ብዙ የጋራ ሚስጥሮች ነበሩዋቸው። ተራቸው ይደርስና አብረው ዶንቦስኮ ይገባሉ። አንደኛው በግምገማዉ ሙቀት ይግላል። ጓደኛውን ይህን አልተናዘዝክም በማለት መቆሚያ መቀመጫ ያሳጣዋል። እነ ካህሳይ ማንቁርቱ ላይ ይቆማሉ። እናም አንድ ለሊት ጓደኛሞቹ ካደሩበት ዶርም የድረሱልኝ ጩኸት ይሰማል። ካድሬው ተሯሩጦ ሲደርስ ወለሉ በደም ተጨማልቋል። ገምጋሚው የተሰነጠቀች ጆሮውን በእጁ ደግፎ ይንፈራፈራል። ተገምጋሚው የዘነጠለበት አፉ ቫንፓየር አስመስሎታል!... ከዛን ቀን በኃላ ሁለቱም የዳቦ ስም ወጣላቸው: ...ተገምጋሚው ታይሰን! ገምጋሚው ሆሊፊልድ!

***

አንድ የማዘጋጃ ቤት ሹምና በእሱ ስር ያለች ኤክስፐርት ዶንቦስኮ ይገባሉ። የሹሙ አውጫጭኝ ይደርሳል። ኤክስፐርቷ አለቃዋ በደንብ እንዳላወረደ ገልባ እሱ ላይ ያላትን ሂስ ታቀርባለች። በወጣ በገባ ቁጥር እነደሚያስቸግራት፣ በረባ ባልረባው ቢሮው እንደሚጠራት፣ የሚሰጣት ስጦታ በእሱ ደሞዝ የማይታሰብ እንደሆነ ትገልፃለች። መጀመሪያ አካባቢ እሷም እንደተቸገረችለትና ባለትዳርና የልጆች አባት በመሆኑ በድርጊቷ እንደተፀፀተች የራሷን ጨምራ ትናዘዛለች። በዚህ ምክንያት እንደተጣሉና በእሷ መደብ ላይ ሌላ ተረኛ ሴት ለመመደብ እየሞከረ እንደሆነ ትገልፃለች።

ሹሙ ይክዳል። አለመግባባት የተፈጠረው ስራዋን በአግባቡ ስላልሰራች እንደሆነ ያስረዳል። መስቀለኛ ጥያቄ ከግራ ቀኝ ተወረወረለት። አላመነም። የሶስት ቀን ማሰላሰያ ጊዜ ተሰጠው።

ቀኑ ደርሶ ቢጠየቅ ለውጥ የለም። ደንቦስኮዎች ስራ ጀመሩ።

"ከስድስት ወር በፊት አዋሳ ሄደህ ነበር? ለምን ሄድክ? ከማን ጋር?"

"ከኤክስፐርቷ ጋር፣ ለስብሰባ።" ሹመ መለሰ።

"ስብሰባውን ማን ጠራው? በምን አጀንዳ ላይ? የትኛው አዳራሽ? አንተና እሷ ገንዘብ ለመቆጠብ ነው በአንድ ሆቴል ተመሳሳይ ቤርጌ ያዛችሁት?" ጥያቄዎች ተዘረገፉ፣ የሆቴሉን ስምና የማደሪያ ቁጥሩ ሳይቀር ተነገረዉ። ሹመ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ። ያሳለፈውን የፍቅር ጊዜ ዘከዘከ። ዋሽቶ ገዜ ስላጠፉ ይቅርታ ጠየቀ። ካድሬው በተለመደ መልኩ ሹመን - ክሊንተን፣ ኤክስፐርቷን - ሞኒካ ሊአንስኪ ብሎ ሰየመ።

***

አንለይ የምትባል የአቃቂ መስተዳድር ካቢኔ አባል ነበረች። እሷን ጨምሮ የአቃቂ ካድሬዎች የግቦት 20 በአል ምክንያት በማድረግ የምግብና መጠጥ ተሀድሶ ያዘጋጃሉ። ከድርጅት ወጭ አድርገው ሁለት የበግ ጥቦት በመግዛት ጠባብሰው ይበላሉ፣ ይጨፍራሉ።

ግብጣው አልቆ ወደ ቤቷ ለመሄድ መኪና ልትገባ ስትል ጥቦቷን ያረደው የጥበቃ ጓድ ወደ እሷ መጥቶ የበግ ቆዳውን ምን ላድርገው ብሎ ይጠይቃታል። ትዝ ሲላት ጠላ ሻጭ አሮጊት ጐረቤቷ የደንበኞቻቸውን ምቾት ለመጠበቅ በቆዳ ላይ ቆዳ መደቡ ላይ ያነጥፉ። እናም ዘበኛውን ማንም ስጠኝ ቢልህ እንዳትሰጥ ትለዋለች። በሚስማር ወጥሮ እንዲያደርቅላት ታዘዋለች። ከሳምንት በኃላም ቁርበቱን ለአሮጊቷ በመስጠት ምርቃቷን ትቀበላለች።

ክብርት አስተዳዳሪዋ ዶንቦስኮ ስትገባ የአሮጊቷ ምርቃት ወደ እርግማን ተቀይሮ ጠበቃት*** ይህ ዶንቦስኮ ነው! የእነ ሞንጆሪኖ፣ ማሚትና ካህሳይ አገር!...

የአንለይ አፈርሳታ ላይ ያቺ ቁርበት እንደ ጅብ ቆዳ የሜርኩሪ ዋጋ ተሰጥቷት ብቅ አለች፣ "ከሌብነት እንዳልፀዳሽ ያመላክታል" ተባለች።

መወጠሩ ሲበዛባት፣

"መውሰድ አልነበረብኝም፣ ይህም ያልተሻገርኩት የሌብነት አመለካከት ስላለብኝ ነው" ብላ የቀረበላትን ሂስ ትሰለቅጣለች። የሰማይ ስባሪዋ አንለይ!... እንቁራሪትን ዝሆን የምታሳክለው ዶንቦስኮ በዋዛ አለቀቀቻትም፣

"አንለይ በትንሹ ስላልታመንሽ፣ ለትልቁ ህዝብ አስተዳዳሪነት እምነት ልንጥልብሽ አንችልም" ተባለች። ዶንቦስኮን ተሰናብታ ወጣች።

***

ዶንቦስኮ ለትላልቅ ባለስልጣናትም አልተመለሰችም። በተለይም የካቢኔ

አባል የነበረችው ጣይቱ አሊ (የቀድሞ ትምህረት ሚኒስትር ገነት ዘውዴ ዘመድ) አውጫጭኝ በካድሬዎች የትውስታ ግድግዳ ላይ ተጽፎ ቀርቷል። ለተተኪው ካድሬ በቅቅበሎሽ ህግ መሰረት እየተላለፈ አመተ -አለም ተሻግሯል።

የጣይቱን ግምገማ የመሩት ሁለቱ ካህሳዩች ነበሩ።

ቀዩ ካህሳይ፣ "ጣይቱ መጀመራያ የት ትሰሪ ነበር" በማለት ጠየቃት።

"ሴቶች ማህበር"

"ከዛ በኋላስ"

"የዞን ስራ አሰፈፃሚ"

ጥቁሩ ካህሳይ፣ "ማነው ወደ ዞን ያመጣሽ"

"የዞኑ ፕሮፓጋንዳ ሀላፊ፣ ..."ዴት"... እንደራረግ ነበር "እንደማፈር እያለች መልስ ሰጠች።

"ቀጥሎስ ?"

"የከተማውን ካቢኔ ተቀላቀልኩ። የብአዴን ስራ አሰፈፃሚ ከሆነውጋር የተለየ ግንኙነት ነበረን..." በድጋሚ እፍረቷ መጣ።

ቀዩ ካህሳይ፣ "የእኛ ክሊኦፓትራ! እንኳንም ስሙን አልጠቀሽ።" በእለቱ ተባረረች። ሻንጣዋን ሸክፉ ወደ ቤቷ ሔደች።

ከዛ ቀን ጀምሮ ካድሬው ከጣይቱ ጋር በተናጠል ማውራት ፈራ። አቶ አርከበ እቁባይ ወደ መዲናይቱ ተመድቦ ሲመጣ መልካም ግንኙነት ፈጠሩ። ድጋሚ የማህበራት ማደራጃ ቢሮ ሀላፊ አድርጉ ሾማት። ብዙም ሳትቆይ እሷ "ተከድኖ ይብሰል" ባለችው ምክንያት አባረራት።

ከሁለት አመታት በኋላ ኢህአዴግ ቢሮ ተመድቤ በምሰራበት ወቅት አንዲት ጠዋት አለቃዬ ወደ ነበረው ህላዌ ዮሴፍ ቢሮ ሄድኩኝ። ያለወትሮው የቢሮው በር ብርግድ ብሎ ተከፍቷል። ገና ኮቴዬን ሲሰማ ጠርቶ አስቀመጠኝ። ተግባባን።

ጣይቱ እንግዳ ማረፊያ ሶፉ ላይ ተቀምጣለች። በስጦታ ወረቀት የተጠቀለለ ነገር እያሳየኝ አሜሪካን ሀገር ለእረፍት ሄዳ መምጣቷን ነገረኝ። ለጣይቱ አሜሪካን የውህ መንገድ ነው። አፍታም ሳትቆይ አርከበ እቁባይ እንዴት ደጅ እንዳስጠናትና እንዳንከራተታት በእንባ ታጅባ ዘረገፈችው። ህላዌ አፅናናት። ለጓዶች ንገሪያቸው አላት። በመሀል ስልክ መጥቶበት ማወራት ጀመረ።

እኔና እሷ ተጋጠምን... ፈራኋት...

መጥፎ ስም! የማወራው ግራ ሲገባኝ፣ "ትዳር መሰረትሽ እንዴ ተስማምቶሻል" አልኳት። በአዘነ ስሜት ውስጥ ሆና፣

"ባገባማ ማንም የሚስቱ ጭን ሙቀት ሲበርድበት አዮኑን ለማስተንፈስ አያንከራትተኝም" አለች።

"ታዲያ ለምን አታገቢም?"

"እድሜ ለዶንቦስኮ ስሜ ከአዲሳባ እስከ አሜሪካ ጠፉ! የማጠልሸት ዘመቻ ተከፈተብኝ። ስንቱ በአደባባይ የሚሰራው ጉድ እያለ የሰው ይፈተፍታል" አለች።

እውነቷን ነበር።

ከጥቂት ቀን በኋላ በየትኛው መንገድ እንዳለፈች ባላውቅም የአዲሳባ ኢህአዴግ ሴቶች ሊግ የመስራቾች ፕሬዝዳንት ሆና ከእኛ ጋር ተቀላቀለች: ...

"I am a single lady!" የእሷ ጓደኛና የስራ ባልደረባችን ገጣሚ ፍሬሀይወት አያሌው በፃፈችው ግጥም እንደገለፀችው።

***

ይህ ደግሞ በአቶ አሊ አብዶ ካቢኔ ውስጥ የነበረ ካድሬ ግምገማ ነው። ካድሬው ለሌላውም ማስተማሪያ ይሆናል በማለት ባለቤቱን በኤድስ ማጣቱንና እሱም ከቫይረሱ ጋር እንደሚኖር ሳይደብቅ ይናገራል። ወቅቱ ደግሞ በቫይረሱ የተያዙ ሰዎች ላይ ከፍተኛ መገለል የሚፈፀምበት ስለነበር የካቢኔ አባሉ ይህን በይፋ በመናገሩ ሁሉም ተገርሟል። ርግጥ ከባለቤቱ መሞትና የሰውየው ቁመና በየቀኑ እየተዳከመ መሄዱን ብዙሀኑ ስለተመለከተ ያልተነገረ ሀሜት ሆኖ ሰንብቷል።

ቀዩ ካህሳይ እንዲህ በማለት ጥርነፋውን ጀመረ፣

"ስማ አስኪ! ስንት ሴቶች በከለሀል? በአንተ ምክንያት የስንት ሰዎች ቤት ፈርሷል? በእጃችን ያለው መረጃ እንደሚያመላክተው ያየሁት አይለፈኝ እንደነበርክ ነው። በተሰይ ወደ ስልጣን ከመጣህ በኃላ ብሶብህ ነበር።" ካድሬው ምላሽ ሳይሰጥ አንገቱን አቀርቅሮ ቀረ።

ማሚት ቀዩ ካህሳይን ተቆጣቸው። ራሱን በማጋለጡ ሊበረታታ እንደሚገባ አሳወቀች። ወደ ካድሬው እየተመለከተች፣

"ቁልፍ ችግሩ የእሱንና ቤተሰቡን ህይወት በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ቅኝት መምራት አለመቻሉ ነው። ቀድመን ብናገኘው ኖሮ እንታደገው ነበር። የፈሰሰ ውሀ አይታፈስም! ከእንግዲህም ቢሆን አብዮታዊ ዲሞክራሲ ባስቀመጠው የችግር መፍቻ አቅጣጫ (ካውንስሊንግና የምክር አገልግሎት) እየተከተለ ቀሪ ህይወቱን መምራት ይኖርበታል። ከመስመር ወጣ የምንለው ይህን የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ችግር መፍቻ አቅጣጫ ካልተከተለ ብቻ ይሆናል።"

ካድሬው በማሚት አስተያየት ተበሳጨ። አንሶላ ከተጋፈፉቸው ብዙዎቹ ለአብዮታዊ ዲሞክራሲ ማሸነፍ የወጣትነት እድሜያቸውን የሰጡ የህውሀት ተጋዳሊቶች መሆናቸውን ስም እየጠራ አጋለጠ። ይበልጥ ስሜታዊ እየሆነ ሲሄድ እንዲህ በማለት የውስጡን ተናገረ፣

"በቅርብ ጊዜ ለህዝብ ይፉ በሆነ መረጃ መሰረት የኤድስ ወረርሽኝ ሀገራዊ ስጋት ከፈጠረባቸው ቦታዎች ዋነኛው የሀገር መከላከያ ሰራዊት ነው። ፌደራል ፓሊስም ተመሳሳይ ነው። በተለይ ከፍተኛ መኮንኖቻችን ከተሰጣቸው ኮከብ ጋር ቫይረሱ አብሮ የታደለ እስኪመስል ድረስ አስደንጋጭ ሆኗል። እነዚህ ባለማዕረግ ታጋዮች ህይወታቸውን የሚመሩት በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ቅኝት ነው።

ካድሬው ስቃይ ስቦ የሚከተለውን ጨኸት ተነፈሰ፣

"...ሌላው ቀርቶ ህመሙ እየባሰባት ሲሄድ ለማስታመምና ለእረፍት እንዲረዳት ከመስተዳድሩ ተዘዋውራ የተከበረው ፓርላማ አባል እንድትሆን የተደረገችው ተጋዳሊት ካውንስሊንግ የምንወስደው አብረን ነው። የፌደራል ፓሊስ ሁለተኛ ሰው የሆነው ባለቤቷ የምክር አገልግሎት እንዲወስድ ደጋግማ ብትጠይቀው ፍቃደኛ አልሆነም። ይህ ቁልፍ የህውሀት ታጋይ ህይወቱን በአብዮታዊ ዲሞክራሲ አቅጣጫ አይመራም ማለት ነው?"

***

የደኢህዴን ማእከላዊ ኮሚቴና የአዲሳባ ምክትል ፕሬዝዳንት። የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ደቀመዝሙር ጓድ ካሊድ አብድርህማን። ካሊድ አክሮባተኛ ነበር። በተለምዶ በኢህአዴግ ግምገማ ላይ ቀድሞ የተናዘዝ ራሱን ለማየት ዝግጁ ነው ተብሎ ስለሚታመን ያለምንም ቅጣት ይታለፋል። ለሌሎችም በአርአያ የሚጠቀስ ይሆናል። የካሊድ መገለባበጥ ይህንን ታሳቢ ያደረገ ነበር። ይህ ለዶንቦስኮ አይሰራም። የእነ ካህሳይ፣ ማሚት፣ ሞንጆሪኖ ግዛት።

ማሚት እንዲህ በማለት አውጫጭኙን ጀመረች፣

"ካሊድ ስለትምህርት ደረጃህ ንገረን። ኢህአዴግን ስትቀላቀል ዲግሪ አለኝ ብለህ፣ እኛም የምርጫ መወዳደሪያ ፓስተር ላይ ከፎቶግራፍህ በታች በፓለቲካል ሳይንስ ዲግሪ ብለን ልደታን በአንተ ፓስተር አጥለቀለቅናት።"

ካሊድ ኮስተር ብሎ፣

"የፓርላማ ማህበራዊ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴው ዶክተር አህመድ ነው ያታለለኝ። ከካናዳ ስለመጣህ ኢህአዴግና የመዲናይቱ ህዝብ እንደተማረ ይቆጥርሀል፣ በንግግርህ ውስጥም ጠንካራ እንግሊዘኛና አብዮታዊ ቃላት ተጠቀም አለኝ።"

ማሚት ጠረጴዛ እየደበደበች፣

"አትዘባርቅ! የተጠየከው የትምህርት ደረጃህ ስንት ነው? እሱን ብቻ መልስ።

"ዲፕሎማ!"

"የምን ዲፕሎማ?"
ካሊድ ጭንቅላቱን እያሻሸ፣
"High School" ብሎ መልስ ሰጠ።
ማሚት ቀጠለች፣
"ነገ አምጥተህ ልታሳየን ትችላለህ?"
ካሊድ እያቅማማ፣
"ዶክመንቶቼን ከካናዳ ገና አልአስመጣሁም። ጊዜ ከተሰጠሽኝ በቅርብ ጊዜ አስመጣለሁ።"
እነ ማሚት የፓርላማው ማህበራዊ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው ዶክተር አህመድም ጉዳይ እንዲጣራ ለኢህአዴግ ቢሮ አስተላለፉ። ካሊድ መቼም ብቻውን ሞቶ አያውቅም!!

***

የኢትዮጵያን ፓርላማ ለአስር አመታት የተከታተለ ሰው የአንድ ትልቅ አዛውንት ገፅታ ከፊቱ ላይ አይጠፉም። የፀጉሩ ጐፈሬ፣ ገብስማነትና አበጣጠሩ የናይጄሪያውን ታዋቂ ፀሀፊ ወሌ ሾይንካም ስለሚመስል የእሱም ቅጽል ስም ይሄ ምሁር ሆኗል። ፀሀፊ ወሌሾይንካም የኖቬል ተሸላሚና የፓለቲካ አቀንቃኝ ነው። ለአፍሪካ ስነ ጽሁፍ እድገት ላበረከተው አስተዋጽኦ የአዲሳባ ዩንቨርስቲ የክብር ዶክትሬት አበርክቶለታል።

የኖቬል ተሸላሚውን ቅፅል እንደተሰጠው የሚያውቀው የእኛ ሰው ቢያንስ በወር አንድ ቀን በፓርላማ ውስጥ ተቋማትን ሲያፋጥጥ ይታያል። ለሸንጐው አባላት አለም አቀፍ ህጐችን፣ የፓርላማ አሰራሮችና ተሞክሮዎችን የአቅም ግንባታ ይሰጣል። ይህ ብርታቱ ከምሁርነቱ ጋር ተደምሮ የማህበራዊ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ሆነ። በተጨማሪም ከፓርላማ እየተወረወረ የአዲሳባን ፓለቲካ ስራ ድጋፍ እንዲሰጥ ተመደበ... "ዶክተር!" አህመድ።

ይህ ከምእራቡ አለም የመጣ ምሁር የኢህአዴግን ክብር ከፍ አደረገ። ባለሁለት ስለት ቢላዋ ቢሆንም አንደኛው የዶለዶመ መሆኑን በተግባር አሳየ። ከእነ ዶክተር ካሱ ኢላላ ቀጥሎ ኢህአዴግ አለኝ ከሚላቸው አብዮታዊ ምሁራን ጐራ ውስጥ ተቀላቀለ። ደኢህዴን ደረቷን ነፋች። ኢህአዴግ ደስ አለው። ሁላችንም ክብርና ሞገስ አጐናፀፍነው።

ከእለታት በአንዱ ቀን ለፓርላማው የህግ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ለሆነው አስመላሽ ወልደስላሴ (አባይ ነብሰ) ከዶንቦስኮ መልእክት ደረሰው። አባይ ሰውየውን ጠርቶ እንዲህ ብሎ ጠየቀው፣
"ዶክተር አህመድ የሁሉንም ሰው ዶሴ እያዘጋጀን ስለሆነ ዶክትሬትህን ነገ ይዘህ በአስቸኳይ እንድትመጣ" አለው።
ሰውየው ደነገጠ። ወገቡ ጐበጠ። ታሞም ለጥቂት ቀናት ተኛ። የማይቀር እዳ ነውና አባይ ነብሰ ጋር ቀርቦ እንዲህ በማለት መልስ ሰጠ፣
"አባይ! አባይነብሰዬ! በተለምዶ ሰዎች ዶክተር ስለሚሉኝ ነው እንጂ ዶክትሬት የለኝም።ደግሞስ ዶክተርነት ምን ያደርጋል ብለህ ነው? ዋናው

አብዮታዊነትና የአላማ ጽናት ነው። በዚህ ደግሞ በፊት መስመር በመሰለፍ ድርጅቴን እያገለገልኩ ነው።"

አባይነብሶ ሊለቀው አልፈለገም። እንዲህም አለው፣

"እንግዲያውስ አለኝ የምትለውን ዶክመንት ይዘህ ና።"

የተከበሩ አቶ አህመድ አንድ አመት የሰለጠነባትን ሰርተፍኬት ይዞ መጣ...

ኢትዮጵያዊው ወሌሾይንካም!!

***

ጦላይ ...1990 አ• ም•

ከህውሀትና ብአዴን የተቀነሱ ሴት ተጋዳሊቶችን የቀለም ትምህርት ለማስተማር ጦላይ ለአንድ አመት ቆይታ አድርጌ ነበር። የጦላይ ህይወት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የመከሰት እድሉ ጠባብ ነው። ጦላይ ርግጥም ልዩ ቦታ ነበር...

ከቁመት በላይ በሆነ ስንደዶ ሳር የተሸፈነ፣ ዘንዶና እባብ መሳ ለመሳ የሚርመሰመሱበት፣ አጋዘንና ከርከሮ በር የሚቆረቁርበት፣ ጦጣና ሰው እየተጋፉ የሚሄዱበት፣ ጨረቃ ውበቷን ለማሳየት የሰፈዱ ያህል ሰፍታ የምትደምቅበት ቦታ... ጦላይ!

በሐሩር በረሀ ውስጥ አስር ሺህ ሴቶች፣ ከሶስት መቶ የማይበልጡ መምህራን የተቆጣጠሩበት፣ አሰቃቂው የደርግና ኢህአዴግ ወታደራዊ እስር ቤት፣ ከደርግ ጀምሮ ሻለቃ ቢራራ የሚል ስያሜ የተሰጠው ምእናባዊ ሴጣንና መንፈስ የነገሰባት... ጦላይ!

ስለ ኢትዮጵያ መስቀለኛ መንገድ ፣አብዮታዊ ዲሞክራሲ ትንታኔ ሰጥተው የማያባሩ፣ ግን ደግሞ ማንበብና መጻፍ የማይችሉ ተጋዳሊቶች ያሉበት። በየሳምንቱ በሴቶቹ ቁጥር ኮንደም ጥቅም ላይ የሚውልበት፣ የሴት ወንዶች የሚበዙበት፣ ከበሮ በተደለቀ ቁጥር በመቶዎች አቅላቸውን ስተው የሚወድቁበት ፣መልአከ ሞት አማጦ የሚታይበት... ጦላይ!

ዘመን የተገለበጠበት ቦታ። ሴት ልጅ ጋብዛና ገንዘብ ከፍላ ተፈጥሮአዊ ስሜቷን የምታረካበት። ሺዎች ቆመው የሚሸኑበት።

መታልዬ መታልዬ ዘጦላይ!!

በዚህ ታሪካዊ ቦታ ከአብሮ አደጌ ከንቡጠር (ስሙ የተቀየረ) ጋር በአንድ ቤት እንኖር ነበር። ከጐናችን የቅርብ ጓደኞችን የመምህርት ነጻነት (ስሟ የተቀየረ) ቤት ይገኛል። በመኝታ ቤታችን መስኮት ማታ ማታ ያለማቋረጥ "eddie's dead shot in the head for a dollar who going to tell his mama..."የሚለው ዘፈን ይንቆረቆራል። ከጐረቤታችን መምህርት ነፃነት ቤት። ነጺ ከሰኞ እስከ ሀሙስ ምሽት ያለውን ብቸኝነት ለማባረር ቴፑን እስከ ጥግ ከፍታ ታጮህለች... ከጦላይ አዲሳባ ጦርሀይሎች ባይሰማም ለእኔና ጓደኛዬ

ከምቡጠር የእንቅልፍ ማምመጫ ኪኒን ሆኖናል።

ሲዲውን ከነማጫወቻው በማስታወሻ የሰጣት የመከላከያ የትምህርትና ስልጠና መምሪያ ሀላፊው ኮረኔል ነጋሽ ነበር። ሽቅርቅሩ ኮሎኔል አንድ ሰሞን ከአርብ እስከ እሁድ ውሎውን ጦላይ አደርጉ ነበር። በማሰልጠኛ ጣቢያው የነበሩ ዲሞብላይዝድ ታጋዮች በየጊዜው እንደ ምግብ ሜኑ ይቀርቡለታል። እሱም አልጫን ከቀዩ፣ ምንቸትን ከከትፎ እያማረጠ ይቀረጥፉል። የትግል ጓደኞቹ ባድመና ዶረና ላይ ይረግፉሉ፣ እሱ ሚስቶቻቸውን እንደ ሽሚዝ ይቀያይራል። ይህ ጦላይ ነውና ነውር አይደለም!!

ከቀናቶች በኋላ ተጋዳሊቶች አንገቱ ጋር ደረሱ። በቁት። ፊቱን ወደ መምህራን አዞረ። መምህር ነፃነትን ተዋወቃት። ጦላይ ለሴት መምህራንም ፈታኝ ነበረች። ጠየቃት። ፍቃደኛ ሆነች። ሁሉንም እርግፍ አድርጉ ከነፃነት ተጣበቀ። ለምክርና ሀሜት እስኪጋለጥ ድረስ ከንፍ አውጥተው በረሩ። ለጦላይ ከዋክብቶች ሆኑ።ከጨረቃዋ ጋር ተጣምረው የምሽት ብርሀን አፈሰሱ።

አፈቀራት... ወደደችው።

ህይወት በዚህ መልኩ ለረጅም ጊዜ ቀጠለ። ይህን ጣፉጭ ጊዜ ዘላለማዊ ለማድረግ የበረሀ ሚስቱን ፊቶ እንዲያገባት ጥያቄ አቀረበ። "አሮጊቷ" ብሎ ከሚጠራት ሚስቱ እንድትገላግለው ተማፀናት።

ነፃነት ማሰላሰያ ጊዜ ጠየቀችው። እኛን አማከረች። ከጊዜያዊ ጥቅምና ስሜት ወጥታ እንድታስብበት ምክር ቢጤ ለገስናት። ምን ያደርጋል! ማሰላሰያ ጊዜው ሳያልቅ እኔ ጦላይን ለመጨረሻ ጊዜ ተሰናብቼ ወጣሁ። ከምቡጠር ተከተለኝ። እሱ የአንድ ግል ኮሌጅ መምህር ሆኖ ተቀጠረ።

ከእለታት በአንዱ ቀን እንዲህ ሆነ፣

ከንቡጠርን ፈልጌ ልደታ የሚገኘው ኮሌጅ ሄድኩኝ። ቅንድቧ ከገጠመ ተማሪው ጋር ሻይ እየጠጣ አገኘሁት። አስተዋውቆን ጨዋታ ጀመርን። የኢህአዴግ ካድሬ መሆኔን ስታውቅ እንዲህ ብላ ጠየቀችኝ፣

"የአዲሳባ ካቢኔ አባሏን ታጋይ ማሚት ገ/አግዚአብሄር ታውቃታለህ?"

"ታጋይ ማሚት! እንዴ እሷን ካላወኩማ ምኑን የአዲሳባ ካድሬ ሆንኩኝ።" አልኳት።

"ወላጅ እናቴ ናት።"

"እድለኛ ነሽ። ጠንካራ እናት አለችሽ።"

"ኧረ ባክህ! ብዙ ሰው እንደዛ ይለኛል። በተለይ ስራውን በአግባቡ የማይሰራ፣ ቤተሰቦቹን የማያከብር፣ የሚማግጥ ሰው አትወድም ሲሉ ሰምቻለሁ። ለነገሩ እቤት ውስጥም ሲርየስ ናት!"

"ምን ትነግሪኛለሽ? ዶንቦስኮ በሚባለው የካድሬ ማሰልጠኛ እንዴት እንደምታንቀጠቅጥ አውቃለሁ።" አልኳት።

ከንቡጠር በአፉ ውስጥ ይዞት የነበረው ሻይ በትንታ ተደፉ። ልጅት መናገሯን ቀጠለች፣

"አባቴንም ታውቀው ይሆናል የመከላከያ ስልጠና ክፍል ሀላፊ ነው። ኮረኔል ነጋሽ ይባላል።"

አፈጠጥኩባት...ደነገጠች። እኔም ከድንጋጤ ሳልወጣ፣

"መጀመሪያ ገጽታሽን ሳየው አዲስ አልሆኑብኝም። የአባትሽ ግልባጭ ነሽ። "አልኳት። ርግጥም የልጅቷ መልክ ቁርጥ አባቷን ነው። የእጅና እግሮቿን ፀጉር ጨምሮ። አፍታም ሳይቆይ ጦላይ ከሀሙስ እስከ አርብ የማየው ጥቁሩ ላንድክሩዘር ኮሌጁ በር ላይ ቆመ። የኮረኔል ነጋሽ ሹፌር ከርቀት አየሁት...

ተሰናብታን ሄደች።

ከንቡጠር ሳቁን ማቆም አልቻለም። በግርምት ውስጥ ሆኖ ኮረኔሉ እንደ ካልሲ የቀያየራቸውን ተጋዳሊዶች ጣቶቹን እያነሳ መቁጠር ጀመረ ... ትርሀስ፣ አባዲ፣ አልማዝ፣ አብርሽት፣ አልጋነሽ ፣ማርታ፣ ትበርሀ፣ ዘርፌ... የእጆቹ ጣቶች አለቁ። እኔንም ወደ ኃላ ጐተተኝ። በፉንታዬ ወደ ዶንቦስኮ በመሻገር በማሚት ምህረት የለሽ ሰይፍ የተቀሉትን መጥራት ጀመርኩ... ንግስቲ፣ አልማዝ፣ ጣይቱ፣ ካሊድ፣ አበበ ዘልኡል... ኧረ ቤቱ ይቁጠረው።

(ፊት ለፊታችን የተጋረጡ ሀገራዊ ጉዳዮች አንስተን ስንጨርስ የደራሲ ተድባበ ጥላሁን ካዘንችሰ መስታወት ግልባጮች ስለነበሩ ሁለት ታሪካዊ ቦታዎች እናወጋለን። ዝዋይ ህፃናት አምባና ጦላይ ካምፕ። በዝዋይ ህፃናት አምባ የዛሬዎቹን ጀነራሎች ፍስህ ማንጁስ፣ ወዲ መድህን፣ ወዲ ነሬ... ለማሰልጠን ቆይታ አድርጌ ነበር። በኢህአዴግ መኮንኖችና በባላንጣዎቻቸው የመንጌ ልጆች መካከል የነበረው መገፋተር አሳዛኝ ነበር። በተለይ ለአቅመ አዳም በደረሱ እንስቶችና በገንዘብና ጉልበት ሊገዟቸው በሚዳከሩት ባለማእረግ ወታደሮች መካከል የነበረው ትግል ከህሊና የሚጠፉ አይደለም። ከመኮንኖቹ ሚስቶች ጋር ደግሞ በጦላይ ... መኃልዬ መኃልዬ ዘጦላይ!)

***

የሞንጆሪኖ ልቅሶ...

በሰፈሩት ቁና ሆነና ነገሩ የህውሀት መሰንጠቅ የሞንጆሪኖን ፍጹማዊ አገዛዝ አንዲያከትም አደረገዉ። በእርግጥ የተስፈማርያምን የህል ውግዝ ከማርዬስ አልደረሰባትም። ከአቶ መለስ ተግሳፅ ውጭ።

አቶ መለስ እንዲህ አላት፣

"ሞንጆሪኖ አዲሳባን የለውጥ ማዕበል ውስጥ አስገብተሽ ታስተካክያለሽ ብለን ነበር የላከንሽ።አንቺ ግን የድርጅቱን አደራ በልተሽ ከጀርባ ስታደራጂ ከረመሽ። ኧረ ለመሆኑ ምን ጐድሎብሽ ነው? እነ ስዬን ሳታዉቂያቸው ቀርተሽ ነው፣ አብረሽ ድርጅቱ ላይ ገመድ ልታጠልቂ የነበረው?"

ሞንጆሪኖ ተንሰቅስቃ አለቀሰች። ስጋ ስውአትን ጠርታ ሁለተኛ እንደማይለመዳት ቃል ገባች። እግሩ ላይ ተደፍታ ይቅርታ ጠየቀች።

ከእነተወልደ ጋር እንዴት እንደተመሳጠረች ዘከዘከች። የህቡዕ እንቅስቃሴው ከስድስት ወር በፊት በአዲሳባ መጀመሩን አስረዳች። በአዲሳባ ያሉት የዞን ሊቀ መናብርት ትልቁ ስራቸው ይህ መሆኑን ገለፀች። ካድሬዎቹ አባዝተው ስለበተኑት ወረቀት ዘከዘከች። አመናት።

ፊቱን ወደ እሷ አነሳ...ራራላት።

እንደ ቀድሞ ባሷ አባይ ፀሀዬ የምህረቱ ተቋዳሽ አደረጋት። የዘመናዊ እውቀት ማነስ የፈጠረው ችግር ሊሆን እንደሚችል በመግለፅ፣ የቀለም ትምህርት እንድትማር ፈረንጅ ሀገር ሰደዳት። ትምህርቷን አጠናቃ እንደመጣች ጓዟን ጠቅልላ መቀሌ ገባች። የትግራይን ካቢኔ ተቀላቀለች። ለአቶ መለስ ያላትን ታማኝነቷን በተግባር አሳየች፣ እሱም ካሳውን በቁሙ ተቀበለ። በዚህ ሳይወሰን በህውሀት ሁለተኛ ትውልድ ውስጥ እንድትታቀፍ የመጀመሪያው ምርጫ አደረጋት!

***

(የአቶ መለስ ግብአተ መሬት ከተጠናቀቀ በኃላ አልፎ አልፎ ኢቲቪ አመለከታለሁ... ታዲያ አንድ ምሽት ቲቪውን ወደ ቻናል 280 ሳዞረው የኢትዮጵያ ፓርላማ እየቀረበ ነበር*** የፓርላማ አባላቱ ለአንድ ሚኒስቴር መ/ቤት ጥያቄ ያቀርባሉ። ከህዝብ የተሰበሰቡ ጥያቄዎችን እንድታቀርብ ለአንዲት የፓርላማ አባል እድል ተሰጠ። ከብርት የፓርላማ አባሷ መናገር ጀመረች። የሴትየዋን ድምፁ አውቀዋለሁ። ካሜራው ቀጥሎ ስሟን አሳየ: **"ፈትለወርቅ"** አላውቃትም። ቀስ በቀስ ምስሏን ሲያሳይ ሴትየዋ ሞንጆሪኖ ናት። ለካስ ሞንጆሪኖ ፈትለወርቅ ሆናለች።... የአዲሷ ፈትለ ወጣትነት የድሮዋ ሞንጆሪኖ ነው። አፍታም ሳይቆይ የህውሀት ድርጅታዊ ጉባኤ በመቐለ ተካሒደ፣ ፈትለወርቅ የህዉሀት ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ሆነች።)

***

ምእራፍ ስድስት

ኢህአዴግን ከአዲሳባ ያባረረው - ምርጫ 92

"እናንተ እኮ ጆሮ ስለሌላችሁ ነው። የአዲሳአባ ህዝብ አንቅሮ ተፍቷችኃል። የተተፋ ምራቅ ደግሞ ተመልሶ አይዋጥም።"

ክንፈ ሚካኤል ደበበ (አበበ ቀስቶ)

የተዳፈነ ታሪክ!

ብዙዎች የአዲሳባ ህዝብ ምርጫ ካርድ በምትባል ሰላማዊ ወረቀት ኢህአዴግን የቀጣው በምርጫ 97 አድርገው ይቆጥራሉ። ይህ የተሳሳተ ነው። ኢህአዴግ ላይ የመዲናይቱ ህዝብ የወሰነው በሁለተኛው አገር አቀፍ ምርጫ 1992 ዓ.ም ነበር። በዚህ ምርጫ ኢህአዴግ አሳፋሪ ሽንፈት ተከናንቧል። ይህ ብዙ ያልተነገለት ታሪክ በወቅቱ መሪ ተዋንያን በነበርን ካድሬዎች ዘንድ የእሳት ዳር ጨዋታ ሆኖ ሰንብቷል... በእንደዚህ መልኩ ለንባብ እስኪበቃ ድረስ።

በምርጫ 92 ኢህአዴግ መሸነፉን አስቀድሞ ካረጋገጠ በኃላ የተከተለው ስትራቴጂ የህዝቡን ወሳኔ ባይቀይረውም ለማጭበርበር ጠቅሞታል። በምርጫው ማግስትም የህዝቡን ተቃውሞ ለማስቀየስ የተለያዩ አገር አቀፍ አጀንዳዎች ተቀርፀው ተግባር ላይ መዋላቸው ጉዳዩ እንዲለዝብ አድርጎታል። የሄኖ አለም አቀፍ ፍርድ ቤት ባድመ ላይ የሰጠው ብይን ተከትሎ "የጦርነቱ ድል በፍርድ ቤት ተደገመ" የሚል የተሳሳተ መግለጫ በመስጠት የመዲናይቱን ህዝብ መስቀል አደባባይ እንዲወጣ የተደረገው በምርጫው ሳምንት ነበር።

በጨፌ ግምገማ ኢህአዴግ በመሸነፉ ላይ ጥያቄ አንስቶ የተከራከረ አልነበረም። ይልቁንስ ሽንፈቱን የሚያሳዩ ሰፋፊ መገለጫዎች ቀረቡ። የውጤቱ መቀልበስ ተከትሎ በመዲናይቱ ተከስቶ የነበረው አመፅና ነውጥ በአጭሩ ባይቀጭ ሊከሰት የነበረው አደጋ በሰፊው ተነገረ። በተሰፉ እጦትና የከተማ ችጋር የተመታው ነዋሪ አደራጅቶ የሚያነቀሳቅስ ተቃዋሚ ቢኖር ኖሮ ዛሬ እንደዚህ ተቀምጦ ስለአዲሳባ የምንነጋገርበት ሁኔታ እንደማይፈጠር ተገለፀ። ምርጫውን ለመቀልበስ በተግባር የዋለው ፀረ ዲሞክራሲ ቢሆንም አብዮታዊ ዲሞክራሲን እንደታደገው አስተያየቶች ቀረቡ።

በተለይም የደህንነቱ ሹም ኢሳያስ ወ/ጊዮርጊስ፣

"የታደግናችሁ እኛ ነበርን" ብሎ በኩራት ሲደሰኩር መስማት አስገራሚ ነበር። በእያንዳንዱ ወረዳ በእሱ ፊትአውራሪነት የተሰራውን ሸፍጥ በዝርዝር ማቅረቡ አስገመተው። እንደ እውነቱ ከሆነ ከአንድ የደህንነት ባለስልጣን የሚጠበቅ አልነበረም። ምንም እንኳን ሀቁ እሱ የተናገረው ቢሆንም።

ኢህአዴግ በሁለተኛው አገር አቀፍ ምርጫ በአዲሳባ ክልል ም/ቤትና የፓርላማ ተወካዮች እንደሚሸነፍ ያረጋገጠው አስቀድሞ ነበር። በወቅቱ የቅድሚያ ዳሰሳ ጥናት እንዲሰራ የታዘዘው ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማእከል ኢህአዴግ ችግር እንደሚያጋጥመው ሲፈራ ሲቸር አቀረበ። በክቡር ገና ሲመራ የነበረው የአዲሳባ ንግድ ም/ቤት በበኩሉ እንደ ዋልታም ባይሆን የተቃዋሚ እጩዎች በሰፊው ም/ቤት እንደሚገቡ አመላከተ።

ይህንን ተከትሎ ኢህአዴግ የምርጫውን ዲሞክራሲያዊነት የሚያጠፉ ሶስት እርስ በራስ የሚመጋገቡ ስትራቴጂዎች ነደፈ። እስትራቴጂዎቹ እንደሚከተለው ነበሩ፣

በእጩ ምዝገባ ወቅት በተቃዋሚ ፓርቲ እጩዎች ውስጥ ለኢህአዴግ የሚሰራ አሰርገው ማስገባት፣ በየወረዳው ምርጫ ቦርድ በሚፈቅደው መሰረት የተፎካካሪ እጩዎችን ብዛት እስከመጨረሻው መለጠጥ፣ እና በምርጫው የመጨረሻ ቀናት የተቃዋሚ ፓርቲ እጩዎችን ከተቻለ በማሳመን ካልተቻለ በመደለልና በማስገደድ ራሳቸውን እንዲያገሉ ማድረግ የሚሉ ነበሩ።

በጨፌው ግምገማ ምርጫ 92 ሙሉ ቀን ፈጅቶ ባለመጠናቀቁ ለበነጋታው ጠዋት ቀጠሮ ተያዘለት። እንደተለመደው ከፍስሀ ጋር ተያይዘን ወደ ራስ ሆቴል ሄድን። እውነት እውነቱን ለመነጋገር። ትኩረታችንም ምርጫ 92 ሆነ። አድማሳችን ደግሞ እኔ እና አሱ ከመራነው ዞን ሁለት የሚነሳ ሆኖ መላ አዲሳባን የሚያዳርስ። ተጨባጭ መገለጫዎችን አንስተን የኢህአዴግን ሽንፈት አረጋገጥን።

በወቅቱ ከመስቀል አደባባይ - አየር ጤና፣ ከፈጥኖ ደራሽ -ላፍቶ የተዘረጋውን ዞን ለመከታተል አራት የዞኑ ካድሬዎች፣ ከካዛንችስ ደግሞ ፍስሀ መአሲ ተመደብን ነበር። በዞኑ ውስጥ ያሉ ወረዳዎችን (ወረዳ 20፣21/22፣23፣ 24) እንድንከፋፈል ተደረገ። ምርጫው ተጠናቆ ሲመጣ የአራቱም ወረዳ ውጤቶች ለየቅል ሆኑ።

እስቲ እያንዳንዱን ወረዳ እያነሳን በዝርዝር ወደ መመልከት

እንሸጋገር።

***

ፍስሀ መአሲ ወረዳ 23 (ላፍቶ ክ/ከተማ) ለመምራት ሳርቤት ከተመ። በእሱ ፊትአውራሪነት በወረዳ 23 ኢህአዴግ ያስቀመጠው የመጀመሪያ እስትራቴጂ በተሳካ ሁኔታ ተፈፀመ። መምህር ዳኛ የሚባል የባስሊዎስ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር መኢአድን ወክሎ ለመወዳደር ፍቃደኛ ሆነ። አሸንፎም ወደ ምክርቤት ገባ። በወሰደው አረንቴሽን መሰረት የተሰጠውን ተልእኮ በአግባቡ አከናወነ።

የምክር ቤት ስብሰባ ከመካሔዱ ሶስት ቀን አስቀድሞ መኢአድን ወክሎ የሚናገረው መምህር አንተነህ ምን እንደሚያቀርብ ሪፓርት በዳኛ በኩል ይደርሰናል። እኛም አሰቀድመን ምላሽ በማዘጋጀትና ማን ምን እንደሚናገር በመከፋፈል ሰውየውንና መኢአድን እንቀጠቅጣለን።

ፍስሀ ረታ የሚባል የአካባቢው ተወላጅ ወጣት እንዲያሸንፍ ከማድረግና መምህር ዳኛን አሰርጉ ከማስገባት ውጭ በሌላው አልተሳካለትም። በወረዳው የተወዳደሩት (የካቢኔ አባልና የኢኮኖሚ ዘርፍ ሀላፊ የነበረው ቶፊቅን) ጨምሮ ሁሉም በዝረራ ተሸነፉ።

***

እኔና የዞን ደህንነት ሀላፊው የትውልድ ቦታዬ ወደ ሆነው ወረዳ 24 ኮልፌ ቀራንዮ ሄድን። ኢህአዴግ ያስቀመጠውን ሁለተኛና ሶስተኛ እስትራቴጂ መተግበር ጀመርን። ፓርላማን በተመለከተ ምርጫ ቦርድ በሚፈቅደው መሰረት የተፎካካሪ እጩዎችን እስከመጨረሻ መለጠጥ ሲሆን፣ ክልል ምክርቤትን በተመለከተ የተቃዋሚ ፓርቲ እጩዎች ከምርጫው ራሳቸውን እንዲያገሉ ማድረግ የሚሉት ነበሩ።

ለፓርላማ መቀመጫ የሚፎካከሩ እጩዎችን ምዝገባው ሊጠናቃቅ አንድ ቀን ሲቀረው ከ6 ወደ 12 አሳደግን። በተለይም ኢህአዴግ ሙሉ ለሙሉ ይሸነፍባቸዋል ብለን በለየናቸው አካባቢዎች በቀበሌያቸው ተቀባይነት ያላቸውን ግለሰቦች ለየን። የግል እጩዎች ሆነው እንዲወዳደሩ አግባባናቸው። ፍቃደኛ የሆኑትን ፒትሽን አባሎቻችንን በማስፈረም ለምርጫ ቦርድ አስረከብን። ፓርላማና ክልል ምክርቤት ተመርጠው ሲገቡ የሚያገኙትን ጥቅም አጋነን አሳየናቸው።የስልጣን ተስፈኞች ሆኑ።

በወረዳ 24 ለፓርላማ የቀረቡት የተቃዋሚ ፓርቲ እጩዎች ከአራት በላይ

መሆናቸው እና የራሳቸው ደጋፊ ያላቸው መሆኑ በተጨማሪነት ጠቀመን:: ኢድአፓን ወክሎ የቀረበው ከንፈሚካኤል ደበበ (አበበ ቀስቶ) በወጣቶች፣ከፍሌ ጥግነህ (የቅንጅት አመራር የነበረ) በምሁራንና ነጋዴው ማህበረሰብ፣ የትግረ ወርጂው ሀጂ መሀመድ በሙስሊም ዘንድ ተቀባይነት ነበራቸው። የሰርቶ አደር ጋዜጣ አዘጋጅ የነበረው ታዲዮስ ታንቱ በቀድሞ ስርአት ደጋፊዎችና ወታደሮች ድጋፍ አግኝቷል። ሌሎቹ 7 የግል ተወዳዳሪ እጩዎች በእኛ የቀረቡ ሲሆን ኢህአዴግን መምረጥ በማይፈልገው አካባቢ ድምፅ እንዲሸሙ የተዘጋጁ ናቸው። ኢህአዴግ በእጩነት ዶ/ር ቶፊቅ አብድላሒን አቀረበ። ለዶክተሩ እጩ መሆን ታሳቢ የተደረገው የእስልምና እምነት ተከታይ መሆኑና የግል የህክምና ተቋም ባለቤት ስለሆነ ታዋቂነት አትርፉል በሚል ነበር ...

ጉድና ጅራት ከወደኃላ ቢሆንም!

ምርጫ ተጠናቆ ቆጠራው ሲካሄድ የኢህአዴግ እጩ 16%፣ አበበ ቀስቶ ??፣ ክፍሌ ጥግነህ 7%፣ ታደዮስ ታንቱ 6 % አገኙ። በመሆኑም በአብላጫ ወንበር አሰራር መሰረት ከ84% በላይ ህዝብ ያልመረጠው የኢህአዴግ እጩ ወደ ፓርላማ ገባ። ከውጤቱ ማየት እንደሚቻለው አግባብተን ካስገባናቸው የግል እጩዎች አንዱ ራሱን ቢያገል ውጤቱ ግልብጥብጡ ይወጣ ነበር፣ ኢህአዴግን የወከለው ሰው ፓርላማ አይገባም ነበር።

የዶክተር ቶፊቅን አሸናፊነት ያረጋገጡት የዜሮ ድምር መጫወቻዎቹ የህገ መንግስት አንቀፅ 54 እና የተፎካካሪ እጩዎችን ብዛት ወደ አስራ ሁለት ያሳደገው የምርጫ ህግ እርስ በራስ ተጉራርሰው ነበር። የህገ መንግስቱ አንቀፅ 54 (4) የምክር ቤቱ አባላት በአንድ የምርጫ ክልል ውስጥ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች መካከል አብላጫ ድምፅ ያገኘ ተወዳዳሪ አሸናፊ የሚሆንበትን ስርአት ይዘረጋል። በዚህ ጉዳይ ላይ ኢህአዴግ ጨፍኑና ላሞኛችሁ አይነት የመከራከሪያ ጭብጦችን ስለሚያቀርብ ሁኔታውን ገለጥለጥ አድርገ ማየት አስፈላጊ ይሆናል።

ኢህአዴግ በመጀመሪያ የሚያቀርበው መከራከሪያ ይህ የህገ-መንግስት አንቀፅ በዲሞክራሲያዊ ሰርአቶች ከሚታወቁት የምርጫ ስርአቶች አንዱ የሆነውን የአብላጫ ድምፅ መጠቀሙን እንደሚያመላክት ነው። ርግጥም ፓርቲው እንደሚለው በዲሞክራሲ ግንባታ እስከ አሁን የሚታወቁት የምርጫ ስርአቶች የብዙሀን ድጋፍ፣ የተመጣጠነ ውክልና እና የአብላጫ ድምፅ ሲሆኑ ኢህአዴግ የሚጠቀመው በመጨረሻ የቀረበውን ነው። ይህ የምርጫ ስርአት ከተወዳዳሪዎች መካከል አብላጫውን ድምፅ ያገኘ አሸናፊ የሚሆንበት ሲሆን በመሰረቱ ዲሞክራሲያዊ ገፅታ ያለውና ምርጫውን ለማስፈፀም ቀላልና ወጪ ቆጣቢ ነው።

የኢህአዴግ ሁለተኛ መከራከሪያ በአለማችን የዲሞክራሲያዊ ግንባታ ቁንጮ ላይ የተቀመጡት እነ እንግሊዝና አሜሪካ የሚጠቀሙት የአብላጫ ስርአት እንደሆነ በመግለፅ የዲሞክራሲያዊነቱን መተማመኛ አማኝ እንደሆኑ ማሳየት ነው። የኮረጅነው ከእነዚህ ሀገሮች ነው በማለት።

አቶ በረከትና ኢህአዴግ ይህንን አመክንዮ ሲያቀርቡ አንድም ጊዜ ከጀርባ በታኮነት ያስቀመጡትን በምርጫ ጣቢያዎች የሚወዳደሩ እጩዎችን ብዛት የሚያሳየውን የምርጫ ህግ አይጠቅሱም። ከዚህ በተጨማሪም በእንግሊዝና አሜሪካ የአብላጫ ድምፅ ስርአት ዲሞክራሲያዊ የሆነበት ምክንያት ስንት ፓርቲዎችና ግለሰቦች እረስ በራስ እንደሚፎካከሩ ለመግለፅ አልፈለጉም። በአሜሪካን ሀገር ከሞላ ጐደል የሁለት ፓርቲ ስርአት የተዘረጋ ሲሆን በምርጫ ወሳኝ ተፎካካሪ ሆነው የሚቀርቡት የሁለቱ ፓርቲዎች እጩዎች ናቸው። በእንግሊዝም ቢሆን የመድብለ ስርአት ቢዘረጋም በምርጫው ብርቱ ተፎካካሪ የሚሆኑት ከሶስት ፓለቲካ ፓርቲዎች አይበልጡም።

የኢህአዴግ የአብላጫ ስርአት ከምርጫ ህጉ ጋር በመመጋገብ በህዝብ ያልተመረጠን ኃይል እንዴት ወደ ስልጣን እንደሚያመጣ ከብዙሀን የድጋፍ ስርአት ጋር በማወዳደር ማየት ይቻላል። ለማሳያ እንዲሆን የወረዳ 24 ምርጫ ውጤት ማየቱ የበለጠ ግልፅ ያደርገዋል።

የብዙሀን ድጋፍ ስርአት ምን ይላል?

ከዲሞክራሲያዊ የምርጫ ስርአቶች አንዱ የሆነው የብዙሀን ድጋፍ ስርአት የሚመራበት መርህ በአንድ የምርጫ መወዳደሪያ ክልል ውስጥ አሸናፊ ሆኖ የሚመረጠው ከሀምሳ በመቶ በላይ የሆነውን የህዝብ ድምፅ ያገኘ እጩ ነው። አንድ ተፎካካሪ ከሀምሳ በመቶ የድምፅ ብልጫ ካላገኘ ሁለተኛ ዙር ምርጫ ይካሄዳል። በሁለተኛው ዙር በተወዳዳሪነት እንዲቀርቡ የሚደረጉት በመጀመሪያው ዙር በድምፅ ብልጫ አንደኛና ሁለተኛ የወጡትን ተወዳዳሪዎች ይሆናል። ይህ የምርጫ ስርአት አብዛኛውን የህዝብ ድጋፍ ያገኘ እንዲመረጥ ስለሚያደርግ ተቀባይነት ያለው መንግስት ለመመስረት ያስችላል።

የኢህአዴግ የምርጫ ስርአት የብዙሀን ድጋፍ የሚከተል ቢሆን ኖሮ በ92 ምርጫ በወረዳ 24 የሁለተኛ ዙር ተፎካካሪ ሆነው የሚቀርቡት ዶክተር ቶፊቅና አበበ ቀስቶ ይሆኑ ነበር። ምርጫው አስር ጊዜ ቢጭበረበር እንኳን የአበበ ቀስቶ አሸናፊነት ሳይታለም የተፈታ ይሆን ነበር።

በአጠቃላይ መልኩ የወረዳ 24 ህዝብ ለአዲሳአባ ክልል ምክርቤት እኔንና ሚፍታህ አብዶ መርጦ የተቀሩትን አራት ወንበሮች ለመኢአድና ኢዴአፓ ሰጠ። እኔና ሚፍታህ የተመረጥነው ህዝቡ ስለፈለገን አይደለም። የወረዳው ደህንነት ሀላፊ (ዘካርያስ ይባላል) የተቃዋሚ እጩዎችን አስፈራርቶ እንዳይመዘገቡ ስላደረገ ነበር። በርግጥ ከኢህአዴግ እጩዎች አብላጫ ድምጽ ያገኘነው በአካባቢው ተወልደን በማደጋችንና ነዋሪው "ላም አሳት ወለደች..." ሆኖበት ነበር።

ህዝቡ ኢህአዴግ ላይ የመረረ ጥላቻ እንዳለው ለማየት የተቃዋሚ ፓርቲዎች እና ኢህአዴግ ያቀረባቸውን እጩዎች ፕሮፉይል ከምርጫው ውጤት ጋር ማገናዘብ በቂ ይሆናል። ኢህአዴግ ለአዲሳአባ ክልል ምክርቤት ሁለት ኢኮኖሚስቶች፣ ሁለት የሒሳብ ሙያተኞች፣ አንድ ኤሌክትሪካል ኢንጂነር፣ አንድ ዶክተር አቀረበ። ኢዴአፓ ሁለት ከ7ኛ ክፍል ያልዘለሉ ትንቢተ ኤርሚያስ የሚባል አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የጥበቃ ሰራተኞች አቀረበ። መኢአድ በበኩሉ ስራ አጥ የነበሩና የአካባቢያቸው ማህበረሰብ በደባል ሱስ የሚያውቃቸውን እጩ አድርጐ አቀረበ። በመሆኑም ከግለሰብ አቅምና ስብእና አንጻር ልዩነቱ የሰማይና የምድር ይህል ነበር። ነዋሪው ግን ዶክተሩም፣ ኢኮኖሚስቱም፣ ኢንጅነሩም፣ አካውንታንቱም ባፍንጫዬ ይውጣ ብሎ ለኢህአዴግ ግልፅ መልእክት አስተላለፈ።

***

ጨዋታችን የፔንዱለም ጉዞ ነውና ጉድና ጅራት ወደተባለው የዶክተሩና አበበ ቀስቶ ወግ እንሸጋገር።

እንዲህ ነበር የሆነው።

የእጩ ምዝገባ ከተጠናቀቀና መቀየር የማይቻልበት ደረጃ በደረሰበት ወቅት በዶክተር ቶፊቅ አብድላሒ ላይ መረጃዎች መጉረፍ ጀመሩ። በየመድረኩ የሚቀርብበት ተጨባጭ ኢንፎርሜሽኖች ጆሮ የሚያቶሉ ሆኑ። በከፍተኛ ወንጀል የሚያስጠይቁት እስከመሆን ደረሱ። ዶክተሩ በቴዎድሮስ አደባባይ አካባቢ ከፍተኛ ክሊኒክ ነበረው። በወቅቱ ለሴት እህቶቻችን የድህነት ማምለጫ መንገድ ተደርጐ የተወሰደው ወደ አረብ ሀገር መሄድ ነበር። ዶክተሩ ይህን በመገንዘብ ወደ አረብ ሀገር በተለይም ወኪል ጽ/ቤት አለኝ ብሎ ወደተናገረው የመን ሀገር በቀላሉ እንደሚልክ ያስታውቃል። የአጠቃላይ ህክምና ምርመራ ኤድስን ጨምሮ ከእያንዳንዷ ሴት ከአንድ ሺህ ብር በላይ ይቀበላል። ከአምስት መቶ በላይ እህቶቻችን የተጠየቁትን ከፍለው ምርመራውን በመውሰድ ጉዞአቸውን ይጠባበቃሉ። ተስፋቸው ሲሚጠጥ ቅሬታ ወደ ማሰማት ይሸጋገራሉ። ሁኔታው በዚህ ደረጃ እንዳለ ነበር ዶክተሩ

የኢህአዴግ እጩ ሆኖ የቀረበው።

አንድ አሁድ ዶክተሩንና ሌሎች የክልል ምክርቤት እጩዎችን ለማስተዋወቅ ወረዳ 24 ቀበሌ 15 (አየር ጤና) አዳራሽ የህዝብ ስብሰባ ጠራን። አንዲት ሴት እንባዋን እየዘራች ዶ/ሩ ለክፉ ቀን ያስቀመጠችውን ወርቅ ማሸጡ ሳይበቃ የኤድስ ቫይረስ ሳይኖርባት አለብሽ እንዳላት አጋለጠች። እሱ የሰጣትን የምርመራ ወጤትና ሌላ ክሊኒክ ተመርምራ ነፃ የሆነችበትን ወረቀት አሳየች።

በቀጠለው ሳምንት በቀበሌ 09 (ፈጥኖ ደራሽ) አዳራሽ በጠራነው ስብሰባ ሌላ ሴት ከባለቤቷ ጋር መጥታ ተመሳሳይ ነገር አቀረበች።አንገታችንን ደፋን።መረጃውን ለካዛንችስ ስውሩ መንግስት ብናቀርብም የድርጅቱ ህልውና ይቀድማል በመባል ውድቅ ተደረገ።

አቶ በረከት ስምኦን በሁለት ምርጫ ወግ መፅሀፉ በገፅ 126 ላይ፣ "... ኢህአዴግ ከምንም ነገር በላይ ህዝቡን ያከብራል፣ ይፈራልም። ሁሌም እንደሚለው ከህዝብ ውጭ ሌላ ጌታ የለውም" ይላል፣

በዚህ የስምኦን ልጅ አባባል ግልባጭ ስሌት መሰረት ደ/ር ቶፊቅ አምስት አመት ያልመረጠውን ህዝብ ወክሎ በፓርላማ ተቀመጠ።ቀጥሎም በየመን የኢትዮጵያ ባለ ሙሉ አምባሳደር ሆኖ በመሾም ለአምስት አመታት አገለገለ።በየመን የጀመራትን ስራ ከግብ አድርሶ ወደ ሀገሩ ተመለሰ። አሁን ደግሞ "የግጭት አፈታትና ምናምንቴ..." የሚባል መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት አቋቁሞ የሪፓርተር ጋዜጣ የዘወትር እንግዳ ሆኗል። ከዛም አልፎ ሁላችንም ቤት አንኳኩቶ ለመግባት ለትልቅ ቦታ ራሱን እጩ አድርጐ ቀርቦ ነበር። ዶክተሮቻችን የሚሯሯጡበት ቦታ።

ይህቺን ቦታ የካፊኞ ልጆች" አሻሮ ይዘህ ወደ ቆሎ የምትጠጋባት" ይሏታል። የሀገራቸው ልጅ ዶክተር አሸብር ወ/ጊዮርጊስ አባባሉን ወደ ተግባር ከለወጡት ሰዎች በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳል። የካፊኞ ልጆች ጊዜያቸው ሲደርስ በሌላ ማስታወሻ የዶክተር አሸብር የህበት ማማ ምንጩን ይነግሩናል። ለአሁኑ ተረኛው ዶክተር ቶፊቅ አብድላሂ ነው። የሀረሬን ክልል ወክሎ የኢትዮጵያ ስፓርት ፌዴሬሽን ፕሬዝዳንት ለመሆን እጩ ተወዳዳሪ ሆኖ ብቅ ብሎ ነበር። ለጊዜው ግማሽ ቢደርስም አልተሳካም። የዛሬው መከራ ለነገ መደላድል ለመፍጠር እንደሆነ ይታመናል። ማን ያውቃል ለዚህ ደረጃ ያደረሰኝ ብሎ የሚያመሰግነው አምባሳደር ግርማ ብሩ "የጠቅላይ ሚኒስትሩ የጥናት አማካሪ" ሆኖ አዲሳባ በመምጣት ህልሙን ያሳካለት ይሆናል።

***

ይህ ደግሞ የከንፈ ሚካኤል ታሪክ ነው... አበበ ቀስቶ።

አበበ ቀስቶ ገራሚ ሰው ነው። በካድሬነት ዘመኔ ኢህአዴግን የሚንቅ እንደሱ አጋጥሞኝ አያውቅም። ብዙሀኑ በፍራቻ አቅማዳ ውስጥ ተደብቆ በነበረበት ሰአት ኢህአዴግን በአደባባይ በመቃወም፣ ሌቦችን በማጋለጥ ፉና ወጊ ነበር። ስለብዙዎቹ ባለስልጣን የማያውቀው ሚስጥር የለም። በምርጫ 92 በተቃራኒ መስመር ብንሰለፍም መቀራረብ ፈጥረን ነበር። ብዙ ነገሮችን አጫውቶኛል። በሂደት ሳጣራው የተጋነኑ ነገሮች ቢኖሩም አብዛኞቹ ትክክል ነበሩ።

በተለይ የህዝቡን ስሜት ከማንበብ አንጻር ከፍተኛ ብቃት ነበረው። ቀበሌዎችን በቁጥር እየጠራ፣ "በዚህ ታሸንፉኛላችሁ፣ በእነዚህ ደግሞ በዝረራ አሸንፉለሁ" ይለን ነበር። እያደር የአበበ አሸናፊነት ፍንትው ብሎ ወጣ። ከምርጫው ፉክክር ገለል የሚልበት አማራጮች ታሰቡ። እሱን ማስፈራራት የሚታሰብ አልነበረም። ምድር ቢንቀጠቀጥ የሚፈራ ሰው አይደለም። በቁጥር ስር ለማዋል ደግሞ ወንጀል ሲሰራ እጅ ከፍንጅ መያዝ አለበት።ስለዚህ የቀረው የመጨረሻ አማራጭ በገንዘብ መደለል ሆነ።

ለመደለያ የሚሆን ገንዘብ ማግኘት አስቸጋሪ አልነበረም። ድብቅ አላማ አንግቦ ፓርላማ መግባት የቋመጠው ዶክተር ቶፊቅ አጠገባችን አለ። የዶክተሩ ቀኝ እጅ መዘ የሚያወጣውን ግራው አያውቀውም። እናም ለአበበ ቀስቶ ሀምሳ ሺህ ብር መደበለት። አግባብተው እንዲሰጡት ደግሞ ጓደኛሞቹ ዳኛ ልዑል ገ/ማርያምና ኪሮስ ተመራጭ ሆኑ። ዳኛ ልኡል በአካባቢው የሚኖር ሲሆን የቀበሌው ካድሬዎች ልዩ አማካሪ ነበር። ይህ የህውሀት አባል የሆነ ዳኛ በኢህአዴግ ከፍተኛ አመኔታ የሚጣልበትና ትላልቅ ፓለቲካ ቀመስ የፍርድ ቤት ጉዳዮችን የሚመለከት ነው። ኪሮስ ደግሞ የቀበሌው የበላይ ጠባቂ ነው። ይህ ማየት የተሳነው የቀበሌ ንጉስ በወረዳው ካድሬዎች ዘንድ "ኪሮስ አይናማው" በመባል ይታወቃል። በወረዳውና በቀበሌ ዘ ውስጥ የፈለገውን እንዲያደርግ ተፈቅዶለታል። ኪሮስ ምንም አይነት ድርጅታዊና መንግስታዊ ስልጣንና ስራ ባይኖረውም የካዛንችሱ መንግስት አለቃ የነበረውን ተስፋማርያም በየጊዜው እያገኘ መረጃ ያቀብላል። የወረዳ አመራሮችን በተናጠል እየጠራ የስራ አረንቴሽን ይሰጣል። ያስፈራራል።

ዳኛልዑልና ኪሮስ አይናማው ገንዘቡን ከዶክተሩ በመቀበል ማግባባቱን ቀጠሉ። በቀበሌያቸው መዝናኛ ክበብ አብረውት መታየት ጀመሩ። እያደር ለኢህአዴግ ምርጫ ኮሚቴ ተስፉ ሰጪ መልእክቶች መሰማት ቀጠሉ። አበበ ቀስቶ ላይ የሚደረገው የእግር ለእግር ክትትል እንዲቋረጥ ተደረገ።

ምርጫው ሊካሄድ ጥቂት ቀናት ሲቀረው አበበ ቀስቶ ውሳኔውን እንዲህ በማለት አሳወቀ፣

"...የተጋበዝኩትና ብራችሁን የተጠቀምኩት እናንተ ጋር የማይነጥፍ የብር ማምረቻ ስላለ ነው። ምርጫ የምወዳደረው ግን ለገንዘብ ሳይሆን ይህን አስከፊ ስርአት ለመጣልና ለነፃነቴ ነው።በዚህ ላይ ለመደራደር ህሊናዬ

አይፈቅድም።"

አበበ ቀስቶ ተወዳደረ። አሸንፎ ተሸነፈ።

ከእለታት በአንዱ ቀን ምሽት ቀበሌ ፲፩ መዝናኛ ክበብ ስገባ አበበ ቀስቶ ቁጭ ብሏል። ከእጁ የማይለያትን የኢትዮጵያ ባንዲራና የምርጫ ምልክቱ የሆነችውን ጭራ ተሸክሞል። ከቀናቶች በኃላ ለሚካሄደው የወረዳ ምክር ቤት ምርጫ እጩ ሆኖ ቀርቧል።

በመዝናኛ ክበቡ አንድ ሁለት ቀዝቃዛ ቢራ ጠጥቼ ሂሳብ ለመክፈል ስጠይቅ አበበ ቀስቶ አስቀድሞ ከፍሎልኛል። ሂሳቤን ሳላወራርድ መሄድ ስላልፈለኩ የቢራ ጠርሙሴን ይዤ ወደ እሱ ሄድኩኝ። እንዲህ በማለት ጨዋታ ጀመርኩ፣

"ምርጫ 92 በዝረራ ስትሸነፍ ከእንግዲህ ፓለቲካ በቃኝ የምትል መስሎኝ ነበር።" አልኩት።

አበበ ሳቀ። ተንተክትኩ ሳቀብኝ።

በማሾፍ እያየኝ እንዲህ አለ፣

"እናንተ እኮ ጆሮ ስለሌላችሁ ነው። አይደለም የወረዳ 24 የአዲሳአባ ህዝብ አንቅሮ ተፍቷችኋል። የተተፉ ምራቅ ደግሞ ተመልሶ አይዋጥም።"

"ምን ማረጋገጫ አለህ?"

"ቅዱስ መጽሀፉ እሹ ይሰጣችኋል አይደል የሚለው። የሲጋራ ሱሰኛ ሲጋራ ቸግሮት አይተህ ታውቃለህ? እኔም የመረጃ ጥማቴ እንደዛው ነው።"
ለጥቂት ደቂቃ በዝምታ ከቆየን በኃላ እንዲህ አልኩት፣
"ልደቱ አያሌውን ቀራንዮ በምትገኝ ቀበሌ 17 ወርዶ እንዲወዳደር ያደረከው አንተ ነህ ይባላል?"

"እናንተ ወያኔዎችና ልደቱ አንድ ናችሁ። የስልጣን ጥማታችሁ እውር አድርጓችኋል። ልደቱ በባዶ እውቀቱ እየተከፈሰ እንደሆነ ለማሳየት ነው ቀበሌ የወረወርነው።" አለኝ።

"ቢሆንም ፍቃደኛ ሆኖ እየተወዳደረ ባለበት ሁኔታ ልትደግፈው ይገባ ነበር። ህዝብ በተሰበሰበበት አዳራሽ ለምን አዋረድከው። መልስ እንዳይሰጥ ደግሞ ሌላ ቀበሌ ላከው።"

ቢራውን እየተገነጨ፣

"አየህ ልደቱ ጆሮ ለማግኘት ብሎ በድርጅታችን ፕሮግራም ውስጥ የሌለ ነገር እንደ ፓርቲያችን አቋም አድርገው እያቀረበ ነው። ኢዴአፓ የቀበሌ ቤት ለባለቤቱ እንመልሳለን የሚል አቋም የለውም። እሱ ግን በአደባባይ እንደዛ ብሎ ተናገረ። ለወያኔ ትልቅ በትር እያቀረብክ ነው ብዬ ብቆጣው አልሰማኝ አለ።ያለኝ አማራጭ እሱ የሚወዳደርበት ቀበሌ 17 ሄጄ ውሸቱን እንደሆነ መግለጽ ነበር። ይህን አድርጌያለሁ።"

አቋረጥኩት፣

"ቢሆንም ልደቱ ፓርቲያችሁን ወክሎ እየተወዳደረ ነው። ያውም

በቀበሌ ደረጃ። በዛ ላይ የሚጣራበት ነገር አለ፣ እውነት ከሆነ ከድርጅታችን እናባርረዋለን ማለት አልነበረብህም። በጐጥ ደረጃ ተወዳድሮ ቢሸነፍ ትልቅ ውርደት ነው።"

እንዲህ በማለት ተቃወመኝ፣

"አየህ ኢዴኣፓ ከኢህአዴግ የሚለየው በዚህ ነው። ከድርጅት ጥቅም በፊት የህዝብ ፍላጐት ያስቀድማል። አዲሳአባ ከመቶሺህ በላይ የቀበሌ ቤቶች እንደሚገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ። ለባለቤቱ እንመልሳለን ብንል እንዴት ይሆናል። ይሄ ሁሉ ህዝብ የት ይሂድ። በምርጫስ እንዴት እናሸንፉለን?... እንደዛ የሚያደርጉት በዘረኝነት የታመመው የእናንተ ሊቀመንበር መለስ ዜናዊና ልደቱ ብቻ ናቸው። ወያኔ ትግራይ ላይ ተግባራዊ አድርጓል።"

ቢራውን እየተጐነጨ፣

"... ልደቱ ኢዴኣፓን ለማፍረስ ከደህንነት ቢሮ የተላከብን እንደሆነ እናውቃለን። ከታቦት ስርቆት ጋር በተያያዘ መረጃዎች ደርሰውናል።የደህንነቱ ቢሮ ይህን ካርድ መዘ በማሳየት ልኮታል ብለን እናምናለን።አስተማማኝ ማስረጃ ስናገኝ ለህዝብ ይፉ እናደርጋለን በዛ ላይ ልደቱ የስልጣን በር ካየ በክላሽ ረፍርፎን እንደሚሄድ እናውቃለን። ከዚህ በፊት ባልተለመደ ሁኔታ የድርጅታችን ሚስጥር እየወጣ ነው።መረጃውን የሚያሾልከው እሱ ነው የሚል ጥርጣሬ አለን። የልደቱ የኋላ ታሪክ የቆሸሸ ነው።"

በድጋሚ ለረጅም ደቂቃ ፀጥታ ሰፈነ። ቢራዎች ተንደቀደቁ። እኔ ሞቅ አለኝ። አበበ ቀስቶ ሰከረ።

ወጋችንን ለመቀጠል፣

"በምርጫ 92 የዶክተር ቶፊቅን ብር ቀርጥፈህ መወዳደርህ እስከ አሁንም ይደንቀኛል። አለመፍራትህም ገርሞኛል" አልኩት።
እየጨለመች በሄደች አይኑ እያየኝ፣

"ለምን እፈራለሁ? በምርጫ ህጉ ከለላ አግኝቻለሁ። እንደምታውቀው እጩ ስትሆን ከባድ ወንጀል ስትፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዝክ በስተቀር አትያዝም። እንደማሸንፍ እርግጠኛ ስለሆንኩ የህግ ከለላው ለሚቀጥሉት አምስት አመታት ይቀጥላል።ገንዘቡን በተመለከተ የሚገርምህ ለራሴ አምስት ሳንቲም አልተጠቀምኩም። አስር ሺህ ብሩን በሙሉ ምርጫ ለቀሰቀሱልኝ ወጣቶች አከፋፈልኩት።"

"አስር ሺህ? የተቀረውስ?"

"ምን ቀረና። ኪሮስ አይናማውና ዳኛ ልዑል ገ/ማርያም መጀመሪያ አስርሺህ ፣ቀጥሎ አምስት ሺህ ብር ሰጡኝ። እምቢታዬን ስገልጽላቸው አምስትሺውን ማንቁርቴ ላይ ቆመው ወሰዱ።"

"እንዴ?"

በመገረም እያየኝ፣

"ለሁለቱ የወያኔ ሌቦች ብዙ ብር እንደሰጣችሁ አውቄያለሁ። በአስራአንደኛው ሰአት ሀያ ሺህ ብር ልጨምርለህ ብለውኝ ነበር። አይሆንም አልኩ።"

"የሚገርም ነው። እየዋሸሽኝ እንዳይሆን?"

"ለምን እዋሽሀለሁ! እናንተ ኪሮስንም ሆነ ዳኛ ልዑልን አታውቋቸውም። እስቲ ልጠይቅህ? ምንም አይነት ስራ የሌለው ሰው እንዴት በየቀኑ ውስኪ ያወርዳል። ኪሮስ ከየት አምጥቶ ነው?

"...በጅማ ሰፈር ዳኛ ልኡል "ትንሹ መለስ ዜናዊ" እንደሚባል ታውቃለህ? ከዳኝነቱ በላይ ቀበሌ አካባቢ ብዙ ገንዘብ ያገኛል። እስቲ ልጠይቅህ? አንድ ትልቅ ዳኛ ቀበሌ ወርዶ የሚርመጠመጠው ለምን ይመስልሀል? ቀበሌ ከመደባት ካድሬ መሰረት ጋር ሲንጐዳጐድ እጅ ከፍንጅ መያዙን ካልዋሸሽኝ በስተቀር በሚገባ ታውቃለህ።"

በድጋሚ አቋረጥኩት፣

"የህግ ስርአቱ አለኝ የሚለውን ትልቅ ሰው ስም እያጠፉህ እንደሆነ እወቅ።" አስጠነቀቅኩት።

በፈገግታ ውስጥ ሆኖ፣

"የቀበሌውን ሊቀመንበር ዘይኑን ቀሰ ብለህ አውጣጣው። አለም ያወቀውን ፀሀይ የሞቀውን ሀቅ ይነግርሀል።የመረጃ እጥረትህን ይሞላልሀል። ውሸማና ሚስትን ያስታረቀው እሱ ነው። ልኡል እንኳን ለናንተ ሰባት ሚስት የማግባት አቅም አለው በግለት።"

አበበ ቀስቶ ሲስቅብኝ አመሸ።

(ዳኛ ልኡል ገ/ ማርያም በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተለያዩ ችሎቶች በሰብሳቢነት ሰርቷል።ግለሰቡ ህገ መንግስቱን በጣሰ ሁኔታ በወረዳ 24 ቀበሌ ፲፩ ውስጥ የህውሀት አባል የነበረ ሲሆን በቀበሌው የሚመደቡትን ካድሬዎች የሚመለምለው እሱ ነበር። ዳኛ ልኡል ከፍተኛ የአቅም ችግር ያለበት ቢሆንም በሀገሪቱ ወሳኝ ተብለው የሚታወሱ ክሶችን ዳኝነት መርቷል። የቴዲ አፍሮ በመኪና ሰው ገጭቶ የማምለጥና በምርጫ 97 የታሰሩ የቅንጅት አመራሮችን ክስ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው። በምርጫ 97 የቅንጅት ክስ ዋና አቃቤ ህግ የነበረው ሽመልስ ከማልና የቴዲ አፍሮ ጠበቃ ሚሊዮን አሰፉ እጅግ ከሚንቋቸው ዳኞች ዋነኛው ልኡል ገ/ማርያም ነው። ሽመልስ ዳኛ ልኡልን፣" ከአቶ መለስ በላይ ህውሀትነቱን ለማሳየት የሚተጋ ባዶ እንቅብ!" ይለዋል። ሚሊዮን በበኩሉ፣" ባጣ ቆየኝ!" ብሎ ይጠራዋል።

እነሆ! ልደቱ በቀበሌ ደረጃ ለወረዳ ምክርቤት ተወዳድሮ ተሸነፈ። ለሽንፈቱ ትልቅ ሚና የተጫወተው አበበ ቀስቶ ለቀበሌው ህዝብ ያደረገው ንግግር ነበር። ይህም የወረዳውና ቀበሌው ህዝብ ከልደቱ በላይ አበበ ቀስቶን እንደሚሰማ አመላካች ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ አበበ ቀስቶ የህዝብ ብሶት የሚያመው ትንታግ ታጋይ ነበር። ከጅማ ሰፈር እስከ ሜክሲኮና ሰድስት ኪሎ በእግሩ እየሄደ የሚያስተጋባ። አበበ ቀስቶ የህዝብ አይንና ጆሮ ነበረ... የነዋሪውን ምሬትና እንግልት በአደባባይ የሚያጋልጥ። አበበ ቀስቶ የኢህአዴግ ካድሬዎችን ንቅዘት እየተከታተለ የሚያጋልጥ አሸባሪ ነበር። ኢህአዴግን በማሸበሩ ምክንያት በሽብርተኝነት ተከሶ ወደማይቀርለት ወህኒ ወረደ። የፀረ ሽብርተኝነት አዋጁ

ኢህአዴግን የሚያሸበር እንደ ሽብርተኛ ይቆጠራል የሚል አንቀጽ እንደሌለው አውቃለሁ።)

***

ወደ ወረዳ 20 (ቄራና ጎፋ) ያመራው ካድሬ የተቃዋሚ አንድ እጩ አስወጥቶም፣ የግል ተወዳዳሪዎች በግፉ አስገብቶም ሳይሳካለት ቀረ። የወረዳ 20 ህዝብ ኢህአዴግን ከፓርላማም ከአዲሳባ ከልል ምክር ቤትም አባረረ። የቄራና ጎፋ ህዝብ ኢህአዴግ ያቀረበለትን ዶክተር፣ ኢንጂነር፣ ጋዜጠኛና ከፍተኛ ነጋዴ ወደ ጎን ትቶ መቃብራቸው የተማሰ፣ በምርኩዝ የሚሄዱ፣ ማንበብና መጻፍ የማይችሉ የመኢአድ አባላትን መረጠ። ይህም ህዝቡ እንደ ወረዳ 24 ሁሉ ኢህአዴግ ላይ ያለውን የመረረ ጥላቻ ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ሆነ። እንደ እውነቱ ከሆነ የስምኦን ልጅም ሆነ አቶ መለስ ወረዳ 20 መጥተው ቢወዳደሩ ኖሮ ወይ ለክብራቸው ሲባል ኮሮጆ አስቀድሞ ይገለበጣል፣ አሊያም የሽንፈት ጽዋቸውን ይጎነጫሉ።

***

የወረዳ 21/22 ነዋሪም ተመሳሳይ እርምጃ የወሰደ ቢሆንም በቆጠራው ወቅት በተሰራ ማጭበርበር ኢህአዴግ ተረፈ። በወረዳው የትግራይ ተወላጅ ይበዛል በማለት "የትግራይ ህዝብ በወረዳ 21 ኢህአዴግን ታደገ" የሚል ማጭበርበሪያ እንዲናፈስ ተደረገ።

የወረዳ 21/22 ምርጫ እንዲመራ የተመደበው ነባር የህውሀት ታጋይ ገ/እግዚአብሔር "እግዜሩ" ይባላል። መጠሪያውና ግብሩ ለየቅል የሆነ ሰው!!

አንዳንዴ ስምን ሰይጣን ያወጣዋል።

የካዛንችሱ ስውር መንግስት ለእግዜሩ ተነግረው የማያልቁ ወንጀሎችን እንዲሰራ ሙሉ ስልጣን ሰጥቶት ነበር። እግዜሩ በስርአቱ ውስጥ ካሉት ሶስት ቁልፍ የዞን ካድሬዎች አንዱ ነበር። መቀመጫውን ሚክሲኮ በማድረግ ሰቅጣጭ ግፎችን ሰርቷል። ብዙ ሰዎችን ያለወንጀላቸው አሳስሯል፣ ከስራ አባሯል፣አገር ጥለው እንዲወጡ አድርጓል። የግለሰቦችን፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቢሮዎችን በለሊት በመክፈት አስበርብሯል፣ ዶክመንት ኮፒ አድርጎ አስወጥቷል።

በእግዜሩ የስለላ መዋቅር የመጀመሪያውን ገፈት የቀመሰው የዞኑ ሊቀመንበር የነበረ መላኩ የሚባል ካድሬ ነበር። መላኩ በከተማዋ በህቡዕ የተቀጣጠለውን የጉራጌ መራሽ አብዮት ከሚመሩት የጉራጌ ልጆች አንዱ ነበር። የአብዮቱ ጥንስስ ወደ አመፅ ተቀይሮ በትላልቅ ሰልፎች መታጀብ ሲጀምር (መስቀል አደባባይን ጨምሮ) መላኩ ግንባር ቀደም መሪ ነበር።

እግዜሩ በበኩሉ የሊቀመንበሩን እያንዳንዷን እንቅስቃሴ በአይነ ቁራኛ መከታተል ይጀምራል፣ ስልኩን ይጠልፋል፣ ማታ ማታ ቢሮውን ከፍቶ በመግባት ዶክመንቶችን ኮፒ አድርጐ ይወጣል። መላኩ አማተር አብዮተኛ ነበርና ከላይ እስከ ታች የተዘረጋውን የሚስጥር አደረጃጀት አሳልፎ ይሰጣል። ለጥንስሱ መጨናገፍ አስተዋጽኦ ያበረከታል። የፓለቲካ ህይወቱም በዛው ፍፃሜ ያገኛል።

እግዜሩ በዛኑ ውስጥ የሚገኙና ጥበቅ ክትትል የሚደረግባቸውን ተቋማት ማስተር ቁልፍ በማዘጋጀት ዶክመንቶችን ያሰርቃል፣ ኮፒ ያስደርጋል። ቢሮአቸው እንዲሰበር ካደረጋቸው ውስጥ በወረዳ 21 ጽ/ቤት ግቢ ውስጥ የሚገኘው የአዲሳባ ሴቶች ማህበር፣የልደታ ቤተክርስትያንና የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ጉባኤ (ኢሰመጉ) ይገኙበታል። የአዲሳባ ንግድ ምክር ቤት ከእግዜሩ የስለላ ወጥመድ ማምለጥ አልቻለም። የንግድ ምክር ቤቱ የተወያየባቸው አጀንዳዎችና ቃለ ጉባኤዎች በቀጥታ ይደርሱታል። ይህንን የሚፈፅምለት ታደለ ይመር የሚባል በንግድ ምክር ቤት ውስጥ ከፍተኛ ስልጣን ላይ የሚገኝ ሰው ነበር... ልማታዊ ባለሀብት።

(ታደለ ይመር በንግድ ምክር ቤት ውስጥ የአገልግሎት ዘርፍ ሀላፊ ነበር። ይህ ሲጠሩት አቤት ሲልኩት ወዴት የሆነ ሰው በካድሬው ዘንድ "የእርጐ ዝንብ" የሚል ስያሜ ተሰጥቶት ነበር። የምይገኝበት ቦታ የለም። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አሳፋሪ ተግባሮች ከፈፀሙ ሰዎች አንዱ ነው። በተለይም በኤርትራ መገንጠል ወቅት የኢትዮጵያን ህዝብ ወክለ ተበሎ ኤርትራ በመሄድ " እኛ የኢትዮጵያ በተለይም የአማራ ተወላጅ የሆንን ሰዎች ስለፈፀምንባችሁ ግፍና በደል ይቅርታ እንጠይቃለን" የሚል ንግግር አድርጓል። ቅሌት አንዴ ከተጀመረ አያልቅምና የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ሲጀመር ደግሞ ንግድ ምክር ቤቱን በመወከል በየአዳራሹ "ሻእቢያ ይደመሰሳል፣ የኤርትራ ህዝብም ልኩን ያውቃል" የሚል ቀራርቶ አሰምቷል...

ታደለስ ታድሏል...
የማይጣላ ጭንቅላት
ተሸክሞ ይዞራል።)

እግዜሩ ትላልቅ የሚባሉ የኢህአዴግ ካድሬዎችን ሳይቀር ደም እንባ አስለቅሷል። የአምባሳደር ገነት ዘውዴ የልቅሶ ታሪክ ጅማሬ በእግዜሩ አማካኝነት ነበር።

እንዲህ ነበር የሆነው።

በምርጫ 92 በወረዳ 21/22 ኢህአዴግን ወክላ ለፓርላማ እጩ ሆና የቀረበችው የትምህርት ሚኒስትሯ ወ/ሮ ገነት ዘውዴ ነበረች። እግዜሩ ደግሞ ምርጫውን በበላይነት ከመምራት በተጨማሪ በዚሁ ወረዳ ለከተማ ምክር ቤት እጩ ሆኗል።

ምርጫው ጥቂት ሳምንታት ሲቀሩት የሁሉም ወረዳ እጩዎችን የስራ ስምሪት ለመስጠት ሜክሲኮ ዙን ጽ/ቤት ጠርተናቸው ነበር። ወይዘሮ ገነት ሀገር ሰላም ብላ በስብሰባው ታድማለች። ጠንከር ያሉ የግምገማ ነጥቦች ሲነሱ እሷም ፀሀዩ መንግስታችንን እንዲጠላ ያደረጉት የበታች ካድሬዎች ናቸው የሚል ወቀሳ አዘል አስተያየት ትሰጣለች። በንግግሯ የተበሳጨው እግዜሩ፣

"... ገነት እኔ ህይወቴን ሙሉ ከህዝብ ጋር እየተገናኘው የድርጅትና ፕሮፓጋንዳ ስራ ሰርቻለው። የህዝብ ሀሳባ አዳምጫለሁ። እውነቱን ንገረኝ ካልሽ እንዳንቺ ህዝብ የሚጠላው ሰው ኢጋጥሞኝ አያውቅም!፣ ከሁሉም የሚያሳዝነው ስትወድቂ እኛንም ይዘሽ መግንደስሽ ነው!" አላት።

ክብርት ሚኒስትሯ ተንሰቅስቃ አለቀሰች።ልቅሶው ሲበርድላት፣

"እኔ የኢህአዴግን የትምህርት ፓሊሲ በቁርጠኝነት ከማስፈፀም ውጭ ምን ያደረኩት ነገር አለ? ፓሊሲው ትውልድ ገዳይ እንደሆነ እየገለፀ ያለው ህዝቡና ምሁራኖች ናቸው። እኔ ፓሊሲ የመቀየር ስልጣን የለኝም! ... ስለዚህ ህዝቡ የጠላኝ በፓሊሲው ምክንያት ነው። ርግጥ ከኢህአዴግ በተቃራኒ የቆመው ዶክተር በየነ ጴጥሮስ "ዮዲት ጉዲት! " የሚል ስያሜ ሰጥቶኝ በህዝቡ ጥላቻ ላይ ቤንዝን ጨምሯል።" የሚል አስገራሚም አነጋጋሪም ምላሽ ሰጠች።

ክብርት ሚኒስትሯ በፓሊሲው ትውልድ ገዳይነት ላይ ጥርጥር የላትም። ባለስልጣናት ልጆቻቸውን ከተቻለ እንደ ሽማግሌው ስብሀትና አርከበ እቁባይ ከሁለተኛ ደረጃ ጀምሮ ውጭ ሀገር ፣ካልተቻለ ደግሞ የሀገሪቷን የትምህርት ስርአት በማይከተሉ የሀገር ውስጥ ምርጥና ውድ ትምህርት ቤቶች እንደምናስተምር ታውቃለች። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት አስረኛ ክፍል ማለቁ ህብረተሰባዊ ውግዘት እየደረሰበት እንደሆነ ለሁሉም ግልፅ ነው። ዩንቨርስቲ ከሚማሩ ተማሪዎች ስማቸውን በአግባቡ መፃፍ የማይችሉ መኖራቸው ሀቅ ነው። የኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ብቃትና አለም አቀፍ ተቀባይነት ቁልቁል ወደ ታች አየተምዘገዘገ እንደሆነ የእለት ሪፓርቷ ሆኗል።

እናም ክብርት ሚኒስትሯ ራሷ ባልፈጠረቸውና መቀየር በማትችለው ሽውራራ ፓሊሲ ምክንያት "ዮዲት ጉዲት" የሚል ስያሜ ወጥቶላታል።ፕሮፌሰር በየነም ቢሆን የፈሪ ዱላ ካልሆነ በስተቀር ፓሊሲውን ማን እንደቀረፀው

ጠንቅቆ ያውቃል። በነካ እጁ የፓሊሲውን ባለቤት "ግራኝ መህመድ!" ቢለው የጀግንነት ካባ እናለብሰው ነበር።

የሴትየዋ የለቅሶ ምንጭ ከቁጥጥሯ ውጭ በሆነ ነገር እንደሆነ ቆይቶ የተገለፀለት እግዜሩ፣ "...ገነት እኔ ያልኩት ጊዜ ሰጥተሽ ከእኛ ጋር እንደ እጩ ተንቀሳቀሽ ነው፣" ብሎ አለዘባት። ወርቃአበባ የምትባል የዞን ካድሬ አብራት እንድትዞር መደበላት።

ክብርቷ የትምህርት ሚኒስቴር ስራዋን ትታ ወረዳ 21/22 ሰነበተች። እግሯ እስኪላጥ ተንከራተተች። በመንደር ውሻ እስከመነከስ ደረሰች።

ምርጫው ሳምንት ሲቀር ባለችው እሁድ አመሻሽ ላይ ሚኒስትሯና ወርቃአበባ ለሳምንታዊ ግምገማ ዞን መጡ። ካድሬዎች እስኪሰባሰቡ ድረስ እኔ ቢሮ አረፍ አሉ። የሚኒስትሯ አይን ከወትሮው በተለየ እንደ ስጋ ቤት አንፓል አብርቷል። ከጫት ላይ ተነስታ የመጣች ትመስላለች...ወርቅአበባን ማን ያምናታል!?

ቅስቀሳው እንዴት እየሄደ እንደሆነ ጠየኳቸው። ሚኒስትሯ እንደ ከዋክብት የደመቀ አይኗን ተክላ፣

"የዛሬው የምረጡኝ ቅስቀሳ ቡና አብሮ በመጠጣት ነው ተብሎ ሀያ ቤት ሂጀ ሀያ አንድ ስኒ ቡና ተጋትኩ" አለችኝ።

ወርቃአበባ ከአፏ ተቀብላት፣

"አየሽ አይደል ገነት! ገኒ! ሴቶቹ እንዴት እንደሚወዱሽ!... በተለይ የልደታ ቤተክርስትያንን ችግር እንደምትፈቺላቸው ቃል ስትገቢ የዳዊት ዘር ለዘላለም ይግዛን አሉሽ "በማለት ዉሉሰአቸውን አዳነቀች።

እኔን ደግሞ በጥቅሻ መታችኝ... የልደታዋ ንግስት!... ወርቅአበባ።

ክብርት ሚኒስትሯ ደስ አላት።

ጨዋታችንን ቋጭተን ወደ ስብሰባ አዳራሹ ስንሄድ ወርቅአበባን ወደ ኋላ ገሎተት አድርጌ፣

"አንቺን ማን ያምናል? በርጫ ወቅጠሽ አጠጣሻት እንዴ? አይኖቿ ጡት መያዣ አስፈለጋቸው" አልኳት።

ከት ብላ እየሳቀች፣

"የእግዜሩን ግምገማ ለማስቀየስ ነው። ታገል (ታገል ጌታቸው ባለቤቷ ነው) ከቤት ስንወጣ ለእግዜሩ አንብቢለት ብሎ ከሚወደው ገጣሚ መፅሀፍ ጽፎ ሰጥቶኛል።"

"እስቲ አንብቢልኝ?"

"የእግዜሩ ስብሰባ ሲያልቅ ገነትን ወደ ኋላ ካስቀራት አነብልሀለሁ።"

ሳታስበው ወረቀቱን መነጨኳት።

በጠራ ጨረቃ በኩለ ለሊት፣
አይኖቿ ሲያበሩ እንደክዋክብት፣...

ሳልጨርሰው መለስኩላት። በቃሌ አነበነብኩት።
አንገቷን አየነቀነቀች "አንተና ታገል?..." አለች።
"ይልቁንስ ቅድም የዳዊት ዘር? ምናምን ያልሽው። አልገባኝም?"
"ተዋት ባክህ! የልደታ ህዝብ ምን እያለ እንደሆነ አላወቀችም!" በማለት ጣቷን እየቆጠረች ዘረዘረች፣

አፈ ጉባኤ ዳዊት ዮሀንስ የሚኒስትር ገነት ዘመድ፣
የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ዶ/ር ከበደ የሚኒስትር ገነት ባለቤት፣
የምርጫ ቦርድ ሀላፊው አሰፋ ብሩ የሚኒስትር ገነት ዘመድ፣
የአዲሳባ ካቢኔ ወይዘሪት ጣይቱ አሊ የሚኒስትር ገነት እህት...

ከብዙ አመታት በኋላ እኔም በተራዬ ለወርቃአበባ በቀጭኑ ሽቦ አንድ በግራ ሌላ በቀኝ ጨምሬ ነገርኳት: -

የኮሙዩኒኬሽን ጽ/ቤት ጭንቅላት ገነነ አሰፋ የአምባሳደር ገነት ወንድም፣ የኢህአዴግና የበረከት ራስ ምታት ፕሮፌሰር ዳኛቸው አሰፋ የአምባሳደር ገነት ወንድም ...

የዳዊት ዘሮች...
ዘላለም ይግዙን!

***

እግዜሩ በቂርቆስ የትግራይ ተወላጅ ስለሚበዛ ኢህአዴግ በአብላጫ ድምፅ እንደሚያሸንፍ አስቀድሞ እንዲነገር አደረገ። የምርጫ አስፈፃሚዎችንና ታዛቢዎችን ከድርጅት መለመለ። ምርጫ ቦርድን ተክቶ አረንቴሽን ሰጠ። የፓሊስ ሀይሉን በስም ዝርዝር ለይቶ በየጣቢያው አስመደበ። የወረዳ 21/22 ከፊል የምርጫ ኮሮጆ አስቀድሞ ተገለበጠ። ተቃዋሚዎች መረጃ ደርሷቸው ለምርጫ ቦርድ ቢያመለክቱም በሬ ወለደ እንደሆነ በምርጫ ቦርድ ሀላፊው አሰፋ ብሩ መግለጫ ተሰጠ...

የዳዊት ዘር!

***

የእግዜሩ የመጀመሪያ መጨረሻ ...

እግዜሩ የካዛንችሱ መንግስት ሲንኮታኮት አብሮ ወደቀ። በአዲሳባ የአነ ተወልደን ቡድን በመደገፍ ቀንደኛ ሆኖ ወረቀት የበተነውና ካድሬውን በፀረ -

መለስ ያደራጀው እሱ እንደሆነ ሞንጀሪኖ አጋለጠች። የህቡዕ አደረጃጀቱ ማታ ማታ ስብሰባ ሲያደርግ የነበረው በሜክሲኮ እንደሆነ ተረጋገጠ። ማምለጫ መንገድ ሲያጣ አቶ መለስን ይቅርታ ጠየቀ። አቶ መለስ እንደ ሌሎቹ አልራራለትም፣ "በዛገ ቢላዋ የድርጅቱን አንገት ዘከዝከህል" ብሎ በቅጣት መልኩ የትግራይ በረሀ ሰደደው።

እግዜሩ ለሶስት አመት ያህል የትግራይ ተራራን ሲቧጥጥ ከረመ። መስመር ማስተካከሉና እርምት መውሰዱ ሲረጋገጥ የተዘጋጀለት የሙስና ፋይል በጐንዮሽ አንዲደርሰው ተደረገ፣ "ሲያዩህ ሌባ ትመስላለህ" ብሎ እንዳላባረረ የእሱ ንቅዘት የሚያልቅ ሆኖ በፋይል ተጠርዞ ተሰጠው። በየአመቱ በሚሊዮን ብሮች የሚዘረፍበትን የአየር ጤና ኬላ (ጉምሩክ) ህሩይ የሚባል የቅርብ ዘመዱን ሀላፊ አድርጐ ሲያሰራ እንደነበር፣ ሲኖርበት የነበረውን የቀበሌ ቤት ለወንድሙ ስም አዙሮ መስጠቱ፣ ኤርትራዉያን ናችሁ በማለት በግፍ ከቪላ ቤታቸው ካፈናቀለ በኃላ እሱ ጉበቶበት መኖር እንደጀመረ፣ በምርጫ 97 ማግስት ኮልፌ ቀራንዮ ላይ አርከበ እቁባይ አይን መሬት እንደሰጠው።

እናም እግዜሩ ይህንን የታሸገ የሙስና ፋይል ይዞ አዲሳባ መጣ። አቶ መለስ የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቭዥን የትግርኛ ፕሮግራም ዋና ሀላፊ አድርጐ ሾመው።የአድርባይ ፊትአውራሪ ከሆነው ዘርአይ አስከዶም ጋር ተቀላቀለ። የኢቲቪ የትግርኛ ፕሮግራም ከእንጨትነት ወደ "አሞራ ስጋነት" ተቀየረ...

እምበር ተጋዳላይ!!

***

እኔና ፍስሀ በራስ ሆቴል ውይይታችን በቀጥታ ከመራናቸው አምስት ወረዳዎች ተሻግረን ወደ ሌሎቹ ሄድን። በአብዛኞቹ በከፉ ሁኔታ ፀረ ዲሞክራሲ ድርጊቶች የተፈፀመባቸው ነበሩ።በተቃዋሚ እጩነት ይመዘገባሉ ተብሎ የተጠረጠሩ ነዋሪዎች እስከመታሰር የተካሄደባቸው፣ እጩ ሆነው ከተመዘገቡ በኋላ የስም ማጥፋት ዘመቻ ተካሂዶባቸው ረሳቸውን ያገለሉ፣ ተቃዋሚዎች የምርጫ ታዛቢ እንዳይኖራቸው የተደረገበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር። በተለይ በአዲሳባ በሚገኙት 29 የገጠር ቀበሌዎች የተካሄደው ምርጫ አሳፋሪ ነበር። የኢህአዴግ ታዛቢ ብቻ የነበረበት ምርጫ፡ ምርጫ አስፈጻሚው፣ ቆጣሪው፣ ታዛቢው በሙሉ ኢህአዴግ... የገጠሪቷ ኢትዮጵያ ትንሹ ግልባጭ።

ይህ ሁሉ የማጭበርበር ስራ ተሰርቶ በነጋዴውና ህዝቡ የተቀናጀ ስራ እነ አሊ አብዶና ምክትሉ የነበረው ካሊድ አብድርህማን የሸንፈት ፅዋ ተጐንጭተዋል። ምንም እንኳን በቆጠራው ሰአት በሰሩት አከሮባት ወደ ምክርቤት ቢገቡም።

እንዲህ ነበር የተደረገው።

በአብዛኛው ምርጫ ጣቢያዎች የተቃዋሚ ታዛቢዎች ባለመኖራቸው ቆጠራ ተጀምሮ ሳይጠናቀቅ ለሊት ዘጠኝ ሰአት ተቋረጠ። ምክንያቱ ደግሞ ታዛቢዎች ስለተዳከሙ እረፍት አድርገው ይምጡ የሚል ነበር። በከተማዋ የተሰማራን ካድሬዎች በየዞናችን በማደር የአዲሳባን ውጤት በየደቂቃዋ እንከታተል ስለነበር አስደንጋጭ ውጤቶችን መስማት ጀመርን። የመጀመሪያው መርዶ የተፈራ ዋልዋ መሸነፍ ሆነ። ለዋልዋ ልጅ ከልቤ አዘንኩኝ። የዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት እስረኛ እንደሆነ ስለማውቅ።

ቀጥሎ የደረሰን የአሊ አብዶና ካቢኔዎቹ ሆነ። ሁሉም ላይ ህዝቡ በትሩን አሳርፉል: ካሊድ (ም/ል ፕሬዝዳንት)፣ ታጋይ ማሚት (አስተዳደር ዘርፍ)፣ ጣይቱ (የምክር ቤት ሀላፊ)፣ ቶፊቅ (ኢኮኖሚ ዘርፍ) ዘመዳ (የካቢኔ አባል) በዝረራ ተሸንፈዋል።

ጠዋት ታዛቢዎች ተመልሰው ቆጠራ ሲካሄድ የነበረው እንዳልነበር ሆነ። ኮሮጆዎች ግልብጥብጣቸው ወጣ። አሊና ካሊድ ቶፊቅ፣ ጣይቱንና ዘመዳን ትተው አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ከመሀል ኮኩበ ያላትን ባንዲራ እያዉለበለቡ ማዘጋጃ ቤት ገቡ።

***

ምእራፍ ሰባት

ዘባተሎው መሪ!

"ወይ አዲስ አበባ ወይ አራዳ ሆይ፣ አለ አሊ አብዶ አላየሽም ወይ"
(ሪፓርተር ጋዜጣ)

ዝርክርክ! ዘባተሎ! ደንታ ቢስ!

በጨፈ እየተካሔደ ባለው ግምገማ አጠቃላይ ችግሮች ከቀረቡ በኃላ ወደ ግለሰብ አውጫጭኝ ተገባ። የመጀመሪያው አቅራቢ አሊ አብዶ ሆነ። ሰውየው ተደናግጧል። በከተማው ግንባር ቦታ የገነባው ቪላና ፎቅ እንቅልፍ ነስቶታል...

አይውጠው ነገር...!

ቢሆንም ግን አልሞት ባይ ለመሆን አይኑን በጨው አጥቦ ጥቂት ዘላበደ:- የሙስና ችግር እንደሌለበት፣ ለጥቅም የዘረጋው ኔትወርክ እ ንደሌለው፣ አዳዲስ አስተሳሰቦችን ለመቀበል ችግር እንደሌለበት አስረዳ።... ቁልፍ ችግሩ "አደራጅቶ መምራት ያለመቻል" እንደሆነ ገለፀ።

ርግጥም ተምታቶበታል...

ሽሮ ቢደነፉ እንጀራ እስኪቀርብ ነው!

አባይ አሊ ያላነሳው ነገር ካለ ቤቱ እንዲያሳየው እድል ሰጠ። በአሊ አቀራረብ መናደዱ ያስታውቃል። ሁለት እጆች ቀድመው ተቀሰሩ። ማካቬሊያኖቹ ዘርአይ አስግዶምና ኢሳያስ። ለዘርአይ አስቀድሞ ተሰጠው።

ዘርአይ ስራውን እንዲህ በማለት ጀመረ፣

"አሊ! የዝች ከተማ መበስበስና መብከት ተጠያቂው አንተ ነህ። ከሙስና የፀዳው ነኝ የምትለው ቦሌ የገነባኸው የሁለት ሚሊዮን ብር ቤት መሬቱንና ገንዘቡን ከየት አምጥተህ ነው?" ብሎ ጠየቀው።

አሊ በበኩሉ፣

"... መሬቱን ህጉን በተከተለ መንገድ በካቢኔ ውይይት ተደርጐበት በአብላጫ ድምፅ ተወስኖ ነው። ብዙዎቻችን ወስደናል። ቤቱን የሰራሁት አረብ ሀገር ባሉ ዘመዶቼ እርዳታ ነው። የተሰራው ዘርአይ እንደምትለው በሩብ

ሚሊዮን ብር ነው።" በማለት መልስ ሰጠ፣ "የካቢኔ አባላት አብራችሁ ነዋ የዘረፋችሁት?" በድጋሚ ጠየቀው።

"አማርኛህን አስተካክል! በካቢኔ የመወሰን ስልጣን አለን።" ሽሮው ደነፋ።

"ካቢኔውን ወደ አይን ያወጣ ዝርፊያ የወሰደከው አንተ ነህ። ይባስ ብላችሁ መሀል ቦሌ ላይ የህዝብ ንብረት ትዘርፉላችሁ?"

አሊ ተናደደ፣

"ስነስርአት አድርግ ዘርአይ! ...ዘራፊ እንድትለኝ አይደለም እዚህ የተቀመጥኩት። ሀቁን ተናገር ካልክ አንተን እንዲህ ያብንነህ ሌላ ነገር ነው። አንተን ጨምሮ የፌዴራል ተቋማት ኢህአዴግ ኮሚቴዎች እኔ ጋር መጣችሁ ለእኛም የቤት መስሪያ ቦታ ስጠን ብላችሁ ጠየቃችሁኝ። ደብዳቤ ፅፋችሁ አምጡና በካቢኔ እናየዋለን አልኳችሁ። በተለይ አንተ ወደ ታላ ቀረት ብለህ ደብዳቤ መፃፍ አደጋ አለው ድርጅቱ ሊሰማ ይችላል አልከኝ።"

አዳራሹ በሳቅ ተሞላ...

ለባለጌ ገድሉ ውርደቱ!

አባይ ግምገማው አቅጣጫ እንዳይስት በማሰብ፣

"የዘርአይን በራሱ ጊዜ እናየዋለን። እነ አሊ ቦሌ ላይ መሬት የተቆራመታችሁት ወንጀል ነው። እርምት ካልተወሰደበት በህግ ሊያስጠይቅ ይችላል። ለጊዜው ስለ ህግ የምናወራበት ስአት አይደለም። እኔ ባለኝ መረጃ የተዘረፈው መሬት የትምህርት ቤት ቦታ ተቆርጦ ነው፣ ይህ ደግሞ የከፋ ያደርገዋል።" አለ።

አጠገቤ የተቀመጠው ፍስሀ "አባይ መቋጠር ጀመረ" ብሎ ማስታወሻዬ ላይ ፃፈ።

ቀጥሎ ለደህንነት ሀላፊው ኢሳያስ ወ/ጊዮርጊስ ተሰጠው። ኢሳያስ የድንቁርና አክሊል ያጠለቀ የአቶ መለስ የቁርጥ ቀን ልጅ ነው። እንደለመደው በእብሪት የታጨቀ ስድብ ካቀረበ በኃላ በማጠቃለያው፣

"አሊ አዲሳባን የመሰለች ውስብስብ ከተማ ቀርቶ ወረዳ ለመምራት ብቃት ያንሰዋል። በዛ ላይ ዝርክርክ ነው" አለ።

አባይ ተመሳሳይ ይዘት ያለው ትችት አቅርቦ ማሳረጊያውን "አሊ ዝርክርክ ብቻ ሳይሆን ደንታ ቢስና ዘባተሎ ነው" በማለት አጠናከረ...

ዝርክርክ ! ... ዘባተሎ!!

አሊ በተቀመጠበት ወንበር ሲፈረካከስ ተመለከትኩት።

የእለቱ ግምገማ በዚህ የአባይ ቃል ተፈፀመ።

ለቃል አቀባይነት የተመረጥነው እኔና ሉልሰገድ ወደኋላ እንድንቀር ተነግሮ ሌላው ተበተነ። እንድንቀር የተደረገው ከኢህአዴግ ቢሮ ጋዜጠኞች እየመጡ ስለሆነ የእለት ውሎውን እንድንገልፅላቸው እንደሆነ ተነገረን። አፍታም ሳይቆይ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ አዘጋጆቹ ሴኮቱሬና ፍሬህይወት አያሌው ተያይዘው መጡ። ውሎውን በጥቅሉ ነግረናቸው በግለሰብ ደረጃ እየተነሱ የነበሩት ማጠቃለያ ስላልተሰጣቸው በንጋታው አመሻሽ ላይ እንደምንገልፅላቸው ተስማምተን ተለያየን።

ወደ ቤቴ ገብቼ ሬዲዮ ስከፍት ሬዲዮ ፋና ሰበር ዜና እያነበበ ነው። በዜናው መዲናይቱን የማደስ ስራ መቀጣጠሉን ያበስራል። ይህን ተከትሎ በአመራሮቹ ላይ ግምገማ እየተካሄደ መሆኑና በእለቱ ውሎ የአዲሳባ ፕሬዝዳንቱ አለ አብዶ መገምገሙን ያትታል። አቶ አለ ከተማዋ እንደ ግመል ሸንት ወደ ታላ እንድትጐተት ያደረገ ደንታ ቢስና ዝርክርክ መሪ እንደሆነ መግባባት ላይ መደረሱን ከግምገማው ቃል አቀባይ መረጃ እንዳገኙ ገለፁ።

ደንታ ቢስ!... ዝርክርክ!!

አሊን በተመለከተ ለፍሬህይወትና ሴኮ ምንም መረጃ ባልሰጠናቸው ሁኔታ እንደዛ አይነት ዜና መለቀቁ አስገራሚ ነበር።

በንጋታው ጠዋት ረፈድ ብሎ የተጀመረው ስብሰባ በአሊ እንባ የታጠበ ሆነ። በእጁ የያዘው የግል ፕሬስ በርዕሰ አንቀፁ በሳለው ካርቶን ስዕል የአሊ ቢሮ በዶሴ ተሞልቶ፣ የሚሰራው ግራ ገብቶትና ንፍጡ ተዝረክርኮ የሚያሳይ ነበር። ይህም ቢሆን አስቀድሞ የተሰራ ካልሆነ በአንድ ምሽት ተፅፎ ለህትመት አይደርስም።

አሊ በሲቃ ተሞልቶ፣

"የእኔስ ይሁን እዳው ገብስ ነው! ቢያንስ ለባለቤቴና ልጆቼ እንዴት አይታሰብም? ባለቤቴ ምሽት ላይ ሀዘን ቤት ሄዳ መሳለቂያ ቢያደርጓት እያለቀሰች መጣች። ዛሬ ጠዋት ልጆቼ ትምህርት ቤት ቢያስጨንቋቸው ደውለው ደንታ ቢስና ዝርክርክ ማለት ምን እንደሆነ ጠየቁኝ" አለ።

ካድሬው በቅንብሩና ቤተሰቦቹ ላይ በደረሰው ውርደት አዘነ እንጂ በአሊ አብዶ ላይ የቀረበበት ስድቦች የሚያንስበት እንደሆነ ያውቃል። አሊ አብዶ በብዙ ጉዳዮች ወንጀለኛ ነው። ኢትዮጵያዊነት እና የጋራ ማንነት እሴቶቻችን እንዲጠፉ አድርጓል። ህዝቡ በዘር መከፋፈሉ ሳያንስ በሀይማኖት ጐራ ለይቶ እንዲጫረስ ለማድረግ ቀን ከሌት የሰራው እሱ ነው። የተጣባውን የንዋይ ፍቅር ለማሟላት ህገ ወጥ መስኪዶችን አስገንብቷል። በዚህ ምክንያት ብዙ ዜጐች እርስ በራስ ተጋጭተዋል። በመንግስት ታጣቂዎች ተገለዋል። የህዝብ ንብረት የሆነው መሬት እንዲዘረፍ አድርጓል። ይህም ከአስር ቢሊዮን

ብር በላይ የህዝብ ገንዘብ ቀልጧል። ህገመንግስት የሚንዱ መመሪያዎች እንዲወጡ በማድረግ ነዋሪው ከአካባቢው እንዲፈናቀል አድርጓል። የከተማው ህዝብ በማያቋርጥ የድህነትና በሽታ ኡደት ውስጥ ገብቶ እንዲማቅቅ የእሱ ድርሻ ከፍተኛ ነው። በከተማዋ የተካሄዱት የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በሱ መሪነት አሊያም አድርባይነት የተፈፀሙ ናቸው።

ስለዚህም ይህንን የሰውየውን ጥፋቶች ገለጥለጥ አድርጐ ማሳየት አሰፈላጊ መስሎ ስለተሰማኝ አስተያየት ለመስጠት የመጀመሪያው የመዲናይቱ ካድሬ ሆንኩኝ። አሊ በእኔ ላይ የፈፀመውን በደል ስለሚያውቀው የእኔ እጅ በቅድሚያ ተቀስሮ ሲያይ ደነገጠ። እንደማለቀው ገብቶታል። በርግጥም አንድ ቀን በሰፈረኝ ቁና እንድሰፍረው አምላኬን ተማፅኜ ነበር። የጨፈ ግምገማ የያዘውን ድብቅ አላማ ባልደግፈውም የሰውየውን ነውረኝነት ለመግለፅ ከዚህ የተሻለ እድል አላገኝም። የመናገር እድሉ ተሰጠኝ። ተረጋግቼ ነጥብ በነጥብ አቀረብኩ ። አንገቱን ደፉ። ለጨፈው በአጭሩ የተናገርኩት፣ በግል ማስታወሻዬ ደግሞ ዘለግ አድርጌ የፃፍኩት ወግ የሚከተለውን ይመስላል...

***

ሮኬት ሳይንስ◆◆◆

እኔና አሊ አብዶ መጀመሪያ የተጋጨነው በውጭ ጉዳይ ፓሊሲ ስልጠና ላይ ነበር። ስልጠናውን የሚሰጡን እሱና የወጭ ጉዳይ ምክትል ሚኒስትሩ ዶ/ር ተቀዳ አለሙ ነበሩ። ከዶክተሩ ገለፃ ቀጥሎ በነበረው ውይይት በፓሊሲው ላይ ያሉኝን ሁለት ልዩነቶች አንስቼ ተከራከርኩ። እነዚህም ፓሊሲው በኤርትራ መንግስትና በግብፅ ላይ ያስቀመጠውን የተመለከቱ ነበሩ ...

የውጭ ጉዳይ ፓሊሲው ከኤርትራ መንግስት ጋር መቼም ቢሆን ሰላማዊ ግንኙነት አይኖረንም ይላል። ግብፅን በተመለከተ ደግሞ በሚስጥር አሊያም በመንግስት ደረጃ መገለፅ በሌለበት መልኩ ተፅፉል። ግብፅ የኢትዮጵያ ስትራቴጂክ ጠላት እንደሆነችና፣ ሀገሪቷ ጫካ ሳይኖራት 50 ሺህ የሽምቅና የጫካ ተዋጊዎችን አሰልጥና ዝግጁ ያደረገችው ለማን እንደሆነ ሳይታለም የተፈታ እንደሆነ ያሳስባል። በመሆኑም ከግብፅ ጋር የሚኖረን ግንኙነት ይህን ከግምት ውስጥ ያስገባ ሊሆን እንደሚገባ ይገልፃል።

እኔ በበኩሌ ፓሊሲ በአጭር ጊዜ እይታና ስሜታዊነት መፃፍ የለበትም ። የኤርትራ መንግስትም ሆነ ሻዕቢያ ሊቀየሩ የሚችሉበት እድል ዝግ መደረግ የለበትም የሚል ነበር። ግብፅንም ቢሆን ከመልካም ግንኙነትና የጋራ ጥቅምን ከማሳየት ይልቅ ሰነዱ ፀብ አጫሪነትን ያሳያል የሚል ነበር።

ፓሊሲው አንዳችም እንከን የማይወጣለትና ድርጅቱ ተጨንቆ ተጠቦ ያወጣው እነደሆነ በመቆጣት ገለፀ። የኤርትራ መንግስትም ሆነ ህዝብ የጥገኛ ፍላጐታቸውን ለማሳካት የሚንቀሳቀሱ በመሆናቸው ምንም ግንኙነት እንደማይኖር አሳሰበ። ግብፅንም በተመለከተ በአይነ ቁራኛ እየተከታተልናቸው መሆኑንና እኛም በበረሀ የሚዋጋ ሰራዊት እንደምናዘጋጅ ሊያዉቁ ይገባል አለ... ተቆጥቶ!

አጠገቤ ተቀምጦ የነበረው የካዛንችሱ መንግስት አባል የሆነው ፍስሀ መአሲ ወደ ጆሮዬ ጠጋ ብሎ፣

"ዶክተር ብርሀኑ ነጋ ያለው ትክክል ነው! የጠላት አስተያየት ብለን ማጣጣል አልነበረብንም። ይሔ ሰውዬ የሚረባ አይደለም። የአስተሳሰብ ዱኩማንነቱን አሳየ። ሌላው ቢቀር ሻዕቢያንና የኤርትራ ህዝብን መለየት አልቻለም" አለኝ።

(በዛን ሰሞን የአዲሳባን ማስተር ፕላን ከመፅደቁ በፊት ለመተቸት ኤግዚብሽን ማዕከል የምሁራን ስብሰባ ተጠርቶ ነበር። በዛ ስብሰባ ላይ የተገኘው ዶክተር ብርሀኑ ማስተር ፕላኑ ሊያሰራ የሚችል እንደሆነ፣ ግን ደግሞ በአሊ አብዶ ብቃትና ችሎታ ይፈፀማል የሚል እምነት እንደሌለው በግልፅ ተናገረ። የዶ/ሩ አስተያየት በአህዴድ ደጃፍ ቁጣን ቀሰቀሰ። ዶክተሩን በረከት ስምኦን ልኮት እንደሆነ መነገር ተጀመረ። በወቅቱ መልካም ግንኙነት እንደነበራቸው ይወራ ስለነበር... የዛሬን አያድርገውና!... ግራም ነፈሰ ቀኝ የዶክተሩ ቃል በተግባር ተፈጽሟል።)

በዉጭ ጉዳይ ፓሊሲው ላይ አስተያየት መስጠት የጀመረው ዶክተር ተቀዳ እኔን ደግፎ ተናገረ። አንድን መንግስት መቼም ቢሆን ዘላቂ ጠላት አድርጐ ማስቀመጥ የተለመደ ፓሊሲ እንዳልሆነ። በሚስጥር መያዝ ያለባቸው እውነቶች በተለይም ወታደራዊ መረጃዎች በመንግስት ከሚገለፁ ይልቅ በሌሎች አካላት ቢነገሩ ዲፕሎማሲያዊ በሆነ መንገድ መልዕክቱን ማስተላለፍ እንደሚቻል አሰረዳ። ከልምድ አኳያም ቢሆን ሀገሮች የመንግስት ተቃዋሚ ፓርቲዊችን፣ መንግስታዊ ያልሆኑና ለሀገር ተቆርቋሪ የሆኑ ድርጅቶችንና የሚዲያ ተቋማትን እንደሚጠቀሙ አብራራ። የውጭ ጉዳይ ፓሊሲው ባጠቃላይ ከአረብ ሀገሮች ጋር የሚኖረውን ግንኙነት በስጋትና ጥርጣሬ ላይ እንዲቃኝ ማድረጉ አግባብ እንዳልሆነ ገለፀ።

በመሆኑም የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፓሊሲ መቀየር አለበት ብሎ እንደሚያምን፣ ግን ደግሞ ፓሊሲ ከመለወጥ አንፃር እሱ አንዳችም ሚና እንደሌለውና ለፃፉት ሰዎች መልእክታችንን እንደሚያደርስ በቅንነት ገለፀ። የዶክተሩ ንግግር በራሱ አግራሞትን የፈጠረ ነበር። አንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚንስትር በራሱ ተቋም የሚፈፀመውን ፓሊሲ ችግር አለበት ግን ደግሞ የመወሰን ስልጣን የለኝም ሲል ምን ሊባል ይችላል?...

ያዉም የዶክተረ ሚኒስትር!!

የዛኑ እለት ማታ አሊ አብዶ ቢሮው ጠራኝ ። ሄድኩኝ። ለመቀመጥ እንኳን እድል ሳይሰጠኝ፣

"ሰድበህ ለሰዳቢ ዳረከን፣ ተቀዳ ኢህአዴግ አለመሆኑን እያወክ እንዴት እንደዚህ አይነት አስተያየት ትሰጣለህ? በዲፕሎማሲው ዙሪያ የስዩምን ክፍተት ይሞላል ተብሎ እንጂ ፀረ - ኢህአዴግ መሆኑን ጠፍቶህ ነው?" አለኝ።

ሰለ ተቀዳ እንደማላዉቅ ገለፅኩለት። ርግጥም በተባራሪ ከሚወራው ዉጭ ስለ ዶክተሩ የማውቀው ነገር የለኝም። የአቶ ስዩምን የብቃት ማነስ የሸፈነለት እሱ እንደሆነ፣ ካለፈው ስርአት ጋር ንክኪ እንዳለው፣ ጐበዝ እግር ኳስ ተጨዋች እንደነበር ሲወራ ሰምቻለሁ። በፓሊሲው ላይ ልዩነት ያነሳሁት በትምህርት ቤት የአንድ ተቋም ራዕይ፣ ፓሊሲና ስትራቴጂ እንዴት እንደሚቀረፅ የተማርኩትን እንደሆነ ጨምሬ ነገርኩት።

አሊ ጨሰ ።

የሰነፍ ስድቡን አዘነበብኝ።

"ፓሊሲውን ያወጡት ሰዎች ያልተማሩ ይመስልሀል? ከልጅ አእምሮ በላይ የሆነ ጉዳይ ስለፃፉ ነው ሮኬት ሳይንስ የሆነብህ!" አለኝ። ዝም አልኩት፣ እንዲገባው ብዬ።

ትንፋሽ ወሰዶ፣

"የምትሰማ ከሆነ ኢህአዴግ ሆኖ በድርጅቱ መርሆዎችና ፓሊሲዎች ላይ ልዩነት ማንሳት አይቻልም።ዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት ማክበር አለብህ። አለበለዚያ ግን ድርጅቱን ለቀህ መውጣት ይኖርብሀል" ብሎ ዛቻ አዘል ማስጠንቂያ ሰጠኝ።

ብናደድም የመጨረሻውን ድንጋይ ሳልወረውር መውጣት ስላልፈለኩ፣

"አቶ አሊ እኔ እስከሚገባኝ ፓሊሲ የሚቀረፀው ከዚህኛው አማራጭ ይሄኛው ይሻላል በሚል ስሌት መሰለኝ። በመሆኑም የድርጅታችንን አማራጭ ሆነ ተግራሪውን በአውቀት ላይ በመመስረት ብንገነዘበው የተሻለ ይመስለኛል" በማለት በስላቅ ተናገርኩት።

እንደወፈፌ አደረገው። ስሜን እየጠራ፣

"ቀስ ብለህ እደግ!... እንደ ጓደኞችህ ብትበስል ይበጅህል!" በማለት

አመናጭቆ አሰናበተኝ።

***

በንጋታው ጠዋት ዶክተር ተቀዳ በፓሊሲው ላይ የተደረጉ ማሻሻያዎች የያዘች አንዲት ወረቀት በተነ። ማሻሻያው በፓሊሲው ላይ የኤርትራ መንግስትን በተመለከተ የተቀመጠው ሙሉ ለሙሉ ተሰርዟል ይላል። አሊን በሾኬ አየሁት ፣እሱም እያየኝ ነው። ትላንትና ዝም ያለው ካድሬ ስለማሻሻያው ትክክለኝነት ለመግለፅ እጁን ችቦ አደረገ።

በምሳ እረፍት በድጋሚ ቢሮው ጠራኝ። ድንቁርናውን ተገንዝቦ ይቅርታ ሊጠይቀኝ እንደሆነ ገመትኩ። "ሮኬት ሳይንስ የሆነብኝ ለእኔ ነው!" የሚለኝ መሰለኝ።

የሆነው ግን ሌላ ነበር***

እኔ አሰተዳደር ዘርፍ ሆኖ በተመደብኩበት ዞን ወስጥ በሚገኘው ወረዳ 24 አስቸኳይ ስራ ስለመጣ ስልጠናውን ማቋረጥ እንዳለብኝ ነገረኝ። ስራው እውነተኛ ኢህአዴግነቴ በወሬ ሳይሆን በተግባር የሚለካበት እንደሆነ አስገነዘበኝ። ከሰአታት በኃላ ካሊድ ቢሮ ስብሰባ ስለሚጀመር ምሳዬን በልቼ እንድሄድ አዘዘኝ።

***

በአሊ አብዶ ቀጭን ትእዛዝ መሰረት ስልጠናውን አቋርጬ ካሊድ ቢሮ ተገኘሁ። ለእኔ ሳይነገረኝ በስሬ ያሉት ወረዳ 24 ሊ/መንበሯ ወይዘሮ ሙለሜ ረሺድና በዛው ወረዳ ቀበሌ 15 (አየር ጤና) ሊ/መንበሩ ዘርሙ ከማል ተገኝተዋል። አንድ የማላውቀው ፂሙን ያጎፈረ በጎልማሳ እድሜ ያለ ሰው የተጠቀለለ ወረቀት ይዞ ተቀምጧል። ግራ የሚያጋባ ነው!

ስብሰባው በካሊድ ዲስኩር ተጀመረ። በመዲናይቱ የከርስትናና እስልምና ተከታዮች ህዝብ ብዛት፣ ቤተክርስትያኖችና መስኪዶች አለመመጣጠን፣ ይህንን ችግር የፈጠሩት ያለፉት መንግስታት እንደሆኑ፣ አብዮታዊ መንግስታችን የተዛባውን ለማመጣጠን በትጋት እየሰራ እንደሆነ፣ ይህ ደግሞ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ የፀና ደጋፊ የሆነውን የሙስሊሙ ማህበረሰብ የበለጠ እያስደሰተው እንደሄደ ተናገረ። እነሱ አንገታቸውን እየነቀነቁ፣ እኔ ደግሞ ተከታዩን ለመስማት በመጓጓት አዳመጥነው።

የተሰበሰብንበት ምክንያት በወረዳ 24 ቀበሌ 15 ሁለት የተለያዩ ቦታዎች ላይ ህጋዊ በሆነ መንገድ የመስኪድ ግንባታ ስለተፈቀደ አፈፃፀሙ ላይ

ለመነጋገር እንደሆነ ገለፀልን። በስብሰባው አብረው ያሉት ጐልማሳ መህመድ እንደሚባልና የመስኪድ ግንባታዉ አስተባባሪ እንደሆነ ጨምሮ ተናገረ።

በአንድ ቀበሌ ውስጥ በተመሳሳይ ጊዜያቶች መስኪድ ለመስራት አንዴት ይፈቀዳል የሚል ጥያቄ አነሳሁ። ሰዎቹ የመስኪድ ግንባታ የጠየቁትና የጠቆሙት በከተማው ማስተር ፕላን መሰረት ህግን ተከትለው እንደሆነ በድጋሚ ገለፀ። ካቢኔው በቅድሚያ ለሚመጣ ጥያቄ ፍትሀዊነቱን እየፈተሸ እንደሚፈቅድ ጭምር ቆጣ ብሎ ተናገረ... እንዳለቃው!

ወይዘሮ ሙለሜ በበኩሏ የመስኪድ ግንባታ ጥያቄው የአስተባባሪ ኮሚቴው ብቻ ሳይሆን በቀበሌው የሚኖሩ ሙስሊሞች መሆኑን የሚያሳይ የድጋፍ ፈርማ የተሰባሰበበት ወረቀት አውጥታ አሳየች። ኮሚቴው በጠራው ስብሰባ በአካል ተገኝታ እንዳረጋገጠች ማስተማመኛ ሰጠች።

የቀበሌው ሊቀመንበር እሱ የሚያስተዳድረው ቀበሌ ከፍተኛ የማስፉፊያ ቦታ ስለሆነ ጥያቄውን ፍትሀዊ እንደሚያደርገው ነገረን። የህዝብ ስርጭቱን በጐሳና ሀይማኖት በመከፋፈል ዘረዘረ። የሀይማኖት ተቋማት ብዛት ኢፍሀታዊ በሆነ መልኩ እንደተሰራጨ ገለፀ።

የመጨረሻው ተናጋሪ ጐልማሳው እንግዳ ሆነ። ሰዉየው ፍቃዱን ለማግኘት ስድስት ወር እንደፈጀባቸው፣ አንደኛውን መስኪድ ለማሰራት ቃል የገቡት የአንድ አረብ ሀገር ልዑል እንደሆኑና ቃላቸውን ሳያጥፉ መፍጠን እንዳለባቸው፣ ሁለተኛውን የሚያስገነቡት በአካባቢው መኖሪያ ቤት የሰሩ የቡና ነጋዴዎች እንደሆኑ ተናገረ። በእጁ ያዘውን ፕላን እየዘረጋ በተጨማሪም በአካባቢው ለህዝቡ የሚጠቅሙ መሰረተ ልማት፣ ትምህርት ቤትና ጤና ጣቢያ አብሮ እንደሚገነባ ማብራሪያ ሰጠ።

እነሱ የተናገሩት እውነት ከሆነ ህብረተሰቡ ሀይማኖት ሳይለይ በጋራ ተረዳድቶ እንደሚሰራ የቀደሙ ልምዶች እንዳሉ ስለማውቅ ዝምታ መረጥኩ። የአዲሳባ ክርስትያንና ሙስሊሙ ማህበረሰብ ከመቻቻል አልፎ እርስ በራስ የሚረዳዳ ህዝብ ነው። ደስታውን ፣ህዘኑን፣ አውደ አመቱን በጋራ የሚያከብር ጨዋና የሚያስቀና። ቤተሰቦቻችን የአመቱ ገብርኤልን ለመዘከር ድግስ ሲያዘጋጁ ሁለት ድስት ጥደው ነው። በተመሳሳይ የረመዳንን ጾም ሙስሊም ጐረቤቶቻችን ቤት ሄደን አብረናቸው እናፈጥራለን። እንደነሱ የጾሙን ወቅት በጉጉት እንጠብቃለን።

ካሊድ ግንባታው እንዴት እንደሚፈፀም ዘርዘር አድርጐ አቀረበ።

ዙሪያውን የማጠር ስራ ለሊት እንደሚጀመር፣ ኮሚቴዎቹ በቂ ድንጋይ፣ አሸዋና ሲምንቶ እንዳዘጋጁ፣ ከዞኑ የተውጣጡ 200 ፓሊሶች እንዲዘጋጁ ለፓሊስ ኮሚሽነሩ ጥብቅ መመሪያ መሰጠቱን ገለፀ። ፀረ ሰላም ሀይሎች ሊያደርሱ የሚችሉትን ትንኮሳ የመመከት ስራ በወረዳው ፓሊስ አዛዥ ተሰፉ ፈርሻ እና በእኔ ላይ እንደወደቀ ነገረን።

እነሱ በገለፁት መልኩ ከሆነ ለምን እንደ ሌባ በለሊት ፣ ያውም በፓሊስ ታጅበን ለመፈፀም እንፈልጋለን የሚል ጥያቄ አነሳሁ። ካሊድ እኩልነትን የማይወዱ ጥቂት የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ጠላቶች እንዳይረብሹ በማሰብ የታቀደ መሆኑን ነገረኝ። ካሊድ ስለ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ሲናገር አወቅሽ-አወቅሽ ከተባለችው የቁሱ ሚስት ያስንቃል!!

ካሊድ አብዮታዊ ነበር።

***

የእነ ካሊድን ስብሰባ እንደጨረስኩ በቀጥታ ጦር ሀይሎች ወደ ሚገኘው የኮማንደር ተሰፉ ፈርሻ ቢሮ አመራሁኝ። ኮማንደር መገናኛ ሬዲዮ ላይ ተተክሏል። ረፍት እንዳጣ ፊቱ ያስታውቃል። ጭላሽት መስሏል። መምጣቴን እንዳረጋገጠ ጊዜ ማጥፉት አልፈለገም። የመጀመሪያው አፕሬሽን ለሊት ስምንት ሰአት፣ ሁለተኛው በንጋታው በተመሳሳይ ጊዜ እንደሚጀመር ነገረኝ። ለመጀመሪያው ቀን 100 ፓሊሶች እንደተዘጋጁና አስቀድመው ሌሊት ሰባት ሰአት ላይ መንገዶቹን እንደሚዘጋጉ፣ እስከዛው ድረስ ከወረዳው መከላከል ሀላፊ ውጭ ማንም ተልእኮውን እንደማያውቅ ገለፀ።

ቀድሞ መንገሩ ችግሩ ምን እንደሆነ ጠየኩት።

ኮማንደር ፊቱን ከስከሶ፣

"ሚስጥሩ እንዳይወጣ ተፈርቶ ነው። እንደምታውቀው የሀይማኖት ነገር በጣም ስሱ ነው። መስኪድ እንዲገነባ ትእዛዝ የተሰጠባቸው ሁለቱም በታዎች በጥምቀት በአል የታቦት ማደሪያ ናቸው፣ የሚቀጥለው ወር ደግሞ የጥምቀት በአል የሚከበርበት ስለሆነ ከፍተኛ ግጭት ሊነሳበት ይችላል የሚል ግምት አለን።" አለኝ።

"ታቦት ማደሪያ! ? ... ታቦት!?..." ከተቀመጥኩበት ተነሳሁ።

"መረጃ ያለህ መስሎኝ ነበር፣ ሌላ ቦታ ቢሆን ምን አስጨነቀን ብለህ ነው። ቢያንስ የጥምቀት በአል ይለፍ ብለናቸው ነበር። አሊ አብዶና ካሊድ እኔንና የፓሊስ ኮሚሽነሩን በፍቃዱ ቶሌራን ጠርተው ማስፈፀም ካልቻላችሁ የስራ መልቀቂያ አስገቡ ብለው አስጠነቀቁን።" አለኝ።

***

ከኮማንደር ጋር አብረን አምሽተን ለሊት ሰባት ሰአት ሲሆን አረንቴሽን

ወደሚሰጥበት ቦታ ሔድን። ቦታው በአየር ጤና ትምህርት ቤት ወደ ውስጥ አንድ ኪሎ ሜትር ያህል የሚያስገባ የተንጣለለ ሜዳ ላይ ነው። ከሜዳው ፊት ለፊት የኪዳነ ምህረት ቤተክርስትያን ይታያል። ቦታው ቤተክርስትያኗ በጥምቀት በአል ታቦት የምታሳድርበት ቦታ ነው። 100 ፓሊሶች በአምስት ቡድን ተከፍለው በሜዳው ዳር ተቀምጠዋል። ግራ መጋባት ይታይባቸዋል። በአካባቢው ህገ ወጥ ግንባታ የማፍረስ ስራ በየጊዜው ስለሚከናወን ለዛ የሚታዘዙ እንደሆነ በሹክሽክታ ይነጋገራሉ። አንዳንዶቹ የወታደር እጥረት ስለተከሰተ ባድመ ሊልኩን ነው ብለው ሲቀላለዱ ሰማኋቸው።

ኮማንደር ተስፉ በየቡድኑ እየዞረ አረንቴሽን ሰጠ። እያንዳንዱ ቡድን ወደ ሜዳው የሚያስገቡ አምስት መንገዶችን እንደሚዘጋ፣ ሁኔታዎች ከቁጥጥር ውጭ መውጣታቸውን ከማዕከል ካልተነገረ በስተቀር አንድም ጥይት እንዳይተኮስ፣ ምግብን ጨምሮ ሌሎች ሎጅስቲክ በተመደቡበት ቦታ እንደሚከፉፈልና ማንም ከምድብ ቦታ መንቀሳቀስ እንደማይቻል ትእዛዝ ሰጠ... ጥያቄ የሌለው ፓሊሳዊ ትእዛዝ!

አጥሬሽኑ ተጀመረ።

የቡና ነጋዴዎች ከተባሉት ግለሰቦች ቤት ውስጥ ድንጋይና አሸዋ ሞልተው የቆሙ ከ10 በላይ የጭነት መኪናዎች ተግተልትለው የጫኑትን አራገፉ። በየቤቱ ተደብቆ የነበረው ግንበኞችና ቀን ሰራተኛ ከፓሊሱ ቁጥር በላይ ሆኖ ተዘረገፈ። የአጥር ግንባታው በአምስቱም መንገዶች ዙሪያ ተጀመረ። ለጠጠር መጣያ እስከሚቸግር ድረስ ሜዳው በወጣት ሙስሊሞች ተጥለቀለቀ። ዘግየት ብለን እንዳጣራነው አብዛኞቹ ወጣቶች የአካቢው ነዋሪዎች አልነበሩም። ከአዲሳአባ ዩንቨርስቲ፣ህንጻ ኮሌጅ፣ ኮተቤ መምህራን ማሰልጠኛ፣ ከመርካቶ፣ አጠና ተራ ... የመጡ ናቸው።

***

ከንጋታው አስራ ሁለት ሰአት:

ከኪዳነ ምህረት ይሰማ የነበረው ቅዳሴ ተቋረጠ። ከቤተክርስትያኑ የድረሱልኝ ጥሪ ተሰተጋባ። የድምፅ ማጉያው የኡኡታ ድምፅ ደጋግሞ አሰማ። የአካባቢው ነዋሪ ቤተክርስትያኒቱ ላይ አደጋ ደረሰ በማለት ሊታደጓት መሯሯጥ ጀመሩ ...ወጣቱ፣ አዛውንቱ፣ ከርስትያኑ፣ ሙስሊሙ። ወደ ቤተክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ቀረብ ብዬ ቆምኩ። ቄሱ በማይክራፎን ህዝቡን የሚያነሳሳ ንግግር እያደረጉ ነበር። መንግስት ፓሊስ አሰማርቶ የጥምቀት ማደሪያውን ለባለሀብት እያከፋፈለ እንደሆነ ይናገራሉ። አጠገቤ የዛፍ ዝንጣይ የያዙ አዛውንት ለየት ስላሉብኝ ምን እንደተፈጠረ ጠየኳቸው። ዝንጣፊውን እየጣሉ፣

"እሳት የተነሳ መስሎኝ ነበር። ከቄሱ እንደሰማሁት የጥምቀት

ማደሪያውን መንግስት ለባለሀብት እየሸጠው ነው። ይሔ መንግስት ግን ምን ነክቶታል? እኔ እዚህ አካባቢ ከኖርኩ ከአስር አመት በላይ ሆኖኛል፣ ፓሊሶቹ አሁን የከበቡት ቦታ በየአመቱ የጥምቀት ማደሪያ እንደሆነ አውቃለሁ። እኔ በእምነቴ ሙስሊም ነኝ። ነገር ግን የሀይማኖት ቦታዎች መከበር አለባቸው።" አሉኝ።

"አባቴ! እኔ እንኳን የሰማሁት ለመስኪድ ሊሰጥ እንደሆነ ነው።" አልኳቸው፣ ስሜታቸውን ለማየት ፈልጌ።

"ተሳስተህል ወንድሜ! ይህ በፍፅም የሚሆን አይደለም፣ ሙስሊሙንና ክርስትያኑን ለማቃቃር ካልታሰበ በስተቀር። እኔ አካባቢውን ወክዬ የወረዳው አስልምና ምክርቤት አባል ነኝ። የመስኪድ ግንባታ ጥያቄ ያቀረብነው ትምህርት ቤቱን ተሻግረህ ባለው ክፍት ቦታ ላይ ነው፣የክርስትያን ወንድሞቻችንን ድጋፍ አግኝተናል።

ከሰውየው ጋር እያወራሁ ሲቪል የለበሰ ፓሊስ ወደ ጆሮዬ አንሾካሾከ። ሁኔታዎች እየተባባሱ መምጣታቸውን፣ ነዋሪው ስለት ያላቸው ነገሮች ይዞ መውጣት መጀመሩን ፣መንግስት መሳሪያ ያስታጠቃቸው ሚሊሻዎች ከህዝቡ ጋር እንደተሰለፉ ነገረኝ። የቤተክርስትያኑን መብራትና ስልክ እንደቆረጡትና ደውሉን ለጊዜው እንደተቆጣጠሩት ገለፀልኝ። በስውር ፓሊሶች ታጅቤ ወደ ግንባታ የሚካሄድበት ቦታ ሄድኩኝ።

***

ጠዋት አንድ ሰአት:

በአጥሩ እየታጠረ ባለበት ቦታ ያሉ ወጣትና አዛውንቶች አምላካቸውንና መንግስትን ያመሰግናሉ። ይዘምራሉ። ግንባታውን ለማፉጠን የሚሰሰት ጉልበት የላቸውም። ብዙዎቹ በደስታ ሰክረዋል። ጥቦቶች በየቦታው እየታረዱ ነው። ሴቶቹ የምጣድ ጥብስ ለቁርስ ለማድረስ ይንደፋደፋሉ። ሰርግና ምላሽ ሆኗል።

በዙሪያው ደግሞ ኡኡታውና የድንጋይ ኡርምታው መሬቱን አንቀጥቅጧል። ...ከየመንደሩ የሚወረወሩት በአሸዋና ጋዝ የተሞሉ ላስቲክ ኩዳዎች ሲፈነዱ የሚያሰሙት ደምፅ ቦታውን የጦርነት ቀጠና አሰመስሎታል። ጉዳቶች መሰማት ጀምረዋል፣ ጊዜያዊ ማዘጋጃ ላይ ያለችው የኮማንደር መገናኛ ሬዲዮ ፉታ አጥታለች።

"ዋልያ 24! ኑበር 24 ነኝ... እኔ ባለሁበት አካባቢ ሁለት አባላት ከባድ ጉዳት ደርሶባቸዋል።"

"ዋልያ 24! አንበሳ 22 ነኝ... እኔ ባለሁበት አካባቢ አምስት አባላት ተገመድተዋል እርዳታ ይፈልጋሉ"

"ዋልያ 24! ዋልያ 23 ነኝ... ከቤተክርስትያኑ መዝሙር እያሰሙ

እንደጐርፍ እየመጡብን ነው... ሀይል ይጨመርልን"

ኮማንደር በዋልያ 23 ተናዶ ምንም ታይል እንደማይጨመርለት መለሰለት፣ "ዘላለሙን እንደፈራ ይኖራል" ብሎ ለራሱ ተናገረ። ማን እነደሆነ ጠየኩት። የወረዳ 23 ፓሊስ አዛዥ የነበረው ጥሩነህ በርታ እንደሆነ ነገረኝ...

(ኮማንደር ጥሩነህ በዞን በሚካሄደው ግምገማ ሁልጊዜ በስንፍናው ይወቀስ ነበር። ኢህአዴግ ውስጥ ከቸሎታ ይልቅ የሚዘረጋ የጥቅም ኔትወርክ ወሳኝ በመሆኑ ከደቡብ ጀምሮ ከገቢዎች ሀላፊ ከነበረው ገብረዋህድ ጋር በዘረጋው ሰንሰለት መሰረት ኮማንደርነቱን ትቶ በተራ ሰራተኝነት ወደ ጉምሩክ እንዲዘዋወር አደረገው። እኔም ታታሪ ነው ብዬ የድጋፍ ደብዳቤ ፃፍኩለት። የገቢና ጉምሩክ ካድሬዎች እስር ውስጥ የገብረዋህድን ስም ስሰማ ጥሩነህ እንደሚኖሮ ለሰከንድ አልተጠራጠርኩም ነበር። የቄራና ገሩ ህዝብም ፊት ለፊቴ ተደቀኑ፣ በምርጫ 97 ገብረዋህድን በእነዚህ አካባቢዎች ለፓርላማ እንዲወዳደር አቅርበነው ነበር። የአካባቢው ህዝብና ጉምሩክ የሚሰሩ ሰራተኞች ለመስማት የሚዘገንኑ ጥቆማዎችን ይዘው ወደ እኛ መጡ። በመረጃ አስደግፈን ለአለቃችን ከንቲባ አርከበ እቁባይ አቀረብንለት። አርከበ "የትግራይ ጠላት የሆነው የቅንጅት ወሬ ነው" ብሎ አጣጣለብን።

እውነት ይዘገያል እንጂ***

ገብረዋህድ ወደ ወህኒ ወረደ። ኮማንደር ጥሩነህንም አጀበው። ከዛ ቀን ጀምሮ ለገብረዋህድ ሀገሪቷ ወዴት እየሄደች እንደሆነ ተገለፀለት። ሁለቱም የቅርብ ጓደኞቼ ነበሩና ለጥፋታቸው ተመጣጣኝ ፍትህ ለነብሳቸው ደግሞ መፅናናት ይሁን!)

***

ሁለት ሰአት...

ሁኔታዎች ከቁጥጥር ውጭ እየሆኑ ሄዱ። እናቶች ነጠላቸውን ታጥቀው ደረት ይደልቃሉ። ወጣት ሴቶች ከፓሊስ ጋር ከፊለከ ግደለኝ በሚል ፀጉራቸውን እየነጩ ይተናነቃሉ፣ ብዙዎቹ ባዶ እግራቸውን ናቸው። ጐረምሳ ወጣቶች የድንጋይ ናዳ ያዘንባሉ።

መሳሪያ ለመንጠቅ በተደረገ ትንቅንቅ አንዲት ሴት በጥይት እግሯ ላይ ተመታ ቆሰለች። ሁለት ፓሊሶች በከባድ ሁኔታ ተጐድተው ወደ ፓሊስ ሆስፒታል ተወሰዱ። ጥይት መቆላት ጀመረ።

ለሁለተኛው ግንባታ ያስቀመጥናቸውን 100 ፓሊሶች አመጣናቸው። በየቡድኑ ተደለደሉ። እንደ እውነቱ ከሆነ የፓሊሶቹ ሁኔታ ራሱን የቻለ ትራጀዲ

ነበር። ከህዝቡ ጋር እያለቀሱ በሚወረወርባቸው ድንጋይ ይደበደባሉ፣ ሲብስባቸው ወደ ላይ ይተኩሳሉ። ብዙዎቹ በወረዳው ተወልደው ያደጉ በመሆኑ ከነዋሪው ጋር ቤተሰብና ጐረቤት ናቸው... ወንድምና እህት፣ ልጅና አባት ውስጣቸው አንድ ሆኖ የሚጨፉጨፉበት ቦታ*** አየር ጤና ***የደም መሬት!

***

በአየር ጤና እየሆነ ያለውን ለካዛንችሱ ስውር መንግስት ካድሬ ለሆነው ለፍስህ መአሲ ደውዬ ነገርኩት። እነ አሊ አብዶ የቀረቡላቸውን የተሳሳተ መረጃ ነገረኝ። ግብር የማይከፍል ገበሬ መሬቱን እንደሚያርሰው፣ በአካባቢው የኢህአዴግ ደጋፊ የሆኑ ሙስሊሞች በሰፊው መስፈራቸውን እንዳስረዳ ገለፀልኝ። እነ አሊ ባህታዊውን እያታለሉት እንደሆነ አስረዳኝ። የተጀመረው ግንባታ ማስቆሙ ችግር ስለሚያመጣ እንዲቀጥል፣ ሁለተኛውን ግን እሱ ምላሽ እስኪሰጠኝ ድረስ እንዳላስፈፅምና ከማንም ጋር እንዳልነጋገር አስጠነቀቀኝ።

ብዙም ሳይቆይ ካሊድ ደወለልኝ። በአንድ ቀን ሁለቱም ማስፈፀም እንደማንችል ነገርኩት። የስድብ ውርጅብኝ አወረደ። አብዮታዊነት መጓደልና የሀይማኖት እኩልነትን አለመቀበል ቁልፍ ችግሬ እንደሆነ ገለፀ። እኔም ጀርባዬን ተማምኜ ሰለነበር ለእንደዚህ አይነት ስራ አስተዳደር መሆን እንደማልፈልግና ለካዛንችሱ መንግስት መልቀቂያ አስገብቼ ወደ ቀድሞ ስራዬ እንደምመለስ ነገርኩት። መጨረሻዬ ከርቸሌ እንደሚሆን እየደነፋ ሲጮህ "ካሊድ! ማን ላይ እግረ መቅ እንደሚታሰር በሂደት እናየዋለን" አልኩት***

ፍስህ የአህያ ባል እንደማይሆንብኝ ተማምኜ!

ቃለ ምልልሳችንን ሲያዳምጥ የነበረው ኮማንደር ተስፉ ፈርሻ ጠጋ ብሎ እንዲህ አለኝ፣

"እነዚህን ሰዎች ተጠንቀቅ። ስውር ተልእኮ አንግበዋል። በያዝነው አመት ብቻ በእኛ ወረዳ ከ10 በላይ መስኪዶች አስገንብተዋል። ማስፋፊያ ቦታ ትኩረታቸው ነው። በተለይም አየር ጤና፣ ቀራንዮ፣ አጠና ተራ፣ ከእኔ ቤት ጀርባ ጅማ ሰፈር የሚጠቀሱ ናቸው። ተከታትለን እንደደረስንበት ከሆነ የጅማ ሰፈሮቹን የመስኪድ ግንባታ የምታስተባብረው በዛ አካባቢ የምትኖረው የአሊ አብዶ እህት ናት። አሊ አብዶ አሷ ቤት ኖሮ ያውቃል። በቅርብ ቀን ከነባሩ መስኪድ 500 ሜትር ርቀት ላይ የግለሰብ ቤት በመግዛት መስኪድ መስርተው ነበር። በምርጫ 92 ኢዴአፓን ወክሎ ለፓርላማ የተወዳደረው አበበ ቀስቶ ህዝቡን አስተባብሮ የሰቀሉትን ጨረቃ አስወረደ። እንደምታውቀው አሊ አብዶ ከሚፈራቸው ሰዎች አንዱ አበበ ቀስቶ ነው።"

ኮማንደር ቀጠለ፣

"... ለአሊ አብዶ ከአረብ ሀገር የሚመጣው ገንዘብ የሚያልፈው በእህቱ አማካኝነት ነው። ቤቱን የሰራው በዛ ገንዘብ እንደሆነ ይታማናል። የእህቱም ህይወት በማይገመት ደረጃ ተለውጧል። በአካባቢው ተወልዶ ያደገው አበበ ቀስቶ ውስጠ ሚስጥሩን ያውቃል። እቤቷ ድረስ በመሄድ አስፈራርቷታል።"

***

ከረቡዱ ሶስት ሰአት:

ፓሊስ የቤተክርስትያኗን ቄሶችና የአመፅ አስተባባሪዎችን እየለየ ማሰር ጀመረ። የደብሩ አሰተዳደሮችና ቄሶችን በአቅራቢያው ወደሚገኘው ወረዳ 23 ፓሊስ ጣቢያ ተወሰዱ። እያስቸገሩ ያሉትን ሴቶች ወደ ዞን ፓሊስ ተጋዙ። አፍታም ሳንቆይ አየር ጤና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በረበሻ ተናወጠ። መስታወቶች፣ መቀመጫ ዴስኮችና አንፓሎች ተሰባበሩ። ተማሪዎች ወደ ክፍል አንገባም በማለት ሜዳ ላይ ተዘረገፉ። ፓሊስ ዙሪያውን ከበበ። ይቺ የጭንቅ ሰአት እንድታጥር ተመኘሁ።

***

የመስኪዱ አጥር ግንባታ በብርሀን ፍጥነት ተጓዘ። በነፃ የሚያግዙት ወጣቶች የስራ ትጋት እስከ ምሽት አልቀነሰም፣ መዝሙራቸው የፍንዳታውን ድምፅ ሸፍኖታል፣ ድግሱም አልበረደም። ከምሽቱ አምስት ሰአት አካባቢ አራት የግል ታርጋ ያላቸው ላንድክሩዘር መኪናዎች አጥሩን አልፈው ወደ ውስጥ ገቡ። ከመጀመሪያው መኪና ውስጥ የአሮሚያ ምክትል ፕሬዝዳንቱ ዶክተር መሀመድና በካሊድ ቢሮ አብሮን የተሰበሰበው የግንባታ አስተባባሪ ወጡ። ከሁለተኛው መኪና የአረብ ሀገር ዜጐች የሚመስሉና ጥምጣም ያደረጉ ሰዎች ተከታትለው ወጡ። ከሶስተኛው በኢጃብ የተሸፈኑ ሶስት ደርባባ ሴቶች። ጠባቂዎች ከኋላ ተሰልፈዋል።

በስራ ተጠምደው የዋሉት ወጣቶች በዝማሬና ለአምላካቸው በሚያቀርቡት ምስጋና ደማቅ አቀባበል አደረጉላቸው። ወጣቶቹ አስቀድሞ መረጃ እንደነበራቸው ያስታውቃል። የመስኪድ ግንባታ አስተባባሪው እየመራቸው ወደ እኔና ኮማንደር ይዟቸው መጣ... ምክትል ፕሬዝዳንቱ ሰላምታ እየሰጠን አጠር ያለ ሰብሰባ እንድናደርግ መምጣቱን ነገረኝ። ...አጅበውት የመጡት ሰዎች ከኋላው ቆመዋል። ..."ማን ልበል አላወኮትም?" አልኩት፣ ሆን ብዬ ...

"የአሮሚያ ምክትል ፕሬዝዳንቱ የተከበሩ ዶክተር መሀመድ ናቸው?..." ብሎ አስተባባሪው ተናገረ።

"የአሮሚያ አስተዳደር ምን አግብቶት ለስብሰባ እንደመጣ አልገባኝም" ሁሉም እንዲሰማ ጮክ ብዬ ተናገርኩ።

"የምናግዛቸው ነገር ካለ ብለን ነው፣ ወረዳው ከኦሮሚያ ስለሚዋሰን ድጋፍ ልንሰጣቸው ስለፈለግን ነው።" ዶክተሩ ቀስ ብሎ ተናገረ።

"አያስፈልገንም። ራሳችን የምንቆጣጠረው በቂ ሀይል አለን።" መልስ ሰጠሁት።

አስተባባሪው ስሜን እየጠራ፣

"ለሊት ለምትጀምሩት ሁለተኛው ግንባታ ተጨማሪ ሀይል ያስፈልጋችኃል፣ የኦሮሚያ ፓሊሶች የአዲሳባ ዩኒፎርም ለብሰው ሊቀላቀሏችሁ ይችላሉ ብለን ነው... ከቡር ፕሬዝዳንቱ ሊተባበሯቹህ ፍቃደኛ ናቸው" በማለት በድጋሚ ገለፀ።

ወደ ምክትል ፕሬዝዳንቱ ዞሬ፣

"ሁለተኛው ግንባታ ከኢህአዴግ ቢሮ መልስ እስክናገኝ አይጀመርም። በዚህም ላይ ቢሆን ምርመራ እየተካሄደ ነው፣ ባልጠፉ ቦታ በጥምቀት ማደሪያ ላይ መስኪድ እንዲገነባ መፍቀድ ምክንያቱ መጣራት ይኖርበታል። በውሳኔው ልዩነት ካለህ ለከተማዋ ኢህአዴግ ቢሮ መደወል ትችላለህ። "ረገጥ አድርጌ ነገርኩት። የአህዴድ ካድሬዎች ማን ሲጠራ እንደሚያስፈራቸውና እንደሚበራገጥ ስለማውቅ።

"እዛ የሚያደርስ አይደለም።" ተሰናብቶን ኩምሽሽ ብሎ ሄደ።

ዘግየት ብለን ባደረግነው ማጣራት ዶክተሩን የላከው በወቅቱ የኦሮሚያ ፕሬዝዳንት የነበረው ጁነዲን ሳዶ እንደነበረ አረጋገጥን። ዶክተሩ ብዙ ጊዜውን የሚያጠፋው እንደዚህ አይነት ስራዎችን ፊት ለፊት ወጥቶ በማስተባበር አንደሆነ ደረስንበት፣ ሰውየው ፅንፈኛ አመለካከቱን በግላጭ የሚያቀርብ፣ አልፎ ተርፎም ኦሮሞነትና እስልምና የአንድ ሳንቲም ግልባጭ ናቸው የሚል አግላይ ቅስቀሳ እንደሚያደርግ በክትትል ደረስንበት።

እነ ጁነዲና አሊ አብዶ ደግሞ መኖሪያ ህንፃቸውን እያስገነቡ ያሉት በግንባታ ኮሚቴው አስፈፃሚነት ከአረብ ሀገራት በሚላክላቸው ገንዘብ መሆኑ ተረጋገጠ። ከእለታት በአንዱ ቀን በምሰራበት ዞን የገቢዎች ምክትል ሀላፊ የነበረችውን አሰፉ ፈንቴ (የበረከት ስምአን ሚስት) ቢሮዬ ጠርቼ በዝርዝር ነገርኳት። አሰፉ ልታይ የማታበዛ፣ ስልጣን የምትሸሽ፣ ጨዋና ትጉህ ሰራተኛ ነበረች። እንደ እውነቱ ከሆነ ከአቶ መለስ በተቃራኒ የበረከትን እድሜ የቀጠለችለት አሰፉ ናት። እሱም ቢሆን በየደቂቃው "አሲ!" እያለ ስልኩን ያስጨንቃል። ውጭ ሀገር እንኳን ሲሄድ ግራ ጐኑን ይዞ ነው።

ዶክተር መሀመድን አስመልክቼ የነገርኳትን በጥሞና ስታዳምጠኝ ቆይታ "ቆይ ዝምበል!" ብላኝ ወጣች። ከወራት በኋላ ዶክተሩ ከምክትል ፕሬዝዳንትነትና አህዴድ አባልነት ተባረረ። ጠባብነትና ጽንፈኝነት የሚል

ማዕረግ ተጨመረለት። በተራዬ አሰፉ ቢሮ ሔጀ እጅ በመንሳት ምስጋና አቀረብኩ።

***

በሳምንት ውስጥ የአየር ጤና መስኪድ አጥርና ጊዚያዊ የቆርቆሮ ቤት ተገንብቶ ተጠናቀቀ። ሁለተኛው ግንባታ እስኪጣራ ድረስ በካዛንችሱ መንግስት ትእዛዝ ተቋረጠ። ህዝበ ክርስቲያኑ በበኩሉ ለጥምቀት አመፅ ቀጠሮ ይዞ አደብ ገዛ። እኛ ደግሞ የአሊ አብዶ የጨለማ ዘመን አካል ነንና ወደ ሌላ አጥፍቶ መጥፉት ተሸጋገርን።

ካሊድ ቢሮ እኔ፣ ኮሚሽነር በፍቃዱ ቶሌራ፣ ኮማንደር ተሰማ፣ ኮማንደር ተስፉ በጠዋት ተገኝተናል። የወረዳ 24 የአርቶዶክስ ሀይማኖት ተከታዩ ህዝብ በእለህ ተነሳስቶ ሁለት ቦታዎች ላይ ህገ ወጥ ቤተክርስትያን በሶስት ቀን ገንብቶና ታቦት አስገብቶ አምልኮ ጀምሯል። ካሊድ ቢሮ የተሰባሰብን ባለስልጣናት ቤተክርስትያኖቹን እንዴት እንደምናፈርስ እየተነጋገርን ነው። የተለመደው የካሊድ አብዮታዊ ደሞክራሲ ኪነን ሽፉኑን ሳይቀይር ህገወጥነትን ለመከላከል ፍቱን መዳኒት ሆኖ ቀርቧል። አዲሱ ነገር የምክትል ፕሬዝዳንቱ ደሳለኝ ሸሹ መገኘት ብቻ ነው።

ህገ ወጥነት ላይ ጠንካራ አቋም ስለነበረኝ ከማስተር ፕላኑ ጋር ተመሳክሮ ወደ ህጋዊ መስመር የሚመጣበት ካልሆነም የማፍረስ ሁኔታ መፈጠር እንዳለበት አስተያየት ሰጠሁ። አስቀድሞ በህዝቡ ዘንድ የማሳመን ስራ መስራት እንደሚገባ እና የሃይማኖቱን ክብር በማይነካ መልኩ መፈፀም እንዳለበት አሳሰብኩኝ። ካሊድ ተልእኮን ለመፈፀም መፍራትና ህዝበኝነት የሚል መሸከም የማልችላቸው ስሞች ጨመረልኝ... አያልቅበት!

የማፍረሱ ስራ ዛሬውኑ መሆን እንዳለበት ካቢኔው መወሰኑን ነገረን። ደሳለኝ ሸሹ በካሊድ ንግግርና በእነ አሊ አብዶ ውሳኔ ደስተኛ እንዳልሆነ ያስታውቃል። አፉ በልጓም የታሰረ እስኪመስል ድረስ ትንፍሽ አላለም። ካሊድ ላይ ያለውን ጥላቻ አይኖቹ መደበቅ አልቻሉም። ስብሰባው አልቆ ወደ ደጅ ስንወጣ በታላቅ ወንድም በሚመስል አይኑ እያየኝ፣

"አይዞህ! ሁሉም ያልፋል።" አለኝ። ደሳለኝ ጥሩ ሰው ነበር።

ሌላ የጭንቀት ሳምንት... ድቅድቅ ጨለማ...

***

ከኮማንደር ተስፉ ጋር ተያይዘን ወደ ወረዳ 24 ሔድን። ዝርዝር መረጃዎቹን ወሰድን። ቤተክርስትያኖቹ የተገነቡት ሚሊፎኒ (በተለምዶ ህዝቡ ሙስና ሰፈር)ከሚላቸው ቦታዎች እና ቻይና ኤምባሲ ጀርባ ኮምፔንሳቶ

እንጨት መሰንጠቂያ አጠገብ ነበር። የመጀመሪያዉ ለሀይማኖት ተቋም የማይሆን ቦታ በመሆኑ ማፍረሱ አማራጭ እንደሌለው ተስማማን። ሁለተኛው ከማስተር ፕላኑ ጋር የማይጋጭና ጫካ ውስጥ ስለሆነ ወደ ህጋዊ መስመር የሚገቡበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንደሚገባን ተማመንን።

የሚሊፎኒ ግንባታ ኮሚቴዎችን ጠርተን አናገርናቸው። መግባባት ላይ መድረስ አልተቻለም። እንደምናፈርሰው በግልፅ ነገርናቸው። ህገወጥ መሆኑን እያመኑ ፉክክራቸው እነ አሊ አብዶ ከዘረጉት ህገወጥ ኔትወርክ ጋር ሆነ። እኛም ከግለሰብ እምነታችን ተነስተን እንድንደግፋቸው ያግባቡን ጀመር። የሚሆን አልነበረም፣ የህግ የበላይነት ሌላው ስለጣሰ እኛም ማክበር የለብንም የሚባል አመክንዮ እንደማይሰራ በግልጽ ነገርናቸው። ለሚከሰተው ጥፋት ሀላፊነቱን እንደሚወስዱ አስጠነቀቅን። እንደማያዛልቅ ስንገነዘብ እነሱ በወረዳው እገታ ተደርጉባቸው ቤተ ክርስትያኑ ፈረሰ።

የፓሊስ መኪና በሙሉ አይናችን ለማየት እንኳን የማንደፍረውን ታቦት ተሸክሞ ወደ ጣቢያ መጣ። ከሌላ አሳዛኝ ድራማ ጋር ተገጣጠምኩ።

የመገናኛ ራዲዮ ላይ የተቀመጡት ሴት ፓሊሶች ሰውነታቸው ይርዳል፣ ይጮሀሉ። አንዲት አብሮ አደጌ የሆነች የፓሊስ አባል ተዝለፍልፋ እግሬ ስር ወደቀች። አፉፍሰን አነሳናት። ለቅሶዋና መንቀጥቀጧ አላባራ ሲል ወደ ቤቷ ሸኘናት። ብዙም ሳትቆይ ስራዋን ጥላ ወደ አረብ ሀገር እንደተሰደደች ሰማሁ። የአዶ መለስ አዲሲቷ ኢትዮጵያ ከፓሊስነት ይልቅ አረብ ሀገር የቤት ሰራተኝነት የሚያስንቅባት ሆናለች። ብሄራዊ ውርደታችን እዚህ ደረጃ ደርሷል።

ኮማንደር ግብታዊ በሆነ ሁኔታ መለዮውን አውልቆ በመወርወር ተንበረከከ። ፀጉሩን እየነጨ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ። የኮሚቴው አባላት ተሯሩጠው ከተንበረከከበት አነሱት። አቧራ የለበሰውን ሱሪ በእጃቸው እየጠረጉ አጽናኑት።

በጥላቻና ባንዳነት ሲፈርጁን አልፎ ተርፎም በፔትሮሊየም ዶላር የተደለልን አድርገው ሲሰድቡን የነበሩት የኮሚቴው አባላት ተደናገጡ። ጭንቀታችንን ተጋሩት። አብረውን አዘኑ። የገባንበትን አጣብቂኝ በመገንዘብ ነዋሪውን ለማረጋጋት ሀላፊነት ወሰዱ። አመስግነን ሸኘናቸው። ወደ ቄያቸው ተመለሱ።

ኮማንደር መፅናናት አቃተው። በዛ ሁኔታ እያለ ጥዬው ለመሄድ አልፈለኩም።

(ኮማንደር ተሰፉ ፈርሻ ወልቂጤ ካፈራቻቸው ቆፍጣና ወታደሮች አንዱ ነው፣ ወታደራዊ ዲስፕልን ከተሟላ ቁመና ጋር የተቸረ። የተሰጠውን ተልእኮ ሲፈፅም በልበ ሙሉነትና የሰው ልጅ ሰው በመሆኑ ያገኘውን ሰብአዊ መብቶች በማከበር ነበር። በቅርብ የምናውቀው አለቆቹ ከባድ ስራ ከመጣብን አይናችን የሚያርፈው እሱ ላይ ነበር። በከተማዋ የሚገኙ የፓሊስ አባላት በአካል ባያውቁትም በአስገምጋሚ ድምፅ ይለዩታል። ኮማንደር በመገናኛ ሬዲዮ ሲናገር ምድብ ቦታቸውን የለቀቁ የፓሊስ አባላት ይሯሯጣሉ። ላልሰሙትም "አንበሳው አጋስቷል! ዛሬ የዞኑ ተረኛ እሱ ነው" የሚል የተጠንቀቅ መልእክት ያስተላልፉሉ።)

ከብዙ ዝምታ በኃላ ወጣ ብለን ብስጭታችንን በቢራ ጠርሙስ እንድናወራርድ ጠየኩት። የመረጃ ክፍል ኢንስፔክተሩን ጠርቶ አዲስ ነገር እንዳለ ጠየቀው። በነብስ ማጥፋት ተጠርጥሮ ለሁለት ሳምንት ክትትል ሲደረግበት የነበረው ሰው በቁጥጥር ስር እንዳዋሉት ነገረው። ወደ ማእከል ከመላኩ በፊት የተቀበሉትን ቃል እንዲያመጣለት አዘዘው።

የሀገሬ ፓሊስ ባለመሆኔ አምላኬን አመሰገንኩ። በሀቅና ታማኝነት ለሚሰራ እስር ቤት የሆነች ሀገር። ኮማንደር ተሰፉ የግለሰብ ቤት ኪራይ መክፈል ከብዶት ባለ አንድ ክፍል የቀበሌ ቤት ጅማ ሰፈር የሰጠነው እኛ ነን።

ኢንስፔክተሩ ቃል የተቀበለበትን መዝገብ ይዞለት መጣ። በአርምሞ ካነበበ በኃላ ተጠርጣሪውን አናግሮት እስኪመጣ እንድታገሰው ጠየቀኝ። አብሬው መሄድ አንደምፈልግ ነገርኩት። የማስገደድ ያህል ተሜንኩት። ሀሳቡን ለውጦ እስረኛው ወደ ቢሮው እንዲመጣ አደረገው።

በፍጹም ያልጠበኩት ነበር...

የመዲናይቱ ነዋሪ "ቆምጬ" ብሎ ከሚጠራቸው ሰዎች አንዱ በሁለት ፓሊሶች ታጅቦ ገባ። እጁ በካቴና የፊጥኝ ታስሯል። እንደ መረብ በተጠላለፈ ክር የተጠቀመ ቁምጣ ና በተለምዶ "ጐጃም አዘነ" ተብሎ የሚጠራውን ነጠላ ለብሷል። በጐማ የተሰራ በረባሶ ተጫምቷል። መረጋጋቱ እንኳን በነብስ ማጥፋት ዶሮ የታሰረችበት ገመድ በመስረቅ የተጠረጠረ አይመስልም።

ኮማንደር ካቴናውን አስፈትቶ የሰጠውን ቃል እያመሳከረ በድጋሚ መጠየቅ ጀመረ። ከተለመዱት የፓሊስ ጥያቄዎች ተሻግሮ የሚያቀርብለት ቀልቤን ሳበው። እንዲህ በማለት ጀመረ፣

"ስንት ቁምጣ ነው ያደረከው?"

"ከውስጥ ግልገሏ ውጭ አንዲት ናት ጌታው! "

"እውነቱን ተናገር!" ኮማንደር አስገመገመ።

"ሁለት ነው ጌታው!"

"አንዱ የማን ነው?"

"የእሱ (ሚች) ነው ጌታው!"

"በእጅህ ላይ ንብረት፣ ገንዘብ አለ?" እንደገና ጠየቀው።

"ኧረ ! ምንም የለም ጌታው። በቀን በላ የምኖር ነኝ።"

ኮማንደር ተናደደ። ፓሊሶቹ ጓንት እና መቀስ ይዘው እንዲመጡ አዘዛቸው። ተጠርጣሪውን ሌላ ክፍል ወስደው ቁምጣዎቹን አስወለቀው ሱሪ አልብሰውት እንዲመጡ ነገራቸው። ይዘውት ሲወጡ ሚች ራቁቱን ወንዝ ውስጥ ተጥሎ መገኘቱን ነገረኝ።

መጨረሻውን ለማወቅ ጓጓሁ...

ፓሊሶቹ የመጀመሪያው ቁምጣ የተጠቀመበትን ክሮች በመቀስ መበጣጠስ ጀመሩ። እያንዳንዱ አራት መአዘን ክር በተፈታ ቁጥር በቁመቱ የተከማቸ ባለ መቶ ብር ኖት ይዘረገፉል። ከአንዱ ቁምጣ ብቻ አስር ሺህ ብር ተቆጠረ።

የማየውን ማመን አቃተኝ። ከሁለት የተሰፉ ቁምጣዎች ሀያ አምስት ሺህ ብር ተገኘ። በቁምጣዎቹ የተደበቀው የኖቶች ብዛትና ተባዩ መሳ ለመሳ ነበር።

"እንዴት ይሄ ሁሉ ገንዘብ ሊኖረው ቻለ ?"ስል ኮማንደርን ጠየኩት። መልስ ሳይሰጠኝ ወደ ሌሎች ጥያቄዎች ተሸጋገረ፣

"የምትኖረው የት ነው? ማደሪያህን ጨምረህ ንገረኝ?"

"አለም ባንክ አካባቢ። ያላለቁ ቤቶች እየጠበኩ።"

"ስንት ቤት ትጠብቃለህ? ምን ያህል ይከፍሉሀል?"

"ሶስት ናቸው ጌታው። በቀን አስር ብር ይከፍሉኛል" ኮማንደር በባዶ ወረቀት ላይ ሰላሳ ቁጥር ጻፈ።

"የቀን ስራ የምትሰራው የት ነው?" ሲል ጠየቀው።

"ቃሊቲ፣ አቃቂ፣ ላፍቶ፣ ቦሌ አካባቢ።"

"ወደ ስራ ስትሄድና ስትመለስ ምን ታደርጋለህ?"

"እንዲዘከሩኝ አየጠየኩና እየለመንኩ እሄዳለሁ ጌታው።"

"ያገኘኸውን ምግብ ምን ታደርገዋለህ?

"ሶስት ቁጥር ማዞሪያና አቡነ አረጋይ አካባቢ እሸጠዋለሁ? በርካሽ ዋጋ ስለምሸጥ ቋሚ ደንበኞች አሉኝ። ከሰዎች የተረፈው ለከብቶቻቸው የሚገዙኝ አሉ።"

ደነገጥኩኝ።

የነዋሪው በችጋር መመታት በዚህ ደረጃ መድረሱ። የእኔ ቢጤ ለምኖ ያገኘውን ምግብ ተሻምቶ የሚገዛ ህዝብ። ለነገሩ ምን ይገርማል? መሀል መርካቶ ጉርሻ ይሸጥ የለ። እጅ ሞላ ያለ አንድ ብር፣ እጅ ጎደሎ ደግሞ ሀምሳ ሳንቲም!! ...የሁለት ምርጫዎች ወግ "የአፍሪካ ነብር!" ብሎ የሰየመሽ አዲሲቷ ኢትዮጵያ የት ነው ያለሽው? ይህን ውርደት ሰምተሽ ይሆን? ...የሙሴን በትር የያዝከው መልአክ የት ነው ያለኸው? በትሩን ያስጨበጠህ አርቲስትም ብትሆን ትራፊና ጉርሻ የሚሸጥባት አዲሳአባን ዞር ዞር ብለህ አይተሀት ይሆን? እርግጠኛ ነኝ የእለት ቀለብህን ከሚሰፍርልህ ሸራተን አዲስ ወጣ ወጣ ብትል ይህን ያገጠጠ እውነት ትመለከት ነበር።

ኮማንደር ጥያቄውን ቀጠለ፣

"ለምነህና ምግብ ሸጠህ በቀን ስንት ብር ታገኛለህ?

"አይ ጌታው እሱ እንኳን ትንሽ ነው። መቶ ብር አይሞላም" ኮማንደር መቶ ብር ጻፈ።

"በቀን ስራህ ስንት ታገኛለህ?

"ብዙ ጊዜ በኮንትራት እሰራለሁ። ሙሉ ቀን ከዋልኩ እስከ መቶ ብር" ኮማንደር 100 ብር ጻፈ።

ወደ እኔ ዞሮ "ጥያቄህ ተመለሰ?" ብሎ ጠየቀኝ።

"ባላውቅ ይሻለኝ ነበር" ስል ምላሽ ሰጠሁት።

***

ምእራፍ ስምንት

"ህግ -መንግስት በጠረባ !"

"ህገ - መንግስት ተጥሷል/ አልተጣሰም የማለት መብት ፍርድ ቤቶች የላቸውም "
(አሊ አብዶ)

"...ህገ - መንግስት ተጥሷል/ አልተጣሰም ብሎ ብይን የሚሰጥ ፍርድ ቤት የሌለባት ብቸኛ ሀገር ኢትዮጵያ መሆኗን ጠፍቶኝ አይደለም!"
(ያልታወቀ ዳኛ)

ታላቋ ቀን!

ወቅቱ ጥቅምት 1994 ዓ.ም ነበር።

የአዲሳባ ምክር ቤት አዳራሽ አስቸኳይ ጥሪ በተደረገላቸው የፌዴራልና ከተማ ካድሬዎች፣ የፍርድ ቤት ባለስልጣናትና ዳኞች፣ የፓሊስ አዛዦች ተሞልቷል... ከዚህ በተጨማሪም የአካል ጉዳተኛ በሆኑት ግለሰብ የሚመራው የአያት መኖሪያ ቤት ስራ ድርጅት ሀላፊዎች በስብሰባው ተገኝተዋል።

አጀንዳው "መሬት ለአልሚዎች በማስረከብ ዙሪያ ያጋጣሙ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው" የሚል ነበር... ህግ አውጭውን፣ ተርጓሚውና አስፈፃሚው በጥድፊያ ያገናኘው አጀንዳ።

የፐሬዝዳንት አሊ አብዶ ፕሮቶኮል ሹም ጤናዳም በየሴክተሩ የመጡትን ሹማምንት አቴንዳንስ ወሰደ።ሁሉም መገኘቱ ሲረጋገጥ በውስጥ በር በኩል የፐሬዝዳንቱን ቢሮና አዳራሽ በምትገኘው በር አሊ አብዶ፣ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር አባይ ፀሀዬ ፣የፌደራል ፓሊስ ኮሚሽነሩ ወርቅነህ ገበየሁ፣ የፍርድ ቤቶቹ ም/ፐሬዝዳንቶች መንበረ ፀሀይና ደሳለኝ፣ የአዲሳባ ፓሊስ ኮሚሽነሩ በፍቃዱ ቶሌራ ተከታትለው ገቡ።

የህግ ምሁሩ ኮሚሽነር በፍቃዱ አጠገቤ መጥቶ ተቀመጠ። ቀልደኛና ቀላል ሰው ስለሆነ እንግባባለን። በከተማዋ የፀጥታ ስራዎች ሳምንታዊ ግምገማ ላይ እንገናኝ ነበር።ህገ ወጥ ግንባታ የመከላከል ስራ በጥምር ሰርተናል። የሀይማኖት ተቋማትን አብረን አፍርሰናል። አስገንብተናል።

የኮሚሽነር ሰላምታ አሰጣጡ የወትሮ አልሆንብኝ ሲል ወደ ጆሮው ጠጋ ብዬ "አይዞህ! የምን መበሳጨት ነው! ግፉ ቢል ወደ ጠመኔህ ትመለሳለህ..." አልኩት።

በአንድ ወቅት የከተማዋ ካድሬዎች በተገኘንበት የሀገር ውስጥ ደህንነት የበላይ ሹሙ ጌታቸው አሰፉ "የኦሮሞ ጠባብነት አለብህ!... የትራፊክ ጽ/ቤት ን በአነግ በምንጠረጥራቸው ሰዎች አጥለቀለከው" ብሎ ሳምንቱን ሙሉ አስጨነቀው። ርግጥም የትራፊክ ፓሊስ አለቃነት ለኦሮሞዎች ተለይቶ የተሰጠ ይመስል ነበር። እጅግ በጣም የሚገርመው የደህንነት ሹሙ የኦሮሞ ልጆች የተከማቹበትን ቦታ ለይቶ የሚያውቅ ህሊና ከነበረው ሌሎች ቦታዎች ላይ እነማን እንዳሉም ጠንቅቆ ያውቃል ማለት እንደሆነ አዙሮ አለማሰቡ ነበር። ኮሚሽነሩ በጌታቸው እይታ ተበሳጭቶ የመጣ ይምጣ በሚመስል መልኩ፣

"...የፓሊስ ዋና ስልጣን የመከላከል ሀላፊ መሆን እንጂ መኪና መጠበቅ አይደለም! የወንጀል መከላከሉ ደግሞ ከፌዴራል እስከ አዲሳባ በማን እንደተያዘ ይታወቃል!... የሚሰማህን ንገረኝ ካልክ ከዚህ አስቀያሚ ስራ ወደ ጠመኔዬ ብመለስ ይሻለኛል" የሚል ምላሽ ሰጠ። ያንን ለማስታወስ ነበር በምክር ቤት አዳራሽ ያነሳሁበት።

"የማይሆን ነገር ለሚስትህ አትንገር ሆኖብኝ ነው" በተራው ወደ ጆሮዬ ተጠግቶ መለሰልኝ።

"አሊ አብዶ ባለበት ስብሰባ ምን ጥሩ ነገር ትጠብቃለህ?" ኮሚሽነሩ ለአሊ አብዶና ምክትሉ ካሊድ አብርሀማን ከፍተኛ ንቀት እንዳለው አውቃለው። በከተማዋ እየተዘመተ ያለው ህገወጥነት ምንጮቹ እነሱ እንደሆኑ ደጋግሞ ይናገራል።

"ኧረ ጉዳዩ ከእነሱ በላይ ነው! ... ተወኝ ባክህ! ... የህግ ሀ - ሁ የቀመሰ ሰው በፓሊስ ሹመት ደጃፍ ማለፍ የለበትም። ዘላለሙን ከራሱ ጋር እንደተጣላ ይኖራል!" አለኝ።

አሊ ጉሮሮውን ሞርዶ ስብሰባውን ጀመረ።

አስተዳደሩ በኢንቨስትመንት ደረጃ ከፍተኛ እምርታ እንዳስመዘገበ፣ ይህ አመርቂ ለውጥ የመጣው በሶስቱ የመንግስት አካላት የተቀናጀ ጥረት እንደሆነ፣ ለዚህ ተስፉ ሰጪ ውጤት በከተማዋ ህዝብ ስም ምስጋና ማቅረብ እንደሚፈልግ ተቆጥቶና ፊቱን አጨማዶ ገለፀ። ይህም ሆኖ በአንዳንድ የልማት ስራዎች ላይ በተለይም መሬት በማዘጋጀት ለአልሚዎች በመስጠት ዙሪያ ችግሮች እያጋጠሙ በመሆኑ ልማቱ እየተጓተተ መሆኑን አስረዳ። አባይና ኮሚሽነር ወርቅነህ ተመሳሳይ ይዘት ያለው ንግግር አደረጉ።

አሊ አጋጥመዋል ያላቸውን እንቅፋቶች መዘርዘር ጀመረ፡ - የከተማው ፓለቲካ ተሿሚዎች ህዝበኝነት፣ የፓሊስ ቁርጠኝነት ማጣት፣ የፍርድ ቤቶች ዳተኝነት እንደሆነ ገለፀ። በተለይም ዳኞች ለትንሹም ለትልቁም "ሁከት ይወገድልኝ " መስጠታቸው ልማቱ ተንገራግጮ እንዲቆም እያደረገው እንደሆነ ተናገረ።

ከተሰብሳቢው ውስጥ የማጉረምረም ድምፅ ተሰማ። አሊ ተልባ ቢንጫጫ በሚመስል መንገድ ጉምጉምታውን ወደ ጐን ትቶ የቸግሩ ዋነኛ ምንጭ የሆነው "ሁከት ይወገድልኝ" የሚለው የፍርድ ቤት ወሳኔ ያስከተለውን ችግር ለመወያየትና ለቀጣይ መፍትሄ ለማስቀመጥ እንደሆነ፣ በዚህ የዳኞች ውሳኔ ሰለባ በመሆን ለከፍተኛ ኪሳራ እየተዳረጉ ያሉ ልማታዊ ባለሀብቶች በስብሰባው ስለተጋበዙ ዘርዘር ያለ ማብራሪያ እንደሚሰጡ ገለፀ። የአያት መኖሪያ ቤት ስራ ድርጅትን ወክለው የመጡት ግለሰብ ቅሬታቸውን እንዲያቀርብ በክብር ጋበዘ።

የአያት ተወካይ አንድ ሳምሶናይት ሙሉ ዶሴዎችን ለተሰብሳቢው በማሳየት ንግግራቸውን ጀመሩ። ሰውየው ፉይል እያገላበጡ የመጀመሪያውን የፍርድ ቤት ክስ በንባብ ማሰማት ሲጀምሩ ከተሰብሳቢዎች መሀከል "ስነ - ስርአት" ... "ሰነ - ስርአት" የሚል ቃል ከየቅጣጫው ተሰተጋባ።

አሊ እንደለመደው የከተማውን ካድሬ የሰበሰበ መስሎት፣

"አንድ ሰው የጀመረውን ሳይጨረስ ማቋረጥ አግባብ አይደለም። ባይሆን የአያት ተወካይ አጠር አድርገው ፍሬ ፍሬውን ይግለፁ" በማለት ተሰብሳቢውን በቁጣ ገሰፀ።

"ስነ - ስርአት!"፣ "ስነ - ስርአት!"... የሚያቆም ተቃውሞ።

አሊ አቧራው ታየ!

ፊቱን ወደ አባይ አዙሮ በምን ይሻላል አይኑ ገረመመው። የስነስርአት ጥያቄ ላነሱት እድሉን እንዲሰጣቸው ፈቀደለት።

የመጀመሪያው ተናጋሪ ዳኛ መሆኑን አስቀድሞ በመግለፅ ስብሰባው ህገ -ወጥ መሆኑን ማስረዳት ጀመረ።እንዲህ በማለት፣

"በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአለም አቀፍ ደረጃ በፍርድ ቤት በተያዘና ብይን ባልተሰጠበት ጉዳይ ላይ አስተያየት መስጠት የፍርድ ሂደቱን ያጨናግፈዋል ተብሎ ስለሚታሰብ የተከለከለ ነው። በተለይም ለፍትህ ስርአቱ አጋዥ ይሆናሉ ተብለው ከሚታሰቡት ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት፣ የፓሊስና የፀጥታ ሀይሎች ከዳኞች ጋር የከስ ጭብጦችን እያነሱ መወያየት የፍርድ ቤቶችን እጅ እንደ መጠምዘዝ ይቆጠራል።"

ዳኛው የሰጠው አስተያየት ስላልገባኝ አጠገቤ የተቀመጠውን ኮሚሽነር ጠየኩት።

"ይህ የህግ ሀ - ሁ ነው። በፍርድ ቤት በተያዘ ጉዳይ ላይ የፓለቲካ ስልጣኑን የያዘው፣ ፓሊስና ሌሎች የፍትህ አካላት ከዳኛ ጋር ቁጭ ብለው አይነጋገሩም። ዳኛው እንዳለው የፍትህ ሂደቱን ያጨናግፈዋል ተብሎ ይታሰባል። ከውሳኔ በኋላ ብዙም ችግር ስለማያመጣ በትምህርት ካሪኩለም ውስጥ ሳይቀር አስገብተው እንደመማሪያነት የሚጠቀሙበት አሉ።" ብሎ ምላሽ ሰጠኝ።

"አንድ ዳኛ በግልፅ የተፃፈለትን አስከተረጉመ ድረስ ምን ለውጥ ያመጣል?"

"ህግ ማቲማቲክስ አይደለም... አንድ ሲደመር አንድ ሁለት ብለህ አታቆምም"

"አንድ ሲደመር አንድ ሁለት ብቻ ነው ያለህ ማነው? ሶስት የሚሆንበት ጊዜ አለ... ሂሳቡን ለባለቤቱ ተውና ህጉ እንዴት እንደሚጨናገፍ በምሳሌ አስረዳኝ።"

ኮሚሽነር እንዲህ በማለት ምላሽ ሠጠኝ።

"የምታውቀውን ልንገርህ። እነ ስዬ አብርሀ በሌብነት ተከሰው ፍርድ ቤት እየተመላለሱ እያለ አቶ መለስ በኢቲቪ ቀርቦ ሌብነታቸውን በዝርዝር አቀረበ። አንድ ተጠርጣሪ ከብይን በፊት እንደ ንጹህ ይቆጠራል የሚለውን አፈረሰ።የፍርድ ውሳኔው አስቀድሞ በፓለቲካ ባለስልጣናቱ ተሰጠ። ተናጋሪው በሀገሪቷ የስልጣን ማማ የመጨረሻው ጫፍ ላይ የተቀመጠ በመሆኑና የዳኝነት ስርአቱ ጠንካራ ስላልሆነ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ቃላቶች ብይኑን ሊያዛቡት የሚችሉበት እድል ተፈጠረ። የህግ ሙያተኞችን ያበሳጨው እነሰዬ ሌባ ስላልሆኑ ሳይሆን የአቶ መለስ ዳኛ ሆኖ መገኘት ነበር"

እንደገባኝ ነግሬው ጆሮዬን ወደ ቀጣዩ አስተያየት ሰጪ አሻገርኩ።

ሁለተኛው ተናጋሪ በተመሳሳይ ዳኛ መሆኑን አስቀድሞ በመግለፅ የአያት ተወካይ በንባብ እያሰሙት የነበረውን ጉዳይ በመዳኘት ላይ ያለው እሱ መሆኑን ተናገረ። በነጐድጓድ ድምፁ፣

"... ሌላው ቢቀር ከሳሽና ተከሳሽ በአንድ መድረክ በሌሉበት የአንድ ወገን አቤቱታ አዳምጦ አስተያየት ለመስጠት ህሊናቸሁ ማሰቡ በራሱ ጥያቄ ሆኖብኛል!... ይህንን ስብሰባ የጠራችሁ አካላት የዜጐች በፍርድ ቤትና ፍርድ ቤት የመዳኘት መብት ጥሳችኃል" ብሎ ተናገረ።

አሊ አብዶ በበኩሉ፣

"ህገ - መንግስት ተጥሷል/ አልተጣሰም የማለት መብት ፍርድ ቤቶች የላቸውም" በማለት በአቶ መለስ የተፃፈውን የዲሞክራሲ ጥያቄ በኢትዮጵያ

የሚለውን ሰነድ አነበነበ።

"ክቡር ፕሬዝዳንት! ህገ - መንግስት ተጥሷል/አልተጣሰም ብሎ ብይን የሚሰጥ ፍርድ ቤት የሌለባት ብቸኛ ሀገር ኢትዮጵያ መሆኗን ጠፍቶኝ አይደለም።ሌላው ቀርቶ ህገ - መንግስትን በተመለከተ ብይን የሚሰጠው ፌዴሬሽን ምክር ቤት ውስጥ ከአራት ሚሊዮን በላይ የሆነው የአዲሳባ ህዝብም ሆነ ክቡርነትዎ እንዳልተወከሉ አውቃለሁ።ነገር ግን የዜጐችን በፍርድ ቤት የመዳኘት መብት የሰጠው ህገ - መንግስት በጠረባ ሲመታ ለማየት ህሊናዬ ስላልፈቀደ ነው።" በማለት ሁለተኛው ዳኛ የመልስ ምት ሰጠ።

ትንሿ አዳራሽ በድጋፍና ማጉረምረም ተነቃነቀች።

አጠገቤ የተቀመጠው ኮሚሽነር በተራው ጠጋ ብሎኝ፣

"አንጀቴ ቅቤ ጠጣ! እኔ ለወንበሬ ፈርቼ ያልተናገርኩትን ተማሪዎቼ አፈረጡት። ይሄ አድርባይ አለቃህ እያየሁት ሰመጠ!" አለኝ።

በዚህ መልኩ መቀጠል እንደማያዋጣ የተገነዘበው አባይ ፀሀዬ የሻይ ሰአት ረፍት እንድንወስድ በማድረግ ስብሰባው እንዲቋረጥ አደረገ። በሻይ ሰአት የፕሬዝዳንቱ ፕሮቶኮል ጤናአዳም አየዞረ ስብሰባው ላልተወሰነ ጊዜ እንዲቀር መደረጉንና ለወደፊቱ አስተዳደሩ እንደሚያሳውቅ በመግለፅ ተሰብሳቢው ወደ መጣበት እንዲመለስ መልእክት አስተላለፈ። የከተማና ዞን ካድሬዎች ወደ ኋላ እንድንቀር በተናጠል ነገረን። አብሮኝ ሻይ ሲጠጣ የነበረው ኮሚሽነር በፍቃዱ "በል ማክሰኞ እንገናኝ። ታዲያ አንደ ቆምጩ አንባው ቀኝ እጅህን ለማውጣት ተዘጋጅ!" በማለት ተሰናብቶኝ ሔደ።

ወደ ስብሰባ ተመለስን።

ከመዲናይቱ ካድሬዎች ውጭ አባይ፣ ኮሚሽነር ወርቅነህ፣ የፍርድ ቤቶቹ ምክትል ፕሬዝዳንት የሆነው ደሳለኝ እና የአያት ድርጅት ተወካዮች ተገኙ።

አቶ ደሳለኝ የጠበቀው ነገር እንዳጋጠመውና እሱ የሚመራው የዳኝነት ስርአት በፀረ-ኢህአዴግ እንደተወረረ ገለፀ። መፍትሔ ይሆናል ብሎ የሚያስበው፡ በህገ - መንግስቱ መሰረት መሬት የህዝብ በመሆኑና የህዝቡን ውክልና ያገኘው ያስተዳደሩ ምክር ቤት በአስቸኳይ ተሰብስቦ ከዚህ ቀደም በፍርድ ቤቶች የሚሰጠው "ሁከት ይወገድልኝ" የሚቀርበትን ውሳኔ ማስተላለፍ እንደሆነ አስረዳ። አክሎም የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ስልጣን ህግ አውጭው ያወጣውን አዋጆችና ህጐች የመተርጐምና በዛ ብቻ የመመራት ግዴታ እንዳለበት ሰፊ ማብራሪያ ሰጠ። አገራችን የምትከተለው የኮንትኔንታል (ሲቪል) ህግ ዘርፍ መሆኑን ነገረን። በዚህ መሰረት ዳኞች አስቀድሞ በህግ አውጭው

የወጣ ህግ ብቻ እንደሚተረጉሙና ስልጣናቸው ህግ አውጭው ያወጣውን አዋጆችና ህጐች የመተርጐምና በዛ ብቻ የመመራት ግዴታ እንዳለበት ሰፊ ማብራሪያ ሰጠ። የአዋጁን ረቂቅ አዘጋጅቶ ለከተማው ፕሬዝዳንት እንደሚሰጥ ቃል ገባ።

አሊ አብዶ በቀጣይ ማክሰኞ በተጠራው የምክር ቤት መደበኛ ስብሰባ ላይ የመጨረሻ አጀንዳ ተደርጐ እንደሚያዝ ገለፀ። እነሆ! ምክርቤት ተጠራ። እንደተጠበቀው በምክር ቤቱ ጉባኤ ማጠናቀቂያ ላይ የማለቂያ ሰአት ተጠብቆ እንደ ተራ አዋጅ ቀረበ...

"የከተማዋን ኢንቨስትመንት ለማሳለጥ ሲባል በፍርድ ቤቶች ሲሰጥ የነበረው ሁከት ይወገድልኝ ለማስቀረት የወጣ አዋጅ... "

እጄን አውጥቼ ህገ-መንግስቱን በጠረባ ከመታው ቡድን ጋር ተቀላቀልኩ። የዲሞክራሲያዊ መዕከላዊነት እስረኛ ነኝና። ቀና ሰል ኮሚሽነር በታዛቢነት ፎቅ ላይ ተቀምጦ ተመለከትኩት።

ቀኝ እጁን አሳየኝ። ግራ እጄን አወጣሁ።

***

የሁከት ይወገድልኝ አዋጅ አያትና ሌሎች መሰል ድርጅቶችን መረን በለቀቀ መልኩ የህዝብ ሀብት መዝረፍ በር ከፈተላቸው። እነሱን ተገን አድርገው በመንግስት ውስጥ ማፊያ ቡድኖች ተፈጠሩ። ሀያት በኢህአዴግ ዙሪያ ባሉ ድርጅቶችና እንደ ወይዘሮ አዜብ መስፍንን ከመሳሰሉ ቁልፍ ካድሬዎች ጋር መልካም ግንኙነት ፈጠረ።

ዝናው ከጫፍ ጫፍ ተናኘ...

አያት! ዞሮ መግቢያዬ!

በመቀጠል አሊ አብዶ ሌላ ህገ-መንግስት የሚንድ ውል ከአያት ጋር ተዋዋለ። ይህ ዉል አያት የመኖሪያ ቤት ስራ ድርጅት የከተማዋን ቦታ እየሸነሸነ መሸጥ የሚያስችል መብት ያጐናፀፈው ሆነ። በወቅቱ ከሁለት ሚሊዮን ካሬ ሜትር በላይ የህዝብ ንብረት ለሪል ስቴት በሚል የተሰጠ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ከሲሶ በላይ የወሰደው አያት ሆነ።

ብድር በምድር እንዲሉ አያት የእነ አዜብን ውለታ ለመክፈል ተንቀሳቀሱ። በትግራይ ውስጥ በሚካሄዱ የልማትና ሌሎች እንቅስቃሴዎች በግንባር ቀደምትነት ተሳተፈ። በተለይም የትግራይ ልማት ማህበር ባዘጋጀው "ከዳስ ወደ ከላስ" በሚለው ፕሮግራም ላይ ከሀያ ሚሊዮን ብር በላይ በመመደብ ትምህርት ቤቶችን ገንብቶ አስረከበ። ለጉናና ደደቢት ስፓርት ክለብ በመቶ ሺዎች ለገሰ። ኢህአዴግ በግንቦት 20 እና የብሔር ድርጅቶች አመታዊ ክብረ

በአል ገቢ ማሰባሰብ ላይ በሚሊዮኖች በየአመቱ መስጠት ቀጠለ። ለኢህአዴግ ማእከል ግንባታ ከፍተኛ ገንዘብ ለማበርከት ቃል ከገቡት ባለሀብቶች የመጀመሪያው መስመር ተሰለፈ።

ይህንን ተከትሎ አያት ልማታዊ ባለሀብት በመባል ተደጋጋሚ ሽልማቶችን አገኘ። በአስተዳደሩ መሬት አስተዳደር ውስጥ የፈለገውን የሚሾምበት፣ የሚሸርበትና የሚያሳስርበት ደረጃ ደረሰ። ከመሬት አስተዳደር አልፎ በምክር ቤት የሚገቡ የፓለቲካ ተመራጮችን የሚመርጥበትና የሚጥልበት በር ወከክ ብሎ ተበረገደለት። በተግባርም አደረገው!

በአቶ በረከት መፅሀፍ ውስጥ "ታሪክ ራሱን ደገመ: መጀመሪያ አሳዛኝ ቀጥሎ ቧልት በሚመስል መንገድ "ተብሎ በተገለፀው ወግ በስተጀርባ ካሉት መሪ ተዋንያን አንዱ አያት የመኖሪያ ስራ ድርጅት ነበር። የዚህ ማስታወሻ ባለቤት ሀገር ጥሎ እንዲወጣ አንዱ ምክንያት ይህ አሳዛኝና ቧልተኛ ታሪክ ውስጥ ራሱን ተዘፍቆ በማግኘቱ ምክንያት ህሊናው ረፍት ስላጣች ነው።

በመሆኑም "እውን ታሪክ ራሱን ደገመ?" የሚል ጥያቄ የሚያነሳ እና ከፍተኛ ቅሌት የተሸከመ ታሪክ ይኖረናል። ጊዜውን ጠብቀን ስለ ድህረ ምርጫ 97 በሚተርከው ክፍል ራሱን በቻለ ምእራፍ እናገኘዋለን።

በአጠቃላይ መልኩ ይህ አዋጅ ከሌሎች መመሪያዎች ጋር በመቀናጀት አዲሳአባን መሬት አልባ እንድትሆን አድርጓል። በቀጣዩ ክፍል ከህጐቹ ጋር ተያይዘው በቅበብሎሽ የተፈፀሙትን የመሬት ወረራ ወደ መተረክ እንሸጋገራለን።

***

ክፍል ሶስት: የጥፉቱ ቅብብሎሽ: ከመመሪያ ቁጥር አንድ ወደ ሁለት ወደ***

ምእራፍ ዘጠኝ

መመሪያ ቁጥር አንድ!!

"መመሪያው ህገ-ወጥ ግንባታን በማያዳግም
መልኩ በቁጥጥር ስር ያውላል!"
(ፕሬዝዳንት አሊ አብዶ ፡ 1993 ዓ.ም)

የጨለማው ዘመን መሪ አሊ አብዶ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ከተንቀሳቀሰባቸው ነገሮች ዋነኛው የተወረሩ ህገወጥ መሬቶችን ህጋዊ ከለላ መስጠት ነበር። ለዚህም እንዲረዳ መመሪያ ቁጥር አንድ የሚባል ህግ በአስፈፃሚ አካል ለማውጣት እንቅስቃሴ ተጀመረ። መመሪያ ቁጥር አንድ በከተማዋ የሚገኙ ህገ ወጥ ይዞታዎችን ወደ ህጋዊ ለመለወጥ በሚል ሽፋን ተዘጋጀ።

በተቃራኒው መመሪያውን ለማፅደቅ አንድ ሳምንት ሲቀረው የተዘረፈው መሬት ብዛት በሁለት አመት ውስጥ ያለው በአጠቃላይ ተደምሮ በእጥፍ ይበልጥ እንደነበር በወቅቱ የካቢኔ አባል የነበረው አበበ ዘለአለ ያቀረበው ጥናት አመላከተ። አበበ በቁጭት ተሞልቶ፣

"መመሪያውን ማውጣት አልነበረብንም። በዚህ መመሪያ ምክንያት የተዘረፈው የህዝብ ንብረት ከሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ሲሆን ይህም ከመቶ በላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን (ቢያንስ በቀበሌ አንድ) እና አስር ደረጃውን የጠበቁ መለስተኛ ሆስፒታሎችን ይሰራ ነበር" ብሎ መመሪያው በፀደቀ አንድ ወር ሳይሞላው አጋለጠ።

ከአመክንዮ ይልቅ ስድብ የሚቀናው አሊ አብዶ፣

"አበበ! በመመሪያው መውጣት ምክንያት የሚገኘው ፓለቲካ ትርፍ በቴክኖክራቶችና ድንክዬ እድሜ በሚኖራቸው ሰዎች የሚታሰብ አይደለም" የሚል ነውረኛ አስተያየት ሰጠ። አበበ ከፓለቲካ ብቃቱ ይልቅ በፕሮፌሽናል ሙያተኝነቱ ከፍተኛ ክብር የሚሰጠው ነበር። ይህ የአሊ አብዶ ንግግር ዶንቦስኮ የሚገኘው የካድሬዎች ማሰልጠኛ ተቋም ከጐዳው በላይ አንገቱን አስደፉው።

መመሪያ ቁጥር አንድ ህግ ሆኖ የወጣበት አካሄድ በራሱ ወንጀል ነበር። በመጀመሪያ ደረጃ ከአዋጅነትና ደንብነት ዝቅ ብሎ ለምን መመሪያ ሆነ የሚለው ከህጉ በስተጀርባ ያለውን ፍላጐት ፍንትው ብሎ የሚያሳይ ነበር። እንደሚታወቀዉ የአዲሳባ ምክር ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ለአያንዳንዱ የስልጣን እርከን ህግ የማውጣት ስልጣን ይሰጣል። በዚህ መሰረት የአስተዳደሩ የህዝብ ተመራጭ ምክርቤት ከተማው ላይ ትርጉም ያለው ፓለቲካዊ ፣ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ ጉዳዮችን በአዋጅና ደንብ መሰረት ያወጣል፣ ካቢኔው አዋጆችን ተንተርሶ መመሪያ ያዘጋጃል። ከዚህ አኳያ መመሪያ ቁጥር አንድ አግባብ እንዳልሆነ የሚያረጋግጠው የምክር ቤቱን ማቋቋሚያ ሆን ተብሎ ወደ ጐን በመተው በካቢኔ ደረጃ በቆረጣ መመሪያ እንዲሆን መደረጉ ነበር።

በወቅቱ በፍትህና ፀጥታ ቢሮ ውስጥ የህግ ነክ ጉዳዮች ሀላፊ የነበረው ወልደሰንበት በመመሪያ መልክ መውጣቱን በመቃወም፣

"የጉዳዩ ባለቤት የሆነው የአዲሳባ ህዝብ መምከር ይኖርበታል፣ ከሁለት ቢሊዮን ብር በላይ የሆነ የህዝብ ሀብት ለህገወጦች እየሰጠን መሆኑን ነዋሪው አውቆ መነጋገር አለበት። ይህ ካልተቻለና ጉዳዩ ህግ ሆኖ መውጣት አለበት ከተባለ ቢያንስ የህዝብ ውክልና ያላቸው የምክር ቤት አባላት ተወያይተውበት በአዋጅ መልኩ መዘጋጀት ያስፈልጋል" በማለት አጥብቆ ተከራከረ።

ለዚህም ህጋዊ ጥያቄ ምላሱ በሙጫ የተጣበቀበት አሊ ቅሌተኛ በሆነ መንገድ የህግ ጉዳዮች ሀላፊውን ስም እየጠራ፣

"መመሪያዉ በአስቸኳይ መውጣት በከተማዋ የሚታየውን ህገወጥነት ሙሉ ለሙሉ እንደሚያስቀር ለመገንዘብ በአብዮታዊ ዲሞክራሲ አስተሳሰብ መቃኘት ብቻ ሳይሆን አይንን ገለጥለጥ አድርጐ በከተማዋ አራቱም አቅጣጫ ዞር ዞር እያሉ መመልከት ይጠይቃል" የሚል አሳፋሪ ምላሽ ሰጠ።

እነ አሊ የህግ ጭብጦችን አንስተው ምላሽ ይሰጣሉ ተብለው ባይጠበቁም፣ ይህን ያህል ወደታች ወርደው የአምላክ ስጦታ የሆነን አካል ጉዳተኝነት ላይ ያላግጣሉ ተብሎ የጠበቀ አልነበረም። ይህ ማየት የተሳነው ሀላፊ "የአስተዳደሩ የህግ መሀንዲስ" በመባል የሚታወቅ ሲሆን በአሊ አብዶና አርከበ እቁባይ የሚፈፀሙ የህግ ጥሰቶችን ፊት ለፊት በመቃወም ይታወቃል። ለግል ጥሬሶችም የመረጃ ምንጭ በመሆን የታቀዱና ሊተገበሩ የተዘጋጁ እኩይ ተግባሮችን የሚያጋልጠው አሱ እንደሆነ በካድሬዎች ዘንድ ይጠረጠር ነበር። በዚህም ምክንያት ከደረጃው ዝቅ እንዲል የተደረገ ሲሆን በምርጫ 97 የቅንጅት ቀንደኛ ደጋፊ ሆኖ አስተባብሯል በሚል መረጃ ቀርቦ ለረጅም ጊዜ እንዲንሳፈፍ ተደርጓል።

በመመሪያ ቁጥር አንድ ላይ ቀጥሎ የተነሳዉ ለምን "ቁጥር አንድ" ተባለ የሚለው ነበር። እነ አሊ የመመሪያው መውጣት በመዲናይቱ የተከሰቱ የመሬት ዝርፊያዎችን ሙሉ ለሙሉ ያስቀራል ባሉበት ሁኔታ ለምን ይህ ስያሜ ተሰጠው። የመሬት አስተዳደር ላይ ሙያተኛ የሆኑት እነ አበበ ዘልኡል፣

"መመሪያው ህገ ወጥነትን የሚያበረታታና ለሌላ አዲስ ህግ ማውጣት የሚዳርገን ይሆናል። ቁጥር አንድ ማለት በቀጣይ ቁጥር ሁለት ... ቁጥር ሰስት... እየተባለ እንደሚወጣ አመላካች ይሆናል" በማለት ተከራከሩ።

ስያሜው በራሱ ህገ - ወጥነትን ያበረታታል የተባለውን የተቃወመው አሊ አብዶ ከተማዋን በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዴት ስርአት እንደሚያሲዛት ዝርዝር የስራ እቅድ አቀረበ። "እመኑኝ በዚህ መመሪያ ምክንያት ህገ ወጥነት በማያዳግም መልኩ በቁጥጥር ስር ይውላል" አለ።

***

"ዘመቻ ጨረቃ መውጣት"

የተፈራው አልቀረም መመሪያ ቁጥር አንድ ይፉ በተደረገ ምሽት መሬት ወረራውና ግንባታው በሻማና ጨረቃ ብርሀን ተጧጧፈ። የህንፃ መሳሪያዎች፣ የሲምንቶና አሸዋ ነጋዴዎች ተቀናጅተው ወደ ጨረቃ ቤት ግንባታ ተመሙ (*የጨረቃ ቤት የተባሉበት ምክንያት ቤቶቹ ጨለማን ተገን በማድረግ በጨረቃ ብርሀን ታግዘው በመሰራታቸው ምክንያት ነው*)። መመሪያ ቁጥር አንድ በወጣ በሳምንቱ ውስጥ የቆርቆሮ፣ ሚስማርና ድንጋይ ዋጋ ጣራ ነክሰ። በሀገሪቱ የሚገኙ ገልባጭ መኪኖች የመከላከያ ካሚዮኖችን ጨምሮ የግንባታ እቃዎችን በምሽት ማመላለስ ጀመሩ።

ከቀንበላ ወደ ጨረቃበላነት የተቀየረው የጉልበት ሰራተኛ እንደአሜሪካ ሀገር በሰአት የሚከፈለው ገንዘብ ከመሀንዲስ በላይ ሆነ። ስርአት አልበኝነት ሲሰፍን ለሙያና ለሙያተኛ የሚሰጠው ዋጋ አፈር ድሜ ይበላል። ህገወጥነት ሊቀናጁ የማይችሉ ሀይሎችን በአንድ መርከብ ያሳፍራል። ለዚህም ነበር የህዝብ ትልቅ ሀብት የሆነው መሬት ሲዘረፍ፡ የመንደር ጐረምሶችና ፓሊሶች፣ ለደህንነት ስጋት የሆኑ ሀይሎችና የሀገሪቷን ሰላም ለማስጠበቅ ሀላፊነት የተሰጣቸው የመከላከያ መኮንኖች፣ የአስተዳደሩ ደንብ አስከባሪና ደላላው የጋራ ትኬት ቆርጠው መሳፈራቸው።

መመሪያውን ተከትሎ በነበሩት ወራት የተሰሩት የጨረቃ ቤቶች የግንባታ ሂደት አሳዛኝም፣ አስገራሚም ነበር። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ

የቆርቆሮ ቤት በሁለት ምሽቶች ተሰርቶ ለአገልግሎት አሊያም ለመሸጥ ዝግጁ ሆነ ቢባል የማይታመን ይሆናል።

እውነቱ ግን ይህ ነበር።

በእነዚህ ወራት ከአርብ ማታ እስከ አስከ እሁድ ምሽት ያለውን የስራ ሂደት ማንሳቱ አስገራሚነቱን ሊያሳይ ይችላል***

እንደሚታወቀው የመንግስት ስራ ቅዳሜና እሁድ ይዘጋል። ለሰራተኞች የእረፍት ቀን ይሆናል። የፀጥታና ህገ ወጥ ጉዳዮችን የሚከታተለው ከፍልም የመንግስት ሰራተኛ ስለሆነ በመስክ ላይ ተገኝቶ ግንባታዎችን አይቆጣጠርም። ይልቁንስ በሰንበት ቀናት ተገንብተው ከተሸጡት ቤቶች ውስጥ በአብዛኛቹ ላይ እነዚህ ደንብ አስከባሪዎች ተሳታፊዎች ነበሩ። በህገወጥነት ገንብቶ ከመቸብቸቡ በተጨማሪ ለስርአት አልበኞቹ መረጃ በማቀበል ቅድመ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ያግዛሉ።

የጨረቃ ቤቱ ግንባታ የስራ ሂደት የሚጀምረው በከተማው የመሀል ቦታዎች በሚገኙ ሰፋፊ ግቢ ያላቸው ቤቶችና የኳስ መጫወቻ ሜዳዎች ላይ ነበር። በየቦታው በከተማዋ ባዶ ቦታዎች በተለይም የዳርቻ አካባቢዎች የተደራጁ ሰዎች በትራክተር በመታገዝ አፈር እየቆፈሩ ይቆልላሉ። ገልባጭና የመከላከያ ካሚዮኖች ከሰኞ እስከ አርብ የተዘጋጀውን አፈር ወደ መሀል አዲሳባ የግለሰቦች ግቢና ሜዳዎቹ ያግዛሉ። ጦር ሀይሎች፣ ልደታ፣ ቄራ፣ አብነት፣መሳለሚያና ጎፋ ሰፈሮች በከፍተኛ ሁኔታ በጥቅም ላይ የዋሉ ቦታዎች ነበሩ። የተራገፈው አፈር እርሾ ተጨምርቦት በእለቱ በመቡካት ወደ ጭቃነት ይቀየራል፣ እስከ አርብ ማታ እየተገላበጠ እንዲቆይ ይደረጋል።

በመሀል ከተማ በተለይም በጦር ሀይሎች፣ ልደታና ሳርቤት አካባቢዎች ተለጥፈው የነበሩት የጭቃ ሽያጭ ማስታወቂያዎች በራሳቸው አዝናኝ ነበሩ።
የጭቃውን ጥንካሬ ለማሳየት፣

"ሲምንቶ የሚያስንቅ ጭቃ እዚህ ይሸጣል!"፣

"አንድ ወር ሙሉ ተጨንቀን ያቦካነው ጭቃ አለ ጐራ ብለው ይጠይቁ "፣

"በከተማችን ታዋቂ ጭቃ አቡኪዎቹ በለጠ ፣ቢሆነኝና ጆርጌ ያቦኩት ጭቃ እንዳያመልጥዎት" ይላል።

ውበቱንና አስቸኳይነቱን ለማሳየት ደግሞ፣

"በአድአ ጤፍ የተበካ..."፣

"ጊዜ የለንም ጭቃ መሸጫ"፣

"ውጤት ተኮር ጭቃ ቤት" የሚሉ ይገኙበታል።

በእለተ አርብ ፀሀይ መጥለቅ ስትጀምር የጭነት መኪኖቹና ካሚዮኖቹ የተዘጋጀውን ጭቃ ወደ መጫን ይሸጋገራሉ። ሌሎች ተሽከርካሪዎች በአዲሳባ ዙሪያ ከሚገኙ የኦሮሚያ ከተሞች ለጨረቃ ቤቱ መስሪያ የሚያገለግሉ ቋሚ፣ ማገርና ፍርግርግ አንጨቶችን ተሸክመው ወደ ግንባታ ቦታ ይተማሉ። አቅርቦቶች መሞላታቸው ሲረጋገጥ ግንባታ ይጀመራል።

ማታዉኑ የቤቱ አፅምና ቆርቆሮ ሽፉን ይጠናቀቃል። ቅዳሜ ጠዋት ማገርና ጭቃ መለጠፍ ጐን ለጐን ይካሄዳሉ። እስከ ማታ ድረስ አዲሱን ቤት የማደላደል፣ የላስቲክ ምንጣፎች የመዘርጋት ስራ ይሰራል። ከነባር ቤቶች በአንድ አንፓል እስከ መቶ ብር በወር የሚከፈልበት መብራት ይጠለፉል። ከነባር ወደ አዲሱ ጨረቃ ቤቶች የሚዘረጋዉ የኤሌክትሪክ ገመድ በኪሎሜትሮች የሚጠጋ ሲሆን እርስ በራሱ ተጠላልፎ የኤሌክትሪክ አውቶብስ የተዘረጋበት ይመስላል።

ከቅዳሜ ማታ ጀምሮ እስከ እሁድ ረፉዱ ድረስ የጨረቃ ቤቶች ሽያጭ እጅ በእጅ ይከናወናል። ቤቱን ሰርቶ ለማጠናቀቅ አስር ሺህ ብር የፈጀበት ህገ - ወጥ በሁለት ቀን ውስጥ እስከ ሀምሳ ሺህ ብር ይቀበላል። ብዙዎቹ በአንድ ጊዜ ከልለው የሚይዙት ቦታ አስከ አስራ ሁለት ቤቶች የሚያሰራ በመሆኑ በሳምንት ውስጥ ወደ ሚሊየነርነት ይቀየራሉ። የራሳቸው ጋንግስተር ቡድን ያደራጃሉ። ይህ አደገኛ ስብስብ አካባቢውን በቁጥጥር ስር በማዋል የትኛውም የመንግስትና ፀጥታ ሀይል አካባቢው እንዳይደርስ ያደርጋል። የአስተዳደሩን ባለስልጣናት፣ ፓሊስና መከላከያ ውስጥ ያሉ ሌቦች የቡድኑ ስውር አባል በመሆን መረጃ ያቀርቡለታል።

በሌላ በኩል በቤት እጦት የሚሰቃዩ ነዋሪዎች "የጨነቀው እርጉዝ ያገባል" አንደሚባለው ያላቸውን ጥሪት ሸጠውና በጐደለው ተበድረው ቤቶቹን ይገዛሉ። የዛኑ እለት በተጠንቀቅ ከሚጠብቁት የጭነት መኪኖች ጋር በእጥፍ ዋጋ በመዋዋል እቃቸውን ወደ አዲሱ ጐጆ ያጓጉዛሉ። በትራንስፓርት ለማስጫን ካወጡት ያልተናነሰ በመከፈል በጫኝና አውራጅ እቃቸውን ያራግፉል። ለሰው ልጅ ኑሮ መሰረታዊ ነገሮች ተደርገው የሚቆጠሩት እንደ የመጠጥ ውሀ ፣የፍሳሽ አገልግሎት፣ መንገድ፣ ትራንስፓርት፣ ትምህርት ቤት፣ የጤና ጣቢያ... በሌለበት ሁኔታ ቤተሰቡ ተሰብስቦ በጨረቃ ቤት መኖር ይጀመራል። ህገ ወጥ በመሆን ተከትሎ የሚመጣው ውጣ ውረድ የእለት ተእለት ህይወት ይሆናል። ወደ ስራና ትምህርት ቤት ለመሄድና ለመምጣት መከራቸውን ይበላሉ። ለሰአታት ከጅብ ጋር እየተጋፉ በእግራቸው ይጓዛሉ። ሚስትና ልጅ እንዳይደፈሩ ይጠብቃሉ። ውሀ ወለድ በሽታ እንደ ጉንፉን ይፈራረቅባቸዋል።

***

የጨለማው ዘመን ታሪክ የጫኝና አውራጆችም ስለነበር ጥቂት ስለእነሱም እናውጋ፦

በአዲሳባ ከተማ ነዋሪዎች ዘንድ ጫኝና አውራጅ በማለት የሚታወቁት ወጣቶች የመስፉፉት መንስኤ በከተማው ተንሰራፍቶ የነበረው ስርአት አልበኝነትና ህገ - ወጥ ግንባታ ነበር። አስተዳደሩ በሁሉም ጉዳዮች ላይ የተኮላሸና የነቀዘ በመሆኑ በተስፉ መቁረጥ ምክንያት ያገኟትን ቀዳዳ ህጋዊና ህገ-ወጥ መንገዶችን በመጠቀም ጥቅም ለማግኘት የተደራጁ ቡድኖች ናቸው።

ጫኝና አውራጆች ወደ አደገኛ ቡድን ከመቀየራቸው በፊት በአካባቢያቸው ለሚካሄዱ ህጋዊ ግንባታዎች ግብአት የሚሆኑ ቁሳቁሶችን በማውረድና በመጫን ይተዳደሩ ነበር። በሂደት ከማውረድና ማውጣቱ በተጨማሪ አፈርና ድንጋይ በመቆፈር ወደ መሸጥ ተሸጋገሩ። ቀስ በቀስ ከመሀከላቸው የቀለም ትምህርት የቀመሱትና ረብሻ ጠል የሆኑት ትላልቅ የጭነት መኪናዎችን ወደ መግዛትና ለግንባታ የሚያስፈልጉ ግብአቶችን ማቅረብ ጀመሩ። አንዳንዶቹ ደግሞ እነ አሊ አብዶ ካሰማሯቸው የመንግስት አካላት ጋር በመሰማጠር ወደ መሬት ደላላነት በመቀየር በአጭር ጊዜ ውስጥ በአስር ሺህ ብሮች መቁጠር የአለት ስራቸው ሆነ።

በፀብ አጫሪነትና አደገኝነት የሚታወቁት ደግሞ የበለጠ አስፈሪ በመሆን የመንደር መንግስታት አለቆች ሆኑ። በቁያቸው የሚካሄዱ ማንኛውም እንቅስቃሴ የእነሱን ይሁንታ ካላገኘ መፈፀም የማይችልበት ደረጃ ተደረሰ። ወደ ለየለት ማጅራት መቺነት ተቀየሩ። በ600 ብር የተገዛ ወንበርና ጠረጴዛ ከመኪና ላይ ለማውረድ መቶ ብር ይጠይቃሉ። የእቃው ባለቤት ራሱ ማውረድ ከፈለገ እስከ 25 ብር የኩቴ መክፈል ግዴታ ሆነ። ቁሳቁሱን ጭኖ የመጣው ሹፌርም ተመሳሳይ ግብር ይጥሉበታል።

የመንደር መንግስታት በትናንሽ የጉልበት ስራዎች ሳይቀር ግብር መቀበል ጀመሩ። በወቅቱ አንገብጋቢ ለነበረው የውሀ ችግር በከፍተኛ ደረጃ ጥቅም ላይ ውላ የነበረችው እንሰሳ አህያ የነበረች ሲሆን አንድ ጄሪካል ውሀ እስከ ሀያ ብር ይሸጣል። ከውሀ ሽያጭ ከተገኘው ገቢ ሩብ ያህሉ ለእነዚህ ለመንደር አለቆቹ ይሰጣል።

የጨረቃ ቤቱን ገዝቶ የገባው ነዋሪ ሚስቱና ልጁ በሰላም ወጥተው

እንዲገቡ በየቀኑ ገንዘብ ይከፍላል። አንዳንዶቹም ህሊና በሚጐዳ መልኩ አንዷን ልጅ ለመንደር አለቆች ገብረው ራሳቸውንና የተቀረ ቤተሰባቸውን ይታደጋሉ።

የጫኝና አውራጆች ቡድኖች የራሳቸውን ክልል ያሰመሩ ሲሆን አንደኛው ወደ ሌላው ገብቶ መስራት አይችልም። ይህንን ተላልፎ የተገኘ በስለታማ ጦር መሳሪያዎችና በድንጋይ ይወገራል። የአንዱ መንደር አለቃ አጉራዘለል ሆኖ የድንበር ማስፋፊያ እርምጃ ቢወስድ ሌሎች ተረባርበው አይቀጡ ቅጣት አሳርፈውበት ወደ ነበረበት ቦታ ይመለሳል።

እነዚህ የመንደር መንግስታት ራሳቸውን በማጠናከር የጦር መሳሪያ እስከመታጠቅ ደርሰው ነበር። በአንድ ወቅት የኮልፌ ቀራንዮ ፓሊስና ደህንነት ባደረገው የተቀናጀ አፕሬሽን ከአንድ ቡድን ብቻ አምስት ሽጉጦችንና ሶስት "ቆመህ ጠብቀኝ" ጠመንጃዎች አግኝቷል። የቡድኑ አለቃዎች በቁጥጥር ስር ውለው በተደረገባቸው ምርመራ አስደንጋጭ ሚስጥሮችን አውጥተዋል። ከላይ እስከ ታች የተዘረጉ የሌብነት ሰንሰለቶችን አጋልጠዋል።

***

የመንደር መንግስታት የሆኑት ጫኝና አውራጆች እያደር ከሰሙ። የምሽት ጭፈራ ቤቶች - የባህል ሙዚቃ ቤቶች - ውስኪ ቤቶች - ራቁት ቤቶች ማደሪያቸው ሆነ። በቀን ያለልፉት የሚያገኙትን ገንዘብ ልደታ፣ ካዛንችስ፣ ዶሮ ማነቂያ የቡና ቤት ሴተኛ አዳሪዎችን በየቀኑ ቀያየሩበት። ያለ እውቀትና ግንዛቤ ባገኙት ገንዘብ የማይድን በሽታ ገዙበት። በወረርሽኝ መልኩ ኤች አይ ቪ ኤድስ ያዛቸው። አብዛኞቹ ያለ እድሜያቸው ተቀጩ።

ጨለማው ሳይነጋ የእነሱ ዘመን ተፈፀመ።

***

የጥፋት ቅቡበሎሹ በጨረቃ መኖሪያ ቤቶች ብቻ አልተገደበም። ሌሎች ማህበረሰቡ የሚጠቀምባቸው አስተምህሮና የህክምና ተቋማት ጨረቃን ተገን አድርገው ተገንብተዋል። መዋዕለ ህፃናት፣ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ክሊኒክ፣ እና የሀይማኖት ተቋማት የሚጠቀሱ ናቸው። በተለይ ቤተክርስትያኖችን (የሁሉም ክርስትና እምነቶች) እና መስኪዶቹን ከህገ - ወጦች መሬት በመግዛት ጨለማን ተገን ተደርጐ ግንባታ ሲሰራ ማየት የስርአቱ አልበኝነት ምን ያህል ስር የሰደደ መሆኑን የሚያሳይ ነበር።

አንደ እውነቱ ከሆነ የእምነቱ አባቶች በዚህ መልኩ የተቋቋመን ማምለኪያ ቦታ ለመንፈሳዊ ስብከት ሲያውሉትና ለህገ - ወጦች ጠበቃ ሆነው

ሲከራከሩ ማየት የተለመደ ነበር። በእርግጥ ብዙዎቹ የእምነት አባቶች በሚያገለግሉበት የእምነት ተቋም አጠገብ የጨረቃ ቤት ባለቤቶች ስለሆኑ ለህገወጥነት ጠበቃ ቢቆሙ የሚገርም አልነበረም...

እነሱስ ቢሆን የጨለማው ዘመን አካል አይደሉ!

መመሪያ ቁጥር አንድን ተከትሎ የተዘረጋው የጥፋት ቅብብሎሽ በዚህ አላበቃም። በመንግስት ስልጣን ላይ ያለው ህገ ወጥ ሀይል የግለሰብ ቤት ኪራይና የቤት ችግር አናቱን አዙሮት የጨረቃ ቤት በመግዛት ቤተሰቡን ሰብስቦ የሚኖረውን የከተማው ነዋሪ ለሁለት ከፍለው ቀይ መስመር ያሰምራሉ። ከመስመሩ ወዲህ በመመሪያ ቁጥር አንድ የሚሸፈኑ፣ ወዲያ ደግሞ በቅርብ ጊዜ የሚፈርሱ የሚል ትእዛዝ ያስተላልፉሉ፣ የማፍረሻ ማስጠንቀቂያዎች ይሸገሙደገሙዳል።

ጥሪቱን ሸጦ፣ ተበድሮና ተለቅቶት የጨረቃ ቤት በመግዛት ኑሮ የጀመረውና ከመስመሩ ወዲያ ያለው ህዝብ ከፓሊስና አፍራሽ ግብረ ሀይሉ ጋር ለመፋለም በየቦታው መደራጀት ጀመሩ። የጦር መሳሪያ እስከመታጠቅ ደረሱ።

በከተማዋ በሚገኙ ማስፋፊያ ወረዳዎች የተሰሩትን የጨረቃ ቤቶች ለማፍረስ የፌዴራል እና የአዲሳባ ፓሊስ ከአፍራሽ ግብረ ሀይሉ ጋር በመቀናጀት "ዘመቻ ጨረቃ መግባት" ለማስፈፀም ተንቀሳቀሱ። የሰው ህይወት በየቦታው መውደቅ ተከተለ። ወላጆች ከነልጆቻቸው ወደ ገዳና ወጡ።

በወቅቱ የነበረውን አሪታና ዋይታ በታዘብኩ ቁጥር በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ኢህአዴግ የፈውዳሉን ስርአት አስከፊነት ለማሳየት በአንዲት ገጠራማ አካባቢ የተፈፀመውን ግፍ በፊልም አስደግፎ በተደጋጋሚ ያሳየንን ያስታውሰኛል። በፊልሙ ላይ አንድ ፊውዳል በትራክተር የገበሬውን ቤት ሲያፈርስ ያሳያል። ገበሬዎቹ ጐጆአቸው በዶዘር እየተገረሰሰ እያዩ ባላባቱን መሬት ላይ ወድቀው ይለምኑታል። ተማፅኖአቸውን ከቁብ ሳይቆጥር ጐጆአቸውን ሲቦድሰው ወጣቱ ገበሬ ላይ የሚንቀለቀለውን የበቀል እሳት ከተሌቪዥኑ አልፎ ተመልካቹን ይለበልባል።

የገበሬው ትናጋ እሳት ፊውዳሉን እንዴት እንደጠበሰው የቅርብ ጊዜ ታሪካችን ነው። ያለውን ብቻ ሳይሆን ከሰው የተበደረውን ያጣው የአዲሳባ ከርታታ፣ በህገወጥ አካባቢ በመኖሩ ሚስቱና ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ሴት ልጆቹ የተደፈሩበት ምስኪን... ከገበሬው ባልተናነሰ ኢህአዴግን ቢጠላና በምሬት ቢሞላ ያንስበት ይሆን?፤ ለሃይማኖቱ ቀናኢ የሆነ ህዝብ የሙሴ ትዕዛዛት ተፅፎበታል ብሎ በሙሉ አይኑ ለማየት የማይደፍረውን ፅላት

(ታቦት) በፓሊስ መኪና ላይ እንደወንጀለኛ ተጭኖ፣ ጣቢያ ለኤግዝቢትነት ከተቀመጠ ጦር መሳሪያ ተቀላቅሎ ሲያየው መንስኤው ምንም ይሁን ምን እንደውርደት መቁጠሩ ይቀራል?

የማፍረሱ ሂደት በሁለት ቢላዋ ለሚበሉት የመንደር መንግስታት ጥሩ አጋጣሚ ነበር። በአንድ በኩል በተልእኮ ተዋጊነታቸው ገንዘብ ከህገ ወጥ ቤቱ ባለቤት ይቀበላሉ። በሌላ በኩል ቆርቆሮና እንጨት እየነቀሉ ወደ ራሳቸው ማከማቻ መጋዘን በጭነት መኪና ይወስዳሉ። መንግስት ያሰማራቸው አፍራሽ ግብረ ሀይሎች ድርጊትም ተመሳሳይ ነበር። የሚታወቅ ትልቁ ደሞዛቸው የፈረሱትን ቆርቆሮ መከፋፈል ነበር። እናም ያፈረሱትን ቆርቆሮ በመሰብሰብ በሽንኩርት ዋጋ ሲሸጡ ታሳቢ የተደረገው መመሪያ ቁጥር ሁለት እንደሚሆን የሚያጠራጥር አልነበረም።

ምእራፍ አስር

መመሪያ ቁጥር ሁለት!

"ከእንግዲህ ህገ -ወጥ ግንባታ ታሪክ ይሆናል!!"

(ከንቲባ አርከበ እቁባይ፡ 1995 አ፦ ም፦)

የማስታወሻው ጉዞ እንደ ፔንዱለም ነውና ገመዷ ከአንደኛው ጫፍ ወደ መሀል ቀርባለች። የተፈፀሙት ጥፋቶች በቅብብሎሽ ስለሆነ ተያያዥነት ያላቸውን ቁም ነገሮች አስተሳስሮ መመልከቱ የተሻለ ስለሚሆን...

ወደ ወጋችን እንመለስ...

የመመሪያ ቁጥር አንድ በተግባር ላይ መዋል ህገ ወጥነቱ በተደራጀ መንገድ እንዲጧጧፍ አደረገው። በፊት መስመር የተሰለፉት የመንግስት ባለስልጣናት፣የኢህአዴግ ካድሬዎች፣ የፓሊስ አባላት፣ የመከላከያ መኮንኖች፣ የአስተዳደሩ የመሬት ልማት ሙያተኞ ሆኑ። አዳዲስ ስያሜ ያላቸው ማህበራት ዶሴ እየተከፈተላቸው ተደራጁ። በአስተዳደሩ ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ የቅየሳ ሙያተኞችና መሀንዲሶች የመንግስት ተሽከርካሪዎችንና የቅየሳ መሳሪያዎችን በመጠቀም ወደ መሬት ሽንሸና ተሸጋገሩ። ከፍፍሉ እንደ ቀድሞው ጨረቃን ተገን በማድረግና በሰንበት ብቻ አልነበረም። በመደበኛ የመንግስት ስራ ሰአት በአዘቦት ቀን ጭምር የሚከናወን ሆነ።

ለዚህኛው የተደራጀ ዝርፊያ መሰረት ከጣለው መመሪያ ቁጥር አንድ በተጨማሪ ህገ - መንግስቱን በጠረባ የመታው "የሁከት ይወገድልኝ "አዋጅ የጐላ ሚና ተጫውቷል። ከዚህ አዋጅ በፊት መሬቶቹን በባለቤትነት ይዘው ሲያርሱ የነበሩ ገበሬዎች እንዲነሱ በሚደረግ ሰአት የካሳ ጥያቄና ሌሎች ከመሬቱ ጋር ተያያዥነት የላቸውን መብቶች ለማስከበር ለፍትህ አካላት አቤቱታ ያቀርቡ ነበር። በዚህም ካልተስማሙ ህገ-መንግስታዊ መብታቸውን በመጠቀም ወደ ፍርድ ቤት በመሄድ ክስ ያቀርባሉ። ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን በደንብ አጣርቶ ብይን እስኪሰጥ የመሬት ይዞታው ባለበት እንዲቆይ የእግድ ትእዛዝ ይሰጣል።

ከአዋጁ መውጣት በኋላ የገበሬው መብት ሙሉ በሙሉ ተገፈፈ። የአርሶ አደሩ አቤቱታ "የተሰጠኝ ካሳ ያንሰኛል" ወደሚል የወረደ ጥያቄ ተሸጋገረ።... ይህም ሆኖ የተገመተለትን ካሳ ለማግኘት ከአንድ ቢሮ ወደ ሌላ መንከራተቱና ቢሮክራሲው አማረረው። በዛ ላይ የተደራጀው የዝርፊያ ቡድን ለካሳ እጅ በእጅ የሚያቀርብለት ገንዘብ እጥፍ የላቀ ሆኖ አገኘው። በኢህአዴግ ፍቅር ያበደው ገበሬ ሳያቅማማ መሬቱን ለቀማኛ በዜሮ ዋጋ አስረክቦ ወጣ።

እንደ እውነቱ ከሆነ በኩተማው አርሶ አደር ላይ የተሰራው ግፍ በዘር ማጥፋት ወንጀል የሚያስጠይቅ ነው።

እንዲህ ነበር የሆነው።

ያለአንዳች ቅድሚያ ትምህርትና ዝግጅት መሬቱን ለመንግስትና ህገ ወጦች ያስረከበው ገበሬ ለካሳ የተሰጠውን ገንዘብ እንደ ጨው ዘራው። በመጀመሪያ አካባቢ በፉሽን መልኩ አርሶ አደሩና ወጣት ልጆቹ የሚኒባስ ታክሲ ባለቤት ሆኑ። መንፈቅ ሳይሞላው የመኪናዎቹ ወጪ ከገቢያቸው በለጠ። በወረደ ዋጋ ለሌላ ሸጡት። በተረፈው ገንዘብ አባት ወደ ውሽማና አረቄ፣ ልጅ ወደ ሴተኛ አዳሪ አቅማዳቸውን ሸከፈው ገቡ። የድርጊቱ ውጤት በአጭር ጊዜ ታየ። እናት መጀመሪያ ባሏን፣ ቀጥሎ መሬታቸውን ከተቀሙ በኃላ የፈጠረቻቸውን ህጻናት ልጆቿን ቀበረች። ታላቅ ልጅ እናቱን ቀበረ። ታዳጊ ልጆች ታላቅ ወንድምና እህታቸውን ቀብረው ወደ ጐዳና ወጡ።

ይህ! በቀራንዮ የነበሩት የአንፎ፣ ታጠቅ፣ ጀሞና ቀርሳ ሰፈሮች ታሪክ ነው!

ይህ! በአቃቂ የሚገኙት የአቡ ጨፈ፣ገላን፣ ቂልንጦ፣ቀርሳ ቀበሌዎች ታሪክ ነው።

ይህ! በቦሌ የነበሩት የቡልቡላ፣ የረር በርና ገራ ሰፈር ገበሬዎች ታሪክ ነው።

ይህ! በላፍቶ ሀና ማርያም ይኖሩ የነበሩ ገበሬዎች ታሪክ ነዉ።

ይህ! በአዲሳአባ የሚገኙ 29 ገጠር ቀበሌዎች የዘር ማጥፋት ወንጀል ነው።

ይህ! በኢህአዴግ ፍቅር የተቃጠለውና ፓርቲው "ተኛ" ሲለው የሚተኛው አርሶ አደር ገድል ነው። የስምአን ልጅ እንዳለው ተኛ ተብሎ ተኝቷል። ችግሩ "ተነስ!" ከተባለ ነው። ለዘላለሙ ስላንቀላፉ!

በሌላ በኩል የማፊያው ቡድን መንግስታዊ ቅርፅ የያዘ በመሆኑ በግላጭ መሬቱን ወደ መከፋፈል ገባ። የከተማዋ ማስተር ፕላን እየተመሳከረ መሸንሸን ተጀመረ። በፕላን የተደራጁ ባዶ መሬቶች ዝግጁ ሆኑ። ሰፋፊ አውራና ውስጥ ለውስጥ መንገዶች ተቀየሱ። የትምህርት ተቋማት፣ ጤና ኬላ፣ አረንጓዴ ቦታዎች

ለብቻቸው ተከልለው ታጠሩ። ከአስራ ሁለት እስከ ሀያ መደቦችን አንድ ላይ በማጣመር የማህበር ስያሜ ተሰጣቸው፡ - መብረቅ ፣አንድነት ፣ጣምራ -ጦር፣ ሀገሬ፣ እፎይታ፣ ዞሮ መግቢያዬ...

አብዛኛቹ የማህበር ስያሜዎች ቢደርግ ዘመን ቤት ለመስራት ለማዘጋጃ ቤት ቀርበው የነበሩ ናቸው። ይህም ማህበራቱ ጥንት መደራጀታቸውን ለማሳየት ሆን ተብሎ የተደረገ ነበር። በመሆኑም መዝገቦቹ አቧራቸው ተራግፎ መጠሪያቸውንና የአባሎቻቸውን ስም ዝርዝር ሳይለቁ ወደ ማስፉፊያ ቦታዎቹ መጡ። የማህበሩ አባላት በስም ይገለፅ እንጂ በአካል አልነበሩም። ግማሾቹ ሞተዋል፣ ከፊሉ ሀገር ጥሎ ተሰዷል፣ ሌላው ከቀድሞ ስርአት ጋር በተያያዘ ወህኒ ተወርውሯል፣ የተቀረው ደግሞ ከደርግ ጋር አብሮ የተቀበረ ፉይል ስለመሰለው እርግፍ አድርጌ ትቶታል።

የቀድሞዎቹ ማህበሮች ነብስ እንዲዘሩ የተደረጉት በወቅቱ የመሬት አስተዳደር ባለስልጣን በነበረው አርቴክት አማረ አስግዶምና አሊ አብዶ አማካኝነት ነበር። ሁለቱም የራሳቸው ማፊያ ቡድን ቢኖራቸውም ተቀናጅተው ማህበሩንና የተሸነሸነውን መሬት አዋደዱ። ሁሉ ሙሉ፣ ሁሉ ዝግጁ የሆነው መሬት አየር ባየር መቸብቸብ ተጀመረ። እነ አማረ ቢጠሯቸው የማይሰሙበት ደረጃ ደረሱ። ነግቶ በመሸ ቁጥር ሚሊየነሮች መፈልፈል ጀመሩ። የቤት እጦት ያማረረው የመዲናይቱ ነዋሪ ለሁለተኛው ዙር የጥፉት አዙሪት ቀበቶውን ፈታ።

ሌባ ሲካፈል እንጂ... እንደሚባለው አማረና አሊ አብዶ ከፍተኛ ፀብ ውስጥ ገቡ። ይህን ተከትሎ አርትቴክቱ ለሀገሩ ልጅና ለሞከሸው የሪፓርተር ጋዜጣ ባለቤት መረጃዎችን ማሹለክ ጀመረ። ዳጐስ ያለ ገንዘብ እንደተቀበለ የሚነገረው ሪፓርተር የአሊን ዱካ እየተከተለ ማጋለጥ ጀመረ። የአስተዳደሩን መሞሸሸና መከላሸት በሁሉም የጋዜጣው አምዶች አስተጋባ። አልፎ በመሻገር በርዕሰ አንቀፁ የሚከተለውን ታሪካዊ ስንኝ አሰፈረ፣

ወይ አዲሳባ ወይ አራዳ ሆይ፣
አለ አሊ አብዶ አላየሽም ወይ።

በሌላ በኩል አሊ አብዶ አርቴክቱን ለማባረር ሌሎች የሌብነት ዶሴዎችን ይዞ ብቅ አለ። በመዲናይቱ የተገነቡት አዳዲስ ግዙፍ ህንፃዎች ካርታና ፕላናቸውን ለማፅደቅ አማረና ቡድኖቹ እስከ ሀምሳ ሺህ ብር እንደሚጠይቁ በመረጃ አስደግፎ አቀረበ። በዚህ ሌብነት ብቻ አርክቴክቱ ከአምስት ሚሊዮን ብር በላይ ሀብት ማካበቱን አጋለጠ። መረጃዎቹን አሊ አብዶ በስሜት ተነሳስቶ በካድሬዎች ፊት በመዘርገፉና እውነተኛ ስለነበሩ ያለደብዳቤ እንዲያባርረው ተፈቀደለት። አሊ አብዶ ደስ አለው... ትልቅ ድራማ

የድራማው ከፊል ገቢር የሚከተለው ነበር። አማረ አስገዶም የህውሀት ባለሀብቶችን መፍጠርና ማገዝ በሚለው ቡድን ውስጥ ተደራጅቶ ከሚንቀሳቀሱ ቁልፍ ሰዎች አንዱ ነበር። ከመሬት ጋር በተያያዘ ለህውሀት ሰዎች የሀብት ምንጭ ሆኗል። ለራሱም አልቦዘነም። ከእለታት በአንዱ ቀን የሚሊየነሮች መስመር ውስጥ ተሰልፎ ተገኘ... እናም በአሊ አብዶ ተባረረ። ጊዜውን ጠብቆ የአብዶ ልጅ "ዘባተሎ፣ ዝርክርክ" ተብሎ ሲሰናበት የአርከበ የምህንድስና ጉዳዮች ዋና አማካሪ ሆኖ በድጋሚ ማዘጋጃ ቤት ገባ።

አርቴክቱ የሰራቸው ወንጀሎች አይን ያወጡ ነበሩ። ከምርጫ 97 በኃላ ከማዘጋጃ ቤት ውስጥ የከተማዋን ካርታ (ማስተር ፕላን) ከአርከበ ጋር በመሰማጠር አሰርቆ አውጥቷል። ይህን ያደረጉት ከምርጫው በፊትና በኋላ የፈፀሙትን ወንጀል ለመሸፈን ነበር። ጠቅላይ ሚኒስትር ሀይለማርያም ዱባይ ድረስ በመሄድ ኮፒውን ገዝቶ መጥቷል።

ይህ አይን ያወጣ ዘረፋ ጥርስ ሳያበቅል በድዱ የሚኖረው የፀረ ሙስና ኮሚሽን ተረጋግጦ ይፉ ሆኗል። ኮሚሽኑ በኮልፌ ቀራንዮ ብቻ 26 ማህበራት በህገ ወጥ እንደተደራጁ አሳውቋል። የአማረ ግብረአበሮች ከመቶ ሚሊዮን ብር የሚጠጋ የህዝብ ንብረት ላይ ጉዳት በማድረስ ተከሰው ቃሊቲ ወርደዋል። አማረ ደግሞ የሰረቃትን ፕላን ተሸክሞ ተወዳጁ አርከበን አጅቦ ወደ ስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ሄደ!

***

በፕላን የተሰሩት ህገወጥ ግንባታዎች ተጠናቀቁ። ቤቶቹን የገዛው ነዋሪም ጠቅልሎ ገባ። ቀስ በቀስ የመሰረተ ልማት ጥያቄዎች በነዋሪዎቹ መነሳት ጀመሩ። በተለይ የመብራት ጥያቄ ጊዜ የማይሰጠው ሆነ። ነዋሪዎቹ መሬቱን የቸበቸቡላቸውን የመንግስት አስተዳደሮች ማስጨነቅ ጀመሩ፣ "መመሪያ ቁጥር ሁለት ይወጣል ብላችሁ ነበር፣ በማይቀመስ ዋጋ ሸጣችሁልን ለምን የውሀ ሽታ ሆነ" የሚል ቅሬታ መቅረብ ጀመረ ። ይህንን የነዋሪው ቅሬታ ተከትሎ ሚስጥሮች ማፈትለክ ጀመሩ። በተለይ ከ16 ማህበራት በላይ የተፈጠረባት ወረዳ 24 (ኮልፌ ቀራንዮ) የተቃውሞው ማእከል ሆነች።

በወረዳ 24 ልዩ መጠሪያው ጊዮርጊስ በሚባለው አካባቢ ከተመሰረቱት ህገ-ወጥ ማህበሮች አንዱ "መብረቅ" ይባላል። ማህበሩ የተመሰረተበት ቦታ በከፍታ ቦታ ላይ በመሆኑ ቁልቁል አዲሳባን ለማየት ያስችላል። ማታ ማታ ከከተማው መብራት ጋር ልዩ ውበት ይሰጠዋል። በዚህ

ቁልፍ ቦታ የተመሰረተው የመብረቅ ማህበር ባለቤትነቱ የአሊ አብዶና የወረዳው ሊቀመንበር የነበረችው ሙለሜ ረሺድ በጥምረት ነበር።

የመብረቅ ማህበርን መሬት ገዝተው መኖሪያ ቤት የገነቡት ነዋሪዎች ጊዜ ጠብቀው የመብራትና ውሀ ይግባልን ጥያቄ በማንሳት የወረዳዋን ሊቀመንበር መቆሚያ መቀመጫ ያሳጧታል። የሰዎቹን መመላለስ የከነከነው የወረዳው ደህንነት (ዘካሪያስ ይባላል) ክትትሉን አጠናክሮ ይቀጥላል።

ከእለታት በአንዱ ቀን ጠልፎ የሚያዳምጠው የሊቀመንበሯ የቢሮ ስልክ ያልጠበቀውን መረጃ አፈሰሰለት። ሴትየዋ ከአሊ አብዶ ጋር እያወራች ነበር። መብረቆች በመብራትና ውሀ ጉዳይ እንዳስጨነቋት ትነግረዋለች ። የውሀውን እሱ እንደሚጨርስ ለመብራት ሀይል ባለስልጣን ግን የድጋፍ ደብዳቤ እንድትፅፍላቸው ይነግራታል። ደብዳቤ ታዘጋጃለች። የወረዳው ደህንነት ደብዳቤዎችንና ሌሎች ዶክመንቶችን ቢሮዋን በሚስጥር ቁልፍ በመግባት በእጁ ያስገባል። ለሙስና ክስ ማደራጀት ይጀምራል፣ ለእኛም መረጃውን ይሰጠናል። በዚህ ሁኔታ ላይ እያለ ነበር ያልተጠበቀ ነገር የተከሰተው።

ጉዳዬ እንዲህ ነው።

የኔዘርላንድ መንግስት ለከተማው አስፈፃሚ አካላት በመሬት መረጃ ሳይንስ የሁለተኛ ዲግሪ የትምህርት እድል ያመጣል። ሙለሜ ረሺድ መመዘኛውን ማሟላት ሳትችል አሊ አብዶ እሷ እንድትሄድ ይወስናል። የሚጣሩ ነገሮች ስላሉ ለተወሰነ ጊዜ አንድትቆይ ብንነግረውም አጣድፎ ወደ ኔዘርላንድ በሚስጥር ይልካታል።

በጨፈ፦ው ግምገማ ሴትየዋን ለማሸሽ አሊ አብዶ ያደረገውን ሩጫ ተነሳ። ሰፊ ውይይት ተካሂዶት ጥፋቱ የእሱ እንደሆነ ተደመደመ። ከሁለት አመት በኃላ ነገሮች ተረጋግተዋል በሚል ሴትየዋ ሁለተኛ ዲግሪዋን ጨርሳ ከባህር ማዶ መጣች።

አርከበን ቀርባ አወያየቸው። አርቆ የሚመለከተው ክቡር ከንቲባ፣ "የመብረቅና ተያያዥነት ያላቸው ማህበራት ችግር በመመሪያ ቁጥር ሁለት ተመልሷል" በማለት የመሬት አስተዳደር ከፍተኛ ባለስልጣን አድርጌ ሾማት። የቀድሞውን ዶሴ እንደማስፈራሪያ አየተጠቀመ በርካታ ህገ-ወጥ ደብዳቤዎች አስፈረማት። አንድ ጊዜ በሌብነት የተነካካ ባለስልጣን አፉን ለጉሞ የተባለውን እየፈፀመ እንደሚኖር ከራሱ ልምድ ያውቀዋል። እሷም ብትሆን "ድመት መንኩሳ..." ነበረችና በድጋሚ ሌብነት ውስጥ ተዘፈቀች። እናም ወህኒ ወረደች።

***

ለገበያ የቀረበው ከንቲባ...

አርከበ እቁባይ ወደ አዲሳባ በመጣ በቀናቶች ውስጥ እሱን ለመሸጥ ሰፉፊ መድረኮች ተከፈቱ። ከህዝብ የተውጣጣ አማካሪ ምክርቤት የሚባል ከከተማ እስከ ቀበሌ ተቋቋመ። በአሊ አብዶ ትርፍራፊ ኔትወርኮች አማካኝነት ረጃጅም ድምፅ ያላቸው ህገ -ወጦች የምክር ቤቱ አባላት ሆኑ። አጅንዳው በሙሉ መመሪያ ቁጥር ሁለት በአስቸኳይ መውጣት አለበት ሆነ...

አማራጭ የለም። አርከበ የተጠየቀው መስዋእትነት ተከፍሎ መሸጥ አለበት። ይህ ካልሆነ አቶ መለስ ከአድማስ ባሻገር የተመለከተው ምርጫ 97 ግቡን አይመታም። እናም አርከበ ተሸጠ።

ይህን ተከትሎ አርከበ ለአማካሪ ምክርቤቱ ባቀረበው የሁለት አመት የከተማው የልማትና መልካም አስተዳደር እቅድ ላይ የሚከተለውን ጽፎ ቃል በቃል አነበነበ፣

"...አስተዳደሩ ህገ-ወጥነትን በማያበረታታና ከማስተር ፕላኑ ጋር በማይጋጭ መልኩ ህገ -ወጦችን ህጋዊ የሚያደርግ መመሪያ ቁጥር ሁለት ያወጣል። መመሪያው ከዚህ በኃላ በመዲናችን ህገ ወጥነት በቁጥጥር ስር በማዋል ልዩ ታሪክ ይሰራል። ከእንግዲህ አስተዳደሩ ህገ ወጥ በሚገነቡ ሰወችና አስፈፃሚዎች ላይ የማያዳግም እርምጃ ይወስዳል። በተለይም በማስተር ፕላኑ ላይ ተለይተው ለአረንጓዴ ቦታ የተባሉ ቦታዎች ላይ ግንባታ የሚፈፅም እስከ አስር አመት የሚፈጅ እስር ይጣልበታል። ይህንን በተደራጀ መንገድ ለማስፈፀም እንዲረዳ ከከተማ እስከ ቀበሌ ድረስ ጠንካራ አደረጃጀት ያለው ደንብ ማስከበር የሚባል ፅህፈት ቤት ይቋቋማል።" ብሎ ተናገረ።

መመሪያ ቁጥር ሁለት በተግባር ላይ ዋለ... አሊ አብዶ ነፃ ወጣ!

ከአመታት በኋላ ሙለሜ ረሺድ ዘበጥያ ወረደች! አሊ አብዶ ከሱዳን ወደ ናይጄሪያ አምባሳደርነት በመሸጋገር ደረጃውን አሻሻለ። የኢህአዴግ ስልጣን የዛፍ ላይ እንቅልፍ... ከላይ ወደ ታች።

ምእራፍ አስራ አንድ

መመሪያ ቁጥር ሶስት!!

"ከእንግዲህ በመዲናችን ህገ-ወጥ ግንባታ አይኖርም!!"
(ሚኒስትር መኩሪያ ሀይሌ : 2005 ዓ. ም)

መመሪያ ቁጥር ሶስት ያለ ቦታው ወደ ድህረ ምርጫ 97 ትረካ ይወስደናል። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ስፍራ ያለው ስለሆነ ዘለግ ተደርጐ በየቦታው ቢተረክ የሚያንስበት አይሆንም። ክስተቶቹ ከህሊና የሚጠፉ ስላይደሉ...

ከምርጫ 97 በኃላ የተካሄደው የመሬት ወረራ የሐማውያን ታሪክ ነው። ዘመኑም የሐማውያን ነበር። ዶክተር ሀይሉ አርአያ በአዲስ ዘመን መጽሔት ላይ "የምስለኔ ዘመን" ብለውታል። አዲሳባን በተመለከተ ታሪክ መጻፍ ለሚፈልግ ሰው እንደ አንድ ምእራፍ ሊወስደው ይገባል። ለመነሻ እንዲሆን የታሪኩ ባለቤቶች ድርሻቸንን መወጣት ይኖርብናል። ይህን ታሳቢ በማድረግ በጊዜውና በሰአቱ ራሱን በቻለ ክፍል እንዲገለጽ ይደረጋል። ለአሁን በእንጥልጥል ላይ ለሚገኘው የጥፉቱ ቅብብሎሽ ማሳረጊያ የሚሆነውን ለይተን እናውጋ!

ከምርጫ 97 በኃላ የተካሔደው የመሬት ወረራ አቶ መለስና አርከበ እቁባይ የተቀናጁበት ነበር። ህገ መንግስቱን በግልጽ የጣሱበት። በህገ መንግስቱ አንቀጽ 12 ላይ የመንግስት አሰራር ለህዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን እንዳለበት፣ ማንኛውም ሀላፊና የህዝብ ተመራጭ ሀላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ እንደሚሆን ይደነግጋል። ወረራው ከተጠናቀቀ በኃላ በበረከት ስምአን መሪነት ኢህአዴግ ቢሮ ግምገማ ተቀመጥን። ግምገማው እየጠነከረ ሲሄድ በበረከትና አርከበ መካከል ጭቅጭቅ ይነሳል። ልብ የሞላውን አፍ ያወጣዋል እንዲሉ የስምአን ልጅ ባልተጠበቀ አፍ ወለምታ ይመታል። እናም፣

"ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል" ብሎ ይናገራል።

አርከበ እቁባይ የጋለ ብረት ነክሶ፣

"በረከት! ማንን ነው ውሻ ያልከው? ማንን ነው ጅብ እያልክ ያለኸው? ግልጽ እንድታደርግልኝ እፈልጋለሁ" ብሎ ጥያቄ አቀረበ።

በረከት ወደ ዝርዝር ሳይገባ፣

"ድርጅቱ ባስቀመጠልህ አቅጣጫ አልሄድክም። እኔን ከድርጅቱ ለማጣላት አስበህ ከሆነ ዘላለም አይሳካልህም" የሚል የአፀፉ ምላሽ ይሰጣል። በግምገማው ላይ የነበርን ካድሬዎች የበረከትን አባባል ለመረዳት ስብሰባውን መጨረስ ነበረብን። መልሱንም አገኘነው። እውነት ይዘገያል እንጂ...

ታሪኩ እንዲህ ነበር...

የምርጫ 97 ውጤት እንደታወቀ አቶ መለስ ከመከላከያ ጀነራሎች ጋር በየቀኑ ስብሰባ ይቀመጣል። ወቅቱ ለአቶ መለስ ከየትኛውም ጊዜ በላይ አስቸጋሪ ነበር። በመዲናይቱ የሚካሄዱት ተቃውሞዎች ረፍት ነስተውታል። ጌቶ ብሎ የሚጠራው የኢህአዴግ መዋቅር ሙሉ ለሙሉ ተበትኗል። ያለው አማራጭ አንድ ብቻ ነበር። የፀጥታና ወታደራዊ ሀይሉን ማጠናከር፣ ፓለቲካዊ ጫንነቱን መጠበቅ። እናም የወታደራዊ ሀይሉን ወገንተኝነት የሚያረጋግጥበት ሁኔታ መፈጠር ነበረበት። ጀነራሎቹም ይህንን ጠንቅቀው ያውቃሉ...

ሰጥቶ የመቀበል ዘመን።

በመሆኑም ጀነራሎቹ በቀኝ እጃቸው የታማኝነት ማህተም፣ በግራ እጃቸው ደግሞ ማመልከቻ ይዘው መጡ። ማመልከቻው አዲሳባ በቅንጅት እጅ ከመውደቋ በፊት በቋሚነት ጐናችንን የምናሳርፍበት መሬት ይሰጠን የሚል ነበር።

አቶ መለስ ሳያቅማማ ጥያቄያቸውን በመቀበል ለከተማው ከንቲባ አርከበ እቁባይ ትእዛዝ ይሰጣል። መመዘኛውን ደግሞ ከ1978 ዓ.ም በፊት በትግል ውስጥ የነበሩና ማእረጋቸው ከኮረኔል በላይ እንዲሆኑ ይነግረዋል።

ይህንን አረንጓዴ መብራት ያገኘው አርከበ ግዜ ማጥፋት አልፈለገም።

በወቅቱ አዲሳባ ከላይ እስከ ታች ያለውን መንግስታዊ መዋቅር በማፍረስ በሰባት ማዘጋጃ ጣቢያ (ኮማንድ ፓስት) ተከፍላ ነበር። ኮማንድ ፓስቱ የፓለቲካና የፀጥታ ክንፍ በማለት ለሁለት ተከፍሏል። ሁለቱንም ክንፎች በበላይነት የሚዘውሩት የህውሀት ካድሬዎች ናቸው።

የፓለቲካ ክንፍን አርከበ እንዲመራው ተደረገ። ከመቀሌ ይዘአቸው የመጡት የህውሀት ካድሬዎች ሰባቱን ጣቢያዎች በፊት መስመር ተመደቡ። እነዚህም፣ ሀይሌ (የላፍቶ ክንቲባ)፣ ግርማጺዮን (የየካ ክንቲባ)፣ አተይ (የቂርቆስ ክንቲባ)፣ ገ/ስላሴ (የቦሌ ክንቲባ)፣ ነጋ (የኮልፌ ም/ክንቲባ)፣ ዘሩ (የልደታ ም/ክንቲባ)፣ ታደለ (የአዲስ ከተማ ም/ክንቲባ)፣ ግሉሽ (የአቃቂ

ፕሮፓጋንዳ) ነበሩ።

የከተማዋን የፀጥታና ወታደራዊ ክንፍ ከአዲሳባና ፌዴራል ፓሊስ፣ ከደህንነትና መከላከያ መኮንኖች ተመደቡ። እነዚህም:- ተስፉዬ መራሳ (የአዲሳባ ፓሊስ)፣ ግርማይ መንጁስ(ፌደራል ፓሊስ ካድሬ)፣ መውጫ (አድማ ብተና)፣ ወልደስላሴ (ደህንነት ሹም)፣ ኢሳያስ (ደህንነት ሹም)፣ ጀነራል ታደሰ ወረደ (መከላከያ) ነበሩ።

የፓለቲካና ፀጥታ ኮሚቴው የጋራ ጥምር በመፍጠር በየቀኑ ማታ ማታ የከተማዋን አዳርና ውሎ ይገመግማል። በህዝቡ ውስጥ ያሉ እንቅስቃሴዎችን መረጃ ያሰባስባል። የተቃዋሚ መሪዎችን የእለት ንግግርና ውሎ እንድምታ ይተነትናል። የአዲሳባ የመሬት ሽንሸና ፍጥነቱን ይገመግማል።

ይህን ተከትሎ የከተማው ባዶ መሬት ሙሉ ለሙሉ በሚባል መልኩ ተሰረቀ። "እዚህ ቦታ ራቁቱን የተቀመጠ መሬት አለ" በሚል ጥቆማ ተዘረፈ። አዲሳባ መሬት አልባ ሆነች።

ይህ ለታሪክ የሚተላለፍ እውነት ለማረጋገጥ ሩቅ መሄድ አያስፈልግም። በድጁ የሚኖረውንና ለአስፈጻሚው ተጠሪ የሆነውን ፀረ ሙስና ኮሚሽን ሪፓርት ማየት በቂ ነው። በፀረ ሙስና ኮሚሽን ተጠንቶ ይፉ በተደረገ ሰነድ መሰረት እስከ 2003 ዓ.ም ድረስ ከ3.5 ሚሊዮን ካሬ ሜትር የሚደርስ የከተማዋ መሬት በወረራ ተዘርፏል። ይህም ወደ ገንዘብ ሲቀየር ከአስር ቢሊዮን ብር በላይ የህዝብ ገንዘብ ወደ ግለሰብ ኪስ ገብቷል። እዚህ ጋር ልብ ሊባል የሚገባው ፀረ ሙስና ኮሚሽን ተዘረፈ ያለው መሬት መከላከያና የኢህአዴግ ተቋማት የዘረፉትን አያጠቃልልም። ይህ አሀዝ በሪፓርቱ ቢካተት ኖሮ የቀረበው መረጃ እጥፍ ይሆን ነበር። መንስኤው ተጣርቶ ለህግ ቢቀርብ ደግሞ ኢህአዴግ አቶ መለስን ወደ ወህኒ በማውረድ አንጻባራቂ ታሪክ ይሰራ ነበር። ፓርቲው ተሰውቼለታለሁ የሚለው የህግ የበላይነት እውን ይሆን ነበር።

***

ቀጥሎ የሚነሳው ነገር ይህንን አይን ያወጣ ወረራና ዝርፊያ በፍጥነት ሩጫ ህጋዊ በማድረግ ከተጠያቂነት መዳን ነው።

እርግጥ ነው ፈላጭ ቆራጭ በሆነ ስልጣን ላይ መቀመጥ ከተጠያቂነት ሊያስመልጥ ይችላል። ነገር ግን ከታሪክ ተወቃሽነት አያድንም። በዚህ በመንግስት የተመራ የመሬት ወረራ አቶ መለስና አርከበ የታሪክ ተጠያቂ ናቸው። የስምአን ልጅ እንዳለው አቶ መለስ እንደ ውሻ ባይቀደው፣ አርከበ

እንደ ጅብ ሰተት ብሎ የመግባት እድሉ ጠባብ ይሆን ነበር።

እነሆ! ሩጫው አጭር ነው፣ የአራት መቶ ሜትር ዱላ ቅብብሎሽ። ዱላዋ ደግሞ መመሪያ ናት። እንደ ቀድሞዎቹ ሁሉ እነ አርከበን ከተጠያቂነት የምታድን።

መመሪያ ቁጥር አንድ!... ቁጥር ሁለት!... ቁጥር...?

አሊ አብዶ የመጀመሪያውን መቶ ሜትር በመሮጥ ለአርከበ አስረክቧል። አርከበ የቆየ ልምዱን አክሎበት ቀጣዩን መቶ ሜትር ከብረወሰን በማሻሻል ጭምር ለአልጋ ወራሹ ሚንስትር መኩሪያ ሀይሌ አስተላልፏል። ሚኒስትር መኩሪያ በኢህአዴግ የአዲሱ አመራር ትውልድ ውስጥ ያለ ካድሬ ነው። በመተካካት ህግ መሰረት የቀጣዩን አጭር ሩጫ ከግብ ለማድረስ ተስፉ ከተጣለባቸው የለውጥ መሀንዲሶች አንዱ ነው። ርግጥም ሩጫው ለሚኒስትር መኩሪያ ላይከብደው ይችላል...

እድሜ "ለመደገፍ መርሀ!"

(ኢህአዴግ "የመተካካት መርሀ "ብቻ እንዳለው የሚቆጥሩ የዋሆች አሉ... ፓርቲው ነገሮችን አስተሳስሮ የሚያይ ነውና በተደራቢነት "የመደገፍ መርሀ" የሚባል ከሰገሌ ጀምሮ በስራ ላይ ያዋለው ውስጣዊ አሰራር አለው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ካድሬው ከሚገመገምበት ቁልፍ ነጥቦች ዋነኛው "ጓዶችህን ምን ያህል ደግፈሀል?፣ ለመደገፍ ያለህ ዝግጁነት እስከምን ደረጃ ነው?..." የሚሉ ሆነዋል።

የኢህአዴግን "የመደገፍ መርሀ" እንደ "መረዳዳት" አድርገው የሚቆጥር ካለም ለዳግም የዋህነት ተጋልጧል። በፓርቲው ቋንቋ ለመደገፍ ዝግጁ መሆን ማለት ቀይ መስመር ለዘለለ ጣልቃ-ገብነት ራስን ማሳመን ማለት ነው። መደገፍ ዳር ድንበርና ጣራ አያውቅም። ተጠያቂነት የለውም። ይህንን በተመለከተ በአቶ በረከት *መፅሀፍ "መቋጫ ወግ"* በሚለው ርእስ ስር በገፅ 312 ላይ "... ከፊት መስመር ገለል ብለን፣ ከኋላና ከጐን ሆነን መደገፍ አለብን..." ተብሎ በነጠረ አማርኛ ተፅፏል...)

ወደ ተነሳንበት እንመለስ... *መመሪያ ቁጥር ሶስት ...*

መኩሪያ ሀይሌ ሚኒስትር ከመሆኑ በፊት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ንግድና ኢንዱስትሪ ሀላፊ ነበር። በዛን ወቅት ከአዋሳ እየተመላለሰ አዲሳባ ላይ የሀብታሞች ጉዳይ አስፈፃሚ ይሆናል። በተለይም በአንድ ወቅት ቦሌ መንገድ ደንበል ሲቲ አጠገብ የሚገኝ ቦታ ላይ የይገባኛል ጭቅጭቅ

ይነሳል፣ ጥያቄውን ካነሱት ግለሰብ አንደኛው ከእሱ ጋር የጥቅም ትስስር ያላቸው የሀገሩ ልጅ ነበሩ። ሰውየው ጉዳዩን ይዞ ወደ አዋሳ ያዘግማል። አቶ መኩሪያ ከአርከበ ጋር በመነጋገር ጉዳዩን ያስፈፅማል። በተቃራኒ ወገን ተሰልፎ የነበረው የዞን አራት ኢህአዴግ የካድሬዎች አለቃ ገ/ፃዲቅ ሀገሶ (በአሁን ሰአት የከተማዋ ካቢኔ አባልና ባህልና ቱሪዝም ሀላፊ) ለኢህአዴግ ቢሮ ያስተላልፉል።

አርከበ የክፉ ቀን መምጣቱን ሲያረጋግጥ ውለታውን ለመቀበል ለትልቅ ቦታ አጨው። ለአዲሳባ ስራ አስኪያጅነት። ወደ ላይ ድጋፍ መስጠት በሚለው መርህ መሰረት መንግስታዊ አለቃው ለሆነው ዶክተር ካሱ ኢላላ ትእዛዝ ያስተላልፉል።

...ጉራጌው ካሱ ፣ጉራጌው መኩሪያን ወደ አዲሳባ እንዲያመጣ ለህይለማርያምና ለድርጅቱ ፕሮፓዛል ያቀርባል። የተፈራው በረከት ነው። እንደተጠበቀው የስምአን ልጅ የብርጭቆ ማእበል አስነሳ፣

"ለዚህ አይን ያወጣ ሌባ ዝረፍ ብለን አዲሳባ አንሰጠውም" ብሎ ደነፋ። የቁራ ጩኸት!

(በረከት ስምአን መኩሪያ ሀይሌንና ግርማ ብሩን "ውስጣቸው ኢህአዴግ ሳይሆን ድርጅቱን የሚያታልሉ ምላሜ ሳሙናዎች" እያለ ይጠራቸዋል።)

በመርህ መመራት ያቆመው ድርጅት የመኩሪያን የትላንት ውለታ መርሳት አልፈለገም። መኩሪያ ለድርጅቱ ከፍተኛ ጭንቀት ፈጥሮ የነበረውን የጉራጌ መራሽ አብዮት እንዲቀለበስ አድርጓል።

መኩሪያ ስራ አስኪያጅ ሆነ!!

የከተማዋ ቻርተር ሲዘጋጅ የአዲሳባ ስራ አስኪያጅነት ሙያ ተኮር በመሆኑ አለም አቀፍ ማስታወቂያ ወጥቶ ከፍተኛ ፕሮፌሽናሎችን በማወዳደር ይፈፀም የሚል አስተያየት አቶ መለስ ጋር እስኪደርስ ድረስ ተቀባይነት አግኝቶ ነበር። አቶ መለስ ይህን አስተያየት እንደሰማ በቁጣ፣ "የአዲሳባን ስራ አስኪያጅነትን አሳልፎ መስጠት ማለት ወደ ጥልቅ ጉድጓድ ኢህአዴግን ከመወርወር አይተናነስም" አለ።

ርግጥም አቶ መለስ እንዳለው የአዲሳባ ስራ አስኪያጅነት ስልጣን ከከንቲባው በላይ ነው። የከተማዋ የዝርፊያ ማእከል የሆኑት እንደ ማዘጋጃ ቤት፣ መሬት፣ መንገድ፣ ውሀ... በቁጥጥር ስር የሚውሉት በስራ አስኪያጁ ነው። ኢህአዴግ ቢሮ ከንቲባ ማን ይሁን ከሚለው በላይ የሚያጨቃጭቀው ስራ አስከከያጅ መምረጥ ላይ ነበር። አቶ አርከበ በለስ ቀንቶት በእሱ ዘመን

የህውሀት ካድሬውንና የመንገዶች ባለስልጣኑን አስመደበ፣ ቀጥሎ መኩሪያ ሀይሌን፣ በመጨረሻም የቅርብ ዘመዱን ሀይሌ ፍስሀ።

በዳግም ምርጫ 2000 ዓ.ም ኢህአዴግ መዲናይቱን በተቆጣጠረ ወቅት አቶ በረከት ቢሮ ውስጥ እኔ፣ ህላዌ፣ ካሚል፣ ፀጋዮና ፍሬህይወት ተሰብስበን ከንቲባ፣ ስራ አስኪያጅ፣ የካቢኔ አባል እየመለመልን ነበር። ስብሰባው ሳይጠናቀቅ ከቤተ መንግስት የአቶ መለስ ስልክ ተንጫረረ። አርከበ ለስራ አስኪያጅነትና ካቢኔ የሚሆን ይዞ እየመጣ ስለሆነ ተቀበሉት የሚል አጭር ትእዛዝ ሰጠ። ስልኩ ሲዘጋ ህላዌ፣

"Welcome! ሀይሌ ፍስሀ፣... Welcome!! መኩሪያ ሀይሌ" ብሎ በዜማ ቅላፄው ዘፈነ። ካሚል ከጣራ በላይ ሳቀ። ፀጋዬ አንገቱን ነቀነቀ። እኔና ፍሬህይወት በአይናችን አወራን። ስብሰባውን ጨርሰን ስንወጣ ፍሬህይወት የምትፅፈውን ግጥም ለማንበብ ጓጓሁ!

በረከት እንደተለመደው፣

"ሀይሌም ሆነ መኩሪያ ወደ ኡዲሳባ የሚመጡት እኔና አርከበ ቦታ ስንቀያየር ነው። ቡምስላግ! እስስት!" በማለት ጥርሱን ነከሰ። አፍንጫውን ፈተገ።

ወቅቱ ለአርከበ ወሳኝ ነውና በድል አድራጊነት ሰሜት ውስጥ ሆኖ የምንግዜም ባላንጣው ቢሮ ተገኘ። ጊዜ ሳያጠፉ፣

"መለስ የካቢኔ አባላትና ስራ አስኪያጅ መልምለህ ስጣቸው ባለኝ መሰረት ሳምንቱን ሙሉ ቁልፍ ስራዬ አድርጌ ስባዝን ነበር። ለካቢኔ አባላት የሚሆኑትን የሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ፕሬዝዳንት ዶክተር ሀይለሚካኤል በጣም አግዞኛል። እነ ህላዌ ደውላችሁ አመስግኑት። ኮሌጁን ባዶ አድርገው ነው መምህራኖቹን እየሰጠን ያለው።"

ትንፋሽ ወስዶ፣

"...በዚህም መሰረት ለትምህርት ቢሮ ሀላፊነት የደኢህዴን ጠንካራ ካድሬ የሆነውን የኮሌጁ መምህር ዴንታሞ መርጫለሁ። የቅንጅት መንፈስ ያለቀቀውን የትምህርት መዋቅር ግልብጥብጡን ያወጣዋል። ለፋይናንስና ኢኮኖሚ ደግሞ የህውሀት ታጋይና የኮሌጁ መምህር በላይነሽ የመጀመሪያ ምርጫዬ ሆናለች። ለንግድና ኢንዱስትሪ እንዝርት የሆነውን የጉራጌ ካድሬ ፍፁምን መልምያለሁ። ብአዴኗ ዶክተር አፀደ የትም ቦታ ብትቀመጥ እንደምትመጥን ዶክተር ሀይለሚካኤል እምነት አለው።"

በድጋሚ ትንፋሽ ወስዶ ወደ ዋናው ተልእኮ ገባ፣

"...ስራ አስኪያጅ የሚሆኑ ሰዎች ሁለት ጠንካራ ካድሬዎች ይዤ መጥቻለሁ። የመጀመሪያ ምርጫዬ መኩሪያ ሀይሌ ነው። የደኢህዴን ሊቀመንበሩ ሀይለማርያምን አስተያየት ጠይቄው ደቡብን ባዶ ተደርግብናለህ

እንጂ ሁነኛ ሰው መርጠሀል ብሎኛል። በሁለተኛ ደረጃ ሀይሌ ፍስሀ ቢሆን የሚል አስተያየት አለኝ። የህውሀት ቢሮ ለመስጠት አንገራግረው ነበር ግን አዲሳባ ላይ ጠንካራ ሰው መመደብ ወሳኝ መሆኑን ነግሬያቸው ፍቃደኛ ሆነዋል። እናም መኩሪያ የመጀመሪያ ምርጫዬ ቢሆንም ደኢህዴን ካለበት የሰው ሀይል እጥረት አኳያ ሀይሌ ፍስሀ ቢሆን ይሻላል..." አለ።

የፍርዬ ቁንጥጫ አጥንቴን ዘልቆ ተሰማኝ።

መኩሪያ ሀይሌ ስራ አስከኪያጅ ሆነ!...

በረከትና አርከበ ቦታ ሳይቀያየሩ ቀረ።

መኩሪያ ሚኒስትር ሲሆን ደግሞ በቅብብሎሽ ህግ መሰረት ለሀይሌ ፍስሀ አወረሰው!

(በመኩሪያ ወደ አዲሳአባ መምጣት ላይ የደኢህዴን ከፍተኛ ካድሬዎች ቅሬታቸውንና የመኩሪያን ሌብነት የሚያሳዩ መረጃዎች በግልጽ አቅርበው ነበር። በተለይም የድርጅቱ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ የነበረው አማኑኤል አብርሀ (የኢትዮጵያ አትሌቲክስ አቃቤ ንዋይ የነበረና በአሁኑ ሰአት የፓርላማ አባል) እና የኢህአዴግ ፉይናንስ ሀላፊው ተፈሪ በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ ናቸው። አማኑኤል አፍ አውጥቶ "አዲሳአባ ከጥቁር ጅብ ወደ ነጭ ጅብ ሽግግር አደረገች።" በማለት ተናግሯል።

አርከበ ለሽፉን ይዞ የመጣቸው የሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ መምህራንም ከሹመት በታላ ሲጣራ የተገኘው ነገር አስገራሚ ነበር። የደኢህዴን ጠንካራ ካድሬ የተባለው ዲንታሞ ከምርጫ 97 ውጤት በኋላ ኢህአዴግነቱን በይፉ ትቷል። ለሶስት አመት ወርሀዊ መዋጮ አልከፈለም። እንዝርት ተብሎ ለንግድና ኢንዱስትሪ የተመደበው ፍፁም መንፈቅ ሳይሞላው በአቅም ማነስ ከካቢኔ ተባረረ። አፈ ጉባኤ የነበረችው ዶክተር አፀደና የኢኮኖሚና ፉይናንስ ሀላፊዋ በላይነሽ ዘግየት ብለው የካቢኔ ሽንጣቸውን ሸክፈው አብሰ አሉ።)

***

ሚኒስትር መኩሪያና ሀይሌ ፍስሀ የቀድሞውን ምድብ ከንቲባ አርከበን ለመታደግ መመሪያ ቁጥር ሶስት እንደሚያወጡ የሚያጠራጥር አልነበረም። መመሪያ ቁጥር ሶስት መውጣት ብቻውን ግን አቶ አርከበን ከተጠያቂነት አይድንም። በከተማዋ ማስተር ፕላን ላይ በምንም መልኩ ድርድር የማይካሄድባቸውና በወንጀል የሚያስቀጡ አረንጓዴ ቦታዎች በእሱ ቀጥተኛ ትእዛዝ ተወረዋል። በመሆኑም መመሪያ ቁጥር ሶስት ብቻ ሳይሆን የማስተር ፕላን ክለሳ ተቀናጅተው መፈፀም ይኖርባቸዋል። መመሪያው ወጥቶ ማስተር ፕላኑ ባይሻሻል ከወንጀለኝነት አያድንም።

ሚኒስትር መኩሪያና ስራ አስኪያጅ ሀይሌ ፍስሀ ተቀናጅተው ህገ

ወጡችን ህጋዊ የሚያደርግ መመሪያ በ2003 ዓ.ም አወጡ። በመመሪያው መሰረት እስከ ህዳር 2004 ዓ.ም ድረስ መሬት በህገ ወጥ መንገድ የያዙ ባለይዞታዎች ህጋዊ እንደሚሆኑ፣ በአምስት አመት ውስጥ ህገ ወጦችን ህጋዊ አድርገው በማጠናቀቅ የህገወጥነት አጀንዳ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንደሚዘጋ፣ በአዋጅ 47/67 መሰረት የይዞታ ማረጋገጫ ሳይሰጣቸው የነበሩትን በሙሉ እንደሚያገኙ አበሰሩ። በተደራቢነት የማስተር ፕላን ማሻሻያ እንደሚደረግ ይፉ አደረጉ።

ሚኒስትር መኩሪያ በወርሀ የካቲት 2005 ዓ.ም ከሪፓርተር ጋዜጣ ጋር ባደረገው ቆይታ የሚከተለውን ገለፀ፣

"...በ2005 ዓ.ም ለአስር አመታት የተተገበረው ማስተር ፕላን ይጠናቀቃል። ከሚቀጥለው አመት ጀምሮ አየተሰራ ያለው ማስተር ፕላን ተግባራዊ ይደረጋል። በዚህ ረገድ ለአረንጓዴ አካባቢዎች አዲሱ ፕላን ልዩ ትኩረት ይሰጣል። ከዚህ ጋር በተያያዘ በ2003 ዓ.ም የወጣው ህገ ወጦችን ህጋዊ የማድረግ ስራ በአምስት አመት ውስጥ ይጠናቀቃል። ከዚህ በኃላ ህገ ወጥ ግንባታ ከተካሄደ አካባቢውን የሚያስተዳድረውም ህገ ወጥ የገነባውም ተጠያቂ የሚሆኑበት ሰርአት ይዘረጋል። በመሆኑም ይህንን ለማስፈፀም በክህሎቱና አቅሙ የፓሊስ ቁመና ያለው ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት እንዲደራጅ ይደረጋል።"

በፕሬዝዳንት አሊ፣ በከንቲባ አርከበ እና ሚኒስትር መኩሪያ መግለጫዎች መካከል ልዩነት የለም። ...ልዩነቱ እንደ ኢትዮጵያ ድርቅ ዘመኑ መለዋወጡ ብቻ ነው።

ርግጥ ሚኒስትር መኩሪያ በመግለጫው ማጠናቀቂያ ላይ በመወለድ ያገኘውን ሳይኮሎጂስትነት አገርሽቶበት፣

"...በህገ ወጥ መንገድ መሬት ያገኙ ሰዎች በመንግስት በኩል ተጠቅመዋል የሚል እምነት የለንም። ህገ ወጥነት የሞራል ቅጣት አለው። ህገ ወጥነት የስብእና መጓደል ነው። ሀፍረት ነው። አጥፍተው ሀብረተሰቡና መንግስት ይቅርታ እያደረጉላቸው ነው" የሚል አስቂኝ ምላሽ ሰጥቷል።

ግራም ነፈሰ ቀኝ መመሪያ ቁጥር ሶስትና ማስተር ፕላን ማሻሻያው ከንቲባ አርከበን ነፃ አውጥተዋል። ከእንግዲህ ራሱን ከፊት ለፊት መስመር አግልሎ ከጉንና ከኃላ ይደግፉል። ካልፈለገም በማይነጥፍ ሀብቱ ከአህጉር አህጉር እየተዘዋወረ ስጋውን ያስደስታል። ይህም ካስጠላው ከታች ድጋፍ እያገኘ በዶክትሬት ላይ ዶክትሬት ይጭናል።

***

መመሪያ ቁጥር አራት?

ከዚህ ቀጥሎ ሊነሳ የሚችለው መመሪያ ቁጥር አራት ሊወጣ ይችላል ወይ የሚለው ይሆናል።አሁን አዲሳአባ በያዘችው ቅርጽ መመሪያ ቁጥር አራት የመታወጅ እድሉ ጠባብ ነው። የማይሆንበት ምክንያት የአስተዳደሩ የሌብነት ቅብብሎሽ ሰለተበጣጠሰ ሳይሆን የአዲሳባ ባዶ መሬት ሙሉ ለሙሉ በሚባል መልኩ በመዘረፉ ነው። በመሆኑም የጥፉቱ ቅብብሎሹ መልኩን በመቀየር በሌላ መልኩ የሚገለፅ ይሆናል። ፍንጮችም እየታዩ ነው..."ከተማዋን መልሶ ማልማት" የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል።

የበሰበሰች ከተማ!

አዲሳባ ከአቅሞ በላይ 800 ሺህ ቤቶችን ተሸክማለች ። ከእነዚህ ውስጥ 80 በመቶ የበሰበሰ ነው። እነዚህ ቤቶች አንደሚፈርሱ ሚኒስትር መኩሪያ የመደገፍ መርሆን ተጠቅሞ ይፉ አድርጓል። በመሆኑም የዝርፊያ ቅብብሎሹ በአዲስ መሬት ላይ የሚፈፀም ሳይሆን ነባር ቦታዎችን በማስነሳት ሒደት በሚፈፀም ሌብነት ይሆናል። ለተነሺዎች ከአቅም በላይ ካሳ ለመክፈል ከመንግስት ካዝና በሚወጣ ገንዘብና አካባቢ በመለየት የማልማት ጥያቄ ከሚያቀርቡ ሰዎች የሚገኝ ምልጃ ዋነኞቹ ይሆናሉ። በተጨማሪም በጨረቃ ቤትነት የተሰሩት አብዛኞቹ ቤቶች ደረጃቸውን ያልጠበቁ ናቸው። መፍረሳቸው አይቀርም። ደረጃውን ያልጠበቀ ሁሉ ከመፍረስ አይድንም...

መመሪያ ቁጥር አራት እንደወረደ አሊያም ስያሜውን በመቀየር የሚከሰትበት እድል ሊመጣ የሚችለው በአንድ ምክንያት ብቻ ነው። አዲሳአባ አሁን የያዘችውን ቅርጽ በመቀየር በእሷ ዙሪያ ያሉ የኦሮሚያ ልዩ ዞኖችን ማስገባት ከተቻለ። ይህን ለመፈፀም በአቶ አርከበ እቁባይ የሚመራ ቡድን 1998 ጀምሮ ጥናት ሲሰራ እንደነበረ አውቃለሁ። በአርከበ የተመራው ቡድን በሚስጥር እንዲያጠና እየተደረገ ያለው ዝርፊያን ከማስፉፉት አንጻር ብቻ ሳይሆን ፓለቲካዊ ፉይዳም አለው። ጥናቱ ወደ ተግባር ከተለወጠ የአዲሳአባ ቻርተር የመለወጥ እድሉ ሰፊ ይሆናል። ቻርተሩ ከተለወጠ ደግሞ የመስተዳድሩ አደረጃጀት፣ የምክር ቤት አወቃቀርና ብዛት አብሮ ይለወጣል።

እነ አባዱላና ግርማ ብሩ በምርጫ 97 ማግስት ወስነው ተግባራዊ ሳይሆን ሸልፍ ላይ አቧራ እየጠጣ ያለው ውሳኔ ተግባራዊ ወደ መሆን ይሸጋገራል። ይህም በአንድ በኩል ያለህዝብ ምርጫ በቀጥታ በአዲሳአባ ምክርቤት የመወከል ሊሆን ይችላል። አሊያም ወደ መዲናይቱ የሚቀላቀሉት ዞኖች በልዩ ሁኔታ የሚወከሉበት ሁኔታ ይፈጠራል። ከእነዚህ ሁለት አማራጮች በተለየ ሊሆን የሚችለው በልዩ ዞኖቹ ምርጫ በማካሄድ የአዲሳአባን ምክርቤት መቀላቀል ይሆናል። ይህ የመጨረሻ አማራጭ ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው የኦሮሚያ ልዩ ዞኖቹን ማህበራዊ አወቃቀር (Social structure) ለመቀየር የተጀመረው ስራ

ውጤታማ ከሆነ ብቻ ይሆናል። ይህም በአካባቢው ነባር የሆኑ ነዋሪዎችንና ገበሬዎችን በማስነሳት ለኢህአዴግ ቅርብ የሆኑና የተጠቀሙ ሰዎች አብላጫ ቁጥር ካስመዘገቡ ይሆናል።

በዚህ ዙሪያ በኦህዴድ ከፍተኛ ካድሬዎች አካባቢ አለመግባባት እንዳለ ለሁለት አመታት በሲኤምሲ ጐረቤቴ የነበረው የአሁኑ የኦሮሚያ ፕሬዝዳንት የሆነው አለማየሁ አቶምሳ አጫውቶኛል። ጐረቤቱ ከመሆኔ በፊት የቅርብ ጓደኛው የነበረው ፍስሀ ዘሪሁን(መአሲ) አስተዋውቆን ስለነበር በፍስሀ አይን ይመለከተኝ ነበር። አለማየሁ ተራ ኑሮ የሚኖር እና በጣም ቀላል ሰው ነው። ከዚህ በተጨማሪ ፀረ ሌብነት አቋሙ የሚያስደስተኝ ቢሆንም ምን ያህል ርቀት ያስኬደዋል የሚለው ያሳስበኛል። ርግጥ የተለያየነው ፕሬዝዳንት ከመሆኑ በፊት ስለሆነ ምን ይህል ወደ ተግባር እንደለወጠው እርግጠኛ አይደለሁም። የዱከም ከንቲባ የነበረው ሚደቅሳ እጣ ፉንታ እንዳይገጥመው ምኞቴ ነው።

አለማየሁ ልዩ ዞኖቹን ወደ አዲሳአባ ለመቀላቀል የኦሮሞ ህዝብ በጉዳዩ ላይ በግልጽ ተወያይቶ መወሰን አለበት የሚል አቋም ነበረው። የኢህአዴግ ካድሬዎችም አቶ መለስን ጨምሮ በህዝቡ ውሳኔ መገዛት እንደሚገባቸው ያሳስባል። እንደ አለማየሁ እምነት የኢህአዴግ ባለስልጣናት በዚህ አጀንዳ ዙሪያ በሶስት ቡድን የተከፉፈሉ ናቸው።

የመጀመሪያው ቡድን የአቶ መለስና በረከትን ሀሳብ የሚደግፈው ነው። እነ አቶ መለስ ዋነኛ ጭንቀታቸው የአዲሳአባን ፓለቲካዊና ማህበራዊ አወቃቀር መቀየር ነው። በኦሮሚያ ስር ያሉት ልዩ ዞኖች ወደ አዲሳአባ ተቀላቅለው የምርጫውን ውጤት ኢህአዴግ ዘመም የሚያደርጉት ከሆነ እንዲቀላቀሉ ይፈልጋሉ። የዘውትር ጥያቄያቸውም ይህ ነበር።የኦህዴድ ፓሊት ቢሮ አባላት የሆኑት ኩማ ደመቅሳ፣ ሙክታር ከድር እና አስቴር ማሞ የአቶ መለስ ቡድን አስፈጻሚዎች ናቸው።

በሁለተኛ ደረጃ ያሉት የአባዱላ እና ምክትል ፕሬዝዳንቱ አብድላዚዝ ቡድን ሲሆን ውሳኔውን የሚቃወሙ ናቸው። ይህ ቡድን በእነዚህ ልዩ ዞኖች በርካታ ህንጻዎችን ገንብቷል። በዚህ ምክንያት ዞኖቹ ወደ አዲሳአባ ከተጠቃለሉ በአካባቢው ያለው የመሬት መረጃ ወደ መሬት ባንክ ስለሚገባና በዘመናዊ መረጃ አያያዞች ስለሚመዘገብ ቀስ በቀስ ዝርፊያቸው ይጋለጣል። ይህ ቡድን አስከ ታችኛው የኦህዴድ መዋቅር አደረጃጀት ያለው ሲሆን በቀላሉ አመጽ ማቀጣጠል የሚችል ብቃት አለው። በተለይም በሁለተኛ ደረጃ እና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚገኙ ተማሪዎችን በመኮርኮር ሀገር አቀፍ ነውጥ ሊፈጥር ይችላል።

በሶስተኛ ደረጃ ያለው በአርከበ እቁባይ፣ ሚኒስትር መኩሪያ ሀይሌና የአዲሳባ ስራአስኪያጁ ሀይሌ ፍስሀ የሚመራ ቡድን ነው። ይህ ቡድን ግቡ የጀመረውን ዝርፊያ አጠናክሮ መቀጠል ብቻ ነው። ለዚህም ስራና ከተማ ልማትን እንደ መሳሪያ ይጠቀማል። ይህ መንግስታዊ ስልጣን በአንድ በኩል ማስተር ፕላን፣ ኢንዱስትሪ ዞን፣ የልማት ኮሪደር፣ተመጋግቦ ማደግ... ወዘተ የሚባሉ አንፀባራቂ ቃላቶችን በማምጣት፣ የአውሮፓ ከተሞችን የሚመሳሰሉ የከተማ ፕላኖችን አዘጋጅቶ በመልቀቅ የማማለል ስራ ይሰራል። ከተሳካለት ህጋዊ በሆነ መንገድ የኦሮሚያ ዞኖችን በመጠቅለል እና መመሪያ ቁጥር አራት በማውጣት የህብት ጉዞውን የመጨረሻ ጫፍ ያደርሳል። ወይዘሮ አዜብ የዚህ ቡድን ደጋፊ ስትሆን የመጨረሻው ቀን ሲደርስ ውጤቱን ወደ ራሷ ለመገልበጥ አሰፍስፋ ትጠባበቅ ነበር።

እነሆ! ትግሉ ቀጥሏል። ማን ያሸንፍ ይሆን? የጥፉቱ ዑደትስ በምን መልኩ ይቀጥል ይሆን?

ክፍል አራት : የምርጫ 97 መባቻ

"... ታሪክ ያሳየን ምስለኔ ሲዘርፍና ሲበዘብዝ ነው ! "

ዶክተር ሀይሉ አርአያ

(ዘመን መፅሔት)

ምእራፍ አስራ ሁለት

"ከተማን በገጠር ስሌት"

"የጠገበው ሄዶ የራበው ጅብ መጣ!"
የአዲሳአባ ህዝብ

የኢህአዴግ ከተማ ቀመሶች

በረከት ስምኦን በሁለት ምርጫዎች ወግ መጽሐፉ በገጽ 44 ላይ የሚከተለውን ጽፎ እናገኛለን:

"... የከተሞችን አመራር የመቀየር ስራ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ ነበር። ከተማውን ሲያስተዳድር የቆየው አመራር እንዲቀየር ከተደረገ በኃላ ከየክልሉ ከተማ ቀመስ ሰው እየተፈለገ ተመልምሎ አዲስ አበባ እንዲገባ ተደረገ... እነዚህ ሰዎች የአገሪቱን ርዕሰ ከተማ እንዲመሩ የተመደቡት ከተሞችን እንደገጠር ሳይሆን እንደ ከተማ ለመምራት ይቻል ዘንድ ነበር።" ይላል።

ከተማ ቀመስ የሚለው የበረከት አገላለጽ ከሀቅ የራቀ ነው ብሎ መከራከር አይቻልም። ኢህአዴግ የእኔ ከተማ ቀመሶች እነዚህ ናቸው ካለ ያለውን ከመቀበል ውጭ። ትልቁ ጥያቄ እነዚህ ካድሬዎች ውስብስብ የሆነችውን ከተማ ለመምራት የሚያስችል ብቃትና ቁመና ነበራቸው ወይ?፣ በመዲናይቱ የመጣው ለውጥ በእነሱ አማካኝነት ነበረ ወይ? የከተማ አመራር ስርአት ቀይረዋል ? የአዲሳአባ ህዝብና ሲቪል ሰርቪሱ እንዴት ሲመዝናቸው ነበር? አዲሳአባን ለወጡ ወይንስ እነሱ ተለወጡ? የመጡበት አላማ አዲሳባን ለመቀየር ወይስ ለምርጫ 97 መደላድል ለመፍጠር? የሚለው ይሆናል።

በመሆኑም ስለእነዚህ ምርጫ ዘጠና ሰባትን በድል ለማሻገር ተስፋ የተጣለባቸው የከተማ እድገት ፉና ወጊዎች እኔም ሆንኩ ኢህአድጋውያን የምናውቀውን እውነታ ወደ መተረክ እንሸጋገር። አስቀድመን የአርከበ ካቢኔ አባላትን፣ በማስከተል ደግሞ የክፍለከተማ ለውጥ ሀዋርያዎችን እንመለከታለን።

***

የተቸነከረው ታጋይ

ሲቪል ሰርቪሱን ፣ትምህርት ቢሮንና አጠቃላይ አቅም ግንባታን እንዲመራ የተመደበው ካድሬ ተክለብርሀን ይባላል። አርከበ ከትግራይ ይዞ ከመጣቸው የህውሀት ቁልፍ ካድሬዎች አንዱ ነበር። ይህ ካድሬ በትምህርት ዝግጅቱ ከሁለተኛ ደረጃ አልዘለለም። ለረጅም አመታት የሰራው በትግራይ ገጠራማ አካባቢዎች አባላት የማደራጀት ስራ ሲሆን አዲሳባን በጣት ለሚቆጠሩ ቀናት ከመምጣት ውጪ አያውቃትም። በትግራይም ቢሆን በየትኛውም ከተማ አስተዳደር ሆኖ አልሰራም። በእንቅርት ላይ እንዲሉ በትጥቅ ትግሉ ወቅት ጉዳት ደርሶበታል። በዚህም ምክንያት ጀሮው አይሰማም። ይህን ተከትሎ ከተክለብርሀን ጋር አንድ አይነት ነገር ማውራት በፍጹም አይቻልም። ግምገማው ስለ ትምህርት ጥራት ችግሮች ሆኖ እሱ ስለ አነስተኛና ጥቃቅን ገለጻ የሰጠበት ጊዜ ነበር።

ከእለታት በአንዱ ቀን የሀገሩ ልጅና የትምህርት ቢሮን የለውጥ ኮሚቴ የመራው ገ/ተንሳይ አፍ አውጥቶ፣

"ተ/ብርሀን! አንተ እኮ ደንቆሮ ነህ! ከአንተ ጋር እንዴት እንደምሰራ አይገባኝም?" ብሎ ተናገረ። ተክለብርሀን በበኩሉ ምን አንዳለው ሳይገባው፣

"ገ/ተንሳይ ልክ ነው። ለመምህራን ስልጠና መስጠት አለብን" የሚል ምላሽ ሰጠ። ምላሹ አራንባና ቆቦ የሆነበት ገብረተንሳይ ማሰሮ ሆዱን እያንቀጠቀጠ ሳቀበት። እንደሌሎቻችን መናደዱን መቆጣጠር ያቃተው ታደሰ የሚባል የአዲስ ከተማ ካድሬ፣ "ጉበረተንሳይ! እንዳንተ ቆዳውን እየቀያየረ ሁለት ስርአት አላገለገለም። መስማት የተሳነው አንተ ስትመራው የነበረውን አስከፊ ስርአት ሲታገል ነው።" የሚል ብሽቀት ያዘለ መልስ ሰጠው ...ብአዴኑ ታደሰ።

የተክለብርሀንን ክፍተት ለመሙላት አርከበ መላ ዘየደ። አማረ ሺበሺ የሚባል ምሁር በምክትል ቢሮ ሀላፊነት መደበለት። አማረ ነባር የአስተዳደሩ ሰራተኛ ሲሆን ቀንደኛ የኢሰፓ ካድሬ ነበረ። በዛ ላይ ለኢህአዴግ ጫፍ የወጣ ንቀት ያለውና አርከበን "ያልተገራ በቅሎ" ብሎ ይጠራ የነበረ ነዉ።

እናም የመዲናይቱ ሲቪል ሰርቪስና የትምህርት ተቋማት የተመሩት በረከት ከተማ ቀመስ ባላቸው መጤዎች ሳይሆን ለኢህአዴግ የመረረ ጥላቻ በነበራቸው የኢሰፓ ካድሬ በሆኑት አማረ ሺበሺና አበባየሁ (የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽነር) ነበር። እነዚህ ምሁራን ሲቻላቸው በሀገሪቱ ህግ መሰረት ትክክለኛ ስራ ሲሰሩ፣ ጫናውን መቋቋም ሲያቅታቸው ደግሞ በግል ፕሬሶች ኢህአዴግንና

አርከበን ሲያጋልጡ ሰነበቱ። ምርጫ 97 ደረሰና ከነዋሪው ጋር ኢህአዴግን ገለባበጡት።

ስለተከለብርሀን በአንድ ነገር ላይ በድፍረት ምስክር መስጠት እችላለሁ። ተክለብርሀን ምስኪንና ጨዋ ሰው ነበር። ብቻውን የሚኖር። ወደ አዲሳባ ሲመጣ ባዶ እጁን፣ ወደ ትግራይ ሲመለስ ደግሞ ቅያሪ ልብሱን ብቻ ይዞ ነበር። መቀሌ ችግሩን ተረድታ የድርጅት ስራ ብቻ እንዲሰራ አድርጋዋለች። በዚህ ምክንያት ውሎው ቀያዮቹ የመቀሌ አዳራሾች ሆነዋል።

***

"ገነት ትልቋ!"

ወደ ጨፌ የኦሮሚያ ምክር ቤት አዳራሽ ተመልሰናል። የጨለማው ዘመን መሪ ወደ ነበረው አሊ አብዶ አውጫጭኝ። ሀብቱ የሚባል የአዲሳባ የትምህርት ቢሮ ሀላፊና የካቢኔ አባል አሊን እንዲ ሲል ጠየቀው፣

"ከፉይናንስና ኢኮኖሚ ቢሮ ሀላፊዋ ገነት አበራ ጋር ያለህ ግንኙነት እስከምን ድረስ ነው?"

የአሊ አንቴና ተነካ። ያልተጠየቀውን ዘባረቀ፣

"ወይዘሮ ገነት ጋር ምንም ግንኙነት የለንም። ባይሆን ተፈራ ዋልዋን ጠይቁት።" አለ። ግምገማውን የሚመራው አባይ ፀሀዬ ባልተጠበቀ ሁኔታ ፊቱ ተለዋወጠ።

ሴትየዋ የኢህአዴግ አባል ስላልነበረች በግምገማው አልተገኘችም። ስጋዋ ከመቦጫጨቅ ግን አልዳነም። የከተማውን ፉይናንስ በተለይም የበጀት ዝግጅትና ገቢ መቀመቅ የከተተችው እሷ መሆኗ መግባባት ላይ ተደረሰ። ግን ደግሞ እንደዚህ ከፍተኛ የብቃት ማነስ ችግር እንዳለባት እየታወቀ እንዴት ከተፈራ ዘመን አስከ አሊ አብዶ በካቢኔ አባልነት አገለገለች የሚለው የካድሬው ያልተገለፀ ሀሜት ሆነ።

በተለይ አርከበ እቁባይ፣

"የአንድ ከተማ የደም ስር የሆነውን ገቢ ገነት አበራን ለሚመስሉ ደካማ ሰዎች የሰጠው አካል ተጠያቂ ነው!" በማለት ደጋግሞ ተናገረ። አባይ ፀሀዬ ተወራጨ።

በኢህአዴግ ቤት መኖር ሁሌም ከኋላ እንደ ጅራት የሚጐተት ጉድ አለውና ቀኑን ጠብቆ ሌላ ተአምር ተሰማ። ወይዘሮ ገነት አበራ የአዲሱ ከንቲባ አርከበ እቁባይ የፉይናንስና ኢኮኖሚ ቢሮ ሀላፊ ሆና ካቢኔውን ተቀላቀለች። ከፊት መስመርም ተሰለፈች። ታሪክም ራሱን ደገመ... መጀመሪያ አሳዛኝ ቀጥሎ

ቧልት በሚመስል መንገድ።

ብዙዎች በአርከበ ጊዜ የነበረውን ማዘጋጃ ቤት ባለ ሶስት በር ያለው "አዳራሽ" (ስያሜው ተቀይሯል) አድርገው ይቆጥሩት ነበር። ታዲያ ወደ እልፍኙ ለመግባት የበሩን ቁልፎች የያዙት ሰዎች ሶስት ነበሩ። ያለእነሱ የሚሞከር አልነበረም፦ አማረ ሺበሺ፣ አርከቴክት አማረ አስግዶምና ገነት አበራ።

አርከበ መቼም ከኋላ የሚሰሩ ሞተሮችን መምረጥ ይችልበታል። እናም ለወይዘሮ ገነት ሞከሼዋን (ገነት ትንሿ) የምትባል ምክትል ሾመላት። ገነት ትልቋ፣ ገነት ትንሿ መባል ተጀመረ።በተመሳሳይ ነባር የአስተዳደሩ ሰራተኛ የነበሩትን ኤፍሬም አለሙና ቴዎድሮስ ተፈራ የሚባሉ ወጣት ምሁራን በገቢዎች ኤጀንሲ ሀላፊነት መደቡ። ገቢዎች ኤጀንሲ በፉይናንስና ኢኮኖሚ ቢሮ ስር ያለ ተቋም ነው።

ገነት ትንሿ እንዝርት ነበረች። ስለእውነትም ከብር የሚገባትና አርአያ የሆነች የጽናት ተምሳሌት። በአውደሰብ ላይ መቅረብ የነበረባት ትንታግ ሴት። መጀመሪያ በጽዳት ሰራተኝነት ተቀጥራ አስተዳደሩን ተቀላቀለች። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን እንዳጠናቀቀች ወደ ተላላኪነት አደገች። ቤተሰብ እየመራች ወደ ኮሌጅ ሄደች። እነሆ ትምህርቷን አጠናቃ የኢኮኖሚና ፉይናንስ ቢሮ ጭንቅላት ሆነች።

የገቢዎች ኤጀንሲ ሀላፊ የነበሩት ወጣቶቹ ኤፍሬምና ቴድሮስ ደግሞ ለትልቋ ገነት አንደኛው የደም ስር ሌላኛው ደግሞ ደም ነበሩ። የሰዎችን ሀሳብ የራሷ አድርጋ በማቅረብ የተካነችው ትልቋ ገነት በደንብ ተጠቀመችባቸው። ለነገሩ ጭንቅላት፣ የደም ስርና ደም የተቀጠለላት ትልቋ ገነት ብቻ ሳትሆን አርከበና አዲሳባ ጭምር ነበሩ።

እንግዲህ በእነዚህ ሰዎች ውሰጥ በረከት "ከየክልሉ ከተማ ቀመስ ፈልገን አመጣን" ብሎ ያላቸው ካድሬዎች እንደሌሉ ልብ ይሏል። ይህ ቦታ የፓርቲ ታፔላን ሳይሆን የከተማን ፓለቲካል ኢኮኖሚን መረዳትና መተንተን ይጠይቃልና ሞፈር ዘመዶቹ ካድሬዎች አለመኖራቸው የሚጠበቅ ነበር።

ምርጫ 97 መጣና እነ ኤፍሬም አሰላለፉቸውን አስተካከሉ። ቴድሮስ ታጋይ ዘሩ የሚባል አርከበን ከመቀሌ አጅቦ የመጣ የህውሀት ነባር ታጋይ በአይነ ቁራኛ እንዲጠበቀው ትእዛዝ ተሰጥቶት ፈደራል ገቢዎች የሰው ሀይል አስተዳደር ዋና ዴሬክተር ሆኖ ተመደበ። በፓርላማ ሚስቱን ያስቀመጠው ዘሩ ኤፍሬምን ብቻ ሳይሆን እነ መላኩ ፉንታን በመሰለል ሪፓርት ያደርግ ነበር።

ከመታሰራቸው በስተጀርባ እሱ መኖሩ የሚያጠራጥር አይደለም።

የዘሩ መረን የለቀቀ ዘረኝነት የተገለፀው ገቢዎችን በተቀላቀለ በወሩ ነበር። የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ህገመንግስቱን በጣሰ መልኩ 600 አዲስ የኮሌጅ ምሩቃንን ያለ አንዳች ይፉ ማስታወቂያ ከኢህአዴግ አባላት ውስጥ መልምሎ እንዲቀጥር አቶ መለስ ትእዛዝ ያስተላልፉል። ይህን እንዲያስፈጽም ሀላፊነት የተሰጠው ዘሩ 400 የህውሀት አባላትን ከመቀሌ ድርጅት ቢሮ ጋር በመቀናጀት እንዲቀጠሩ አደረገ። የተቀረውን ቁጥር ለሶስቱ ብሄር ድርጅቶች እኩል አካፈለ።

ከሁሉም የሚያሳዝነው ከገቢዎች ኤጀንሲ የስራ መደቦች ውስጥ ከፍተኛ ሌብነት የሚፈፀምባቸው ቦታዎች አዲቲንግና ኢንተለጀንሲ በመባል ይታወቃሉ። ዛሬ በፀረ ሙስና ታሰሩ የምንላቸው ባለስልጣናትና ነጋዴዎች ስለላ የሚካሄድባቸው በኮሚሽኑ ሳይሆን ገቢዎች ኤጀንሲ ውስጥ ባለው ኢንተለጀንሲ ዲፓርትመንት ነው። በዚህ ዲፓርትመንት ውስጥ ከተመደቡት 50 ወጣቶች 40 ያህሉ ከመቀሌ የተላኩት የህውሀት ካድሬዎች ናቸው። የእነ ሚኒስትር መላኩ ፉንታ እስር ላይ አድሎ አለበት የተባለበት አንዱ ምክንያት ይህ ነው። ከቡር ሚኒስትሩም ቢሆን እነዚህን ሚስጥሮች በጉያው ደብቆ "እዚህ ነው የምከሰሰው! እዛ መዳኘት የለብኝም!" የሚል የህፃን ልጅ ጨዋታ ትቶ እውነቱን በማውጣት የኢትዮጵያን ህዝብ ይቅርታ መጠየቅ ይኖርበታል።

ከቡር ሚኒስትር መላኩ ፉንታ በፍስሀ መአሲ በኩል የሩቅ ወዳጄ ነበረና እንዲህ በማለት ላግዘው፣

"ታላቁ መሪ እንኩን የለሹን ህገመንግስትና የሀገሪቱን ሲቪል ሰርቪስ ህግ ጥሶ በገቢዎችና ግምሩክ 600 ካድሬዎችን በሲቪል ሰራተኛ መደብ ላይ እንዲቀጠር አድርጓል። እነ ታጋይ ዘሩ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ አዲቲንግና ኢንተለጀንሲ ዲፓርትመንትን በህውሀት ካድሬዎች ቁጥጥር ስር ያዋሉበት ምክንያት መርጦ ለመክሰስ መሆኑን ተረድቻለሁ። እኔ የታሰርኩት ግብር ቀነሰ ተብዬ ነው፣ እነ አርከበ GTZ የተባሉ ድርጅቶች መክፈል ያለባቸውን ከ10 ሚሊዮን ብር በላይ ግብር እንዳይከፈል አድርገዋል። ይህ ዝርዝር ጥናት ተደርጐ የተወሰነ ነበር። ይሁን እንጂ ጥናቱን ያካሄዱት ከፍተኛ ሙያተኞች አቶ አርከበ እቁባይ ቢሮው ጠርቶ ስላስፈራራቸው ሀገር ጥለው ወደ አሜሪካን ተሰደዋል... ለምሳሌ እነ እከሌ!..."

እነሆ! ታጋይ ዘሩን በቀጣይም በዘመናዊ መተካካት ማእቀፍ ውስጥ ተካቶ የህውሀት ሁለተኛ ትውልድ በመሆን በፊት መስመር እናገኘዋለን። የሀገሪቱን ገቢ ና ጉምሩክ ለመቆጣጠር እነ አርከበ ተስፉ ጥለውበታል።

ከገ/ዋህድ ተሞክሮ በመውሰድ ቢያንስ በቤቱ ያከማቸውን የጦር መሳሪያ አስቀድሞ ከመሬት በታች ይቀብራል።

የገቢዎች ኤጀንሲ ዋና ዴሬክተር የነበረው ኤፍሬም ከምርጫው ጋር ተያይዞ ክትትል እየተደረገበት እንደሆነ ከውስጥ መረጃ እንዳገኘ በሚያስታውቅ መልኩ አገር ጥሎ ወደ አሜሪካን ሀገር ተሰደደ።

ከሁለት አመት በኋላ በሀምሌ ወር 1997 የድሬደዋ ዩንቨርስቲ ተማሪዎችን ለማሰልጠን ድሬ ሄጂ ነበር። እረፍት ያደረኩት የከተማዋ ከንቲባ የነበረው ፍስሀ ዘሪሁን (መአሲ) ቤት ነበር። ታዲያ! በአንድ ምሽት የውስኪ ጨዋታ ወቅት የጨፈ ምክርቤት የተካሄደው የአሊ አብዶ ግምገማ ተነሳ። ዘባተሎና ዝርክርኩ መሪ ከትልቋ ገነት ጋር ስለነበረው ግንኙነት ሲጠየቅ የዋልዋ ልጅን ማንሳቱ አስገራሚ አንደነበር አንስተን ተሳሳቅን። ሁልጊዜም ሲከነክነኝ የኖረውን ጥያቄ ለፍስሀ እንዲህ በማለት አነሳሁለት፣

"ፊሽ! እንዴት ግን ገነት አበራ በአርከበ ዘመን ተመልሳ ካቢኔ ሆነች? አርከበ እንደዛ ሲወርድባት ከርሞ እንዴት የደም ስሩ አደረጋት? አባይ ባልተለመደ ሁኔታ ለምን ተወራጨ?" ፍስሀ ውስኪውን እየጨለጠ፣

"...አየህ! እኛ የህውሀትና ብአዴን ነባር አመራሮች መሻገር ያቃተን ትልቁ ችግር ከሴቶች ጋር የተያያዘው ነው። በትጥቅ ትግሉ ወቅት ግብረስጋ ግንኙነት መከልከሉ አሁን ለሚታየው ሴሰኝነት አስተዋጽኦ አበርክቷል። ከተፈቀደም በኋላ ብዙ ታጋይ ጋብቻ የመሰረተው በአብዮታዊነት መመዘኛ ነበር። ጉበዝ ተዋጊና አዋጊ ከሆነች ሁሉም ተሽቀዳድሞ የራሱ ሊያደርጋት ይተጋል። ከተማ ሲገባ ሁሉም ነገር ተገለባበጠ። ተፈጥሮአዊ መመዘኛዎች አብዮታዊነትን ተኩት። ቆነጃጅት የከተማ ሴቶች አመራሩን አሸፈቱት። በዚህ ምክንያት ብዙ ታጋይ ትዳሩን ፈታ። ከዚህ በተጨማሪም ሚስቶቻቸውን እየወደዱ የባልና ሚስት ቦታ ተቀያይሮ ስለነበር የተፋቱ አሉ። አባይ ፀሀዬና አዲሱ ለገሰ አብነቶች ናቸው። አባይ ሚስቱን ቢወዳትም እሳት ከምታዘንብ ጋር መኖር አልቻልም በማለቱ የበረሀ ቃልኪዳናቸውን አፈረሰ። በተቃራኒው መለስ ለኢትዮጵያ ህዝብ በቴሌቭዥን ቀርቦ "ሚስቴ እሳት የምትተፋ ቢሆንም አምኖ ከመቀበል ውጭ አማራጭ የለኝም" በማለት ተገዶ እየኖረ እንደሆነ በተዘዋዋሪ ገለፀ።"

ፍስሀ ብርጭቆውን እየሞላ፣

"...ገነት አበራን በድጋሚ ካቢኔ እንድትሆን ያደረጋት አባይ ነው። በዋልዋ የተጀመረው የነቀዘ ታሪክ በአባይ ተደገመ። አርከበ ይህን ንቅዘት ስለሚያውቅ ነበር ደጋግሞ የተቃወመው። ለሶስት አመታት ከገነት ጋር ሳይግባቡ ኖረው የተለያዩት የማይጋፉው ባላጋራ ደጀን አድርጋ ስላስቀመጠች ነበር።"

የሚገርም ነው! ዛሬ ገነት አበራ የባለሀብቶች ጐራ ተቀላቅላለች። በምርጫ 97 አርከበ ህቅ እንቅ እያደረገው የመሬቶች ባለቤት አድርጓታል። ምንጩ በታወቀ ሀብት አስመጪና ላኪም ሆናለች። ኑሮዋን አንድ እግር ኢትዮጵያ ሌላኛው አሜሪካ አድርጋለች።

***

አባዱላና ጁነዲን...

ሁለቱ የአህዴድ ካድሬዎች አንድ ሰሞን ፍቅራቸው ጣራ ነክሶ ነበር። የአህዴድ ካድሬም የተቀናጁበትን ሁኔታ "አርሴናል" በሚል አንዲት ቃል ገለፀው። ታዲያ ይሄ ከአባዱላና ጁነዲን ጋር ምን አያያዘው ?...

ነገሩ እንዲህ ነው :

አርሴናል በተለያዩ ሀገሮች ውስጥ የጦር መሳሪያ፣ የቦንብና ጥይት ዱቄት (ባሩድ) የሚሰራበት፣ የሚጠገንበት፣ የሚከማችበትና የሚሰራጭበት ማእከላዊ ቦታ ነው። የአህዴድ ካድሬዎች አንድ ሰው ለትልቅ ስልጣን ታጭቶ ከሆነ "ከአርሴናል ነው እንዴ?" ብለው ይጠይቃሉ። ሌላ ሳይሆን "ከአርሲ ነወይ?" ብለው እየጠየቁ ነው። የአባዱላና ጁነዲን ጦር መሳሪያና ባሩድ ማምረቻ ቦታ። ትግራይ ላይ የአድዋ ልጆች እንደሚባለው። ልምድ በመውሰድ ተወዳዳሪ የሌላቸው አባዱላና ጁነዲን አድዋን ጐትተው አሮሚያ ላይ አመጧት። የአርሲ ልጆች ሰልጣኑን ተቆጣጠሩት። አርሲ አድዋና አርሴናል ሆነች።

በዚህ መቀናጀት ነበር እነ ድሪባ በአርከበ ካቢኔ ውስጥ ለመቀላቀል ከአርሲ የመጡት። ድሪባ ከአንዲት የአርሲ ገጠር ወረዳ አመራርነት ተነስቶ የከተማ ልማት ጥልቅ እውቀት የሚጠይቀው የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ሀላፊ ሆነ። ከጥቂት ቀናት የጫጉላ ወቅት በኋላ የሚይዘው የሚጨብጠው ጠፉው። የእለት እቅድ ማውጣት የማይችል ሰው ራዕይና ስትራቴጂ ቅረጽ ሲባል እውነትም ግራ ያጋባል። በእውር ድንበሩ ሲፈራገጥ ሳምንታት አለፉ። በአቶ መለስ ጭንቅላት የተቀመጡ እቅዶች አፈር ድሜ በላቸው። በተለይም ትልቅ ተስፉ ጥሎበት የነበረው የከተማው ጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ወደኋላ ሲጐተት የተመለከተው አቶ መለስ አርከበንና ካቢኔውን ጠርቶ፣

"አርከበ! ጣድ ያልተባልከውን ዘጠኝ ድሰት ጣድክ። ትክክለኛ አማሳይና ማመሲያ ሳታዘጋጅ አጐረናሽው" ብሎ ተቆጣው።

ከአማሳዮቹ አንዱ ድሪባ ነበር። የአባዱላ አርሴናል!

የአቶ መለስ መልእክት የገባው ክቡር ከንቲባ እንደ ሌሎቹ ሁሉ ለንግድና ኢንዱስትሪ ከጀርባ ታኮ ማስቀመጥ ጊዜ የማይሰጠው መሆኑን ተገነዘበ። በከፍተኛ ሙያተኝነቱ የሚታወቀው ግን ደግሞ የቀድሞ ስርአት

ንክኪና ለኢህአዴግ ጥላቻ እንዳለው በየጊዜው የሚነገርለት አቶ ዮሀንስ የሚባል ትልቅ ሰው ተገኘ። በምክትልነት ተመደበ። ክንዴ የሚባል በአካባቢ ልማት ላይ የገመበተ ልምድ ያለው ነባር የአስተዳደሩ ሰራተኛ ተጨመረለት። የፓለቲካ ቅኝቱን እንዲያስተካክሉት ደግሞ ሁለት የክፍለ ከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ነባር ካድሬዎች ተመደቡለት። የድሪባ ስራ መቀስ እየተሰጠው ሪባን ወደ መቁረጥ ተሸጋገረ።

አነሆ! የበረከት ከተማ ቀመሶች ከላይ ባለው ካቢኔ ደረጃ ይህን ይመስላሉ። ወደ ክፍለ ከተማ ሲወረድ ደግሞ ለመጻፍ እንኳን ይዘገንናል። ታሪክ ነውና ምን ይደረጋል...

***

የዘረኝነት አንድ እግር በመሬት...

በአቶ መለስ የፍራቻ ቻርተር መሰረት አዲሳባ በአስር ክፍለ ከተማ የተከፈለች ሲሆን የአራቱ ክፍለ ከተማ ከንቲባዎች አርከበ ከትግራይ ይዘአቸው የመጣው የህውሀት ካድሬዎች ነበሩ ...ቂርቆስ አተይ (በአሁን ሰአት የኤፈርት ማርኬቲንግ ዴሬክተር)፣ የካ ግርማጺዮን (በአሁን ሰአት የአፋር፣ ጋምቤላ፣ ቤኔሻንጉል፣ ሱማሌ የበላይ ጠባቂ)፣ ላፍቶ ሀይሌ ፍስሀ (በአሁን ሰአት የአዲሳባ ስራ አስኪያጅ)፣ ቦሌ ሀ/ስላሴ (የትግራይ ዞን አስተዳዳሪ)።

ከንቲባ ባልሆኑባቸው ክፍለከተሞች ደግሞ ምክትል ነበሩ... ኮልፌ ነጋ በርሄ (በአሁን ሰአት የኢህአዴግ ስልጠና ማእከል ካድሬ)፣አራዳ መውጫ (ስራና ከተማ ልማት)፣ አዲስ ከተማ ታደለ (ፓስታ ድርጅት ስራ አስኪያጅ)፣ ቦሌ ገ/ተንሳይ (ስራና ከተማ ልማት)፣ ጉለሌ ከበደ ብሩ(ስራና ከተማ ልማት)፣ ልደታ ዘሩ (የገቢዎች የሰው ሀይል ዳሬክተር)...

በፊት መስመር ላይ የህውሀት ካድሬዎች እንዲሰለፉ የተደረገው በታቀደ መልኩ በአቶ መለስ፣ አባይ ፀሀዮና አርከበ መቀናጀ ነበር። ምክንያቱ ደግሞ መዲናይቱ ከፌደራል ሊመደብላት የታቀደው ማለቂያ የሌለው ገንዘብና ድግፍ ምክንያት ልማት መምጣቱ የማይቀር ስለነበር፣ የለውጡ ሀዋርያት እነዚህ ካድሬዎች መሆናቸውን ለማሳየት የታቀደ ነበር። የአዲሳአባ እድገት በትግራይ ልጆች ዳግም መስዋእትነትና ቁርጠኛ አመራር እንደመጣ ለመናገር። አዲሳባ የትንሳኤ አክሊል ያጠለቀችው በእነ አርከበ፣ ተከለብርሀን፣ ግርማጺዮን፣ ሀይሌ ፍስሀ፣ አተይ፣... አማካኝነት መሆኑን ለማብሰር።

እንደ እውነቱ ከሆነ የኦህዴድ ከተማ ቀመሶችን ለመግለጽ ያሳፍራል። ከአርሲ ገጠር መጥቶ የላፍቶ ክ/ከተማ አፍና ጆሮ እንዲሆን የተመደበው ካድሬ በመጣ በሁለት ወሩ ስራውን አልቻልኩትም በማለት ወደ መጣበት ተመለሰ።

ልደታ ሲቪል ሰርቪሱን፣ መምህራንንና አቅም ግንባታን ይመራል ተብሎ ከአርሲ የተመደበው ካድሬ (ከበደ ይባላል) አንድም ቀን ሰራተኛና መምህራን ሳይሰበስብ ዘመኑ አለቀ... "ገና ሳያቸው ያስፈሩኛ" ብሎ።

ብአዴንም ተመሳሳይ ነበር፣ "ጋንጃ ጋንጃውን" የሚለው ወግ ከገጠራማው የአማራ ክልል የመጣው ታረቀኝ ታሪክ ነው። ተራውን ጠበቆ ይመጣል። ህላዌ "ፈላስፉው" ብሎ የሚጠራው የአቃቂ ምክትል ከንቲባ ጫኔ ይባላል። ርግጥም ጥሩ ሰው የነበረው ጫኔ የታላቁ ፈላስፉ ሲስሮ ደቀመዝሙር ነበር። የልደታ ከንቲባ የነበረው ቢያዝን በሚያሳዝን ሁኔታ የአማኑኤል አእምሮ ህሙማን ሆስፒታል ቤተኛ ሆነ። ከምርጫ 97 በኃላ ቢያዝን ኢህአዴግ ቢሮ ተመድቦ እኛን ተቀላቅሎ ነበር። ከአለታት በአንዱ ቀን አስደንጋጭ ነገር ተከሰተ።

እንዲህ ነበር የሆነው።

በህላዌ ቢሮ የከተማው ኢህአዴግ ከንፍ ስራ አስፈፃሚዎች የስራ ግምገማ እያደረግን ነበር። ግምገማው እየጠጠረ ሲሄድ አህዴድ ለመዲናይቱ የወከለው የማእከላዊ ኮሚቴ አባል ቀንአ ሶና የሚባል ካድሬ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ። በፍጹም መጽናናት አቃተው። ህላዌ ተደናግጦ እኔ፣ ቢያዝንና ፀጋዬ ሀይለማርያም ለብቻ ወስደን እንድናግባባው አዘዘን። ካሚል ቢሮ ይዘነው ሄድን። ከብዙ ማግባባት በኃላ የአእምሮ ጭንቀት እንደያዘው ነገረን። ምድር ሰማይ እንደዞረበት፣ በአይኑ እንቅልፍ ከዞረ ወራት እንዳለፈ አጫወተን። ምክንያቱ ደግሞ በምርጫ 97 ብጥብጥ ወቅት የሞቱ ህፃናትን በመመልከቱ ከጭንቅላቱ ማውጣት እንዳልቻለ ነገረን።

የቀናአ ልቅሶ ለወራት ማባራት አልቻለም። አማራጭ ሲጠፉ እንባውን የሚጠበቅለት ቦታ ተገኘ። እምባ ጠባቂ ኮሚሽን። የህዝብ እምባ ጠባቂ ተቋም የፓለቲካና ህግ ጉዳዮች ሀላፊ በመሆን የተቋመ ሁለተኛ ሰው ሆነ። እንደ እውነቱ ከሆነ ቀንአ የዋህና ሆደ -ባሻ ካድሬ ነበር።

የቀንአን እምባ ባስጠበቅን በሳምንቱ የልደታ ከንቲባ የነበረው ቢያዝን ልብሱን ቀዳደደ። እኔና ፀጋዬ በድጋሚ አደራ ተጣለብን። የሚሆን አልነበረም። ቢያዝን ለያዥ ገናዥ አስቸገረ። የሚናገረውን ሳተ። እንዲህ በማለት ሚስጥር አወጣ፣

"የእኔ ምክትል ታጋይ ዘሩ ነው የተኮሰው! እኔ አይደለሁም ምክትሌ ዘሩ ነው የተኮሰው! እሱን ሂዱና ጠይቁት። ለምን እኔን ረፍት ትነሱኛላችሁ?"

ቢያዝን አማኑኤል ገባ። ለሶስት ወራት ህክምናውን እየተከታተለ ከቤቱ

እንዳይወጣ ተደረገ። ማገገሙ ሲታወቅ አስቀድሞ ወደ ገቢዎች የሄደው ታጋይ ዘሩ ተሯሩጦ ገቢዎች ኤጀንሲ በከፍተኛ ሀላፊነት አስመደበው። ይሁን አንጂ የዘሩ ጥይት ወደ ሰማይ ይሁን ወደ ሰው መተኮሷን ማጣራት አልተቻለም። የሚደፍርም ጠፋ። ይሄ እውነት ቢያንስ በህላቄ፣ ካሚልና ፀጋዬ ሀይለማርያም እጅ ይገኛል።

***

ምእራፍ አስራ ሶስት

ቆርኪው ሲላጥ

አቶ በረከት በሁለት ምርጫዎች ወግ መጽሐፉ ምእራፍ አንድ ማሚሻ ወግ በሚለው ርዕስ ስር፡

"...አዲሱ የአዲሳባ አመራር በከፍተኛ ተነሳሽነት ሰራ በጀመረ ማግስት በብዙ መስኮች የቆየውን አዝጋሚ አካሄድና አመራር የሚቀይር በኢትዮጵያ አዲስ የከተሞች አድገት ምእራፍ መከፈቱን የሚያበስር ሰፊ እንቅስቃሴ አቀጣጠለ። ነባሩን የሰው ሀይል በተለይ ሲቪል ሰርቪሱን በአጭር ጊዜ ገምግሞ ግልብጥብጡን አወጣው። በአዲስ አበባ የለውጥ መንፈስ ብቻ ሳይሆን ተጨባጭ የለውጥ መስቃቃት ታየ። በዚህም የአዲስ አበባ ትንሳኤ ተበሰረ።" በማለት ይገልፃል።

አቶ በረከት በዚህ መልዕክቱ የአዲሳባን ቢሮክራሲ በመገምገምና በማስተካከል የተጀመረው ለውጥ ለትንሳኤ ብስራት መነሻ እንደሆነ ይነግረናል። ማን ያርዳ የቀበረ ነውና በወቅቱ የነበረውን እውነታ ከውስጥ ሆነን ለምናውቀው ሰዎች ውጤቱ የተለየ ነበር።

የከተማው ነዋሪና ሲቪል ሰርቪሱ፣ "አርከበ በሚባል የህዳር በሽታ ተረፈረፍን" ያለበት "የለውጥ ኮሚቴ" ተብሎ የተሰየመው አካል በጐሰኝነት፣ በጥቅማ ጥቅምና ዘመደ አዝማድ የተቆላለፈበት ነበር። ግምገማው በዝጉብኝ የተከናወነ ሲሆን ለወራት የተራዘመ ነበር። ቢሮክራሲው ጭንቅ አርግዞ ቀንና ለሊቱን በፀሎት ያገጣጠመበት መጥፎ ወቅት።

በመሆኑም ይህ የሺዎች እንባ የፈሰሰበትን አጋጣሚ ገለጥ ገለጥ አድርገ ማየት ያስፈልጋል። እንግዲህ የከተማው ሲቪል ሰርቪስና የኢህአዴግ አባላት የተገላበጡበት ሂደት ቆርኪው ሲላጥ የሚከተለውን ይመስላል፡ -

***

"አርከበ የህዳር በሽታ!!"

በአንድ ወቅት በከተማችን ውስጥ "አርከበ የህዳር በሽታ" በማለት

ህዝቡ የሰየመው በሽታ ይነሳል። በሽታው በጅምላ ጠራርጐ የሚገል ወረርሽኝ ነበር። ይህ ወረርሽኝ አርከበ እቁባይ ከንቲባነት በተመደበ በወራት ጊዜ ውስጥ የተከሰተ ሲሆን እያሳደደ የገደለው ከ10ሺህ በላይ የሚሆነውን የአስተዳደሩ ሰራተኞንና የኢህአዴግ ካድሬዎችን ነበር።

የአርከበ የተሳሳተ ትርጉምና ጠባብ አስተሳሰብ በፈጠረው ችግር ምክንያት በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ቤቱ ያልተንኳኳበት የከተማው ነዋሪ አልነበረም። አራትና አምስት የልጅ ልጆች የሚያሳድጉ እናቶች ሰለባ ሆነዋል። በጥበቃ ስራ የሚተዳደሩ አዛውንቶች ወገባቸው ተሰብሯል። አስተዳደሩ ከፍተኛ ወጪ አውጥቶ ውጭ ሀገር ድረስ ያስተማራቸው ከፍተኛ ሙያተኞች ሳይቀር በወረርሽኙ ተጠቅተዋል።

መንስኤው ክቡር ከንቲባው አቶ መለስ የሰጠውን ትእዛዝ ስላልተገነዘበና በተሳሳተ መንገድ ስለተረገመ የተከሰተ ነበር። በወቅቱ አቶ መለስ አስተዳደሩ አዲስ አስተሳሰብ ሊቀበሉ በሚችሉ የተማሩ ሰዎች እንዲመራ ትእዛዝ ያስተላልፉል። ሁልጊዜም ቁንጽሉን ወስዶና የራሱ ፈጠራ አድርጐ የሚሮጠው ክቡር ከንቲባ የቢሮክራሲውን ውስብስብ ያለ ችግርና ብሶት ሳይገባው ወደ ስራ ይገባል። የሀገሪቷን ሲቪል ሰርቪስ ህግ ባልተከተለ መንገድ "የለውጥ ኮሚቴ" የሚባል የሌባ ጥርቅም ከላይ እስከ ታች ያደራጃል። የለውጥ ኮሚቴዎቹ ተጠሪነት ለእሱና ወደ መዲናይቱ ይዞአቸው ለመጣው አዲሶቹ ካድሬዎች ያደርጋል።

በወቅቱ አርከበ በአውደ አመት ልዩ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ላይ ቀርቦ ስለ በሽታው ተጠይቆ ነበር። እሱም ተኮፍሶና ፈገግ ብሎ "በከተማው ከዚህ ውጭ ሌላ ወሬ ያለ አይመስለኝም!" የሚል ምላሽ ሰጥቷል። ይህቺ ንግግሩ ሰውየው ምን ያህል ነገሮችን አዙሮ ማየት እንደማይችልና የብአዴን ቁንጮዎች "የፓለቲካ ደሀ" ብለው የሚጠሩትን ያረጋገጠ ነበር።

ሲጀመር ህዝቡ እየተናገረ ያለው ስለሚያስደስተው ነገር ሳይሆን ስለ በሽታ ነው። ያውም በአዲሳባ ታሪክ ውስጥ በመግደል ተወዳዳሪ የሌለውና ማንንም ሳይለይ የጨረሰ ወረርሽኝ። የአዲሳባ ታሪክ በተነሳ ቁጥር የከተማዋን ነዋሪዎች የጨረሰውና በ1911 ዓ.ም የተከሰተው "የህዳር በሽታ" አብሮ ይታወሳል። ሲቀጥል በሽታው ያጠቃው ኢህአዴግ ማህበራዊ መሰረቶቹ ናቸው እያለ የሚዘምርላቸው በዝቅተኛ ስራ ላይ የተሰማሩ እናቶችንና ብልጣ ብልጥ ያልሆኑ ሙያተኞችን ነበር። በመጨረሻም አብዮት ልጆቿን ትበላለች በሚለው ታሪክ ደጋሚ እሳቤ መሰረት የገዛ አባሉንና ካድሬው የተረፈረፈበት።

***

ራሱን የለወጠው የለውጥ ኮሚቴ...

ኮሚቴው በከተማ፣ ወረዳና ተቋም ደረጃ እንዲቋቋም ተደረገ። አንዳንዶቹ የለውጥ ኮሚቴዎቹ በመጣው ስርአት ቆዳቸውን እየቀያየሩ ሰራተኛውን ደም እምባ ሲያስለቅሱ የነበሩት ሆኑ ። በተለይ በቢሮዎች የተመሰረቱት የለውጥ ኮሚቴዎች ስብጥር አስደንጋጭ ነበር። መረጃ የደረሳቸው የግል ፕሬሶች ኢህአዴግ አይንና ጆሮ የለውም የሚሉ ሰፉፊ ጽሁፎችን በመፃፍ ሂደቱን አጋልጠዋል። ርግጥም የአርከበ ዘረኝነት ከመጀመሪያው ፍንትው ብሎ የወጣበት ነበር።

ለአብነት የትምህርት ቢሮ የለውጥ ኮሚቴ ብሎ ከሰየማቸው ሰባት አባላት ውስጥ ስድስቱ የህውሀት ካድሬዎች ነበሩ። ከዚህ በመነሳት የትምህርት ቢሮ ምደባ ምን ሊመስል እንደሚችል መገመት ቀላል ይሆናል። ለማሳያ እንዲሆን በቀጣዩ ክፍል ይቀርባል።

የለውጥ ኮሚቴው በኢህአዴግ እንደተለመደው በዝጉብኝ ስብሰባ ስራውን ጀመረ። ሰራተኛውን "የለውጥ ሀይል"፣ "የለውጥ ሀይል ያልሆነ" በሚል ሁለት ጐራ ከፈለ። ይህ አሰራር ህገ መንግስቱንና የህገሪቱን ሲቪል ሰርቪስ ህግ ባልተከተለ መንገድ ሰራተኛውን የፈረጀ ነበር። የህገሪቱ ሲቪል ሰርቪስ ህግና የአስተዳደሩ ደንቦች አንድ ሰራተኛ ሲመዘን፣ ሲቀጣና ከስራ ሲሰናበት በምን አግባብ ሊሆን እንደሚችል በግልጽ ያስቀምጣል። ሰራተኛው የሚወሰድበት እርምጃ በምን ምክንያት እንደሆነና የቅጣቱ ደረጃ የት ላይ ማረፍ እንደሚገባው ተዘርዝሮ ሰፍሯል። ሰራተኛውም በየጊዜው ስልጠና ወስዶበት የሰራው መመሪያ አድርጐታል። አተገባበሩም በየደረጃው ከሰራተኛው የተመረጡ ዲስፕልን ኮሚቴዎች በማቋቋም የሚፈፀም ነበር።

ለህግ የበላይነት ቁብ የማይሰጠው አርከበ ስራውን ሲጀምር መጀመሪያ የደረመሰው ይህንን ህግ ነበር። የአስተዳደሩን ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ከጨዋታ ውጭ አደረገ። በየደረጃው በሰራተኛው ምርጫ የተቋቋሙትን የዲሲፕሊን ኮሚቴዎች አፈረሰ። በወቅቱ ህግ ተጥሷል በማለት የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ኮሚሽነር አበባየሁ በመናገሩ ለጊዜው ምደባ እንዳያገኝና እንዲንሳፈፍ አደረገው። ምርጫ 97 ተከትሎ "ቅንጅትን ደግፏል፣ ቀንደኛ ኢሲፓ ነበረ" በማለት ከኮሚሽነርነት አውርዶ የውሀና ፍሳሽ ባለስልጣን በተራ ሰራተኝነት እንዲመደብ አደረገው።

በሌላ በኩል ቀን ቀን በሩን ዘግቶ የለውጥ ሀይል የሆነና ያልሆነ በሚል የሚፈርጀው ኮሚቴ ነውረኛ ተግባሩ መሸት ሲል በየመሸታ ቤቱ መገለጽ

ጀመረ። በጭንቀት ላይ ያለው ሰራተኛ እንደ እንቁራሪት ተወጥረው ሊፈነዱ ወደደረሱት የኮሚቴ አባላት ምሽቱን ጠብቆ ይሄዳል። ለክፉ ቀን ያስቀመጣትን ገንዘብ በማውጣት እሰከ አፍንጫቸው ይጋብዛል። ጉርና ሆዳቸውን ይሞላል። ዘመነኞቹ ሲጠግቡና ሲሰክሩ የቀን ሚስጥራቸው ይዘከዝካሉ። ይህም በሰራተኛው ዘንድ የበለጠ ሽብር መፍጠር ጀመረ።

በሂደትም በተቋማት ያለው የለውጥ ኮሚቴው ወደሚያስፈራ ሀይል ተቀየረ። በወራት ውስጥ አስተዳደሩ እጅ ያሉ ጉዳዮችን እያስፈፀሙ ኪሳቸውን አደለቡ። መሬት መስጠት በታገደበት ሁኔታ የሞቱ ፉይሎችን ህይወት እየዘሩ የከተማዋን መሬት ተቆራመቱ። ወትሮ በዘር ስልቻ ውስጥ ራሱን ከቶ የማያውቀው የከተማው ሲቪል ሰርቪስ በለውጥ ኮሚቴዎቹ በነዙት ወሬ ምክንያት ዘሩን መቁጠር ጀመረ። አማራነት፣ ጉራጌነት፣ ኢትዮጵያዊነት የሚያስጠቃ ሆነ።

ርግጥ ከዘር ማንዘር ጋር በተያያዘ በኮሚቴው አባላት ያሰራጩት ወሬ ከእውነት የራቁ አልነበሩም። አርከበ በውስጠ ድርጅት ስብሰባ ላይ፣

"ከአዲሳባ ቢሮክራሲ ውስጥ 65% አማራ በመሆኑ አስተዳደሩ የትምክህት ጫካ ሆኖ ከርሟል። ይህንንም መስበር ይኖርብናል " በማለት በተደጋጋሚ ሲገልጽ ነበር። የእሱን ንግግር ተከትሎ በአቅም ግንባታ ቢሮ በተዘጋጀው የስልጠና ሰነድ ላይ 65% ያህሉ ሲቪል ሰርቪስ አማራ መሆኑ ፍትሀዊ እንዳልሆነና በተራዘመ ጊዜያቶች ቢሮው የማመጣጠን ስራ እንደሚሰራ አስታወቋል።

ከጉራጌ ተወላጆች ጋር ተያይዞ የነበረው ውሳኔ በተቻለ መጠን በፓርቲ አመራር ደረጃ እንዳይመጡ መከላከል ነበር። ርግጥ በዚህ ጉዳይ የመጀመሪያው ተጠያቂ አቶ መለስ ሲሆን አርከበ የማስፈፀም ሚና ነበረው። በዚህ ምክንያት በአርከበ የከተማ ካቢኔ ውስጥ የጉራጌ ተወላጅ የሆነ ካድሬ አልነበረም። ክፍለ ከተማ ከነበረው 70 ስራ አስፈጻሚ ውስጥ ሁለት ካድሬዎች ብቻ የጉራጌ ተወላጆች ነበሩ። የላፍቶው ሚፍታህ አብዶና የጉለሌው ዳንኤላ አርጋው። የሁለቱ ካድሬዎች መጨረሻም አሳዛኝ ነበር። ሚፍታህ ወደ ቃሊቲ ሲወረወር ፣ ዳንኤል ከስራና ድርጅት ተባሯል።

ወራት ከፈጀ ዝጉብኝ በኃላ የለውጥ ኮሚቴ አባላት ስራቸውን ማጠናቀቃቸው ታወቀ። ይህንን በማስመልከት አርከበ በቴሌቪዥን ቀርቦ መግለጫ ሰጠ። የአስተዳደሩ ሰራተኞች በየወረዳው በሚገኙ አዳራሾች በመሰብሰብ ምደባቸውን እንዲሰሙ ጥሪ አስተላለፈ። በከተማው የምንገኝ ነባር ካድሬዎች ደግሞ በየወረዳው እየተዘዋወርን ሂደቱን እንድንመለከት ትእዛዝ

ተሰጠን። መድረኮቹን የሚመሩት እነ አርከበ ይዘዋቸው የመጡት ምስለኔዎች እንደሆነ በጥብቅ ተገለፀልን።

ወደ 50ሺህ የሚጠጋው ሰራተኛ በየአምነቱ ፀሎቱን አድርሶ፣ ፊት ለፊቱ ከተደቀነው የህዳር ወረርሽኝ እንዲያወጣው ስለቱን ተስሎ ወደ አዳራሾቹ ተመመ።

በረከት በመፅሀፉ ላይ "ግልብጥብጡን አወጣነው" ያለው ቢሮክራሲ አጀግመሩ ይህን ይመስላል። የለውጥ ኮሚቴዎች ዝቅተኛ ሰራተኛውን በጅምላ፣ ሙያተኛውን ደግሞ ለራሳቸው አስቀድመው የመደቡትን ወንበር ሊቀናቀን ይችላል ብለው ያሰቡትን የጠረጉበት አጋጣሚ። ወደ ውስጥ ገብተን ሽግሽጉ ከየት ወደ የት እንደሆነ በግልጽ ስለሚያሳይ እጅግ በጣም ጥቂቶቹን በማንሳት ወደ መመልከት እንሸጋገር።

***

"ቢሮ ሀበሬታ ትምህርቲ!"

የአርከበ ግልጽ ዘረኝነት ከተገለጸባቸው ቦታዎች ሌላኛው ትምህርት ቢሮ ነበር። ይህ በታሪክ ተወቃሽ የሚያደርግ ስራ የተመራው ከበደ ብሩና ገ/ትንሳይ (ከቤና ገሬ) በሚባሉ የአርከበ ቀኝ እጅ የህውሀት ካድሬዎች ነበር። እነዚህ ካድሬዎች ከከተማ እስከ ትምህርት ቤት ያሉትን የለውጥ ኮሚቴዎች በህውሀት ካድሬዎች ጠቀጠቁት።

እንደ እውነቱ ከሆነ የትምህርት ቢሮ የዝጉበኝ ግምገማውን አጠናቆ ውጤቱ ይፉ ሲደረግ ያልደነገጠ አልነበረም። ቢሮው የለውጥ ሀይል አይደሉም ብሎ ካባረራቸው 60% የአማራ ተወላጆች ሆኑ። በተቃራኒ በመላው አዲስ አበባ በሚገኙ ኮሌጆች፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤቶችና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተመደቡት ባለስልጣናት፣ ዲኖችና ርእሰ መምህራን አብዛኛው የህውሀት አባላት ሆኑ።

ከአስተዳደሩ መዋቅር ውስጥ የአድሎአዊ አሰራርና የዝርፊያ ዋነኛ ማእከል የሆነው ትምህርት ቢሮ አመራሩ በህውሀት ካድሬዎች ተዋጠ። ከሌላ ብሔረሰብ ለታይታ እንዲመች ካፊኞው ዶክተር ዘሪሁንና አማራው ወርቅዬ ብቻ ለማጣፈጫ ጣል ተደረጉ (በከፍተኛ የትምህርት ሙያተኝነቱ የተጨበጨበለት ወርቅዬ በተመደበ በስድስት ወሩ "ከህሊናዬ ጋር እየተጣላሁ እስከ መቼ" ብሎ ስራውን ለቆ የውጭ ድርጅት ተቀጠረ)።

የትምህርት ቢሮ የጐጥ ምደባ በትምህርት አመራርና ሙያተኛ ብቻ የታጠረ አልነበረም። የአቶ መለስ ታናሽ እህትን ጨምሮ የተቀረው ቢሮክራሲና ድጋፍ ሰጪ ከአመራሩ ጋር ቀጥተኛ ትስስር ያለው ሆነ። የቢሮው የስራ ቋንቋ በይፋ ባልተገለፀ ሁኔታ ወደ ትግርኛ ተለወጠ። የተዘረጋው ኔትወርክ የቢሮው ሀላፊ ዶክተር ዘሪሁን አስነጥሶ ሳይጨርስ እነ ከቤና ገሬ ጋር የሚያደርስ ሆነ። በዚህ የተማረረው ዶክተር ዘሪሁን የተስፋ መቁረጥ ዥዋዥዌ ሲጫወት ከረመ።

በከተማ ደረጃ የነበረው ዝቅጠት በክፍለ ከተማ ደረጃ ተመሳሳይ ነበር። የቂርቆስ፣ የካ፣ ጉለሌ፣ ላፎቶ፣ ልደታ፣ ኮልፌ፣ አራዳ፣ ቦሌ ክፍለ ከተማ ትምህርት መምሪያ ሀላፊዎች የህውሀት ካድሬዎች ሆኑ። ሁለት ክፍለ ከተማ ብቻ አዲስ ከተማ (ወ/ሮ አበዜ) እና አቃቂ (አቶ ግርማ ጀርመን) ከሌላ ተቀላቀሏቸው። አንድ ከአማራ፣ አንድ ከኦሮሞ።

በጥሬው የሚበላባቸው በከተማው ስር የሚገኙ ኮሌጆች ፕሬዝዳንቶችና የትምህርት አመራሮች ውስጥ ከ80% በላይ የህውሀት ካድሬዎች ሆኑ። የሁለተኛ ደረጃ ርእሰ መምህራንም ተመሳሳይ ነበር። ይህ አይን ያወጣ ብልግና በመምህራን ዘንድ በመድረሱ ምክንያት የትምህርት ቤቶች መነጋገሪያ ሆነ። የመምህራን ማህበር በሂደቱ ባይተዋር በመደረጋችን የመጣ ችግር በማለት የተቃውሞ መግለጫ አወጣ። መምህራን ኢህአዴግ እንደዚህ ዝቅ ብሎ አያላግጥንም በማለት ቂም አዝለው እስከ ምርጫ 97 ድምጻቸውን አጠፉ።

የምሁራን መናኸሪያ የሆነ ቦታ ላይ እንዲህ አይነት እርምጃ መውሰድ የህዝብ ንቀትና በዘር ላይ የተመሰረተ ሌብነት ካልሆነ በስተቀር ሌላ ምን ሊሆን ይችላል? ርግጥም በመጨረሻ የተረጋገጠውም ይህ ነው። የለውጥ ኮሚቴውን የመሩት ከቤና ገሬ በከፍተኛ ሌብነት ውስጥ ተዘፍቀው ተገኙ።

***

"ጋንጃ ጋንጃውን"

የሲቪል ሰርቪሱ ምደባና አረንቴሽን እየተዟዟርን እንድንመለከት በተነገረን መሰረት ወረዳዎች ተከፋፈልን። ለእኔ ወረዳ 21 (ቂርቆስ) እና ወረዳ 20 (ጐፋ ገብርኤል) ደረሰኝ። በቅድሚያ ወደ ወረዳ 21 ቀበሌ 09 አዳራሽ ሄድኩኝ።

ብዙዎቹን ሰራተኞች አውቃቸዋለሁ። በሶስት ወር ውስጥ ባደረባቸው ስጋት ምክንያት ፊታቸው ገርጥቶ አመድ የተነሰነሰባቸው መስለዋል። የታመቀው ጩኸታቸው አጥንት ሰርስሮ ይገባል። የአንዳንድ እናቶች ድምፅ መታፈን

አልቻለም። ሳያስቡት ይፈነዳል፣

"የጭንቅ አማላጅቷ እንግዲህ አንቺ ታውቂያለሽ"፣

"ገብርኤል! አንተ እያለህ መቼም ለምግብ እንጂ ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ሁለት የሙት ልጆችን ባዶ ሜዳ ላይ አትጥል" ይላሉ።

ብአዴን ካመጣቻቸው አንዱ የሆነውና የቂርቆስ ምክትል ከንቲባ ሆኖ የተመደበ ታረቀኝ የሚባል ካድሬ ስብሰባውን እየመራ ነው። ሰራተኛው አይቶ ስለማያውቃቸው አንዱ ለሌላኛው፣ "ደሞ እነዚህ እነማን ናቸው?፣ አይ! ይሄኛው ደግሞ እንደወረደ ነው።" ይላል። ሌላኛው ደግሞ፣ "አልሰማህም እንዴ በድፍን ከተማ እየተወራ ያለውን። የጠገበው ሄዶ የራበው ጅብ መጣ የተባሉት እነዚህ ናቸው" በማለት በተባረር የሰማውን ይናገራል።

የመድረክ መሪው ታረቀኝ በበኩሉ የፈረደበትን የቀድሞ ካድሬ እንዲህ በማለት መኮነን ጀመረ፣

"ከዚህ ቀደም የነበረው አመራር የከተማዋን ህዝብ ጋንጃ ጋንጃውን ሲመታ ነበር፣ እኛ ግን አዲሳባን የቤጂንግ ታናሽ እህት ለማድረግ ቆርጠን ተነስተናል"። እንደ እውነቱ ከሆነ ታረቀኝን ጨምሮ ብዙዎቹ በቴሌቭዥን እንኳን የቻይናን ከተማ አይተዋት የሚያውቁ አይደሉም።

ከኮሜን በለመዱት የአርሶ አደር ቅኝት ለመሰብሰብ የፈለጉት ካድሬዎች ከልቡ የሚያዳምጣቸው ጠፉ። ከምንም በላይ ሰራተኛው እንደ ዝንጀሮዋ መቀመጫዬን ብሏል። የታረቀኝ ገጠር ቀመስ ዲስኩር ማቆሚያ ሲያጣ ሰራተኛው ተሰላቸ። ማጉተምተም ጀመረ።

አንድ ተሰብሳቢ ሳይፈቀድለት፡ -

"ስማ ወንድሜ! ጋንጃ ጋንጃውን ስትል አልገባኝም? ኢህአዴግ ግን መቼ ይሆን ትላንትናን አመስግኖ መናገር የሚጀምረው። አዲሳባን ከተቆጣጠራቸሁ ስንት ዘመን አለፋቸሁ? ንጉሱና ደርግ ጠላታቸሁ ስለሆነ ሀጢያት ብታበዙባቸው አይገርምም። የሚደንቀው ትላንትና ኢህአዴግ የመደባቸውን ባለስልጣናት ድክመት በማጉላት ዛሬን ልትሻገሩ መፈለጋችሁ ነው። የአዲሳባ ከንቲባ የነበሩት አቶ ተፈራ ዋልዋ ጥሩ ሰርተዋል ተብሎ መሰለን የአቅም ግንባታ ሚኒስትር የሆኑት፣ አቶ አሊ አብዶ 4 ሚሊዮን ከሚሆነው የአዲሳባ ነዋሪ ወደ 30 ሚሊዮን በላይ የሚሆነውን የኦሮሚያ ክልል ነዋሪ ለማስተዳደር መስሎን የኦሮሚያን ካቢኔ የተቀላቀሉት። አይ አይደለም የምትሉንና የተለየ ግምገማ ካላችሁ ንገሩንና አብረን እንኮንናቸው።" ብሎ ተነገረ።

አዳራሹ በጭብጨባ ተናወጠ። ከየቦታው ስድቦች ተወረወሩ...
"ምድባችንን እንድትነግሩን ነው የመጣነው!"፣
"ስብከቱን ለነገ አቆዩልን!"፣
"እሳት ካየው ምን ለየው? ሁላችሁም አንድ ናችሁ!"
"የጠገበው ሄዶ የራበው ጅብ መጣ!"...

ስብሰባው ተቋረጠ። አፍታም ሳይቆይ ሞባይሎች መንጫረር ጀመሩ። በአርምሞ ሁሉንም መመልከት ጀመርኩ። አጠገቤ የተቀመጠው ጐልማሳ ስልክ ያወራል። የሚያናግረው እንባውን እያፈሰሰ ነበር። ለምን እንደሚያለቅስ ጠየኩት። ወረዳ 20 ስብሰባው ተጠናቆ የሰራተኛው ምደባ ግድግዳ ላይ መለጠፉንና ታላቅ እህቱ የለውጥ ሀይል አይደለሽም ተብላ እንደተባረረች ነገረኝ። ሶስት የሙት ልጆች የምታሳድገው ለብቻዋ እንደሆነ ጨምሮ ገለፀ።

ስብሰባውን መቀጠል ስላልቻለ ምደባ ወደ ተነገረበት ወረዳ 20 በፍጥነት ሄድኩኝ። በመንገዴ ላይ የታረቀኝ "ጋንጃ ጋንጃውን" ማንን እንደመታ ማሰብ ጀመርኩ። የትምህርት ደረጃቸው ከ9ኛ ክፍል በታች የሆኑት በሙሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከምደባ ውጭ ሆነዋል። አዲስ የተሰራው መዋቅር ጽዳትና ተላላኪነትን፣ ጥበቃና አትክልተኛን ወደ አንድ መደብ ስለጨፈለቀ በዚህ ስራ ላይ ከተሰማሩት ግማሽ ያህሉ መቀነሳቸው ግልጽ ነበር። ያለምንም ጥፋታቸው ከስራ እንደሚባረሩ እየታወቀ አስቀድሞ የተዘጋጀላቸው ቦታ አልነበረም። እነዚህን ብቻ ለአብነት ወስደን ከስራ እየተባረረ ያለው ማነው? ወደ ጐዳና እንዲወጣ እየተገፋ ያለው የማን ልጆች ናቸው? የአርከበ ጋንጃ የቆራረጠው እነማንን ነው?

በነገራችን ላይ ታረቀኝ በጨፈ አሮሚያ በተደረገው የካድሬዎች ግምገማ ላይ ይህቺ ኪሱ ይዟት የሚዞረውን "ጋንጃ ጋንጃውን" የምትል ቃል በተደጋጋሚ ተጠቅሞባት ነበር። ለእኔም ስም የማውጣት ተራ ደርሶኝ" ጋንጃ ጋንጃውን" ብዬ የዳቦ ስም አወጣሁለት። ከዛ ቀን ጀምሮ ስንጠራው የነበረው በአዲሱ ስም ነበር። ዘመን አለፉና የምርጫ 97 ማግስት ላይ ለምን ተሸነፍን በሚለው ጥያቄ ላይ ህላዌ ነብሴ አረንቴሽን ሊሰጥ ጠራን። በስብሰባው ላይ የተገኘው ታረቀኝ እጁን አውጥቶ፣

"ህላዌ! የአዲሳባ ህዝብ ጋንጃ ጋንጃችንን ለምን እንደመታን አልገባኝም?" ብሎ ጠየቀው።

ህላዌ ነብሴ ቆጣ ብሎ፣

"ታረቀኝ! ዛሬም አልከተምክም? የከተማዋ እምብርት ከሆነችው ቂርቆስ ከማኖር ውጭ የት እንውሰድህ?" ብሎ ገሰፀው።

ታረቀኝ መከተም ቢያቅተውም ከአዲሳባ ሳይወጣ ቀርቷል። የግብርና ሚኒስቴር ጀሮና አፍ ሆኗል። ያውም የተቋሙ ሁለተኛ ሰው። ታረቀኝ የግብርና ሚኒስቴር የህዝብ ግንኙነትና የፓለቲካ ጉዳዮች ሀላፊ ሹመት ተሰጥቶታል። በየአመቱም በተወዳጁ ኢቲቪ አማካኝነት እያንዳንዳችን ቤት ይመጣል። የአመቱን የጀግና አርሶ አደሮችን ስም ዝርዝር ሊነግረን። እንደ እውነቱ ከሆነ ታረቀኝ መልካም ሰው ነበር። በረከትም ይህንን አውቆ ከኢህአዴግ ቢሮ ውጭ ግንኙነት አውጥቶ ጫጫታ የሌለበትና በኢህአዴግ ፍቅር ወደ ተለከፈው አርሶአደር እንዲጠጋጋ አድርጐታል።

***

የታፈሱ እንባ...

ወረዳ 20 ቀበሌ 46 አዳራሽ ስደርስ መድረኩን እንዲመራ ሀላፊነት ተሰጥቶት የነበረው አዲሱ የቂርቆስ ክንቲባ አተይ በቦታው የለም። ከሁሉም መድረኮች ቀድሞ የሚበተነው የእሱ እንደሚሆን አስቀድሜ መገመቴ ትክክል ነበር። አተይ ቃላቶችን አሳክቶ ለ5 ደቂቃ በተከታታይ መናገር አይችልም። የአማርኛ እጥረት ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ የብቃት ማነስ ችግር አለበት። ክንቲባ የሆነው የሽማግሌው ስብሀት ነጋ የስጋ ዘመድ ስለሆነ ነበር። በትምህርት ዝግጅቱም ብዙ ይታማል። ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ገብቶ ዲግሪውን የወሰደው ከስምንተኛ ክፍል እንደሆነ የኮልፌው ነጋ በርሄ በአደባባይ ነግሮናል። ፍስሀ መአሲ እውነት መሆኑን አረጋግጦልኛል።

ነጋ የነገረን በዚህ መልኩ ነበር...

በአዲሳባ ማዘጋጃ ቤት የምክር ቤት አዳራሽ የስራ አስፈጻሚ ድልድል የተነገረን እለት ነጋ ከንቲባነት ለእኔ ነው የሚገባው ብሎ አርከበን ይከራከራል። የህውሀት ካድሬዎች በስልጣን ጉዳይ ላይ ይሉንታና እፍረት አያውቁም። አይናቸውን በጨው አጥበው ይሟገታሉ።

በነጋ ክርክር የተበሳጨው አርከበ፣

"ነጋ መጀመሪያ ማትሪክ ተፈተን" ብሎ መልስ ይሰጠዋል።

በምላሹ የተናደደው ነጋ፣

"አእምሮአችን አልፈቅድ ብሎ አንጂ እንደ አተይ በሚኒስትሪ ካርድ ኮሌጅ መግባት የሚከለክለን አንዳችም ሀይል አልነበረም" ብሎ መልስ ይሰጣል። አተይ በዲግሪ ሳይወሰን ሀንድ አገር ሄዶ ማስተርሱን ይዞ መጥቷል። መቼም አተይን ዲግሪ አሸክሞ የላከው የሀንድ ዩንቨርስቲ የሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ የጡት አባት መሆን አለበት።

ስለ አተይ እያሰላሰልኩ ወረዳ 20 ቀበሌ 46 አዳራሽ ደረስኩ። ሰራተኛው ከአዳራሽ ወጥቶ ፊት ለፊት ባለው የእግር ኳስ ሜዳ ላይ ቡድን ሰርተው ተሰብስበዋል። በዋናው መንገድ ጠርዝ በኩል ከ50 የማያንሱ እናቶች ነጠላቸውን አዘቅዝቀው ደረታቸውን ይደልቃሉ። ስም የተለጠፈበት ግርግዳ አጠገብ ወጣቶች "እንኳን ደስ አለህ" በመባባል ይተቃቀፉሉ...አልቃሽና ዘፋኝ!

ከ30 በላይ የቀበሌ ነባር ካድሬዎች ከአዳራሹ በር አጠገብ ፈዘው ቆመዋል። የካድሬዎቹ ተራ ገና አልደረሰም። ሰለሞን የሚባል ቀልደኛ ካድሬ "አለ ገና! አለ ገና! የካድሬውም አለ ገና!" እያለ ይጨፍራል።

ማንንም መቀላቀል አልፈለኩም። የመጣሁበትን መኪና ተደግፌ በትምህርት ዝግጅታቸው ማነስ ምክንያት ሰለተባረሩት እናቶች ማሰብ ጀመርኩ። ይህን ተከትሎ ስለሚከሰተው ከተማ አቀፍ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ አሳሰበኝ። በአንድ ወቅት ኃይለልኡል የሚባል የአስተዳደሩ ማህበራዊ ጉዳዮች ከፍተኛ ሙያተኛ በመንግስት ሰራተኛ እናቶች ላይ ያደረገውን ጥናት ሲያቀርብ በአውደ ጥናቱ ተሳትፌ ነበር። ከጥናቱ ውጤቶች አንዱ ከ20% በላይ የሚሆኑት የመንግስት ሰራተኛ ሴቶች እማወራ (single mam) ናቸው። እነዚህ እናቶች በአማካይ ሁለት ልጆች ያሳድጋሉ። እንግዲህ! የአርከበ ግልብጥብጡሽ ቆርኪው ሲላጥ እነዚህን እናቶችና ህፃናት ወደ ጎዳና ለመስደድ የተዘጋጀ ነበር።

የቀበሌ 46 ካድሬዋ ዮርዳኖስ አጠገቤ መጥታ ቆመች። ከማልቀሷ ብዛት አይኗ ቀልቷል። አፍታም ሳትቆይ ሲቃ እየተናነቃት፣ "ወይኔ ጉዴ ከማን ጋር ልኖር ነው? ይሄ ሁሉ ቤት እንዴት በአንድ ቀን ይፈርሳል?" በማለት ሯሷን እየጠየቀች ተነፋረቀች። መልስ አልሰጠኋትም።

አፍታም ሳይቆይ ታፈሱ የምትባል ጠቆር ያለች ሴት ደረታቸውን ገልብጠው ከሚያለቅሱት መሀከል እየሮጠች መጥታ እግሬ ላይ ተደፉች። በቁራ በሚገኘው ቀበሌ በተላለኪነት የምትሰራ የኢህአዴግ አባል ናት። የወረዳው ድፍን ህዝብ ኢህአዴግ ኢህአዴግ ስለምትሸት በደንብ ያውቃታል። የኢህአዴግ ሴቶች ክንፍ፣የአዲሳአባ ሴቶች ማህበር፣ እና ሴቶች ፎረም ውስጥ በአመራርነት ተሳትፋለች። የወረዳው ግንቦት 20፣ የካቲት 11 መታሰቢያ በአላት ያለ ታፈሱ አይደምቅም። ለዞን ሁለት የካድሬዎች አለቃ የነበረው ታጋይ ገብረእግዚአብሄር "እግዜሩ" ዋነኛ ጀሮ ነበረች። እንደ ጅብ በለሊት እየመጣች የቀበሌ ካድሬዎችን የምታስወጋ። ታፈሱ በዚህ ብቻ ሳትወሰን ለወረዳው ሴቶች በአብዮታዊ ዲሞክራሲ መስመሮች ላይ ስልጠና ትሰጣለች፣ በስልጠናው የጠራ አመለካከት የያዙ ቢጤዎቿን ለፓርቲ አባልነት ትመለምላለች። እድሜ ለዘመነ ደርግ መሰረተ ትምህርት ተምራለች። ምንም እንኳን ማንበብና መጻፍ ቢችግራትም።

ታፈሱ ስሜን እየጠራች፣

"ልጆቼን ተረከበኝ! ልጆቼን ተረከበኝ! አብዮታዊ ዲሞክራሲ ይፉረደኝ!" እያለች ጮኸች። ሁለቱን ልጆቿን አውታቸዋለሁ። ብቻዋን እንዳሳደገቻቸው አጫውታኛለች። ቀስ በቀስ ሌሎቹም እናቶች ከበቡኝ።

አይናቸው ሊውጠኝ ደረሰ። የመንፈስ ብርታት አነሰኝ። አጥንቴን የሚበረቡር መሪር ሀዘን ዋጠኝ። ከዮርዳኖስ የቢሮዋን ቁልፍ ተቀበልኳት። የቢሮውን በር ዘግቼ ለረጅም ሰአት ብቻዬን ተቀመጥኩ። ጉልበትና ሞራሌ ደቀቀ።

"ጨነቀን ያየ በፊደል አይቀልድም!"

ሚያዝያ 1995 ዓ. ም

የአዲሳባ ማዘጋጃ ቤት በአስቸኳይ ስብሰባ በመጡ ከአንድ ሺህ በላይ ካድሬዎች ተጨናንቋል። ካድሬዎቹ የክፍለ ከተማና ቀበሌ ናቸው። ስብሰባውን የሚመሩት አርከበና ህላዌ ሲሆኑ አስቀድመው ወደ መድረክ ወጥተዋል። ሰዓቱ ሲደርስ አርከበ ጉሮሮውን ስሎ የተሰበሰብንበትን ምክንያት መግለጽ ጀመረ። የከተማው ነዋሪ በአገልግሎት አሰጣጣቸን ላይ ላይ ምሬት እያሰማ እንደሆነ፣ ምክንያቱ ደግሞ ብዙዎች ትምህርት ቤት መሄድ በመጀመራቸው መሆኑ አስረዳ።

ቀጣዩን ሳይናገር ቤቱ በተቃውሞ አጉተመተመ። አጠገቤ የተቀመጠው ሺሰማ (በወቅቱ በኮልፌ የአንዲት ቀበሌ የካድሬዎች አለቃ ነበር፣ በአሁን ሰአት የአዲሳባ ካቢኔ አባል ነው) ወደ ጆሮዬ ጠጋ ብሎ ፣" ይሄ ሰውዬ አሁንስ ይበልጥ ግራ ተጋብቷል። ትላንትና ሰው የሀገሪቱ እምብርት ላይ ተቀምጦ እንዴት መሀይም ይሆናል ባለ አንደበቱ ለምን ትምህርት ቤት ሄዳችሁ ይለናል?" ብሎ ጠየቀኝ።

አርከበ ንግግሩን አቋርጦ ካድሬው ለምን እንዳጉተመተመ ጠየቀ። ከብዙ ፀጥታ በኃላ አንድ ካድሬ ከጫፍ አካባቢ እጁን አወጣ። ማይክራፎን ተሰጠው፣

"ጨነቀን ያየ በፊደል አይቀልድም!!" የሚል መፈክር ጮክ ብሎ በማሰማት ተቀመጠ።

አዳራሹ በሳቅ ተናወጠ። ቀጥሎ ሞቅ ያለ ጭብጨባ።

አርከበ ካድሬው የተናገረው እንዳልገባውና እንዲደግምለት አሳሰበው።

"ጨነቀን ያየ በፊደል አይቀልድም !!" ደገመለት።

አርከበ እኔና በጣም ጥቂቶች አልገባንም። አጠገቤ የተቀመጠው ሺሰማ በሳቅ ይንተከተካል። ጨነቀ የሚባለው ታታሪ ካድሬ እሱ በተመደበበት ወረዳ

ሲሰራ እንደነበር ስለማውቅ ምን እንደሆነ ጠየኩት። ምንም አለመስማቴ ገርሞት በዝርዝር አጫወተኝ።

የሺሠማ ጨዋታ እንደሚከተለው ነበር።

አርከበ ሲቪል ሰርቪሱን እያገላበጠ ጐን ለጐን ዘመቻውን በነባሩ ካድሬና አባላት ላይ ሆነ። ለዚህ ደግሞ የአባይ ፀሀዬ፣ " የከተማው የድርጅት ማሽን ጥሬ ከቶ ጥሬ የሚያወጣ " ብሎ የገለፀውና አቶ መለስ፣ " ይህንን ጌቶ (getto) መዋቅር ከህዝብ ጫንቃ ላይ አውርደን ፊደል የቆጠረ ሰው ከተማውን መምራት ይኖርበታል " የሚለው አባባል ለአርከበ ጅምላ ጠረጋ ጠቅሞት ነበር።

የአቶ መለስም ሆነ አባይ ንግግር ትክክል ነበር። የአዲሳባ ኢህአዴግ መዋቅር እንኳን የመሪነት ሚና ሊጫወት ቀርቶ ለህዝብ ጭራነት ብቁ አልነበረም። ካድሬውና አባላቱ በተግባር ኢህአዴግ አልነበሩም። ዘባተሎውን አሊ አብዶ ጨምሮ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ምንነትና ግብ ምን እንደሆነ የማያውቁ ነበሩ። አቶ መለስ ይሄንን ክፍተት በማየት ነበር የተማረ ሰው ፈልጉ ያለው።

በዚህ ምክንያት ለነባሩ ካድሬ በስራ መቀጠልና መባረር ትልቁ መመዘኛ የትምህርት ደረጃ ሆኖ ብቅ አለ። ቀድሞ የነበሩት የመገምገሚያ ነጥቦች (አብዮታዊነት፣ የአላማ ጽናት፣ ወገንተኝነት፣ ህዝባዊነት...) ገደል ገቡ። መዋቅሩ ተደናገጠ። የለመደው ስለቀረበት።

ከግምገማው በኋላ የነበረው የምደባ ሂደት የጨነቀን ስም በማይረሳ መልኩ እንዲተከል አደረገ።

ጨነቀ ካድሬ ነበር። መርካቶ ውስጥ በሚገኝ ወረዳ ለረጅም ጊዜ የአስተዳደር ዘርፍ ሀላፊ ሆኖ ያገለገለ። ጨነቀ በአብዮታዊነቱ፣ በታማኝነቱና የአላማ ጽናቱ ተወዳዳሪ አልነበረውም። አቅም በመገንባትም የሚስተካከለው የለም። የመንግስት ሰራተኞችን፣ መምህራንን ሰብስቦ ስለ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ስልጠና ይሰጣል። የአገሪቷን የልማት አቅጣጫ በየመድረኩ ያብራራል። መካከለኛ ገቢ ያላቸው የአውሮፓ ሀገሮችን እያጣቀሰ በ20 አመት አዲሲቷ ሀገራችን እንደምትደርስባቸው ትንተና ይሰጣል። ኢትዮጵያ አጋጥሞት የነበረውን መስቀለኛ መንገድ፣ አንቀጽ 39 የአንድነታችን መሰረት እንደሆነ ፣ የልማትና ዲሞክራሲ ጥያቄ ተነጣጥለው የማይታዩና የህልውና ጥያቄ እንደሆኑ ሳይታክት ባገኘው አጋጣሚ ያስተምራል።

ጨነቀ ትጉህ ነበር...

ለውስጥ ለውስጥ መንገድ በእሱ ወረዳ በአመቱ ውስጥ አንድ ሚሊዮን

ብር ከህዝብ መዋጣት አለበት ተብሎ እቅድ ይላክለታል። በአመቱ መጨረሻ ከራሱ ቤትና ቤተሰብ ጀምሮ የእያንዳንዱን በር አንኳኩቶ ሁለት ሚሊዮን ብር ሰብስቦ ገቢ ያደርጋል። ታዲያ ይህንን ብር ለማሰባሰብ የማይቆፍረው ጉድጓድ የለም። የአካባቢው ነዋሪዎች በራቸው ያለማቋረጥ ከተንኳኳ ፣" ጨነቀ ነው መሰለኝ!! የተጣለብንን መዋጮ ከከፈልን ወር ሞላ እንዴ ? በሉ በር እንዳትከፍቱ" እስኪባል ድረስ እግሩ እስኪነቃ ይመላለሳል። ህገ ወጥ ንግድ መርካቶን አስቸገረ ከተባለ ጨነቀ ይላካል። ድምጥማጡን አጥፍቶ ይመለሳል። ... ለኢህአዴግ ማጠናከሪያ ሩብ ሚሊዮን ሰብስብ ተብሎ ኮታ ከተጣለበት ግማሽ ሚሊዮን ሰብስቦ የሌሎቹን ይሸፍናል።

ጨነቀ ጀግና ነበር...

ወንጀለኞችን፣ጉልበተኞችንና ሴሰኞችን ልክ በማስገባት ተወዳዳሪ አልነበረውም። በአንድ ወቅት በትምህርት ቤቶች ዙሪያ " ሹገር ዳዲ" የሚባሉ አዛውንቶች ላይ የተቀናጀ ዘመቻ ተጀመሮ ነበር። ታዲያ በፈጠራ ማንም የማይደርስበት ጨነቀ አድብቶ በመጠበቅ አንዱን የሸማግሌ ቀላል እጅ ከፍንጅ አልቤርጌ ውስጥ ይይዘዋል። እናም " እኔ ሹገር ዳዲ ነኝ። እኔን ያየ ይቀጣ! " የሚል ወረቀት ለጥፎበት በወረዳው ፒካፕ ላይ አስጭኖ አዞረው። ሹገር ዳዲዎች ለጊዜው ደብዛቸው ጠፋ።

ጨነቀ ጨዋ ነበር...

መህል መርካቶ እያስተዳደረና አማላይ ጉቦዎች እየተላኩለት ሰጪውን እየተከታተለ የሚቀጣ። ልጆቹን ሸራ ጫማ አልብሶ ትምህርት ቤት የሚልክ። ሚስቱ የቋጠረችለትን ሽሮ በቧንቧ ውሀ አያወራረደ የሚሰለቅጥ ምስኪን።

ጨነቀ አብዮታዊ ነበር...

የትምህርት ሰርተፍኬትን እንደ መመዘኛ ይዞ ብቅ ያለው የአርከበ አዲሱ ምደባ ጨነቀን የመጀመሪያ ተጠቂ አደረገው። የቀለም ትምህርትን ከ8ኛ ክፍል አልዘለለም። በግምገማ ወቅት ለምን አልተማርክም ተብሎ ተጠየቀ። ጨነቀ ጠንካራ አብዮታዊ መከራከሪያ ከተጠያቂነት ጋር አያይዞ አቀረበ። እንዲህ በማለት፣

"ያዘናጋኝ የድርጅታችን ሊቀመንበር አቶ መለስ ዜናዊ ነው። በፓርላማ ቀርቦ ለኢህአዴግ ካድሬነት መመዘኛችን የትምህር ደረጃ አይደለም። አብዮታዊ መሆን በቂ ነው ብሎ ተናገረ። እኔም ልማር ያሰብኩትን እሱን በማመን እርግፍ አድርጌ ትቼ አብዮታዊነቴን ስጠብቅ ኖርኩኝ።"

ጨነቀ እውነትም ወደ ላይ የሚታገል አብዮታዊ ነበር። በግለሰብ ደረጃ ቱባ ካድሬዎችን እየጠራ የሚሞግት፣

"*እነ ህላዌ፣ አባዱላ፣ የዘናቸን ሊ/መንበር ሉልሰገድ ይፍሩ*

መቼ ሰርተፍኬት አላቸው? ...ተፈራ ዋልዋ የተግባረድ ዲፕሎማ አይደል የያዘው? ...አርከበ ከመቀሌ ይዞአቸው የመጡት እነ ነጋ በርሄ፣ ግርማ ዲዮን፣ሀይለስላሴ ዘጠነኛ ሲደመር ጭጭ እንደሆኑ ሰምቻለሁ" በማለት ተከራከረ።

ጨነቀ ህውሀት አልነበረም...

የጨነቀ አብዮታዊ መከራከሪያ ነጥቦች አልጠቀሙትም። ከካድሬ ምደባ ውጭ ሆነ። ምንም አይነት አማራጭ ሲጠፉ ወደ ቢሮክራሲው መዋቅር እንዲመደብ ስሙ ተላለፈ። እዛም ቢሆን መደብ አልተገኘለትም።በአቶ መለስ ቀጭን ትእዛዝ አዲስ የተፈጠረው የደንብ ማስከበር መደብ እንኳን ትንሹ መመዘኛ አሱ ካለው ደረጃ ከፍ ይላል። ይህም ሆኖ የካድሬነት ዘመኑ እንደ አገልግሎት ተቆጥሮለት ደንብ ማስከበር ተመደበ። ቆመጥ ተሰጥቶት ሰልባጅ ነጋዴንና ሱቅ በደረቴን ማባረር ቁልፍ ስራው ሆነ።

ጨነቀ ከፍተኛ የሞራል ውድቀት ደረሰበት። ራሱን ከማህበራዊ ተሳትፎዎች ሳይቀር አገለለ። ጨነቀን ...ጨነቀው። የቢሮክራሲውን፣ የመምህራንና የነዋሪውን አይን ፈራ። በቀናቶች ውስጥ ጠላና አረቄ ውስጥ ተደብቆ ተገኘ።

በሌላ በኩል ጨነቀና እሱን መሰል ካድሬዎች የተቀጠሩን አይቀጡ ቅጣት ያየ የከተማው ካድሬ "ዘመቻ - ጨነቀ" አውጀ ወደ አስኳላ ተመመ። የካድሬው ወሬ በሙሉ ትምህርት ሆነ። ይህንን ተከትሎ የመንግስት ጽ/ቤቶች ከቀኑ ዘጠኝ ሰአት መዘጋት ጀመሩ። አገልግሎት ፈልጌ የሚመጣው ነዋሪ ሀላፊዎች ባለመኖራቸው በንጋታው እንዲመለሱ መነገር ተጀመረ። ህዝቡ አርከበ በሚዲያ የሚያወራውና መሬት ላይ ያለው ነገር ተለያየበት።

እንግዲህ በማዘጋጃ ቤት የተጠራው ስብሰባ ይህን የህዝቡን ቅሬታ ለማስተንፈስ ያለመ ነበር። "ጨነቀን ያየ በፊደል አይቀልድም!!" የምትለዋ መፈክር የተነሳቸው በዚህ ሁኔታ ነበር። በስብሰባው ማጠቃለያ አርከበ ማስጠንቀቂያ ሰጠ። እንዲህ በማለት፣ "እማራለሁ የሚል ከዛሬ ጀምሮ ከካድሬነት ተሰናብቷል። መንገዱን ጨርቅ ያድርግለት።"

እንደ አውነቱ ከሆነ የውሳኔው አፈጻጸም የኢህአዴግ ልጅና የእንጀራ ልጅ ማን እንደሆነ አጋልጧል። የእንጀራ ልጆቹ ሊመረቁ አንድ ሴሚስተር እየቀራቸው ትምህርታቸውን አቋረጡ። መጨረስ አለብን ያሉ ከስራ ተባረሩ። ብዙ ካድሬዎችን በማባረር ሪከርድ የሰበሩት የላፍቶ ክፍለ ከተማ ከንቲባው ሀይሌ ፍስሀና የአዲስ ከተማው ሉልሰገድ ይፍሩ ነበሩ። ሉልሰገድ የተማረ

የማይወድና ትምህርት አለርጂክ የሆነበት ነባር ካድሬ ነው።

ሀይሌ ፍስሀ ሌላውን ፎርም አስሞልቶ እያባረረ ለራሱ ግን ሁለት ማስተርስ ይሰራ ነበር። አንደኛውን በአራት ኪሎ ዩንቨርስቲ ጂኦሎጂ ዲፓርትመንት የሙሉ ጊዜ ተማሪ በመሆን፣ ሌላኛውን ከእኛ ጋር በሊደርሺፕ። ሀይሌ ሲያጠና እንኳን ሁለት እግሩን የቢሮው ጠረጴዛ ላይ ሰቅሎ ነበር። እንደ ሀይሌ ሁሉ ለሌሎቹ የህውሀት ካድሬዎች የፈቀዱትን መማር ይችሉ ነበር። የኮልፌና የካ ከንቲባ የነበሩት ነጋ በርሄና ግርማጺዮን ለተራዘመ ወራት መቀሌ በመሄድ እየተማሩ ይመጡ ነበር። የአራዳ ድርጅት ሀላፊ የነበረው ሀይላይ ሲቪል ሰርቪስ የቀን ገቡቶ አየተማረ በሳምንት ሁለት ቀን ይሰራ ነበር።

ከዚህ በተቃራኒ ከአርከበና ከትምህርት ጠሎች ከሆኑ ካድሬዎች የሚደርስባቸውን ጫና በመቋቋም ከስራቸው ያለው ካድሬ የጀመረውን እንዲያጠናቅቅ ያገዙ ነበሩ። መማር የዜግነት መብት ቢሆንም ካድሬው መማር አለበት ብለው አቋም የወሰዱ የበላይ ሀላፊዎች ምስጋና የሚገባቸው ናቸው... በተለይም የአቃቂ ከንቲባ የነበረው ተክለፃዲቅ፣ የጉለሌው ኤቢሳ፣ የኮልፌው አባተ ስጦታው ለአርከበ ሪፓርት ሳያደርጉ ካድሬዎቹ እንዲማሩ ሽፋን ሰጥተዋል። ዛሬ በአዲሳባ አስተዳደር ካቢኔ ውስጥ የምናገኛቸው እነ ሺሰማ፣ ኢንተርናሽናል አልቢትር ተስፉዬ አሜጋ በሚስጥር እንዲማሩ ስለተደረገ ነው።

ክፍል አምስት: የምርጫ 97 ክስተቶች

ምእራፍ አስራ አራት

ለምን እናሸንፋለን?

"ኢህአዴግ ከፍተኛ የአርሶ አደር ፍቅርና ድጋፍ ያተረፈ ድርጅት ነው!"
በረከት ስምኦን (ሁለት ምርጫዎች ወግ)

ኢህአዴግ በምርጫ 97 አሸናፊ ሆኖ የሚወጣባቸው ምክንያቶች በዝርዝር የቀረቡት በመላ ሀገሪቱ የሚገኙ የድርጅቱ ካድሬዎችና አባላት በስነ ምግባር መመሪያው ላይ በጥላዝም ሁለትዮሽ ኮንፍረንስ በተካሄደ ወቅት ነበር። የፌደራልና አዲሳአባ ካድሬዎች በማዘጋጃ ቤት አዳራሽ፣ የክልል ካድሬዎች ደግሞ በተዘጋጁላቸው ማእከል በመሰብሰብ በኮንፍረንሱ ተሳትፈዋል። በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት በመሆን ስልጠናውን የሰጠው በረከት ስምኦን ነበር። የበረከት አቀራረብ ፍፁም መኩራራት የታየበት ሲሆን በተደጋጋሚ፣

"ወደ ምርጫ እየገባን ያለነው ምቹ የፓለቲካ ሁኔታ ፈጥረን ስለሆነ ያለ ፀረ-ዲሞክራሲ እርምጃ በዝረራ እናሸንፋለን። በግለሰብ ሆነ በቡድን ደረጃ ለሚፈፀም ፀረ-ዲሞክራሲ ኢህአዴግ ሀላፊነት አይወስድም። አስቀድሞም ለህግ የሚያቀርባችሁ ኢህአዴግ ነው።" የሚል ማስፈራሪያ ይጠቀም ነበር። በረከት ምርጫ 97 በሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ መንገድ የምናሸንፍባቸው በማለት በርካታ ምክንያቶች አቅርቧል። ከእነዚህ ውስጥ ጐላ ብለው የሚጠቀሱት እንደሚከተለው ቀርበዋል።

***

"በተግባር የተፈተሹ ፓሊሲዎች ባለቤት ስለሆንን"

ኢህአዴግ የሚያሸንፍበት የመጀመሪያ ምክንያት ተደርጐ የተወሰደው "የህዝቦችን የላቀ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥና በተግባር የተፈተሸ የጠራ ፓሊሲዎች ባለቤት ነን" የሚለው ነበር። ተቀርፀው ተግባራዊ በሆኑት ፓሊሲዎች ምክንያት በ1995 እና 1996 አመተ ምህረት ፈጣን እድገት አስመዝግበናል። በሁለቱም አመታት የተመዘገበው አገራዊ የኢኮኖሚ እድገት ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ባለ ሁለት አህዝ በመሆን አንፀባራቂ ድል ተደርጐ በህበረተሰቡ ታይቷል የሚል ነበር። በመሆኑም ምርጫ 97 የምናስተናግደው ተከታታይ ከፍተኛ ልማት ባመጣንበትና ለእምርታ እየተጋን ባለንበት ሁኔታ

ስለሆነ አንዳችም የሚያሰጋ ሁኔታ አይኖረም ተባለ። በተለይ የገጠሩ ህዝቡ የተጀመረው ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ሳይስተጓጐል እንዲቀጥል ስለሚፈልግ ድምፁን ይሰጠናል የሚል ድምዳሜ ተያዘ።

እንኪን የለሽ ምርጫ አድርገን የምናሸንፍበት ምክንያት ፈጣን የኢኮኖሚ ልማት ስላመጣን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም በየደረጃው ተጠቃሚ ማድረግ ስለቻልን እንደሆነ ሰፊ ማብራሪያ በበረከት ስምኦን አማካኝነት ተሰጠ። በረከት ስልጠናውን ሲሰጥ በልበ ሙሉነት ውስጥ ሆኖ፣

"የሀገራችን ፈጠን እድገትና የህዝቦች ተጠቃሚነት ህዝቡ ነጋሪ ሳያስፈልገው እየመሰከረ ነው። በ1993 የተለኮሰው ተሀድሶ ጨለማውን ገፎ በሁሉም አቅጣጫ ብርሀን ማፈንጠቅ ጀምሯል። ድርጅታችን በተሀድሶው ምክንያት ለተፋጠነ ለውጥ መሰረት የሚሆኑ የፓሊሲና ስትራቴጂ ማእቀፎችን አዘጋጅቶ ተጨባጭ ለውጥ እያመጣ ነው። ህዝቡ የኢህአዴግ አመራር በቁርጠኝነት ሀገሩን ለመለወጥ ቀን ከሌት እየፈጋ እንደሆነ ተገንዝቧል። ይልቁንስ ፍራቻው በዚህ ምርጫ ምክንያት ኢህአዴግ እንዳይዘናጋና ተስፋ ያደረጋቸው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ለውጦች እንዳይደናቀፉ ነው። እንደዚህ አይነት ምቹ ፓለቲካዊ ሁኔታ ይዘን እንኪን የለሽ ምርጫ ያላካሄድን መቼ ልናካሂድ ነው?" በማለት በምርጫው ኢህአዴግ እንደሚያሸንፍ በእርግጠኝነት ተናግሯል።

***

"ተቃዋሚዎች ለዲሞክራሲ ግንባታችን አስተዋጽኦ አላቸው"

ከ1993 ዓ.ም በኃላ በኢህአዴግ ከፍተኛ ካድሬዎች ተነስቶ አከራካሪ የነበረው "ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለዲሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ አስተዋጽኦ አላቸው/የላቸውም?" የሚለው ነበር። ይህ ክርክር የመጨረሻውን ድምዳሜ ባይለውጠውም ኢህአዴግ የስልት ለውጥ አድርጓል። ይህም ተቃዋሚዎች በተዘዋዋሪ መንገድ ለዲሞክራሲ ግንባታ አስተዋጽኦ አላቸው በማለት። በተዘዋዋሪ መንገድ ማለት ሀሳባቸውን በመግለፃቸው ምክንያት ፀረ - ህዝብና የጥፋት ሀይሎች መሆናቸው ይጋለጣል የሚል ነበር። በዚህ ምክንያት የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ትክክለኛነት ይረጋገጣል የሚል ማሳመኛ ቀረበ። ከዚህ በተቃራኒው የመታፈን እድል ካጋጠማቸው ግን የአብዮታዊ ዲሞክራሲ የተሻለ አማራጭነት አብሮ ይታፈናል፣ ተቃዋሚዎችንም እርቃናቸውን ማስቀረት አይቻልም፣ የተተነተነ የፓሊሲ አማራጭ እንደሌላቸው ህዝቡ መገንዘብ እንደማይችል ተገለፀ። ይህ ሳይሆን ቀርቶ የመታፈን እድል ካጋጠማቸውና አመለካከታቸው ወደ አደባባይ ካልወጣ አብዮታዊ ዲሞክራሲ የአስተሳሰብ ልእልናውን ማረጋገጥ ስለማይቻል የተቃዋሚ አስተሳሰብ ውስጥ ውስጡን የመፋፋት እድል ያገኛል የሚል ነበር።

ይህን ሀሳብ ለማጠናከር በኢህአዴግ ቢሮ ሁለት ሰነዶች ተዘጋጅተው ካድሬው እንዲሰለጥንበት ተደረገ። የመጀመሪያው ሰነድ "የህዝብ ግንኙነት መርሆዎች" በሚል ርእስ የተዘጋጀ ሲሆን ስለ ህዝብ ግንኙነት ምንነት፣ ብሄራዊ መግባባት፣ የኢህአዴግ የህዝብ ግንኙነት አላማና ግቦች፣ የዲሞክራሲና አስተምህሮ ተቋማት፣ ፓለቲካ ፓርቲዎች... ወዘተ የሚያነሳ ነበር። ሁለተኛው ሰነድ "በነፃነት ያልተገለፀ ማንኛውም ሀሳብ አይታወቅም፣ ያልታወቀ ደግሞ አይሸነፍም!" የሚል ይዘት ያለው ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ በኢህአዴግ የካድሬነት ዘመኔ ብቻ ሳይሆን ዛሬም ድረስ የምወደውና ከህሊናዬ ያልጠፉ ዶክመንት ነው። ህላዌ የሴፍ ሀገር ጥዬ እስከወጣሁ ድረስ በሰኔ ጐሎጐታ መልኩ አሳትሚት በደረቱ ይዟት ይዞር ነበር። እናም ከኪሱ አውጥቶ ተግባራዊነቷን ቢፈትሽ ግልጽ ምላሾች ያገኝ ነበር። የእኔም የዘወትር ጥያቄ ይህ ነው። በነፃነትና ያለፍራቻ ማንኛውም ሀሳብ (የሴጣንም ቢሆን) እንዲገለፅ ማበረታታት አለብን፣ በነፃነት ያልተገለፀ ሀሳብ አይታወቅም ብሎ የጻፈ እጅ የፐሬስ ህጉን እንዴት ሊጽፍ ቻለ?

በአጠቃላይ መልኩ በምርጫ 97 ኢህአዴግ በሩን በልበ ሙሉነት ገርበብ አድርጐ የከፈተበት አንዱ ምክንያት ተቃዋሚዎች በተዘዋዋሪ መንገድ ለዲሞክራሲ ግንባታችን አስተዋጽኦ አላቸው ከሚል ነበር።በረከት ስምኦን በከንፍረንሱ ላይ፣

"ተቃዋሚዎች የያዙትን ሀገር የሚያጠፉ ሀሳብ በነፀነት እንዲገልጹ እናድርግ። ይህን ተከትሎ ህዝቡ አይቀጡ ቅጣት በመቅጣት የአብዮታዊ ዲሞክራሲን ትክክለኛነት ያፀናል። ይህም ኢህአዴግ ለሀገ መንግስቱ ያለውን ታማኝነት፣ የሚመራባቸው የልማትና ዲሞክራሲ አማራጮች ትክክለኛነት፣ የማስፈፀም አቅሙና ያለው የህብረተሰብ ተቀባይነት ላይ መተማመን ይደረሳል "በማለት ማብራሪያ ሰጥቶ ነበር።

***

"የተቃዋሚው ጐራ እርስ በራስ መበላላት ጀምሯል።"

ኢህአዴግ ምርጫ 97 እንከን የለሽ እንዲሆን የወሰነበት ሌላኛው ምክንያት የተቃዋሚው ጐራ ይበልጥ እየተዳከመ ሄዷል፣ እርስ በራሱም መበላላት ጀምሯል ከሚል መነሻ ነበር። ተቃዋሚዎች ያላቸው ግንኙነት በጥርጣሬ፣ በመናናቅና አንዱ ከሌላው አሻላለሁ የሚለውን ለማሳየት ቀን ከሌት የሚባዝኑ እንደሆነ ተገለፀ።

በረከት የስነምግባር መመሪያውን ሰልጠና ሲሰጥ፣

"የኢህአዴግ ተቃዋሚዎች የተቃኙት በዜሮ ድምር ጨዋታ ሰለሆነ ዋነኛ መገለጫቸው መጠፋፋት እና የስልጣን ሽኩቻ ነው። በአሜሪካን ሀገር ሲዶልት

የከረመው ህብረት ፍርክስክሱ ወጥቷል። በየነ ጴጥሮስና እና መራራን ከመንደርተኝነት ያልወጡ በማለት እየከሰሷቸው ነው። የቀድሞ ስርአት ናፋቂው መኢአድ እና አደገኛ ቦዘኔዎችን ማህበራዊ መሰረቱ አድርጐ የሚወስደው የልደቱ ፓርቲ ጓዛቸውን ጠቅልለው ከህብረቱ ወጥተዋል። ሀገሪቷን መግለጫ በመግለጫ አድርገዋታል። ይህ የሚጠበቅ ነበር። ምክንያቱም የተቃዋሚ ፓርቲዎች አመሰራረትና እንወክለዋለን የሚሉት የህበረተሰብ ክፍል የተለያየና የማይታረቅ በመሆኑ" በማለት የተቃዋሚ ጐራ ያለበትን ሁኔታ አስረድቷል።

***

የአዲሳባ ትንሳኤ መበሰር...

የአዲሳባ የለውጥ ምክንያቶች በማስታወሻው የመጀመሪያው ክፍል ለመግለጽ ተሞክሯል።እነዚህም የአርከበን ቡድን ከትግራይ ማስወጣት፣ የአዲሳባ ህዝብ በምርጫ 92 የወሰደው እርምጃ አገራዊ አደጋን እያስከተለ መሄዱ፣ የምርጫ 97 ፍራቻ እና እነ ጋዳፊን በመሰሉ የአፍሪካ መሪዎች አዲሳባ እየደረሰባት ያለው ጫና ለመቀነስ እንደሆነ በማብራራት። እነዚህ ምክንያቶች በምንም መልኩ የኢህአዴግን "ከተማን በገጠር ስሌት መምራትና የነፍጠኛ ከተሞችን ማዳከም" የሚለውን እቅድ የቀየሩ እንዳልሆኑም ተመላክቷል። በተመሳሳይ የአዲሳባ ህዝብ ራሱን በራሱ የማስተዳደር ሉአላዊ መብቶችን ያጐናፀፉ አይደሉም። ተደጋግሞ እንደተገለፀው ምርጫ 97 ያሰጋው የፍራቻ ቻርተር ከ5 ሚሊዮን በላይ የሚሆነው ህዝብ የመረጠውን ምክርቤት ፓርላማው ፀጥታ ማስከበር አቅቶህል ብሎ የመበተን ስልጣን አለው።

በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱት መሰረታዊ የህዝብ መብቶች ሳይከበሩ አዲሳባን ለመቀየር መነሳት ከጊዜያዊ አደጋዎች ለመዳን ከማሰብ እንጂ ዘለቄታዊ ፉይዳ የሚያመጣ አይደሉም።

ግራም ነፈሰ ቀኝ አዲሳባ መለወጥ አለባት ! ምርጫ 97 አይኑን አፍጦ እየመጣ ነው!

ይህንን ገቢራዊ ለማድረግ የልማትና ፕሮፓጋንዳ ስራ ተቀናጅተው ሊፈፀሙበት የሚያስችል ስትራቴጂዎች ተቀየሱ። የልማት ስራው በረከት በመጽሐፉ እንደገለፀው ናዳን ለመግታት የሚካሄድ ሩጫ አይነት ሆነ። "ሁሉም ነገር ወደ አዲሳአባ" የሚል አዋጅ ታወጀ። በፕሮፓጋንዳው መስክ የጀርመናዊው የጐብልስ ትእዛዛት ማጠንጠኛ "The Big Lie theory" ተቀይሶ ተግባራዊ ሆነ።

አቶ መለስ በጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ የሀገሪቱን ዋነኛ የኢኮኖሚ ነክ ዘርፎችን ሰብስቦ፣ "ሁሉም ነገር ወደ አዲሳባ" ነጋሪት ጐሰመ። የሙገርና ሞሶቦ ሲምንቶ ፋብሪካ የመዲናይቱን ፍላጐት ሳያሟሉ ለሌላ መሸጥ እንደማይችሉ አስጠነቀቀ። የመንግስት የብረታ ብረት ፋብሪካዎች በልዩ ትእዛዝ ለአዲሳባ እንዲያቀርብ ተወሰነ። በአቶ መለስ ልዩ ትእዛዝ ከሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ከፊዴራል መንግስት በመመደብ ብረትና ሲምንቶ ከውጭ ሀገር እንዲገዛ

ተወሰነ። የግርድ ሂደት መንግስታዊ አሰራርን ሳይከተል ያለጨረታ የተከናወነ ነበር። በዚህም ምክንያት ህገመንግስቱና የህግ የበላይነት ተጣሰ። የመንገዶች ባለስልጣን፣ ቴሌና መብራት የጥምር ግብረሀይል እንዲያቋቁሙ ተደረገ። በተለይ መብራት ሀይል አዲሳባ ላይ ለሚቋቋሙ የጥቃቅንና አነስተኛ ማምረቻ ተቋማትና ሼዶች ልዩ ሪዘርቭ እንዲይዝና ለሚቀርቡ ጥያቄዎች በቀናት ውስጥ ምላሽ እንዲሰጥ ታዘዘ። አቶ መለስ ባዶ መሬቶች ተለይተው ለኮንደሚኒየምና የጥቃቅን ሼዶች ግንባታ እንዲውሉ፣ በፌደራል መንግስት ባለቤትነት የተያዙ ሰፋፊ መሬቶች ለአስተዳደሩ እንዲያስረክቡ አደረገ። ከዚህ አንፃር መከላከያ ሚኒስቴር እንዲለቅ የተደረገው የጐፋ ገብርኤል ካምፕ በአብነት ሊነሳ የሚችል ነው። የልማት ስራውን እንዲመራ የመንገዶች ባለስልጣን የበላይ ሀላፊውን የአዲሳባ ስራ አስኪያጅ አድርጐ መደበ። በዲዛየንና ምህንድስና ሙያዋ ምስጉን የሆነችውን ወይዘሪት ፀዳለ በምክትልነት ተሾመች። የአዲሳባ መንገዶች ባለስልጣን ለመምራት ከፌደራሉ መንገዶች ባለስልጣን ቀጥተኛ ዝውውር ተደረገ።

በመሆኑም የሚካሄዱት ግንባታዎች በመሰረቱ የህብረተሰብ መፈናቀል ሳያመጡ በባዶ ቦታዎች ላይ በመከናወናቸው፣ ለልማቱ ማስኬጃ ከፌደራል መንግስት የሚመደበው ገንዘብ የተትረፈረፈ በመሆኑ፣ ሁሉም ተቋማት በአቶ መለስ ማስጠንቀቂያ ቅድሚያ ለአዲሳባ በመስጠታቸውና በመቀናጀታቸው፣ ከፍተኛ ሙያተኞች ከፌደራል መንግስትና ከነባሩ መዋቅር በመመደባቸው ምክንያት በመዲናይቱ ታይቶ የማይታወቅ ለውጥ ሊመጣ ቻለ። ስለዚህም በአዲሳባ የተመዘገበው ልማት በአቶ መለስ መልካም ፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ፣ እንደ ሰጐን እንቁላል በተደረገ ክትትል ሲሆን ምንጩ ደግሞ መለወጥን ከአምነት የወሰደ ሳይሆን ምርጫ 97 የፈጠረው ፍራቻና መረበሽ ነበር።

በመሆኑም በኢህአዴግ ግንዛቤ ወደ ምርጫ 97 ሲገባ እንደ ማሸነፊያ ምክንያት የተወሰደው አዲሳባ የሚታይ ለውጥ አምጥታለች፣ የከተማዋን እድገት ህዝቡ መመስከር ጀምሯል፣ የስራ እድል ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ተፈጥሯል የሚል ነበር። ይህ በመሆኑ ለኢህአዴግ ማሸነፍ ምቹ ኢኮኖሚያዊና ፓለቲካዊ ምህዳር ተፈጥሯል የሚል ድምዳሜ ተይዞ ነበር።

***

ምእራፍ አስራ አምስት

የምርጫ 97 ዋዜማ

"ፕሮፌሰር መራራ በአይናችን ስር ቁጭ ባሉበት ወንበር
ወደታች ሲሰምጡ ተመለከትን።"
በረከት ስምኦን (የሁለት ምርጫዎች ወግ)

ከመስከረም በፊት ኢህአዴግ ምርጫ 97 እመራበታለሁ ብሎ ባወጣው እቅድም ሆነ የተቃዋሚዎች የሀይል አሰላለፍ ትንታኔ ላይ ቅንጅት የሚባል ፓርቲ አልነበረም። ቅንጅት ለኢህአዴግም ሆነ ለሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶች ብራ መብረቁ ነበር። በህብረተሰቡ ዘንድ ታዋቂ የሆኑት እነ ፕሮፌሰር መስፍን፣ ዶክተር ብርሀኑ፣ ዶክተር ያቆብ፣ ዶክተር በፍቃዱ ...ይሳተፉሉ ብሎ የገመተ አልነበረም። እንኳን እኛ አቶ መለስም ሆነ የደህንነቱ መስሪያ ቤት የሚያውቀው ነገር አልነበረም። ከዓመታት በኋላ ከበረከት እንዳረጋገጥኩት እነዚህ ምሁራን ለተቃዋሚዎች የኋላ ደጀን እንደሚሆኑ የተጠበቀ ቢሆንም በግላጭ የተቃዋሚ ፓርቲ ይመሰርታሉ፣ ሌላውንም ያቀናጃሉ የሚል ግምት አልነበረም።

የምሁራን ተሳትፎና እንድምታው...

ኢህአዴግን ከሚያስደነግጠው ነገር አንዱ ኢትዮጵያዊ አጀንዳ ያላቸው ታዋቂ ሰዎችንና ምሁራንን በተቃዋሚ ፓርቲ ውስጥ ሲያገኛቸው ነው። በተለያዩ ምክንያቶች።

የመጀመሪያው ኢህአዴግ በውስጠ ድርጅት መመሪያ ደረጃ ምሁራን እንዳይቀላቀሉት ገድቦ የተቀመጠ በመሆኑ ሌላው ፓርቲ በሩን በርግዶ ከተቀበላቸው የተሻለ የፓሊሲ አማራጮችን ስለሚያቀርቡ የኢህአዴግ "ተቃዋሚዎች አማራጭ ፓሊሲ የላቸውም" የሚለው ክስ ታሪካዊ ይሆናል። ከዚህም በተጨማሪ በታቀደ መልኩ በሀገሩ ጉዳይ ላይ ባይተዋር እንዲሆን የተደረገው የምሁሩ ክፍል የፓለቲካ መድረኩን መቀላቀል ይጀምራል። በሂደትም እንደታየው በተማረው የህብረተሰብ ዘንድ እንዲሰፍን ተደርጎ የነበረው የፍርሀት ደመና እየተገፈፈ መሄድ ጀመረ። "ፓለቲካን በሩቁ" የሚለውና "የሸፈን ጠባሳ ያየ በእሳት አይጫወትም" የሚሉት ኋላቀር ብሂሎች ታሪካዊ ሆኑ።

በሁለተኛ ደረጃ የኢትዮጵያ ህዝብ ለተማረ ሰው ያለው ከበሬታ አጅግ በጣም ትልቅ እንደሆነ ኢህአዴግ ይገነዘባል። ፕሮፌሰር መስፍንና የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ጉባኤን አቀናጅቶ የማይመለከት ኢትዮጵያዊ አይኖርም። ሰብአዊ መብት በተጣሰ ቁጥር ምነው ፕሮፌሰር መስፍን ዝም አሉ? እስኪባል ድረስ። ዶክተር በፍቃዱ ደግፌንና የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ማህበርን አስተሳስሮ የሚያየው ብዙ ነው። ዶክተሩ የሚያወጧቸው ጥናታዊ ጽሁፎች በጉጉት የሚነበቡ ናቸው። ዶክተር ብርሀኑ በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ውስጥ ሰፍኖ የነበረውን የጌታና ሎሌ ስርአት ከስሩ እንዲነቀል ባደረገው ፉና ወጊ ስራ በዩንቨርስቲው ያለፈ በሙሉ በቅቡበሎሽ ህግ መሰረት ለተራዘመ ጊዜ ይዘከረዋል። ከዩንቨርስቲ ተማሪዎች ጋር የቅርብ ግንኙነት ስለነበረኝ የሲምስተር ሪፓርቴ ነበር። በምርጫ 97 ለቅንጅት ምርጫ ታዛቢነት በብዛት የዩንቨርስቲ ተማሪዎች እንደነበሩ በምርጫው ያለፍን በሙሉ እናውቃለን። እነዚህ ተማሪዎች የምርጫው እለት ዳር ድንበር እንደሚጠብቅ ወታደር ንቁ ነበሩ። ይህ የሆነበት ምክንያት ከላይ የተጠቀሱት ሰዎች የነበራቸው ከበሬታ ምን ያህል ጥልቅ መሆኑን የሚያሳይ ነበር።

በሶስተኛ ደረጃ የኢህአዴግ ፍራቻ እነዚህ ምሁራን ከኢህአዴግ ካድሬዎች ጋር ለምርጫ ክርክር ቢቀርቡ በዝረራ እንደሚያሸንፉ የሚያጠራጥር አይደለም። ኢህአዴግ ለክርክር የሚያዘጋጃቸው ካድሬዎች በዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት የታሰሩ፣ የተጻፈውን ብቻ ማነብነብ የሚጠበቅባቸው፣ ከዛ ውጪ መናገር የማይችሉ ተመሳሳይ ፊት ያላቸው መሆኑ አይቀርም። በተቃራኒው በተቃዋሚ ወገን የሚቀርቡት ምሁራን አንባራዊ በሆነ መንገድ ለሚናገሩት ነገር የሂሳብ ስሌት የማይሰሩና ነፃነት ያላቸው ይሆናሉ። በኢትዮጵያ ምድር የሚያስፈራውን የተቃዋሚ ጐራ መቀላቀል መወሰናቸው በራሱ ልበሙሉነታቸውን ስለሚያረጋግጥ በነፃነት ማሰብና መናገራቸው የሚጠበቅ ነው። በተግባርም እንደታየው እነዚህ ምሁራን ወደ ምርጫ ክርክር መግባት ሲጀምሩ የኢህአዴግ አመራሮች ገመና መጋለጥ ጀመረ። ህዝቡ በግላጭ "በእነዚህ ነበር እንዴ ስንመራ የቆየነው?" የሚል ሀዘኔታ ውስጥ ገባ። ኢህአዴግ ይዞ የቀረባቸው ተከራካሪዎች በቂ መልስ መስጠት አቅቷቸው ወደ መሳደብና ማስፈራራት ሲገቡ ደግሞ የህዝቡ ንቀት እየጨመረ ሄደ። በመሆኑም የተካሄዱት የምርጫ ክርክሮች በወሳኝ መልኩ የምርጫውን ውጤት ወደ መወሰን ተሸጋገሩ።

በአራተኛ ደረጃ እነዚህ በቅንጅት ስር የተሰባሰቡ ምሁራን የሚያደርጉት የምርጫ ቅስቀሳና ክርክር ወትሮ ከተለመደው የኢህአዴግ ፓሊሲዎች በመፈፀም ሂደት የታዩ የአፈጻጸም ድክመቶችን በማሳየት ላይ ብቻ የተመረኮዙ

አልነበሩም። በመስከረም ወር በረከት ስምኦን የምርጫ ስነምግባሩን ሲያስለጥነን "ተቃዋሚዎች አማራጭ ሀሳብ እንደሌላቸው ህዝቡ ተገንዝቧል" በማለት በተደጋጋሚ ይገልጽ ነበር። የቅንጅት መፈጠር ይህን የበረከት ፉከራ አፈር ከድሜ ሲያስበላው ተንሸራቶ "ተቃዋሚዎች በደንብ የተዘረዘረና የተተነተነ አማራጭ የላቸውም" ማለት ጀመረ። እሱ ይሄን ይበል እንጂ በኢህአዴግ መዋቅር ውስጥ የነበሩና በእውቀት ላይ የተመረኮዘ አስተሳሰብ እንዲኖራቸው የሚፈልጉ ካድሬዎች የቅንጅት ማኒፌስቶን ኮፒ በማድረግ ማንበብና መወያየት ጀምረው ነበር። ከኢፌዲሪ ህገመንግስት እና የኢህአዴግ ፓሊሲዎች አንፃር ማኒፌስቶው የሚለይባቸው አንኳር ነጥቦች ተለይተው ከርከር ይደረግባቸው ነበር። የሚያስቀው ነገር ልብ ለልብ ከሚግባቡ ካድሬዎች ውጪ ስለ ማኒፌስቶው ትንፍሽ የሚል ነበር። በደርግ ጊዜ ኢህአፓ የበተነውን ወረቀት ይዞ እንደመገኘት ያስፈራ ነበር። ከእለታት በአንዱ ቀን ኢህአዴግ ቢሮ ስብሰባ ላይ ተቀምጠን የጉለሌን ምርጫ የሚከታተለው ከበደ ብሩ የሚባለው ካድሬ ቦርሳ ውስጥ ወሽቆት ተመለከትኩ። ወደ ጆሮው ተጠግቼ "ከቤ! የቅንጅት ማኒፌስቶን እንዴት አየኸው?" አልኩት። የከቤ ፊት ተቀያየረ። በፉንታው ተጠግቶኝ "በበረከት ልታስጠምደኝ ነው?" በማለት የሚገርም ምላሽ ሰጠኝ።

ከዚህ በተጨማሪም ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን ውድድር እንደሚገቡ ይፉ ሲያደርጉ ኢህአዴግን ሁልጊዜም የሚያስበረግገውን "ኩበሄር የዘለለ ኢትዮጵያዊነት" አጀንዳ ይዘው ይነሳሉ ተብሎ አልተጠበቀም ነበር። ኢህአዴግ ኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነትን ዋነኛ ጠላቱና የትምክህት መገለጫ አድርጐ ይወስዳል። ከጠባብነት ይልቅ ትምክህተኝነት የስርአቱ ዋነኛ አደጋ እንደሆነ። በብዙዎቹ ከፍተኛ ካድሬዎች እምነት ጠባብነት የተወለደውና የፉፉው በትምክህት ምክንያት ነው። በዚህም ምክንያት ኢህአዴግ ጠባቦች ብሎ የፈረጃቸው የፕሮፌሰር በየነ እና ዶክተር መራራ ፓርቲዎች ዋነኛ ስጋቶቹ አይደሉም። እንደውም ለማጣፈጫነት ይፈልጋቸዋል። በመሆኑም ኢህአዴግ ወደ ምርጫው ሲገባ ሙሉ በሙሉ እንደሚያሸንፍ ግብ ይዞ የገባው እነዚህን ተቃዋሚዎች ታሳቢ በማድረግ ነበር። ርግጥም እነዚህ ተቃዋሚዎች በተናጠል አዲሳአባ ፣አማራ ክልል፣ የሀገሪቷ ከተሞች፣ አምቦ፣ አርሲ፣ ወለጋ፣ ሀድያ... ሊፎካከሩ ይችሉ ይሆናል እንጂ በሌላው ቦታ ከባድ ይሆንባቸው ነበር።

***

ከአዲሳአባ አንፃር መነሳት ያለበት ጥያቄ ቅንጅት ባይፈጠር ኖሮ የመዲናይቱ የምርጫ ውጤት ምን ይሆን ነበር? ቅንጅት በመፈጠሩ በአዲሳአባ ምርጫ ሂደት ላይ ምን ተጽእኖ አሳረፈ? የሚሉት ይሆናሉ። ስለዚህም እነዚህን ፉይዳ ያላቸው ጥያቄዎች በማንሳት የግል እይታን አስቀምጦ ማለፍ ተገቢ ይመስለኛል።

ተደጋግሞ እንደተገለፀው የአዲሳአባ ህዝብ ኢህአዴግን አልፈልግም ካለ ቆይቷል። ከዚህ በመነሳት በምርጫ 97 ሊሆን የሚችለው የተቃዋሚ ፓርቲዎች ጥንካሬ ምንም ደረጃ ላይ ይሁን "ኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነት እና የግለሰብ ነፃነት" አንግቦ የተነሳ ድርጅት እንደሚያሸንፍ የሚያጠራጥር አይደለም። በመሆኑም በቅድሚያ የልደቱ ፓርቲ (ኢዴአፓ) እና የኢንጅነር ሀይሉ ፓርቲ (መኢአድ) ማሸነፋቸው አይቀርም ነበር። ሁለቱ ፓርቲዎች የተጠናወታቸው እርስ በራስ መጠፋፋት እንደተጠበቀ ሆኖ በየምርጫ ክልሉ እጩ ቢያቀርቡ እንኳን የምርጫ ውጤቱ በመሰረቱ አይቀየርም። በዚህ ሁኔታ ውስጥ የምርጫ ውጤቱ በቅደም ተከተል ይቀመጥ ቢባል ኢዴአፓ፣ መኢአድ፣ ኢህአዴግ ይሆን ነበር። የፕሮፌሰር በየነ እና ዶክተር መራራ ፓርቲ መቼም ቢሆን በአዲሳአባ ላይ የማሸነፍ እድል የላቸውም። ከአስር አመት በላይ በሆነ የካድሬነት ዘመኔ የአዲሳአባ ህዝብ፣ መምህራን፣ ተማሪዎች፣ የመንግስት ሰራተኛውን ከኮልፌ እስከ የካ፣ ከጉለሌ እስከ አቃቂ በአራቱም ዋልታዎች የማግኘት እድል አጋጥሞኛል። ይህ ህዝብ የፕሮፌሰሩንም ሆነ የዶክተሩን ፓርቲ ወኪሎቹ አድርገው አይቆጥርም። ፕሮፌሰር በየነ በፓርላማ ቀርበው "ህዝባችን በመሬት ጥበት እየተሰቃየ ነው!" ብለው ሲያማርሩ የመዲናይቱ ህዝብ ስለማን እየተናገሩ እንደሆነ የራሱን ትርጉም ይሰጥ ነበር። በዚህ ምክንያት የሁለቱ አንጋፉ ሰዎች ፓርቲዎች በአዲሳአባ ህዝብ እዚህ ግባ የሚባል መሰረት የላቸውም። ሌላው ቀርቶ በምርጫ 92 ማግስት ተፈጥሮ ለውድድር የቀረበው የልደቱ ፓርቲ በእቅድ የተመራ ማጭበርበር ተጽምበት እንኳን በርካታ ወንበሮችን አግኝቷል። በዛን ወቅት የእነ ፕሮፌሰር በየነ ድርጅት እንኳን ተወዳድሮ ሊያሸንፍ የተሟላ እጩ ማቅረብ እንኳን ተስኖት ነበር። በመሆኑም የቅንጅት መፈጠር የአዲሳአባን ውጤት ከመቀየር አንፃር የሚለውጠው ነገር አይኖርም ነበር። የአዲሳአባ የለውጥ መንፈስ አስቀድሞ በመታየቱ።

ታዲያ ከአዲሳአባ አኳያ የቅንጅት ፉይዳው ምንድን ነበር?

በእኔ እምነት ቅንጅት የሚባለው የፓለቲካ ፓርቲ መፈጠር ከመዲናይቱ አንፃር የተለያዩ እንድምታዎች ነበሩት። የአዲሳአባ ህዝብ በግለሰብ ነፃነት እና ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት ያነገቡትን ፓርቲዎች ሊመርጥ ቢዘጋጅም መጻኢው ግዜ ያስፈራው ነበር። በተለይ ቀለም በቀመሱ የከተማዉ ነዋሪዎች ዘንድ ከፍተኛ ስጋት ነበር። የፓርቲዎቹ የማስፈፀም አቅምና ኢህአዴግ ሊፈጥረው የሚችለውን እንቅፋት አስቀድሞ በመረዳት ውጤቱ ከድጡ ወደ ማጡ እንዳይሆን ይጠራጠራሉ። በምሁራን የተፈጠረው ቅንጅት እነዚህን በስጋት የተሞሉ እና የሚዋልሉ ልቦችን እንደ አለት አፀና። የህዝቡ ጥርጣሬ ሙሉ በሙሉ ተገፈፈ። ሁለተኛው ፉይዳ ኢህአዴግ ወትሮም የሚፈልገውን እና በምርጫ 92 እንደ አንድ ስትራቴጂ የተጠቀመበትን ተቃዋሚዎች እርስ በራስ

እንዲፎካከሩ የማድረግ አካሄድ እንዲቀር ማድረጉ ነበር። ርግጥም አንዱ አንደኛው ወገብ ላይ የተጣበቀ ተባይ አድርገው የሚተያዩትን ኢንጅነር ሀይሉ ሻወልና ልደቱን የመሳሰሉ ሰዎች ማቀራረብ መቻል በኢህአዴግ ውስጥ ለነበርን ካድሬዎች ሳይቀር አስደናቂ ነበር። ይህ በመሆኑ የተበታተኑ አቅሞች ተሰባሰቡ። ኢዴአፓ እና መኢአድ በገነቡት አጥር ላይ ቆሞ የነበረው ህዝብ እንደ በርሊን ግንብ አጥሩን አፈራረሰው። ልክ አቶ መለስ በድህረ ምርጫ ግርግሩ ወቅት እነ ዶክተር ብርሀኑ ነጋን ቤተመንግስት ጠርቶ "ያስቸገራችሁን አጥር ላይ ቆማችሁ ነው!!" እንዳለው።

በመሆኑም በአንድ በኩል ኢህአዴግ ባልገመተውና ባላቀደው ሁኔታ ቅንጅት መፈጠሩ፣ በሌላ በኩል ቅንጅትን የመሰረቱት ሰዎች ተከለሰውነት ከኢህአዴግ ካድሬዎች ገዝፎ መታየቱ፣ አንግበውት የነበረው ኢትዮጵያዊነት አጀንዳ፣ በምርጫ ክርክሩ ወቅት በአግባቡ ራሳቸውን መሸጣቸውና አማራጭ ፓሊሲ መያዛቸው የምርጫ 97 የፓለቲካ ምህዳር በሀገር ደረጃ ግልብጥብጡን አወጣው። መስከረም ሳይጠባ የምናሸንፍባቸው ምክንያቶች ተበለው በኢህአዴግ የቀረቡት ቁምነገሮች በዜሮ ተባዙ። ኢህአዴግ ተደናገጠ። ይህን ተከትሎ በየጊዜው የሚለዋወጡና ያልሰከኑ አዳዲስ እቅዶችና እርምጃዎች ግብታዊ በሆነ መንገድ መውጣት ጀመሩ። ኢህአዴግ ከአጥቂነት ወደ ተከላካይነት ተንሸራተተ። ይህም ሆኖ የሚገቡበት ጉሎች የህንድና የብራዚል እግር ኳስ ቡድኖች ቢጫወቱ ሊቆጠር የሚችለውን ያህል ነበር። ኢህአዴግ እንደ ህንዶቹ አስማት በመስራት ኳሷን ድንቢጥ አሊያም የዳሸን ተራራን ካላሳከላት በስተቀር የሚያዛልቅ እንዳልሆነ ወለል ብሎ መታየት ጀመረ። መውጫ ቀዳዳው ይህና ይህ ብቻ መሆኑን አስቀድመው የተገነዘቡት አባዱላና ጁኒዲን አዳራቸውን "የአሩሲዋ ወይዘሮ" ጋር እንዳደረጉ የውስጥ ወግ ሆነ። ቅቤ የጠገበ ጋቢ እየለበሱ በየወንዙ ዳር የሚማማሉትን ተወዳጁ ኢቲቪ ማሳየት ጀመረ። እነ ሽፈራው ጃርሶና እሸቱ ደሴ "እያንገዋለለ" የሚለውን ነጠላ ዜማ መዝፈን ጀመሩ። የኢህአዴግ ማእከል ደግሞ ግብታዊ እቅዶችን ወደ ማውጣት ተሸጋገረ።

በመበራገግ ከወጡት ግብታዊ እቅዶች ቅድሚያውን የሚይዘው ምርጫው ሊካሄድ ሁለት ወራት ሲቀረው "ኔትወርኪንግ" በሚል ስያሜ የተፈጠረው አዲስ አደረጃጀት ነበር። የወጣቶች፣ የሴቶች፣ የጥቃቅን ተጠቃሚዎች፣ የመምህራን፣ የተማሪዎች፣ የኮንደሚኒየም ተጠቃሚዎች፣ የወያላና ተራ አስከባሪዎች፣ የሙስሊሞች፣ የሸማኔዎች... ወዘተ የሚባሉ ኔትወርኮች እንዲፈጠሩ ተደረገ። ለእያንዳንዱ ኔትወርክና በውስጡ ላሉት አባላት "ኤ"፣ "ቢ"፣ "ሲ"፣ "ዲ" የሚል ደረጃ እየወጣላቸው እንዲሄድ አቅጣጫ ተቀመጠ። "ኤ" ማለት ኢህአዴግን በፅናት የሚደግፍና ሌሎችም ኢህአዴግን

እንዲመርጡ የሚቀሰቅስ የሚል ደረጃ ተሰጠው። "ቢ" ማለት በግለሰብ ደረጃ ኢህአዴግን ለመምረጥ የወሰነ ፣ግን ደግሞ የማይቀሰቅስ ሆነ። "ሲ" ደግሞ ገና ያልወሰነና ቢሰራበት ወደ ላይ ሊመጣ የሚችል፣ "ዲ" የሚያገኘው ተቃዋሚን ለመምረጥ የወሰነ በሚል ተፈረጀ። እንደ እውነቱ ከሆነ የኔትወርኪንግ ስራ አስቂኝም አሳዛኝም ነበር። ሁሉም ተመሳሳይ ቢሆንም ለትዝታ እንዲሆን ሁለቱን ብቻ ለይቼ ላውጋችሁ።

የከበደ ብሩ "የሽማኔዎች ኔትወርክ"

ምርጫ 97 ሁለት ወር ሲቀረው...

እንደተለመደው አመሻሽ ላይ የአዲሳአባን ምርጫ የምናስተባብር ካድሬዎች በኢህአዴግ ቢሮ ሁለተኛ ፎቅ ከስምአን ልጅ ጋር ተቆጠናል። ትንሿ አዳራሽ በጭንቀት በተወጠርን ካድሬዎች ትንፋሽ አጥሯታል። በግራዬ ተፈራ ዋልዋ ተቀምጧል። ተፈራ እኔ በምከታተለው ወረዳ የፓርላማ እጩ ሆኖ ቀርቧል። በቀኜ በኩል ደግሞ የትምህርት ቢሮን በህውሀት ካድሬዎች የጠቀጠቀው ከበደ ብሩ አለ።

ሪፓርት የማቅረብ ቅድሚያ የልደታን ምርጫ ሲያስተባብር ለነበረው ተክሌ ለሚባል ካድሬ ተሰጠ። ተክሌ ሀቀኛና ያመነበትን ነገር እስከ መጨረሻ የሚናገር ነበር።እናም በልደታ ስለተዘረጋው የጥቃቅን ተጠቃሚዎች ኔትወርክ አፈጻጸም ማቅረብ ጀመረ። በተክሌ ሪፓርት መሰረት በክፍለ ከተማው ከተደራጁት 3000 የጥቃቅን ተጠቃሚዎች ኔትወርክ ውስጥ 30% "ኤ"፣ 25% "ቢ"፣ እና የተቀሩት "ሲ" ደረጃ እንደሚታዩ አሳወቀ። በረከት እና አርከበ እቁባይ እየተቀባበሉ አንባረቁበት። በተለይ አርከበ በስሜት ውስጥ ሆኖ፣

"የጥቃቅን እና አነስተኛ ተጠቃሚ በ"ኤ" ደረጃ ያልተቀመጠ ሌላ ማን ሊቀመጥ ነው? ምርጫውን መምራት አቅቶሀል! በልደታ ብንሸነፍ ተጠያቂው አንተ ነህ" በማለት አስፈራራው።

በቀኝ ጐኔ የተቀመጠው ከበደ ብሩ ተደናግጦ ማስታወሻውን ሲገላልጥ ትኩረቴን ወደ እሱ እጅና ማስታወሻው አደረኩ። በቆረጣ የሚያደርገውን መመልከት ጀመርኩ። ሶስት ሺህ ብሎ የጻፈው ላይ አንድ ዜሮ ሲጨምር፣ 34% የሚለውን 84% ሲያደርግ ተመለከትኩ። ከበደ ብሩ ሪፓርት ማቅረቢያው ሲደርስ ጉሮሮውን ስሎ፣

"እኔ የምከታተለው በጉለሌ ቀጨኔ አካባቢ ያለውን የምርጫ ክልል ነው። በዚህ ክልል የሚኖረው አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል የደቡብ ኢትዮጵያ ብሄረሰብ ሆኖ በሽመና ስራ የሚተዳደር ነው። በዚህም ምክንያት የፈጠርነው የሽማኔ ኔትወርክ ነው። እስከ አሁን ድረስ በሰራነው ጠንካራ የፓለቲካ ስራ 30

ሺህ ሰዎች በኔትወርኩ እንዲታቀፍ አድርገናል። ከእነዚህ ውስጥ 84% "ኤ"፣ 10% "ቢ"፣ የተቀሩት ደግሞ በ "ሲ" ደረጃ የሚታዩ ናቸው። ይህ አንፀባራቂ ውጤት የመጣው እነዚህ ጭቁን ብሄረሰቦች ኢህአዴግ ባገኖፀፉቸው ህገ መንግስት ምክንያት ቀና ብለው መሄድ በመጀመራቸው ነው። የህዝቦችን የላቀ ተጠቃሚነት በሚያረጋግጠው ፓሊሲያችን ምክንያት በከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚ ሆነዋል። በተለይም አርከበ ከንቲባ ከሆነ በኃላ እንደ ጅብ በጉድጓድ ውስጥ እንድንሰራና እንድኖር የተደረገውን በማስቀረት እንደ ሰው እንድንሰራ አድርገናል ብለዋል።" በማለት ረጅም ዲስኩር አሰማ።

አርከበ አወደሰው።

በረከት ደስ አለው።

ምርጫ 97 አንድ ወር ሲቀረው...

ከበደ ብሩ ከወር በኃላ እንዲህ በማለት ተናገረ፣

"የሸማኔ ኔትወርክ ለምርጫ ከተመዘገበው በላይ ሆኖ ከ30ሺህ ወደ 40ሺህ አድጓል። በምርጫ ያልተመዘገቡት እጅግ በጣም ቢቆጫቸውም ካርድ የወሰደው ኢህአዴግን እንዲመርጥ እየቀሰቀሱ ነው። የህይል አሰላለፉ መለስተኛ መሻሻል በማሳየት በ" ኤ" ደረጃ የተቀመጡት ወደ 90% ደርሷል።"

ምርጫ 97 አምስት ቀን ሲቀረው...

ከበደ ብሩ ተስፉ በቆረጠ አንደበት፣

"በሸማኔ ኔትወርክ የታቀፉ ሰዎች ቅንጅት በጠራው ሰላማዊ ሰልፍ እንዳልተሳተፉ አረጋግጠናል።ይልቁንስ የኔትወርክ ስራችንን እያመሱ ያሉት በአካባቢው የሚያስተምሩት መምህራን ናቸው። ዛሬ ሁለት የስነ ዜጋ መምህራን በከፍል ውስጥ ከኢህአዴግና ቅንጅት ማን ያሸንፉል በማለት ተማሪዎችን አከራክረዋል። መምህሩኑ ቅንጅት እንዲያሸንፍ አድርገው ተማሪው እንዲያጨበጭብ አስደረጉ። በዚህ ምክንያት ሁለቱንም ከስራ አገድናቸው" ብሎ ተናገረ።

አጠገቤ የነበረው ተፈራ ዋልዋ ተናደደ። እድል ሳይሰጠው፣

"ከበደ ብሩ! አንዲት ጥያቄ ብቻ ልጠይቅህ። እነዚህ መምህራን የክርክሩን መጨረሻ ኢህአዴግ ያሸንፉል አስብለው ቢያስጨበጭቡ ከስራ ታግዳቸው ነበር?"

በረከት በብርሀን ፍጥነት፣

"አሁን እንደዚህ አይነት ንትርክ የምንገባበት ሰአት አይደለንም። ከበደ! ራስህ መምህራኖቹን ጠርተህ ይቅርታ በመጠየቅ ወደ ስራቸው መልስ።

የተፈራ ዋልዋ "ወጣቶች ኔትወርክ"

ምርጫ 97 ሁለት ወር ሲቀረው...

ጊዜው የመጋቢት ወር የመጀመሪያዋ ቅዳሜ ያረፈበት ነበር። የቀድሞ ወረዳ 21 ቀበሌ 09 አዳራሽ እስከ አፍንጫው ጢም ብሎ ወደ ውጪ ፈሷል። ከአንድ ሺህ በላይ በተፈራ ኔትወርክ የታቀፉ ወጣቶች ነበሩ። ዋልዋ ስራውን በአቅም ግንባታ መጀመር ፈልጓል። የመጀመሪያው የአቅም ግንባታ ትኩረት በትምህርት ላይ እንዲሆን ወስኗል። ተፊ ግርግር በተዘጋጀለት ፕሮጀክተር ላይ ወረቀቶችን እያስቀመጠና ቀበቶ አልባ ሱሪውን በየጊዜው ከፍ እያደረገ፣

"ኢህአዴግ ካስመዘገባቸው ድሎች ዋነኛው በትምህርት ስርጭት የተገኘው ነው። በንጉሱና ደርግ ጊዜ የነበሩት አንደኛ፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተጨፍልቀው ቢደመሩ ኢህአዴግ የሰራው በአስር እጥፍ ይበልጣል..."

የማያቋርጥ ጭብጨባ። እንደገና የማያቋርጥ ፊሽካ።

ምርጫ 97 አንድ ወር ሲቀረው...

የዋልዋ ልጅ ሁለተኛውን ዙር የአቅም ግንባታ በዲሞክራሲ ስርአት ግንባታ ላይ ለማድረግ ተዘጋጅቶ መጥቷል። ስልጠናው እንደሚጀመር የተገለፀው ሶስት ሰአት ቢሆንም እስከ ረፉድ ድረስ ተንጠባጥበው ከመጡ 150 ወጣቶች ውጪ ዝር የሚል ጠፉ። ወጣቶቹ ያልመጡበት ምክንያት የአመቱ ንግስ ፣ የኮንደሚኒየም ቤት ምርቃት፣ የእንግሊዝ ፕሪምየር ሊግ ወሳኝ ጨዋታ ስላለ የሚሉ ሰበቦች ተደረደሩ። በመሆኑም በዚህ ያህል ቁጥር መቀጠል ስለማይቻል ጥሪው ተጠናክሮ ስልጠናው በሚቀጥለው ቀን እንዲሆን ተወሰነ። በንጋታው የመጡት ወጣቶች ቀንሰው ከመቶ በታች ሆኑ። የዋልዋ ልጅ ስለ ዲሞክራሲ ምንነት እና ኢህአዴግ ስለከፈለው መስዋእትነት ገለጻ ሰጠ። ሲጨርስ ተጨበጨበለት። አመስግኖ ሄደ። ከዛን ቀን በኃላ ተፈራና ወጣቶቹ ሳይገናኙ ምርጫ 97 ደረሰ።

ብዙ የተለፉበት ሰላማዊ ሰልፍ ...

ምርጫ 97 አንድ ወር ሲቀረው ከተፈጠሩት ስራዎች ሌላኛው በመስቀል አደባባይ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ ነበር። የሰላማዊ ሰልፉ ምክንያት ኢህአዴግ በምርጫ ክርክሩ ወቅት የደረሰበትን ከፍተኛ ሽንፈት ለመቀልበስ እንደ አንድ አማራጭ በመወሰዱ ነበር። በየእለቱ ማታ ኢህአዴግ ቢሮ በምናደርገው ግምገማ መሬት አንቀጥቅጥ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ እንደምንችል መግባባት ላይ ተደረሰ። ይህን ማድረግ የምንችልባቸው ምክንያቶች በዝርዝር

ቀረቡ። እነዚህም በየምርጫ ክልሉ ከመራጩ ብዛት በእጥፍ (ከሁለት ሚሊዮን በላይ) የተደራጁት ኔትወርኮች፣ ከኔቶርኮቹ ውስጥ ከ90% በላይ በ "ኤ" ደረጃ የሚታይ በመሆኑ ኢህአዴግን ከመምረጥ አልፎ ኢህአዴግን ምረጡ በሚል ቅስቀሳ እየተሳተፈ መሆኑ፣ የከተማዋ የልማት ትንሳኤ በኢህአዴግ አማካኝነት መበሰሩ፣ የኢህአዴግ ልማታዊ አቅጣጫ በመላ ሀገሪቱ ያስመዘገበው ባለሁለት አሀዝ እድገት የፈጠረው መነቃቃት ዋና ዋናዎቹ ነበሩ።

ከሰላማዊ ሰልፉ ጋር ተያይዞ አከራካሪ ከነበሩት ቁምነገሮች መካከል መቼ ይካሄድ የሚለው ነበር። በአማራጭነት የቀረቡት ቀኖች በምርጫው የመጨረሻ ሳምንት የሚውሉት ቅዳሜ፣እሁድ እና ሀሙስ ነበሩ። ከሁሉም ቀናት በመጀመሪያ የተመረጠው እሁድ ሆነ። ምክንያቱ ደግሞ ከዛ በኋላ የሚኖሩት ቀናት የስራ ስለሚሆኑና የምርጫ ቅስቀሳው የሚያበቃበት በመሆኑ ተቃዋሚዎች ሰላማዊ ሰልፍ የመጥራት እድል አይኖራቸውም፣ እሁድ የምናካሂደው መሬት አንቀጥቅጥ ሰልፍ አከርካሪያቸውን ስለሚመታ ሳምንቱን ሙሉ የተሰፋ መቁረጥ ዥዋዥዌ ይጫወታሉ የሚል ነበር። በዚህም ምክንያት በእሁድ ተስማማን። መዋቅራችንን አረንቴሽን ሰጥተን ቅድመ ዝግጅቱ ተጀመረ።

በሳምንቱ የተካሄደው የኢህአዴግ ቢሮ ስብሰባ ባልተጠበቀ ሁኔታ የሰላማዊ ሰልፉ ቀን ወደ ቅዳሜ መቀየሩ ተነገረ። የተቀየረበት ምክንያት ደግሞ ተቃዋሚዎች ቅዳሜ የድጋፍ ሰልፍ ለመጥራት እየተነጋገሩ መሆኑ መረጃ ስለደረሰን ነው ተባለ። እነሱ ቅዳሜ በሚጠሩት ስብሰባ ባልተጠበቀ ሁኔታ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ህዝብ ቢወጣ አደጋው የከፉ እንደሚሆን ተነገረን። በመሆኑም አስቀድመን ተሰፉ ማስቆረጥ እንደሚኖርብን መግባባት ላይ ተደረሰ። የተለወጠውን እቅድ ይዘን ወደ መዋቅራችን ወረድን። የመጣውን ሁሉ ልክነው ብሎ መቀበል የለመደው መዋቅራችን ለአዲሱ እቅድ አላስቸገረንም።

ቅድመ ዝግጅቱ ፉታ በሚነሳ መልኩ መፈፀም ጀመረ። ሰላማዊ ሰልፉን ሊያደምቁ የሚችሉ ባነሮች ለመስራት የሚያስችል በጀት ተመደበ። የህዝብ ዝውውር በሚበዛባቸው የከተማዋ አካባቢዎች ከፍተኛ ወጪ በማውጣት የቅስቀሳ ሰሌዳዎች ተተከሉ። በሺህ አላሙዲን ወጪ የተሰሩ ቲሸርቶችና ፒኖች በየወረዳው ተሰራጩ። የኢፌዲሪ ባንዲራና የኢህአዴግ አርማ በሚሊዮኖች ታትሞ ተከፋፈለ። መዋቅራችን በየቤቱ እየሄደ ህዝቡን ማስጨነቅ ጀመረ። ህዝቡ የልቡን በልቡ ይዞ ሰላማዊ ሰልፉን እንደሚወጣ ፍቃደኝነቱን አሳየ።

የድጋፍ ሰልፉ ሳምንት ሲቀረው ማስፈፀሚያ እቅድ በህላዌ ተዘጋጀ። በማታው መደበኛ ስብሰባችን ራሱ አረንቴሽን ሰጠን። በእቅዱ መሰረት ህዝቡ ወደ መስቀል አደባባይ የሚመጣው ተበታትኖ ሳይሆን በተደራጀ መንገድ

ባለበት ኔትወርክ ታቅፎ እንደሚሆን ተገለፀ። መነሻ ቦታዎች የቀበሌ ጽህፈት ቤቶች፣ ትምህርት ቤቶች፣ የመንግስት ተቋማት እና መንግስት የሰራቸው የጥቃቅን ሼዶች እንዲሆኑ ተደረገ። የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሳይቀር በሰላማዊ ሰልፉ የመሳተፍ ግዴታ ተጣለባቸው። ነዋሪው ወደ መስቀል አደባባይ ሲተም የሚያሰማቸው መፈክሮች ይፉ ተደረጉ። ጉዞው በብሄረሰቦች ባህላዊ ጭፈራና አልባሳት እንዲታጀብ ማጉሊያ ስፒከሮች፣ ከበሮና እንቢልታ እንዲገዛ ተደረገ። ከመስቀል አደባባይ ራቅ ብለው ላሉ ቀበሌዎች የአንበሳ አውቶብስ መደበኛ አገልግሎቱን አቋርጦ በነፃ እንዲያመላልስ ትእዛዝ ተሰጠ።

ይህም ሆኖ እስከ ቅዳሜ ሚያዝያ 29 ረፉዱ አራት ሰአት ድረስ በመስቀል አደባባይ የከብር እንግዳ ማን እንደሚሆን አልተወሰነም ነበር። ይህም የራሱ ምክንያቶች ነበሩት። በአንድ በኩል ኔትወርክ የተባለው አደረጃጀት በየእለቱ እየሟሸሸ መሄዱ ባልተነገረ መልኩ ይታይ ነበር። በሌላ በኩል ቅንጅት በሚጠራው መለስተኛ የአዳራሽ ስብሰባዎች የሚገኘው ህዝብ በከፍተኛ ሁኔታ ከመጨመሩም ባሻገር የምሁራን የፍርሀት ቆፈን እየተራገፈ ነበር። የለውጥ ንፋሱ ከአዲሳአባ ዘሎ ወደ ክልሎችም ተሸጋግሯል። ከመንደራቸው መሻገር አቅጧቸው ሲንገታገቱ የቆዩት የፕሮፌሰር በየነ እና ዶክተር መራራ ድርጅቶች ሳይቀር ባልጠበቁትና ባልገመቱት ሁኔታ የለውጥ ማእበሉ ከግራ ቀኝ ፋታ ነስቶአቸዋል። ርግጥ ከውጭ ሀይሎች ጋር ያደረጉት ጥምረት ከድሮው በተሻለ ቁመና እንዲገኙ አድርጓቸዋል። የኢህአዴግ ስጋት የመነጨው እነ ፕሮፌሰር በየነ በሀገር ውስጥ ካላቸው ጥንካሬ ሳይሆን ከውጭ የተቀናጁቸው ሀይሎች ጉልበት ነበር።

(በረከት ስምኦን (ኢህአዴግ) በብሄር የተደራጁ ተቃዋሚ አመራሮችን የሚያዩበት አይን የተለያየ ነው። ዶክተር መረራን ፈሪ እንደሆነ በመግለጽ እጅግ ይንቀዋል። ዶክተር መረራ ደፈር ብሎ ሲናገር ከሰማ እየሳቀ "ይሄ ፈሪ በስሱ ጃስ እንበለው እንዴ?" ይለን ነበር። ለነገሩ የሁለት ምርጫዎች ወግ "... ፕሮፌሰር መረራ በኢይናቸን ሰር ቁጭ ባሉበት ወንበር ወደታች ሲሰምጡ ተመለከትን" በማለት ጽፉለች። ፕሮፌሰር በየነን ደግሞ "ያለ ቦታው የአፄዎቹ አስተሳሰብ የተሸከመ፣ የተምታታበትና አድርባይ" በማለት ይጠራዋል። ከአለታት በአንዱ ቀን ፕሮፌሰሩ በሰንደቅ ጋዜጣ ላይ ለምን ሰልጣኑን ለወጣቶች አታስረክብም የሚል ጥያቄ ይቀርብለታል። ፕሮፌሰሩም "ምን ወጣት አለና?" በማለት ይመልሳል። ይህን አሳፋሪ መልስ እኔና ሽመልስ ከማል በሚዲያ ሞኒተሪንግ ሰአት ለበረከት ነገርነው። በረከት በአማርሞት ውስጥ ሆኖ "ኢህአዴግ እምቢ አለ እንጂ በሚኒሊክ አልጋ ላይ አንድ ወር ብናስተኛው የሰልጣን ምኞቱ ይተነፍስ ነበር" የሚል ምላሽ ሰጠን። ከሁለቱ መሪዎች በተቃራኒ አቶ ቡልቻ ደመቅሳን "ለኢህአዴግ ባይመቹም ቅን እና ሀገር ወዳድ" በማለት ይገልጻቸዋል።

)

ግራም ነፈሰ ቀኝ የኢትዮጵያን ህዝብ የለውጥ መንፈስ በጊዜያዊነት የተረከበው ቅንጅት እዛው ሳለ ለአመታት አንቀላፍተው የነበሩትን እና ኢህአዴግ የሚንቃቸውን የብሄር ዘመም ተቃዋሚ ፓርቲዎች አንገታቸውን ቀና አስደርጓል። ከአዲሳአባ ውጭ ይህ የሚባል መዋቅርና ታዋቂነት የሌለው የልደቱ ፓርቲ በመቀናጀው ውስጥ በመካተቱ ከዘገምተኛ እድገት በመላቀቅ መሪ ተዋንያን ሆኗል። ታዋቂ ምሁራን ፓርቲውን በፍላጐት መቀላቀል ጀምረዋል። መላ አማራ ድርጅትን በጀርባው በማረድ እና የአልባሳት ለውጥ በማድረግ መኢአድን የመሰረተው የኢንጅነር ሀይሉ ድርጅት በተመሳሳይ መንገድ በመቀናጀው በመታቀፉ ትንሳኤው ተበስሯል። በዚህም ምክንያት እንደ ካሮት የቁልቁል እድገቱን በማቆም ህልውናውን ማረጋገጥ ችሏል። (በነገራችን ላይ ከሌሎቹ የተቃዋሚ ብሄር ድርጅቶች በተቃራኒ ለኢህአዴግ ከመኢአድ ይልቅ መአድ እጅግ የሚያስፈራውና በተደጋጋሚ ጊዜ ተጨባጭ አደጋ የጋረጠበት ነበር። መአድ በአማራ ክልልና በሌሎች አማርኛ ተናጋሪ በሚበዛባቸው ክልሎች ሰፊ ማህበራዊ መሰረት ነበረው። የሰው ለውጥ ሳያመጣ ስያሜውን የቀየረው የኢንጅነሩ ድርጅት ቁልቁል የወረደው በዚህ ምክንያት እንደሆነ ይገመታል።)

በመሆኑም ኢህአዴግ የጠራውን የቅዳሜ ሰላማዊ ሰልፍ ለማስተናገድ የተዘጋጀነው በእንደዚህ አይነት አጣብቂኝ ሁኔታ ውስጥ ሆነን ነበር። እስከ ረፉዱ ድረስ የአቶ መለስ መገኘት ያልተነገረበት ምክንያትም ይህ ነው። ይሁን እንጂ የተፈራው ቀርቶ ከአንድ ሚሊዮን በላይ የሚሆን ህዝብ መስቀል አደባባይን አጥለቀለቀ። አቶ መለስ በብርሀን ፍጥነት ልጆቹን ይዞ መጣ። ጭፈራው እና እልልታው አስከሮት፣

"ይህ ጐርፍ ከምርጫ ባሻገር ግልፅ መልእክት አስተላልፉል። ይህን ህዝብ ይዘን ለምን እናጭበረብራለን" በማለት ታሪካዊ ንግግር አደረገ። እለቱ በኢህአዴግ ካድሬዎች ዘንድ ከፍተኛ ፈንጥዝያ ፈጠረ። ህላዌ ዮሴፍ በድል አድራጊነት ተጀብኖ "በሰልፉ የተሳተፉት ካርድ የያዙ መራጮች በመሆናቸው አሸናፊዎች እንሆናለን" የሚል መግለጫ በምሽቱ ዜና አቀረበ። መደበኛው የኢህአዴግ ቢሮ ስብሰባ ተሰርዞ ሁለት ጥበቅ መመሪያዎች ለአባላችን እና ደጋፊዎቻችን እንድናስተላልፍ በስልክ ተነገረን። እነዚህም በኔትወረክ የተደራጁት አባላትና ደጋፊዎች በእሁዱ ሰላማዊ ሰልፍ እንዳይሳተፉ የሚል እና መዋቅራችን በምንም መልኩ የቅንጅትን ሰላማዊ ሰልፍ እንዳያደናቅፍ ማድረግ እንዳለብን የሚገልፅ ነበር። ይህን ተከትሎ የክፍለ ከተማ ፓሊስ አዛዦችን ውሳኔውን ጠርተን ነገርናቸው። ሰልፉን ሊያደናቅፉ የሚፈልጉ ሰዎች ካሉ በአስቸኳይ ሪፓርት እንዲያደርጉ አሳሰብን።

በዚህ ምሽት መሸታ ቤቶች በኢህአዴግ ደጋፊዎችና አባላት ተጥለቀለቁ። እኔም ወረዳ 20 ላይ ለፓርላማ እንዲወዳደር እጩ ሆኖ ከቀረበው የገቢዎች ሀላፊ ከነበረው ገብረ ዋህድ እና የወረዳ 23 ፓሊስ አዛዥ ከነበረው ጡሩነህ በርታ ጋር ለሊቱን ሙሉ ከአንደኛው ወደ ሌላኛው ጭፈራ ቤት በመሄድ አሳለፍን። እኛ በገባንበት መጠጥ ቤት ሁሉ እኛን የተመለከተ ሰው በቁጭት ውስጥ ሆኖ ውልቅ እያለ ይወጣ ነበር። ይህ የህዝብ ድርጊት በአዲሳባ መጠጥ ቤቶች ብቻ ሳይሆን በመላ ሀገሪቱ እንደነበር የምርጫው ውጤት በተገመገመ ሰአት ለማረጋገጥ ችያለሁ። በየቤቱም ህዝቡ ሬዲዮና ቴሌቪዥን እስከመዝጋት የሚያደርስ እልህ ውስጥ እንደገባ ማወቅ ተችሏል። ይህ ቁጭት ነበር የሚያዝያ 30ውን ሰላማዊ ሰልፍ የወለደው... ብሶት! ቁጭት! እልህ የወለደው ሰላማዊ ሰልፍ።

እሁድ ረፉዱ ላይ ከእንቅልፌ የቀሰቀሰኝ የወረዳ 20 ፓሊስ አዛዥ ስልክ ነበር። ቡልጋሪያ አካባቢ ሶስት የእኛ አባላት ህገ ወጥ ስራ እየሰሩ እንደሆነ ሪፓርት እንደደረሰው ነገረኝ። በፍጥነት ወደ ቦታው ሄድኩኝ። ሶስቱ ወጣቶች ጉልበታቸው ላይ የንብ አርማ ለጥፈው "ገና ረግጠን እንገዛችኋለን" በማለት እና አውራ ጣታቸውን ወደ መሬት በመዘቅዘቅ ይደነፉሉ። በግሩፕ በግሩፕ ሆነው የቴዲ አፍሮን ያስተሰይራል እየዘፈኑ የሚሄዱት ወጣቶች የልጆቹን ድርጊት ሲመለከቱ "ዝንቦ! ዝንቦ" እያሉ ይጮሀሉ። አይጠጓቸውም። ሁኔታው ስላበሳጨኝ ማንነቴን ሳልናገር ለምን እንደዚህ እንደሚያደርጉ ጠየኳቸው። አንደኛው ሽጉጥ መያዙን ማሳየት ስለፈለገ ጃኬቱን ወደ ላይ ከፍ አደረገ። የኢህአዴግ አባልነት መታወቂያቸውን እንዲያሳዩኝ ጠየኳቸው። በድጋሚ ጃኬቱን ከፍ አድርጐ አሳየኝ። ወጣቶቹ እኔን አለማወቃቸው ጥርጣሬ ውስጥ አስገባኝ። ቢያንስ ፎቶ ግራፌ በየአስር አርምጃው ተለጥፉል። ከ1992 ጀምሮ የዞኑ ካድሬ ነበርኩ። ከወረዳው ወጣቶች መምህራን እና ነዋሪዎች ጋር ሰፉፊ ስብሰባዎችን አድርጌያለሁ። በወረዳው የሚካሄደውን የምርጫ ሂደት እየመራሁ ያለሁት እኔ ነኝ። በወረዳው እነ ልደቱ ቅንጅትን ወክለው እኔ ፣ሚፍታህ አብዶ እና ሚኒስትር ጌታቸው ኢህአዴግን ወክለን ባደረግነው ክርክር አባላችን የሆኑ ወጣቶች በሙሉ እንዲታደሙ አድርገናል። ሌላው ቀርቶ እንደ ጐርፍ አየተጓዙ ያሉት ወጣቶች እንኳን ለይተውኛል። ብዙዎች የኢህአዴግ ወጣቶች ኔትወርክ አባላት ሆነው "ኤ" የተሰጣቸው ናቸው። መጨረሻውን ሳያዩ መሄድ ስላልፈለጉ ቡልጋሪያ አደባባይን ሞልተው ፈሰዋል።

ከተንኳሾቹ ወጣቶች ጋር እሰጣ ገባ ሳልገባ በርቀት የቆሙትን የከተማዋ ፓሊሶች በቁጥጥር ስር እንዲያውሏቸው ነገርኳቸው። አደባባይ ሞልተው የሚጠባበቁኝን ወጣቶች የኢህአዴግ ፍላጐት እንዳልሆነ፣ ሰላማዊ ሰልፉ በሰላም እንዲጠናቀቅ ፍላጐታችን መሆኑን ገልጬ እንዲሄዱ አደረኩ። ወደ

ወረዳ 20 ፓሊስ ጣቢያ የተወሰዱትን አጥፊ ወጣቶች ለመምከር እና የኢህዴግን አቅጣጫ ለማሳወቅ ወደ ጣቢያው ስሄድ ወጣቶቹ የሉም። የወረዳው ወንጀል መከላከል ስማቸው እንኳን ሳይመዘገብ እንደለቀቃቸው ተነገረኝ። የመከላከል ሀላፊው ከፌደራል ፓሊስ የተመደበ የህውሀት ነባር ታጋይ ነበር። የት እንደሄዱ ስጠይቀው በትእቢት ውስጥ ሆኖ "የበላይ ትእዛዝ ፈጽሜያለሁ። ከፈለግክ ለሀይሌ ፍስሀ ደውልለት" አለኝ። የሚገርም ነበር። ከዚህ ስራ በስተጀርባ የገቢዎች ሀላፊው ጉበረዋህእድ እና አርከበ እቁባይ መኖራቸውን ዘግየት ብዬ አረጋገጥኩ።

እነሆ! የተቀናቃኞቻችን ሰላማዊ ሰልፍ ምድር አንቀጥቅጦ ተፈፀመ። የዛን እለት ምሽት ሶስት ሰአት ኢህአዴግ ቢሮ አስቸኳይ ስብሰባ ተጠራን። ቀደም ብዬ ስለደረስኩ አዳራሹ አጠገብ ከቆሙት የህውሀት ካድሬዎች ውስጥ አርከበ ከትግራይ ይዞአቸው የመጡት ሀይሌ ፍስሀ፣ ዘሩ እና ይሳቅ አበራ(ቆሪጥ) ጋር ተቀላቀልኩ። ሀይሌ ፍስሀ "በጦርነት የተሸነፈው ሻእቢያ በእጅ አዙር በተላላኪዎቹ ሊያሸንፈን ነው።" እያለ በተደጋጋሚ ይናገራል። ይሳቅ ቆሪጥ ደግሞ አብዛኛው የቅንጅት ሰልፈኛ የምርጫ ካርድ ያልያዘና ነውጥ ለማንሳት ያቆበቆበ አደገኛ ቦዘኔ እንደሆነ ያስረዳል። በእልህ የተበከነከነው ዘሩ በጐማ ቁጠባ አካባቢ የሚያልፈው ሰልፈኛ "ትግሬ ወደ መቀሌ፣ ንብረት ወደ ቀበሌ" አያለ ሲፎክር እንደነበረ እጁን እየጠበጠበ ይናገራል። ዝምታዬን የተመለከተው ዘሩ ወደ እኔ ዞሮ "የአንተ ሀገር ሰው ልቡ አይታወቅም። ያ! ዙምባቤ የተደበቀው ጩሩራ ባሪያ ወርቅ እና ፉንድያን ያነሳው ወዶ አይደለም" አለኝ። ህዝቡ ለቅንጅት ድጋፍ ንቅል ብሎ መውጣቱ ቢያበሳጨኝም እነ ዘሩ እያነሱ የሚጥሉት ሀሳብ አስደነገጠኝ። በሀገሩ ምርጫ የማያውቀው ሻእቢያ የኢትዮጵያ ምርጫ መሪ ተወንያን እንደሆነ ሲነገር ርግጥም ያስደነግጣል። እንደ ማእበል የተመመው ህዝብ የምርጫ ካርድ ያልያዘ እንደሆነ ሲነገር ጤንነትን ያጠራጥራል። የትግሬ ወደ መቀሌ መልእክት ይህን ጊዜ ጠብቆ መናገሩ ያበራግጋል።ይህን ሰምቶ መጻኢው ግዜ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት የማይችል ሰው ጭንቅላት የሌለው ነው።

ወደ ስብሰባ አዳራሹ ስገባ ለመሞት የሚያጣጥር ሰው የሚጠባበቁ ሰዎች የተሰበሰቡ ይመስላል። ብዙ መረበሽ የማይታይበት (ወይም መረበሹን ዋጥ ያደረገው) በረከት ስምኦን ብቻ ነው። ባልተጠበቀ ሁኔታ የሁለቱም ቀናት ሰላማዊ ሰልፎች በድል መጠናቀቅ ሊያኮራን እንደሚገባ፣ ኢህአዴግ የተሰዋለት አላማ እንደሆነ አስረዳን። የተቃዋሚዎች የሰላማዊ ሰልፍ ግብታዊ እንደሆነና በብዛት መራጭ ካርድ የሌላቸው ከኦሮሚያ አቅራቢያ ዞኖች (ዱከም፣ ደብረዘይት እና አዳማን ጨምሮ) የተቀላቀሉበት እንደሆነ አስረዳን። በመሆኑም ኔትወርኮቻችን ተደናግጠው እንዳይበታተኑ መጽናት የሚያስችል ስራ መስራት

እንደሚገባን አሳሰበ። ከዚህ አንፃር ትልቁ ስራ እሁድ ላይ ከወጣው ሰልፈኛ በላቀ ቁጥር ያለው ህዝብ ሀሙስ ከሰአት ሰላማዊ ሰልፍ በመጥራት አዲሳአባን ማንቀጥቀጥ እንደሆነ ገለፀ።

በረከት ካቀረበው የድጋሚ ሰላማዊ ሰልፍ ተከትሎ የተሰጡት "አይቻልም! በጣም አስቸጋሪ ነው" የሚሉት የካድሬዎች አስተያየት የበረከትን እውነተኛ ባህሪያት ግልፅ አድርጎ የሚያሳዩ ነበሩ። የሁለት ምርጫዎች ወግ ከውቅያኖስ የጠለቀ ትእግስት ያገኘናፀፈችው የስምአን ልጅ አራስ ነብር ሆነ። አፍንጫውን እየፈተገ፣

"በምርጫው መለስ እንዲሳተፍ ስላልፈለግን እንጂ ነገ ማታ ወጥቶ ለህዝቡ የሰላማዊ ሰልፍ ጥሪ ቢያቀርብ አልጋ ላይ የወደቁ አረጋውያን ሳይቀር አልጋቸውን ተሸክመው መስቀል አደባባይን ያጥለቀልቁታል" ብሎ ተናገረ። ይህ ንግግሩም ቢሆን ካድሬዎች ከገባንበት ድንጋጤ ሊያወጣን አልቻለም። በመሆኑም መዋቅራችንን ሰኞ ጠዋት አረንቴሽን ሰጥተን ማታ እንድንገናኝ ቀጠሮ ተይዞ ተለያየን።

ሰኞ ጠዋት አብዛኛዎቹ ወረዳ ላይ ከምድብተኛ ካድሬዎቻችን ውጪ ዝር የሚል ጠፉ። ለአባላት ስልክ ቢደወል የሚያነሳ የለም። የቀበሌ ካድሬዎች አባላትን ቤት ለቤት እያሰሱ መጥራት ጀመሩ። ብዙዎች ጉንፉን፣ ብርድ፣ ቁርጥማት፣ ማይግሬን የሚባሉ የማርያም መቀነቶች አደናቀፉቸው። ኢህአዴግን ወደ ስልጣን ለማምጣት ተስፉ ተጥሎበት የነበረው ኔትወርክ ውሀ በላው። ጥቃቅን እንደ ስሙ ጥቃቅን ሆነ። የኮንደሚኒየም ተጠቃሚና ተስፈኛ ኔትወርክ "ቅንጅት በአጭር ጊዜ ተስፉችንን ወደ እውን ሊቀይርልን ቃል ገብቶልናል" በማለት በግላጭ ተናገሩ። ከትምህርት ቤቶች የሚነፍሰው የለውጥ ንፉስ ኢህአዴግን የሚያስጠጋ አልነበረም። በቋፍ ላይ የነበረው ቢሮክራሲ የኢህአዴግ ካድሬዎችን ተገላገልን በሚመስል መልኩ ሽርጉድ ጀምሯል። የቴዲ አፍሮ በአስራ ሰባት መርፌ የተጠቀመችው ቁምጣ "በአርከበ ሱቆች" ሳይቀር መሸጥ ጀምራለች።

(ወይዘሮ አዜብ መስፍን በአርቲስቶች ኔትወርክ ታቅፎ የተያዘውን አርቲስት ጌዲዮን ዳንኤል (ጌዲ በተራ) ቢሮ ድረስ ጠርታ "ቴዲ አፍሮ ምን አደረግነው? መለስ እኮ ይወደው ነበር!" አለቻው። በቴዲ የተበሳጨው ጌዲዮን አንዲት ለሊት እኔና ገብረዋህድን ተደግፎ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ። ልናግባባው ብንሞክርም አልተሳካም። እኛና ጌዲ በተራ አልገባንም እንጂ ቴዲ አፍሮ "ለእቴጌ አቤት ከማለት ውጭ መቼ ለውጥ መጣ!" ብሎ እቅጩን ነግሮናል።)

ሰኞ ማታ ወደ ኢህአዴግ ቢሮ ሄድን። ሁሉም ተስፉ ቆርጧል።

የህውሀት ታጋዮች በእድሜ ባለፀጋነቱ የሚያሙት አርከበ እቁባይ ርግጥም መግፉቱ አስታወቀ። ገብስማ ኮፍያ ያደረገ ይመስል ነበር። ከወትሮው ባህሪ አንዳችም ለውጥ የማይታይበት ተፈራ ዋልዋ ብቻ ነው። ስንጥር የወደቀበት አይመስልም። ዞር ዞር ስል አርከበ የሚወዳደርበትን የየካ ምርጫ ክልል የሚመራው ካድሬ የሁሉ ደነቀ ለብቻው ተገንጥሎ በጥግ በኩል ተቀምጧል። ስለምንግባባ አጠገቡ ሄድኩኝ። ልቀመጥ ስል ስሜን እየጠራ፣

"ጋን ጋን ሸተትከኝ ማለት አይሰራም። ፈቅደህ ነው አጠገቤ የተቀመጥከው" አለኝ።

"ምን ተገኘ?"አልኩት።

"የየካ ምርጫ ቅስቀሳ እንደ እናንተ በደረቁ አይደለም።"

"እንዴት ማለት?" በግርምት ውስጥ ሆኜ ጠየኩት።

"ሳምንቱን ሙሉ በየቀኑ እስከ አምስት የሀረር ሰንጋ እየጣልን በሚኒሊክ ብርጭቆ ጠጅና ጠላውን እየሞላን ከህዝቡ ጋር እየጨፈርን ነው። በተለይ የገጠር ቀበሌዎች ዳስ ጥለው አርሶ አደሩን እየጋበዙ ነው። የአርከበ ፎቶ እንደ ሙሽራ ድግሱን አሙቆታል።"

"በየቀኑ ከሀምሳ ሺህ ብር በላይ እያወጣችሁ ነው። ማነው ወጪውን የሚችለው?"

"አንተ ደግሞ! የከንቲባ ጽህፈት ቤት ነዋ! ዶክተር አብርሀምና የፐሮቶኮል ሹሙ ጤናዳም እየከፈሉ ይሄዳሉ። ዛሬ ሰንጋዎቹ የሚሸጡበት በረት ሄጀ ነበር። የሚያስቅ ነገር ሰምቼ መጣሁ?"

"ምን ሰማህ?"

"የከብት ደላሎቹ ፎክ ብለው ማስታወቂያ ያሰማሉ።"

"ምን እያሉ?"

"ለተወዳጁ ከንቲባ ምርጫ ቅስቀሳ የሚሆኑ የሀረር ሰንጋዎች እዚህ ይገኛሉ እያሉ ይጮሀሉ" አለኝ።

ከየሁሉ ጋር እየተጫወትን በረከት ወደ አዳራሽ ገባ። ሰላማዊ ሰልፉ እንደቀረ ነገረን። በፉንታው ሀሙስ ማታ የሻማ ማብራት ስነስርአት በየክፍለከተማው እንዲካሄድ መወሰኑን ገለፀ። የሻማ ማብራቱ ጥሪ ኢህአዴግን የሚደግፍ የሚቃወም በሚል ሳይሆን ሀገራችን እንከን የለሽ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ማድረግ መቻሏን ለማወደስ አላማ ያለው መሆኑን አስረዳ። የአዲሳአባ ህዝብ በሙሉ ደረጃ ሳይወጣለት በክፍለከተማው እንዲሳተፍ ማድረግ እንደሚያስፈልግ አሳሰበ። ደጋግሞ፣

"መለስን በምርጫ ማሳተፍ ስላልፈለግን እንጂ ህዝቡ በየአካባቢው በተዘጋጁት ቦታዎች ሻማ እንዲያበራ ጥሪ ቢያደርግ ጠጠር መጣያ አይገኝም ነበር" በማለት ገለፀ።

ውሳኔውን ተከትሎ አባል፣ ደጋፊ፣ ተቃዋሚ ሳይባል መላው የአዲሳአባ ህዝብ እንዲሳተፍ ቅስቀሳ ተደረገ። ልዩ ትእዛዝ የተሰጣቸው ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች አሰልፈው ወደ ሻማ ማብራቱ አመጡ። የሻማ ማብራቱ ስነ ስርአት የጨረባ ተዝካር ሆነ። ልደታ፣ አዲስከተማና አማኑኤል አካባቢ የተካሄዱት መለስተኛ ግጭቶችን አስተናገዱ። የመንግስት ሚዲያ ተቋማት የሆኑት ኢቲቪ እና ኢዜአ ለመቅረጽ ሲሞክሩ እጆች የቅንጅት ምልክት በሆነው የድል ምልክት ተወረሩ። እንደ እውነቱ ከሆነ ኢህአዴግ የጠራው የሻማ ማብራት ስነስርአት ለቅንጅት የምርጫ ቅስቀሳ ማሳረጊያ ነበር።ምርጫው ከተጠናቀቀ በኃላ በየወረዳው የተደረገው የአባላት ግምገማ ያረጋገጠው ይህንኑ ነበር። ከአመታት በኋላ የወጣቸው የሁለት ምርጫዎች ወግ ይህን ሀቅ ያላለፈችበት ይመስል እንደሚከተለው ጽፉ አስነበቡችን፣

"ኢህአዴግ በተቃዋሚዎች የድጋፍ ሰልፍ ግብታዊነት ላይ ጥርጣሬ ባይኖረውም የሰልፉ ትልቅነት እልህ አጋብቶታል። እናም ለሐሙስ እለት ምሽት በየወረዳው የሻማ ማብራት ስነስርአት በማካሄድ እንደገና ሀይሉን ለመገንባት፣ እንደገና የሚዋልሉ ልቦችን ለማጽናት ወሰነ። በከተማ ደረጃ ሰልፍ ማድረግ ትተን በየክፍለከተማው የጠራነው የሻማ ማብራት ስነስርአት በታላቅ ድምቀት ተካሄደ።"

ከሻማ ማብራቱ ቅድመ ዝግጅት ጐን ለጐን አርከበ የታክሲ ሹፌሮችን ሰብስቦ የቅጣት ምህረት አደረገ። የነጋዴዎችን ውዝፍ ግብር በተመሳሳይ እንዲነሳ አደረገ። ድርጊቱን የአዲሳባ ምርጫ የምናስተባብር ካድሬዎች ኢህአዴግ ቢሮ በሚኖረን የምሽት ስብሰባ ላይ በድል አድራጊነት ውስጥ ሆኖ ነገረን። የዚህ እርምጃ የመጨረሻ ውጤትም እንደ ሻማ ማብራቱ የቅንጅት ምርጫ ቅስቀሳ ማጠቃለያ ሆነ።

የመጨረሻዋ ጥይት...

ሁሉን አሟጠን ለመውሰድ አስበን ሁሉንም ያጣንበት የምርጫ 97 ቅስቀሳ አስራ አንደኛው ሰአት ደርሷል። ዘለግ አድርገን የነደፍነው ስትራቴጂ በየጊዜው እየተከላሸ ወደ አለታዊ አቅድ ተወርውረናል። ህዝቡ እያየነው አሰላለፉን ቀይሯል። መንፈሱም ሙሉ በሙሉ ተለውጧል። ኢህአዴግን የሚመርጡ እና በትጋት የሚቀሰቅሱ በማለት "ኤ" የሰጠናቸው በሚሊዮን የሚቆጠሩ የኔትወርክ አባላት በኮንፒተር ቋንቋ የእሳት ግድግዳ (Firewall) አጋጥሟቸው ማለፍ ሳይችሉ ተቆርጠው ቀርተዋል። ኢህአዴግን ምረጡ ብለው ባይቀሰቅሱም እኛን ለመምረጥ የወሰኑ በማለት "ቢ" ያገናዘፍናቸው መቶሺህ የኔትወርክ አባላት ደራሽ ውሀ ወስዷቸዋል። የጥፋት ሀይሎች ያልናቸው ቅንጅቶች ርግጥም ከስልጣን ሊያጠፉን የመዲናይቱን ህዝብ ይሁንታ ለማግኘት ተቃርበዋል። ርግጥ ይህ ሁሉ ባጠገባችን እያለፈ አንዲት ያልተተኮሰች ጥይት

አለች። ይህቺ የመጨረሻ ጥይት በተለይ ለበረከት ስምኦን አንድ አመት ሙሉ ቀን ከሌት ከፈጋባቸው እቅዶች ሁሉ ታላቋ ናት። ለክፉ ቀን የተቀመጠች የሞት ሽረት ጥይት!!

በረከት በፍፁም ድል አድራጊነት ውስጥ ሆኖ፣

"ዛሬ ተቃዋሚዎችን ሰራሁላቸው። በምርጫ ቅስቀሳው ወቅት አስቀድሞ ያልነበረ ፕሮግራም እንዲጨመር አደረኩ። ቅንጅት እና ህብረት በመረጡት ጋዜጠኛ ጥያቄዎች አስቀድመው አዘጋጅተው እንዲቀርቡ የአየር ሰአት ሰጠናቸው። እኛም ገዳይ የሆነ ቃለምልልስ መለስ እንዲያደርግ ወሰነናል። የመጨረሻውን ሰአት ጠብቀን ሰራንላቸው። ኢህአዴግን አልመርጥም ብሎ የወሰነው ሳይቀር የመለስን ቃለ ምልልስ ሲሰማ ሀሳቡን ይቀይራል። የጥፋት ሀይሎች ልካቸውን ያውቃሉ።" በማለት የመጨረሻዋ ድል አድራጊ ጥይት የመለስ መግለጫ እንደሆነ ነገረን።

እነሆ! በቃለ ምልልሱ መጀመሪያ ህብረት፣ ቀጥሎ አቶ መለስ ቀረበ። በመጨረሻ ላይ ደግሞ ልደቱ አያሌውና ዶክተር ብርሀኑ ቀረቡ። ቅንጅቶች በንግግራቸው መሀል አጽንኦት የሰጡት የኢህአዴግ አባላትን ማረጋጋት ነበር። አስበውበት ይሁን/አይሁን የማውቀው ነገር የለም። በታቀደ መልኩ የፈፀሙት ከሆነ ግን አድናቆቴ ከፍተኛ ነው። እነ ልደቱ እንዲህ ነበር ያሉት፣

"እኛ ስልጣን ብንይዝ የኢህአዴግ አባላት የሆኑ የመንግስት ሰራተኞች የንብ ምልክት ያለባትን ቲሸርት ሳያወልቁ እንዲሰሩ እናደርጋለን።"

እንደ እውነቱ ከሆነ ይህ ለታሪክ ሊቀመጥ የሚገባ አባባል ነው። በተግባር ለመገለፅ ዝግጁነቱ ነበረ/አልነበረም የሚለውን ለጊዜው ትተን መገለጹ በራሱ ምስጋና የሚቸረው ይሆናል። የኢትዮጵያ ፓለቲካ ከቂም በቀልና መጠፋፋት ተላቆ ሁሉም የመሰለውን አመለካከት እያራመደ እንዲኖር በር ከፋች ስለሆነ። ይህን የእነ ልደቱ ማሳረጊያ ያዳመጡ አባሎቻቸን ከመደናገጥ ወጥተው መጽናናት ጀምረው ነበር። በንጋታው በመዋቅራችን ውስጥ ትልቅ መነጋገሪያ ሆኖ ነበር።

በተቃራኒው የአቶ መለስ ንግግር ከየትኛውም ወቅት ባነሰ መልኩ አድማጭ ያገኘ ሆነ። ሲጀመር በመሀል ላይ የስንግ መያዙ በራሱ የኮሙዩኒኬሽን መርሆ ድህነትን የሚያሳይ ነበር። አለም ተቀብሎ ባደረበት የኮሙዩኒኬሽን ህግ መሰረት አንድ መልእክት በሰዎች ህሊና ውስጥ ተቀርጾ የሚቀረው ወይ በመጀመሪያ፣ አሊያም በመጨረሻ የሚቀርበው ነው። በማስከተል አቶ መለስ የተጠቀመባቸው ቃላት ማስፈራሪያ ያዘሉና በንቀት የታጨቁ ነበሩ። የተቃዋሚ አባላትን ወደ ማጽናናት እና አብረን እንሰራለን የሚል እንድምታ ያለው

አልነበረም። በዚህ ምክንያት የበረከት የመጨረሻዋ ጥይት ባሩድ የሌላትና የደነበሸች ነበረች።

(በረከት አቶ መለስን በተመለከተ ከልቡ የሚያምንበትን እንደተናገረ ያረጋገጥኩት ከአመት በኃላ በቅርብ ከሱ ጋር መስራት ስጀምር ነበር። እስከዛ ድረስ ከአንገት በላይ የሚናገር ይመስለኝ ነበር። አቶ መለስ ለበረከት የልቡ ላይ አለት፣ የዘላለም ርስቱ... አልፉና አሚጋው ነው። እጅግ በጣም እርግጠኛ ሆኜ መናገር የምችለው ነገር ቢኖር አቶ መለስ ለበረከት የሰው ዘር አይደለም። ለጠቅላይ ሚኒስትር ሀይለማርያም "ዘላለማዊ ከብር ለታላቁ መሪያችን!" የሚል "መልእክተ ዜናዊ ወደ አቢሲኒያ" ሰዎች ጽፎ እየሰጠው በተከበረው ፓርላማ ዘላለማዊነቱን የሚያፀናለት እንጂ!!)

ምእራፍ አስራ ስድስት

ግንቦት 6: 1997 (የጠቆረ ትዝታ)

ቅዳሜ ግንቦት ስድስት አመሻሽ ላይ ኢህአዴግ ቢሮ በነበረን ስብሰባ የምርጫው አለት ሊኖረን የሚገባውን አደረጃጀት እና ግንኙነት የሚያመላክት አቅጣጫ ተቀመጠ። በሀገር አቀፍ ደረጃ ምርጫውን በበላይነት የሚከታተለው ታደሰ ካሳ (ጥንቅሹ) ተደረገ። የአዲሳአባን ደግሞ ህላዌ የሴፍ እና አሊ ሲራጅ ሆኑ። በአዲሳአባ ምርጫ ክልሎች አስተባባሪ የሆንን ካድሬዎች ሪፓርት የምናደርገው ለአሊ ሲራጅ እንደሆነ ተነገረን። ለሊት አስር ሰአት ምድብ ቦታችን ተገኝተን ሪፓርት እንድናደርግ ጥብቅ መመሪያ ተሰጠ። ማን መቼ እና እንዴት ይምረጥ የሚለው በዝርዝር ቀረበ። በዚህም መሰረት በኔትወርክ ተደራጅተው "ኤ" እና "ቢ" ደረጃ የተሰጣቸው ነዋሪዎች እስከ ጠዋት ሶስት መርጠው እንዲያጠናቅቁ፣ ሌሎች ኢህአዴግን ሊመርጡ የሚችሉ በኔትወርክ ያልታቀፉት ነዋሪዎች እስከ ቀትር ድረስ ቀስቅሰን በማስወጣት እንዲመርጡ ግድረግ እንደሚገባን ተገለፀ። የኢህአዴግ አባላት ደግሞ በየግማሽ ሰአቱ ተመዳድበው ወደ ምርጫ ጣቢያ በመግባት እንዲመርጡ እና መረጃዎች ከኢህአዴግ ታዛቢ እንዲወሰዱ ማድረግ እንዳለብን ስምምነት ተደረሰ። በመጨረሻም ለግንኙነት የሚሆኑ 500 ተንቀሳቃሽ የቤት ስልኮች ከቴሌኮሙዩንኬሽን በልዩ ትእዛዝ እንዲመጡ ተደርጉ በየምርጫ ጣቢያው ብዛት ታደለ። ለእኔም ወደ 40 ስልኮች ተሰጠኝ።

ከምሽቱ ሁለት ሰአት ስብሰባው ሲጠናቀቅ በቀጥታ ወደ ቤተሰቦቼ ቤት ቀራንዮ (ወይራ ሰፈር) ሄድኩኝ። ቤታችን በመሪር ሀዘን ከተዋጠ ሰማኒያ ቀን ሆኖታል። እህቶቼ፣ አክስቶቼ እና የአካባቢው ማህበረሰብ ጥቁር ሽማ ለብሶ ከቤታችን አይጠፉም። ዘመዶቼ እና የእናቴ ጓደኞች በየቀኑ በሚዘሩት እንባ አይናቸው ወደ ውስጥ ገብቷል። እንኳንም እንደዚህ አይነት መሪር ሀዘን ደርሶባቸው ወትሮም ልቅሶ አነፍናፊ ናቸው። ባገኙት አጋጣሚ እየተጠራሩ ሙሾ የሚያወርዱ። ፊት አውራሪዋ ደግሞ ያቺ! ዛሬ አጠገባቸው የሌለችው የአካባቢው ነዋሪ "ጠይሚ ሴት!" እያለ የሚጠራት ታናሽ እህታቸው ናት።

ያቺ! ለቅሶ የምታደምቅ ያልተቀጠረች አስለቃሽ።

ያቺ ! ለአመታት ደረት እየደለቀች በድጋፍ ወደ ቤቷ የምትገባ ሴት።

የባሏ ሀዘን ውስጥ ውስጡን እየቦረቦረ ያለጊዜዋ ከመሬት በታች ያዋላት

ምስኪን። ለእኔ ደግሞ አንዴ እናት፣ ሌላ ጊዜ አባት፣ ደግሞ ሌላ ጊዜ ታናሽ እህት። አንድም ሶስትም! ... እቴነሽ ቸርነት!!

"ጠይሚ ሴት!" የማንነቴ መሰረት፣ የስብእናዬ ምንጭ፣ የመኖሬ ምክንያት፣ የምኞቴ መዳረሻ ነበረች። ሀዘን እና ደስታዬ፣ ውድቀት እና ስኬቴ፣ ፍቅርና ጥላቻዬ የተመሰረተባት። ከልጅነቴ እስከ እውቀት የነበረኝን የህይወት ጀልባ መሪውን የጨበጠች።

የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ እያለሁ ጥናት የምጀምረው ለሊት ዘጠኝ ሰአት ነበር። በዛው ሰአት በመነሳት ሻይ እያፈላች ስትጠብቀኝ ለሊቱ ይነጋል። እሷ መጋኛ ብላ የምትጠራው እርኩስ መንፈስ እንዳይመታኝ። ሲነጋጋ እየተዳፋች ወደ ስራዋ ትሄዳለች። ለመናገር ቢያሳፍርም ማትሪክ አልፌ አራት ኪሎ ዩንቨርስቲ ስገባ እጄን ይዛ የሄደችው እሷ ነበረች። የሶስተኛ አመት ተማሪ እያለሁ በዩንቨርስቲ ውስጥ ብጥብጥ ተነስቶ እንዳንወጣ ተከልክለን ነበር። የዛን እለት ከለሊቱ ዘጠኝ ሰአት ዶርሜ ያለቅጥ ሲንኳኳ ደንግጬ ተነሳሁ። የጥበቃ ጓዱ እናቴ እደጅ እንደቆመች ነገረኝ። እየተበሳጨሁ ስሄድ አገልግል አሸክማ፣ ልጆቿን አስከትላ፣ ከሁለት ሰአት በላይ በእግሯ ተጉዛ መጥታለች።...ከዛም አልፉ የልጅነት ጓደኞቼ ከሁለት አስርተ አመታት በላይ የእሷም ጓደኞች ነበሩ። "የሁሉም አትሁን፣ በኋላ የማንም ሳትሆን ትቀራለህ!" የሚለው ንግግር የዘወትር ምክሯ ነበር። ከአፉ ላይ የማይጠፉ። እኔም ለትዝታ እንዲሆነኝ የዚህ መጽሀፍ መሪ ቃል "የሁሉም የሆነች፣ የማንም ያይደለች!!" አልኩት። አዲሳአባን በእናቴ የዘወትር ልሳን ውስጥ ወድቃ በማግኘቴ። አዲሳአባ የሁሉም ናት! ሁሉም ግን የእሷ አይደለም!!... ነዋሪ አልባ ከተማ።

"ጠይሚ ሴት!" በልቅሶ ቤት እንጉርጉሮዋ ብቻ የምትታወቅ አልነበረችም። ሀዘንተኛን በማጽናናት፣ የድብርት ድባብን በመግፈፍ ድንኳን ሙሉ በሳቅ የምታፈነዳ ተጫዋች ነበረች። እሷ እና ጓደኞቿ ካሉ ጥርስ አይከደንም። እርስ በራስ በሚያደርጉት "ውረጅ እንውረድ!" ሙግትና መበሻሸቅ ሀዘንተኛውን ለጊዜውም ቢሆን ፈታ እንዲል ያደርጉታል።

ታዲያ የአካባቢው ነዋሪ ከአፏ ላይ በማይጠፉ አባባሎች ያውቃታል። ድግሱ ያላማረ ቦታ ሄዳ ከመጣች "የጨረባ ተዝካር!" በማለት ትገልፀዋለች። እቃ በድንገት ሲወድቅባት አሊያም ያላስደሰታት ነገር ካየች "የባሪያ ለቅሶ!" ትላለች። ያልደመቀ ልቅሶ፣ ልቅሶ አይደለም። መጥፎ ባህል። ታዲያ ይሄ አባባሏ ያልታሰበ ብስጭት ቀስቅሰባት ያውቃል።

እንዲህ ነበር የሆነው፣

ከእለታት በአንዱ ቀን እሷና ታላቅ እህቷ ፀሀይ አማረ ልቅሶ ሊደርሱ ወደ አንድ ትልቅ ሰው ቤት ይሄዳሉ። የሞቱት አዛውንት የሰውየው አባት ነበሩ። ሀዘን የተቀመጡት ትልቁ ሰው በደርግ የቀበሌ ሸንጎ ውስጥ የነበሩ እና ከአካባቢው በኑሮ ደረጃቸው ልቀው የሚታዩ ናቸው። በወይራ ሰፈር የመጀመሪያው የቀለም ቴሌቪዥን የነበራቸው። ከኢትዮጵያ ውጭ ፈረንጅ ሀገር ይመላለሳሉ። ፈረንጂኛም ይናገራሉ። የአካባቢውን ሰው በመርዳትም ይታወቃሉ። በዚህ ሰናይ ምግባራቸው ምክንያት አስተዛዛኙ ድንኳኑን ሞልቶ ይጫወታል።

የእራት ግብር ደርሶ መቅረብ ሲጀምር ወጥ አሳላፊዋ ሴት ተደናቅፉ ልትወድቅ ስትል ጠይሚ ሴት "የባሪያ ለቅሶ!" ብላ ትጮህለች። ድንኳኑ ረጭ ይላል። ታላቅ እህቷ ተደናግጣ ብትጠቅሳት፣ ብትቆነጥጣት አልገባትም። ትንሽ ቆይቶ ውህ የሚያድለው ወጣት የያዘው ትሪ አምልጦት ሲወድቅ የአፍ ልማድ ነውና "የባሪያ ለቅሶ!" የሚል ድምጽ በድጋሚ ታሰማለች። በሁኔታው የተበሳጩት ትልቁ ሰው የተቆጣ ጥቁር ነብር መስለው ከድንኳን ወደ ቤት ይገባሉ። ድንኳኑ በማጉረምረም ሳቅ ይሞላል። ሁኔታው ያላማራት እህቷ ወደ ጆሮ በመጠጋት፣

"ልጄን አሞታል ብለው ነገሩኝ። በአስቸኳይ እንሂድ" ትላታለች። እህታማቾቹ ተሯሩጠው ወደ ቤት ይመጣሉ። እቤት ሲደርሱ ፀሀይ አማረ በራሷ ሳቅ ታጅባ፣

"አንቺ ሴትዮ ይሄን መጥፎ ልማድ ተይ አላልኩሽም? ብቆነጥጥሽ እንኳን አይገባሽም። ሰውየው ተቆናጥሮ ሲወጣ እና ህዝቡ ሲስቅ እንዴት አታስተውይም። ሚቹ ሽማግሌ በሀይለስላሴ ዘመን ገበሬ እና ወለቴ አድርገዋቸው እንደነበሩ እያወቅሽ!..."

እናቴ ልታስጨርሳት አልቻለችም። የአክስቴም የቁጣ መንፈስ ተቀየረ። ሆዳቸው እስኪቆስል ተንተከተኩ። በህይወቴ እንደዛ ለማያቋርጥ ሰአት ስትስቅ አይቻት አላውቅም። ጠዋት ወደ ስራዋ ለመሄድ ስትነሳ እንኳን "ወይ መጥፎ ልማድ!" እያለች አንገቷን ትነቀንቅ ነበር። እፍረት ይዟት ለአንድ ቀን ከሀዘን ቤቱ ቀረች። ትልቁ ሰው "ወይዘሮ እቴነሽ የቀረችው ምን ሆና ነው? እሷ ከሌለች እኮ ቤቱ አይደምቅም!" ብለው መልእክት ላኩባት። በሀዘኑ ወቅት የተፈፀመው ድርጊቱ ግን የምንግዜም የሳቅ ምንጭ ሆኖ ከረመ። እህቶቿ ዛሬ አጠገባቸው ባትኖርም የትዝታቸው አካል አድርገውት ላለፉት አርባ ቀናት እያነሱ ሲጥሉት ነበር።

***

ግንቦት 6 1997 ከምሽቱ ሶስት ሰአት ወላጆቼ ቤት ስደርስ ቤቱ ጥቅጥቅ ብሏል። ወንዶቹ ድንኳን ተክለው መሬቱን እየደመደሙ ነው። ወጣቶቹ ወንበር

ይደረድራሉ። እኔ ቤቴን ትቼ በንጋታው ለሚካሄደው የግንቦት ሰባት ምርጫ በየቀበሌው እየዞርኩ ድንኳን አስተክላለው የአካባቢው አዛውንቶች እንደራሳቸው ቤት እኔን ተክተው በንጋታው ለሚውለው የእናቴ ተዝካር ይፈጋሉ። ሴቶቹም ወገባቸውን ቋጥረው እዛም እዛም ድስት ጥደዋል። ከማመስገን ውጭ ሌላ የምለው የለኝም እና አየዞርኩ አከብሮቴን ገለጽኩ። ዘር እና ፓለቲካ መሰረት ሳያደርግ እንደ ድርና ማግ በተያያዘ ማህበረሰብ ውስጥ በመፈጠሬ ልዩ ስሜት ተሰማኝ። ርግጥ የሚነፍሰው ንፋስ ይገባኛልና ከአብሮአደጐቼ እና ከአካባቢው ሰዎች ሁለት የተደበላለቁ ስሜቶችን አነብ ነበር። በአንድ በኩል እንደ ምርጫ 92 በተወለድኩበት ቦታ አለመወዳደሬ የህሊና ረፍት ሰጥቷቸዋል። በሌላ በኩል ከእነሱ የተለየ አቋም ስላለኝ ሀዘን ገብቷቸዋል። ሀገሩን ስላንቀጠቀጠው ቅንጅት ጮክ ብለው ማውራት እየፈለጉ አልቻሉም። በሹክሹክታ ይነጋገራሉ። ይህን በድንኳን ውስጥ ቆሜ እየታዘብኩ አክስቴ ፀሀይ አማረ ጐትታ ወደ ውስጥ አስገባችኝ።

በስስት እያየችኝ፣

"እኔ እናትህ ሀውልቱን እንዴት ጥሩ አድርጌ አሰራሁት መሰለህ። ቅልብጭ ያለ ነው። ይበቃታል! አንተም ላደረከው ነገር ቤተዘመዱ ኮርቶብሀል" አለች። መልስ አልሰጠኋትም። ሀውልቱ ሲጀመር ከማየት ውጪ ሌላ ቀን መመለስ እንኳን አልቻልኩም። ዝምታዮ ቢረዝምባት፣

"ነገ ስታየው አንተም ደስ ይልሀል። ከነገ በኋላ ማዘን፣ ማልቀስ የለም። የዘላለም ቤቷን ሰርተህላታል በሰላም ትተኛበት።" እራሷ እያለቀሰች እኔን ለመጠገን ትሞክራለች። እንባዋን እየጠራረገች፣

"አንተም ቢሆን እዚህ አገር ምን ቀረህ? ጀርመንም ከናዳም ያሉ ወንድሞችህ ለምን አይመጣም እያሉህ ነው። ዛሬ ካናዳ ያለው ደውሎ ነበር። እዚህ ካለነው በላይ በጣም ፈርተዋል። እውነቴን ነው ማን ቀረህ?አሷ እንደሆን ላትመለስ ሄዳለች።ለጉብኝት ብለህ ቪዛ ብትጠይቅ አይከለከሉህም። በቴሌቪዥን የምትታይ ባለስልጣን ሆነህል። ቤተሰቡ ስላንተ ተጨንቋል።" በእርጋታ ውስጥ ሆኜ፣

"እትዬ! ምን አዲስ ነገር ይመጣል ብለሽ ነው?" አልኳት።

"አዬ እውነት የሚወራውን ሳትሰማ ቀርተህ ነው።አለቃህ መለስ ዜናዊም እንደ መንግስቱ ሀይለማርያም ሊሸሽ መሆኑን አልሰማህም። አንድ ጥይት እስኪቀር ምናምን አለማለቱም ትልቅ ነገር ነው፣ ሌላውም ባለስልጣን ሻንጣውን እየሸከፈ ነው። ወደ ውጭ ሀገር ገንዘብ እና ቤተሰባቸውን እያሸሹ እንደሆነ ድፍን ሀገሩ እያወራ ነው።"

ከልቤ ሳቅኩባት።

"አንተ ምንታደርግ! የሚወራው ሁሉ ከባድ እንደሆነ ማንም አይነግርህ። ቤተክርስቲያን ዛሬ ፀሎቱ እና ትምህርቱ ይሄ ነበር። ህዝቡ እየዛተ ነው። ሆ! ብሎ ለመነሳት ቆርጧል።ከኑግ የተገኘ ሰሊጥ ከምትሆን ሰው የሚልህን ብትሰማ

ጥሩ ነው። እናትህ እማዜር ስለሚወዳት በጊዜ ጉዷን ሳታይ ወሰዳት። ይሄኔ እንጦሽ ብላ ትፈነዳ ነበር።"

"አይዞሽ እትዬ የሚመጣ ነገር የለም። ሁሉም ነገር በሰላማዊ መንገድ ይጠናቀቃል። ይልቁንስ ከሶስት ሰአታት በኋላ ስለምሄድ ትንሽ እረፍት ልውሰድ። ሁሉንም ስጨርስ በቀጥታ ቤተክርስቲያን ቁርባኑ ላይ እደርሳለሁ።"

"ብቻ በደንብ አስብበት። ጦላይ ድረስ መጥታ የምትጠይቅ እናት አሁን የለችም!"

"ሰሞኑን አልሰማሻቸውም ተቃዋሚዎቹን? ስልጣን ብንይዝ የንብ ምልክታችሁን እንዳደረጋችሁ ትሰራላችሁ ብለዋል።"

መልስ ሳትሰጠኝ በሩን ዘግታ ሄደች።

ለመተኛት ብሞክርም ከመገላበጥ ውጪ እንቅልፍ ሊወስደኝ አልቻለም። የጠቆረ ትዝታ ተፈራረቀብኝ። ዛሬ ያለሁበት ደረጃ እንዴት እንደረስኩ ማሰብ ጀመርኩ። ኢህአዴግን ከመቀላቀል አልፌ ከፍተኛ ካድሬ እስከመሆን ያደረሰኝ ምክንያት ? ...ተመልሶ የማይገኘውን የወጣትነት እድሜዬን በሙሉ ፍላጐት ከኢህአዴግ ፓለቲካ ጋር ተጣብቄ የምኖረው ለምንድነው? ...እነዚህ ጥያቄዎች ፉታ ነስተው እንቅልፌን አባረሩት። እናም ባልተጠበቀ ሁኔታ ወደ ረጅም የህይወት ትዝታ ገፉፍቶ አስገባኝ። ምርጫ 97 ሊጀመር የሰአታት እድሜ ቀርቶት የእኔ ትውስታ ረጅም አመት ወደ ኃላ ተጉዞ ልጅነቴ ላይ አረፈ። ይህ ወቅት አሁን ያለሁበት የህይወት ዘመን መሰረት የተጣለበት፣ ሀዘን እና ደስታ የተፈራረቀበት ነውና ዘለግ አድርጌ ስለ ልጅነት እና ወጣትነት እድሜዬ ላወጋችሁ ፈለኩ። ይህ ማስታወሻ ለአዲሳአባ (ኢትዮጵያ) ወጣቶች ስለተጻፈ እንደማይቆረፍድ ተስፉ በማድረግ።

***

የልጅነት ትዝታ

ተወልጄ ያደኩበት ወይራ ሰፈር እንደ ማንኛውም የአዲሳአባ አካባቢዎች ዝቅተኛ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚኖሩበት ነው። ከፍተኛ የመሰረተ ልማት ችግር የነበረበት ሲሆን በተለይም በክረምት ወራት በአካባቢው መኖር በጣም አስቸጋሪ ነበር። ነዋሪው በተለይም ወደ መሀል ከተማ ስራ ያላቸው እህቶቻችን ክረምት ሲመጣ ሁለት ጫማ መሸከም ግዴታቸው ነበር። አስፓልት ዳር ያሉት የእነ ሸምሱ ሱቆች አንዱ ገቢያቸው የእህቶቻችንን ጫማ በማስቀመጣቸው የሚያገኙት ገቢ ነበር። ከእለታት በአንዱ ቀን የአካባቢው ተወካዮች ችግሩን ይዘው ተፈራ ዋልዋ ጋር ይሄዳሉ። የዋልዋ ልጅ በንጋታው ወይራ ሰፈር በመምጣት ነዋሪውን አናግሮ በሳምንቱ በልዩ ትእዛዝ የአስፓልት መንገድ እንዲጀመር ያደርጋል። ስሙንም ይተክላል።

(በነገራችን ላይ ድሮ ድሮ የወይራ ሰፈር አዛውንቶች በዋልዋ ልጅ ቀልድ አያውቁም ነበር። በየአመቱ እንደ ኢድባር በሚጠቀሙባት እና በሚመራረቁበት ወይራ ሰር ሳይቀር ስሙን አያነሱ ይመርቁት ነበር። "የዋልዋን ኢድሚ ያርዝምልን!!" ተፈ ግርግርም ፓለቲካውን ችሎበት ነበረና በልባቸው መጐዝጐዝ ቻለ። የአስፓልቱ ምርቃት እለት የአካባቢው ህዝብ በፍላጐቱ ገንዘብ በማዋጣት የአስር ሺህ ብር ወርቅ በመግዛት አበረከተለት። ተፈራም የተበረከተለትን ሰጦታ ከአንገቱ በማውለቅ " በሚቀጥለው ጊዜ ለምታሰቡት የልማት ሰራ እንዳዋጣሁ ይቆጠርልኝ!" በማለት ሰጦታውን መለሰ። ከአካባቢው ወጣቶች ግጥም እንድናቀርብ ከተመረጥን ተማሪዎች አንዱ ነበርኩና "እናመሰግናለን!" የሚል ግጥም ለመጀመሪያ ጊዜ ለዋልዋ ልጅ አቀረብኩ። ምንአልባት ተፈራን የማይበት አይን የዛን ወቅት ያሳረፈብኝ ተጽእኖ ይሆን? ...ለበጐ ሰራ እውቅና ከሚሰጥ ማህበረሰብ መፈጠሬም ሊሆን ይችላል። ለነገሩ ማንነታችን ከሚቀረጽበት ቦታ አንዱ የምናድግበት ማህበረሰብ አይደል።)

ሌላው የማስታውሰው ነገር የወይራ ማህበረሰብ ገጠር ካሉ ወገኖቹ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ነበረው። ከእኛም ቤተሰብ አንጻር አባቴ እንደዛ ነበር። ገጠር ካሉ ዘመዶቹ ጋር ትስስር ስላለው አዝመራ በደረሰ ቁጥር ቤታችን በበቆሎ እና ሽምብራ እሸት ይሞላል። የእናቴ ትላልቅ በርሜሎች በተቀቡት ቀለም አይነት ከገጠር የመጣ ጤፍ ይሞላባቸዋል። ቀዩ በርሜል የቀይ ጤፍ ጐተራ ነበር። ነጩ ደግሞ የነጭ ጤፍ። ታዲያ እናታችን የአማቾቿን ውለታ ለመመለስ ለገጠሩ ህዝብ ብርቅ የሆኑ ቁሳቁሶችን ከመስከረም ጀምራ እየሸመተች ታጠራቅማለች። እንደጐተራዋ ሁሉ አማቾቿም የራሳቸው ሻንጣ አላቸው። የቤኛ፣ ለሚቻ፣ ጃንቦ፣ ተሬሳ ...ሻንጣዎች። የአባቴ ወንድሞች።

በየአመቱ የታህሳስ ገብርኤል ንግስ ሲደርስ የቤተሰብ አባላት ተያይዘን የአባቴ የትውልድ መንደር "አዋሽ...ጌጃ" እንሄዳለን። የአካባቢው ተወላጅ በሙሉ ከያለበት ተጠራርቶ ወደ ጌጃ ይተማል። የእኛ ቤተሰብም እናቴ ለወራት ያጠራቀመቸውን ባትሪ ድንጋይ፣ ፉኖስ፣ ስኳር፣ ዘይት፣ ሽቶ፣ አልባሳት... እንደ እድሜያችን መጠን ተሸክመን እንሄዳለን። ጉዞ ወደ ገጠሪቷ የአባቴ ሀገር! አዋሽ ጌጃ!

ወቅቱ ከገብርኤል ንግስ በሻገር የሰርግ ነውና ጌጃ ትደምቃለች። በየገጐጃው መኳት እየታረደ፣ ጠላ እና ጠጅ እየተንቆረቆረ፣ የሽማግሌዎች ምርቃት በላይ በላዩ እየፈሰሰ፣ ጭፈራው እየደራ ለሳምንት ያህል ያለማቋረጥ ይቀጥላል። ታዲያ የሀገር ሽማግሌዎቹ ምርቃት እና ጭፈራውን ስመለከት ሁለት ነገሮች ይገርሙኝ ነበር። ሽማግሌዎች በምርቃታቸው መሀል፣

"የጀግናው ወታደር ለገሰ አስፋው እድሜ ያርዝምልን! ልጆቻችን እንደ እሱ የሀገር ፍቅር እንዲኖራቸው ያድርግልን!" ይላሉ። ለገሰ አስፋው ለአባቴ ጋብቻ ዘመዱ ነው። አባቴ እጅግ ከሚጠየፋቸው ሰዎች አንዱ ነበር። በሚቀርብለት ምርቃት ከልቡ ያዝን ነበር። "ገበሬው ከአብራኩ ስለወጣ ብቻ ወንጀለኛን ማመስገን የለበትም!" ይላል። አባቴ ልክ ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ ከሀያ ምናምን አመት በኋላም ይህን ችግር አለመሻገራችንን ሳይ ያሳዝነኛል። በተለይ የአህዴድ ድርጅታዊ ጉባኤን ስሳተፍ የሚሰማኝ ስሜት የገጃ ሽማግሌዎች ለለገሰ አስፋው የሚያቀርቡት ነበር። የአህዴድ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሆኖ ለመመረጥ መመዘኛው ሌባ፣ ወንጀለኛ፣ አድርባይ አለመሆን አይደለም። ትልቁ ብቃት የመንደርን ሰዎች የሚደራጀት ብቃት ብቻ ነው። የጐጥ ልጆች የያዙት ሆቴል በመሄድ መጋበዝ፣ ያስቀየሙትን ይቅርታ መጠየቅ። በቃ! ሰው ቢገደል፣ ቢበዘበዝ፣ ቢቀጠፍ ጐጡን ማደራጀት እስከተቻለ ድረስ በስልጣን ላይ ስልጣን ይጨመራል።

ሁለተኛው የጌጃ ትውስታዬ ደግሞ ዘፈን እና ጭፈራቸው ነበር። የአባቴ መንደር ሰዎች አሮሞዎች ናቸው። ቋንቋቸውም አሮምኛ ነው። ጭፈራቸው ግን ጉራጊኛ። በአሮሚኛ እየዘፈኑ፣ በጉራጊኛ ይጨፍራሉ። ምንአልባት ትንሽ ወደኋላ ሄዶ ማጥናት ሳያስፈልገው አይቀርም። ማንነትን ማጥናት እና ማወቅ ነውር አይደለም። ክፉት የሚሆነው የፓለቲካ መሳሪያ ካደረግነው ብቻ ነው። የፓለቲካ ግብ ሳይቀመጥ በህሊናችን የሚንገዋለሉ እና ያልተመለሱ ጥያቄዎችንም አንስቶ መነጋገሩ የሚበረታታ ነው። ለምሳሌ የአያቴ ስም ዋቅጅራ ነው። ሁለት የአሮሚኛ ቃላት ተጣብቀው "እግዜር አለ" የሚል ትርጉም ሰጥተውታል። ቅድመ አያቴ ሀዋዝ ይባላል። ሀዋዝ በእርግጠኝነት አሮምኛ ቃል አይደለም። አጐቶቼንም ጠይቄ ስለአያታቸው ብዙ የሚያውቁት ነገር የለም። ታዲያ ሀዋዝ ከየት የመጣ ስያሜ ነው?

እንዲህ እንዲህ እያለ ቀናት ይሄዳሉ። ለሳምንታት ጌጃን በአሮሚኛ እና ጉራጊኛ ጨፍረንባት፣መኩት እና ፍሪዳ በልተን፣አዋሽ ወንዝ ላይ በአሮሞ ባህል መሰረት በተዘጋጁ ሽማግሌዎች ተመርቀን መሰናበቻችን ይደርሳል። ገበሬዎቹ የአባቴ ወንድሞች በሚያስታውቅ ፉከክር ጐተራቸው ይከፈታል። አህያና በቅሎዎች ለጭነት ይሰናዳሉ። አጐቶቼ ቀድመው ባዘጋጁት ስልቻ ነጭ፣ ሰርገኛ ጤፍ እና ሽምብራ ይሞላሉ። በአባቴ ወንድሞች መካከል የእኔ ካልተጫነ በሚል ጭቅጭቅ ይነሳል። እናቴ አስታራቂ ሆና ትገባለች። ከለሚቻ ነጭ ጤፍ፣ከጃንቦ ሰርገኛ፣ ከተሬሳ ሽምብራ ...እያለች ታከፋፍላለች። ደስተኛም ባይሆኑ ይስማማሉ። እኛም የአመት አቅማዳችንን ሞልተን ወደ አዱነነት እንመጣለን።

***

በልጅነቴ ለትምህርቴ የማልቦዝን ነበርኩ። አስታውሳለሁ ስምንተኛ ክፍል የመጀመሪያው ሴምስተር ከአጠቃላይ ትምህርት ቤቱ አንደኛ ወጣሁ። በተለይ የሂሳብ ውጤቴ መቶ ከመቶ ነበር። በዛው አመት ስምንተኛ ክፍል ሚኒስትሪ ወስጄ ባገኘሁት ውጤት የተፈጠረብኝን ስሜት አልረሳውም። የዛሬን አያድርገው እና ለስምንተኛ ክፍል የሚኒስትሪ ውጤት የሚሰጠው ክብር ትልቅ ነበር። ሁሉም በጉጉት ይጠብቀዋል። በተለይ ከ96% በላይ ያመጣ ተማሪ ስፔሻል ክፍል ተብሎ አዲስከተማ ሁለተኛ ደረጃ ለብቻው እንዲማር ይደረጋል።ርግጥም ሚኒስትሪ ወሳኝ ነበር። እናም እኔ ከነበርኩበት ኮልፌ ሰላም በር ትምህርት ቤት አምስት ልጆች ብቻ ከሚፈለገው ውጤት በላይ አመጣን።

እንዲህ እንዲህ አያለ ጊዜያቶች መጓዝ ጀመሩ። ዘጠነኛ ክፍል ስደርስ የሀብታም ልጆችን ማታ ማታ በማስተማር የኪስ ገንዘብ አገኘሁ። በተቃራኒው ጊዜ እንደ ቁምጣ አጠረኝ። አካላዊ ድካሙ ቀላል አልነበረም። በዛ ላይ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ ሆነው እንደ ማትሪክ ተፈታኝ የሚተጉትን የክፍል ጓደኞቼ መወዳደር በራሱ ትልቅ ፈተና ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ በአዲስ ከተማ ስፔሻል ክላስ መማር ዩንቨርስቲ ገብቶ ከመማር ያላነሰ ከባድ ነበር። ከተማይቱ አሉኝ የምትላቸው ጐበዝ ተማሪዎች የተቯጠጡበት። በዚህ ምክንያት አማካይ ውጤቴ 95% ሆኖ አምስተኛ ወጣሁ። ሂሳብ 100%፣ ፊዚክስ እና ኬምስትሪ 98% ነበር ያመጣሁት። አብሮአደጌ አማካይ ውጤቱ ከእኔ ከሁለት ቢያንስም ያገኘው ደረጃ 28ኛ ነበር።

የአስረኛ ክፍል ትምህርት "አትነሳም ሆይ! አትነሳም ሆይ! ይሄ ባንዲራ ያንተ አይደለም ወይ!" በሚል ተደጋጋሚ አመጽና ሰላማዊ ሰልፍ ተናወጠ። እንዘምታለን በሚሉ ተማሪዎች ግፊት ትምህርት ተቋረጠ። ሰልፉም ሆነ የእንዘምታለን ፉከራው አይዋጥልኝም ነበር። ሀገሪቷም ሆነ ባንዲራዋ የሁላችንም መሆኗን ባውቅም አምባገነን የሆነው ስርአት ይህን የማስጠበቅ ቁመና እንደሌለው አባቴ ይነግረኝ ነበር። የአትነሳም ወይ ጫጫታ በማየሉ ምክንያት ትምህርት ተቋረጠ። ለእኔ ለውጥ አልነበረውም። ቀኑን ሙሉ ቁጭ ብዬ አጠና ነበር። በየቀኑ ማታ ማታ ልጆች ማስጠናቴንም አላቋረጥኩም።

***

እንዲህ እንዲህ እያለ ግንቦት 19 1983 ደረሰ። ለብዙዎች በተለይም በደርግ ስርአት ተጠቃሚ ለነበሩ ሰዎች መራራ የሆነችው ቀን አፍጣ መጣች። ኢህአዴግን እንደ አውሬ የሚያየው የአካባቢያችን ህዝብ በፍርሀት ተዋጠ። በመዲናይቱ የመንግስት ተቋማት ላይ ዘረፋው ተጧጧፈ። በተለይ የፈረደበት የቀበሌ ጽህፈትቤት እና የህዝብ ሱቅ የዝርፊያ ማእከል ሆነ። አንድ ስሙን መጥቀስ የማልፈልገው የአካባቢያችን ትልቅ ሰው ህዝብ ሱቅ ሊዘርፍ ሄዶ ባዶ

ሆኖ ሲያገኘው በር እና መስኮቶቹን በመንቀል ወደ ቤቱ ይዞ መጣ። በጥቆማ ተደርሶበት ተሸክሞ መለሰ።

ምሽቱን የኢህአዴግ ሬዲዮ አዲሳአባ ዙሪያ መክበቡን እና በተለይም በቅርባችን የሚገኘው የቀድሞ አየር ማረፊያ በራዳር ውስጥ ማስገባቱን አሳወቀ። ይህን ተከትሎ የመጨረሻዋ ምሽት ጥይት ኡሩምታ ከየቦታው ተሰማ። እነሆ! ግንቦት 20 ብሶት ወለደኝ ያለው የኢህአዴግ ሰራዊት አዲሳአባን መቆጣጠሩ በሬዲዮ ተበሰረ። በዛን እለት ፀሀይ ማዘቅዘቅ ስትጀምር የኢህአዴግን ሰራዊት ለማየት ወደ ጦርሀይሎች ከሰፈሬ ልጆች ጋር ሄድን። የደርግ ካድሬዎች ሲናገሩ እንደነበረው ሶስት አይን፣ ጭራ ያላቸው ጭራቆች እንደሆኑ ለማረጋገጥ።

ጦርሀይሎች በር ላይ ስንደርስ ያገፋረ ፀጉር ያላቸው የኢህአዴግ ታጋዮች በየቦታው ህዝቡን በቡድን በቡድን ሰብስበው ማብራሪያ ይሰጣሉ። ህዝቡም እንዲህ በማለት ይጠይቃል፣

"አስገንጣዮች ናችሁ፣ በኢትዮጵያ አንድነት አታምኑም የሚባለው አውነት ነው?"

"ከደርግ በምን ትሻላላችሁ?"

"ስለ ብሄራዊ እርቅ ምን ታስባላችሁ?" ያገፋረው ታጋይ፣

"እኛ የታገልነው አስከፊውን ስርአት ለመጣል ነው። ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን የመገንባት ስራ የህዝቡ ውሳኔ ነው። የኤርትራም ህዝብ የራሱን እድል በራሱ እንዲወስን እንፈልጋለን።" በማለት ለጠየቁት ሁሉ ያስረዳል። አንዲት እናት በስጋት ውስጥ ሆነው፣

"ቆይ! ቆይ! እናንተም አብዮት ትላላችሁ እንዴ? አብዮት አባቱ ይጥፉና? ደግሞ ትንሽ ቆይታችሁ ፀረ -አብዮት፣ አብዮታዊ ጥሪ እያላችሁ ልጆቻችንን ልትፈጁ ነው። የደርግ አብዮት ሁለት ልጇን በልቶ ልጅ አልባ አደረገኝ። የእናንተ አብዮት ደግሞ የልጆቼን ልጅ ሊበላ ነው?።"

(በወጣትነት አእምሮዬ የተመላለሰው ጥያቄ "አብዮታዊ ጥሪ!"፣ "ፀረ - አብዮት" የሚለው ነበር። አብዮት የሚለውን ቃል ትርጉም አላውቀውም። ያገፋረውን ታጋይ የሚጠይቁት እናትም አያውቁትም። "አብዮት አባታቸው ይጥፉ" በማለት የአብዮት አባትን እስከመሳደብ ያገዳቸው ምድራዊ ሀይል ግን አልነበረም። ስንቶቻችን ይሆን የማናውቀውን ነገር የምንሳደበው?... እውነት ግን አብዮት አባት አለው? የደርግ እና ኢህአዴግ አብዮት አባታቸው አንድ ነው? ኢትዮጵያ ለምትባል ትልቅ ሀገር አብዮት ይመጥናታል? እስከመቼስ በአብዮት ውስጥ ትኖራለች? ...እነዚህ ጥያቄዎች ሳይመለሱ ብዙ ዘመናት ተሻግረው ነበር። ከእለታት በአንዱ ቀን ከአንድ አንጋፋ ምሁር ጋር በመገናኘቴ ምላሽ አገኘሁ።

አጋጣሚው እንዲህ ነበር...

በኢህአዴግ የካድሬነት ዘመኔ ከፐሮፌሰር እንድሪያስ እሸቴ ጋር ወደ ሶስት ሺህ የሚጠጉ የአዲሳአባ ዩንቨርስቲ ተማሪዎችን በስብሰባ ማእከል ሰብስበናቸው ነበር። የግንቦት 20 በአል ለመዘከር። ከተሰበሰቡት ተማሪዎች አንዱ፣

"አብዮታዊ ዲሞክራሲ ምንድነው" የሚል ጥያቄ ወረወረ። በቀኝ ጐኔ ለተቀመጡት ፐሮፌሰር ጥያቄውን ገፉ አደረኩ። እሳቸውም "በአጭሩ አዲስ ነገር መፍጠር፣ ወገንተኛ መሆን... " የሚል ምላሽ ሰጡ። ከትልቅ ሰው የወጣች ትርጉም ናትና በጭንቅላቴ መዘገብኳት። የስንት አመት ጥያቄዬን ፐሮፌሰሩ መለሱልኝ።ከትልቅ ሰው ጋር ትልቅ ቦታ መዋል ትልቅ ምላሽ ያስገኛል። ኧረ! እንኳንም ኮንኮርድ ሆቴል አልተገናኘን... የቀላል እና ትንሽ ሰው መገኛ ቦታ!። የፐሮፌሰሩን ትርጉም ዘግየት ብሎም ከበረከት ሰምኦን አዳመጥኩ። ታዲያ! አዲሱ ነገር ምንድነው? ደርግ "አብዮታዊት ኢትዮጵያ" ይላል። ኢህአዴግ ደግሞ ኢትዮጵያን በዲሞክራሲ ተከቶ "አብዮታዊ ዲሞክራሲ" ይላል። ኢትዮጵያ የምትለው ጉልበተኛ ቃል የተተካችበት ምክንያት "ታላቁ መሪ" ይህቺን ቃል መናገር ስለሚሸከከው እንደሆነ የኢህአዴግ ደጋፊ የሆነው የኢትዮጵያ ሲቪልቲ ፎረም ባለቤት ብርሀኑ ዳምጤ (አባመላ) በቅርብ ቀን ሲናገር ሰምቻለሁ። አባመላ ከታላቁ መሪ ጋር ካለው ቅርበት አንፃር የተሳሳተ መረጃ ሰጥቷል ብዬ ማስተባበል አልችልም። አቶ መለስን በዚህ ደረጃ አውርጄ የመመልከት ስብእና የለኝም። እንዲኖረኝም አልፈልግም። በዚህ የአባመላ ሀሳብ ለተስማማን ግን አዲሱ ነገር እሱ ያለው ይሆናል!)

***

ከአባታችን ሞት በኃላ "ጠይሚ ሴት" ዙሪያው ገደል ሆነባት። ጭንቅላቷ ሊሸከመው የማይችለው ዱብ እዳ ወረደባት። በደህና ጊዜ የተቀለሰ ጐጆ ቢኖረንም ብርሀኑን አጥቷልና በጨለማ ተወረሰ። የእናቴ ውስጣዊ እልህ፣ ቁጣው እና አትንኩኝ ባይነቱ ተጨምሮ በተናደደች ቁጥር አእምሮዋን እየሳተች መውደቅ ጀመረች። "ይህቺን ሴት ተቆጣት! አንድ ቀን መኪና ይበላታል" እስክንባል ድረስ በመንገድ እየሄደች ብቻዋን ማውራት ጀመረች። የእናታችን ተስፋ እየሞተ ሄደ። ርግጥም ከ300 ብር በማይበልጥ ደሞዝ ያውም ብዙ የለመደ ቤት ማስተዳደር ቀላል አልነበረም። መሸቶ በነጋ ቁጥር የሚከፈቱ አምስት ጉሮሮዎች አሉ። በዚህም ምክንያት ሁላችንም እሷን ለማገዝ መጣር ነበረብን። በአንድ በኩል እየሞተ ያለውን ተስፋዋን መጠገን፣ በሌላ በኩል ፍቅራችንን ማላየት ከፊታችን የተደቀነ ከባድ ፈተና ሆነ። ይህ ወቅት ከእሷ አንፃር ብቻ ሳይሆን የእኔም የህይወት መንገድ የተቀየረበት ሆነ። ምንም እንኳን የ14 አመት እና የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ብሆንም።

ከዚህ መጥፎ ወቅት በፊት እየጓጓሁ የምጠብቃቸው ነገሮች ትርጉም አልሰጠኝ አሉ። በተለይ ድንቡሎ አጠራቅሜ እና ከእናቴ ተደብቄ ስቴዲዮም የምገባውን እርግፍ አድርጌ ተወኩት። ኧረ! ፊሪም ሆኖ ነበር። የአቃቂን ወንዝና ግድብ በጀርባዬ እየቀዘፍኩ ሁለት ሶስት ዙር የማቋርጥ ጅግና የመልካቆራኒ(ቀራንዮ) ትንሽ ጅረት መሻገር ፈራሁ። ለነገሩ በዚያን ሰሞን ኢንፊሌ እና አቡሹ የሚባሉ የልጅነት ጓደኞቼ የአቃቂ ወንዝ በልታቸው በቤተሰብ ላይ የደረሰው መሪር ሀዘን ከባድ ስለነበር አደጋውን ወደ እኛ ቤት ገልብጬው ነበር። ያቺ ምስኪን ሴት በስንቱ ትጐዳ! ...እንደ እውነቱ ከሆነ የመኖርህ መሰረት የሆነው ሰው እስካለ ድረስ ወይ ፈሪ አሊያም ከመጠን ያለፈ ደፋር ትሆናለህ። የመሀል መንገድ የለም። በቡድን ደረጃም ቢሆን ተመሳሳይ ነው። የህልውናዬ መሰረት የምትለው ህዝብ ግፍና መከራ ላይ ነው ብለህ የምታስብ ከሆነ እስከ ጫካ የሚያስገባ አደገኛ ውሳኔ በመወሰን ትወይናለህ። አሊያም በተቃራኒው "ጆሮ ዳባ" ልበስ በማለት እርግፍ አድርገህ ትተዋለህ። እንደ ልደቱ ፓርቲ አጥር ላይ የምትቆመው የማንነት መሰረት ከሌለህ ብቻ ነው።

ፍርሀቴ በዚህ ብቻ አልበቃም። አብሮ አደጐቼ በካርታ ወጣ ገባ እና በመኪና ሞላ ጐደል ቁማር ሲጫወቱ "እናቴ ታዝንብኛለች!" በማለት ተመልካች ነበርኩ። ርግጥ አብሬያቸው ወደ ጫካ በመሄድ ካርታ ሲጫወቱ እመለከታለሁ። አልፎ አልፎም በጦር ሀይሎች አስፓልት ላይ ያለፈው መኪና ታርጋ የመጨረሻ ቁጥር ሙሉ ይሁን ጐደሎ ምስክር እሰጣለሁ።

(ከአብሮአደጐቼ የልጅነት ቁማርተኞች የማይረሳኝ አበበ ኢፉ ነበር። ዛሬ በአሜሪካን ሀገር ሜሪላንድ ግዛት ይኖራል። በየቀኑ ካልደወለልኝ ይጨንቀዋል። አቤ!ቁማር አይቀናውም ነበር። ኪሱ የነበረች ሸልንግ በሙሉ አራግፎ ወደ ቤቱ ይገባል። እናም እናበሸቀው ነበር። በተለይ በእኔ ማብሸቅ ይናደድ ነበር። ስለማልጫወት አልበላ/አልበላ። በጨዋታ ውስጥ የሌለ ሰው ሲያበሽቅ እንደሚያናድድ ያረጋገጥኩት ከዛ በኋላ ነበር። አቤ! ቀን ይጠብቅልኝ ነበር።ከአለታት በአንዱ ቀን ማጠናከሪያ ትምህርት እየተማርን የሂሳብ መምህሩ ጥያቄው ይከብደዋል። ከአንድ ጊዜም ሶስቴ ወደ ብላክቦርድ በመሄድ ሰራሁለት። በዚህ የተደሰተው አስተማሪያችን ስሜን እየጠራ "የሂሳብ ሊቅ ይሆናል" በማለት አስጨበጨበልኝ። ቅጽል ስም ከማውጣት ቦዝኖ የማያውቀው አበበ "ምን ሊቅ ነው! ሊጥ ነው!" አለኝ። ለአራት አመታት ስሜ ተረስቶ "ሊጡ!" ተባልኩኝ። ...ዘመን አልፎ ከአመታት በኃላ አቶ መለስ ዜናዊ በዶክተር ካሱ ተናዶ "ዘላለምህን ያልቦካ ሊጥ ይዘህ ትመጣለህ!" ብሎ መናገሩን ከጉራጌ ካድሬዎች ጋር በእሳት ዳር ጨዋታችን በተደጋጋሚ ሰማሁ። እናም

ፈጠን ብዬ "ታዲያ ለምን ስም አናወጣለትም?" አልኳቸው። ተስማምተው አድሱን ለእኔ ተሰጠኝ። "ሊጡ!" አልኩት። ስድስት የቢራ ብርጭቆዎች ከፍ ብለው እርስ በራስ ተገጫጩ ...ቺርስ!! ...ለአራት አመታት "ሊጡ" እና "አስጠቂው" የሚሉ ስያሜዎች እየተቀያየሩ ዶክተር ካሱን አገለገሉ። እኔም ከአቤ ጋር የነበረኝን የፍራቻ ሂሳብ በዶክተር ካሱ አወራረድኩ።)

***

የአራት ኪሎ ትዝታ

የነበረው እንዳልነበር ሆኖ አዲሳአባ ወደ መደበኛ ኑሮዋ ተመልሳለች። አመታት እየሮጡ ነው። እንደተጠበቀው ማትሪክን አልፌ አዲሳአባ ዩንቨርስቲ አራት ኪሎ ሳይንስ ፋክልቲ ገባሁ። የማቲማቲክስ ተማሪ ሆንኩ። ፍላጐቴ ስለነበረ ብዙም አልተቸገርኩም። በአዲስ ከተማ ስፔሻል ክፍል ውስጥ ለአራት አመት በአንድ ክፍል ውስጥ ከተማርን ጓደኞቼ ከ25 በላይ የምንሆነው አራት ኪሎ ገባን። ግንኙነታችን እንደ ድሮው መፎካከር ላይ የተመሰረተ ሳይሆን የወንድም እና እህት ያህል ሆነ። ርግጥም የሚያስቀና ነበር።

ገሬን ለገሬን የፓለቲካ እና አይዲኦሎጂ ግንዛቤዬን ለማሳደግ የተለያዩ ጥረቶች ማድረግ ጀመረኩ። ለኢህአዴግ ወትሮም ጥላቻ አልነበረኝምና ፓርቲው የሚጠራቸው የወጣቶች ፎረም እሳተፋለሁ። ኢህአዴግ ዘመም መጽሄቶች፣ ጋዜጣዎች እና መጽሀፎች አነፍንፌ አነባለሁ። የመንግስት ሬዲዮ እና ቴሌቪዥን እከታተላለሁ።

ከቴሌቪዥን ፕሮግራም ጋር በተያያዘ በዩንቨርስቲ ተማሪዎች ዘንድ አንድ የተለመደ ነገር አለ። ተማሪዎች በሚኖሩበት እያንዳንዱ ብሎክ የቴሌቭዥን ክፍል (tv-room) የሚገኝ ሲሆን ተማሪዎች የሚፈልጉትን ፕሮግራም መርጠው ይከታተላሉ። ታዲያ የተማሪዎችን እንቅስቃሴ አተኩሮ ለተመለከተ እዛው ሳለ የፓለቲካ ፍላጐታቸውን ማወቅ ይችላል። ፊልም፣ የእንግሊዝና ጣሊያን ክለቦች እግርኳስ እና ህብረት ትርኢት ፕሮግራም ላይ ክፍሉ ጥቅጥቅ ብሎ ይሞላል። Acapuco Bay የሚባለው ተከታታይ የፍቅር ፊልም በተማሪዎች ተወዳጅ ነበር። እንደዛሬው "ማንቼ" እና "አርሴ" ሳይሆን የጣሊያን ክለቦች ገዝፈው ይታዩ ነበር።

ዜና፣ <u>ሪፓርታዥና</u> ሌሎች ኢህአዴግ ተኮር ፕሮግራም ገና ሲጀምር ተማሪው ውልቅ ብሎ ይወጣል። እኔን የመሰሉ ጥቂት ተማሪዎች እና የትግራይ ልጆች እንቀራለን። ይህ አጋጣሚ ነበር በህውሀት ካድሬዎች አይን ውስጥ እንድገባ ያደረገኝ። በተለይም አስፋው ወሰን የሚባል የጂኦሎጂ ተማሪ እና

በየጊዜው ስሙን እየለዋወጠ የሚኖር ጐልማሳ ጋር እንድተዋወቅ አደረገኝ። ጐልማሳው ለብዙ አመታት ዩንቨርስቲ ውስጥ የሚኖር ሲሆን ዋነኛ ስራው ተማሪዎችን መሰለል ነበር። እንደዚህ አይነት ሰዎች በተማሪዎች ዘንድ "የማይመረቁ ተማሪዎች" በመባል የሚታወቁ ሲሆን በሁሉም ፋከልቲዎች ይገኛሉ። በዚህ አመት ጂኦሎጂ የሚማሩ ከሆነ ከሰስት አመት በኃላ ተከርብተው ፊዚክስ ሊያጠኑ ይችላሉ።

(እንደዚህ አይነት አሰራር መኖሩን ያረጋገጥኩት በካድሬነት ዘመኔ ነበር። ከምርጫ 97 በኃላ ውጤታማ እንዳልነበረ በመገምገሙ እንዲቀር ተደርጓል። በምትኩ ደሞዝ ከኢህአዴግ ቢሮ የሚከፈላቸው ቋሚ ምድብተኞች እንዲከታተሉት ተደርጓል።)

ከ"ማይመረቀው ተማሪ" ጋር የነበረኝ መቀራረብ ሚስጥራዊ የነበረ ሲሆን ኢህአዴግን ለማወቅ በር ከፈተልኝ። በተለይም የሁለተኛ እና ሶስተኛ አመት ተማሪ ሳለሁ በነበሩት የክረምት ወቅቶች ኢህአዴግ ባዘጋጀው የዘመቻ ፕሮግራም በመሳተፍ ወደ ክልሎች የመሄድ እድል አጋጠመኝ። በዘመቻው ፕሮግራም መሰረት ጠዋት የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን እያስተማርን ከሰአት በኃላ በፍቃደኝነት የፓርቲው ፕሮግራሞች ላይ እንወያይ ነበር። ይህ ሁኔታ በተለያዩ ፓለቲካ ፓርቲዎች መካከል ያለውን የፓለቲካ እና አይዲኦሎጂ ልዩነት እና የመንግስት አወቃቀር እንድገነዘብ እድል ከፈተ። ኢህአዴግን ለማወቅ ይበልጥ ጓጓሁ።

ይህም ሆኖ በዩንቨርስቲ ቆይታዬ ፊትለፊት ወጥቼ ለኢህአዴግ ያለኝን ድጋፍ የማላሳይ እና ለዘብተኛ ነበርኩ። ቢሆንም ውስጥ ለውስጥ ከጓደኞቼ ጋር በመሆን የመምህራ እና ዩንቨርስቲው አስተዳደር ብሉሽነት የሚያሳዩ ጽሁፎችን አዘጋጅ ነበር። የማይመረቀው ተማሪ የኢህአዴግ ውሳኔዎችን በተለይም ሊታፈኑ አሊያም አድማሳቸው እንዲሰፉ የሚፈለጉ ተቃውሞዎች በተመለከተ መረጃ ያደርሰኝ ነበር። ለምሳሌ የተማሪዎች ካውንስል እንዲቋቋም እና እነ ቢኒያም የሚባሉ ተማሪዎች ወደ ካውንስል አመራርነት እንዲገቡ ከጀርባ አመጹን የመራው ይሄ "የማይመረቀው ተማሪ" እና ኢህአዴግ ነበር። እኛ በአጫፋሪነት አገልግለናል። የአመጹ መንስኤ የምግብ ጥራት ችግር ቢሆንም የመጨረሻ ግቡ ኢህአዴግ የሚቆጣጠረው የተማሪ ካውንስል ማቋቋም ነበር።

(ቢኒያም ትምህርቱን እንደጨረሰ የደህንነት መዋቅር ተመደበ። ብዙም ሳይቆይ ክልል ላይ በጥይት ተመቶ እንደሞተ ሰምቻለሁ)

***

የአጋጣሚ ነገር ሆኖ የአዲሳአባ ዩንቨርስቲ ሳይንስ ፋከልቲ በልጅነቴ፣

ንግድ ስራ ፋክልቲውን ደግሞ በካድሬነት ዘመኔ አውቀዋለሁ። ይህ አንጋፋ ተቋም በውስጣዊ እና ውጫዊ ችግሮች በመተብተብ እንደ ካሮት ቁልቁል እያደገ ነው። መሰረታዊ ለውጥ ማምጣት ካልቻለ ተፈጥሮአዊ ሞት የማይቀርለት ይሆናል። በኢህአዴግ የሚደርስበት ጫና፣ የሪሶርስ እና ዘመናዊ ቴክኖሎጂ እጥረት፣ የሚቀበላቸው ተማሪዎች ጥራት እየወረደ መሄድ መሰረታዊ ችግሩ መሆኑ አንደተጠበቀ ሆኖ በመምህራን እና ተቋሙ አስተዳደር ፀረ-ዲሞክራሲ እና ኋላቀር አመለካከት ምክንያት የተበላሸ ሆኗል። በዩንቨርስቲው ያለፍን በተለይም የምእራቡን አለም ዩንቨርስቲዎች ለማየት እድሉ ያገኘን ሰዎች በተገናኘን ቁጥር ትዝታዎቻችን በቁጭት የተሞሉ ናቸው። ፈረንጆቹ መምህራኖቻችን ኮርሳቸውን ሲጀምሩ እና ሲያጠናቅቁ የሚያዘጋጁትን ፓርቲ እየተመለከትን..." ተማሪዬ ምን ያውቃል?" ከሚል የፈተና መርህ የተጠጋጀ ጥያቄ እየተፈተንን ... "C" እና "D" መስጠትን እንደውርደት እና የራስ ድክመት አድርገ የሚቆጥሩ ፕሮፌሰሮች እያስተማሩን ቁጭት ባይገባን ነበር የሚገርመው።

በሳይንስ ፋክልቲው ቆይታዬ ወቅት እጅግ ከሚገርሙኝ ህጐች አንዱ ተማሪዎች ያገኙት ውጤት እንዲመረመረላቸው ሲጠይቁ የሚሞሉት ፎርም ነበር። ተማሪው፣

"መምህሬ የሰጠኝ ውጤት ልክ አይደለም ይታይልኝ፣ ልክ ከሆነ ግን አንድ ግሬድ ይቀነስብኝ" ብሎ ይፈርማል። የምንኮራበት ዩንቨርስቲ እንደዚህ አይነት ድራኮኒያን ህግ የተሸከመ ተቋም ነው። ጨቋኝ፣ ኋላቀር እና የነተበ ህግ። በጥቂት መምህራን እና ሴት ተማሪዎች ዘንድ የነበረው ግንኙነት የሚያስተዛዝብ ነበር። በፋክልቲው የቀድሞ ተማሪዎች የተፈተኑትን ጥያቄ ማግኘት አስቸጋሪ ቢሆንም ለአንዳንድ ሴት እህቶቻችን ከባድ አልነበረም። ይህን ተከትሎ ከእህቶቻችን ጋር ቅርበት ያለን ወንዶች በሌላው መለመናችን እና በእጅ አዙር መጠየቃችን የተለመደ ነበር። ከዚህ በተጨማሪም በሀይማኖት ወገንተኝነት የተመረኮዘ አድሎአዊ ነገሮች ተፈጽመዋል። የማህበረ ቅዱሳን አባል የሆነ መምህር አባላቶቹን ሰብስቦ ቲቶሪያል ሲሰጥ፣ ፕሮቴስታንት፣ ሙስሊም የሆነውም የፈተናው ትኩረት በታዎች ሲናገር ማየት መደበኛ አሰራር ይመስል ነበር። ከዚህ በከፉ ሁኔታ የሰቀሉ ተማሪዎች ዩንቨርስቲው እንዲቀሩ ለቃለ መጠይቅ ሲቀርቡ መንደርተኝነትን መሰረት ባደረገ መልኩ ለአንደኛው "የኢትዮጵያ ህዝብ በማምት ስንት ይሆናል?"፣ ለሌላኛው ደግሞ "የኢትዮጵያ ህዝብ በማምት ስንት ይሆናል? ስማቸውን ጨምረህ ግለጽ?" የሚመስሉ ጥያቄዎችን ታዝበናል።

በአጠቃላይ መልኩ አዲሳአባ ዩንቨርስቲ እንደ ኢህአዴግ ሁሉ ከውስጥ ወደ ውጭ ሲታይ ውስጡ ለቁስ እንደሚባለው አይነት ነበር። ዛሬም ከድጥ ወደ

ማጥ የሚያደርገው ጉዞ የተገታ አይመስልም። እስቲ ቅስናውን እንደተገፈፈ ለፍላፊ ቄስ ሆኖ ጥቂቶቹን ላውጋችሁ።

***

የኢትዮጵያ ባህር ኃይል ሲፈርስ ነጥባቸውን በማየት አራት ኪሎን የተቀላቀሉ ወጣቶች ነበሩ። ለእነዚህ ወጣቶች አንፃራዊ በሆነ መልኩ ሳይንስ ፉክልቲው ይከብዳቸው ነበር። የሚያገኙት ውጤትም በዛው መልኩ ዝቅ ይላል። በእንቅርት ላይ እንዲሉ "ተማሪው ምን አያውቅም" በሚል ቅኝት የሚዘጋጁት ፈተናዎች እነሱን ብቻ ሳይሆን ሌላውንም መቀመቅ የሚከቱ ነበሩ። የጅምላ አጨዳ። እናም አንድ ባህር ሀይል የነበረ ተማሪ ሁለተኛ አመት ሲጨርስ ከዜሮ ነጥብ አንድ(0.1) ባነሰ ውጤት ምክንያት የሚባረሩ ሊስት ውስጥ ራሱን ወድቆ ያገኘዋል። ወጣቱም በቀጥታ የፉክልቲው ትምህርት ፕሮግራሞች ሀላፊ ወደነበረ ማርሻል የሚባል ፈረንጅ ጋር ይሄዳል። ለማርሻል ውጤቱን ከነገረው በኃላ ከሱ ቢሮ እንደወጣ ራሱን እንደሚያጠፉ ይገልጽለታል። ሽማግሌው ማርሻል እጅግ በመበሳጨት፣

"እንዴት ሰው በዜጋው ላይ ይጨክናል። ያስተማረውን ቢፈትን ይሄ ሁሉ ተማሪ አይወድቅም።" በማለት ያጽናናዋል። ባጋጣሚ የውጤት ወረቀቱን ሲመለከት እሱም አስተምሮት "B" ሰጥቶታል። ማርሻል ጊዜ ሳያጠፉ "B" ወደ "A" በመቀየር ወጣቱን ይታደጋል። ይህ ወጣት የዩንቨርስቲ ቆይታው አንድ አመት ቢጨምርም ተመርቆ ለመውጣት ችሏል። በስራው አለም የኮምፒዩተር ከፍተኛ ሙያተኛ ከመሆኑም ባሻገር የአንድ ግል ኮሌጅ መምህር ሆኖ ሀገሩን እያገለገለ ነው።

(ማርሻል በዩንቨርስቲ ተማሪዎች ዘንድ "አባታችን" በሚል ሰያሜው ይታወቃል። ተማሪዎች ውጤታቸው አደጋ ላይ ከወደቀ መጥፎ የሚባለውን መምህር ኮርስ በመሰረዝ (drop) በማድረግ የማርሻልን ኮርስ ይጨምራሉ። የዘራውን ብቻ ለማጨድ የሚፈልገው ማርሻል የፈተና አወጣጡም ቢሆን ተመሳሳይ ነበር። እንዲህም ሆኖ በቂ ካልሆነ እሱ ፊት ሄደው እንባቸውን ያሳያሉ። ሰርዞ ደልዞ ወደ መስመር ያስገባቸዋል። ማርሻል ኢትዮጵያ የምትባለውን ሀገር እና ህዝብ ከልቡ ይወድ ነበር።

እነሆ! ማርሻል አረጀና ኢትዮጵያን ተሰናብቶ ወደ ሀገሩ ሄደ። ወደማይቀረው አለም መጓዙን የተገነዘበው ማርሻል እንዲህ በማለት ተናዘዘ፣

"ወደ ኢትዮጵያ ወሰዳቸሁ ልጆቼ ይቅበሩኝ!"

ማርሻል ሞተ።

አስከሬኑ በኢትዮጵያ አየር መንገድ መጣ። ኢትዮጵያዊ ልጆቹ ከያሉበት ተጠራርተው፣ አዲሶቹ ተማሪዎች ደግሞ ቀድሞ በተከለው ዝና ምክንያት ተሰባሰቡ። "ማርሻል አባታችን" የሚል የሀዘን እንጉርጉሮ እያሰሙ ቀበሩት።

መልካም ስሙንም ከመቃብር በላይ ተከሉ።

በዋሽንግተን ዲሲ እምብርት ላይ የሚገኙትን "ጆርጅ ታወን" እና "አሜሪካን ዩንቨርስቲ" ለመገብኘት ሄጄ ነበር። በዩንቨርስቲው የሚገኙ ህንፃዎች፣ አዳራሾች፣ መማሪያ ክፍሎች፣ ካፊቴሪያ፣ ላይብረሪዎች፣ ሜዳ እና ጀምናዚየሞች ለዩንቨርስቲው አስተዋጽኦ ባበረከቱ ሰዎች ይሰየማሉ። የሰዎቹ የህይወት ታሪክ በመቅረጽ ሲያሜ በተሰጠበት ቦታ እንዲኖር ይደረጋል። ጆርጅ ታወን ዩንቨርስቲ ከዚህም አልፎ የመቃብር ቦታ እንዳለው ተመልክቻለሁ። አሜሪካኖቹ ከህገራቸው አልፈው ሌላ አገር ውስጥ ጀግኖቻቸውን ይዘክራሉ። የአዲሳአባ ዩንቨርስቲ ትልቁ ዩንቨርስቲ በጆኔፍ ኬኔዲ የተሰየመ ነው። ታዲያ! የህክምና ፉክልቲው በእውቁ የቀዶ ጥገና ሊቅ ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ ቢሰየም ምን አለበት? እነ ማርሻል፣ ፕሮፌሰር አለማየሁ ሀይሌ ፣ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ እና የመሳሰሉት ምሁራን መታሰቢያ ቢቀመጥላቸው የማይደሰት ኢትዮጵያዊ ወጣት ይኖር ይሆን?

ነገርን ነገር ያነሳዋል እንዲሉ በአቃቂ ቃሊቲ የተሰራው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደራርቱ ቱሉ ተብሎ ሲሰየም ጭቅጭቅ አስነስቶ ነበር። በእሷ ስም መሰየም የለበትም ከሚሉት ወገን አንዱ ነበርኩ። የምንወዳት ብርቅዬ አትሌታችን በትምህርት ሰኪቷ ውጤታማነት እና ሞዴልነቷ የተመዘገበ ነገር ሰለሌ። አባቶቻችን አበበ ቢቂላ ስቴዲየም ብለው ሲሰይሙ ምክንያታቸው ግልጽ ነበር። ለነገሩ አሁንም ቢሆን አልዘገየም። በአዲሳአባ፣ ባህርዳር ሌሎች ከተሞች ዘመናዊ ስቴዲየሞች እየተገነቡ ነው። አትሌት ሀይሌ ገብረስላሴ፣ ቀነኒሳ፣ ጥሩነሽ፣ መሰረት ደፋር ...በሲያሜ ውስጥ ከግምት መግባታቸው እርግጠኛ አይደለሁም።)

***

ማቲማቲክስ ዲፓርትመንት ውስጥ "አንድ ለእናቷ" ብለን የምንጠራት ጓደኛችን ነበረች። ሲዲሴ ቡላ ትባላለች። አንድ ለእናቷ ያልናት ምክንያት ሶስተኛ አመት ላይ ስንደርስ እንስት እህቶቻችን በሙሉ ተራግፈው እሷ ብቻ ቀረች። አናም አንድ ለእናቱ አልናት። እንደዚህ አይነት ነገር በማቲማቲክስ እና ፊዚክስ ዲፓርትመንት ውስጥ የተለመደ ነው። ለምን እንደሆነ ባይገባኝም። ከክብደት አንፃር ኬምስትሪን የመሳሰሉ ፊልዶች ቢልቁ እንጂ የሚተናነሱ አይደሉም። ላብራቶሪ ውስጥ ውሎ ማደር ያለበት ፊልድ።ይህም ሆኖ ብዙ "ሴት ወንድሞቻችን!" ይደፍሩታል።

ሶስተኛ አመት ስንደርስ ከምንወስዳቸው ኮርሶች አንዱ አድቫንስድ ካልኩለስ (Math-361) ይባላል። በሂሳቢኛ አነጋገር "የፊለጣ ትምህርት" የሚባለው አይነት ነው። በቃ ካባ ተቀጥሮ ጥቁር ድንጋይ እንደመፍለጥ ነው። ለምን እንደምንፈልጥ? ተፈልጦ የሚገኘው ድንጋይ ምን ላይ ሊውል

እንደሚችል የሚያውቁት ጥቂቶች ብቻ ናቸው። የሚያስፈልጠን መምህር ደግሞ አካሉ ይባላል። አካሉ በጣም ጐበዝ፣ ታታሪ እና ጨካኝ ሰው ነበር። ሂሳብና ፊዝክስ ላይ እንደ አልበርት አንስታየን እየፈለጠ፣ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ እንደ ከብት የሚያስብ። ከክፉቱ የተነሳ ገድል የተናገረ ይመስል፣

""A" ለተማሪ አይሰጥም፣ "B" ም ቢሆን እጅግ በጣም ጥቂት (extraordinary) ተማሪ" ብሎ የሚናገር መምህር ነበር። ተማሪዎች በእውቀቱ የሚያከብሩት ሳይሆን በጨካኝነት የሚፈሩት። አንድ የጐደለ ነገር ከሌለ በስተቀር ሰው እንዴት ጐበዝ ሆኖ እንዲፈራ ይፈልጋል?

መምህር አካሉ በካምፓስ ውስጥ በተለያዩ አስገራሚ ድርጊቶቹ ይታወቃል። ይህ ድርጊቶቹ ሲወርድ ሲዋረድ ለእኛም ዘመን ደርሷል። አንድ ጊዜ የአለም ዋንጫ የፍፃሜ ጨዋታ ይሆናል። የአለም ህዝብ አይኑን ወደ ቴሌቪዥን ይተክላል። የዩንቨርስቲው ተማሪዎች ቲቪ ሩም የተሰየሙት ጨዋታው ከመካሄዱ ሶስት ሰዓት አስቀድመው ነበር። ከዚህ ሁሉ ህዝብ እድሉ እያለው ጨዋታውን ያልተከታተለው አንድ ሰው ብቻ ነበር። መምህር አካሉ። ጓደኞቹ እጅግ ተደንቀው ጠየቁት። አካሉ የሚያጠናውን መጽሐፍ እያሳያቸው፣

"ይሄን አለም ዋንጫ ማን ይጫወተው!" ብሎ እርፍ አለ።

ሌላ ወግ ልጨምርላችሁ...

በፉክልቲው ውስጥ "አካሉ -ወክ" የሚባል ነገር ተለምዶ ነበር። በተለይ ፈተና ከታወጀ በኋላ።ይህ ስያሜ የመጣው አካሉ ተማሪ በነበረ ሰአት በሀያ አራት ሰአት ውስጥ የሚጠቀመውን ረፍት በመመርኮዝ ነበር። የአካሉ እለታዊ ህይወት ከመማሪያ ክፍል ሜንሲ ቤት፣ ከሜንሲ ቤት ላይብረሪ፣ ከላይብረሪ ስፔስ ነበር። (ስፔስ የሚባለው ተማሪዎች ቀን ቀን የሚማሩበት፣ ማታ ማታ እያጠኑ የሚያድሩበት ቦታ ነው)። እናም አካሉ የነበረችው አንዲት ረፍት ከምሽቱ አራት ሰአት ላይ ላይብረሪውን ሁለት ጊዜ ዞሮ ወደ ስፔስ ለአዳር መሄድ ነበር። በቃ! አካሉ እንደዚህ ነበር። እራሱን ለማበረታታት ሲፈልግ ደግሞ እንዲህ ይላል፣

"አካልሻ! ዛሬ ቁጭ ብለሽ ካደርሽ ነገ ጠዋት ወፍራም ወተት እጋብዝሻለሁ!" በማለት ራሱን የሚያበረታ እና የሚጋብዝ ትጉህ!

እናም ይሄ ሰው ነበር ድንጋይ እያስፈለጠን የከረመው። እነሆ!የፈለጣ ኮርሱ ማብቂያ ይደርስና የፈተና ቀን ይታወጃል። በአጋጣሚ ሆኖ መምህር አካሉ የሚሰጠን ኮርስ የፈተና ወቅት አርብ ዘጠኝ ሰአት ይሆናል። አንድ ለእናቱ ብለን የሰየምናት ሲዲሴ በላ የምትከተለው ሀይማኖት ከአርብ ፀሀይ ያዝ ማድረግ ጀምሮ ቅዳሜ ሙሉ ቀን ምንም መስራት ይከለክላል። ይህን ስለምናውቅ ተማሪዎች ተስማምተን ሰአቱ ወደፊት የሚጐተትበት ሁኔታ እንዲያመቻች ጠየቅነው። እሷም ለመነችው። ባልጠበቅነው ሁኔታ፣

"ህይማኖት እኮ እየለፋ መኖርና በስበሶ መሞት ነው።" በማለት ፍቃደኛ ሳይሆን ቀረ። ፈተናውም በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳ ተካሄደ። ሶስት ሰአት የተሰጠውን ፈተና ሲዲሴ ቡላ በሁለት ሰአት ለመጨረስ ተገደደች። ውጤቱም እንደተጠበቀው ሆነ። በዚህ ምክንያት የዩንቨርስቲ ቆይታዋ በአንድ አመት ተራዝሞ ከእኛ ጋር ሳትመረቅ ቀረች። እኔና ጓደኞቼ፣

"ደርግ በአራት ኪሎ ገና አልሞተም!" የሚል ርእስ ያለው ጽሁፍ በመዋጮ ጽፈን ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ተደበቀን ለጠፍን። ሁልጊዜም የማይመረቀው ጆሮጠቢ ጓደኛዬ በጽሁፉ ይዘት ቢስማማም አራት ኪሎ የምትለውን አድማሳዊ ቃል አልወደዳትም ነበር።አራት ኪሎ ኢንተርሀምዌይ ሆነችበት።

(መምህር አካሉ በአሜሪካን ሀገር በሚገኝ ዩንቨርስቲ ውሰጥ እንደሚያስተምር በተባራሪ ሰምቻለሁ። እርግጠኛ አይደለሁም። ርግጥ ከሆነ ግን ትላንት የሀገሩ ልጆች ላይ ያደረገውን "ኤ" እና "ቢ" ለተማሪ አይሰጥም ፍልስፍና በሀገረ አሜሪካ ከተገበረው ከወገቤ ጐንበስ ብዬ አክብሮቴን አሰጣለሁ። ከዛ በላይ ለአሜሪካ ተማሪዎች" ተማሪው ምን አያውቅም?" ከሚል መነሻ ፈተና የሚያዘጋጅ ከሆነ እጅግ አደንቀዋለው።)

እንደ አውነቱ ከሆነ የማይዳሰስ እና የማይጨበጡ፣ ብዙዎቻችን በገሀዱ አለም የማናገኛቸው ምንአባዊ ትምህርቶች ላይ መጨከን ተገቢ አልነበረም። ለነገሩ ከሶስተኛ አመት በኃላ የተማርናቸው የሂሳብ ትምህርቶች ጉንጭ አልፋ ሆነው ይሰሙኛል። አልአስፈላጊ የጡንቻ ፍተሻ። እኔ ለአስርተ አመታት አብዮታዊ ዲሞክራሲ የሚባል ጥቁር ድንጋይ ስፈልጥ በመክረሜ ይሆናል በማለት አስብ ነበር። እናም የክፍል ጓደኞቼን እየፈለግኩ ማጠያየቅ ነበረብኝ። አየር መንገድ የሚሰራው ቴዲ፣

"ከሁሉም የሚገርመኝ ቁጥሮች መኖራቸውን እየተመለከትን ለማረጋገጥ ሶስት ገጽ ሙሉ የምንሰራው ማሳመኛ ነው (proof that numbers exist?) ... እንደ ክሮንከር እግዜር መቁጠሪያ ቁጥርን ፈጠረ፣ የሰው ልጅ ደግሞ ሌሎቹን ፈበረከ በማለት ጊዜያችንን ባናጠፋ ጥሩ ነበር" አለኝ።

የዲፓርትመንት ሰቃያችን የነበረው አሰግድ መከላከያ ሚኒስቴር ሄጀ ያገኘሁት ጊዜ፣

"ባከህ ተወኝ ትልቁ ስራዬ excel ላይ በመሰረታዊ የሂሳብ ስሌቶች መጫወት ነው።" በማለት ንዴቱን ነገረኝ።

የአለማያ ዩንቨርስቲ መምህር የሆነው ጐመራው፣

"ነብሳቸውን ይማረውና እንደ ፕሮፌሰር አለማየሁ ተማሪዎቼን በምእናባቸው ስፔስ 99 አስገባና መንኩራኩሯ ስትጠፉብኝ እመልሳቸዋለው" በማለት እየሳቀ አጫወተኝ።

ወግን ወግ ያነሳዋል እንዲሉ የዩንቨርስቲው ማቲማቲክስ ዲፓርትመንት ሲነሳ አብሮ ስማቸው የሚነሳው ፕሮፌሰር አለማየሁ ሀይሌ ናቸው። ስለዚህ ትልቅ ሰው የነበሩንን ትዝታዎች በስሱ ላጫውታችሁ።

ፕሮፌሰር አለማየሁ በመጨረሻው የህይወት ዘመናቸው 3D ጂአሜትሪ የሚባል ኮርስ አስተምረውን ነበር። የፕሮፌሰሩ ኮርስ ባለ ሶስት ዲያሜንሽን ነውና በየቀኑ በምእናብ ይዘውን ወደ ጠፈር(space) ይሄዳሉ። ከትንሽ ሰአት በኋላ እሳቸው ይደናበራሉ። X,Y, እና Z የሚባሉት ቅጦች ይደባለቃሉ። በብስጭት ወደ እኛ ሲዞሩ አፍጠናል።ከመቅጽበት እጃቸውን ወደ አንድ ጓደኛዬ እየጠቆሙ፣

"አንተ እያለህ እንዴት አይምታታብኝ!" ይሉታል። ጓደኛዬ አምታታው ቺፉሞ ይሸማቀቃል። ብዙዎች ይስቃሉ።መጀመሪያ ሰሞን እኔም እስቅ ነበር። በሂደት አምታታው የእሳቸው ክፍል ሲደርስ ሲጨነቅ ሳየው አሳዘነኝ። ፕሮፌሰሩ ጥሎባቸው እንደ ድሮ መምህር አንድ በአንድ አቴንዳንስ ጠርተው ነበር ወደ ማስተማር የሚገቡት። እናም የአምታታው መሳቀቅ እየበረታ ሲሄድ እደጅ ስንወጣ እጠበቅና እንዲህ በማለት አግባባዋለሁ፣

"አይዞህ አምታታው ስያሜ ማንነትን አይገልጽም። የአንተ ጥፋትም አይደለም። ማንም ፈቅዶ ስሜ ይሄ ነው ብሎ የተሰየመ የለም። ደግሞስ በሂሳብ ዲፓርትመንት ውስጥ ጓደኞቻችን ደምመላሽ፣ ሰውበሰው፣ አንጋጋው አሉ አይደል። በፉክልቲው ደግሞ ተንኮሉ፣ አናጋው፣ ቢቸግር፣ ሰጥአርጌ፣ ለጥአርጌ..." አሉ አይደል።

አምታታው በምክሬ ይጽናናል።

አራተኛ አመት እያለን የሰፈሬ ልጅ የሆነች ወጣት ፍሬሽማን ገባች። ቤተሰቦቿ አደራ ሰጥተውኝ ስለነበር እንደወንድም ተንከባከብኳት። ከቀናት በኋላ አምታታው እንደወደዳት ነገረኝ። ላስተዋውቅህ ብለው አሻፈረኝ አለ። እናም እንደወደዳት ኖረ። ከአመት በኋላ እኔ ከአዋሳ እሱ ከመቀሌ መጥቶ አራት ኪሎ ጆሊባር ተገናኘን። ከቦርሳ ውስጥ አንዲት የምስክር ሰርተፍኬት አውጥቶ እያሳየኝ፣

"ይህን ያህል አከብርሀለው። ምክሮችህን መቼም አልረሳቸውም" አለኝ። ሰርተፍኬቱን ሳየው "ኤርሚያስ ቺፉሞ" ይላል።
መገረሜን እየተመለከተ፣

"ያቺን ልጅ እንደዛ እየወደድኳት አልተዋወቃትም ያልኩህ ለምን እንደሆነ ታውቃለህ? በስሜ እንዳትሰቅብኝ ብዬ ነው" አለኝ።

ከልቤ አዘንኩኝ።

ወላጆች ለልጆቻቸው ስም በሚያወጡ ሰአት ምን ያህል ጥንቃቄ

ማድረግ እንዳለባቸው ተገነዘብኩ። እጅግ ስለከነከነኝ ደምመላሽን ቤተሰቦቹ ለምን እንደዚህ አይነት ስም እንዳወጡለት ጠይቄው ነበር። ከሰሜን ኢትዮጵያ የመጣው ደምመላሽ በቁጭት እንደበት፣

"እኔ ስወለድ ከድንበር ጋር በተያያዘ አባቴ በጐረቤታችን ተገደለ። እኔ ሳድግ የአባቴን ደም እንድመልስ ይጠበቃል። ይሄን ካላደረኩ እኔ ደምመላሽ አይደለሁም!" ብሎኝ ነበር። ከዛ በኋላ ለስም እና ስያሜዎች ልዩ ትኩረት ሰጥቼ መከታተል ጀመርኩ። ርግጥም ማህበረሰባችን ደስታውን፣ መከራውን፣ ፍላጐቱን፣ የሚቆጨውን ... ነገሮች ከሚገልጽባቸው ነገሮች አንዱ በሚሰጠን ስያሜ ነው። ባደኩበት ሰፈር "ዋስይሁን" እና "ዲቆ" የሚባሉ ልጆች አሉ። ዋስይሁን ስያሜውን ያገኘው በአባት እና እናቱ መካከል "የእኔ ልጅ አይደለም፣ የአንተ ልጅ ነው" የሚለው ጭቅጭቅ ተነስቶ ትዳር በመፍረሱ ምክንያት የተሰጠ ነበር። "ዲቆ" ደግሞ ነዋሪው ዲቃላ የሚለውን ለማሳየት ተጠቀመበት። ይህ ልጅ ማህበረሰቡ ያሳደገው ሲሆን በጣም ታዛዥ ነበር። በዚህ ምክንያት በድፍን ቀበሌው ይታወቃል። ነዋሪው "ዲቆ" እያለ ይጠራዋል፣ እሱም ሀያ ምናምን አመታት "አቤት" እያለ ይኖራል።

የፕሮፌሰር አለማየሁን ስም ካነሳሁ ዘንዳ አንድ በጅምር የቀረ ስራ እንደነበራቸው አስታውሳለሁ። የሂሳብ ቋንቋዎችን ወደ አማርኛ መቀየር። ርግጥም ከልባቸው ለፍተዋል። ኧረ! እኛንም አስጨንቀውን ነበር። አማርኛን ጥርስ ነቅለንበታል ብለን የምንኮፈስ ሰዎች በራሳችን አፍረናል።

እንዲህ ነበር የሆነው።

ከእለታት በአንዱ ቀን ከተማሪዎች ውስጥ "በፍቃደኝነት መፈተን የምትፈልጉ ካላችሁ?"ብለው ጠየቁን። የሸገር ልጆች የነበርን እና በአንድ ዶርም የምንኖረው ቴዲ፣ ሀይሌ እና እኔ ፍቃደኛ ሆንን። ወደ ቢሮአቸው ወስደውን በእንግሊዘኛ የተፃፈውን ከአማርኛ ጋር የሚያዛምድ አስር ጥያቄ ሰጡን። በግራ በኩል የነበሩት የእንግሊዘኛ ሂሳቦች (Asymptote, Absolute value, Depression, elevation, Graph, constant, Integer, inductive, deductive, Series) ይላሉ። በቀኝ በኩል ያሉት ደግሞ (ልጥጥቅ, ትንቢት, መንስኤ, ያዊት, ንጥር-እሴት, አይነኬ-ይጠን, እጐራ, ፅፍ, እርደት, ንስት) ይላሉ። በቀራንዮ! የትኛውን ከየትኛው እናዛምደው። እኔ በህይወቴ አማኝቼ የማላውቀውን 4/10 አገኘሁ። ሀይሌ 5/10፣ ቴዲ 1/10 አገኙ። ቴዲ ማዘመድ የቻለው Asymptote የሚለውን ከ"አይነኬ-ይጠን" ከሚለው ጋር ነበር። ፕሮፌሰር ተበሳጩ። በተለይ የቴዲን ውጤት እየተመለከቱ፣

"ለመሆኑ አማርኛ ትናገራለህ? ዘመኑ የወለዳቸው የአማርኛ ጠላት የሆኑ ትምህርት ቤት ነው የተማርከው? አንደኛውን አምታታው መጥቶ ቢያምታታው ይሻል ነበር" አሉን። አንገታችንን ሰብረን ወደ ዶርማችን ሄድን። ሰው

እንዳይሰማ ዶርማችንን ዘግተን ተማማልን። የዛን ምሽት ወደ ቆጣችን ስንሄድ ወግ የሚያመጣው ሀይሌ መሀላችንን ዘንግቶ ከት ብሎ ሳቀ። አስከትሎም፣

"ግን እኮ ቴዲ Asymptote የሚለውን ከ "አይነኬ-ይጠጌ" ባያዛምድ ነበር የሚገርመው" አለ።

ነገር ለማዳነቅ "ለምን? እውነትህን ሊሆን ይችላል?" ብዬ ጠየኩት። በድጋሚ እየሳቀ፣

"በዚህ ካምፓስ እንደ ቴዲ አይነኬ-ይጠጌ" አለ?" በማለት ማብራሪያ ሰጠን።

ሀይሌ እውነቱን ነበር።

ቴዲ መልከ-መልካም እና ተግባቢ ነበር። የሀብታም ልጅ ስለሆነ አልፎ አልፎ የእናቱን መኪና ሰርቆ ይመጣል። እኛም እንደራሳችን መኪና ደስ ይለናል። አራት ኪሎን ሁለት ሶስት ጊዜ እንዞራለን። ...ጐረቤት ዶርሞች ሬዲዮ የላቸውም፣ እኛ ግን በቴዲ ምክንያት ሁለት ሲዲ የሚውጥ ቴፕ ነበረን፣ቴዲ ካፌ የሚገባው ለእኛ ጓደኞቹ ሞራል ተጨንቆ እንጂ ምድቡ "Non- cafe" ከሚባሉት ወገን ነበር። እናም ብዙ "ሴት ወንድሞቻችን" ይቀርቡታል። እሱም ሳያማርጥ ይወዳቸዋል። ተራ በተራ አብሮአቸው ይውላል፣ ይስቃል፣ ይጫወታል። በቃ! ዳር ድንበሩ ይህ እና ይህ ብቻ ነበር። ቴዲ ይጠጋል እንጂ አይነካም።እናም መሀላችንን አፍርሰን በካምፓሱ ውስጥ ስሙ የተረሳ እስኪመስል ድረስ" አይነኬ - ይጠጌ" ተባለ።

***

እነሆ! ጥቁሩን ካባ እና መነሳንስ ለማድረግ የስምንት ወራት እድሜ ብቻ ቀርቶናል። አቤት ይሄ ወቅት እንዴት ደስ ይላል!! በካምፓሱ የመጨረሻ ጣሪያ ላይ ያለነው እኛ ነን። ለዩንቨርስቲው እንግዳ የሆኑ የመጀመሪያ አመት ተማሪዎችን "ፍሬው ጦጣ!" እያልን ማደናበር ጀምረናል። በእድሜያቸው እና ቁመታቸው ዘለግ ያሉ ጓደኞቻችን እንደመምህር ሆነው ፍሬሽ ማን ተማሪዎች ክፍል በመግባት የሶስተኛ እና የአራተኛ አመት ኮርሶችን ሌክቸር በመስጠት ግራ ያጋባሉ። ከአስር በላይ ተማሪዎችን አንበርክኮ የቀጣም ነበር። በተለይ ሶስት ጓደኞቻችን ያደረጉት የሚረሳ አይደለም።

እንዲህ ነበር ያደረጉት...

ፍሬሽማን ተማሪዎች ማደሪያ ህንፃቸው ለብቻ ራቅ ብሎ የተሰራ ነው። ውስጥ ለውስጥ እስከ አምስት ደቂቃ ያስኬዳል። ቅድሚያ ማደሪያ የሚሰጣቸው የክፍለሀገር ልጆች ስለሆኑ የተወሰኑት ለከተማ ህይወት አዲሶች ናቸው። ርግጥም አለባበሳቸው፣ አነጋገራቸው፣ ቁጥብነታቸው ከርቀት ያስታውቃል። አንዳንዶቹ ደግሞ ኪሳቸው ሞላ ያለ ነው። ይህን የሚያውቁት ጓደኞቻችን አንድ ተንኮል ያሴራሉ። እናም የሚከተለውን ይዘት የያዘ ማስታወቂያ የፍሬሽ ማን

ህናግ ላይ በመሄድ ይለጥፉሉ፣

" ... እንኳን የእውቀት አምባ ወደሆነው ዩንቨርስቲ በሰላም መጣችሁ። የዩንቨርስቲው አስተዳደር እናንተን ለማገልገል ከመቼውም ጊዜ በላይ ዝግጅቱን አጠናቋል። በዩንቨርስቲው በሚኖራችሁ ቆይታ የምግብ፣ የመጽሐፍት፣ የላይብረሪ፣ የማደሪያ አገልግሎት በነፃ ይቀርብላችኋል። ይህን አገልግሎት እንድታገኙ ፕሮሰስ ማስደረጊያ ለአንድ ጊዜ ብቻ 10 ብር ይከፈላል። ቅድሚያ የከፈለ ቅድሚያ አገልግሎት ያገኛል። በቅድሚያ መክፈል ለምትፈልጉ በነገው አለት ከሚካሄድ የቁርስ አገልግሎት በኋላ ፍሬሽማን ላይብረሪ አጠገብ ባለው ቦታ መክፈል የምትችሉ መሆኑን እናስታውቃለን። አትርሱ! ቅድሚያ የከፈለ ቅድሚያ አገልግሎት ያገኛል..."

እናም የመጀመሪያ አመት ተማሪዎች ዩንቨርስቲውን እያመሰገኑ ከቋጠሯት ገንዘብ ቀይ ቀዩን በመምዘት በወረፋ ይከፍላሉ። ሲኒየሮቹ የሰበሰቡት ገንዘቡ ከአቅማቸው በላይ መሆን ሲጀምር የያዙትን ይዘው ይሰወራሉ። ለሊት ሲመጡ "ፍሬው ጠጣ ሰራንለት!" በማለት በስካር መንፈስ ይጨፍራሉ። ሄዶ ሄዶ ጉዳዩ የዩንቨርስቲው አስተዳደር ጋር ይደርሳል። ተማሪዎቹም እስከ መታገድ የሚደርስ ቅጣት ይጣልባቸዋል።

ከቀድሞዎቹ ሲኒየር ተማሪዎች የወረስናቸውን ፀያፍ ተግባራትም እንደ መደበኛ ህይወት በመቁጠር እንተገብራለን። ለቀጣዩም ተረኛ በቅብብሎሽ ህግ መሰረት እናወርሳለን። የነበረው ሁኔታ ለጥቂቶች ቢሆንም ለደባል ሱስ እስከመዳረግ እና ለበሽታ (በወቅቱ አባባል "ጆከር መሳብ") አድርሷቸዋል። ተማሪው እንደ አቅሙና ፍላጐቱ የተዘጋጁ መጠጥ ቤቶች ነበሩ። ከአቶ መለስ ቤተመንግስት ፊትለፊት የነበረው "ኤጀርሳ ባር" ከተማ ቀመስ ተማሪዎች እየጨፈሩ የሚያድሩበት እና የሚዳሩበት ነበር። ከዩንቨርስቲው ወረድ ብሎ ደግሞ "ይገባዋል" የሚባል ጠጅ ቤት አለ። ቀላል የማይባል ደንበኞቹ ተማሪዎች ናቸው። በኤጀርሳ እና ይገባዋል መሀል ደግሞ በተማሪው አጠራር "DC" የሚባል ሰፈር አለ። ዲስትሪክት አፍ ኮለምቢያ እንዳትመስላችሁ! DC የሚለው ምህፃረ ቃል "Dirty Corner" የሚለውን ለመተካት የምንጠቀምበት ነበር። መንደሯ የተሞላችው ስጋቸውን ሸጠው በሚተዳደሩ እህቶቻችን ነበር። እናም "ኤጀርሳ" እና "ይገባዋል" ገብቶ ስክር ያለው ተማሪ ማሳረጊያው DC ይሆናል። ከመመረቁ በፊት ጆከሩን ይስባል። የስንት አመት የግል፣ የቤተሰብ እና የሀገር ልፋት ገደል ይገባል።

እነሆ! ተዝቆ የማያልቀውን የአራት ኪሎ ትዝታ እያገባደድኩ ነው። በመሆኑም በመጨረሻው አመት በሳይንስ ፋክልቲ ቆይታዬ የነበረኝን የግል ትዝታ ላውጋችሁ እና አራት ኪሎን እንሰናበት።

ከእለታት በአንዱ ቀን በአንድ ዶርም ለነበሩት ጓደኞቼ የግል ትዝብቴን የሚያሳይ ሽሙጥ አዘል መጣጥፍ እና የካርቶን ስእል አሳየኋቸው። በአሸሙሩ እና ስእሉ የተማረኩት ጓደኞቼ ሌላውም ማየት አለበት በማለት በህንፃው ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ለጠፉት። በህንፃው መነጋገሪያ አጀንዳ ወደመሆን ተቀየረ። እስከ አሁንም በወል ባላወኩት ሁኔታ የህንፃው ፕሮክተር ሀላፊ እኔ አንደፃፍኩት በማወቁ ቢሮው ጠራኝ። ጽሁፉ የፓለቲካ ይዘት የሌለው በመሆኑ ብዙም አልተደናገጥኩም። ፕሮክተሩ የዩንቨርስቲው አስተዳደር ውስጥ ያለ ሌላ ሰው ጋር ይዞኝ ሄደ። ሰውየው እንድንቀመጥ እንኳን ሳይፈቅድ፣

"አንተ ነህ የዱርዬ ጽሁፍ የጻፍከው? ጽሁፍ ምን ያህል ዋጋ ሊያስከፍልህ እንደሆነ ታውቃለህ? አስተዳዳሪው ቢያዩት ኖሮ እንደዚህ ቁጭ ብለን አንመክርህም ነበር? ለአሁኑ ለአንድ ሳምንት የምግብ አገልግሎት እንዳታገኝ ተወስኗል። ረሀብ ሲሞሸልቅህ ያጣጣልከው የካፌ ምግብ የሸራተን ሆቴል ይሆንብሀል" አለኝ። መልሴን ሳይጠብቅ ከፕሮቶኮል ሹመ ጋር አባረረኝ። ወደ ደጅ ስንወጣ ፕሮክተሩ፣

"ዝም በለው። ሌብነቱ ይታወቅብኛል ብሎ ስለፈራ ነው። የካፌ ምግብ ጥራት እየወረደ የሄደው ከአቅራቢዎች ጋር መሞዳሞድ ስላለ ነው። በዚህ ደግሞ የሚታማው እሱ ነው። ሌሎች አገልግሎቶችም አስደንጋጭ ደረጃ ደርሰዋል። የተሰበረ አልጋ ዛሬ ተጠግኖ ነገ ይሰበራል። የጽዳት ስራ የሚሰራባቸው ቁሳቁሶች ይገዛልን ብለን ጠይቀን አይገዛም፣ ከዚህ በላይ ማመጽ አለባችሁ!" አለኝ። አያይዞም፣ "ካፌ ገብተህ ብላ። አቴንዳስ ለሚይዘው ልጅ እነግረዋለሁ" አለኝ።

እነሆ! የመመረቂያ ዘመን ደረሰ። የአራት ኪሎ ዩንቨርስቲ የምርቃት መጽሄት ኢዲቶሪያል ኮሚቴ ተመረጥኩ። የስነጽሁፍ ዝግጅት ክፍሉ በእኔ እና ሁለት ተማሪዎች ላይ ወደቀ። የተቋጠረ ቂም ነበረና" የአራት ኪሎ ሽሙጠኛ" በሚል ርእስ አስፉፍቼ፣ የካርቶን ስእሉን ደግሞ በመዋጮ አሳምረን በመጽሄቱ ላይ እንዲወጣ አደረኩ። መጶ የማይሞሉ ተማሪዎች ያነበቡት መጣጥፍ በሚሊዮኖች ተነበበ። በእያንዳንዱ ተመራቂ እጅ ለዘመናት እንደ አልበም እየተገለጠ ለትዝታ የሚቀርብ ሜኑ ሆነ።

"የአራት ኪሎ ሽሙጠኛ" የታዘበው ነገር የሚከተለው ነበር...

በዩንቨርስቲ ህይወቴ የታዘብኩት የመጀመሪያው ነገር የፉክክሊቲው አስተዳደር የፍሬሽማን ተማሪዎችን እንዴት እንደሚበድል እና እንደሚንቅ መመልከቴ ነበር። በተቃራኒው መሆን ሲገባው!... እስቲ አንዳንዶቹን ላንሳ...ለፍሬሽማን ተማሪዎች የተዘጋጀው ላይብረሪ እጅግ በጣም ጠባብ እና ያረጀ ነበር። ተማሪዎች እያጠኑ በላያቸው ላይ ከአንዴም ሁለቴ ኮርኒስ

ተደርምሷል። ከተገረሰሰው ኮርኒስ ጋር አብረው የወረዱት የሞቱ አይጦች የፉሲጋ ዶሮ ያካክሉ ነበር። የፉዚቲው ሽታ፣ እየተቀረፈ ሲወድቅ የተሸከመው አስቤስቶ የሚፈጥረው አቧራ ተማሪዎችን ለበሽታ ይዳርግ ነበር። ሀገሩ ኢትዮጵያ መሆኑ በጀ እንጂ በህግ ያስጠይቅ ነበር። ...በፀጥታ ለማጥናት የመጣው ተማሪ እንደ ገደል ማሚቴ የሚሰሙ ድምጾች ረብሸውት ለመውጣት ይገደዳል። ይህም ሆኖ የፍሬሽማን ተማሪዎች ትልቁ ላይብረሪ ገብተው ከተገኙ እንደ በግ ማንቁርታቸው እየተያዘ እንዲወጡ ይደረጋል። ይህን የሚመለከተው ሲኒየር ተማሪ እየሳቀ አልፎ አልፎም እያጨበጨበ ይሸኛቸዋል። ትላንትና የእሱም እጣ ፋንታ እንዲህ ነበርና። ይህን የታዘበው "የአራት ኪሎ ሽሙጠኛ" የመጀመሪያው ምልከታው እዚህ ላይ እንዲሆን አደረገ።

እነሆ! ሽሙጠኛው ከአመት በኃላ በዩንቨርስቲው በኩል ሲያልፍ የፍሬሽማን ላይብረሪ በቦታው የለም።

ሁለተኛው የሽሙጥ ትኩረት የፉክልቲው ክሊኒክ ነበር። ማንኛውም ተማሪ የትኛውንም አይነት በሽታ ይታመም የሚሰጠው መዳኒት አንድ ለእናቱ ብቻ ነበር። በአስቤስቶው አፍንጫው የተደፈነው፣ በጭንቀት የራስ ምታት የያዘው፣ እንቅልፍ እምቢ ያለው፣ DC ተንጐዳጉዶ በጨብጥ የተጠቃው በሙሉ የሚሰጣቸው ፍቱን መዳኒት እንደ ነጭ ሽንኩርት ያቺው ነበረች። ይህን የተገነዘቡት ተመራቂ ተማሪዎች የዛችን ኪኒና የገበያ ዋጋ ፉርማሲ በመሄድ ያጠናሉ። በቃ! ከዛ በኃላ ሁሉም መታመም ጀመረ። የጠበሸው ተማሪ ይመጣና "ለዛሬ ታመመ.ልኝ!" ብሎ ተማሪዎች ሰብስቦ ይጠይቃል። ሁሉም በቡድን በቡድን ይታመመ.ለታል።

እንደ እውነቱ ከሆነ ሶስተኛው ሽሙጥ መለስተኛ ዋጋ አስከፍሎኛል። ቅር የተሰኙብኝ እህቶቼ ነበሩ። ርግጥ ያልሆነ ነገር ስለጻፍኩ ሳይሆን ምልከታዬ ስላበሳጫቸው ነበር። እስከመጨረሻ ያኮረፉኝ ሴቶችም ነበሩ። እስቲ ፍርዱን ለአንባቢ ልተው እና ወደ አሽሙሩ ልውሰዳችሁ።

እንዲህ ነበር የተጻፈው...

ዩንቨርስቲው የሚቀበላቸው የሴት ተማሪዎች እየጨመረ ይሄዳል። ይሄን ተከትሎ ወንዶች ይኖሩበት የነበረው ህንፃ ቁጥር 407 ለፍሬሽማን ሴቶች ይዘጋጃል። ሲኒየር ሴቶች ቀድሞ በነበሩበት ህንፃ እንዲፀኑ ይደረጋል። ይህን ተከትሎ የካምፓሱ አስተዳደር ሁለቱን ብሎኮች ለመለየት እንዲያስችል ሁለት ትላልቅ ማስታወቂያዎች በህንፃዎቹ ግርግዳ ላይ ይለጥፋል። ፍሬሽማን ተማሪዎች ላይ የተለጠፈው ማስታወቂያ "Girles Dormitary"፣ ሲኒየሮቹ ጋር ደግሞ "Womans Dormitary" ይላል። ሽሙጠኛው የጨመረው የቀነሰው

ነገር የለም። እንግሊዘኛውን ወደ አማርኛ ከመተርጐም ውጪ። ዩንቨርስቲው ስህተቱን ማመኑን ባላውቅም ማስታወቂያውን በብርሀን ፍጥነት ቀይሮታል። የተበሳጨብኝ እህቶቼ ግን ወደ ሴትነት ተቀይረውም አልረሷትም። በአጋጣሚዎች ስንገናኝ "የምንረሳልህ እንዳይመስልህ! የምረቃ መጽሐፉን በገለጥን ቁጥር እናስታውስሀለን" ይሉኝ ነበር።

አራተኛው ሽሙጥ የካርቶን ስእል ነበር። ሁለት ጓደኛሞች መመገቢያ ካፌ ቁጭ ብለው ምሳቸውን እየበሉ የሚያወሩትን የሚያሳይ። በምስሉ ላይ አንደኛው ተማሪ እንደ ጐማ የጠነከረ ስጋ የያዘ አጥንት ለመንጨት ይታገላል። ስጋውን ማላቀቅ ሲያቅተው ለጓደኛው እንዳልቻለ ይነግረዋል። ጓደኛውም እንደ ማፌዝ ባለ ምስል፣

"በቃ ተወው። በእራት ሰአት እሳት አግኝቶት ስታገኘው ሊነጭልህ ይችላል!" የሚል ምላሽ ይሰጠዋል።

***

የኮሜርስ ትዝታ

የአዲሳአባ ንግድ ስራ ፉክልቲ የተቀላቀልኩት በኢህአዴግ ካድሬነቴ ዘመን ነበር። በቆይታዬ ፉክልቲው እንደ አራት ኪሎም ባይሆን ችግሮች እንዳሉበት ተመልክቻለሁ። ከመምህራን ውስጥ "ስሜ ሚስተር ኤፍ (Mister F) ነው" በማለት ያወጁ አሉ። እንደጅግንነትም ይናገሩታል። ሌላው አሳፋሪ ነገር የተመለከትኩት የፈተና አወጣጣቸው ወጥ አለመሆን ነበር።

ይህ ወቅት የካድሬነት ዘመኔ ከመሆኑም ባሻገር ከተማሪዎቹ ጋር ድርጅታዊ ኔትወርክ የፈጠርኩበት ስለነበር፣ በተማሪዎች የተካሄደውን አመጽ ከጀርባ ድጋፍ ሰጥቻለሁ። በወቅቱ ተማሪዎችን በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ለማጥመቅ በምመራው ስልጠና የመንግስት ዩንቨርስቲ ተማሪዎች በተደጋጋሚ የሚያነሱት ጥያቄ ነበር። ከምርቃት በኃላ ራሳቸውን ለገበያ በሚያቀርቡ ሰአት ከግል ተቋማት ተማሪዎች ጋር መወዳደር አልቻልንም፣ የእነሱ ጂፒኤ ላይ መድረስ አልቻልንም የሚል ነበር። ርግጥም በአንዳንድ ድርጅቶች ጂፒኤ እንደ ዋነኛ መለኪያ እየተወሰደ ስለነበር የመንግስት ተቋም የተማሩ ተማሪዎች መቀጠር አልቻሉም። ይህን ቅሬታ በመንተራስ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ጥናት ወደ መስራት ተሸጋገርን።

የጥናቱ ውጤት ካመላከታቸው ነገሮች ዋነኛው የፈተና አወጣጡ ፍትሀዊነት እና ወጥነት የጐደለው መሆኑን ነበር። አንዳንድ የኮሜርሻል ኮሌጁ መምህራን በፓርታይም ተቀጥረው የግል ተቋም ያስተምራሉ። ሌሎቹ ደግሞ ተሰባስበው የራሳቸውን ኮሌጅ ከፍተዋል። ታዲያ! ለተመሳሳይ ቁጥር ላላቸው

ኮርሶች በመንግስት እና የግል ተቋማት የሚቀርበው ፈተና የሰማይ እና ምድር ያህል ይራራቃል። እንደዚህ አይነት ስብእና ያለው መምህር ስለ ትምህርት ጥራት የሚያወራ ህሊና ሊኖረው አይችልም።

***

በምርጫ 97 ማግስት የተፈጠረውን ግርግር ለማቀዝቀዝ ከተያዙት እቅዶች አንዱ የዩንቨርስቲ ተማሪዎችን በክረምት ማወያየት ነበር። በዚህም መሰረት ወደ ድሬደዋ ሄጄ እንዳሰለጥን ተመደብኩ። በወቅቱ በቃኪልቲው የምወስደው ኮርስ ማናጅሪያል ስታቲክስ የሚባል ነበር። መምህሬን የምሄድበት ምክንያት በቅንነት ነግሬው ለሁለት ሳምንት ፍቃድ ጠየኩት። ደብዳቤ ይዤ እንድመጣ ስላዘዘኝ ከኢህአዴግ ቢሮ ይዤለት መጣሁ። በፈገግታ ውስጥ ሆኖ ፈቀደልኝ።

በድሬደዋ የተከፈተው የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተማሪዎች መድረክ በካድሬነቴ ዘመን ካጋጠሙኝ ሁሉ በጣም አደገኛ እና ፈታኝ ነበር። ወትሮ በኢህአዴግ የሚከፈቱ መድረኮች ክርክር የሚካሄደው በሰብሳቢው እና በተሰብሳቢው መካከል ለሁለት ተከፍሎ ነበር። ተሰብሳቢው በአንድ መስመር ይሰለፋል፣ ሰብሳቢው በሌላ ጐራ። ከዚህ በተጨማሪም በኢትዮጵያ ፓለቲካ ውስጥ አጨቃጫቂ የሆኑ አጀንዳዎች (የመሬት እና የብሔር ጥያቄ) በተለይም የኢህአዴግ አቋም ላይ እስከመጨረሻው ውግዘት የሚቀርብበት ነበር። መስማማት ሳይደረስ ስብሰባው ይጠናቀቃል። እኔ እስከማስታውሰው ድረስ በእነዚህ ጥያቄዎች ዙሪያ በግድ የምንላችሁን ተቀበሉ ብሎ ከማስገደድ ውጭ በከፊል እንኳን ማሳመን አይቻልም። በተለይ በአንቀጽ 39 ላይ ህብረተሰቡ፣ መምህራን እና ተማሪዎች ያላቸው ጥላቻ በቃላት ሊገለጽ አይችልም። ካድሬዎቻችን ሳይቀሩ "ይቺ እስከ መገንጠል የምትለው ብትቀር እኮ ከህብረተሰቡ ጋር መቀራረብ ይቻላል" የሚል ግለሰባዊ ቅሬታ ሲያቀርቡ መመልከት የተለመደ ነው። እጅግ በጣም እርግጠኛ ሆኖ መናገር የምችለው ኢህአዴግ ወደ ህዝቡ ሳይሄድ በአዲሳአባ አሉኝ ላላቸው መቶሺህ አባላቶቹ "አንቀጽ 39 በህገ መንግስቱ መስፈሩን ትቃወማላችሁ?" ብሎ ቃለ-መጠይቅ ቢያወርድ 97% በላይ የሚሆነው አባል "አዎ! እንቃወማለን!" የሚል ምላሽ ይሰጣል። ይህ አንቀጽ ህገ መንግስቱ ላይ የሰፈረው ኢህአዴግ በመርህ ደረጃ አምነቱ ስለሆነ እንጂ ህዝቡ (በተለይም የከተማ እና የተማረው ክፍል) የሚቀበለው ስለሆነ አይደለም።

በካድሬነት ዘመኔ ያለማጋነን ከአስርሺህ በላይ መምህራን እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተማሪዎች ጋር ከሳምንታት የዘለቀ የአዳራሽ ውይይት አድርጌያለሁ። እናም በእነዚህ መድረኮች የብሔር ጥያቄ ከመጀመሪያው እስከ

መጨረሻው በጭብጨባ የታጀበ ውግዘት ይቀርብበት ነበር። ኢህአዴግ የሚያራምደው የብሔር ጥያቄ ኢትዮጵያን ለመበታተን እንደሆነ፣ በተራዘመ ሂደት ትግራይን ለመገንጠል፣ ከፉፍሎ ለመግዛት እንዲያመች... ወዘተ የሚሉ ምክንያቶች በቁጭት ታጅበው ይቀርባሉ። ይህ ፀሀይ የሞቀው እውነት ነው!! አቶ መለስም ሆነ በረከት ስምኦን ወደ ታች ወርደው እንደ እኛ ከመምህራን እና ተማሪዎች ጋር ፊትለፊት ተገናኝተው አያውቁም። እናም በተሳሳተ የካድሬ ሪፓርት ላይ ተመስርተው የተዛባ ድምዳሜ ቢይዙ አይገርምም። ነውር የሚሆነው ለህዝቡ እንደወረደ በመጽሐፍ መልክ አዘጋጅተው ማቅረባቸው ነው። ለዚህ ማሳያ እንዲሆነን የሁለት ምርጫዎች ወግ በምእራፍ አራት ስር ከምርጫው ማግስት የተካሄዱትን የዩንቨርስቲ ተማሪዎች መድረክ በተመለከተ፣

"... የማታ ማታ ደግሞ ብዙዎቹ የኢህአዴግ አቋሞች ትክክለኛ እንደሆኑ መግባባት ላይ ተደረሰ። ኢህአዴግ የሚያራምደው የብሔር ጥያቄ አፈታት ትክክለኛ እንደሆነና የኢትዮጵያን አንድነትም በዲሞክራሲያዊ አኳኋን በጠንካራ መሰረት ላይ ለመገንባት የተሻለው አቅጣጫ እንደሆነ ስምምነት ላይ ተደረሰበት" ይላል።

ፍርዱን ለመምህራን እና በወቅቱ የዩንቨርስቲ ተማሪዎች ለነበሩ ወጣቶች ትቼ በድሬደዋ ያጋጠመኝን ለየት ያለ ውይይት ላንሳ። በድሬደዋ በተካሄደው የተማሪዎች መድረክ አንቀጽ 39 በተመለከተ ዱላ ቀረሽ እና በእንባ የታጀበ ክርክር ሲካሄድ የነበረው እርስ በራስ በተማሪዎች መካከል ነበር። ክርክሩ ኢህአዴግ ለብሔር አፈታት ከሚሰጠው ትንታኔ በፍጹም ተቃራኒ በሆነ መልኩ የሚቀርብ ነበር። በአንድ በኩል ከ80% በላይ የሚሆኑ ተማሪዎች ሲሆኑ፣ እነዚህ ወጣቶች "ኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነት" የሚያራምዱ፣ ኢህአዴግ በዘረጋው የዘር ስርአት እነሱ እና ቤተሰቦቻቸው ሰለባ እንደሆኑ በልቅሶ የሚገልጹ ናቸው። ስርዓቱ ባይተዋር ከማድረጉም ባሻገር ሀገር አልባ አድርጐናል በማለት በተጨባጭ ማስረጃዎች የሚከራከሩ ናቸው። በሌላ በኩል ያሉት ደግሞ ሲጀመር ውይይቱ በአማርኛ መደረጉን የሚቃወሙ፣ ከፊል ንግራራቸውን በእንግሊዘኛ ያደረጉ እና አንቀጽ 39 የወረቀት አንበሳ ነው በማለት የሚከራከሩ ናቸው። እነዚህ ወጣቶች የህዝባቸው የራስን እድል በራስ የመወሰን እስመግንጠል እንደተነፈጉ፣ በውይይቱ ማግስት ሪፈረንደም ይደረግ ብለው የሚሞግቱ ናቸው። በእነዚህ ሁለት ቡድኖች መካከል አቶ መለስም ሆነ አብዮታዊ ዲሞክራሲ የሉም። የሁለት ምርጫዎች ወግም የለችም!!

በዚህ ምክንያት ስልጠናው ተጨማሪ ቀናት መራዘም ነበረበት። ምንም አንኳን መጨረሻው መጀመሪያው ቢሆንም። ስለሆነም የማናጀሪያል ስታስቲክስ አስተማሪዬ ከፈቀደልኝ አንድ ሳምንት ለማሳለፍ ተገደድኩ። እናም ለዛች ቀን ይቅርታ ጠይቄ መማር ጀመርኩ። ከተወሰኑ ቀናት በኃላ ማጠቃለያ ፈተና

ተሰጠ። ትምህርቱ የሂሳብ ባህሪ ስለነበረው ብዙም አላስቸገረኝም ነበር።

እነሆ! የፈተና ውጤቱ ሰሌዳ ላይ ተለጠፈ። ተጋፍቼ ስመለከት "NG" የሚል ተጽፏል። ተደናግጬ መምህሬ ጋር በቅድሚያ ሄድኩኝ። በጣም ያዘነ በመምሰል ፍቃድ ከሰጠሁህ አንድ ሳምንት በማሳለፌ እንደሆነ እና የዩንቨርስቲውን ህግ መጣስ እንደማይችል ገለፀ። በተበሳጨ አንደበት ለምን መጀመሪያ ምክንያቴን የገለጽኩ ጊዜ እንዳልገለፀልኝ ስጠይቀው፣

"አውቃለሁ! ባለስልጣን መሆንህን። ህግ የመጣስ መብትም በእጃችሁ ስለሆነ የፈለከውን ማድረግ ትችላለህ! ከፈለግክ አሳሰረኝ እንጂ ህግ አልጥስም" አለኝ።

እንደ እውነቱ ከሆነ ሁለት ፀጉር ካወጣ ምሁር እንደዚህ አይነት ነገር አልጠበኩም። በዚህ ምክንያት አንድ አመት የዩንቨርስቲ ቆይታዬ መራዘሙ አበሳጨኝ። በአጋጣሚ ሆኖ ከክፍል ጓደኞቼ መሀመድ ሳሎ እና ተናኞ የሚባሉት እኔ በክፍል ካልተገኘሁበት በእጥፍ አልተገኙም። ይህም ሆኖ ውጤታቸው ተለጥፏል። በተለይ መሀመድ በመምህሩ ፓለቲካዊ ውሳኔ በጣም ተበሳጭቶ ወደ ሚመለከተው አካል እንድሄድ ገፋፋኝ።

(መሀመድ ሳሎ በአሁን ሰአት በአሜሪካን ሀገር የሚኖር ሲሆን የሙስሊም ችግሮች መፍትሄ አፈላላጊ አክቲቪስት ሆኗል። "ኡስታዝ አቡበከር ይፈታ! ጣልቃ ገብነት ይቁም!" እያለ በድምጽ ማጉሊያ የሚያደርገው ቅስቀሳ ድህረ ገጾች ላይ ተለጥፉል።)

እናም መሀመድ ሳሎ ራሱን አብነት አድርጌ ቅሬታዬን እንዳቀርብ ገፋፋኝ።ቀስ ብዬ ማጣራት ስጀምር ከአምስት በላይ ተማሪዎች ከእኔ በከፉ ቀርተው ውጤት ተሰጥቷቸዋል። ይህን መረጃ በመያዝ (ግን ደግሞ ሳልነግረው) መምህሬን በድጋሚ ለማግባባት ያደረኩት ጥረት አልተሳካም። ደግሞ ደጋግሞ የዘመኑ ሰው መሆኔን እና የፈለኩትን የማድረግ ስልጣን በእጄ ላይ እንዳለ ገለፀ። የነበረኝ የመጨረሻ አማራጭ የፉከልቲው ፕሬዝዳንት ዶክተር ፍስሀ ጋር መሄድ ነበር። ፕሬዝዳንቱ ዞኑን በማስተዳድር ወቅት በተደጋጋሚ በስልክ ከመገናኘት ውጪ በአካል አንተዋወቅም። ኢህአዴግ ዘመም መሆኑን ስለማውቅ በዝርዝር ነገርኩት። መምህሩ በየጊዜው ከሚያራምደው አቋም በመነሳት የፓለቲካ ውሳኔ እንደወሰነ ለደቂቃም አልተጠራጠረም። እኔ በተቀመጥኩበት መምህሬን ጠርቶ አናገረው። ያደቆነ ሴጣን እንዲሉ መምህሬ ሁለታችንንም በጥላቻ እየተመለከተ፣

"ህግ ታወጣላችሁ፣ እናንተ ጋር ሲደርስ ሻሩ ትላላችሁ። የማስተካከል ስልጣን በእጃችሁ ስላለ የፈለጋችሁትን ማድረግ ትችላላችሁ" አለን። ዶክተር

ፍስሀ ትንፍሽ ሳይል መምህሬን እና አኔን ይዞ ወደ መምህሬ ቢሮ ይዞን ሄደ። ቢሮው እንደደረስን አቴንዳስ የያዘበትን ወረቀት ተቀበለው። የእኔን፣ የመህመድን እና ሌሎች የሰጠሁትን አራት ተማሪዎች አቴንዳንስ ተመለከተ። መምህሬ ምላሽ አልነበረውም። ደርቆ ቀረ። ዶክተር ፍስሀ የዲሲፒሊን እርምጃ እንደሚወስድ ሲዝት በመሀል ጣልቃ ገብቼ፣

"እባክህ የተከበረውን የመምህርነት ሙያ ለፓለቲካ ፍላጐትህ እና በቀል አታውለው!" አልኩት።

***

በአዲሳባ ዩንቨርስቲ ከተጨመሩት አዳዲስ ኮርሶች አንዱ የስነ ምግባር እና ስነ ዜጋ የሚባለው ትምህርት ነው። እነዚህ ትምህርቶች የተጨመሩት እንደ ጂኦግራፊ እና ታሪክ የመሳሰሉ ትምህርቶችን በማጠፍ ነበር። በዚህም ምክንያት አብዛኞቹ የህብረሰብ ሳይንስ መምህራን እጥፍ ብለው የስነ ዜጋ መምህራን ሆኑ። የስነ ዜጋ ትምህርት ደግሞ በኢህአዴግ ልዩ ትኩረት ስለሚሰጠው የካሪኩለም ቀረጻው ሳይቀር በአቅም ግንባታ ሚኒስቴር በኩል ክትትል ይደረግበታል። የሚዘጋጁት መጽሐፎችም እንደሌላው በዋዛ የሚታዩ አልነበረም። በተለይ በህገመንግስቱ የተቀመጡ የቡድን መብቶች ላይ አጽንኦት ተሰጥቶ ሰፊ ቦታ እንዲያገኝ ተደርጓል። አንዳንዶች አፍ አውጥተው የኢህአዴግ የፓለቲካ ፕሮግራም ማስተማሪያ እስከማለት ይደርሳሉ። ብዙዎቹ የሁለተኛ ደረጃ የስነ ዜጋ መምህራን እንደ ኢህአዴግ አባል የሚቆጠሩበት ምክንያት በዚህ መልኩ የተቀረፀውን ካሪኩለም ስለሚያስተምሩ ነው።

ወደ ኮሜርስ መምህራን ስንመጣ በተቃራኒው ነው። በግለሰብ ነፃነት ላይ የተመረኮዘ የሊብራል አስተሳሰብ ያላቸው መምህራን ስለቡድን መብት ታላቅነት እንዲያስተምሩ ይደረጋል። አንዳንዶቹ ቃር ቃር እያላቸው የተቀሩት ደግሞ" መጽሐፉ እና ህገ - መንግስቱ እንዲህ ይላል" በሚል የማስተማር ዘይቤ ዘመናቸውን ይገፉሉ። ከእንደዚህ አይነቶቹ በተለየ የራሱን አቋም ጨምሮ ተማሪውን የሚያከራክር፣ ህይወት ያለው ትምህርት የሚያስተምር መምህር አለ። ይህ ትልቅ ሰው መምህር ዘውዱ ይባላል። ዘውዱ ያመነበትን በግልጽ የሚናገር ነው። የዩንቨርስቲ መምህራን ከአቶ መለስ ጋር በነበራቸው ስብሰባ ድምፃቸው ጐልቶ ከተሰማ ሰዎች አንዱ እንደሆነ በተባራሪ ሰምቻለሁ።

እናም ዘውዱ የስነ ዜጋ አስተማሪዬ ሆነ። እኔ በአብዮታዊ እሱ በሊብራል ዲሞክራሲ ቅኝት ተፋጠጥን። ክፍላችን በእኔ እና በእሱ ጭቅጭቅ በአንድ እግሯ ትቆማለች። አንዳንዴ የምርጫ ክርክር ላይ እንደቀረበ ሰው ጠንካራ ቃላቶችን እንለዋወጣለን። የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እስከመገንጠል፣ ጋራ ሸንተረር ሳይሆን የህዝቦች ሉአላዊነት፣ ልማታዊ መንግስት

...ወዘተ የሚሉ አብዮታዊ ቃላት በእኔ በኩል ይዘረገፉሉ። ርግጥ ብዙ ተማሪዎች በእሱ መስመር ስለሚሰለፉ የሀይል ሚዛኑ ወደ እሱ ያጋደለ ነበር። ክርክሩ እስከመጨረሻው ድረስ ስለሚዘልቅ ሳናውቀው ክፍለጊዜው ያልቃል። የእኔ አጥብቆ መከራከር ያልተዋጠላቸው ጓደኞቼ፣

"ተው ይቅርብህ! ይሄ ሰውዬ መጨረሻ ጠብቆ ባንዲራ ያሸክምሀል" ይሉኝ ነበር።

እነሆ! የሲቪክስ ፈተና ተፈተንን። ውጤቴን ለመመልከት ስሄድ የመምህር ዘውዱ ትምህርት አልተለጠፈም። በቀጥታ ወደ ቢሮው ስሄድ ተቀምጦ አገኘሁት። ገና ሲያየኝ በፈገግታ ውስጥ ሆኖ እና ስሜን ከእነአባቴ እየጠራ፣

"ወርቃማው ክፍለጊዜ አሳልፈናል። ክፍላችሁን መቼም አልረሳውም። ያገኘሽው ውጤትም የሚገርም ነው። ዩንቨርስቲው ገጅ ላይ መስቀል ማጥለቅ ትርጉም የለውም እንጂ አኖርልህ ነበር" በማለት ውጤቴን ነገረኝ። እኔም አኩብሮቴን ገለጽኩ።አያይዤም አንዳንድ ተማሪዎች የነበራቸውን ስጋት እና የሰጡኝን ምክር ነገርኩት። በሀዘኔታ ውስጥ ሆኖ፣

"የአንድን ሰው አመለካከት በመቅጣት አታስጥለውም። እንዳውም መበረታታት አለበት። የግል ፓለቲካ እምነትን ተንተርሶ የተማሪን ውጤት ማዛባት ልክ አይደለም። እጅግ በጣም አደገኛ ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል" አለኝ።

***

የመንግስት ሰራ ጅማሮ

የመጀመሪያ ስራዬን የተቀጠርኩት በመከላከያ ሚኒስቴር ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖችን ለማሰልጠን ነበር። በቅጥሩ ሂደት ላይ መከላከያ ትሰራ የነበረው እናቴ፣ "የማይመረቀው ተማሪ"፣ እና የግል ፍላጐቴ አስተዋጽኦ አበርክተዋል። እናም ተቀጥሬ ወደ ዝዋይ ህፃናት አምባ (አላጌ ኮሌጅ) ሄድኩኝ። በአምባው ውስጥ አጋዴን በሚባለው መንደር የመከላከያ ከፍተኛ መኮንኖች በአዳሪነት እንዲማሩ ተደርገዋል። ከእነዚህ ውስጥ የዛሬዎቹ ጀነራል ፍስሀ መንጁስ (የቤተመንግስት ዙሪያ ጥበቃ ሀላፊ)፣ የዘመቻ መምሪያ ሀላፊው ጀነራል ገብረእግዜር (አራንሺ)፣ ወዲ መድህን (ጀነራል)፣ ኮረኔል ገብረመድህን (ወዲ ነጮ- የአጋዚ ምክትል አዛዥ)፣ ኮረኔል ወርቅአይኑ (የዴዴሳ ማሰልጠኛ አዛዥ) ተማሪዎቼ ነበሩ። ሁሉም አምስተኛ ክፍል ነበሩ። ትምህርቱ በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት በመቋረጡ ምክንያት ትምህርታቸውን መቀጠል አልቻሉም። አሁንም አምስተኛ ክፍል ናቸው። በነገራችን ላይ የመከላከያ ካሪኩለም በአመት ሁለት ክፍል የሚያሳልፍ በመሆኑ አምስተኛ ክፍል የደረሱት በሁለት አመት ውስጥ ነበር።

የተሰጠኝ መኖሪያ ቤት ከጀነራል ፍስሀ መንጁስ እና ኮረኔል ፍስሀ የሚባል የብአዴን ታጋይ አጠገብ ነበር። ኮረኔል ፍስሀ እና ሌሎች ስማቸውን መጥቀስ የማልፈልጋቸው የብአዴን ታጋዮች የነበሩ መኮንኖች ጥሩ ሰዎች የነበሩ ሲሆን በሰራዊቱ ውስጥ ያለውን ዘር የተሞረኮዘ አድልኦ ይቃወሙ ነበር። በተለይ የኮረኔል ማእረግ የነበራቸው ፍስሀ (ከምርጫ 97 በኃላ ከተቀነሱ መኮንኖች ጋር የተቀነሰ)፣ አዘዘው (ባድመ ላይ የሞተ)፣ ቄሴ (ዛላንበሳ ቆስሎ ጦር ሀይሎች ሆስፒታል የሞተ) እና ሌሎች አሁንም በሰራዊቱ ውስጥ ያሉ በግልፅ በማምገማ ያቀርቡ ነበር።

ከእለታት በአንዱ ቀን በዚህ ጉዳይ ላይ በህውሀቱ ወዲነፍ እና ብአዴኑ ፍስሀ መካከል ጭቅጭቅ ተነሳ። ወዲነፍ ከራሱ ጋር የተጣላ፣ ከህውሀት ሰዎች ውጪ ሌላውን በንቀት የሚመለከት፣ በረባ ባልረባው አንባጓሮ በመፍጠር ሩሲያ ሄዶ ቲኳንዶ መማሩን ለማሳየት የሚፈልግ ትእቢተኛ ነበር። በትምህርቱ ጐበዝ ቢሆንም ሌላ ወታደር በአንዲት ማርክ ከበለጠው አንኳን መምህራንን ያስፈራራ ነበር። ለምን እንደሆነ ባይገባኝም በተለይ የብአዴን ሰራዊት አባላት ከበለጡት ቂም ይይዝ ነበር። ጭቅጭቁ ወደ ፀብ ሲቀየር ኮረኔል ፍስሀ በዛ ሰፈድ እጁ በጥፊ ሲያጮለው ወዲነፍ በደም ተነክሮ መሬት ላይ ተንደፉደፈ። ሁለቱም እግር እና እጃቸው በሰንሰለት ታስሮ ለሁለት ቀን ያለምግብ ጨለማ ቤት ታሰሩ። ቀኑ ደረሰና ትእቢትን እስከ አፍንጫው የተሸከመው ወዲ ነፍ ቋጥሮ የከረመውን በቀል በምርጫ 97 ማግስት ተወጣ።

ከብአዴን ታጋዮች በተለይም ከቄሴ እና ባዘዘው ጋር እጅግ በጣም ቅርብ ግንኙነት ነበረኝ። ቄሴ በህውሀቶች ሁሉን ለመጠቅለል ያላቸውን ፍላጐት ቢቃወምም በኢህአዴግ ላይ ያለው አመኔታ ከፍተኛ ነበር። "ድርጅቱን እንጂ ሰው አልመለከትም" የሚል አባባል ነበረው። ጓደኞቹ በጠንካራ አዋጊነቱ የሚመሰክሩለት ሲሆን እስከ ክፍለጦር አመራር ደርሶ ነበር። በህውሀቶች ላይ ቅሬታውን በማቅረቡ ምክንያት ባይቀጠቀጥ ኖሮ እነ ጀነራል አበባው የደረሱበት ቦታ ይደርስ እንደነበር እምነታቸው ነው።

ኮረኔል ባዘዘው ደግሞ ሰባተኛ ክፍል ቢሆንም (በኃላ ላይ እንደነገረኝ አስረኛ ክፍል አቋርጦ ነበር ወደ በረሀ የገባው) በፓርቲው ፕሮግራሞች፣ መርሀዎች እና ህገ መንግስቱ ላይ ግንዛቤው ሰፋ ያለ ነበር። በረሀ በነበሩ ሰአት የሚሰራው ስራ ህዝብ ማንቃት እና ማደራጀት ነበር። ለብአዴን ሰራዊት የፓለቲካ ትምህርት ይሰጥ ነበር። የኢህዴግን ፕሮግራም እና ህገ - መንግስቱን ለመጀመሪያ ጊዜ የሰጠኝ እሱ ነው። ለእኔም በኢህአዴግ ፕሮግራሞች ላይ ሰፋ ያለጊዜ በመውሰድ አስተምሮኛል። በወቅቱ (እስከ አሁንም ድረስ) በኢትዮጵያ

ፓለቲካ ውስጥ አጨቃጫቂ ስለሆኑት የመሬት እና የብሄር ጥያቄ ሰፊ ማብራሪያ ያገኘሁት ከዚህ ሰው ነበር። በሁለቱ አከራካሪ ጥያቄዎች ዙሪያ የሚሰጠኝ ምክንያቶች እና ምሳሌዎች በዛን ሰአት ከነበረኝ ንቃተ ህሊና አንፃር አሳማኝ ነበሩ። አንዳንዴ ወደ ቤቴ ስመለስ በማስታወሻ ደብተሬ ላይ አከትባቸዋለሁ። በተለይም አንቀፅ 39 በተመለከተ ለትክክለኝነቱ የሚሰጠኝ ምክንያት ወደ ቤተሰብ የወረደ ስለነበር ከአዕምሮዬ አይጠፉም።

ባዘዘው አንቀፅ 39 በተመለከተ እንዲህ ነበር የሚለኝ፣

"አባት እና እናትህ ተፈቃቅደው ነው የተጋቡት። አንተም ነገ ሚስት ስታገባ የፈቀድካት እና የወደድካትን መሆኑ አይቀርም። እሷም እንደዛው። በጋራ መኖር ጀምራችሁ በፍጹም የማያግባባችሁ (የማይታረቅ) ነገር ቢፈጠር እና ከፍተኛ ጉዳት እያስከተለ ቢሄድ ምን ታደርጋላችሁ? ...ወይ መፋታት አሊያም ዘላለም እየተጨቃጨቁ መኖር። የኢህአዴግ የህዝቦች የራስን አድል በራስ የመወሰን እስከ መለያየት አቋም ምንጩ ይሄ ነው። የህዝቦች መብት ሳይሸራረፍ ማክበር ቁልፍ የዲሞክራሲ ጥያቄ ነው። የኢፌዲሪ ህገ - መንግስት ይህን የኢህአዴግ መርሆ እንዳለ በመቀበል የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ያለአንዳች ገደብ እስከ መገንጠል እንዲሆን አደረገ። ከሚስትህ ጋር እስከተፈቃቀዳችሁ ድረስ አባራችሁ ለመኖር እንደምትወስኑት ኢትዮጵያዊነትም በመፈቃቀድ ላይ መመስረት ይኖርበታል።"

የመሬት ጥያቄን በተመለከተ ደግሞ፣

"መሬት መሸጥ መለወጥ የለበትም። አሁን ባለንበት ነባራዊ ሁኔታ መሬት ይሸጥ ይለወጥ ቢባል አርሶ አደሩ በተለይም በተደጋጋሚ ድርቅ የሚያጠቃው መሬቱን በሞተ ዋጋ ሸጦ ባዶ እጁን ይቀራል። በወለድ አገድም እንዲያሲዝ ቢፈቀድ ውጤቱ ተመሳሳይ ነው። በሂደትም ስራ አጥ በመሆን ወደ ከተሞች ይሰደዳል። በተቃራኒው መሬት ሳይሸጥ በገበሬው እጅ ቢሆን በየትኛውም ወቅት ዋስትና ይሰጣቸዋል። መሬታቸውን ለመንከባከብ ፍላጎት ያድርባቸዋል። ይህም ምርታማነት እንዲጨምር ያደርጋል። ለገበሬው የሚሰጠው ዋስትና ለቤተሰቦቹ እስከ ማውረስ ስለሚሄድ ከፍተኛ ፓለቲካዊ ጠቀሜታ አለው" ይለኝ ነበር።

ከባዘዘው ከማገኘው ትምህርት በተጨማሪ በካምፑ የሚካሄዱት አንቅስቃሴዎች የፓለቲካ አመለካከቴን በአውቀት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን አደረጉት። በዚህ መልኩ የማገኘው መረጃ እያደር ወደ እውቀት መቀየር ጀመረ። ኢህአዴግን ለደርግ ከነበረኝ ጥላቻ ብቻ ሳይሆን ፕሮግራሞቹ ላይ ተመስርቼ መደገፍ ጀመርኩ። ለረጅም ቀናት በግምገማ መቀመጥ ፣የግምገማ ስርአት እና ሌሎች የስብሰባ አመራሮችን መገንዘብ ቻልኩ። ለሰራዊቱ የሚሰራጨው "ወጋገን" ጋዜጣ ለተማሪው ማንበብ እና ማወያየት ጀመርኩ።

ተማሪዎች በየሳምንቱ አርብ ጠዋት ለሁለት ተከፍለው የመጀመሪያው ሳምንት "ከንጉሱ እና ኢህአዴግ"፣ በሚቀጥለው ሳምንት "ከደርግ እና ኢህአዴግ" ማን ይሻላል የሚል ክርክር ያደርጋሉ። በመጨረሻም ኢህአዴግ ያሸንፋል። አንዳንዴም ያልተጠበቁ አስቂኝ ነገሮች ያጋጥማሉ። ከእለታት በአንድ ቀን ጐይቶም የሚባል ኤርትራዊ መምህር "ከንጉሱ እና ደርግ ማን ይሻላል" በሚል አከራከረ። ንጉሱ አሸነፉ። የኢትዮ-ኤርትራ ግጭት ሲነሳ "ነጭ እና ጥቁር ጅብ አወዳድረሀል" ተብሎ በጦርነቱ ማግስት ሻንጣውን ሸክፎ ወጣ።

እንዲህ እንዲህ እያለ ቀናቶች ሲሄዱ ኤርትራ የኢትዮጵያን ድንበር አልፉ መግባቷ ተነገረ። ለኢትዮጵያ ህዝብ ሳይነገር በሚስጥር ቢያዝም እኛ ያለንበት ካምፕ ታመሰ። ትምህርት ተቋርጦ የጦርነት ዝግጅት ተጀመረ። እኛን የሚቀርቡን የብአዴን መኮንኖች በለሊት እየመጡ መረጃዎች ይነግሩን ነበር። ከመኮንኖቹ የተረዳነው ነገር ቢኖር የኤርትራ ወረራ ፊጽሞ ያልተጠበቀ ነበር። ሻእቢያ በመከላከያ ውስጥ የፈለገውን ማድረግ የሚችልበት ነበር። እኛ ያለንበት ካምፕ እንኳን እንደ አብነት ቢወሰድ ከነበርነው መምህራን ስድስቱ ሙሉ ለሙሉ ኤርትራውያን ነበሩ። ኮረኔል መንግስቱ (ባሪያው) የሚባለው የከፍለጦር አዛዥ ያገባት ሴት በሻእቢያ ሰላይነት የምትጠረጠር መምህር ነበረች። የካምፑ የበላይ ሀላፊ (የበረሀ ስሙ "ቢቢሲ" ይባላል) ፀሀፊው በተመሳሳይ የምትጠረጠር ሲሆን፣ ካዛ በላይ የከፉ የሆነው የቢቢሲ ከፀሀፊዋ ጋር መንጐዳጐድ ነበር።

መኮንኖቹ ወደ ግንባር እንደሚሄዱ ሲነገራቸው የምቀርባቸው ዘጠኝ የብአዴን መኮንኖች ሊሰናበቱኝ በለሊት እቤቴ መጥተው ነበር። ሁሉም የማእረግ ልብሳቸውን ለብሰው ግርማ ሞገሳቸው ልዩ ነበር። በፍጹም እምባዬን መቆጣጠር አቃተኝ። የጦርነት መጥፎ ገጽታ ስራዬን በጀመርኩ ሶስት ወር ሳይሞላኝ አይቼው ስለነበር።

እንዲህ ነበር የሆነው...

የመምህርነት ስራዬን በጀመርኩ ሶስተኛ ወር ላይ በዋለች አንዲት ሰኞ ለማስተማር ወደ ክፍል ስሄድ ግቢው ጭር ብሏል። ማስታወቂያ ሰሌዳው ላይ ተማሪዎች ለአስቸኳይ ግዳጅ መሄዳቸውን ይገልፃል። ለካስ ሱዳን ብራ መብረቁ ሆና የኢትዮጵያን ድንበር አልፉ በመዝለቅ ሰፊ መሬት ተቆጣጥራለች። እናም የስራዊቱ አዛዥ የሆኑት ተማሪዎቻችን በለሊት ከካምፑ ወጥተው ወደ ጦርነት ሄደዋል። አንድ ሳምንት ባልሞላ ጦርነት የኢትዮጵያ ወታደሮች ሱዳን ድንበርን ተሻገሩ። ጦርነቱም በአጭር ጊዜ ተጠናቀቀ። ከሀሊናዬ የማይጠፉ ነገር የተከሰተው ከወር በኃላ ተማሪዎቻችን ወደ ካምፕ ሲመለሱ ነበር። ከእኔ ተማሪዎች ውስጥ አምስቱ የሉም። ለዘላለሙ አንቀላፍተዋል። አንድ በሙሉ

አይኑ ያየሁት ተማሪዬ አንድ አይኑ ፈሶ በቆሻ ተጠቅልሏል። ሁለቱ ደግሞ በከባድ ሁኔታ ቆስለው ጦርሀይሎች ተልከዋል። ከዛም በኃላ ወደ ትምህርት አልተመለሱም።

ይህን አጋጣሚ በማየቴ ነበር የብአዴን መኮንኖች ሊሰናበቱኝ ሲመጡ በሀዘን የተዋጥኩት። እንደ እውነቱ ከሆነ የወታደር አስተማሪ መሆን ከባድ ነው።

ባዘዘው እያቀፈኝ፣

"አይዞህ! እኛ የለመድነው ህይወት ነው። የሚቆጨኝ ትምህርት ማቋረጤ ነው። በድል ስንመለስ እንገናኛለን። አንተም ኢህአዴግን የምታገለግልበት የተሻለ ቦታ ለሲቪል ጓዶች ነግረናቸዋል። በቅርብ ቀን ያገኙሀል።" አለኝ።

ቁሴ የታሸገ ፓስታ እየሰጠኝ፣

"ለምትወዳት እናትህ መከላከያ ምድር ጦር ስንደርስ ሰጥተናት ለመሄድ ፈልገን ነበር። ምንአልባት በቀጥታ ልንሄድ ስለምንችል ለአንተ መስጠቱን መረጥን። ሳናስበው በመሆኑ ትንሽ ናት።"

ተሰናብተውኝ ሄዱ።

የሰጡኝን ፓስታ ስከፍተው ተማሪ እያለን እንደምናዘጋጀው የፍቅር ደብዳቤ መጻፊያ ልብ፣ ጦር፣ አበባ ስለው ምስጋናቸውን ጽፈዋል። ስምና ፊርማቸውም በትልቁ አለ። ተማሪ ሁሌም ተማሪ ነው!! በፓስታ ውስጥ ያለው ገንዘብ አምስት ሺህ ብር ነበር።

እነሆ! የኢትዮ - ኤርትራ ጦርነት ተጀመረ።

በወሩ አስደንጋጭ ዜናዎች መጉረፍ ጀመሩ።

ባዘዘው ጦርነቱ የተጀመረ እለት ሞተ!!

***

ምእራፍ አስራ ሰባት

ግንቦት 7 1997

ለግንቦት ሰባት አጥቢያ ለሊት ስምንት ሰአት ከቤተሰቦቼ ቤት ወጥቼ ወደ ጊዜያዊ የምርጫ መከታተያ ማዕከል ወዳደረግነው ቄራ አመራሁ። ማእከሉ ስደርስ የተወሰኑ የወረዳ እና ከፌደራል የተመደቡ ካድሬዎች ቀድመውኛል። ሁሉም ወደ የኢህአዴግ ምርጫ ታዛቢ የተመደቡ አባላት እየደወሉ ከእንቅልፋቸው ይቀሰቅሳሉ። በቅንነቱ የማውቀውን ፀጋዬ የሚባል የወረዳ 20 ካድሬ ይዤ በየምርጫ ጣቢያው አረንቴሽን ለመስጠት ተንቀሳቀስን። ከማዘጋጃ ቤት የተሰጠኝን 40 ስልኮች ለጣቢያው አዛዦች አደልኳቸው። አቶ በረከት የምርጫ ስነምግባሩን ሲያወያየን ምንም አይነት የመንግስት ንብረቶችን መጠቀም አይቻልም ቢልም በተግባር የሆነው ግን በተቃራኒው ነበር።

ለምሳሌ በአዲሳባ ለሚገኙ የኢህአዴግ ምርጫ ጣቢያ አስተባባሪዎች የተሰራጨውን ስልክ ወጪ የተከፈለው ፒያሳ የሚገኘው ማዘጋጃ ቤት ነበር። ስልኮቹ ከአንድ ሳምንት በላይ ካድሬዎች እጅ ቆይተው ስለነበር አስተዳደሩ ከመቶ ሺህ ብር በላይ ወጪ አድርጓል። አሳዛኙ ነገር ስልኮቹ ወደ ወረዳ ምርጫ መከተታተያ ማእከል ከተሰባሰቡ በኃላ ባለቤት ስላልነበራቸው አባሎቻችን ሰሜን አሜሪካ እና አውሮፓ ያሉ ዘመዶቻቸው ጋር ሳይቀር ይደውሉ ነበር። የመንግስት መኪናዎችም ቢሆን ለኢህአዴግ የምርጫ ስራ ውለዋል። መኪኖቹን ወደ ስራ ለማሰማራት መጀመሪያ የተደረገው ታርጋቸውን ወደ ግል ማዞር ነበር። እኔ በምመራው ምርጫ ክልል ብቻ ስምንት የመስተዳድሩ እና የፌደራል መንግስት መኪኖች ታርጋቸው ተቀይሯል። ከዚህ በተጨማሪም ኢህአዴግን እንደግፉለን የሚሉ ባለሀብቶች ማእከላችን ድረስ በመምጣት አስር መኪኖችን ከሙሉ ነዳች ወጪ ጋር ሰጥተውናል። በወቅቱ ጭንቅላቴ ውስጥ ያልመጣ እያደር ያሳዘነኝ ነገር ቢኖር መኪኖቹን ከሰጡን አስር ባለሀብቶች ዘጠኙ የአንድ አካባቢ ሰዎች ነበሩ።

ከፀጋዬ ጋር ምርጫ ጣቢያዎችን እና የኢህአዴግ ምርጫ መከታተያ ጊዜያዊ ቢሮዎችን እየዞርን መከታተል የጀመርነው ከለሊቱ ዘጠኝ ሰአት ነበር። የቄራ፣ ገፋ ፣ገፋራ መንገዶች ጭር ያሉ ሲሆን አልፎ አልፎ ጥንድ ጥንድ ሆነው በፍጥነት የሚሄዱ ወጣቶችን እንመለከት ነበር። ሁኔታው ቀልቤን ስለሳበው ለሶስት ያህል ጊዜ መኪናችንን አቁመንና ማንነታችንን ገልፀን

ወጣቶቹን ጠየቅናቸው። ከስድስት ኪሎ እና አራት ኪሎ ዩንቨርስቲ በአግራቸው እንደመጡ እና የቅንጅት ምርጫ ታዛቢዎች እንደሆኑ ገለጹልን። ሁለቱ ወጣቶች ሀና ማሪያም አካባቢ ወደሚገኘው ምርጫ ጣቢያ እየሄዱ እንደሆነ ስሰማ ማመን አቃተኝ። ርግጥም ገና ከአንድ ሰአት በላይ በአግራቸው እንደሚጓዙ መገመት " ሳስበው ደከመኝ" የሚለውን የአቶ መለስ የዘወትር አባባል ያስታውሳል።

ለሊት አስራአንድ ሰአት ላይ ሁሉንም ጣቢያዎች ዞረን ተመለከትን። የኢህአዴግ ታዛቢዎች እና ምርጫውን የሚከታተሉ ቡድኖች ቦታ ቦታቸውን ይዘዋል። በቡድኑ አባላት ዘንድ ተስፋ ማጣት የሚነበብ ቢሆንም የተሰጣቸውን ተልእኮ ሳያንጠባጥቡ ለመፈፀም የሚሰስቱት ጉልበት የላቸውም። በዚህ አደገኛ ሰአት በምንም መልኩ ተጠያቂነት የሚያስከትል ጥፋት ላለመስራት መወሰናቸው ያስታውቃል። ከወዲሁ ጣት መቀሳሰሩ ስለተጀመረ የዛ ሰለባ እንዳይሆኑ መጠንቀቃቸው ተገቢ ነበር።

በዚህ መልኩ እየተዋከብን ወፍ መንጫጫት ጀመረ። ወደ ዋናው ማዘዣ ጣቢያ በፍጥነት በመመለስ የክትትል ቡድን አደራጀን። በዚህ መሰረት የመረጃ ጥንቅር፣ ሎጅስቲክ፣ የፀጥታ እና የኩነቶች ምዝገባ ቡድኖች ተደራጁ። የመረጃ ጥንቅሩ ኮሚቴ ከየምርጫ ጣቢያው መርጦ የወጣውን ህዝብ እየመዘገበ ሪፓርት እንዲሰጠን ተደረገ። ሎጅስቲክ ኮሚቴው የምግብ፣ ነዳጅና ሌሎች አስፈላጊ ቁሳቁሶችን እየተከታተለ እንዲያሟለ ተደረገ። የኩነቶች ምዝገባ ቡድን የካሜራ እና ስነጽሁፍ ሙያ ያላቸውን የድርጅት አባላት የያዘ ሲሆን ለታሪክ ሊቀመጡ የሚገባቸውን አጋጣሚዎች እየተከታተለ የሚቀርጽ እና የሚመዘግብ እንዲሆን ተደረገ። ይህ ቡድን የተቋቋመው የመንግስት ሚዲያ ተቋማት ሁሉም ቦታ ደርሰው አጋጣሚዎችን መዘገብ ስለማይችሉ እነሱን ለማገዝ በማሰብ ነበር። የፀጥታ ቡድኑ ከፓሊስ እና ከአካባቢ ሚሊሺያዎች ጋር በመቀናጀት ሰላም የሚያስጠብቅ ሆነ።

ከጠዋቱ ፲፩ ሰአት ተኩል ገና ርክክቡ ሳይጠናቀቅ ምርጫ ጣቢያዎች በመራጩ ህዝብ ተጥለቀለቁ። አንዳንዶቹ የፉ-ቢሪካ ስራ እንደሚሰሩ በመግለጽ ምርጫው እንዲጀመር ግፊት የሚያደርጉ ነበሩ። በአብዛኞቹ ለመምረጥ ከመጓጓት የመነጨ ትዕግስት ያጡ ወጣቶች ናቸው። በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ ምርጫው የተጀመረው እጅግ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ነበር። ከየጣቢያው የሚመጣልኝን ሪፓርት እየተከታተልኩ ከኢህአዴግ ማእከል አሊ ሲራጅ ደወለልኝ። ሁሉም ነገር በሰላማዊ መንገድ እየተከናወነ እንደሆነና ያጋጠመን ችግር እንደሌለ ነገርኩት። እሱም በመላው አዲሳአባ ምርጫ ጣቢያዎች እንደተጨናነቁ እና በ"ኤ" ደረጃ የተቀመጡት የኢህአዴግ ኔትወርኮች እንደሆኑ

በኩራት ነገረኝ። እኔም እየደረሰኝ ያለው መረጃ በ"ኤ" ደረጃ የተሰየሙት ወጣቶች መስመሩን እንደሞሉት ገለጽኩ። በዝረራ ማሸነፋችንን አጽንተን ስልኩ ተዘጋ።

ከጠዋቱ 12 ሰአት ሌላ ምርጫ ክልል የሚያስተባብር ወዳጄ ደወለለኝ። እጅግ በተደናገጠ ሁኔታ ስሜን እየጠራ፣

"It is over! It is over! ህዝብ በተለይም ወጣቱ ደረቱ ላይ እጅቹን በድል ምልክት በማጠፍ ጐርፍ ሆኖ ተሰልፉል። It is over!!" በማለት ነገረኝ። ከወዳጄ ጋር ያደረኩት የስልክ ልውውጥ ስላስደነገጠኝ አርከበ የሚወዳደርበትን የምርጫ ክልል ለሚያስተባብረው የሁሉ ደነቀ ደወልኩለት። የሁሉ በቀልደኛ አንደበቱ፣

"አዬ! አርሶአደሩ ሳይቀር የቅንጅት ምልክት ላይ አድርጉልኝ እያለ ነው! ያ ሁሉ የሀረር ሰንጋ ገደል ገባ" አለኝ።

በጣም ደነገጥኩ። መንፈሴም በድንገት ተለዋወጠ። በአንድ በኩል በእድሜዬ ሰላማዊ እና ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ሲካሄድ ከዛም አልፎ ምርጫው ሲነሳ በመራጭነት ብቻ ሳይሆን በንቁ ተሳታፊነት የምታወስ መሆኑ ልቤን ኩራት ሞላው። ከዚህ በተጨማሪም የአዲሳአባ ህዝብ በፍጹም ጨዋነት ለሚስተራዊ ድምጽ መስጠት ተገኘ ሆኖ መታየቱ በጣም ደስተኛ አደረገኝ። ከዚህ በተቃራኒው መጻኢው ግዜ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመቱ ስጋት አሳደረብኝ። ይህቺን ትልቅ ከተማ ማነው የሚረከባት?

ቅንጅት ስለተባለው ድርጅት ከውስጥ ወደ ውጭ የምንሰማው ነገር በፍጹም አመኔታ የሚጣልበት አልነበረም። በኢህአዴግ ማእከል በሚኖረን ግምገማ የተለያዩ ኢንፎርሜሽኖች ይቀርቡ ነበር። ከእነዚህም ውስጥ ቅንጅት ውስጥ ያሉ ፓርቲዎች የተሰባሰቡት "የጋራ ጠላታችን" በሚል እሳቤ እንደሆነ በተደጋጋሚ ሰምተናል። መቀናጀው የዘይት እና ውሀ መደባለቅ አይነት እንደሆነ በውስጣቸው ያለው ልዩነት የማይታረቅ መሆኑ ተነግሯል። ግማሹ ሶሻሊስት፣ ግማሹ ሶሻል ዲሞክራት፣ ሌላው ሊብራል፣ የተቀረው ከነፈሰው ጋር የሚነፍስ አመለካከት እንዳላቸው አዳምጠናል። ከሁሉም የከፉው እነዚህ ሀይሎች በከፍተኛ መስዋዕትነት የተገኙትን የብሄር ብሄረሰቦች ያልተገደበ መብት ለመንጠቅ የሚፈልጉ እና ምንጫቸው የቀድሞው አስከፊ ስርአት መሆኑ እስኪሰለቸን ሰምተናል።

በተለይም ቅንጅት ለአዲሳአባ ምክርቤት ያቀረባቸውን እጩዎች ማንነት የማጥናት ሀላፊነት የወሰደው መዋቅራችን እና የደህንነት ካድሬዎች ያመጡት መረጃ የኦሮሞ ልጆችን ያላካተተ መሆኑ አስገርሞን ነበር። ይህ ኢንፎርሜሽን

"ቅንጅት የነፍጠኞች ስብስብ ነው። አላማውም የቀድሞውን ስርአት ለመመለስ ነው" የሚል ማእከላዊ ለመቅረጽ መደላድል ፈጥሮ ነበር። በተለይ የአህዴድ ካድሬዎች እና አባላት በዚህ መልእክት ሰለባ በመሆን እልህ ውስጥ ተጋብተው ነበር።

(ዘግየት ብዬ መገንዘብ የቻልኩት ነገር ቢኖር -- በተለይ ከምርጫው በኃላ -- የአዲሳአባ ህዝብ እኛ ቀርፀን ያስተላለፍነውን መልእክት የሚገነዘበው ገልብጦ ነበር። የአዲሳአባ ነዋሪ ስብጥር፣ ማመጣጠን፣ ብሄር ብሄረሰቦች ከሚሉ የቡድን አስተሳሰቦች ርቆ ከቆመ ቆይታል። ለሁለት የምርጫ ዘመናት የመዲናይቱ የምክርቤት አባል እንደመሆኔ መጠን የህዝቡን አስተሳሰብ እጋራለሁ። ከዛም አልፎ እርግጡን እንኒጋገር ከተባለ እንደ አዲሳአባ ምክርቤት የውሸት ምክርቤት አይቼ አላውቅም። የምክርቤት አባላት በሁለት ወር አንዴ ለሁለት ቀናት ይሰበሰባሉ። ይበተናሉ። በቃ!!! ኢህአዴግ የምክርቤት አባላትን የሚፈልጋቸው ለአንድ ጊዜ ድምጽ መግዣ ብቻ ነው። ድኩማን የሆኑ አባላቶቹን አወዳድሮ ድምጽ ማግኘት ሰለማይችል ቢያንስ በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውን እያደነ እጩ ያደርጋል። ተወዳድረው ወደ ምክርቤት ከገቡ በኃላ ዞር ብሎ አያያቸውም።)

የሆነው ሆኖ ምርጫው በተጀመረ አንድ ሰዓት ሳይሞላው ካድሬው ጓደኛዬ "It is over!"፣ የሁሉ ደነቀ ደግሞ "አርሶ አደሩም አሰላለፉን ለውጧል" ብለው አለመረጋጋት ውስጥ ከተተኙ። ሁኔታው በአንድ ጊዜ መታወቁ አግራሞት ቢፈጥርብኝም የማነሳ የምጥለው ግራ ገባኝ። በዚህ አይነት የተምታታ ሀሳብ ውስጥ ተጠምጄ ባለሁበት ሰአት ከአንድ አቅራቢያችን ከሚገኝ ምርጫ ጣቢያ አንዲት ሙሽራ ቬሎዋን እንደለበሰች ለመምረጥ እንደተሰለፈች ተነገረኝ። የኩነት ኮሚቴውን ከሚመራው አባል ጋር ካሜራ ይዘን በፍጥነት ሄድን። እንደተባለው ሙሽሪት ቬሎዋን ቂቅ አድርጋ መስመር ይዛለች። ህዝቡ ቅድሚያ እያለ ቢያስገድዳትም አሻፈረኝ በማለት ቆማለች። ካሜራ የያዘው አባል ሙሽሪት አጠገብ ሄዶ መቅረጽ ሲጀምር የድል ምልክት በእጆቿ አሳየችው። ከጫፍ እስከ ጫፍ የተሰለፈው ህዝብ ያሰማው የድጋፍ ጩኸት ጆሮዬን አደነቆረው። ከመሀል መስመር አንድ ወጣት ጮክ ብሎ፣

"ስነስርአት ለምን አታደርጉም? ኢህአዴግ ብጥብጥ ተነሳ ብሎ ምርጫውን እንዲያስተጓጉል ትፈልጋላችሁ? እባካችሁ እንደተነጋገርነው በሰላማዊ መንገድ ምርጫው እንዲፈፀም እናድርግ" አላቸው።

ከልጁ ንግግር በኃላ ጠጠር ቢወድቅ ይሰማ ነበር። ሁሉም ፊቱን ቅጭም አደረገ አደብ ገዛ። በጠቆረው ፊት ውስጥ የሚንቀለቀለውን የለውጥ ስሜት ማንበብ ግን በቀላሉ ይቻል ነበር። አይናችንን አውቀን መጨፈን

ካልፈለግን በስተቀር። ነዋሪዎች ድምፃቸውን ለማን እንደሚሰጡ ወስነው ስለመጡ የምርጫ ቦርድ ገለጻ ሰጪዎችንም ለመስማት ፍላጐት የላቸውም። ድምጽ መስጠቱ በጣም ፈጣን የነበረ ሲሆን መርጦ የሚወጣው ለሌላው ሰላምታ የሚሰጠው በቅንጅት ምልክት ነበር። ይህን በመሰለ ሁኔታ ውስጥ መቆየት ውስጤን ስለረበሸው ወጥቼ ወደ ዋናው ማዘጋጃ ጣቢያ ሄድኩኝ። ከወትሮው የተለየ መቆጨት ስሜት አደረብኝ። ወንበር ላይ ጋደም እንዳልኩ ሌላ የስልክ ጥሪ መጣ። ጐፉ ገበርኤል ጋር ባለ ጣቢያ ለመውለድ ቀናት የምትጠብቅ ሴት ለመምረጥ በድጋፍ እንደመጣች ተነገረን። በወረዳው ለፓርላማ እየተወዳደረ ያለውን ገብረዋህድ (ገቢዎች ሀላፊ) ይዤ ወደ ቦታው ሄድኩኝ። ባጋጣሚ ሴትየዋ መርጣ ስትወጣ ደረስን። ካሜራውን የያዘው አባላችን ምርጫውን እንዴት እንዳገኘችው ጠየቃት። እሷም መስመር ሰርቶ ወደሚጠባበቀው ህዝብ እየተጠጋች እና ሆዷን እየነካካች፣

"ነፃነቴን ሳታውጂ አልወለድም ብሎ አስቸግሮ ነበር። ልክ የድምጽ ካርዱን ሳስገባ ተፈራገጠ። ካልወጣሁ ብሎ አስቸግሯል። ዛሬ ማታ ከነነፃነቱ ይወለዳል። በነገራችን ላይ ስሙን ልደቱ ብዬዋለሁ! ልደቱ ማንዴላ!!" በማለት ተናገረች። በጉጉት ሲያዳምጣት የነበረው ህዝብ ድንኳኑን በጭብጨባ አቀለጠው። ለካስ ህዝቡ አንድ አካል አንድ አምሳል ሆኗል። የነበረኝ እንጥፍጣፊ ተስፋ ሙሉ ለሙሉ ተሟጠጠ።

እንዲህ እንዲህ አያለ የጠዋት ፀሀይ ወጣች። መዋቅራቸን በመደናገጡ ምክንያት የተለያየ ሰበባ ሰበቦችን መደርደር ጀመረ። የመጀመሪያው ጣት የተቀሰረው ምርጫ ቦርድ በመደባቸው የምርጫ አስተማሪዎች ላይ ነበር። አስተማሪዎቹ የቅንጅት ምልክት ላይ የያዟትን እንጨት በማቆየት "እንደዚህ ነው የምትመርጡት! እዚህ ላይ ነው ምልክት የምታደርጉት" እያሉ እንደሆነ ተነገረኝ።እንደዚህ አይነት ቅሬታ እየቀረበባቸው ወዳሉት ጣቢያዎች ከገብረዋህድ ጋር ተያይዘን ሄድን። በመጀመሪያው ጣቢያ ላይ አንድ በጉልምስና እድሜ ያለ ሰው የምርጫ ምልክት እንዴት እንደሚደረግ፣ የሚስጥር ሳጥን ውስጥ ምን እንዳለ፣ በኮሮጆ ውስጥ እንዴት እንደሚከተት፣ የጣት ምልክት መጨረሻ ላይ ማድረግ ግዴታ እንደሆነ ያስረዳል።ምንም የተለየ ውግንና አይታይበትም። እንደውም እኛ ስንደርስ አንዲት እድሜያቸው ገፋ ያለ እናት፣

"ልጄ የቅንጅት ምልክትን ብቻ አሳየኝ! ሌላ አልፈልግም። በተለይ ዝንቧንማ ከቤቴም ጭስ አጫጭሼ አባሬያታለሁ!" አሉት።

አስተማሪው ብዙም ሳይደናገጥ፣

"እናቴ ይሄኛው የኢህአዴግ፣ ይሄኛው የቅንጅት፣ ያኛው ደግሞ የህብረት..." በማለት በአግባቡ ያስረዳል። እኔም ሆንኩ ገብረዋህድ እንኪን ልናገኝበት አልቻልንም።

በማስከተል ቅሬታ የቀረበባቸው የአዲሳአባ ፓሊሶች ነበሩ።የቀረበው ቅሬታ ፓሊሶቹ የኢህአዴግ አባላትን እየመረጡ ከ500 ሜትር ከልል ጉበታችኋል በማለት እንዳይቀሰቅሱ አድርገዋል፣ በተቃራኒው የቅንጅት አባላት እንደፈለጉ እንዲፈነጩ እያበረታቱ ነው የሚል ነበር።ይህንን ወቀሳ ለማጣራት ተከፉፍለን ተንቀሳቀስን። እንደ እውነቱ ከሆነ በየጉራንጉሩ ያገኘነው የእኛን አባላት ብቻ ነበር። በምርጫው እለት ቅንጅትን ለማስመረጥ ስራዬ ብሎ የሚቀሰቅስ ሰው አላጋጠመንም። በየቤቱ እያንኳኳ ምረጡ የሚል አደረጃጀት መፍጠራቸውንም እጠራጠራለሁ። ህዝቡ ገንፍሎ የፈሰሰው ከምርጫው ቀን በፊት በተሰሩ ስራዎች እና በራሱ ፍላጐት እንጂ በእለቱ በተደረገለት ቅስቀሳ አልነበረም።

የአዲሳአባን ምርጫ የምናስተባብር ካድሬዎች ወደ ማእከል መደወላችንን ትተን በጐንዬሽ መተራረብ ጀመርን። የመርካቶን ምርጫ የሚያስተባብረው መስፍን መንግስቱ "አሮማይ!" በማለት ቴክስት አደረገልኝ። አስከትሎም አሜሪካን ግቢ በሚባለው ሰፈር ያለው ህዝብ ለጭፈራ እየተዘጋጀ መሆኑን መረጃ እንደደረሳቸው ነገረኝ። የአቃቂ ቃሊቲ ከንቲባ ተክለፃዲቅ ሬባ በግርምት ስሜት ውስጥ ሆኖ "አቦ! ይብላኝ ላንተ መሄጃ ለሌለህ። እኔስ ፈዲስ አቅፉ ትቀበለኛለች" አለኝ። የቂርቆሱ ታረቀኝ" ይሄ ህዝብ ጋንጀ ጋንጀችንን ሳይመታን አልቀረም" አለኝ። የኮልፌው ነጋ በርሄ" የዚህ ሁሉ ጥፉት ተጠያቂው አርከበ እቁባይ ነው!" በማለት ያልጠበኩት አስተያየት ሰጠኝ።ቤተመንግስት ዙሪያ ሲያስተባብር የነበረው ይሳቅ አበራ (ቆሪጥ) "በጣም ጥሩ እየሄደ ነው። የመከላከያ ሰዎች ቤተሰባቸውን አስተባብረው እያስመረጡ ነው። ፍሬህይወት በዝረራ አሸንፉ ፓርላማ ትገባለች" በማለት የተለየ አስተያየት ሰጠኝ።

ጠዋት ሁለት ሰአት የእናቴን መቃብር ለማየት ቀጠሮ ይዣለሁና ወደ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ሄድኩኝ። ከቄራ ፣ጦርሀይሎች እና የወይራ ሰፈር መንገዶች በሰው ተሞልተዋል። ባለፍኩባቸው ቦታዎች የሚገኙ ምርጫ ጣቢያዎች በሰልፍ ተጨናንቀዋል። ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ስደርስ ከወትሮው ጭር ብሏል። የሙታን መንደር ፀጥ ሲል ያስፈራል። እነሱም መቃብሩን ፈንቅለው የአዲሳአባን የለውጥ ንፋስ እየተቋደሷት እንደሆነ ተሰማኝ። ምንአልባትም ከሌላው በተለየ "ልጄ ይመጣል" ብላ የተጫነባትን ድንጋይ ያላነሳችው እናቴ ትሆናለች። ርግጥም ወደ መቃብሯ ስደርስ ያልደረቀ ነጭና ጥቁር ቀለም የተቀባው ሀውልት የእሷ ነበር። ዛሬ! ሰማንያ ቀኗ ነው። በኦርቶዶክስ እምነት ስርአት መሰረት ቁርባኗ (ተዝካር) የሚወጣበት ቀን። ከሰአታት በፊት ከልጆቿ የተበረከተላት ጉንጉን አበባ ሽታው ከሩቅ ይጣራል። እኔም ደረብኩላት።

ስቅስቅ ብዬ አለቀስኩ።

የውስጤ ጩኸት ጆሮዬን አደነዘዘው። የ"ኤጥሮስ ያቺን ሰአት" ታሪካዊ ተውኔት መነባንብ ወደ ራሴ ገለበጥኩት። እናም በሙታን መሀል ቁጭ ብዬ እንዲህ በማለት ጮህኩ...

አዎን ብቻዬን ነኝ ፈራሁ
እሸሸግበት ጥግ አጣሁ
እምፀናበት ልብ አጣሁ።...

***

የእናቴን መቃብር ተሰናብቼ ወደ ቤተሰቦቼ ቤት ሄድኩኝ። የአካባቢያችን ነዋሪ የተዘጋጀውን ፀበል ፀዲቅ እየተቋደሰ በድንኳን ውስጥ መደበኛ ወጐቹን ይጠርቃል። ጥድፊያ ላይ ነኝና እንደትላንቱ ሁሉንም አመስግኜ ወደ መጣሁበት ተመለስኩ። የምርጫ ሂደቱ በሰላማዊ መንገድ እየተከናወነ ቢሆንም ካድሬዎቻችን ተስፉ ቆርጠዋል። ገጠመኞችን እየተካታተሉ መቅረጽ ሌላ ራስ ምታት ሰለነበር እንዲቋረጥ ተደረገ። ከቀኑ ስድስት ሰአት ሲሆን መሸነፋችን በማያሻማ መልኩ ተረጋገጠ። የቅንጅት መሪዎች በአዲሳአባ አሸንፈናል የሚል መግለጫ እንደሰጡ መዋቅራችን ጋር ደረሰ። ይህን የቅንጅት መሪዎች መግለጫ በሰማን በግማሽ ሰዓት ውስጥ ከኢህአዴግ ቢሮ ጥብቅ መልእክት ለአባሎቻችን እንድናስተላልፍ ተነገረን። ይህም የተቃዋሚ መሪዎች መግለጫ ህገወጥና ከእውነት የራቀ መሆኑን የሚያመላክት ነበር።

የሚገርመው ነገር የቅንጅት መሪዎች በአዲሳአባ ማሸነፋቸውን ገለጹ የተባለው መግለጫ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ህብረተሰቡ ዘልቆ ገብቶ ነበር። ከየአካባቢው የሚመጣው መረጃ ነዋሪው ደስታው ለመግለጽ ስልክ እየተደዋወለ መሆኑን የሚያሳይ ሆነ። ሰዎች ድምጽ ሰጥተው ከወጡ በኋላ በግላጭ "ቅንጅትን መርጬ ወጣሁ!" በማለት በየመንገዱ፣ ኪዮስኩ እና ሆቴሉ መናገር ጀመሩ። በተለይ በቀበሌ መዝናኛ ክበቦች ከወትሮው በተለየ የህዝቡ ቁጥር ከፍተኛ የነበረ ሲሆን ሻይ ቡና መገባበዙም ይታይ ነበር። ማታ ፌሽታ ለማድረግ የሚቀጣጠሩም ቁጥራቸው ቀላል እንዳልሆነ መረጃዎች ፈሰሱ።

እንዲህ እንዲህ እያለ ድምጽ መስጠቱ በተጨማሪ ሰአት ተጠናቀቀ። የምርጫ ቆጠራ በተጀመረባቸው አንዳንድ የአዲሳአባ ምርጫ ጣቢያዎች የሚያስደነግጡ ቁጥሮች መሰማት ጀመሩ። መጀመሪያ የሰማነው የትምህርት ሚኒስትሯ ገነት ዘውዴ እና የገቢዎች ሚኒስትሩ ጌታቸው በላይ ውጤት ነበር። አስከትሎም የተፈራ ዋልዋ፣ የአፈ ጉባኤው ዳዊት ዮሀንስ እና የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ዋና አዘጋጁ ፍሬህይወት አያሌው ሆነ። ሁሉም በዝረራ መሸነፍ ጀምረዋል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለን ከኢህአዴግ ማእከል የህዝቡን ስሜት የሚያሳዩ መረጃዎች አሰባስበን እንድንመጣ ተነገረን። ለእኔ የደወለልኝ የአርከበ

ፕሮቶኮል የሆነው ጤናዳም በመሆኑ ግራበገባው ሁኔታ "አሊ ሲራጅ የት ሄዶ ነው?" አልኩት። በተዳከመ ድምጽ፣

"አሊ ትንሽ ስሜታዊ ሆኖ ሌላውንም ረበሸ። ህላቄ ለብቻው ወስዶ እያጽናናው ነው። አልቅሶ ሁላችንንም አስለቀሰን። እንኳን አልነበርክ ኢህአዴግ ቢሮ ለቅሶ ቤት ይመስል ነበር" በማለት የሰፈነውን የሀዘን ድባብ ነገረኝ።

በህዝቡ ዘንድ ያለውን ስሜት አሰባስቤ ወደ ኢህአዴግ ቢሮ ሄድኩኝ። ካድሬዎች እየተንጠባጠቡ ቢመጡም በጣም ጥቂት ነበሩ። የተገናኘነው በአሊ ሲራጅ ቢሮ ሲሆን የመጣው በሙሉ መረጃውን እየሰጠና መመሪያ እየተቀበለ ይሄዳል። በመጨረሻ የቀረሁት እኔ ስለነበርኩ ከአሊ ጋር ለብቻ ተፋጠጥን። በርበሬ የለበሰ አይኑ ለብዙ ሰአት እንደተነፋረቀ ያስታውቃል። አሊ የኢህአዴግ ካድሬ መሆን የሌለበት በጣም ቅንና ግልጽ ሰው ነው። ሁሉም ሰው የፈለገውን እየጫነበት ከአቅሙ በላይ ተሸክሞ አየጐበጠ የሄደ ካድሬ ነው።

ጥቂት በፀጥታ ከቆየሁ በሁዋላ፣

"ያ ሁሉ መከራ ታይቶ የሚገርም ውጤት ነው። መሸነፋችን ሳያንስ የቁጥሩ ልዩነት የሚያስደነግጥ ነው" አልኩት።

አሊ የያዘውን ማስታወሻ እየገላለጠ፣

"የአዲሳአባ ብቻ ቢሆን ባልከፉ ነበር። አስቀድሞ የደረሰን የጉራጌ ዞን ነበር። እጩ የነበሩት ዶክተር ካሱ ኢላላ፣ ካሚል አህመድ ተሸንፈዋል። ከአሮሚያ ሻሸመኔ እየተወዳደረ ያለው ኮሚሽነር ወርቅነህ ገበየሁ እና አባዱላ ገመዳ መውደቃቸው ተረጋግጧል። አባዱላ ቅድም ደውሎልኝ ነበር፣ ለሽንፈቱ ተጠያቂ የሚያደርገው ጁነዲን ሳዶን ነው።" አቋርጬው፣

"ለምን? ጁነዲን ምን አደረገ?"

"በሁለቱ መሀል የቆየ ችግር አለ። ጁነዲን ከአሮሚያ ፕሬዝዳንትነት የተነሳሁት በወታደራዊ ኩዴታ ነው የሚል እምነት አለው። የፕሬዝዳንትነቱን ቦታ አጥብቆ ይፈልገዋል። በዛ ላይ አባዱላን በጣም ይንቀዋል። ወታደራዊ አምባገነን አድርጐ ይቆጥረዋል። እንደምታውቀው ጁነዲን በአርሲ ሙስሊሞች አካባቢ ተቀባይነት አለው። ይህን ተጠቅሞ አባዱላ እንዳይመረጥ አድርጓል" አለኝ።

ትንሽ ቆይቼ፣

"እስከአሁን መልካም ዜና የተሰማበት አለ?" በማለት ጠየኩት።

"ከተለመዱት ትግራይ፣ ስልጤ እና አጋር ድርጅቶች ውጪ የሌላው ገና አለየም።"

"በል! የወረደውን መደብ ንገረኝና ወደ ከልሌ ልሂድ" አልኩት።

"ድርጅቱ ከሰአታት በኃላ በቴሌቪዥን እና ሬዲዮ ቀርበ መግለጫ ይሰጣል። በአዲሳአባ ለአንድ ወር የሚቆይ የሰላማዊ ሰልፍ እና ስብሰባ እገዳ

መደረጉን ያሳውቃል። የፀጥታ ስራውም በሰባት ኮማንድ ፖስት እንደሚከፈል ይፉ ያደርጋል። በንጋታው ደግሞ በአዲሳአባ መሸነፋችንን እና በፌደራል ደረጃ ማሸነፋችንን ያስታውቃል"

በድጋሚ አቋረጥኩት፣

"የምርጫውን ውጤት ምርጫ ቦርድ ሳያሳውቅ መግለጹ ህገ - ወጥ አይሆንም?"

"ድርጅቱ መጥቶ ነበር። ከበጣም መጥፎ ፣መጥፎ ይሻላል በሚል እሳቤ እንደሆነ ገለፀልን። ለተወሰነ ጊዜ ጫጫታ ቢያስከትልም አማራጭ እንደሌለ ነገረን። በተለይም በፌደራል ደረጃ ኢህአዴግ ማሸነፉን መግለጽ ለሻእቢያ እና ለመከላከያ ሰራዊት ትልቅ ፋይዳ እንደሚኖረው አብራራልን። ከፍተኛ መደናገጥ ውስጥ የገባው መዋቅራችንን መግለጫውን ሲሰማ ጭንቀቱ ይቀንስለታል። የውጭ ሀይሎች ለሚያነሱት የህገወጥነት ጥያቄ የቅንጅት አመራሮች በአዲሳአባ አሸንፈናል ሲሉ ለምን አልተቃወማችሁም የሚል ጥያቄ እናቀርብላቸዋለን አለን"

አያያዘና ቀጠለ፣

"የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ያስፈለገበት ምክንያት ህዝቡ ከሚያዝያ 30 በላቀ ሁኔታ ግልብጥ ብሎ በግብታዊነት ወደ መስቀል አደባባይ ሊወጣ እንደሚችል በመገመቱ ነው። እንደ አሜሪካን ግቢ፣ ፈረንሳይ፣ መርካቶ፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ዩንቨርስቲዎች አካባቢ ምልክቶች አየታዩ ነው።"

"አሊ! የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለማወጅ ፓርላማው ተጠርቶ መወሰን አለበት። አለበለዚያ ህገወጥ ይሆናል። ተቃዋሚዎች ወደ ፍርድ ቤት ቢሄዱ ሊረቱ ይችላሉ" አልኩት።

"ጉዳዩ የፍርድ ቤት ሳይሆን የህገመንግስት ይሆናል። ህገ መንግስት ተጣሰ/ አልተጣሰ ብሎ የሚወስነው ፌዴሬሽን ምክር ቤት ስለሆነ ችግር አያመጣም። ፌዴሬሽን ምክር ቤት ወሳኝ የሚሆነው እንደዚህ አይነት ፈታኝ ወቅት ሲያጋጥም ነው።"

እነሆ! ለአንድ ወር የሚቆይ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በአዲሳባ ማወጁን ተናገረ። አዲሳአባ በሰባት ማዘጋጥ ጣቢያ ተከፈለች። ከፍለ ከተማ እና ቀበሌ ባልተገለፀ አዋጅ እንዲፈርሱ ተደረገ። ነባሩ መዋቅር ከስራ ውጪ ተደረገ። አርከበን ከትግራይ አጅበውት የመጡት ካድሬዎች የሰባቱ ማዘጋጥ ጣቢያ ሀላፊዎች ተደረጉ። አርከበ እቁባይ ፊት አውራሪያቸው ሆነ። እያንዳንዱ ውሳኔ በእነሱ ስር ማለፍ ግዴታ ሆነ። ከየትኛውም የኢህአዴግ ካድሬዎች በላይ ቂም የቋጠሩት እነዚህ የህውሀት ካድሬዎች ከተማዋን ራቁቷን ለማስቀረት ዘመቻ ጀመሩ።

በአስተዳደሩ ቋት ውስጥ ያለው ገንዘብ ሙሉ በሙሉ እንዲወጣ ተደረገ። ለዓመታት ተቋርጦ የነበረው የመደበኛ ደሞዝ ጭማሪ ተፈቀደ። ብዙዎቹ የቀረጥ አይነቶች በሚዘገንን ሁኔታ ቅናሽ ተደረገ። በህይወቴ እንደዚህ አይነት የዱርዬ እና ማጅራት መቺነት ስራ አላጋጠመኝም። ከአሊ አብዶ ዘመን ጀምሮ የተሰሩ ቪላ እና ቁጠባ ቤቶች በዜሮ ዋጋ ለኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎች ተሸጠ። ለጥቃቅን ተጠቃሚዎች በመንግስት ወጪ የተሰሩ ማምረቻ ሼዶች ለሚቀርቧቸው አዳዲስ ባለሀብቶች ሸጡ። በመዲናይቱ የሚገኙ ክፍት ቦታዎች ተለቅመው ተሸጡ። የአዲሳባ ትራንስፓርት አገልግሎት ሙሉ በሙሉ ወደ ፊደራል ዞረ።

ምእራፍ አስራ ስምንት

ለምን ተሸነፍን?

"አንድም ሁሉን ታገኛለህ፣ አሊያም ሁሉን ታጣለህ።"
በረከት ስምኦን (የሁለት ምርጫዎች ወግ)

በኢህአዴግ የካድሬነት ዘመኔ ፓርቲው በምርጫ 97 ለምን ተሸነፈ የሚለው ሀሳብ ሰፋ ተደርጐ የተነሳው እና የተሳተፍኩት ለሶስት ያህል ጊዜያቶች ነበር።

በመጀመሪያው በምርጫ 97 ማግስት ከኢህአዴግ ማዕከል በተዘጋጀ ጽሁፍ በመላ ሀገሪቱ የሚገኙ መካከለኛና ከፍተኛ አመራሮች እንዲወያዩ ተደርጓል። በዚህ ስብሰባ በሀገር ደረጃ ሊነሱ የሚችሉ የሽንፈቱ ምክንያቶች ተገልፀው ነበር። ከኢህአዴግ ማእከል የተበተነው ጽሁፍ በችኮላና በስሜት የተፃፈ ስለነበር እጅግ አስደንጋጭ አርፍተ ነገሮችን የተሸከመ ነበር። ህዝብን እንደ ህዝብ (በተለይም የጉራጌ ፣የአማራ እና የአዲሳባ) የሚፈርጅ ሰነድ ተዘጋጅቶ ነበር።

የምርጫ 97 ሽንፈት **ለሁለተኛ** ጊዜ ተነስቶ ያነጋገረው በአዳማ የከፍተኛ ካድሬዎች ስልጠና ላይ ነበር። ይህ ለወራት የዘለቀው ስልጠና ሁሉም ሚኒስትሮች፣ የክልል ባለስልጣናት፣ በመላ ሀገሪቱ የሚገኙ ከፍተኛ ካድሬዎች የተገኙ ሲሆን የቀረበው ሰነድ በአቶ መለስ የተፃፈው "ዲሞክራሲና ዲሞክራሲያዊ አንድነት በኢትዮጵያ" የሚለው ነበር። ይህ ስልጠና አንጻራዊ በሆነ መንገድ የተለያዩ አመለካከቶች የተራመዱበት ስለነበር በብዙ ካድሬዎች ዘንድ በበጐ መልኩ ይነሳል። ለእኔም በበርካታ ሀገር አቀፍ አጀንዳዎችና የካድሬዎች ስብእና ላይ የተሻለ ስእል እንድይዝ አድርጐኛል። አስገራሚ ክስተቶችም ነበሩ።

ከሁሉም ያስገረመኝ አጠገቤ ተቀምጦ የነበረው ሽማግሌው ስብሀት ነጋ እስከ ምሳ እረፍት ለሁለት ሰአት፣ ከምሳ በኃላ ደግሞ ለሶስት ያህል ሰአታት ያለማቋረጥ እያንኮራፉ ይተኛ ነበር። ከእንቅልፉ ሲባንን የሚሰጣቸው አስተያየቶች በፍጹም ከአጀንዳው ጋር የማይያያዙ፣ መያጋርና መጨበጫ

የሌላቸው፣ አናዳጅ ነበሩ። አንዳንዴም ከአዲሱ የኢህአዴግ ፓሊሲ ጋር የማይሄዱና ፓርቲው እርግፍ አድርጌ የተዋቸውን ያነሳ ነበር። የስብሀት ወንበር አጠገብ ጐትቶ የወሰደኝ የአጐቱ ልጅና የቂርቆስ ከንቲባ ታጋይ አተይ ወደ ጆሮዬ እየተጠጋ፣

"የሚገርምህ ለሊቱን ሙሉ መጠጣትህን አቁም፣ አንድ ቀን በተቀመጥክበት ትፈነዳለህ ብሎ ያልመከረው ቤተሰብ የለም። በቀን ግማሽ ጠርሙስ ሺቫስ ጠጥቶ ያድራል። በዚህ ምክንያት ከ1995 በኃላ ጭንቅላቱ ማሰብ አቁሚል። አዲስ አስተሳሰብ መቀበል አይችልም። እንደ ላሜ በራ የድሮውን እያመነዠከ ነው የሚኖረው። ምርጫ 97 መካሄዱን ስለማወቁ እርግጠኛ አይደለሁም።" ይለኝ ነበር። ለነገሩ የሚዲያ ሞኒተሪንግ ላይ እኔና ሽመልስ ከማል ለበረከት ስምኦን "ስብሀት ነጋ የመንግስትን ውሳኔ ተቃርኖ ለቪኦኤ መግለጫ ሰጠ" ብለን ስንነግረው እየተናደደ፣

"እናንተ ደግሞ ስጋ ቁጠር ቢሉት ጣፊያ አንድ አለ! እንዳለው ሆናችሁ! ይህን ተፈጥሮ ያቆመችውን ሽማግሌ ትታችሁ ሌላ ካለ ንገሩኝ "ብሎን የለ።

የምርጫ 97 ሽንፈት **በሶስተኛ** ደረጃ የተነሳው የምርጫ 2000 ስትራቴጂዎችን ለመወሰን የከተማው ኢህአዴግ ከንፍ በበረከት ቢሮ በተሰበሰበን ወቅት ነበር። ይህ ግምገማ በረከትን ጨምሮ ከሰባት የማንበልጥ ካድሬዎች የተሳተፍንበት ስለነበር ወደ ዝርዝር ጉዳዮች ገብተን ለመፈተሽ እድሉን ሰጥቶናል። ምርጫ 97 ታሪክ ሆኖ አልፏልና ሁሉም የልቡን ለመናገር ፍራቻ አልነበረውም። ከጣራ በላይ በመሳቁ የምናውቀው ካሚል ወደ ህላዌ ዞሮ፣

"ህላዌ ነብሴ! ያቺ ሚያዝያ 29 የተቀመጥክባትንና መቶ ሰማኒያ ዲግሪ እያሽከረከርክ መግለጫ የሰጠህባትን ተሽከርካሪ ወንበር ለማስታወሻ እቤትህ መውሰድ ነበረብህ!" በማለት ቀልዶበታል። በረከት በበኩሉ እንባውን እየዘራ አባዱላ በክርክሩ ወቅት እንዴት እንደተደናበረ በድራማ መልክ አሳይቶናል።

እንዲህ ነበር ያጫወተን...

አባዱላ ለክርክር ሲሄድ በማስታወሻው ላይ ኢንተርሀምዌይ የሚለውን ቃል ያሰፍራል። ክርክሩ ሲጀመር አደገኛ ቃላትን ከማምረት የማይቦዝን የተባለው ዶክተር መራራ ጉዲና ወደ አባዱላ ዞሮ፣

"ጀነራል ልበልህ?፣ፕሬዝዳንት ልበልህ?፣ አቶ ልበልህ?" ብሎ ይጠይቀዋል። በጥያቄው የተደናበረው አባዱላ ተራው ደርሶ መናገር ሲጀምር ይህቺ ሲያጠናት የከረመቸው ከይሲ ቃል ትጠፉበታለች። ማስታወሻውን እየገላለጠ ለሶስት ጊዜ "እናንተ እኮ! እናንተ እኮ! እናንተ እኮ!" እያለ ባጋጣሚ አገኛት። በደስታ ፊቱ ፈክቶ፣

"እናንተ እኮ ኢንተርሀምዌይ ናችሁ!" በማለት ምጡን ተገላገለ።

የአርሲዋ ወይዘሮ በሽልም አወጣችው።

በበረከት ቢሮ በነበረን ስብሰባ በ97 ምርጫ ስለነበረው ከርከርና የኢህአዴግ ካድሬዎች ደካማ ብቃት፣ ኢንተርሀምዌይና የአቶ በድሩ ያልተገራ ንግግር፣ ብራ መብረቁ ቅንጅት፣ የኢህአዴግና የቅንጅት ምርጫ ምልክት... ወዘተ አንስተን ነበር። በመሆኑም እነዚህን የተመለከቱ ቁምነገሮች ስለ ምርጫ 2000 በሚተርከው ክፍል ላይ በጊዜውና በሰአቱ ይቀርባል። ለዚህኛው ክፍል በምርጫ 97 ማግስት በኢህአዴግ ማእከል በተዘጋጀው ሰነድ ላይ እና በአዳማ የካድሬዎች ስልጠና ላይ ቀርቦ ከርከር የተደረገበትን ለይተን እንመልከት።

ለምን ተሸነፍን? (በምርጫ 97 ማግስት)

"Protesting Vote"

(የእንግሊዘኛ ቃላትን የተጠቀምኩት በአማርኛ ተስተካካይ ፍቺ ስለሌላቸው ሳይሆን እልም ባለ ገጠር የሚኖሩ አርሶ አደር ካድሬዎቻችን ሳይቀሩ ገበሬውን ሰብስበው በዚህ መልኩ ዲስኩር ሲያሰሙ ስለነበር ለአርሶ አደር ካድሬዎቻችን ማሰታወሻ እንዲሆን ብዬ ነው። ነብሱን ይማረውና የኮመዲያን ተሰፉዬ ካሳ "ፈንዱ!" ቀልድ ልብ ይሏል።)

የመሸነፋችን የመጀመሪያ ምክንያት ተደርጐ የተወሰደው "ህዝቡ የሰጠው የተቃውሞ ድምጽ (protesting vote) ነበር" በሚል ተገለፀ። ኢህአዴግ በከተሞች ሙሉ በሙሉ በገጠር ደግሞ በጥቂት ቦታዎች ውድቀት ያጋጠመው ህዝቡ ለምንግዜውም ኢህአዴግን ማየት አልፈልግም ፣ የሚሻሉኝ ተቃዋሚዎች ናቸው ከሚል መነሻ እንዳልሆነ ፣ህዝቡ በጊዜያዊ ቅሬታና ብሶት ተነሳስቶ ለኢህአዴግ የደውል ማንቂያ የተቃውሞ ድምፅ አሰምቷል ተባለ። ከተቃውሞ አንጻር ልዩ ትኩረት የተሰጠው የመልካም አስተዳደር እጦት ነበር። የዚህ ግምገማ ይዘቶች፣

"ኢህአዴግ የህብረተሰቡን ችግር ለማዳመጥ የሚያስችል ጆሮ አልነበረውም፤ አሳምኖ ከማሰራት ይልቅ በአስተዳደራዊ ጫናዎችና የተለያዩ አስገዳጅ ተጽእኖዎችን እንጠቀም ነበር፣ ፀረ-ዲሞክራሲያዊ አካሄዳችን ህብረተሰቡ እንዲያማርርና ተስፉ እንዲቆርጥ አድርጐታል፣ ለመልካም አስተዳደር እጦት ምክንያት የሆኑ ችግሮችን ተቋማዊ በሆነ መንገድ አልፈታንም" የሚል ነበር።

"Too little Too late"

በሁለተኛ ደረጃ ኢህአዴግ ሽንፈት ያጋጠመው የተጀመሩት ተስፉ ሰጪ የልማት ስራዎች እጅግ በጣም ትንሽ እና ዘግይተው የተጀመሩ በመሆናቸው

እንደሆነ ተገለፀ። በተለይም በከተሞች ኢህአዴግ ስራ የጀመረው ዘግይቶና በቁጥቁጥ በመሆኑ የስራ አጥነት ቁጥር (በተለይም በወጣቱ) አደገኛ ደረጃ ላይ መድረሱ ለምርጫው መሸነፍ አበይት ምክንያት እንደሆነ ተነገረ።

ከማእከል በወረደው ሰነድ ላይ በተደረገው ውይይት ካድሬዎች፣ "አስርተ አመታትን በስልጣን ላይ ቆይተን እንዲህ አይነት ግምገማ ተገቢ አይደለም። ለወጣቱ ስራ መፍጠር የመንግስት ሀላፊነት መሆኑ እየታወቀ አደገኛ ቦዘኔ፣ ፍንዳታ የሚሉ ቃላትን መጠቀም በአንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ አቅጣጫ ተከትለናል። ወጣቱ በአገሩና በመጻኢ እድሉ ላይ ተስፉ በመቁረጥ ስደትን እንደ አማራጭ ወስዷል። ወጣቱ በሀገሩ ጉዳይ ላይ ባይተዋር እንዲሆን ተደርጓል። በአደንዛዥ እጽ የደነዘዘ ጫት ቃሚ ትውልድ እንዲፈጠር አድርገናል" በማለት አንስተው ነበር።

"እግር ከወርች"

ከዚህ አንፃር ትልቅ ውርጅብኝ ያረፈበት ለካድሬውና አባላት የተዘጋጀው የምርጫ ስነምግባር ደንብ ነበር። በታህሳስ ወር 1997 በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ጋዜጣ ልዩ እትም የስነምግባር ደንቡን ሙሉ ለሙሉ በመፃፍ ለእያንዳንዱ አባል መስጠታችን ልክ እንዳልሆነ ተገለፀ። አባላችንን ከድርጅት ትባረራለህ፣ በህግ ትጠየቃለህ ማለት አልነበረብንም ተባለ። ኢህአዴግ አባላቶቹን በስነ ምግባር መመሪያ እግር ከወርች መታሰሩን የተመለከቱት ተቃዋሚዎች ፓስተር ከመቅደድ ጀምሮ በርካታ ፀረ ዲሞክራሲ ተግባራት እንዲፈጽሙ እድል ተፈጠረላቸው በማለት ሰነዱ ተቃዋሚዎችን ተጠያቂ አደረገ። ተቃዋሚዎች ምርጫውን ለአመጽ እንደሚጠቀሙበት ከግምት ከተን አባላችንን ማዘጋጀት ነበረብን ተባለ። ከዚህ በተጨማሪ የፀጥታ አካላት በተለይም የአዲሳአባ ፓሊስ አባላት የኢህአዴግ አባላትን በአይነ ቁራኛ በመከታተል ለተቃዋሚ ሽፉን ሰጥተው እንደነበር ተገለፀ። ርግጥ ሰነዱ አባላትንም ተጠያቂ ከማድረግ አልተመለሰም። ተቃዋሚዎች የምርጫ ቅስቀሳ ለማድረግ ህጉ የማይፈቅላቸው ቦታ ሲንቀሳቀሱ፣ ህግ መንግስቱን የሚቃረን ተግባር ሲፈጽሙ አይቶ እንዳላየ ሆነዋል በማለት።

"ጥገኝነት የተሸከመ የከተማ ነዋሪ"

በዚህ ርዕስ ስር ሰነዱ ለማመላከት የሞከረው በአንድ በኩል በከተማ የሚኖረው ዜጋ ከልማትና መልካም አስተዳደር እጦት አንፃር ወደ ብሶትና ተስፉ መቁረጥ እንዲሄድ አድርገነዋል ይላል። በሌላ በኩል ጥገኝነት በከተማው ህዝብ አወቃቀር ላይ የተመሰረተ ነባራዊ ሀቅ እንደሆነና የተሟሟቀ ትግል

ባልተለኮሰበት ሁኔታ ነዋሪው ጥገኝነት መሸከሙ አይቀሬ መሆኑን ከግምት መግባት እንዳለበት ያሳስባል። በተለይም በሞቀበት የሚጣደው የተማረው ክፍል በባህሪው የሁለት አመለካከቶች ተሸካሚ በመሆኑ በምርጫ 97 የጥገኝነት አመለካከቱ የበላይነት በመያዙ ፀረ - ዲሞክራሲ ሀይሎችን ተቀላቅሏል። በከተማው የተዘረጋው የኢህአዴግ መዋቅር ከህብረተሰቡ በባሰ የጥገኛ ዝቅጠት የተተበተበና ዋነኛ አቀንቃኝ በመሆኑ ነዋሪውን ከቀዝቃዛ ሁኔታ አውጥቶ በማያቋርጥ የሰላ ትግል ማስገባት እንዳልቻለ ያስገነዝባል።

በማእከል የተዘጋጀው ሰነድ ለምርጫ 97 ውድቀት በተዘዋዋሪ መንገድ የከተማው ነዋሪን ተጠያቂ አድርጓል። ኢህአዴግ የከተማው ህዝብ ያለበትን ችግር በመረዳትና ከስሩ ለመንቀል በማሰብ ልማታዊና ዲሞክራሲያዊ ፓሊሲዎችን ቀርጾ እየተንቀሳቀሰ ባለበት ሁኔታ ህዝቡ መፃኢ እድሉን የሚያጨልም ውሳኔ መወሰን እንደማይገባው በማመልከት። ምርጫ 97 ከመካሄዱ በፊት በነበሩት ሁለት አመታት በሀገራችን ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ባለሁለት አሀዝ እድገት ማስመዝገባችንን እየተመለከተ ድምጹን ለፀረ-ዲሞክራሲ ሀይሎች መስጠት ሚዛናዊ አይደለም በማለት ይወቅሳል። በተለይም የአዲሳባ ህዝብ በአጭር ጊዜ ውስጥ አይቶ የማያውቀውን ልማት በተመለከተበት ሁኔታ ተስፉውን የሚያጨልም ውሳኔ መወሰኑ የተሸከመው ጥገኝነት በቀላሉ የማይራገፍ መሆኑን እንደሚያሳይ ሰነዱ አስምሮበታል። ኢህአዴግ ለከተማው ህዝብ ከፍተኛ በጀት በመመደብ ከ30,000 በላይ ኮንደሚኒየም ገንቢቶ የቤት ባለቤት እያደረገ ባለበት ወቅት፣ ለአስር ሺዎች የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የመስሪያ ሼዶችንና መሸጫዎችን በመንግስት ወጪ ሰርቶ ባስረከበበት ሁኔታ፣ ሌሎች መሰረተ ልማቶች በተለይም ትምህርት ቤቶች፣ ጤና ጣቢያዎችና ደረጃቸውን የጠበቁ መንገዶች ተገንበተው ለአገልግሎት በቀረቡበት ሁኔታ የመዲናይቱ ነዋሪ ፀረ -ልማት ሀይሎችን መምረጡ የጠገኝነት ሰለባ በመሆኑ እንደሆነ ሊታወቅ እንደሚገባ የቀረበው ጽሁፍ አመላክቷል።

በፀረ ዲሞክራሲ የተወረረ የከተማ መዋቅር

ኢህአዴግ ጥገኛ ሀይሎች ብሎ በፈረጃቸው ሰለባ ከመሆን አንፃር የአዲሳአባ ህዝብ ብቻ ሳይሆን በመዲናይቱ የነበሩ የኢህአዴግ ካድሬዎችና አባላት ተጠቂ እንደነበሩ ተገልጾ ነበር። በተለይም ነባር የቀበሌ ካድሬዎችና አባላት ኢህአዴግን አልመረጡም የሚል ክርክር በየመድረኮቹ ተደምጧል። ይህ አስተያየት በግል የፕሬስ ውጤቶች፣ማህበራዊ ድህረ ገጾች እና ምርጫ 97 አስመልክቶ በተፃፉ መጽሐፍት ሳይቀር በተደጋጋሚ ተገልጾአል። አንዳንዶቹ የሂሳብ ስሌት በመስራት ግምቶችን ወደ እውነት በማስጠጋት አሳይተዋል።

ርግጥም ከስሌቱ ተነስቶ የቀረቡት ግምቶችና ድምዳሜዎች መሬት የሚወድቁ አይደሉም።

ድህረ እና ቅድመ ምርጫን በኢህአዴግ ውስጥ ሆኖ እንደተከታተለ ሰው ይህን ድምዳሜ ሙሉ ለሙሉ ለመቀበል ያስቸግረኛል። ርግጥ ድምጽ መስጠት በሚስጥር የሚካሄድ በመሆኑ ወረቀቷ ላይ የሰፈረውን የመጨረሻ ምልክት ግለሰቡና እግዜር ብቻ ያውቁታል። ስለዚህ እኔም ብሆን ልሰጥ የምችለው ቁጥር በመቀነስና በመደመር ከሚሰጥ መላምት የሚዘል አይሆንም። ልዩነቱ ከውስጥ ወደ ውጭ የሚሰጥ ግምት መሆኑ ብቻ ነው።

ወደ ግላዊ ምልከታዬ ከመግባቴ በፊት ሁላችንንም ሊያስማሙ የሚችሉ ቅድመ ሁኔታዎች (assumption) የሚመስሉኝን ሁለት ቁምነገሮች ላስቀምጥ። የመጀመሪያው በአዲሳአባ የተካሄደው ድምፅ መስጠትና ቆጠራ በመሰረቱ መጭበርበር አልተፈፀመበትም የሚለው ይሆናል። በሁለተኛ ደረጃ ሁላችንንም የሚያግባባው ቁምነገር የአዲሳአባ የቆጠራ ውጤት ይሆናል። በየትኛውም መስመር ያለ ሰው እንደታዘበው በሁሉም የመዲናይቱ ምርጫ ጣቢያዎች የቅንጅት እጩዎች እጅግ በሚገርም ቁጥር (landslide) የህዝብ ድምፅ አግኝተዋል። በብዙዎቹ ምርጫ ጣቢያዎች ተከታዩን ድምፅ ያገኙት የኢህአዴግ እጩዎች ነበሩ። ለምሳሌ እኔ በቀጥታ ከተከታተልኳቸው የምርጫ ክልሎች አንዱ በሆነው ወረዳ 20 (ቄራና ጐፋ ሰፈር) የቅንጅት እጩ ከ20 ሺህ በላይ ድምፅ ሲያገኝ የኢህአዴግ እጩ የነበረው ገበረዋህድ 3 ሺህ አካባቢ አግኝቷል። ከምርጫ 97 በኃላ የአዲሳአባን የፓለቲካ ስራ አቅጣጫ ለማስቀመጥ ስንሞክር እንደ ግብአት ከተጠቀምንባቸው ነገሮች አንዱ በመዲናይቱ ምርጫ ክልሎች የኢህዴግ እጩዎች ያገኙትን የድምፅ መጠን ነበር። በወቅቱ ያሰባሰብናቸው መረጃዎች እንደሚያመላክቱት የሁሉም ምርጫ ውጤቶች በወረዳ 20 ከተገኘው ጋር ተቀራራቢ ነበር። በድምሩም ሲታይ ኢህአዴግ በአዲሳአባ ከ70 ሺህ ያላነሰ ድምፅ አግኝቷል።

ከእነዚህ ሁለት መነሻዎች ተነስተን ሁለት መሰረታዊ ጥያቄዎችን በማንሳት ጉዳዩን እንመርምረው። ከምርጫ 97 በፊት ኢህአዴግ በመዲናይቱ ስንት አባላት ነበሩት? ኢህአዴግ የመዲናይቱን ካድሬዎች ለሽንፈቱ ለምን ተጠያቂ አደረገ?

የአዲሳአባ ኢህአዴግ መዋቅር ፍርክስክሱ የወጣው አርከበ እቁባይ ወደ አዲሳአባ ተመድቦ በመጣ በጥቂት ወራት ውስጥ ነበር። በወቅቱ እሱን ጨምሮ ከየክልሉ የመጡት ንቅል ካድሬዎች የመጀመሪያ ስራ ይህን መዋቅር በማፈራረስ ባዶ ማስቀረት ነበር። አርከበ በውስጠ ድርጅት ስብሰባ ላይ አፍ አውጥቶ፣

"አባላት አያስፈልገንም። ምርጫ 97 በዝረራ የምናሸንፈው እየሰራን ያለነው የልማት ስራ በህዝቡ ዘንድ እርካታ እተፈጠረ ስለሆነ ነው" በማለት ተናግሮ ነበር።

የአርከበን ቃል እንደወረደ የሚያስተጋቡት አዲሶቹ ካድሬዎች ሳይቀንሱ ሳይጨምሩ አባላትን አዳራሽ በመሰብሰብ ተናግረዋል። ይህ ንግግር ወትሮም "ኢህአዴግ ነኝ!" ብሎ አዲሳአባ ህዝብ ፊት መናገር እንደ ውርደት እንደሚያስቆጥር እና እንደሚያሸማቅቅ ካለመገንዘብ የሚመነጭ ነበር። በአዲሳባ የሚገኙ የኢህአዴግ አባላት ፓርቲውን በመቀላቀላቸው ከህብረተሰቡ እንደተገለሉ ጠንቅቀው ያውቃሉ። ከዚህም አልፎ ህዝቡ "ለሆዳቸው ያደሩ! ህሊናቸውን የሸጡ!" የሚል ስያሜ እንደሰጣቸው ዘወትር የሚያዳምጡት ነው። እናም የህብረተሰቡ አመለካከት ህሊናቸውን እያቆሰለ ኢህአዴግን መቀላቀላቸው እንደ ውለታ መቆጠር ይገባዋል ብለው ሲጠብቁ "አታስፈልጉም" መባላቸው ቁጣ ቀሰቀሰ። ብዙዎቹ እየዛቱ ድርጅቱን ለቀው ወጡ። አንዳንዶቹም ከፓርቲው በተፃራሪ በመሰለፍ ፀረ-ኢህአዴግ አቋማቸውን በግላጭ ማስተጋባት ጀመሩ። እነዚህ አባላት ቁመናቸው ድኩማን ቢሆንም የኢህዴግን አየር የተሞላ ፊኛነት አብጠርጥረው ስለሚገነዘቡ በአወቅኩሽ ናቅኩሽ አፈር ድሜ ማብላት ቀጠሉ።

(በነገራችን ላይ ከብዙ ተቃዋሚዎች በባሰ ኢህአዴግን አምርሮ የሚጠላው፣ በግላጭ የሚሳደበው፣ በፓርቲው ውስጥ ያለ የዘረኝነት እና አድሎን የሚያጋልጠው በኢህአዴግ አምኖ እና ተጠምቆ የኖረውና በተለያየ ምክንያት ድርጅቱን ለቆ የወጣው ነው። አብዛኛውን ጊዜ ካድሬዎች ኢህአዴግን ጥለው ሲወጡ የፓርቲውን ባዶነት ስለሚገነዘቡ ከሌላው በባሰ ይንቁታል። አንዳርጋቸው ጽጌ "ለኢትዮጵያ ከኢህአዴግ በላይ ጠላት የለም!" ሲል ሰምተነዋል። ስዬ አብርሀ "አቶ መለስ እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል እንዳለችው እንስሳ ነው!" በማለት የፃፈውን አንብበናል። በተመሳሳይ ዶክተር ነጋሶ ኢህአዴግን ለቀው ሲወጡ "አሁንስ መንግስቱ ሀይለማርያም መሰልከኝ!" በሚለው ታሪካዊ ንግግራቸው እናስታውሳቸዋለን። የአንድነት የህዝብ ግንኙነት ሀላፊው ወጣት ሀብታሙ አያሌው በኢቲቪ ቀርቦ " አሰፉ ማሩን በጠራራ ፀሀይ ገደላችሁ!" በማለት ሲከራከር ሰምተነዋል።

ነገርን ነገር ያነሳዋል እንዲሉ ወጣት ሀብታሙን በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ለማጥመቅ ከተጉት ካድሬዎች አንዱ እኔ ነበርኩ። አላጌ ድረስ በመውሰድ። ሀብታሙ ሲያስፈልገው ጥላሁን ገሰሰን፣ ሲያሰኘው ቴዲ አፍሮን፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ አርቲስት ጌትነት እንየውን የመሆን ተሰጥኦ ያለው ወጣት ነበረና ዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት እንደሚቆረቁረው የሚጠበቅ ነበር።ግራም ነፈሰ ቀኝ

ኢህአዴግ ትልቅ ወጣት አጥቷልና የበቀል ጅራፉን በመምዘዝ ከእነ አንጂለም አራጌ ጋር መቀላቀሉ የጊዜ ጉዳይ ብቻ ይሆናል። ደግነቱ ሀብታሙ የበላይ ዘለቀ ልጅ ነውና ...)

በመሆኑም ኢህአዴግ ወደ ምርጫ ዋዜማ የገባው ግማሽ አባሉን አታስፈልጉኝም በማለት አባሮ፣ ከፊሉን ጥገኛ እና ፀረ-ዲሞክራሲ ብሎ ከሚጠራቸው ቀላቅሎ ነበር። በዚህም ምክንያት በወቅቱ የተመዘገቡ አባላትና ደጋፊዎች ቁጥር በከተማ ደረጃ ከ3,500 አይበልጥም ነበር። እነዚህ አባላት ራሳቸውን ጨምሮ ቤተሰባቸውን እና በአካባቢያቸው የሚገኙትን በመቀስቀስ ለኢህአዴግ ድምፅ እንዲሰጥ አድርገዋል። ቁጥሩ እጅግ አነስተኛ ቢሆንም 70 ሺህ ያህል ህዝብ ኢህአዴግን የመረጠው በእነዚህ አባላት ጥረት እንደሆነ ይገመታል። ስለ ምርጫው ቆጠራ ትክክለኛነት እስከተስማማን ድረስ እውነቱ ይህ ነው።

ከግል ሚዲያ ተቋማት እና ከተጻፉ መጽሐፍት አንፃር "ኢህአዴግ አባላቶቹም አልመረጡትም!" የሚለው ድምዳሜ ምንጩ ሁለት ይመስለኛል። በአንድ በኩል ትክክለኛ መረጃ ስላልነበረ እና ኢህአዴግን አግዝፎ ከማየት የሚነሳ ሲሆን በሌላ በኩል ኢህአዴግ አስቀድሞ ባዘጋጀው ወጥመድ በመጠለፍ የትግራይ ተወላጅ እና የመከላከያ ሰራዊት የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎች አድርጎ ከማሰብ እንደመጣ ይታመናል። በርግጥም እየቀረበ ያለው የሂሳብ ስሌት ማብራሪያ ሲሠጥበት ያንን ያመላክታል።

በተቃራኒው ኢህአዴግ በአዲሳአባ የሚገኘው መዋቅሬ ያልመረጠኝ በፀረ-ዲሞክራሲ ስለተወረሩ ነው የሚል ምክንያት ያቀርባል። መዋቅሩ ከድርጅቱ መርህ ተቃራኒ በመቆም ፀረ-ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ እንደተንቀሳቀሰ፣ በተለይም በቤት ማፍረስና ልማት መዋጮ ነዋሪውን ከማሳመን ይልቅ አስተዳደራዊ መንገድ እንደተጓዘ፣ በሌብነት እና ጉቦ በመጨማለቃቸው ህዝቡ የተቃውሞ ድምፁን (protesting vote) እንደሰጠ አስታውቋል። ይህም በአንድ በኩል የአዲሳአባ ህዝብ የመርህ ሳይሆን የአፈጻጸም ጉድለታችን ተመልክቶ ድምፁን እንደነፈገን ተደርጎ እንዲነገር አደረገ።ይህ ድምዳሜ ነባሩን ካድሬ በማጨድ ድርጅቱን ለማዳን መደላድል ፈጠረ። መዋቅሩን ገሎ ድርጅቱን ማዳን!!

"በሁለት ቢላዋ የሚበላ ባለሀብት"

ባለሀብቱ ላይ የተቀመጠው መደምደሚያ የሁለት ምርጫዎች ወግ ሳትቀንስ ሳትጨምር ውርስ ስላደረገችው እኔም እንደ ወረደ ማቅረብ መረጥኩ።

በሁለት ምርጫዎች ወግ ምእራፍ ሁለት "ሶስተኛው አገራዊ ምርጫና የቅድመ ምርጫ ሂደት" በሚለው ርእስ ስር፣

"... ቁጥሩ የማይናቀው ባለሀብት ለማትቀረው ለዚህች ቀን በመዘጋጀት ላይ መሆኑን በሚያሳይ አኳኃን ወንበር ለማግኘት የሚወዳደሩ ፓርቲዎች በጠሩት ስብሰባ ላይ ሁሉ መገኘት ጀምሯል። በተገኘበት መድረክ ግንባሩን ከማስመታት አልፎ ለሁሉም የማሸነፊያ ምክሩን ይሰጣል። ለተቃዋሚ የነገረውን የማሸነፊያ ስትራቴጂ ሳይጨምር ሳይቀንስ ለኢህአዴግ ይለግሰዋል። ለኢህአዴግ የነገረውን ስልት ለተቃዋሚዎች ይመክራል። ሁለት ባላ ትከል አንዱ ቢሰበር በአንዱ ተንጠልጠል የሚለው አገርኛ ብሂል ዛሬ ገና የተገለጠለት ይመስል ለሁለቱም ብር ይበትናል። ለኢህአዴግ በግራ እጁ ከሰጠ ቀኝ እጁን ለቅንጅት ይዘረጋል። የሚጠነቀቀው ለአንዱ ሲሰጥ ሌላው እንዳያየው ብቻ ነው።..." በማለት ለንባብ አብቅታለች።

"ጉራጌ መራሽ አብዮት"

በምርጫ 97 ማግስት አቶ መለስና በረከትን ጨምሮ ከፍተኛ የኢህአዴግ ካድሬዎች "ጉራጌ አብዮት አካሄደብን" በማለት ይናገሩ ነበር። በኢህአዴግ ማእከል በተዘጋጀው ሰነድ ላይ የጉራጌ ብሄረሰብ ከትምክህት ጐራ ጋር በተቀላቀሉ ልጆቹ ምክንያት የሀይል አሰላለፍ ቀውስ ውስጥ በመግባት ከጥገኛ ሀይሎች ጋር ተሰልፎ ወደ ዝቅጠት ገብቶ እንደነበር ይገልፃል። በመላ ሀገሪቱ የሚገኙ የብሄረሰቡ ተወላጆች (በጉራጌ ዞን ያለው መዋቅራችንን ጨምሮ) የዜጐችን በነፃነት የማሰብና የመምረጥ መብት በመጋፋት እስከ ጐጣቸው በመሄድ "ኢህአዴግን የመረጠ ውሻ ይውለድ!" የሚሉ ቃል ኪዳኖችን እስከ ማጥለቅ እና መማማል ዘልቀው ነበር በማለት ይከሳቸዋል። የጉራጌ ብሄረሰብ እንደ ሌሎች የሀገራችን ጭቁን ብሄረሰቦች ህገ -መንግስታዊ መብቱ በተከበረበት፣ ራሱን በራሱ የማስተዳደር መብት በተገሩናፀፈበት ሁኔታ ወደ ትምክህት ሀይል ሽግሽግ ማድረጉ ያልተጠበቀ እንደነበር ሰነዱ አመላክተ።

በቀረበው ዶክመንት ላይ በመመስረት በየወረዳው የተካሄዱት መድረኮች አስደንጋጭ ነበሩ። የምርጫ 97 ውጤት የኢትዮጵያ ህዝቦች የትግል ውጤት መሆኑን በመካድ "ጉራጌ መራሽ አብዮት" የሚል ስያሜ እስከ መስጠት ተደረሰ። ጣቶች በመሉ ወደ ጉራጌ ብሄረሰብ በተለይም የብሄሩ ተወላጅ የኢህአዴግ ካድሬዎች ላይ ተቀሰሩ። ነጋዴው ፀረ -ኢህአዴግ እንዲሆን ከአመታት በፊት የተጠነሰሰ ሴራ እንደሆነ በሰፊው ተነገረ። የጉራጌ ካድሬዎች አንገታቸውን ደፉ።

እንደዚህ አይነት ፍረጃና አካሄድ እንደማያዋጣ የተገነዘበው አቶ መለስ

እራሱ የሚመራው "የጉራጌ መራሹን አብዮት የሚቀለብስ" ብሎ የሰየመው አቢይ ኮሚቴ አቋቋመ። ዶክተር ካሱ ኢላላን የኮሚቴው ጠርናፊ አደረገ። ከአባላቱ መካከል ካሚል (ኢህአዴግ ቢሮ)፣ ትእግስቱ (የጉራጌ ዞን ሊቀመንበር)፣ ሺሰማ (የአዲሳባ ኢህአዴግ ዞን አንድ ሊቀመንበር)፣ ፊለቀ (የዞን ሶስት ድርጅት ጉዳይ)፣ ሚፍታህ (ስራና ከተማ ልማት)፣ዳንኤል (የጉለሌ ካድሬና በመህል ከድርጅት የተባረረ)፣ ሰለሞን (ኢትዮጵያ ሬድዮ ስራ አስኪያጅ) ይገኙበታል። አቶ መለስ በየሶስት ቀኑ የሚሰራ እቅድ እያስቀመጠ አፈጻጸሙን በቤተመንግስት መገምገም ጀመረ። ይህም ሆኖ ስራው ፈቀቅ ማለት ሲያቅተው ዶክተር ካሱን፣

"ዘወትር ያልበካ ሊጥ ተሸክመህ ትመጣለህ!" በማለት ከጠርናፊነት አባረረው። በምትኩ በወቅቱ የደቡብ ክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ሀላፊ የነበረውን መኩሪያ ሀይሌ ሰብሳቢ አደረገ።

መኩሪያ እና አባላቶቹ በአዲሳአባ እና በጉራጌ ዞን እስከ ሰፈር የሚዘልቅ ንዑስ ኮሚቴዎች አቋቋመ። በአዲሳባ የሚገኙ የሌሎች ብሄር ድርጅቶች ካድሬዎችና አባላት ቁልፍ ስራ ይሄ እንዲሆን ተደረገ። በእያንዳንዱ ቀዬ አዲስ የተወለደ የጉራጌ ልጅ ሳይቀር ተቆጠረ። በአዲሳአባ እና በጉራጌ ዞን መጀመሪያ በቀጠና፣ ቀጥሎ በቀበሌ በማስከተል በክፍለከተማ ሰፋፊ እና ተከታታይ ስብሰባዎች ተደረጉ። በከተማ ደረጃ ከሁለት ሺህ በላይ የጉራጌ ባለሀብቶች፣ ታዋቂ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ነጋዴዎችና ምሁራን የሚሳተፉበት ኮንፍረንስ በስብሰባ ማእከል ተደረገ። ዶክተር ካሱና አቶ መኩሪያ ከሳምንት በላይ ኮንፍረንሱን መሩ።

(የኮንፍረንሱ ሂደት እና የነበረው መንፈስ ጉንጭ አለፉ በሚለው ምእራፍ " ሉሌና ሮማን" በሚለው ርዕሰ ስር ተካቷል።)

ገጠ ለገጠ በአቶ መለስ ቀጭን ትእዛዝ በጉራጌ ዞን በእያንዳንዱ መንደር መብራት በአጭር ጊዜ እንዲገባ ተወሰነ። የመንገዶች ባለስልጣን ትላልቅ አውራ ጎዳናዎችን እና የውስጥ ለውስጥ መንገዶችን እንዲያስገባ ታዘዘ። በወልቂጤ ኮንደሚኒየም በሰፊው እንዲሰራ ክልሉ ልዩ በጀት እንዲመድብ ተደረገ። በትምህርት ሚኒስቴር እቅድ ውስጥ የሌለ የዩንቨርስቲ ግንባታ ተፈቀደ። ህዝቡ የሚያነሳቸው ቅሬታዎች በሙሉ ተሰብስበው ምላሽ ተሰጣቸው። "ለወልቂጤ ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ" በሚመስል መልኩ ሚዲያው ቀን ከሌት አስተጋባ።

የአብዮቱ ቅልበሳ ማሳረጊያ በወልቂጤ በሚካሄድ ህዝባዊ ኮንፍረንስ እንዲጠቃለል ተወሰነ። ከአስር ሺህ በላይ በሀገር ውስጥና በውጭ ለሚኖሩ የጉራጌ ልጆች ጥሪ ተላለፈ። ሚኒስትሮች፣ የክልል ባለስልጣናት፣ ከፍተኛ ባለሀብቶች፣ እነ አርቲስት ተሾመ ወልዴንና አቦነሽ አድነው የመሳሰሉ ታዋቂ

ሰዎች እንዲሳተፉ ተደረገ። ኮንፍረንሱን የሚመራው አቶ መለስ ሆነ። ስብሰባው ሲጀመር በእነ መኩሪያ ሀይሌ የተመረጡት የሀገር ሽማግሌዎች ተራ በተራ እየተነሱ አቶ መለስን፣

"ቂም እንዳትይዝብን አጥፍተናል። መጀመሪያ ልባዊ ይቅርታህን እንሻለን" በማለት ተማጽኖ አቀረቡ። አቶ መለስም እንደለመደው አክሮባት በመስራት፣

"በህይወቴ ትልቅ ትምህርት ከወሰድኩበት ቀን አንዱ የእናንተን የ97 ምርጫ ውሳኔ የሰማሁ እለት ነው። ኢህአዴግ አጠፉ ቀጣችሁት። ጥፋቱን አምኖ እርምት መውሰድ ሲጀምር ደግሞ ከጐኑ ተሰለፋችሁ።" አላቸው። የማያቋርጥ ጭብጨባ። ኮንፍረንሱም እድሜህን እንደ ማቱሳላ ያርዝምልን በሚል ምርቃት ተጥለቀለቀ። በመጨረሻም አቶ መለስ ለዩንቨርስቲ ምስረታው የመሰረት ድንጋይ እንዲያኖር በማድረግ የአብዮቱ ቅልበሳ ተጠናቀቀ።

(የጉራጌ ካድሬዎች እነ ካሚል፣ ሚፍታህ፣ ሺሰማ፣ ፈለቀ ጥሩ ጓደኞቼ ነበሩ። በመልካም ወዳጅነት ዘልቀናል። የልብ በሚወራበት የአሳት ዳር ጨዋታቸው ሳይቀር አብሬያቸው ነበርኩ። በእነዚህ ካድሬዎች እምነት የጉራጌ ብሄረሰብ የለውጥ ጥንስስ የተጀመረው በድሮዎቹ የኢህአዴግ ዝሆኖች ዘመን ከ1990 ጀምሮ ነው። በህቡዕ አደራጅተው በመሰቀል አደባባይ ሰላማዊ ሰልፍ እስከማድረግ ሄደዋል። ሴራው በመታወቁ ምክንያት ግለሂስ አድርገው አይቀጡ ቅጣት ተቀጥተዋል። በምርጫ 92 የጉራጌ ብሄረሰብ ነጋዴዎች ከሌሎች ጋር በመቀናጀት ኢህአዴግን ከአዲሳአባ ለማባረር እንደሰሩ እምነታቸው ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ እነዚህ ካድሬዎች ለታሪክ የሚቀመጥና ትላልቅ መጽሐፍ የሚወጣው ገድል ተሸከመዋል። ከእነዚህም ውሰጥ "ያለ ኢኮኖሚ የበላይነት የፓለቲካ የበላይነት አይመጣም" የሚለው እና "የጉራጌ ባለሀብትን ማዳከም" የሚለው የህውሀት ሚስጥር፣ የጉራጌ ልማት ማህበር የመዳከም መንስኤ፣ የስልጤ ጉራጌ አይደለም እንቅስቃሴ እና የኢህአዴግ ተሳትፎ፣ የመስቀል አደባባዩ ተቃውሞ፣ ምርጫ 92 እና የነጋዴው ተሳትፎ፣ በምርጫ 97 ውጤት የደረሰባቸው መከራ፣ እነ አቶ መለስ ጉራጌ መራሽ ብለው የጠሩት አብዮት የሚጠቀሱ ናቸው። አብዮት ነው አይደለም የሚለውን ለታሪክ ተመራማሪዎች ትተው የህዝባቸውን ሰላማዊ ትግልና ውጤቱን ቢጽፉት ቢያንስ የህሊና እረፍት ይሰጣቸዋል... ለ" ነውጥ አልባ ትግል" የተግባር ምሳሌ ይሆናል።)

ለምን ተሸነፍን? ("ዘመቻ መጋላ አዳማ!")

በአዳማ በተካሄደው ስልጠና የምርጫ 97 የሽንፈት መንስኤዎች ከአንድ ሳምንት በላይ አከራክረው ነበር። በሌሎች የስልጠና ርዕሶችም እንደ ጨው እየገባ ክርክር እንዲካሄድበት ተደርጓል። በግምገማው ጐላ ብለው የተነሱት

የህዝብ ግንኙነት ስራችን ደካማ በመሆኑ ድርጅታችንን መሸጥ አልቻልንም፣ ጥገኛና ፀረ - ዲሞክራሲያዊ ሀይሎች የአብዮታዊ ዲሞክራሲን ታዳጊነት እና የህዝቡን የጥገኛ ተሸካሚነት በመጠቀም ሀገር አጥፍተው ነበር፣ እየተንሰራፋ የሄደው የኪራይ ሰብሳቢነት አደጋ፣ የልማታዊ መንግስትነታችንን እንደ ቀይ መብራት የቆጠሩ አከራሪ ኒዮ ሊብራል የሆኑ የውጭ ሀይሎች የፈጠሩት ጫና እና የኤርትራ መንግስት ኢትዮጵያን ለማተራመስ እንደ አንድ እቅድ ይዞ መንቀሳቀሱ ዋና ዋናዎቹ ነበሩ። እስቲ እያንዳንዱን እያነሳን ወደ መመልከት እንሸጋገር።

" ያልተሸጠው ድርጅት"

በአዳማው ስልጠና ሰፊ ሰአት ያገኘው የህዝብ ግንኙነት ስራችን ደካማ እንደነበር የተገለፀበት ነበር። ይህን በተመለከተ የሁለት ምርጫዎች ወግ በገጽ 66 ላይ፣

"... ኢህአዴግ በባህርይው ሰርቶ በማሳየት የሚያምን ድርጅት ነው። ጥሩ በሰራ ቁጥር ቅን ልቦና ያለው ሁሉ በቀላሉ ይመለከተዋል የሚል እምነት በመያዝ የሰራውን ስራ ለማስተዋወቅ ብዙም አልተጋም። በባህርይው የሚሰራ እንጂ የሰራውን የሚያስተዋውቅ ድርጅት ያልሆነው ኢህአዴግ በምርጫ 97 ይህን ሰራሁ ያን ደገምኩ ብሎ ራሱን ለማስተዋወቅ ብዙም ትኩረት የሰጠበት አልነበረም።" በማለት ገልፃዋለች። በአዋሳ በተካሄደው የኢህአዴግ ጉባኤ አቶ መለስ፣

"የተቆረጠ ምላስ ይዘን ነበር በምርጫ 97 የተሳተፍነው።" በማለት በረከትን ጎሸም አድርጎ ጉባዔተኛውን አስጨብጭቧል።

ይህን ድምዳሜ ተከትሎ የተወሰኑ ውሳኔዎችና የተሰሩት ስራዎች የኢትዮጵያን የፓለቲካ መድረክ ኢህአዴግ በብቸኝነት እንዲቆጣጠረው አድርጓል። በመጀመሪያ የተከናወነው አራቱ የብሄር ድርጅቶች አሉኝ ከሚሏቸው ካድሬዎች አንድ አንድ ሺህ (በድምሩ አራት ሺህ) መልምለው ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ እንዲያስገቡ ተደረገ። በረከት ስምኦን ለሁለት ወር የፓርቲውን የህዝብ ግንኙነት መርሆዎች አሰለጠነ። ይህን ተከትሎ በሁሉም የፌደራል ተቋማት፣ የልማት ድርጅቶች፣ የፓርላማ ጽህፈት ቤት፣ ምርጫ ቦርድ፣ የአዲሳባ መስተዳድር ውስጥ ከ5 -10 ካድሬዎች "የህዝብ ግንኙነት ሀላፊና ኮሙዩኒኬተር" የሚል ስያሜ በመስጠት ተመደቡ። በኪራይ ቤቶች ባለቤትነት የተያዙት የመንግስት ቤቶች ተለይተው በነፃ ታደላቸው። ቢሮክራሲው "ቆንጆዎቹ" የሚል ስያሜ ሰጣቸው። የኮሙዩኒኬተሮቹ ሀላፊ የተቋሙ የህዝብ ግንኙነት ሀላፊ፣ የፓለቲካ ጉዳዮች ሀላፊና ከሚኒስትሩ ቀጥሎ ሁለተኛ ሰው እንዲሆን ተደረገ። ኩፌሌ፣ መንገዶች ባለስልጣንና ጤና ጥበቃ

ሚኒስትር ውጪ በሌሎቹ ተቋማት ሲያገለግሉ የነበሩ ነባር የህዝብ ግንኙነት የበላይ ሀላፊዎች ከሀላፊነታቸው ተነሱ። አንዳንዶቹም ተባረሩ። ከእነዚህ ሰለባዎች አንዱ የኢትዮጵያ መብራት ሀይል ሲነሳ ስሙ አብሮ የሚነሳው ሰንደቁ አርአያ ይገኝበታል።

(የሰንደቁ አርአያ መባረር ላይ ከፍተኛ ሚና የተጫወተው በወቅቱ የኢነርጂ ሚኒስትር የነበረው አለማየሁ ተገኑ ነበር። የተባረረው ደግሞ በእኔ ቀጭን ደብዳቤ። ሪፓርተር እንደልማዱ አህያውን ፈርዶ በሚመስል መንገድ በርእሰ አንቀጹ ከፍ ዝቅ አድርጐኛል። ርግጥም የሰንደቁ መባረር የሚቆጭ ነበር። ከውሳኔው በፊት የመብራት ሀይል ስራአስኪያጅ ምህረት ደበበ በስልክ አግኝቸው ነበር። ምህረት በሀዘን ውስጥ ሆኖ "ሚኒስትሩ ከወሰኑ ምን ይደረጋል?" ብሎኝ ነበር። ግን ለምን ሰንደቁ ተባሮ ሳይጠሩት አቤት የሆነው ምስክር ተመደበ? ከሀንድ ሀገር በሚሊዮን ዶላር ሰለተገዛው ሰልባጅ ትራንስፎርመር ተጠያቂው ማነው? ... ለሌላ ጊዜ ወግ ይቆየን።)

በማስከተል ማስታወቂያ ሚኒስቴርን በማፍረስ የኮሙዩኒኬሽን ጽህፈት ቤት እንዲቋቋም ተደረገ። የሁሉም ተቋማት የህዝብ ግንኙነት ሀላፊዎች ተጠሪነት ለኮሙዩኒኬሽን ጽህፈት ቤት እንዲሆን በፓርላማ እንዲፀድቅ ተደረገ። ይሄ ማለት በአጭሩ የኮሙዩኒኬሽን ጽህፈት ቤት በየተቋማቱ ውስጥ ሁለተኛው ወሳኝ አካል ሆነ። በዚህ ሳይወሰን ከየብሄር ድርጅቱ ተመልምለው ከመጡት ካድሬዎች ውስጥ 60 ያህሉ በኮሙዩኒኬሽን ጽህፈት ቤት፣ 50 ያህሉን ደግሞ በኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቭዥን በኮሙዩኒኬተርነትና ጋዜጠኝነት እንዲመደቡ ተደረጉ። በጽህፈት ቤቱ "የክልሎች ላይዘን" የሚባል ኢ-ህገመንግስታዊ ዳሬክቶሬት በማቋቋም ሁሉም ክልሎች በተዘዋዋሪ መንገድ ለጽህፈት ቤቱ ሪፓርት የሚያደርጉበት ስርአት ተዘረጋ። የቅንጅት ሀንጐበር አለቀቀውም የተባለው ነባሩ ሰራተኛና ጋዜጠኛ ከስራ ውጪ ሆነ። ከትትል ሲደረግባቸው ከነበሩት እንደ ጋዜጠኛ አሸብር (የህትመት ዳሰሳ አዘጋጅ) ያሉት ደግሞ የልባቸውን በልባቸው ይዘው የአሰላለፍ ለውጥ አደረጉ።

ከየክልሉ በመዋጮ የመጡት አዲሶቹ ኮሙዩኒኬተሮችና በሁለት ወር የበረከት ስልጠና የጋዜጠኝነት ማእረግ የተሰጣቸው ካድሬዎች የኢኮኖሚውን ድል የሚያበስሩ ጽሁፎች፣ ዜናዎችና ፕሮዳክሽኖች (ዶክመንተሪ ፊልሞች) ወደ ማዘጋጀት ተሸጋገሩ። ኢትዮጵያ በልማት ጐዳና እየተመነጠቀች መሆኑን አበሰሩ። የኢትዮጵያ ህዝብ አማራጭ የሚያዳምጥበትን አድል ዝግ አደረጉ። ኢህአዴግ ብቸኛው የልማትና ዲሞክራሲ ምንጭና ፉና ወጊ መሆኑን አስተጋቡ። ያልተሸጠውን ድርጅት ምላስ ቀጥለው ለገበያ አቀረቡ። ድርጅቱ በጋሸበ ዋጋ መሸጥ ጀመረ።

ድርጅቱን መሸጥ አለብን የሚለው ውሳኔ በማስከተል የወሰዳቸው እርምጃዎች በኢህአዴግ አጠራር "ህጋዊና ዲሞክራሲያዊ መሳሪያዎች" በመጠቀም አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ተቋማት፣ የፕሬስ ውጤቶችና ተቃዋሚ ድርጅቶች ላይ እርምጃ መውሰድ ነበር። የዚህ ስራ ዋነኛ ባለቤት ሽመልስ ከማል ሆነ። አልሞ የሚተኩስበት መሳሪያም የፕሬስ፣ የበጎ አድራጐትና ፀረ ሽብርተኝነት አዋጆቹ ሆኑ።

የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ታዳጊነት

የኢህአዴግ የውስጠ ድርጅት ሰነዶች 97% የሚሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ የኢህአዴግ ማህበራዊ መሰረት እና ድልብ አቅም እንደሆነ ይገልጻል። የተቀረው 3% ብቻ የተቃዋሚዎች (የጥገኛና ፀረ-ዲሞክራሲ ሀይሎች) ማህበራዊ መሰረት እንደሆነ ያሰምሩበታል። በእነዚህ ሰነዶች እንደተገለፀው ይህን 97% የሆነ ድልብ አቅም በተደራጀ መንገድ ወደ ማያቋርጥ ትግል ካላስገባነው የጥገኝነት ተሸካሚ በመሆን ከእኛ በተቃራኒ ሊቆም እንደሚችል ያሳስባል። በምርጫ 97 ሆነ የተባለው ይህ ነበር። ከዚህ አንፃር "ዲሞክራሲና ዲሞክራሲያዊ አንድነት በኢትዮጵያ" በሚለው መጽሐፍ በምአራፍ ሁለት ገጽ 66 ላይ የሚከተለው ማእከላዊ መልእክት ሰፍሮ እናገኛለን፣

"ከቁጥር የማይገቡና እፍኝ የማይሞሉ ጥገኞች እና ፀረ-ዲሞክራሲ ሀይሎች አደገኛ የሚሆኑት ሁሉም የዲሞክራሲ ሀይሎች በተለያየ ደረጃ ለፀረ-ዲሞክራሲያዊ የጥገኝነት አስተሳሰቦች የተጋለጡና ሰለባ ሊሆኑ የሚችሉ በመሆናቸው ነው። አብዮታዊ ዲሞክራሲ እጅግ ሰፊ በሆነ መሰረት ላይ የተመሰረተ ቢሆንም ታዳጊ ከመሆኑ የሚመነጭ ድክመቶች ስላሉት፣ ሰፊው ማህበራዊ መሰረቱ ለጥገኛ አስተሳሰብ የሚጋለጥ በመሆኑ በሚያቋርጥ ትግል ያለበትን ውስንነቶች መቅረፍ ካልቻለና በህዝቡ ውስጥ ያሉ ጥገኛ አስተሳሰቦች ካልተገሩ በጥገኛ ፀረ-ዲሞክራሲ ሊሸነፍ ይችላል። ይህ አደጋ በንድፈ ሀሳብ ደረጃ የሚቀመጥ ብቻ ሳይሆን በሶስተኛው አገራዊና ክልላዊ ምርጫ እንደታየው ሀያው የሆነ አደጋ ነው።"

(በኢህአዴግ ካድሬዎች ዘንድ ጥገኛ እና ኪራይ ሰብሳቢነት ተወራራሽ ትርጉም አላቸው። ኪራይ ሰብሳቢነት የፓለቲካል ኢኮኖሚ ትንታኔ ላይ፣ ጥገኝነት ደግሞ ከውስጠ ድርጅት አንፃር የሚቀርብ ነው። ሆኖ ብዙውን ጊዜ ጥገኝነት "ትምክህተኛ እና ጠባብ" የሚለውን ቃል በመተካት ይገባል።)

የመውሰና አደጋ

በአዳማው ስልጠና ልዩ ትኩረት የተሰጠው ሙስና ነበር። ይህ ችግር ለምርጫ 97 መሸነፍ አንዱ ምክንያት ከመሆኑም ባሻገር የስርአቱን ህልውና የሚፈታተን ወቅታዊና ተጨባጭ አደጋ ሆኗል በሚል ተገለፀ። በመላ ሀገሪቱ በተለይም በፌደራል ተቋማትና ከተሞች የተንሰራፋው ዝርፊያ ለፀረ- ዲሞክራሲ መስፋፋት መደላድል መፍጠሩ መግባባት ላይ ተደረሰ። ከዚህ በተጨማሪም በተቋማት የነገሰው ኋላ ቀር አሰራር፣ በአድሎና ጉቦ ላይ ያተኮረ አገልግሎት አሰጣጥ የህዝቡን ቁጣና ምሬት እንዲስፋፋ እንዳደረገ ተነገረ። የሙስና አደጋን በተመለከተ በዘመቻ መጋላ አዳማ አከራካሪ የነበረው፣

"ኢህአዴግ እያራመደ ካለው የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፓሊሲዎች አንፃር ሙስና ሊጠፋ አይችልም። በልማታዊ መንግስት ፍልስፍና መሰረት የኢኮኖሚው፣ ማህበራዊ ልማቱና ኢንቨስትመንቱ ዋነኛ ምንጭ መንግስት በሆነበት ሁኔታ፣ ባለስልጣናት እና ካድሬዎች እንደ መሬት፣ ገቢ፣ ኢንቨስትመንትና ትላልቅ ጨረታዎች ላይ የመወሰን ስልጣን በእጃቸው ስለሚሆን ሙስና የስርአቱ ዋነኛ መገለጫ መሆኑ አይቀርም።...ባለስልጣናት የገቡበት የሙስና አረንቋ ሰፊ ስለሆነ መከላከል የማይቻልበት ደረጃ ደርሷል። ... አድርባይነት፣ በአካባቢ ማሰብና የሀገሬ፣ የወንዜ ልጅ የሚል መንደርተኝነት እየገመለበተ በሄደበት ሁኔታ ሙስና አይጠፋም" የሚል ነበር።

"የትሮይ ፈረሶች!"

በኢህአዴግ አመራሮች ዘንድ የትሮይ ፈረሶች ተደርገው የሚቆጠሩት የአሜሪካ መንግስት፣ የአውሮፓ ህብረት፣ የአሜሪካን አለም አቀፍ ተራድኦ ድርጅት (ዩ* ኤስ* ኤ* አይዲ)፣ አመንስቲ ኢንተርናሽናል፣ ሂዩማን ራይትስዎች፣ የጋዜጠኞች መብት ተከራካሪ ድርጅት (ሲፒጄ)፣ አይ ፒ አይ ፣ ጀኖሳይድዋች ፣አለም አቀፍ የሚዲያ ተቋማት(ቢቢሲ፣ ሲኤንኤ፣ አልጀዚራ) የመሳሰሉት ድርጅቶች ናቸው።

አቶ መለስ በፃፈው "ዲሞክራሲና ዲሞክራሲያዊ አንድነት በኢትዮጵያ" ፣ እና አቶ በረከት በአዲስ ራእይ መጽሄት ላይ የበጉ አድራጐት አዋጁን ለማብራራት በጻፈው አርቲክልና በሌሎች የውስጠ ድርጅት ሰነዶች እንደተጠቀሰው እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ድርጅቶች ኢህአዴግ መንግስታዊ ስልጣን ከያዘ ጀምሮ ላለፉት ሀያ ምናምን አመታት ጠላትነታቸውን በግላጭ አራምደዋል።ሀገሪቷ ችግር ባጋጠማት ቁጥር የኢህአዴግን እጅ ለመጠምዘዝ ተንቀሳቅሰዋል።በምርጫ ሂደትና ውጤት ላይ ጭላሸት ለመቀባት በተቀናጀ መንገድ ቀን ከሌት ሰርተዋል። የኢህአዴግ ሰነዶች እነዚህ ድርጅቶች በስም ይለያዩ እንጂ በአላማቸው ላይ ልዩነት እንደሌላቸው ይገልፃሉ። የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያቤት ዓመታዊ የሰብአዊ መብት ሪፓርት ዋነኛ ምንጮች

እነዚህ ተቋማት እንደሆኑ ያሰምሩበታል።

እንደ ኢህአዴግ እምነት እነዚህ ተቋማት የምእራቡን አለም አከራሪ ኒዮ ሊብራል ሀይሎች ጥቅም ለማስከበር የህዝብ ግንኙነት መሳሪያ በመሆን ያገለግላሉ። ከአከራሪው ኒዮ ሊብራል በተቃራኒው የቆመውን አብዮታዊ ዲሞክራሲ ያወግዛሉ። የውግዘታቸው መንስኤ ከኢህአዴግ ጋር በቀላሉ የማይታረቅ የርዕዮተ አለም ልዩነት በመኖሩ ነው። በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ቅኝት የተቀረጹት ፓሊሲዎች መቀየር አለባቸው ከሚል እምነታቸው የሚመነጭ። እነዚህ ሀገሮችና ድርጅቶች መንግስት በኢኮኖሚው ዘርፍ የመሪነት ሚና እንዲኖረው አይፈልጉም። ከዚህ በተጨማሪም መንግስት ህግና ስርአት የማስከበር ጠንካራ አቅም እንዲኖረው አይፈልጉም። የመሬት ፓሊሲው ተቀይሮ መሬት እንዲሸጥ እንዲለወጥ ጠንካራ ፍላጐታቸው ነው። ቴሌና መብራት የመሳሰሉት ተቋማት ሙሉ በሙሉ በግለሰብ ቁጥጥር ስር እንዲውል ተግተው ይሰራሉ። በመሆኑም በምርጫ 97 የእነሱን ፍላጐት ሊያስጠብቁላቸው የሚችሉትን ቅንጅትን የመሳሰሉ ኪራይ ሰብሳቢዎች ወደ ስልጣን ለማምጣት የትሮይ ፈረስ ሆነው አገልግለዋል በማለት ይከሳቸዋል።

በዘመቻ መጋላ አዳማ በተደረጉት የቡድን ውይይቶች ይሄ የአቶ መለስ አቋም ብዙ ትችት ደርሶበታል። በአብዛኛው የቡድን ውይይቶች ካድሬዎች፣

"አሜሪካና አውሮፓ ህብረትን የመሳሰሉ አለምን የሚያሽከረክሩ ሀገሮችንና ግዙፍ ተቋማትን በጠላትነት ፈርጀን እድሜ ይኖረናል ወይ? ...ኢህአዴግ አለም ተቀብሎ የበለፀገበትን ስርአት ተፃሮ እስከ መቼ ይኖራል? ...ኢህአዴግ እነሱ የሚያቀርቡት አማራጭ ለምን በደንብ አይመረምርም?፣ ከመጀመሪያው በጠላትነት ከመፈረጅ በሚያግባቡ ጉዳዮችና የጋራ ፍላጐቶች ላይ ለምን በጋራ አንሰራም። የሰብአዊ መብት ድርጅቶቹ የሚያቀርቡት ወቀሳ አስቀድመን መሰረተ ቢስ እና ከሀቅ የራቀ ከምንል በገለልተኛ ወገን አጣርተን ለምን ምላሽ አንሰጥም?፣ በህበረተሰቡ ውስጥ ያሉ ቅሬታዎች በተለይም ከሰብአዊ መብት ጥሰት አንፃር በይበልጥ እየገለበቱና ስር እየሰደዱ በሄዱበት ሁኔታ ተቋማቱ የሚያቀርቡትን ክስ ለምን መሰረተ ቢስ እንላለን?...እነዚህ ሀገሮች፣ ተቋማትና አለም አቀፍ ሚዲያው ልማታዊ መንግስት የግል ዘርፉን የሚደግፍና የሚያበረታታ አይደለም፣ ውድድርና ግልፀኝነት ያጠፉል፣ መንግስታዊ ሌብነትን ያስፉፉል የሚል ወቀሳ ስለሚያቀርቡ ምላሻቸን ምንድነው? የግል ባለሀብቱ እየቀጨጨ መሄዱ እውነት አይደለም ወይ?፣... መሬት አይሸጥም አይለወጥም ብለን በተዘዋዋሪ መንገድ አርሶአደሩ በማዳበሪያና ምርጥ ዘር እዳ መሬት አልባ እያደረግነው ነው። በከተሞች በተለይም በአዲሳባ የመሬት ወረራው ከቁጥጥር ውጭ የወጣው በመሬት ፓሊሲው ምክንያት ነው" የሚሉ ነበሩ።

ምእራፍ አስራ ዘጠኝ

ያልተቋጨው የፌንፊኔ አጀንዳ

"የአዲሳባ ህዝብ ቅንጅትን እንደመረጠ፣ ቅንጅት ያድነው!..."
ፍቃዱ (የአህዴድ ድርጅት ጉዳይ ሀላፊ)

ከምርጫ 97 በፊት አህዴድ የተመሰረተበትን ቀን በየአመቱ በአዲሳባ ባከበረ ቁጥር በድርጅቱ አባላት ግልፅ ተቃውሞዎች ይቀርቡ ነበር። የታሰሩ የሚጫና ቱለማ መረዳጃ ማህበር አመራሮች ይፈቱና ካሳ ይከፈላቸው በማለት። እነዚህ ሰዎች የታሰሩበት ምክንያት የኦሮሚያ ዋና ከተማ ከአዲሳባ ወደ ናዝሬት (አዳማ) መዘዋወሩን በመቃወማቸው ምክንያት በ1996 ዓ.ም በመስቀል አደባባይ ሰላማዊ ሰልፍ በማድረጋቸው ነበር። በወቅቱ "ፌንፊኔ የኦሮሚያ ዋና ከተማ ናት፣ የኦሮሞ ህዝብ በፌንፊኔ ላይ ያለውን የባለቤትነት መብት መነጠቅ የለበትም" የሚሉ መፈክሮችን አንግበው ነበር። ይህ ማህበር ፓለቲካ ይዘት ያላቸውን የመብትና እኩልነት ጥያቄዎች ፊት ለፊት በማንሳቱ ግንቦት 1996 ዓ.ም የድርጅቱ አመራሮች በሽብርተኝነት ተከሰሱ። በአንድ ወር ውስጥ ፍቃዳቸው ተነጥቆ ንብረታቸው ተወረሰ።

ዋና ከተማው ወደ አዳማ (ናዝሬት) መዘዋወሩን ተከትሎ ሰራተኛውና ቢሮዎች አብረው ተዘዟሩ። በአዲሳአባ ቤት ሰርተው ቋሚ ኑሮ የጀመሩ ሰራተኞች ቤታቸውን እያከራዩና እየሸጡ ወደ አዳማ ተጓዙ። አንዳንዶች ከትራንስፓርት ጋር በተያያዘ ተመላልሶ መስራት ስላልቻሉ ስራቸውን ለቀቁ። ምትሀተኛው ምርጫ 97 መጣና ውሳኔው ግልብጥብጡ ወጣ።

ሲጀመር የኦሮሚያ ዋና ከተማ ወደ ከአዲሳባ እንዲወጣ ያደረጉት አቶ መለስና ተፈራ ዋልዋ ናቸው። የዋልዋ ልጅ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ኦሮሚያ የራሷን መዲና እንድትመሰርት ግፊት አድርጓል። የኦሮሞ ጠላት ተደርጐ እስኪወሰድ ድረስ ተጨቃጭቋል። ጥረቱ ፍሬ በማፍራቱ በ994 ዓ.ም በተሻሻለው የኦሮሚያ ክልላዊ ህገ መንግስት ላይ እስከመካተት ደረሰ። በክልሉ ህገ መንግስት አንቀፅ ስድስት ላይ "የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ ከተማ አዳማ ነው።" የሚል ተደነገገ።

የምርጫ ዘጠና ሰባት ውጤት ተከትሎ ወደ ነበረበት እንዲመለስ ያደረገው ደግሞ አቶ መለስ ነበር። የአዲሳባ ህዝብ የወሰነው ውሳኔ እልህ ስለከተተው የበቀል ጅራፉን ለማጮህ። በየጊዜው የጨረባ ተዝካር የሚደገስባት ከተማ ለማድረግ።

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው በመሄዲም በመመለሷም ዙሪያ እነ አባዱላ የሉበትም። ርግጥ የፕሮፐጋንዳውን ስራ የያዙት እነሱ ነበሩ። ወደ አዳማ ሲሄዱ ጥልቅ ጥናት እንዳደረጉና በውሳኔው ተቃውሞ የሚያሰሙት የአነግ አመለካከት ያላቸው ፀረ ሰላም ሀይሎች አንደሆኑ በየመድረኩ ተናገሩ። እኛም እነሱን ተቀብለን አስተጋባን። መመለሳቸው ደግሞ የኦሮሞ ህዝብ አስቀድሞም እንዳልፈለገውና በየጊዜው ተቃውሞ ሲያነሳ እንደነበረ ገለፁ። እኛም እንደነሱ ተናገርን።

ሁላችንም ለአንድ ነገር ግን መልስ አልነበረንም ።የቀድሞውን ውሳኔ በመቃወማቸው ምክንያት ወደ ወህኒ ስለተወረወሩት የሚጫና ቱለማ አመራሮች፣ ትምህርታቸውን አቋርጠው ስለተሰደዱት የኦሮሞ ልጆች፣ ከዩንቨርስቲ የተባረሩ ተማሪዎች፣ በተለያየ ምክንያት ስራቸውን የለቀቁ የጨፌ ሰራተኞች...

ከእነዚህ መገላበጦች በስተጀርባ አሁንም ድረስ ያልተመለሱ መሰረታዊ ጥያቄዎች አሉ። የአቶ መለስ ሌጋሲ ለምን የፌንፌኔን አጀንዳ መዝጋት አልፈለገም? ከተማዋ በማያልቅ ኢኮኖሚያዊ ፣ፓለቲካዊና የእዝ ውጥንቅጥ ውስጥ እንድትገባ ለምን ተፈለገ? ህገ መንግስቱ በነጠረ ቋንቋ ለኦሮሚያ ክልል የባለቤትነት መብት ሰጥቷታል ወይ?፣ ከዲሞክራሲ መብት አኳያ አዲሳአባና ፌንፌኔ ስልቻና ቀንቀሎ ልንላቸው እንችላለን?... በመሆኑም እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ይቻል ዘንድ ይበልጥ ፉይዳ ያላቸውን ቁምነገሮች በማንሳት ነገርየውን መመልከት የተሻለ ይሆናል። አስቀድመን በምርጫ 97 ማግስት ስለነበረው ሁኔታ እንመልከት።

***

የምርጫ 97 አሳዛኝ ክስተት...

የአቶ መለስ ሌጋሲ የፌንፌኔን አጀንዳ ሳይዘጋ ላይመለስ ሄዷል። ታላቁ መሪ ከተማዋ ላይ ያስቀመጠው የተሰላ ሰይፍ ወደ አፎቱ አልገባም። አሁንም ከተማዋ በማያልቅ ኢኮኖሚያዊ፣ ፓለቲካዊና የእዝ ውጥንቅጥ ውስጥ እንደገባች ትገኛለች። ጭቆናና በደሉ ተጠናክሮ ቀጥሏል። የመዲናይቱ ነባነት ተነጥቋል።

ይህንን ተከትሎ የአዲሳባ ህዝብ ነባነቱን የሚያረጋግጥለት ውሳኔ ባሳረፈ ቁጥር በአቶ መለስ ይሁንታ እነ አባዱላ አዳዲስ ወንጀሎችን ሰርተዋል። በተለያየ ጊዜ የአዲሳአባን ነዋሪ እንደ ባላንጣ በመመልከት ለመጉዳት ተንቀሳቅሰዋል። መዲናይቱ በትምክህት አስተሳሰብ ተወራሰች የሚል የማጠልሸት ዘመቻቸውን አጠናክረው ቀጥለውበታል።

በምርጫ 97 ማግስት አቶ መለስ አጥር ሲያፈርስ የተመለከቱት እነ

አባዱላና ግርማ ብሩ የግዛት ማስፋፉት እቅድ አውጥተው ሲሶውን የአዲሳባ መሬት ለመውረር ተንቀሳቀሰዋል። ይህም አልበቃ ብሎአቸው በህገመንግስቱ መሰረት አሮሚያ ልዩ መብት አላት የሚለውን ዝርዝር ህግ አስደንጋጭ በሆነ መልኩ እና የአዲሳባን ህዝብ ሉአላዊ መብት ለመንጠቅ በሚያስችል ደረጃ ዶሴ አዘጋጅተው ነበር። ዶሴው አዲስአባ ከምትሰበስበው ታክስ ፣0% ለመውሰድ፣ አዲሳአባ ካላት አምስቱ ኬላዎች የምታገኘውን ቀረጥ እኩሌታ ለመካፈል፣ በአዲሳባ መግቢያ በሮች በሙሉ የቁም ኩበት በረቶችን በማቋቋም ቀረጥ መሰብሰብ (ይህ ውሳኔ ከምርጫው በፊት የነበረና እንደ አቃቂ ባሉ ክፍለከተሞች በተግባር ላይ ውሎ በደረሰበት ህዝባዊ ተቃውሞ እንዲቀር የተደረገ ነበር።)፣ በመዲናይቱ ምክርቤት ውስጥ ለመሳተፍ ያለ ህዝቡ ምርጫ በምደባ ለመወከል... የመሳሰሉ ጉዳዮችን ያካተተ ነበር።

እንደ እውነቱ ከሆነ እነ አባዱላ ይህን እርምጃ ለመውሰድ ያነሳሳቸው በቂ ምክንያት ነበራቸው። የመጀመሪያው በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ ያጡትን ተቀባይነት ለመቀልበስ ሲሆን፣ ሁለተኛው በአዲሳባ የፈፀሙትን መሬት ወረራ ሽፋን ለመስጠት በማሰብ ነበር። የኦሮሞን ህዝብ የስልጣን ባለቤትነት ነጥቀው ፀረ ዲሞክራሲያዊ ስርአት እየገነቡ ባለበት ሁኔታ አጀንዳ ማስቀየሪያ ውሳኔ ይዘው ብቅ ያሉበት ምክንያት ይህ ነበር።

የአዲሳአባ ህዝብ ከግልፅ አመጽ ተቆጥቦ እጁን በመሰብሰቡ ምክንያት ሰነዱ ወደ ተግባር አልተለወጠም። በአህዴድ ጽ/ቤት ጊዜውን ጠብቆ ሊፈነዳ እንደሚችል ቦንብ ተጠቅልሎ በሼልፍ ላይ ተቀምጧል። እንደ 97 ሁሉ አዲሳአባ ላይ የሚያሸንፍ ተቃዋሚ ፓርቲ ቢመጣ አቢራው ተራግፎ ይወርዳል።

እነ አባዱላ ይህን የህገመንግስት አንቀፅ በማጣቀስ ከአእምሮ የማይጠፉ ወንጀሎችን ሰርተው ነበር። ርግጥም በእንጭጩ ባይቀጩ ኖሮ ማቆሚያ የሌለው ደም መፋሰስ ይከሰት ነበር። በተለይም ምርጫ 97 ተከትሎ በታህሳስ ወር 1998 ዓ.ም የሰሩት ወንጀል ከህሊና የሚጠፉ አይደለም።

እነሆ! ታህሳስ 1998 ዓ.ም እንዲህ ነበር የሆነው...

የጨፌው ባለስልጣናትና ፓሊሶቹ በታዘዙት መሰረት በቀራንዮ፣ ለፍቶና አቃቂ እየዘሩ ችካልና ታፔላ ይተክላሉ። ታፔላው የኦሮሚያ ግዛት ወሰን የሚያርፍበትን ለማመላከት የታሰበ ነበር። ይህ እርምጃ በተለይ የሁለቱን ክፍለ ከተሞች ግምሻ ያህል ቆርሶ የወሰደ ነበር። ከአቃቂ ድልድይና ከቀራንዮ ትምህርት ቤት ወዲያ ያለውን በሙሉ ወደ ኦሮሚያ የሚወስድ ዱብ እዳ ነበር።

እጅግ የሚያስደነግጠው የተወሰደው እርምጃ የቀራንዮ መድሀኒአለም ቤተክርስቲያንና የመቃብር ቦታውን ለሁለት የሚከፍል ነበር። ቤተክርስቲያኑ አዲሳአባ ስትቆረቆር የተሰራ የመጀመሪያው በመሆኑ እና በታሪክ ቅርስነት የተመዘገበ በመሆኑ የከተማው ነዋሪ በልዩ ሁኔታ ይመለከተዋል። የእነ አባዱላ እርምጃ የአዲሳአባን ታሪክ የማጥፋት ተደርጎ የተወሰደው አንዱ ምክንያት ይህ ነበር።

የግዛት ማስፋፋቱን የተቃወሙ ነዋሪዎች ከኦሮሚያ ፓሊስ ጋር ፍልሚያ ገጠሙ። ህዝቡ በልበ ደንዳኖቹ ፓሊሶች ተቀጠቀጠ። ከቀራንዮና አቃቂ ብቻ ከአስር በላይ ነዋሪዎች ታፍነው ተወሰዱ። በአካባቢዎቹ የተነሳው ሁከትና ብጥብጥ ወደ መሀል ከተማ እየተሸጋገረ ከቁጥጥር ውጭ እየወጣ ሄደ። የሁለቱ ክፍለከተማ ነዋሪ ተወካዮች ከአንድ ሺህ በላይ የቅሬታ ፒቲሽን የተፈረመበት ደብዳቤ ይዘው ወደ አራት ኪሎ ኢህአዴግ ቢሮ መጡ። ሁኔታውን እንድናጣራ ለእኔና ፀሀይቱ ባህታ ሀላፊነት ተሰጠን።

(ፀሀይቱ የህውሀት ነባር ታጋይ ነበረች። በአሊ አብዶ ዘመን የአዲሳባ ሚሊሺያ ጽ/ቤት የበላይ ሀላፊ ሆና ተሾመች። በአርከበ ዘመን ደግሞ በከፍተኛ ብቃት ማነስ ተገምግማ በላፍቶ ክፍለከተማ በምትገኝ አንዲት ቀበሌ ካድሬ ሆነች። ከምርጫ 97 በኃላ አራት ኪሎ መጣች። የኢህአዴግ አዲሳባ ከንፍ ሆና አንድትመደብ ያደረገው የአከስቷ ልጅ ሽማግሌው ስብሀት ነጋ ነበር። ህውሀት ከኢህአዴግ ቢሮ ራሱን ያገለለበት ወቅት ስለነበር ሽማግሌው ከቀበሌ አንስቶ ለመመደብ አልተቸገረም።)

የቀራንዮንና አቃቂን ችግር ለመፍታት ፀሀይቱ እንድትጨመርልኝ ያደረኩት ሆን ብዬ ነበር። የመዲናይቱ ካድሬዎች ጣይቱን "የአዲሳባ አዜብ" ብለው ይጠሯታል። እንደ አዜብ መስፍን ሁሉ የስልጣኗ ምንጭ ብቃቷ ሳይሆን ከፊትና ኋላ ያሰለፈቻቸው የኢህአዴግ ባለስልጣናት ናቸው። ሽማግሌው ስብሀትን ከፊት መስመር አሰልፉለች። ከኋላ የአጐቷ ልጅ ሚኒስትር ጌታቸው በላይ አለ። ከቀኝ ጐኗ ደግሞ የሱማሊያው ስውር አለቃ ኮረኔል ገ/እግዚአብሔር አለላት። ከአጠገቧ ደግሞ እንደ ህፃን ልጅ፣ "ፀሀይቱ ብልህ!፣ የአላማ ጽናት ተምሳሌት! ኢህአዴግ አንቺን ባያገኝ ምን ይውጠው ነበር? ከሴቶች ሁሉ በአመራር ብቃትሽ የተመረጥሽ ነሽ!" ብዬ የምኮፍሳት እኔ አለሁ። እናም በባዶዋ ፀሀይቱ ልቤ ሞላ። ግማሽ ጭንቀቴ ተራገፈ። የኢህአዴግ አሰራር እንዲህ ነው። የካድሬ ጉልበት በችሎታ ሳይሆን በተከበበው ባለስልጣን ብዛት የሚለካበት።

በመሬት ላይ ያለውን እውነታ ለማረጋገጥ ከፀሀይቱ ጋር ተያይዘን ወደ አቃቂ ቃሊቲ ወረድን። እንደተባለው የአቃቂን ወንዝ ሰንጥቆ ከሚያልፈው ማዶ ባለው ጨፌ ላይ ችካሎች ተቸክለዋል። ወደ ኦሮሚያ ክልል "እንኳን ደህና መጣችሁ" የሚል ታፔላ ተተክሏል። ሁለት ፓሊሶች ምልክቶቹ እንዳይነቀሉ ለመከላከል መሳሪያ ታጥቀው እንደ ጅብራ ተገትረዋል። ህዝቡ በየቦታው ተሰብስቦ ጩኸት ያሰማል።

አካባቢውን ሳለቅ ለኦሮሚያ ስራና ከተማ ልማት ሀላፊው ደወልኩለት። ተክለፃዲቅ ሬባ ይባላል። ከምርጫ 97 በፊት የክፍለከተማው ከንቲባ ስለነበር አካባቢውን እንደራሱ ሳሎን አብጠርጥሮ ያውቀዋል። ይህን እውነታ እያወቀ የቸካል ማስተክሉን ሂደት እሱ እንደመራው ስሰማ ውስጤ በሀዘን ተሞላ። የበላበትን ወጪት ሰባሪ ሆኖ ተሰማኝ። ስንት አመት እንኖር ይሆን?

ከተክሌ ጋር በስልክ ያደረግነው ንግግር ይበልጡን አበሳጨኝ። እየተወሰደ ያለው እርምጃ እንደማያምንበት ግን ደግሞ ከአቅሙ በላይ እንደሆነ እቅጩን ነገረኝ። አልፎ ሄዶ "አቦ! ቁልቢን ነው የምልህ እንዲህ አይነት ነገር ውስጥ እጅህን አታስገባ" ብሎ አስጠነቀቀኝ። መሬትን የማስተዳደር ሀላፊነት የተሰጠው የስራና ከተማ ልማት ቢሮ ሀላፊ፣ የካቢኔ አባል ጉዳዩ ከእኔ በላይ ነው፣ አንተም አርፈህ ተቀመጥ ሲል ታዲያ ምን ይባላል? በእውቀቱና አርቆ ተመልካችነቱ ስኮራበት የነበረ ጓደኛዬ ባልጠበኩት መልኩ ቁልቁል ተንሸራቶ ሳገኘው ልቤ ተሰበረ። ትላንትና የእነ አርከበን ሙስና፣ ዘረኝነትና ፀረ-ህዝብነት አውርቶ የማይጠግበው ጓደኛዬ ተክሌ ምን ነካው? ትላንትና አባዱላና ጁኑዲን ተቀናጅተው የአርሲን ልጅ ብቻ ወደ ስልጣን እያመጡ እንደሆነ የሚከስ ስብእና የነበረው ጓደኛዬ ይህን ለመቃወም እንዴት አቅምና ሞራል አነሰው?

ጩኸት የሚያሰማው የአቃቂ ህዝብ እኛን ሲመለከት ግር ብሎ ወረረን። የማያባራ ልቅሶ ከወዲያም ከወዲህም ተሰማ። ተቃውሞ ካሰሙት ውስጥ አምስት አባወራዎች ወዳልታወቀ ቦታ ፖሊሶቹ እንደወሰዷቸው ገለጹልን። ልጆቻቸው ለአመፅ እየተዘጋጁ እንደሆነ ነገሩን። በሚካሄደው ትንቅንቅ የህይወት መውደቅ ሊከሰት ስለሚችል በአስቸኳይ ጣልቃ እንድንገባ ተማጸኑን። ህዝቡን በንጋታው እንደምሰበስባቸው ቃል ገብቼ በቀጥታ ወደ ስድስት ኪሎ አህዴድ ጽ/ቤት አመራሁ። ፀሀይቱ ደግሞ ወደ ሌላኛዋ የትርምስ ቦታ ቀራንዮ ሄደች።

የአህዴድ ቢሮ ሀላፊዎች የሆኑትን ዘላለም ጀማልና ፍቃዱ አገኘኋቸው። የፖለቲካ ጉዳይ ሀላፊ የነበረው ዘላለም የመጣሁበትን ምክንያት እንዳወቀ በሚያስታውቅ መልኩ ተደናብሮ ሄደ። ከድርጅት ጉዳይ ሀላፊው ፍቃዱ ጋር ተፋጠጥን። በፍጹም ልንግባባ አልቻልንም። አልፎ በመሄድ የግዛት ማስፋፋቱ አካል እንድሆን አግባባኝ።

በግርምት ውስጥ ሆኜ እንዲህ በማለት ጠየኩት፣

"አዲሳአባ የኦሮሚያ አካል እንደሆነች የሚያምን ፣መቀመጫውንም

እዛው ያደረገ ድርጅት እየቆራረሰ መውሰድ ለምን አስፈለገው? የተምታታና ግብ የለሽ ስራ ለመፈፀም ያነሳሳችሁ ምክንያት ምንድነው?"

መልስ ሊሰጠኝ አልቻለም። ይበልጥ በበቀል ውስጥ ሆኖ፣

"ምላሽ እየሰጠን ያለነው የኦሮሞን ህዝብ ጥያቄ ነው። ይህን በማድረጋችን ትርጉሙ የትየለሌ ነው። በጥቂት ቀናት ውስጥ ተቀባይነታችን መጨመሩን ገምግመናል። የአዲሳባ ህዝብ ቅንጅትን እንደመረጠ፣ ቅንጅት ያድነው!... አንተ የኦሮሞ ልጅ እንደመሆንህ መጠን ከእኛ ጋር መሰለፍ ይኖርብሀል" የሚል ምክር ቢጤ ሰጠኝ።

ይገፍው ወደ መጣሁት ሌላ ጥያቄ ተሸጋገርኩ፣

"በቁጥጥር ስር ያዋላችኋቸውን ለምን አትለቁም?" አልኩት።

"አንተ ከአቃቂ ሳትወጣ ለቀናቸዋል። ይልቁንስ የዚህ ምእራፍ ቀያሪ ተልእኮ አካል ሳትሆን እንዳይረፍድብህ!"

ትንፋሼን እንደዋጥኩ ተነስቼ ወጣሁ።

***

በንጋታው ከሰአት ላይ የአቃቂን ህዝብ ለማወያየት ከሰጥቷልና ቤኩማ መረዳሳ ጋር ጋር ሄድኩኝ። ሰጥቷል የከፍለከተማው ካድሬ ሲሆን ቤኩማ የባለአደራው ከንቲባ ነበር። ሁለቱ ሰዎች በተወሰደው እርምጃ እርር ትክን ብለዋል። ቤኩማ አፍ አውጥቶ ሁኔታዎች ወደ ነበሩበት ካልተቀለበሱ ለከንቲባ ብርሀኑ ዴሬሳ መልቀቂያ እንደሚያስገባ ነገረኝ። በአንድ ወቅት ቤኩማ ኢህአዴግ እንዲሆን ለመመልመል ፈልገን የተቃወመው ተከለፃዲቅ ሬባ ነበር። የአነግ አመለካከት አለው በማለት። እነሆ! የሰዎች ማንነት መለኪያ ቀን ደረሰና አነጉ ቤኩማ ከአቃቂ ህዝብ ጐን ተሰለፈ። ህዝብ እየተበደለ ስራዬን አልሰራም በማለት ህዝባዊነቱን አስመሰከረ።

የአካባቢው ህዝብ የቀበሌ 04 አዳራሽ ሞልቶ እደጅ ፈሷል። መጥፎ ጊዜ። ሰው ሰውን ለመጉዳት መሪ የሚኮንበት ወቅት። የኦሮሚያ ፓሊሶች አማተዋቸው የነበሩትን ሰዎች እንዳይሞቱ እንዳይድኑ አድርገው ቀጥቅጠዋል። ግንባራቸው በፉሻ ተጠቅልሎ በአዳራሹ ፊት መስመር ተቀምጠዋል። በመጨረሻው ጫፍ የተቀመጡት ወጣቶቹ ቁጭት ከርቀት ይነበባል። ቄሶችና ሼሆች በህዝቡ ስም ተማጽኖ ለማቅረብ ተገኝተዋል። የተማሪና መምህራን ተወካዮች ዩኒፎርማቸውን ሳያወልቁ በቁጣና ብስጭት ውስጥ ሆነው ታድመዋል።

ለአታት ከፈጀ ውይይትና ማጽናናት በኋላ ሁኔታዎች ወደነበሩበት

እንደሚመለሱ ቃል ገባሁ። በቅርብ ቀን ምላሽ ይገፍ እንደምመጣ በመግለጽ ተሰናብቼ ወጣሁ። እንደ እውነቱ ከሆነ ምን እንደማደርግ ማን ጋር እንደምሄድ አላውቅም ነበር። ፍላጐቱ ከየት እንደመነጨ ማወቅ እንኳን አልቻልኩም። እነ አባዱላ አረንጓዴ መብራት ሳያዩ እንደዚህ አይነት ድፍረት ውስጥ ይገባሉ ብሎ ማሰብ አልዋጥልህ አለኝ። አቶ መለስን ጨምሮ የኢህአዴግ ፓሊት ቢሮ አባላት የአዲሳአባ ህዝብ ላይ ያነገቡት በቀል ጉልበት እንደሆናቸው ጠረጠርኩ። ኢህአዴግ ቢሮ እንዳጣራ የላከኝ ለይምሰል እንደሆነ ማሰብ ጀመርኩ።

ወደ ቢሮ መመለስ ልቦናዬ አልቀበል አለኝ። የህዝቡ ጩኸትና ብሶት እየደጋገመ ያቃጭልብኛል። ተስፉ የሚያስቆርጠው ንግግራቸው መረጋጋት አይሰጥም። የማደርገው ጨነቀኝ። ጭንቅላቴ በመርፌ እየተጠቀጠቀ ጭምድድ ያለ መሰለኝ። መኖሪያ ቤቴ ቡልጋሪያ አጠገብ ወደሚገኝ ባር በመሄድ ባንኮኒ ላይ በጊዜ ተሰየምኩ። በባዶ ሆድ በአናት በአናቱ ቸለስኩበት። የምጠጣው ደረቅ አልኮል እየለበለበኝ ወረደ። እያባበለ ይዞኝ ሄደ።

እኩለ ለሊት አለፈ።

ባለቤቴ መጥታ አፉፍሳ ወሰደችኝ። በሷ እርዳታ ወደ ቤቴ ገባሁ። ከዛ በኋላ የሆነውን አላውቅም። ምንአልባትም ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ሳይወስደኝ አልቀረም። የነቃሁት ቀስቅሳ የሸሮ ፍትፍት ስታጐርሰኝ ነበር። ለካስ ብዙ ለፍልፌያለሁ። ሆደ ባሻ ሆኖ ተንሰቅስቄም አልቅሻለሁ። ሆድ ያባውን ብቅል አውጥቶታል! እንኳንም የግራ ጐኔ ሆነች። በላይ በላዩ እያጐረሰች የምታጽናናኝ። እንደእውነቱ ከሆነ ብዙ ጊዜ የስራ ጭንቀቴን አላካፍላትም። ይሄኛው ግን ሞልቶ ገነፈለ።

ገና በጠዋት ጣይቱ ደወለች። የእነ አባዱላ ውሀ ቅዳ ውሀ መልስ ጨዋታ ሰልችቶኛል።ጨጓራ የሚልጥ ስራ እየተሰራ እስከመቼ ይኖራል?... አንበጣና በረሮ ከወረረው የኢህአዴግ ፓለቲካ መቼ ይሆን የምላቀቀው? የአዲሳአባ ህዝብ ላይ እየደረሰ ያለው የመከራ ዶፍ ዝናብ መቼ ይሆን የሚያባራው? ...በተስፉ መቁረጥ ውስጥ ሆኜ ስልኩን አነሳሁት። ስሜን እየጠራች፣

"አባዱላ በለሊት ተነስቶ ቾካልና ታፔላውን እንዲነቅል አደረግነው። ፓሊሶቹም ወደ መጡበት ተመልሰዋል።"

ከተኛሁበት ዘልዬ ተነሳሁ።

"ጣይቱ አንዴት ሊሆን ቻለ? አንቺ እኮ ብልህ ነሽ!፣ የአላማ ጽናት ተምሳሌት! አንቺን ባናገኝ ምን ይውጠን ነበር? ከሴቶች ሁሉ በአመራር

ብቃትሽ የተመረጥሽ !" አልኳት። የዘወትር መዝሙሬን።

በድል አድራጊነት ስሜት ውስጥ ሆና፣

"ገሬ ከሱማሊያ ለስብሰባ መጥቷል። በተሰራው ፀረ-ህዝብ ስራ ጭንቅላቴን እንዳመመኝ ነገርኩት። የአቃቂና ቀራንዮ ህዝቡ ያለውን በሙሉ አጫወትኩት። ከመለስ ጋር ጠዋት ቀጠሮ ስላለው እንዲነግረው ብዬ ነበር። እንደተናደድኩኝ ሲያውቅ እሱም ተናደደ። በቀጥታ ለአባዱላ ደውሎ ተቆጣው። በሀይለ ቃል እየሰራችሁት ያለው ፀረ -ህዝብ ነው ፣በአስቸኳይ መቀልበስ አለባችሁ በማለት አስጠነቀቀው።"

"የሚገርም ነገር እየነገርሽኝ ነው! አንቺ እኮ ብልህ ነሽ! የአላማ ጽናት ተምሳሌት..."

በማያቋርጥ ሳቅ ውስጥ ሆና፣

"አባዱላ ተደናግጦ የማውቀው ነገር የለም አይል መሰለህ? ምን አይነት ቀጣፊ ነው? የዞን አመራሮች የፈጠሩት ሊሆን ይችላል ብሎ ድርቅ አለ። የሌባ ደረቅ አይን ምንትሴ የምትሉት አባባል። ረሳሁት"

"የሌባ አይነ ደረቅ፣ መልሶ ልብ ያደርቅ። እንደዛ ነው የሚባለው ፀሀይቱ! አንቺ እኮ..."

"Thank You! በደንብ አስታወስከኝ ! የሌባ አይነደረቅ ልብ ያድርቅ! ...እኔማ እሱን ከለቀቅኩ የባህታ ልጅ አይደለሁም! ከመለስ ጋር በሚኖረን ስብሰባ ልክ ልኩን እነግረዋለሁ!"

"እንዳትለቂው ፀሀይቱ! አንቺ እኮ ብልህ ነሽ!..."

ቢሮ ለመገናኘት ተቀጣጥረን ስልኩ ተዘጋ። ወደ አቃቂና ቀራንዮ ካድሬዎች ደወልኩ። ርግጥም በለሊት ተነቅሏል። ህዝቡ ለሊቱን ሙሉ ደስታውን ሲገልጽ እንዳደረ ሰማሁ። መብቱ በጉልበተኞችና አጉራ ዘለሎች እየተነጠቀ ሲመለስለት የሚደሰት ህዝብ!

ግራም ነፈሰ ቀኝ ፀሀይቱ በገሬ ውስጥ አድራ የነዋሪውን ልቅሶ አብሳለች። ኮስታራው ገሬ ለሱማሊያ ብቻ ሳይሆን ለአዲሳአባም ፍቱን መዳኒት ሆነ። ምእራፍ ቀያሪ የተባለው እርምጃ ጉዳዩ በማይመለከተው ሰው ተቀጨ። የአህዴድ ካድሬዎች በሀፍረት ተቀሉ።

ገሬ ከበረሀ ጀምሮ የፀሀይቱ ባለቤቷ ነው። ሙሉ ስሙ ኮሎኔል ገ/እግዚአብሄር አለምሰገድ ይባላል። የመከላከያ መረጃና ደህንነት ስራ በእሱ ጫንቃ ላይ ወድቋል። ከመለስ ጋር ቅርብ ግንኙነት አለው። በሱማሊያ የነበረው የኢትዮጵያ ጦር የበላይ አዛዥ ነበር። ከጦርነቱ በኋላ የሱማሊያ ጐሳዎችን የማግባባትና ማደራደር ስራ ይሰራል። ሱማሌዎች "ሐጂ አብድላሂ" ብለው ይጠሩታል።

እስከማውቀው ድረስ ገሬም ሆነ ፀሀይቱ በሙስና የሚታሙ

አይደሉም። ሳር ቤት አካባቢ መከላከያ በሰጣቸው እጅግ በጣም ጠባብ አፓርትመንት ውስጥ ከሁለት ልጆቻቸው ጋር ተፋፍገው ይኖራሉ። ከሳሎኑ ወደ መኝታ ቤቱ በሁለት እርምጃ ይደረሳል።ወንድና ሴት ልጆቻቸው አልጋ ደርበው በአንድ መኝታ ቤት ይኖራሉ። ፀሀይቱ በሽተኛ ሆናለች። ህመሟ በሀገር ውስጥ ህክምና ስለማይድን በውጭ ሄዳ እንድትታከም ሀኪም አዟታል። ጥርሷን የነቀለችበት ኢህአዴግ ወጪውን አልሸፍንም በማለቱ ከፍተኛ ቅሬታ ውስጥ ወድቃ ነበር።

***

እውን ፌንፌኔና አዲሳአባ አንድ ናቸው?

ስልቻም ቀንቀሎ... ቀንቀሎም ስልቻ??
የኢትዮጵያ ህገ - መንግስቱ ምን ይላል ?

የህገመንግስቱ አንቀፅ 49 ንኡስ አንቀፅ ሶስት እንደሚከተለው ይላል፣

"የኦሮሚያ ክልል ፣የአገልግሎት አቅርቦት ወይም የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምና የመሳሰሉት ጉዳዮች በተመለከተ እንዲሁም አዲስ አበባ በኦሮሚያ ክልል መሀል የሚገኝ በመሆኑ የሚነሱ ሁለቱን የሚያስተሳስሩ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ያለው ልዩ ጥቅም ይጠበቅለታል። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።"

እነሆ! ዝርዝሩ ህጉ ሳይሰራ ሁለት አስርተ አመታት ሊሞላው ጥቂት ዘመናት ብቻ ቀርቷል። በርካታ አጨቃጫቂ ህጐች በወጡበት ሁኔታ ለዚህ ዳተኛ የመኮኑ ምክንያት አቶ መለስ የሚፈራው ፓለቲካዊ ምክንያት ስለነበረው ነበር።

ይህ ንኡስ አንቀፅ ኦሮሚያ በተመረጡ ጉዳዮች ላይ ልዩ ጥቅሟ እንደሚጠበቅላት ይደነግጋል። እነዚህም የአገልግሎት አቅርቦት፣ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምና ሁለቱን በሚያስተሳስሩ አስተዳደራዊ ጉዳዮች በማለት በግልፅ ሰፍሯል። ከዚህ ውጪ ኦሮሚያ አዲሳባን እንደ ዋና ከተማዋ መውሰድ እንደሚገባት የሚያመላክት አንድም ህገ- መንግስታዊ ድንጋጌ የለም። አስተዳደራዊ ጉዳዮች የሚለው ተለጥጦ ዋና ከተማ አስከሚለው ዘልቆ ይሄዳል እስካልተባለ ድረስ።

ህገ መንግስቱ ትክክል ሆነም አልሆነ አዲሳባ የኦሮሚያ አካል እንዳልሆነች አመላክቷል። አዲስአባ በኦሮሚያ ክልል መሀል የምትገኝ መሆኗን ለይቶ በማሳየት። ይህን የህገ መንግስት ድንጋጌ በሚደግፉት ዘንድ መዲናይቱ በተለያዩ አካላት የእዝ መሳሳብ እንዳይደርስባት፣ ራሷን በራሷ የማስተዳደር መብቷን በነፃነት እንድትተገብር ታሳቢ ተወስዶ የተቀረፀ እንደሆነ ይታመናል።

የአዲሳአባ ቻርተር ምን ይላል?

የቻርተሩ ክፍል አንድ ምእራፍ አምስት እንደሚከተለው ይላል፣

"አሁን ያለው የከተማው ክልል እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የከተማው ወሰን የከተማው አስተዳደር ከኦሮሚያ ክልል ጋር በሚያደርገው ስምምነት ይወሰናል። የወሰን ምልክትም ይደረግበታል።"

ከዚህ በተጨማሪም በቻርተሩ ክፍል ዘጠኝ የከተማው አስተዳደርና የኦሮሚያ ክልል ግንኙነት በሚጠቅሰው አንቀፅ 62 ላይ የሚከተለው ሰፍሮ እናገኛለን፣

"የከተማው አስተዳደር ከኦሮሚያ ክልል ጋር ፍሬያማ ትብብርን መሰረት ያደረገ ግንኙነት ይኖረዋል። በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ 49(5) መሰረት የኦሮሚያ ክልል ጥቅም የተጠበቀ ነው። ዝርዝሩ በከተማው አስተዳደርና በኦሮሚያ ክልል መካከል በሚደረግ ስምምነት ወይም በሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት በሚወጣ ህግ ይወሰናል።"

እነሆ! ቻርተሩ በስራ ላይ ከዋለ አስር አመት አለፈው። የከተማው ወሰን አይታወቅም። ወሰን ሳይታወቅ ደግሞ ምልክት አይደረግም። "የወደፊት በህግ ይወሰናል" እንጥልጥልም መቋጫ አላገኘም። በኦህዴድና የአዲሳባ ህዝብ መካከል ያለው ግንኙነት ፍሬያማ ውጥረቶችንና ግጭቶችን በየጊዜው ይፈለፍላል። ኢህአዴግ የአዲሳባን ህዝብ ንቆ ኦህዴድ እንዳይከፉው አንድ ጊዜ ኩማ ደመቅሳን ሌላ ጊዜ ድሪባ ኩማን ከንቲባ እያደረገ ያስቀምጣል። ከእንግዲህ በኃላ ኢህአዴግ በኢትዮጵያ ፓለቲካ ውስጥ እስካለ ድረስ ከንቲባነት የኦህዴድ ቋሚ ንብረት ይሆናል። የአዲሳአባ ህዝብ ፈለገም አልፈለገም ይህ ኦህዴድን የማባበያ ውሳኔ ለተራዘመ ጊዜ ይቀጥላል።

ከዲሞክራሲ መብት አኳያ...

ርግጥ ይህ የህገ መንግስት ውሳኔ ከዲሞክራሲ መብት አኳያም ቢሆን ሚዛን የሚደፉ ነው። በአዲሳባና ኦሮሚያ ሊገነባ የሚችለው የዲሞክራሲያዊ ስርአት በይዘታቸው የተለያዩና በቀላሉ የማይጣጣሙ ናቸው።

(ይህ ማስታወሻ ትኩረቱ አዲሳአባ በመሆኑ እንጂ አብዛኛው የኢትዮጵያ ከተሞች በዚህ ማእቀፍ ውስጥ የሚያርፉ ናቸው። ጅማ፣ ናዝሬት (ቢሾፍቱ)፣ ናዝሬት (አዳማ)፣ ዝዋይ፣ ነቀምት፣ ባሌ ሮቤ፣ አሰላ፣ አዋሳ፣ አርባምንጭ፣ ድሬደዋ፣ ሀረር...ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው።)

የኦሮሚያ የፓለቲካ ምህዳር...

የኦሮሚያ ክልል ለረጅም ጊዜያቶች በቡድን መብት በተለይም በኦሮሞ ብሔርተኝነትት እንደሚቃኝ የሚያጠያይቅ አይሆንም። ይህንን ሀቅ ያልተገነዘበ የፓለቲካ አካሄድ በክልሉ ቦታ አይኖረውም። ከየትኛውም በኢትዮጵያ ከሚገኙ ብሔሮች በላይ የኦሮሞ ብሔርተኝነት ጫፍ የረገጠ የፕሮፓጋንዳ ስራ ተሰርቶበታል። ለኦሮሞ ህዝቦች እንታገላለን የሚሉ ነፃ አውጪነን ባዮች፣ ድርጅቶችና ንቅናቄዎች ቁጥራቸው ብዙ ነው። በክልሉ የሚንቀሳቀሱ የፓለቲካ ድርጅቶች ፍጥጫ እኔ ከዛኛው በተሻለ የኦሮሞ ብሄርተኝነትን እወክላለሁ በሚል ቅኝት የሚመራ ሆኗል።አንዳንዶቹ የኦሮሞ ዲሞክራሲያዊ ብሔርተኝነት በኢትዮጵያዊነት ማእቀፍ ውስጥ እንዲጓዝ ፕሮግራም ቀርፀው ይንቀሳቀሳሉ። የኦሮሞ መብት የሚከበረው የሁሉም ብሄር መብቶች በኢትዮጵያዊነት ጥላ ስር ሲከበር እንደሆነ ይገልጻሉ። ሌሎቹ ደግሞ ኦሮሚያ የምትባል ነፃ ሀገር ተመስርታ ማየት አለብን በማለት እስከ ብረት ማንሳት ይዘልቃሉ። ጫፍ በወጣ ሁኔታ ኦሮሚያ ነፃ ወጥታ በእስልምና ህግ የምትተዳደር እንድትሆን የሚፈልጉ ቡድኖችም ይገኛሉ። ሁሉንም የሚያስማማቸው አንድ ነገር አለ።አማራውን እንደ ጨቋኝና በነፍጥ የገዛ ብሄር አድርጐ መመልከት።

አህዴድ በቲአሪ ደረጃ የኦሮሞ ዲሞክራሲያዊ ብሔርተኝነት በኢትዮጵያዊነት ማእቀፍ ውስጥ እንዲጓዝ ፕሮግራም ቀርጾ የሚንቀሳቀስ ድርጅት ነው። የኦሮሚያን ህገ መንግስት ሲያዘጋጅ እንደ መተክል አድርጐ የወሰደው የኦሮሞ ህዝብ የብሔር ጭቆና ደርሶበታል የሚለውን ነው። ይህን እንደ መነሻ በመውሰድ የኦሮሞ ብሄርተኝነት ማረጋገጥ የህገመንግስቱ መሰረታዊ አላማ ተደርጐ እንዲቀረጽ ተደርጓል። በመሆኑም ህገ መንግስቱ ከጅምሩ አርቆ አስተዋይነት የጐደለው፣ ሁሉን ማካተት የተሳነው፣ በጥላቻ ፓለቲካ ላይ የተመሰረተና ፀረ - ዲሞክራሲያዊ ነው።

ከኢኮኖሚ ጥያቄዎችም አንፃር የኦሮሚያ ህገ መንግስት መነሻ ያደረገው "የኦሮሞ ህዝብ የኢኮኖሚ ጭቆና ደርሶበታል፣ በገዛ መሬቱ ባሪያ ሆኖ ነበር..." የሚሉ ወደፊት ሳይሆን ወደኃላ የሚያዩ ቁምነገሮችን በመንተራስ የተዘጋጀ ነው። በዚህ ምክንያት በህገ መንግስቱ የመሬት ጥያቄ ከኢኮኖሚ ፋይዳው ይልቅ ፓለቲካዊ ይዘት እንዲኖረው ተደርጓል። ይህንን ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ በመንተራስ አግላይ ፓሊሲዎችና ህጐች እንዲወጡ ተደርጓል። በዜጐች መካከል ክፍፍል እንዲፈጠር በማድረግ ያለመተማመንና የጥላቻ መንስኤ ሆኗል። በክልሉ አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ ደረጃ የሚወጣላቸው ዜጐች እንዲፈጠሩ ተደርጓል።

(በመኮረጅ ተስተካካይ ያልተገኘላቸው እነ አባዱላ ከህውሀት በመቅዳት "የኦሮሞ ባለሀብት መፍጠር" የሚል ስትራቴጂ በመንደፍ ተንቀሳቅሰው ነበር። የማስፈፀሚያ መንገዶች የነበሩት ለኦህዴድና ባለስልጣናት ቅርብ የሆኑ የኦሮሞ ተወላጆችን በመለየት በተመረጡ ኢንቨስትመቶች፣ በብድር አገልግሎትና ቁልፍ ቦታዎች ላይ መሬት በመስጠት እንዲፈፀም ማድረግ የሚል ነበር። ይህ ስትራቴጂ እንደ ህውሀት ሁሉ እዛው ሳለ የጉራጌ ባለሀብቶችን የማዳከም አቅጣጫ ተከትሏል። እንደ እውነቱ ከሆነ የኦሮሞ ባለሀብት መፍጠር የሚለው ስትራቴጂ ጭምብሉ ሲገለጥ አባዱላን ወደ ሚሊየነርነት፣ ግርማ ብሩን ወደ ደንበል ሲቲ ሴንተር የበላይ ጠባቂነት አሸጋገረ። በአዲሳአባ ዙሪያ ያሉ የኦሮሚያ ዞኖችንና ናዝሬት (አዳማን) ደግሞ በባለቤት አልባ ህንፃና ፎቆች እንዲጥለቀለቁ አደረገ።)

በመሆኑም የኦሮሚያ ህገ መንግስት የኦሮሞ ህዝብ እንደ ኦሮሞነቱ ሊይዛቸው የሚገቡ የጋራ ፍላጐቶች የሚንፀባረቅበት እንጂ በተሞላ መልኩ የተናጠል ግለሰባዊ መብቶችን እውቅና አይሰጥም። እንዲህ በመሆኑ ምክንያት የመጀመሪያው ገፈት ቀማሾች የኦሮሞ ተወላጆች ሆነው ግለሰባዊ መብታቸው እንዲቀድም የሚፈልጉት ይሆናሉ። የዲሞክራሲ የመጀመሪያው መገለጫ የግለሰብ መብት ማክበር ስለሆነ። እነዚህ ግለሰቦች ከቡድን ቀፎ ወጥተው የግለሰብና ቤተሰብ ህይወታቸውን የመወሰን የማይገደብ መብታቸውን ተነጥቀዋል።

የኦሮሚያ ህገ መንግስት ወደ ኃላ የሚያይ በመሆኑ በቅድሚያ የበቀል ጡንቻው ታርጌት ያደረገው በክልሉ የሚኖሩ ከኦሮሞ ብሄረሰብ ውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያንን ነው። ይህ ጊዜ ያለፈበት አስተሳሰብ እነዚህ ዜጐች እንደ ቡድንም ሆነ ግለሰብ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብታቸው በተሟላ ሁኔታ እንዳይረጋገጥ አድርጓል። ከኦሮሞ ውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያን በክልሉ ተረጋግተው እንዳይኖሩ፣ ቋሚ ንብረት እንዳያፈሩ ፣በምርጫ ተወዳድረው እንዳይመረጡ አድርገውአቸዋል። በኦሮሚያ በተዘረጋው ስርአት አመኔታ የሌላቸው በመሆኑ አስተዳደራዊና የፍትህ ስርአቱ ከጅምሩ የተጨናገፈ ሆኗል። በዚህም ምክንያት በብሄሩ ተወላጆችና በሌሎች ዜጐች መካከል እርስ በራስ መተማመን እንዲጠፋ፣ ሌሎች ኢትዮጵያውያን የኦሮሞ ተወላጅን በጥርጣሬና ፍራቻ፣ አልፎ ተርፎም በጠባብ ብሄርተኝነት እንዲመለከታቸው አድርጓል።

የአዲሳአባ ፓለቲካ ምህዳር...

በተቃራኒው የአዲሳአባ የፓለቲካ ምህዳር በግለሰብ መብት ላይ

ያነጣጠረ በመሆኑ ኦሮሚያ ጋር ካለው ነባራዊ ሁኔታ መገታተሩ አይቀርም። በእርግጥ በግለሰብ ላይ የሚመሰረት የዲሞክራሲ ስርአት የቡድን መብትን ማጣጣም እድሉ ከፍተኛ ቢሆንም።

አብዛኛው የአዲሳባ ህዝብ በየትኛውም የብሄር ማእቀፍ የተደራጁ ፓለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ መመደብ እንደማይፈልግ በተለያዩ ጊዜያቶች አረጋግጧል። ለዚህ አባባል ማሳያ እንዲሆን በምርጫ 97 ማግስት ኢህአዴግ ነዋሪውን በብሄር ማደራጀት እርግፍ አድርጉ በመተው ወጣቶች፣ ሴቶችና ነዋሪዎች የሚሉ ፎረሞች እንዲፈጠሩ ያደረገበት ምክንያት ከላይ የተጠቀሰው እውነታ ነበር።

እንዲህ ነበር የሆነው...

በብሔር ላይ የተመረኮዘ የቡድን መብት ዋነኛ አቀንቃኝ የሆነው ኢህአዴግ የህልውና ጥያቄ ሲያጋጥመው ተንሸራቶ ህዝቡን በማህበራዊ ቦታው ለመከፋፈል የሞከረው በዚህ ተጨባጭ እውነታ ነበር። የ1998 ዓ.ም የአዲሳአባ የፓለቲካ ስራ አቅጣጫ ለማስቀመጥ ከአቶ መለስ ጋር በነበረን ስብሰባ፣

"ከእንግዲህ በአዲሳባ ምድር የብሄር አደረጃጀት መከተል ራስን ለተደጋጋሚ ሽንፈት ማዘጋጀት ነው። የመዲናይቱ ነዋሪ በተለይም ወጣቱ የዘር አጀንዳ እንዲነሳበት አይፈልግም።" በማለት ተናግሮ ነበር።

ይህን የአቶ መለስ ውሳኔ ተከትሎ ከህውሀት ውጭ ያሉት የብሄር ድርጅቶች እጃቸውን ከአዲሳአባ አነሱ። ህውሀቶች አስቀድመው ራሳቸውን ከኢህአዴግ ቢሮ ስላገለሉ ውሳኔውን አልቀበልም በማለት በመዲናይቱ የትግራይ ወጣቶች እስከማቋቋም የትእቢት እርምጃ ወሰዱ። ለድርድር ቢጠሩም ፍቃደኛ ሳይሆኑ ቀሩ። ሌሎቹም የእነሱን እርምጃ እንዲከተሉ ከጀርባ አደራጁ። እሰጣ ገባው ሳይጠናቀቅ የኢህአዴግ ጉባኤ በአዋሳ ተጠራ።

በአዋሳው ጉባኤ የአዲሳአባ ጉዳይ የመጀመሪያ አጀንዳ እንዲሆን የማያወላዳ ጥናት ሰራን። ለአዲሳባ ኢህአዴግ ሊግ ለተመለመሉ 30 ሺህ ወጣቶች "መደራጀት የምትፈልጉት በምን መልኩ ነው?" የሚል መጠይቅ እንዲበተን አደረግን። መጠይቁ ተሞልቶ ሲመጣ 92% በላይ የሚሆኑት ምላሽ ሰጪዎች" የብሄር አደረጃጀት አንፈልግም።ከአዲሳባ አስወግዱልን!" የሚል ምላሽ ሰጡ። በነገራችን ላይ የእነዚህ ወጣቶች የዘር ግንድ ከሁሉም ብሄረሰብ የተውጣጣ ነበር።

ጥናቱን የመራው ለብሄር አደረጃጀት ጥላቻ ያለው ለስልጣን መቆናጠጫ ሲል ብቻ ከኪሱ መዞ የሚያወጣት ሬድዋን ሁሴን ነበር። በጉባኤው ያቀረበውም እሱ ሆነ። አቶ መለስ መፈናፈኛ ሲያጣ በጉባዔ መወሰን ያለበትን ጉዳይ ለስራ አስፈጻሚ ውክልና ይሰጠን ብሎ በማስፈቀድ የኢህአዴግን ህገ ደንብ ጣሰ። ከዋልዋ ልጅ ተቃውሞ ውጭ በሌላው ጉባኤተኛ ተፈቀደለት። የዋልዋ ልጅ ባልተጠበቀና በሚያስደነግጥ ሁኔታ፣

"ለምንድነው በአዲሳባ ብቻ? በአጠቃላይ በዘር የተደራጀው ኢህአዴግ ፈርሶ ወደ አንድ ፓርቲ መምጣት አለበት። ይህ ታሪካዊ ውሳኔ በዚህ ጉባኤ መወሰን ይኖርበታል!" የሚል አስተያየት ሰጠ።

ጉባዔተኛው ተደናገጠ። ሁኔታዎች ወደማይፈለግ አቅጣጫ እንዳያመሩ ስጋት የገባው በረከት ስምኦን፣

"አደረጃጀት አንድን አላማ በተሻለ ደረጃ ለማስፈፀም የሚቀረፅ ነው። በራሱ የመጨረሻ ግብ አይደለም። በመሆኑም አላማችንን ለማሳካት የትኛው አደረጃጀት ይሻለናል የሚለውን በጉባዔ ከምንወስን ዝርዝር ጥናት ሰርተን ለሌላ ጊዜ ብንመለከተው ይሻላል።" የሚል አስተያየት ሰጠ። የበረከት ፈጣን አስተያየት በሁለት ጫፍ ሊጨቃጨቅ የተዘጋጀውን ካድሬ ምላስ የቆረጠ ነበር።

የበረከት አስተያየት ያልተዋጠለት ተፈራ በድጋሚ እጁን ቢያወጣም መለስ ነፈገው። በቀጥታም ለስራ አስፈፃሚው ውክልና ይሰጥ/አይሰጥ የሚለው ላይ ድምፅ እንዲሰጥበት አደረገ። ከዋልዋ ውጭ ጥናቱን ሰርተንና ሴራ ጠንስሰን የገባነው ህላዌ፣ሬድዋን፣ካሚል፣ ፀጋዬ ሀይለማርያም እና በአጠቃላይ ጉባኤተኛው መለስን በመደገፍ ለፓሊት ቢሮው በውክልና እንዲሰጥ ወሰን። የተፈ እጅ ለብቻዋ ተቀሰረች። በንጋታው የወጣው ሪፓርተር ጋዜጣ የፊት ገጹ ሙሉ ሽፉን የተፈራ ዋልዋ ፎቶ ሆነ። በማስታወሻነት በማህደሬ አስቀመጥኩት። በፎቶ ግራፉ ወይዘሮ አዜብ ዋልዋን በአግርሞት ትመለከታለች፣ ኩማ ደመቅሳ፣ ሙክታር ከድርና ዶክተር ሙላቱ ተሾመ ይስቃሉ።

ጉባኤው በተካሄደ በሳምንቱ ስራ አስፈፃሚው ሳይጠራ የኢህአዴግ ፕሮግራምና ህገ ደንብ ተሻሻለ። የአዲሳባ ወጣት ከሌላው አካባቢ በተለየ የኢህአዴግ አባል መሆን ከፈለገ በብሄር ድርጅት መታቀፍ ሳያስፈልገው በግለሰብ ደረጃ መሆን እንደሚችል ይፉ ሆነ። ይህም ኢህአዴግ የግለሰብ አባል የለውም የሚለውን ህግ እንዲሻሻል አደረገ። ከመዲናይቱ ኢህአዴግን በራሱ ጉባኤ አባረርነው።

(ርግጥም ክስተቱ ታሪካዊ ነበር። ኢህአዴግ የመኖርና ያለመኖር ጥያቄ

ሲያጋጥመው ፕሮግራሙንና ህገ ደንቡን ያሻሻለበት ወቅት። ከጉባኤው በኋላ በነበሩት ዓመታት በነበሩት የአሳትዳር ጨዋታዎች ዋልዋን አወደስን። ኢህአዴግ በሰልጣን ላይ ሆኖ የሰልጣኑ ማማ ላይ የመጨረሻው ሰው እሱ ቢሆን ኖሮ ምንአልባትም ኢትዮጵያ አሁን የያዘቸው ቅርጽ ላይሆን እንደሚችል ተከራከርን። የበረከትን ፈጣን አከሮባት አደነቅን። መለስን በህገ ደንብ ጣሺነት ከሰስን። በኢህአዴግ ወጣት ሊግ ውስጥ አባል ቢሆኑም የልባቸውን ምላሽ የሰጡንን 30 ሺህ የአዲሳአባ ወጣቶችን አመሰገንን።

ከእለታት በአንዱ ቀን በረከት እንደዛ ላይነት አስተያየት ፈጥኖ ለምን እንደሰጠ ጠየኩት። የሰምአን ልጅ አፍንጫውን እየገሙተ፣

"እንደ ተፈ ግርግር የብሄር አደረጃጀት ይቅር ብንል የጠባብነት ፊትአውራሪ የሆነው መራራ ጉዲና እና መሰል ጓደኞቹ ይነግሱብን ነበር።" የሚል ምላሽ ሰጠኝ።)

ምእራፍ ሃያ

ጉንጬ አልፉው ግምግማ

"... እኔን ከድርጅቱ ለማጣላት አስበህ ከሆነ ለዘላለም አይሳካልህም!!"
በረከት ስምአን

"... የእኔና የአንተ ችግር የዛሬ ሳይሆን ከበረሀ ጀምሮ ነው!!"
አርከበ እቀሳባይ

በምርጫው ቀን እኩለ ለሊት የተቋቋመውና በአርከበና ጀነራል ታደሰ ወረደ የሚመራው የፓለቲካና ፀጥታ ጥምር ኮሚቴ በአንድ በኩል የአቶ መለስ ዙፋንን እየጠበቀ በሌላ በኩል የአዲሳባን መሬት መዝረፍ ጀመረ። "መመሪያ ቁጥር ሶስት" በሚለው ርዕስ እንደተጠቀሰው ከ1978 በፊት ታጋይ የነበሩና ማእረጋቸው ከኮረኔል በላይ የሆኑት ቦሌ ላይ መሬት ተሰጣቸው። አፈጻጸሙ ቦሌን "ትንሿ መቀሌ" የሚል ስያሜ እንዲሰጣት አደረገ። ከዚህ አንፃር ለምን ተለይቶ ቦሌ የሚለው ጥያቄ በብዙዎች ዘንድ ይነሳል። ነገሩ እንዲህ ነው።

በተለየ ሁኔታ ቦሌ እንዲወሰዱ የተደረገበት ሶስት መሰረታዊ ምክንያቶች ነበሩ። የቦሌ መሬት ማግኘት ወረቅ እንደመዝገን ስለሚቆጠር፣ ከአየር መንገዱ ጋር ተያይዞ አለም አቀፍ ትኩረት የሚሰጠው ቦታ በመሆኑና የአካባቢውን ህዝብ የሀይል ሚዛን ለማዛባት የታሰበ ነበር። በኢህአዴግ የሀይል አሰላለፍ ትንተና መሰረት የቦሌ ነዋሪ ፀረ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ተደርጐ የተፈረጀ ሲሆን ኢህአዴግ ተፈራ ዋልዋን የሚያካክሉ ካድሬዎቹን ለምርጫ አቅርቦ ከአንዴም ሁለቴ ሀፍረት የተከናነበበት ነበር። እናም ይህን የሀይል ሚዛን መቀየር እንደ አንድ ታሳቢ መውሰድ አስፈላጊ ሆኗል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአዲሳባ ህዝብ ቦሌ አካባቢን "ትንሿ መቀሌ" ያለበት ምክንያት ይህ ነው። ርግጥም አቶ መለስ እንደገመተውም የሀይል ሚዛኑ ተዛብቷል። በተጭበረበረ የድምፅ ቆጠራ እንኳን ኢህአዴግ አሸንፎባት የማያውቃት ወረዳ 18 ቦታዋን ለመርካቶ ለቃለች... ለተከበሩ የፓርላማ አባል ግርማ ሰይፉ!... የመርካቶ መልሶ ማልማት እስኪጠናቀቅ ድረስ።

ከሙሉ ኮረኔል በታች ያሉት ወታደሮች በሌሎች ማስፉፊያ ክፍለ ከተሞች ተደለደሉ። ወሬው ባድመና ጸረና ጦር ግንባር ድረስ ተዳረሰ። ወታደራዊ መኮንኖቹ ምሽጋቸውን አየለቀቁ በጦር ኢሊኮፍተሮች ጭምር እየተሳፈሩ አዲሳባን ወረሯት። የክፍለ ከተሞች ግቢ አቧራ በጠጣ የኮከብ፣

ጋሻና ጦር ከምር የተሸከመ ካኪ ተጥለቀለቀ።

ከቀናት በኋላ አዲስ አበባ አጥንቷ ተግጦ እርቃኗን ታየች። አዱነነትና ልጆቿ አለቀሱ። እንባዋን ባያብሱላትም የነቀዘውን ታሪክ በዚህ መልኩ መከተቡ አስፈላጊ መስሎ ስለታያቸው በዝርዝር ወደ ማሳየት ተሸጋገሩ። በመሆኑም ይህን የዝርፊያ ሂደት በትክክል ለመገንዘብ ይቻል ዘንድ ይበልጥ ገሃ ብለው ስለተፈፀሙት ሌብነቶችና ግለሰቦች እያነሳን እንመልከተው። ወደ ዝርዝር ከመግባታችን በፊት ለንጽጽር እንዲረዳ በረከት ስምኦን በሁለት ምርጫዎች ወግ መጽሀፉ ላይ ያስቀመጠውን መልእክት እናስቀድም።

አቶ በረከት በመጽሀፉ የመቋጫ ወግ በሚለው ርእስ ስር የኢህአዴግ ካድሬዎች ከብዙ መሰል ሀይሎች የሚለዩባቸው ብሎ ከገለፃቸው አራት ባህሪያት ውስጥ ሁለተኛው ይህን ይላል፣

"...ሁለተኛውና ምንአልባትም የኢህአዴግ መሪዎችና ታጋዮችን ከብዙ መሰል ሀይሎች ለየት ባለ ደረጃ እንዲታዩ የሚያደርጋቸው ፣እንደ ቡድን ስልጣንን ለህዝብ ጥቅም እንጂ ለራስ ጥቅም ማካበቻ ማድረግ የለብንም ብለው ማመናቸውና ይህንንም በተግባር ለማዋል ያለመሰልቸት መስራታቸው ነው።... ሀብት መፍጠር እንጂ የተፈጠረን ሀብት መቀራመት ከድህነት አያላቅቅም ብለው ያመኑት ኢህአድጎች፣ እነሆ ስልጣንን የሀብት መቀራመቻ ሳይሆን አገር የመለወጫ መሳሪያ አደረጉት። አገር በመለወጥና ራስን በመጥቀም መካከል ያለውን ልዩነት ለአፍታም ሳይዘነጉ በመስራታቸው፣ በአገራችን እጅግ በጣም ፍትሀዊ ሊባል የሚችል ፈጣን እድገት እንዲመጣ ለማድረግ በቁ..."

በአራት ኪሎ ኢህአዴግ ቢሮ በረከት በመራው ግምገማ ይህንን አባባል የሚጣሉ ግኝቶች ተደምጠዋል። ለግምገማው መነሻ የተዘጋጀውን ሀያ ገጽ ጽሁፍ ራሱ በረከት የፃፈው ሲሆን ርእሱ፣" ከምርጫው በኃላ የድርጅታችንን ስም ያጉደፉና የህዝቡን ቅሬታ ያባባሱ ተግባራት" የሚል ነበር። ከግምገማው በኋላ የተዘረፈውን መሬት ማስመለሻ የይቅርታ ፎርም ያዘጋጀውም በረከት ነበር። ይህ የይቅርታ ፎርም ህገ መንግስቱን የጣሰና ኢህአዴግ ለህግ የበላይነት ደንታ የሌለው፣ ለፍትህ ስርአቱ ንቀት ያለው መሆኑን የሚያመላክት ነበር። ፍርድ ቤት መስጠት ያለበትን ብይን በቆረጣ ኢህአዴግ ዳኛ የሆነበት አጋጣሚ። የተዘረፈው ህዝብ ሆኖ ሳለ ይቅርታ የተጠየቀው ኢህአዴግና እሱ የሚመራው መንግስት እንዲሆን የተደረገበት ነበር። ህላዌን ጨምሮ ከ600 በላይ ካድሬዎች የይቅርታ ፎርሙን የሞሉ ሲሆን፣ በፉይል ተጠርዞ በኢህአዴግ ቢሮና በክፍለከተሞች መሬት አስተዳደር ለታሪክ ተቀምጧል። ከሁሉም በጣም የሚያሳዝነውና ጭንቅላት የሚነካው መሬት እንዲመልሱ የተደረገውና የይቅርታ ፎርም እንዲሞሉ የተደረገው ህላዌን ጨምሮ ነባሩ የከተማው ካድሬና በግምገማው ላይ የተገኙት ብቻ ናቸው። ሚኒስትሮች፣ ወታደራዊ መኮንኖች፣ የኢህአዴግ ልማት ድርጅቶች፣ ፌደራል ፓሊስ፣ ዋልታ፣ ሬዲዮ ፉና፣ ደህንነት ቢሮ፣ ከየክልሉ ተንደርድረው በመምጣት መሬት የዘረፉ የካቢኔ አባላት ጫፉቸው ጋር የደረሰ የለም።

እነሆ! ለታሪክ የተቀመጠው የይቅርታ ፎርሙ እንደሚከተለው ይላል፣

ለቦሌ ክፍለከተማ መሬት አስተዳደር

እኔ ህላዌ ዮሴፍ ድርጅቴ ኢህአዴግና መንግስት የጣሉበኝን አደራና ሀላፊነት ወደ ጐን በመተው ህገ ወጥ በሆነ መንገድ የመሬት ወረራ ላይ በመሰማራት አንድ መሬት ወስጃለሁ። በመሆኑም ይህን ያለአግባብ የወሰድኩትን መሬት አስተዳደሩ እንዲረከበኝ በማክበር እጠይቃለሁ። ድርጅቴ ኢህአዴግና በእሱ የሚመራው መንግስትም ይቅርታ እንዲያደርግልኝና ከእንግዲህ ወዲያ በየትኛውም የድርጅቴንና መንግስት ስም በሚያጐድፍ ተግባራት ላለመሰማራት ቃል እገባለሁ።

ከሰላምታ ጋር
ህላዌ ዮሴፍ

ግልባጭ
ለአዲስ አበባ ጊዜያዊ ባለአደራ አስተዳደር
ለቦሌ ክፍለከተማ ጊዜያዊ ባላደራ አስተዳደር
ለኢህአዴግ ጽ/ ቤት

ከምርጫው በኃላ የተደረገው ግምገማ ይሄን ይመስል ነበር። ምንም እንኳን በሁለት ምርጫዎች ወግ መጽሐፉ የትኛውም ገጽ ላይ ባይጠቀስም። በረከት አንድ ጊዜ ፓናዶል ፣ሌላ ጊዜ ኖባልጅን እየዋጠና ቁና ቁና እየተነፈሰ ያዳመጣቸው ወጐች ዝርዝር ደግሞ እንደሚከተለው ቀርቧል።

***

ከቤና ገሬ

ከበደ ብሩና ገ/ተንሳይ የትምህርት ቢሮን የለውጥ ኮሚቴ የመሩ የህውሀት ካድሬዎች ናቸው። ሁለቱ ካድሬዎች በግለሂሳቸው አስደንጋጭ የሆኑ የሌብነት ታሪኮችን ነግረውናል።

መጀመሪያ ያቀረበው ከበደ ብሩ ነበር። ከቤ አምስት ኪሎ ጀርባ የህዝብ ንብረት የሆነ ትምህርት ቤት ለግለሰብ ሸጠ። ከአሜሪካን ሀገር ከመጣ ፓስተር ባደግ ከሚባል ሰው ጋር በመሰማጠር እስከ አፍንጫው ኪራይ ሰበሰበ። አርከበ ቦሌ ላይ መሬት ሰጠው። መቀሌ ላይ የሙስና መንደር ተብሎ በሚታወቀው ገረቡቡ በሚባል ቦታ ቪላ ሰራ።

የገ/ተንሳይ የሚገርም ነው...

የምረጫ 97 ማግስት የተካሄደውን የመሬት ወረራ አስመልክቶ በረከት ስምአን በመራው ግምገማ ላይ ወደ ሚሊኒየርነት መሸጋገሩን በራሱ አንደበት አረጋገጠ።

ገ/ተንሳይ ከብዙ አውጫጭኝ በኋላ የገለፀው ተጠቃሎ ሲታይ የሚከተለውን ይመስላል፦

መጀመሪያ የሚኖርበትን የቀበሌ ቤት በሀምሳ ሺህ ብር ሸጠ። ቀጥሎ አሊ አብዶን አስፈራርቶ ቦሌ ላይ አይን መሬት ወሰደ። የትምህርት ቢሮ ቁሳቁስና ማቴሪያል በመጠቀም ሺላ ቤት ሰራ። ምርጫ ዘጠና ሰባትን ተከትሎ በተካሄደው መሬት ወረራ በራሱ ስም ሁለት፣ በልጁ ስም ሁለት መሬት ወስዶ ሸጠ። ቦሌ የገነባውን ሺላ ቤት ምርጫው በተካሄደ በሳምንቱ በግማሽ ሚሊዮን ብር አሻገረ። አርከበ በሲኤምሲ ከተገነቡት የአስተዳደሩ ቤቶች ውስጥ ሩብ ሚሊዮን የጨረታ ዋጋ የተለጠፈበትን ቤት ጨረታውን በማንሳት በሰባ ሺህ ብር ያውም በሀያ አመት ተከፍሎ በሚያልቅ ዱቤ ሰጠው። አንድ የቀድሞ ጓደኛው በእግርህ ስትሔድ ማየት አልፈልግም ብሎ የ200 ሺህ ብር መኪና በስጦታ መልክ ሰጠው።

ገሬ ቀልደኛ ነው...

በንዴት ተንተክትኮና አይኑ ቀልቶ የሚያዳምጠውን በረከት ስምኦን መምከር ጀመረ። እንዲህ በማለት፣

"በረከት ዘመኑ ካፒታሊዝም ነው። ከማንም በላይ ይህ ማለት ምን እንደሆነ አንተ ይገባሀል። በጀማሪ ካፒታሊዝም ግንባታ ውስጥ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ካፒታል ማከማቸት ግድ የሚልበት ወቅት ነው። ከታች ወደ ላይ በሚደረገው የሀብት ጉዞ ሽግሽግ ውስጥ የኢህአዴግ አባላትን ይዞ መገኘት ለፓርቲው ህልውና ወሳኝ ነው...በዛ ላይ አዲሳባን ከእንግዲህ ወደ እኛ የመመለሳቸውን ሁኔታ የማይቻልበት ..."

በረከት አልአስጨረሰውም ። ቁጣው ገንፍሎ መጨረሻ ደረጃ ሲደርስ እንደሚያደርገው አፍንጫውን እየጐተተ፣

"ገ/ተንሳይ ይህንን ጠንቃራ ትንታኔ ቃሊቲ አስር ቤት ውስጥ ጊዜ ስለምታገኝ ቁጭ ብለህ ትጽፈዋለህ" አለው። ገሬ ፈገግ አለ... እኛ ደነገጥን።

የስምኦን ልጅ እንደዛተው ከዛሬ ነገ ወደ ቃሊቲ ይወረወራል ብለን ስንጠብቅ አቶ አርከበን አጅቦ ከጓደኛው ከቤ ጋር ወደ ስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ሄደ። ከሚኒስትር በላይ በሆነ ደሞዝ የሰው ሀይል ልማት ዋና ዲያሬክቶሬት ሆኖ ተሾመ። ከቤ ደግሞ ምክትሉ። ይህ ማንም ፍላጐት ያደረበት ተቆርቋሪ ወርዶ ሊያረጋግጠው የሚችል ነውረኛ ታሪክ ነው። ምንም እንኳን ለኢህአዴግ አመራሮች አዲስ ባይሆንም። በረከት የታሪኩ ባለቤት ነው። በዝዋይ ህፃናት አምባ ጠቅላይ ሚኒስትር ሀይለማርያም በቁጭት ደጋግሞ ሲያነሳ ሰምቻለሁ። ከሚኒስትር ሬድዋን ጋር ደግሞ የአርከበን ስጋ በቦጨቅን

ቁጥር የገሬ ታሪክ ፊታችን ትደቀናለች።

በረከት በመራው ግምገማ ገ/ ተንሳይ የወንጀሉ ጥፋት በመግዘፉ ፣ግን ደግሞ ለእናት ድርጅቱ ህውሀት ታማኝ በመሆኑ በሹመት ላይ ሹመት ተሰጥቶታል። በተቃራኒው ከከበደ ብሩ ጋር በጥምር ሲሰራ የነበረው ዳንኤል አርጋው የሚባል የጉራጌ ካድሬ የአርከበ ግምገማ ሲቀርብ ብዙ መገለጫዎችን በማንሳት፣ "አርከበ ሌባ ነው! ለሌቦችም ከለላ ይሰጣል፣ አርከበ ዘረኛና አምባገነን (Totaliterian) ነው።" የሚል ማሳመኛ ያቀርባል። ዳንኤል ራሱን አስመልክቶ ሁለት ቦታ መሬት መዝረፉን እያለቀሰ በፀፀት ተናገረ። አንዱን ቢሸጠውም የተቀረውን ለመመለስ ፍቃደኛ እንደሆነ ገለፀ።

የዳንኤል ግምገማ የምርጫ 97 ጥፋቶች ሳይሆኑ የአመለካከትና ውግንና ችግር ሆነው ብቅ አሉ። "ትምክህተኛው ዶክተር ብርሀኑ ነጋ አዲሳአባን ይለውጣታል ብለህ ለጓደኞችህ ተናግረሀል" የሚል ሂስ ቀረበበት። የተቀለበሰው የጉራጌ መራሹ አብዮት ላይ የነበረውን ሚና እንዲዘከዝክ ተገደደ። እንደሌለበት ደጋግሞ አስረዳ። የእምነት ቃሉ አልጠቀመውም። ከድርጅትና ማንኛውም የመንግስት ስራ እንዳይመደብ ተደረገ። በተማርኩበት የማቲማቲክስ መ.ያ የማስተማር ስራ ልመደብ ብሎ ቢጠይቅ በድጋሚ ይከለከላል። ቅሬታውን ይዞ የጉራጌ ካድሬዎች አለቃ ወደ ሆነው ዶክተር ካሱ ኢላላ ጋር ይሄዳል። ዶክተር ካሱ ዳንኤል የሚያቀርበው ቅሬታ ትክክል መሆኑን እንደሚያምንበት ግን ደግሞ እነ አርከበን የሚያካክሉ ዝሆኖች መጋፋት እንደማይችል በግልፅ ይነግረዋል። በወቅቱ ዶክተሩ የስራና ከተማ ልማት ሚኒስትር የነበረ ሲሆን አርከበ ደግሞ ምክትሉ ነበር። ህሊና ያለው ሰው ለሆዱ ከተሸነፈ የጥፋት አውራ ይሆናል።

ዳንኤል ለሶስት አመታት ስራ አጥቶ ተንከራተተ። ቅሬታዉን ለማሰማት ያልረገጠበት ቦታ የለም። በመጨረሻም ለአቶ መለስ፣ "የጉራጌ መራሹ አብዮት እንዲቀለበስ ግንባር ቀደም ሚና እንደነበረኝ ከአንተ በላይ ምስክር የለኝም። በየሶስት ቀኑ ከአንተ ጋር ለስብሰባ እንገናኝ ነበር። ለምልክት እንዲረዳህ የመርካቶና አካባቢዋን ሪፓርት የማቀርበው ካድሬ ነኝ" የሚል ደብዳቤ ላከ። የአቶ መለስ ቅርጫት ውጦ አስቀረው።

ሀገር ጥሎ ከወጣው ከአመታት በኃላ ጓደኛዬ ዳንኤል እቤቴ ድረስ በቴሌቭዥን መስኮት ብቅ አለ። ያውም ቤተመንግስት ግቢ ውስጥ። ወቅቱ ደግሞ የአቶ መለስ ዜና እረፍትን አስመልክቶ ህዝቡ ልቅሶ የሚደርስበት ነበር። እናም ዳንኤል የአልቃሽ ሰራዊት አሰልፎ አንዴ ከፊት ሌላ ጊዜ ከኃላ ይመራል። በጣም ገረመኝ። በውስጤም ብዙ ጥያቄዎች ተመላለሱ። የድሮ የዩንቨርስቲ ያውም ዶርምተሪ ወዳጄ ለአቶ መለስ አለቀሰ ወይስ አስለቀሰ? ...እንደው

ስገምት እንደ ጐዳና ተዳዳሪው ወጣት፣ "አንተን ተማምኜ አርከበን ሌባና ዘረኛ በማለቴ አይቀጡ ቅጣት ተቀጣው" ብሎ ወቀሳ ቢጤ ያቀረበ ይመስለኛል... ሙት ወቃሽ!!

***

"ምቴና መውጫ"

የበአዴን ቁንጮዎቹ ተናደዋል...በረከት፣ ህላዌና ፍሬህይወት አያሌው።

ከንቲባ አርከበን እየተከታተለ መረጃ ይሰጠናል ብለው ከባህርዳር ያስመጡት የበአዴን ካድሬ ከድቷቸዋል።

ቀውላላው ምትኩ ሀበነ።

ምትኩ በአማራ ክልል የምትገኝ አንዲት ወረዳ የሲቪል ሰርቪስ ጽ/ ቤት ሀላፊ ነበር። አዲሳባ በመዋጮ እንድትተዳደር በተወሰነው መሰረት ወረዳዋን ለቆ ወደ መዲናይቱ መጣ። የአራዳ ክፍለ ከተማ ከንቲባ ሆኖ ተመደበ። በመጀመሪያዎቹ ወቅቶች ከተማው ግር እንዳይለውና የቅርብ ድጋፍ እንድታደርግለት ከኢህአዴግ ቢሮ ፍሬህይወት አያሌው ተመደበችለት። ፍሬ በደንብ አላመደቻው። የከተማውን መግቢያ መውጫ አሳየችው። መኖሪያ ቤቱና የሚሰራበት ህንፃ እሷ የምትኖርበት አራት ኪሎ ፊት ለፊት ከሚገኙት መንታ ህንፃዎች እንዲሆን አደረገች። ከፍሬ ቀልደኛ አንደበት እንደሰማነው አስፓልት ሲሻገር እንኳን መኪና እንዳይበላው የትራፊክ መብራት አስተምራዋለች።

ከባህርዳር ሲመጣ መለመሉን እንደሆነ የተገነዘበችው ፍሬ ከኪሷ አውጥታ የቤት ቁሳቁስ ሳይቀር ገዛችለት። አሮጌ ሞዝቦልድ አልጋዋን በስጦታ መልክ ሰጠችው። ቤተሰቦቹን እንዲያመጣ ድጋፍ አደረገችለት። ወይዘሪት ፍሬህይወት መልካም ሴት ነበረች።

ምትኩ ከበአዴን ባገኘው አረንቴሽን መሰረት ስራውን ጀመረ። ከህላዌ ጋር እየተደረበ አርከበን መቃወም ስራው አደረገው። ታማኝነቱን በተግባር አሳየ። ሁኔታው አላምር ያለው አርከበ ከትግራይ አምጥቶ ምክትል ከንቲባ አድርጐ የሾመውን መውጫ የሚባል የህውሀት ካድሬ አስታጥቆ ላከው... መውጫ የቤት ስራውን በአግባቡ ሰራ።

ምትኩ የቅርብ ድጋፍ እንድታደርግለት ከተመደበችለት ፍሬህይወት ደብዛውን አጠፉ። ስልኳን ማንሳት አቆመ። ግራ ቢገባት ወደ መኖሪያ ቤቱ ሄደች። ያየቸውን ማመን አቃታት። 60 ሺህ ብር ወጪ የተደረገበት ቆዳ ሶፋ እንደ ጥቁር ዘንዶ ተዘርግቷል። ለቢሮው ከተገዛለት ጋር ተመሳሳይ ነበር። በወቅቱ የክላስ መለያ ተደርጐ የሚቆጠረው ጠፍጣፉ ቴሌቭዥን ግርግዳውን አድምቆታል። ተመሳሳይ ዋጋ የወጣባቸው ምንጣፎችና መደርደሪያዎች መኖሪያ ቤቱን የአርከበ አቁባይ ቢሮ አስመስለውታል። ወደ ውስጥ ሲገባ ደግሞ የሚኒሊክ አልጋን የሚያስንቅ ሞዝቮልድ የመኝታ ቤቱ ግርማ ሞገስ ሆኗል።

ልጆቹ አስጠኚ ተቀጥሮላቸው ይማራሉ።

አርከበ ስኳር ካላሰው በታላ እንደ ሻንጣው ይዞት ይዞር ጀመር። በየመድረኩ ከግራ ጐኑ መቀመጥ ጀመረ። ውጭ ሀገር ሀላቄን ተክቶ እስከመሄድ ደረሰ። አርከበ አፍ አውጥቶ፣ "ብአዴን ስራ የማይወደውን ሀላቄ ከሚመድብልኝ አንተን ቢያደርግ ኖሮ የት በደረስን ነበር!" በማለት አሞካሸው። የህውሀት ካድሬዎች ሀላቄን እንደ ስራ ጠል ይቆጥሩታል።

ጨዓራቸው የቆሰለው እነ ሀላቄ እሸህን በእሸህ በሚለው ፈሊጥ መሰረት ይሳቅ ቆሪጥ የሚባል የህውሀት ነባር ታጋይ የአራዳ የድርጅት ጉዳይ ሀላፊ አድርገው መደቡ። ይሄ ማርሽ ቀያሪ ካድሬ ጊዜ ሳያጠፉ ወደ ስራ ገባ።

(ይሳቅ ቆሪጥ በአንድ ሰርአት ውስጥ ከሚፈጠሩ ልዩ ሰዎች አንዱ ነው። ይሳቅ ብዙ ሰው ነው፡- አለቃ ገብርሀና፣ ቆምጬ አምባው፣ ወልደሰላሴ(የደህንነት ሹም የነበረው)፣ ኢኮኖሚስቱ ንዋይ ገብርአብ አጣምሮ የያዘ ካድሬ ...

አቶ መለስና ሚስታቸውን፣ በረከትን፣ ሽማግሌው ስብሀትን፣ ኢህአዴግን ከገቡበት ማጥ አውጥቷል። ጉድ ሰርቷል።ዛሬ ኢህአዴግ "ሊግ" እያለ የሚመፃደቅበት አደረጃጀት ባልተጠበቀ ሁኔታ በመዲናይቱ የሚገኙ አደገኛ ሌቦችና ነብስ ገዳዮችን በማደራጀት ወደ ተግባር የቀየረ የቁርጥ ቀን ታጋይ ነው።

ይሳቅ ቆሪጥ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ደቀ መዝሙር ነው፡ እነ አርቲስት አረጋኸኝ ወራሽ፣ ሳፎንቴኖች፣ ኢዮብ (ነብሱን ይማረውና)፣ ጌዲ በተራ፣ ሀመልማል አባተን ኢህአዴግ ቢሮ በመጥራት ሊያጠምቃቸው ተግቷል...

ይሳቅ የፍትህዊነት ንጉስ ነው፡ ኢንተርናሽናል አልቢትር የሚመራበት እግር ኳስ ውድድር ላይ በከብር እንግድነት ተገኝቶ የነባ ጐል፣" በአብዮታውያን መካከል መሸናነፍ የለም" በማለት የሚሸር።

ይሳቅ ቆሪጥ የሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ፕሬዝዳንት ዶክተር ሀ/ሚካኤል ያገሳፀፈው ኢኮኖሚስት ነው፡ የፍላጐትና አቅርቦትን ተዛምዶ የማያውቅ የምጣኔ ሀብት ምሁር። ይሳቅ ቁልፍ ባለስልጣን ነው፡ ትላንትና የክፍለጦር አዛዦ፣ የደህንነት ሹም፣ የአዲሳባ ኢህአደግ ክንፍ ስራ አስፈፃሚ፣ የኢትዮጵያ ደረቅ ወደብ አገልግሎት ዋና ስራ አስኪያጅ፣ ዛሬ ደግሞ የኢትዮጵያ መድን ፈንድ ስራ አስኪያጅ። ይሳቅ ቆሪጥ ራሱን የቻለ መጽሐፍ ነው፡ "ዘመን ተሻጋሪ ካድሬ" በሚል ርእስ ተጽፎ አልቋል... ተራው ሲደርስ ይነበባል።)

እናም እነ ሀላቄ ይሳቅን መምረጣቸው ትክክል ነበር። በአጭር ጊዜ ምትኩ፣ መውጫና የትምህርት ቢሮን የለውጥ ኮሚቴ የመራው ከበደ ብሩ የተቀናጁበትን ሌብነት ይፋ አወጣ።

ታሪኩ እንዲህ ነበር።

አምስት ኪሎ ከሚገኘው ሲኖዶስ ጀርባ አንድ በህዝብ የሚተዳደር አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነበር። ይህ የከተማዋ አይን ቦታ ላይ የተቋቋመ ትምህርት ቤት ከ40 አመት በላይ ያስቆጠረ ሲሆን ባለቤቱ የአካባቢው ህዝብ ነው። ነዋሪው እንደ ማንኛውም የህዝብ ትምህርት ቤት ከመንግስት ድጋፍ አየተደረገለት ልጆቹን ያስተምርበታል።

እናም እነዚህ ካድሬዎች መምህራኑንና ህፃናቱን አባረው ለአንድ ከአሜሪካ ለመጣ ፓስተር ባደግ በቀለ ለሚባል አጭበርባሪ በዜሮ ዋጋ ይሰጡታል። ፓስተሩም ኢንተርናሽናል ሊደርሺፕ ኢንስቲትዮት የሚል ማሰልጠኛ ተቋም ያቋቁማል። እኔን ጨምሮ በረከት፣ ሀይለማርያም፣ ኩማ፣ ሬድዋን፣ ሽፈራው ሽጉጤ፣ ጁነዲን፣ ደግፌ ቡላ፣ አስቴር ማሞ፣ ጀነራሎቻችን፣ የአማራ፣ ኦሮሚያና ደቡብ፣ ሱማሊያ ካቢኔ አባላት... ኧረ ስንቱ ማስተርሳችንን የሰራነው በዚህ የሌብነት ተምሳሌት በሆነ ለሰርተፍኬት ማስተማር እንኳን ብቁ ባልሆነ የአየር ባየር ተቋም ነው። የተከበረው ፓርላማ ሚኒስትር በሾመ ቁጥር "በተቋማዊ አመራር" አየተባለ የሚቀርበው የትምህርት ደረጃ የፓስተር ባደግ "ኪራይ ሰብሳቢነት" ልዩ ስጦታ ነው።

በሌላ በኩል ይሳቅ ቆሪጥ ክትትሉን አጠናክሮ ይቀጥላል። ከ200 በላይ የአካባቢውን ነዋሪዎች ፒቲሽን ያሰባስባል። ህዝቡን በአዳራሽ ሰብስባ በመጥራት የተፈፀመውን ሌብነት በካሜራ እንዲቀረፅ ያደርጋል። ለእማኝነትም በአካባቢው የሚኖረውንና የህዝቡ አቤቱታ አልአስቀምጥ ያለውን የኢህአዴግ ቢሮ ካድሬው ካሚል አህመድን እንዲሳተፍ ያደርጋል። መረጃዎቹን ከካሚል ጋር አጠናቅሮ ወደ ፀረ ሙስና ሊልከው መዘጋጀቱን ለእመቤቱ በሚስጥር ሹክ ይላል። ሴትየዋም ለባለቤታ አቶ መለስ ታቀብላለች። ነገሮችን አስተሳስሮ የማየት ብቃት ያለው አቶ መለስ ችግሩን ከስር መሰረቱ ለማወቅ የኢህአዴግና የብሄር ድርጅቶች ግምገማ እንዲካሄድ ያዛል።

ይህ ግምገማ የተደበቁ ሚስጥሮችን አወጣ። የህገ መንግስቱንና ኢህአዴግን ህልውና አደጋ ገጠመው። የሀሪሬ ክልላዊ መንግስት ጥያቄ ውስጥ ገባ። የብአዴን አጣብቂኝ (paradox) በይፋ ተገለፀ። የኢህአዴግ ካድሬዎች ባለቤት የሆኑባቸው ሼሮችና አክሲዮኖች ይፉ ወጡ። ሽፈራው ሽጉጤ እቤት የተቀመጡ የ80 አመት አባቱን ስራ አስኪያጅ በማስደረግ በወር 10 ሺህ ብር እንዳስቀጠረ ተጋለጠ (የቀጠረለት ደግሞ በቡና ልማት ለመሰማራት አሰፍስፎ የነበረው ፓስተር ባደግ በቀለ ሆነ::) አባዱላ ምርጫ ተሰጠው (በ5 ሚሊዮን ብር የገነባውን ቤት እንዲያስረክብ አሊያም ከእነ ታምራትና ስዬ ጋር መቀላቀል። የቁርጥ ቀን መምጣቱን አውቆ ለአህዴድ በስጦታ መልክ አስረከበ፡ የተዘረፈው ህዝብ የሚወርሰው ድርጅት!!)። የባለስልጣናት ንብረት ምዝገባ ሊካሄድ መረጃ ሲሰባሰብ አባዱላ የስጦታ ወረቀቱን ቀዶ የግሉ ንብረት አደረገ።

ይህ ሁሉ የተንዛዛ ንቅዘት ይሳቅ ቆሪጥ የገሎተው ነው። "ዘመን

ተሻጋሪው ካድሬ" በሚለው ማስታወሻ ላይ "የፓስተሩ መዘዝ" በሚል ርእስ ሰፊ ቦታ ተሰጥቶታል። ለአሁኑ ወጋችን ይሳቅን ያመጣነው ስለ አራዳ እንቁዎቹ ምትኩና መውጫ በምርጫ 97 ማግስት የፈፀሙትን ሌብነት ሊተርክልን ስለሆነ ወደዛው እንውሰደው።

በምርጫ 97 ማግስት እነ ምትኩ ይህን አደረጉ።

ምትኩና መውጫ ለህዝብ ጥቅም ሲባል በዶሮ ማነቂያ የገነቡትን የጥቃቅንና አነስተኛ ሼድ ለባለሀብትና ገንዘብ አዋጥተው ለሰጧቸው ወጣቶች በመቶ ሺዎች ሸጡ። የተሰፋ ቃል ሲመገቡ የነበሩ ከ50 በላይ ወጣቶች በይሳቅ ፊትአውራሪነት ሌብነቱን የሚያሳይ ፒቲሽን ተፈራርመው ለኢህአዴግ ቢሮ አስገቡ። በረከት በመራው ጉንጭ አልፋ ግምገማ ላይ በዝርዝር ቀረበ። ተሰብሳቢውም ምትኩና መውጫ በግምገማው ላይ እንዲገኙ ጥያቄ አቀረበ።

የስምኦን ልጅ ለምትኩ ስልክ ደወለ። መልስ አልሰጠውም። ለአርከበ በንጋታው ይዞት እንዲመጣ ትእዛዝ አስተላለፈ። በሚቀጥለው ቀን አርከበ ብቻውን መጣ። ምትኩና መውጫ በአፋር ክልል ያለውን የቤት ግንባታ ለመመልከት ወደዛው ማቅናታቸውን አስረዳ። በምላሹ የተበሳጨት የብአዴን ዝሆኖች ምትኩን ከድርጅት ማገዳቸውን ይፋ አደረጉ። ከአፋር ሲመለስም ወደ አማራ ክልል በመመለስ የቀድሞውን ሲቪል ሰርቪስ ሰራተኝነቱን እንዲሰራ ወሰኑ።

የሆነው ግን ሌላ ነበር። ምትኩ እነ በረከት ላይ ምላሱን አውጥቶ አላገጠባቸው። ወደ አማራ ክልል ሳይመለስ ከመውጫ ጋር አርከበን አጅበው ወደ ስራና ክተማ ልማት ሚኒስቴር ሄዱ። ምትኩ በቢሊዮን ብር የሚፈስበት የአፋር ቤት ልማት ፕሮጀክት ዋና ዴሬክተር በመሆን በወር 15ሺህ ብር የሚከፈለው ባለስልጣን ሆነ። ያለ ጨረታ በመቶ ሚሊዮኖች እየወጣ ሲምንቶና ብረት የሚገዛበት ተቋም በንብረትነት ተሰጠው... ከተገዛው ውስጥ ምን ያህሉ አፋር እንደሚደርስ እግዜርና የፈረሰው የአሊ ሴሮ ጨረቃ ምርምር ቢሮ ይወቀው!...

በመጨረሻው ውጤት የተበሳጨው ይሳቅ ቆሪጥ መላ ዘየደ። እንደለመደው ማርሽ ቀየረ። የክስ ዶሴዎችን ይዞ ፓስተር ባደግ ጋር ሔደ። እየገላለጠ አሳየው። ስለ ኪራይ ሰብሳቢነት ምንነትና ትርጉም ከሀገረ አሜሪካን ለመጣው ፓስተር ቁጭ አድርጐ አስረዳው። አፍታም ሳይቆይ በተቋማዊ አመራር ማስተርስ በማግኘት እኛን ተቀላቀለ... የልጆቹን ስም አስተካክሎ መፃፍ የማይችለው ይሳቅ በኢኮኖሚክስ ባችለር፣ በሊደርሺፕ ማስተርስ ባለቤት ሆነ።

***

ሮምና ሉሌ

ሉልሰገድ ይፍሩ... ሉሌ።
የዛሬዎቹ የአዲሳባ ካቢኔ አባላት ፀጋዬና ሺሰማ "ሻለቃ! የቁረጠው

ፍለጠው ጌታ" ይሉታል። አገዛዙ ወታደራዊ አምባገነን መሆኑን ለማሳየት። በተለይ ሺሰማ ሰለ ሉልሰገድ ባህሪ ሲገልጽ፣

"መጀመሪያ እንደ ዶሮ አንገትህን ጠምዝዞ ይገልህል... ቀጥሎ ቢሮው ወሰጥ ጥልቅ ጉድጓድ በመቆፈር ይቀብርሀል... ጠዋት ሰራ ከመጀመሩ በፊት ወንበሮቹን እያነሳሳ አለመነሳትህን ያረጋግጣል " ይለዋል።

ሉሌ ማለት ይህ ነው። እንደስያሚው ከእንቅልፉ በተነሳ ቁጥር አንድ ሰው ያባርራል። ስራውን በአባረራቸው ሰዎች ቁጥር ይለካል። ደብዛቸውን ለማጥፉት ያሰባቸውን ካድሬዎችና የመንግስት ሰራተኞች የማይገረሰስ ስም አስቀድሞ ይለጥፉል፣ "የምሁር ትምክህት አለበት"፣ "የአነግ ባንዲራ እቤቱ ተገኘ"፣ "የህገመንግስቱን አንቀፅ 39 አይቀበልም"፣" የቅርብ ጓደኛው በመአድ ስብሰባ ላይ ተገኝቶ ነበር"... ሉሌ በፍረጃ ቃላት ሀብታም ነው።

ይህ ጭካኔው በአብዮታዊ ታጋይነት እንዲቆጠር አደረገው። የአሊ አብዶ ቀኝ እጅ ሆነ ...የአሊን የብቃት ማነስና የፈፀማቸውን ወንጀሎች ያጋለጡ ካድሬዎችን እያሳደደ ደፈጠጠ። የምርጫ ኮሮጆ ግልብጥብጡን በማውጣት አሊን ከመሸነፍ ታደገው።

አሊ አብዶም ቢሆን የሉሌን ውለታ መርሳት አልፈለገም። ራሱን የማልረባ፣ ዝርክርክ፣ ዘባተሎ ባለ በወሩ የተካሄደ ምደባ ላይ አውራ ሆኖ ተገኘ። ለነባሩ የአዲሳባ ካድሬ በክፍለ ከተማ ለመመደብ የመጀመሪያ ዲግሪ እንደ ቅድመ ሁኔታ ቢወሰድም፣ ለሉሌ እንደ ህውሀት ካድሬዎች በልዩ ሁኔታ 12 ኛ ክፍል በቂው ተደርጐ እንዲያዝለት አደረገ። በዘመነ አርከበ የአዲስ ከተማ ከንቲባ እንዲሆን አደረገ።

በአፍሪካ ትልቁ ገበያ የሆነችውን ውስብስቧን መርካቶ መምራት በሉሌ አቅም የሚሆን አልነበረም። የታቀዱ ስራዎች ዘጭ ብለው ወደቁ። በተለይ ከፍተኛ ግብር ይሰበሰብበታል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት የንግዱ ዘርፍ ነጠፈ። አርከበና ሉሌ ግብግብ ገጠሙ። አፍታም ሳይቆይ አርከበ ከትግራይ ሮማን ተስፉይ የምትባል ካድሬ አምጥቶ ስራ አስኪያጅ አድርጐ ሾመ። ሮማን ወፍ ከሰማይ የምታረግፍ፣ በንግግሯ አራት ነጥብ የማታውቅ የመቀሌ ጩልሌ ናት።

ሉሌ የማይጋፉው ባላጋራ ስለገጠመው የሀይል አሰላለፍ ቀየረ። ከተወዳጁ ከንቲባ በተቃራኒ ለተሰለፉት ህላዌና በረከት ገበረ። ይህን ያወቀው አርከበ ሉሌን ለማባረር የሚያስችሉ ጥፉቶችን የከተማው ካድሬዎች በተሰበሰብንበት ዘረገፈ። እንዲባረር አሊያም ከደረጃው ዝቅ እንዲል የውሳኔ ሀሳብ አቀረበ። ህውሀቶች የድጋፍ አስተያየት አቀረቡ። በተለይም የላፍቶው ከንቲባ ሀይሌ ፍስሀ ዛሬውኑ ተፈጻሚ ካልሆነ ሞቼ እገኛለሁ በማለት ተከራከረ።

ሁኔታው ያላማረው ህላዌ ጊዜ ስጡኝ ብሎ ወደ ደጅ ወጣ አለ። ከበረከት ጋር ተማክሮ በመመምጣት ካድሬው በተሰበሰበበት፣ "ብአዴን

ስላልፈቀደች የሉልሰገድን ጫፍ እንዳትነካ!" በማለት አርከበንና የህውሀት ካድሬዎችን አስጠነቀቀ።

በነገራችን ላይ "ብአዴን አልፈቀደችም"፣ "ህውሀት እያየችው ነው"፣ "አህዴድ አላመነበትም" የሚሉ ቃላቶች በኢህአዴግ ደጃፍ የተለመዱ ናቸው። ኢህአዴግ የግለሰቦች ስብስብ ስላልሆነ የማባረር ስልጣን የለውም የሚል ምክንያት ይቀርባል። የብሄር ድርጅቶቹ የሌባ ጫካ ፣ሙሰኛ ካድሬዎች ደግሞ አፍቅሮ ብሄር የሆኑባቸው አንዱ ምክንያት ይህ ነው። ኢህአዴግ ያባርራል፣ ህውሀት ይሾማል!... ኢህአዴግ ሌባ ይላል፣ አህዴድ ለአምባሳደርነት እጩ አድርጎ ያመጣል። ኢህአዴግ የመምራት አቅም የለውም ይላል፣ ህውሀት የክልል ካቢኔ ያደርጋል።

የማባረሩ አማራጭ እንደማይሰራ የተገነዘበው አርከበ ከሉሌ ጋር ያለውን ግንኙነት ሙሉ ለሙሉ አቋረጠ። ስብሰባ አይጠራውም። ስራውን አይገመግምም። ሉሌ ቸግሮት እንኳን ለአርከበ ቢደውል "ከሮማን ጋር ተነጋግረናል እሷ ትሰራዋለች" ይለዋል።

እያደር የሉሌ የመርካቶ ከንቲባነት የስም ብቻ ሆነ። የመንግስት ሀላፊነቱ ባዶ ሲቀርበት ወደ ፓለቲካ ስራ አዘነበለ። ይህም የሚሆን አልነበረም። የህውሀት ካድሬዎች ሉልሰገድ አይመራንም በማለት ተገንጥለው ወጡ። ሀይሌ ፍስሀና ፀሀይቱ ባህታ ከላፍቶ መርካቶ እየተወረወሩ ህውሀትን መምራት ጀመሩ። በዚህም ምክንያት የአዲስ ከተማ ኢህአዴግ ለሁለት አመት ያህል (እስከ ምርጫ 97) ድረስ የሶስት ብሄር ድርጅቶች ጥምረት ነበር... ብአዴን፣ አህዴድና ደኢህዴን።

ሮማን በበኩሏ አዲስከተማን ነገሰችበት።መርካቶን አሳርሳ ለአዲሶቹ የህውሀት ባለሀብቶች ቸበቸበች።አርከበ ከባላንጣዎቹ እነ ተወልደና አለምሰገድ ተረከቦ ያስቀጠለውን የህውሀት ባለሀብቶች መፍጠር አላማ ዋነኛ አስፈፃሚ ሆነች። የጉራጌ ነጋዴዎችን ደም እምባ አስለቀሰች። የህውሀት ነጋዴዎችን የመፍጠር ስትራቴጂ አዛው ሳለ የጉራጌ ነጋዴዎችንና ባለሀብቶችን ማዳከም የሚል አላማ እንደነበረው ተደጋግሞ ተገጿል። ኢኮኖሚውን የሚቆጣጠር ሀይል በሂደት ፓለቲካል ኢኮኖሚው ላይ የበላይነት ማሳረፉ ስለማይቀር ጉራጌን ከንግዱ አለም ማስወጣት ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም። ሮማን የጉራጌ ነጋዴዎችን እንዳያንሰራሩ የምትቀጣበት ምክንያት ይህ ነበር።

እነ ሮማን በፈጠሩት ልዩነት ጉራማይሌዋ መርካቶ ይበልጥ ተዘበራረቀች።ተመሳሳይ እቃዎች በነባሮቹና አዲሶቹ ነጋዴዎች መካከል የዋጋ ልዩነት አሳየ።የግብርና ሊዝ እፎይታ ያገኙት አዲሶቹ ነጋዴዎች ዋጋቸውን አወረዱ። ሸማቹ ሚስጥሩ ሳይገባው ቅናሽ ወዳገኘበት አዲሶቹ ነጋዴዎች ፊቱን አዞረ።ቀስ በቀስ ነባሩ ነጋዴ ከገበያ ወጣ።

የማፊያ ባህሪ ያላቸው አዲሶቹ ነጋዴዎች ሰው ሰራሽ እጥረት

በማስከሰትም ተወዳዳሪ አልነበራቸውም።በሰአታት ውስጥ የአንድ ኪሎ ጨው ዋጋ ከአንድ ብር 50 ብር የተሸጠበትን አጋጣሚ ልብ ይሏል።

ነባሩ ነጋዴ ከገበያ መውጣቱ እልህ የተጋቡት የጉራጌ ካድሬዎቹ እነ ሺሰማ ክትትል ማድረግ ይጀምራሉ። ከብዙ ጥረት በኋላ ሸፍጥ የሚሰራበትን ቦታ ይደርሱበታል። ሮማንና ወዳጆቿ ፉይል የሚሰርዙና የሚደልዙት፣ግብር የሚጨምሩትና የሚቀንሱት፣ሱቅ የሚሰጡትና የሚቀሙት አምባሳደር ፊልም ቤት የሚገኘው ካፍቴሪያና ሆቴል ነበር። ይህ በህውሀት ነባር ታጋይ ባለቤትነት የተያዘ ካፍቴሪያ የህገወጥነቱ ማእከል ነበር። ብዙዎች ይህን የማፊያ ማእከል በሚሊየነሙ ዓመት የአቶ መለስና ፕሬዝዳንት ግርማ ፎቶ ለ360 ቀናት በመስቀሉ ያስታውሱታል።

ከምርጫ 97 በኃላ የጉራጌ አብዮትን ለመቀልበስ በስብሰባ ማእከል በተጠራ የመጀመሪያው ዙር ማጠቃለያ ኮንፍረንስ ላይ ተገኝቼ ነበር። በጉባኤው የተሳተፉት ከአንድ ሺህ በላይ የጉራጌ ነጋዴዎችና ባለሀብቶች ነበሩ። ይህን ለአንድ ሳምንት የዘለቀ ጉባኤ የመራው ዶክተር ካሱ ኢላላና ሚኒስትር መኩሪያ ነበሩ። ነጋዴዎቹ በሲቃ ስለ ሮማንና ሉሌ የሚያነሱት ወንጀል ጨጓራ የሚልጥ ነበር። በተለይ የክፍለ ከተማው የገቢዎች ኤጀንሲ ሙያተኛ የሆነ የጉራጌ ተወላጅ ስራዮን ለመልቀቅ ብዙ ተሟግቻለው በማለት የገለፀው ታሪክ ዶክተር ካሱ አንገቱን አቀርቅሮ እንዲቀር አድርገውታል። ከመቀመጫው ተነስቶ የኮንፍረንሱን ተሳታፊ እንባ እየተናነቀው ይቅርታ ጠይቋል።

እንዲህ ነበር ያደረጉት፣

ሎሌና ሮማን ከቢሮአቸው ሳይወጡ ከአስር እጥፍ በላይ ግብር እንዲጥሉ ሙያተኞቹን አስገደዱ። ከስረው ለመዘጋት አፋፍ ላይ ያሉ ነጋዴዎችን ከግብር ህጉ በተቃራኒ ታክስ አስከፈሉ። በድርጊቱ የተበሳጨ አንድ ነጋዴ ራሱን በገመድ አንጠለጠለ። ተመሳሳይ ሱቅና የንግድ አይነት ያላቸውን ጉረቤት ነጋዴዎች አንዱን በዜሮ ፣ሌላውን በአስር ሺዎች ታክስ እንዲከፍል አድርገዋል። ይህ በዘር ላይ የተመሰረተ እርምጃ ቀድሞ በነጋዴዎች ዘንድ የነበረን መደጋገፍ እንዲቀር በማድረግ አርስ በራስ በጥላቻ እንዲተያዩ አድርጓል። በዚህ ምክንያት መሳሪያ የተማዘዙ፣ በገጀራ ተፈነካከተው ወህኒ የወረዱ ነጋዴዎች ይገኙበታል።

ሮማን የመርካቶ ንግስናዋን ምርጫ 97 አደናቀፈው። የፈፀመቸውን ወንጀል እንድትናዘዝ የበረከት ጉንጭ አልፉ ግምገማ ላይ ትገኝ የሚል ጥያቄ ቀርቦ ነበር። ሁኔታው ያላማረው አርከበ "ሮማን ከድርጅት አባልነት ራሷን ካገለለች ስድስት ወር አልፏታል። ማመልከቻዋ የህውሀት አዲሳባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ይገኛል።" የሚል መከራከሪያ አቅርቦ እንዳትመጣ አደረገ። ይህም ሆኖ የጡት አባቷ የሆነውን አርከበ እቁባይ አጅባ ወደ ስራና ከተማ ልማት ከመሄድ አንዳቸም ምድራዊ ሀይል አላገዳትም። ባላንጣዋ ሉሌ ደግሞ ወደ ኢህአዴግ ቢሮ የአዲሳባ ክንፍ በመመደብ ወደ ህላዌ ነብሴ መጣ።

ሉሌና ሮማን ሲሰሩ የከረሙት ይህንን ነው። የስምአን ልጅ በረከት

በመጽሐፉ ገጽ 310 ላይ ደግሞ፣

" ...የኢህአዴግ አመራርና ኮትኩቶ ያሳደጋቸው ታጋዮች፣እጅግ ወሳኝ የሆነው ጥንካሬያቸው ለህዝብ የተለየ ፍቅር፣ አከብሮትና የፀና ወገናዊነት የነበራቸውና ያላቸው መሆኑ ነው። አመራሩና ታጋዮቹ ህዝብ ሲበደል አይወዱም። በህዝብ ላይ የሚፈጸም ግፍና በደል አምርረው ይጠላሉ ። የሚጠሉትን ግፍና በደል በፅናት ይታገላሉም።ከባድ መስዋዕት ቢጠይቅም ባይጠይቅም። የኢህአዴግ አመራርና በትግል እሳት ተፈትነው ያለፉት የድርጅቱ አባላት ህዝብ እንዳይጐዳ፣ይልቁንም መብቱና ጥቅሙ ተከብሮለት ይኖር ዘንድ፣ ብዙዎች ሊከፍሉት ቀርቶ ሊያስቡትም የማይቻላቸውን መስዋዕት እድሜ ልካቸውን እየከፈሉ የዘለቁት፣ በእርግጥም ለህዝብ ሲሉ የመሰየፍን ፅዋ ሊጐነጩ የተዘጋጁ በመሆናቸው ነው።" ይላል።

ለዚህ የበረከት መልእክት ቀለል ያሉ ጥያቄዎች እናንሳ። እንዲህ በማለት፣

"አቶ በረከት ስለእነማን አያወራህ ነው?"

...አዲሳባ ከንቲባ እንዲሆን ፊልገህ የነበረውን ሚኒስትር መላኩ ፉንታ፣ ...በማሰሮ ውስጥ ገንዘብ ሲያከማች የነበረውን የጉምሩክ ሹሙን ገ/ዋህድ፣ ...የኤርትራውያን ንብረት በጠራራ ፀሀይ የዘረፈውን የደህንነት ሀላፊ ወልደስላሴን ...

"አቶ በረከት ስለእነማን አያወራህ ነው?"

...በሚሊዮን ብር ምልጃ ልጆቻቸውን ቻይና ያስተማሩት ሽማግሌው ስብሀት ነጋና አርከበ እቁባይ፣ ...የስብሀት ነጋ የአጐት ልጅ የሆነውና በሚሊዮን ዶላር ገንዘብ ይዞ የተሰወረውን ሚኒስትር ጌታቸው በላይ፣ ...አቃቂ ላይ ሹፌሩን መህንዲስ አድርጐ መሬት የሸነሸነውና የሁለት ቪላ ባለቤቱ አባዱላ፣ ...ምላጫ ሳሙና እያልክ የምትጠራቸው አምባሳደር ግርማ ብሩና ሚኒስትር መኩሪያ፣ ...አቶ ሽጉጤን በስተርጅና የቡና ልማት ስራ አስኪያጅ ስላደረገውና ከአፈጉባኤዋ ጋር የጀመረው ድብብቆሽ ጨዋታ በመጋለጡ ወደ ሚኒስትርነት የተሸጋገረው ሽፈራው ሽጉጤ፣ ...የጨለማው ዘመን ንጉስ አሊ አብዶን፣ ...

አቶ በረከት ስለእነማን አያወራህ ነው?"

...ቪላቸውን በዶላር አከራይተው ግብር ሳይከፍሉ ቀበሌዎች ያጋለጧቸውን አምባሳደር ተሾመ ቶጋንና ሌሎች አምባሳደሮች፣... የደህ አጥንት የጋጠውን አምባሳደር ቶፊቅ አብድላሂን... ከአውሮፓ የሚያስንቁ ህንፃዎችን ገንብተው በምንዛሪ የሚያከራዩ ጀነራሎቻችን፣ ዘመኑ ካፒታሊዝም ስለሆነ በማንኛውም መንገድ ሀብት ማካበት የስፈልጋል ብሎ የመከረህን ገ/ተንሳይን፣... አዲሳባን ወዳልደረቀ አፅም የቀየራት ዶክተር አብርሀምን፣ ... በዘረኝነት በሽታ የሚሰቃየውንና እግሩን ጠረጴዛ ላይ አድርጐ ህዝብ የሚያናግረውን ሀይሌ

ፍስሀን፣... የህዝብ ትምህርት ቤት የሸጠውን ምትኩ፣ መውጫና ከበደ ብሩ፣ ... የማፍያ ቡድን ያደራጀችውን ሮማን ተስፉይን ... አዲሳባ ከሚገኙት አስር ሺህ አባላቶቹ 80% የአንበሳ ባንክ አክሲዮንና ሼር ባለቤቶች ያደረገውን ህውሀት??

***

ነጋና አባተ

አርጌው አውሮፕላን ማረፊያ አገልግሎት መስጠት ካቆመ ቆይቷል። ይህ ከጦር ሀይሎች እስከ ሳርቤትና ልደታ የተለጠጠ ሜዳ ተጉዘውበት የማያልቅ ባህር ነው። ኢህአዴግ አዲሳባን ከተቆጣጠረ በኋላ አገልግሎት መስጠት በማቋረጡ እንደ ጥቁር ዘንዶ የተጥመዘመዘው የኢሊኮፍተር ማረፊያ የተቦዳደፈና ከቁመት በላይ በሆነ ሰንበሌጥ የተሸፈነ ሆኗል። ወደ እባብና የዱር አይጥ ማራቢያነት ተቀይሯል።

ይህ ደረቱን ገልብጦ ያለስራ የተቀመጠ ቦታ ለብዙ ነዋሪዎች ጥያቄ የፈጠረ ነበር። እርግጥ በሳር ቤት በኩል ከፊሉ ተቆርሶ ለሼህ አልአሙዲ ተሰጥቷል። ሼሁ መለስተኛ ህንፃዎችንና "መቻሬ ሜዳ" በመባል የተሰየመ የእግር ኳስ መጫወቻ ስታዲየም ገንብተውበታል።

በርግጥ ይህ ቦታ የክፉ ቀን በመጣ ቁጥር በጥቅም ላይ በመዋሉ የኢህአዴግ ባለውለታ ነው። በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ወቅት ሰንቅና ትጥቅ የሚያመላልሱ ኢሊኮፍተሮች አጨናንቀውት ነበር። የህውሀት ከፍፍል ወቅት አቶ መለስ ወደ መቀሌ የተመላለሰበት መነሻ ከዚህ ቦታ ነበር። በምርጫ 97 ማግስት የሆነውም ተመሳሳይ ነበር...

እንዲህ ነበር የሆነው።

በምርጫ 97 ማግስት በዋለ አንዲት ጠዋት ሶስት ኢሊኮፕተሮች ተከታትለው በአሮጌው አውሮፕላን ማረፊያ ሜዳ ላይ አረፉ። የአካባቢው ነዋሪ የኢትዮ ኤርትራ ጦርነት የተቀሰቀሰ መስሎት በሀዘን ተዋጠ። እኛ ካድሬዎች ደግሞ አቶ መለስ ያቋቋመውን ሰባት ማዘዣ ጣቢያ ለማጠናከር የመደባቸው ተጨማሪ ወታደራዊ መኮንኖች እንደሆኑ ጠረጠርን። እኛም ሆነ ነዋሪው የገመትነው ልክ አልነበረም...

ከኢሊኮፕተሯ ውስጥ የወጡት ስምንት የኮረኔል ማእረግ የለበሱ ወታደሮች ነበሩ። መኮንኖቹ በቀጥታ ፊትለፊታቸው ወደሚገኘው የኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ሄዱ። የከንቲባ አባተ ስጦታው ቢሮ። መሬት እንደሚሰጥ መረጃ ደርሶአቸው ከጦር ግንባር እንደመጡ ነገሩት። እያንዳንዳቸው የማህበር ስም የተሰጣቸው የአስራ ሁለት መኮንኖች ስም ዝርዝርና ፊርማ የያዘ ወረቀት አስረከቡት... "ዘመቻ ፀሀይ ግባት የቤት ማህበር"፣ "ሀየሎም አርአያ የቤት ማህበር"፣ "ዛላአንበሳ ቤት ማህበር"፣...

አባተ ደነገጠ። የተሰጠው መመሪያ ስለሌለ እንደማይፈርም ተናገረ። መንግስታዊ አሰራርን አስረድቶ ሳይጨርስ ግንባሩ ላይ ከተደቀነ ሽጉጥ ጋር ተጋፈጠ። ማስፈራሪያዎች ተዥጎደጎዱ፦ "የቅንጅት ተላላኪ መሆንህን ደርሰንበታል"፣ "ኢህአዴግ እንዲሸነፍ ያደረጋችሁት እንዳንተ ያሉ ሰርገው ገቦች ናቸው"፣ "እዚሁ ደፍተንህ እንሄዳለን "...

በዚህ አሰጨናቂ ሰአት ነበር ምክትል ከንቲባው ነጋ በርሔ የአባተን ቢሮ በርግዶ የገባው። አባተ ላይ ከተነጣጠረው ሽጉጥ አንዱ ወደ እሱ ዞረ። ነጋ የዶሮ ላባ የተደቀነበት እንኳን አልመሰለውም። መሳደብ ጀመረ፣

"ነፍጥ ከእናንተ በፊት አንግበን ተራራ ደርምሰናል። የምታስፈራሩትን ሂዱና ሌላ ቦታ አስፈራሩ" ይላቸዋል። ተደናግጠው መሳሪያዎች ወደ አፎታቸው ይመልሳሉ። ሙልጭ አድርጎ ከሰደባቸው በኃላ ከንቲባውን ይቅርታ እንዲጠይቁ ያዛቸዋል። በተባሉት መሰረት ወታደራዊ ይቅርታ ጠየቁ። ነጋ የመጨረሻውን ተግሳጽ ተናገረ፣

"ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ጥያቄያችሁን ብታቀርቡ ኖሮ አባተ እንኳን ቤተሰባችሁን ጥላችሁ ግንባራችሁን ለጥይት ለምትሰጡት ቀርቶ ለሌላውም አይጨክንም። ያውም ከቀናት በኋላ ጠላት ተረክቦ ለሚዘርፉት አዲሳባ ! ።" ልብ የሚነካ ንግግር ነበር።

አባተ መሬቱን ፈቀደ።

መኮንኖቹ የተሰጣቸውን መሬት እንኳን ማየት አልፈለጉም። እያንዳንዳቸው ከግማሽ ሚሊዮን ብር አየር ባየር ተቀበሉ። እነ ፀሀይ ግባት፣ እነ ዛላንበሳና ሀየሎም አርአያ ንፉሰ ወሰዳቸው። ኮረኔሎቹ ለሊቱን ሙሉ ከበረሀ ትግል ጓዳቸው ነጋ በርሔ ጋር የጥንቱን እያወጉና እየጨፈሩ አሳለፉ። ወፍ ሳይንጫጫ አመስግነውት ወደ ግንባር ተመለሱ።

ነጋ ተልእኮውን በማጠናቀቁ በብርሀን ፍጥነት መቀሌ ተላከ። የህውሀት ማእከላዊ ኮሚቴና የትግራይ ክልል ካቢኔ ውስጥ ተቀላቀለ። በረከት በመራው ጉንጭ አልፋ ግምገማ በአስቸኳይ እንዲመጣ ቢጠየቅ፣

"በረከትን እየቀለድክ አትኑር በሉት። በድሮ በሬ እያረሰ መሆኑን ንገሩት! " በማለት ቀረ። ዘመን አለፈና አዲሱ ለገሰን ለማገዝ ኢህአዴግ ቢሮ የስልጠና ማእከል በምክትል ሚኒስትርነት ማእረግ ተመደበ።

እነሆ! የበረከት ግምገማ እንዲህ ነበር።

የአዲሳባ ልጆች የሆኑ ፀጋዬ ፈለቀና ፀጋ የሚባሉ የላፍቶና የቦሌ ካድሬዎች አንድ መሬት ወሰዳችኃል ተብለው ከካድሬነትና የመንግስት ስራ ተባረዋል። በተቃራኒው ቀራንዮ ላይ የተንጣለለ የመንግስት ቤት፣ ቦሌ ላይ መሬት የወሰደው ነጋ በርሔ በሳይናሳዊ መተካካት ማእቀፍ ውስጥ ተካቶ አዲሱ ለገሰን ለመተካት እየተዘጋጀ ነው። ህውሀት የተነጠቀውን የፓለቲካ ክፍልና ኢህአዴግ ቢሮን ለማስመለስ ተስፉ ተጥሎበታል። የህውሀት ሁለተኛው ትውልድ ግንባር ቀደም መሪ ተደርጎ ተወስዷል።

ምስኪኑ አባተ ድራማውን የተገነዘበው ውሎ ካደረ በኃላ ነበር። በፀፀትም ግለሂስ አደረገ። በምደባ ወቅት የአዲሳባ ኢህአዴግ ቢሮ አባል እንዲሆን ተደረገ። በአሁን ሰአት በስራ ትጋቱ የአዲሳባ ምክትል ከንቲባ ሆኗል...በግል እውቀቴ ንፅህናውንና ታታሪነቱን መመስከር አችላለሁ። ይገባልም። ምንም እንኳን ከእንክርዳድ ከምር ውስጥ የተወሸቀ ስንዴ ቢሆንም።

***

ዶክተር አብርሀምና ሀ/ስላሴ

ከምርጫ 97 በኃላ የነበረው ጊዜ ለከንቲባ ጽ/ቤት ሀላፊው ዶክተር አብርሀም ምቹ አጋጣሚ ነበር። አዲሳባን ለማጥፋት ቆርጦ የተነሳው አርከበ ብዙዎቹ የፈፀማቸው ወንጀሎች በዶክተር አብርሀም አማካኝነት ነበር።

እንደሚታወቀው ከአሊ አብዶ ዘመን ጀምሮ የአዲሳባ አስተዳደር በተለያዩ ቦታዎች ዘመናዊ አፓርትመንቶችንና ቁጠባ ቤቶችን አስገንብቷል... በፊረንሳይ፣ ቃሊቲ፣ ሲኤምሲና አቃቂ። አነዚህ ቤቶች በተለያየ ጊዜ ለጨረታ ቀርበው መነሻ ዋጋቸው ከፍተኛ በመሆኑ ለብዙ አመታት ሳይሸጡ ቆይተው ነበር።

በምርጫ 97 ማግስት እነዚህን ቤቶች የማጥፋት ሀላፊነት ለዶክተር አብርሀም፣ ለአርከበ ጠባቂዎችና ሹፌሮች ተሰጠ። ለዓመታት የጨረታ መነሻ ዋጋው 150 ሺህ ብር የነበረ ቤት በ50 ሺህ ብር አሻገሩት። በአንድ ሳምንት ውስጥ ከ200 ቤቶች በላይ ሸጠው ከሁለት ሚሊዮን ብር በላይ የህዝብ ገንዘብ ወደ ኪሳቸው አስገቡ።

ቀጥሎ ዶክተር አብርሀም የቦሌ ክንቲባ የሆነውን ሀ/ ስላሴ እንዲያግዝ ተመደበ። እስቲ ቦሌ ላይ የተደረገውን ጆሮአችንን ደፍነን እናንብብ፦

የቦሌን የመሬት ዝርፊያ የመሩት ሶስት የህወሀት ካድሬዎች ናቸው፦ የከንቲባ ጽ/ቤት ሀላፊው ዶክተር አብርሀም፣ የቦሌ ክንቲባው ሀ/ስላሴና ትምህርት ቢሮን ያገላበጠው ገ/ተንሳይ። ሶስቱ ጓዶች በመጀመሪያ ያደረጉት በፊዴራል ተቋማትና አዲሳባ ተመድበው ለሚሰሩ ካድሬዎችና ባለስልጣናት መሬት መስጠት ነበር። የሀገሪቱ ደህንነት፣ ሚኒስትሮች፣ የፊዴራል ፓሊስ፣ ኢህአዴግ ቢሮ፣ አጋዚ ክፍለ ጦር፣ የመከላከያ ጀነራሎች፣ የትግል ዘመናቸው ከ1978 በፊት የነበሩና ከኮረኔል ማዕረግ በላይ የሆኑ ወታደሮች፣ የክልል ካቢኔ አባላት፣ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ኤፈርት፣ ዋልታ፣ ሬዲዮ ፉና፣ የአዲሳባና ከፍለከተማ ካድሬዎችና ባለስልጣናት ሙሉ ለሙሉ በሚባል መልኩ መሬት የወሰዱት በዚህ ክፍለ ከተማ ነው።

ሶስቱ ካድሬዎች ወሳኝ የሆኑ አካላትን አፍ የማዘጋት ስራ በዚህ መልኩ ካከናወኑ በኃላ ፊታቸውን ወደራሳቸው አዞሩ። ዶክተር አብርሀምና ሀ/ስላሴ

ከመከላከያ ሚኒስቴር ፉይል ውስጥ የትግል ዘመናቸው ከ1978 በፊት የነበሩት ባለማእረገኞች ዝርዝር በማስመጣት አስራ ሁለት ሰዎች የያዘ ሁለት ማህበር ፈጠሩ። መሬቱን ከወሰዱ በኃላ በዛው ሳምንት ስም አዘዋውረው ሸጡ። ገ/ተንሳይ የመጀመሪያ ልጁን አስማራ። ይህ የአባቱ ልጅ በህይወት የሌሉ ሰዎችን ጨምሮ አንድ ማህበር መስርቶ የመሬት መቀራመቱን ጮራ ተቀላቀለ። በጥሩ ዋጋ አሻግሮት የሚሊኒየሮች ጮራ ተሰለፈ።

በጉንጭ አልፉው የበረከት አውጫጭኝ ይህ ሀቅ በዝርዝር ቀረበ። በግምገማው ላይ ዶክተር አብርሀም እንዲመጣ ግፊት ቢደረግም አርከበ ለአስቸኳይ ስራ ወደ ክልል ሄዷል በሚል እንዳይገኝ አደረገ።

አቶ በረከት በመጽሐፉ ላይ፣ "ስልጣንን ለህዝብ ጥቅም እንጂ ለራስ ጥቅም ማካበቻ አላደረግንም" በሚለው ስሌት መሰረት ዶክተር አብርሀም አርከበን አጅቦ ወደ ስራና ከተማ ልማት ነጎደ። ቀጥሎም የዘመናዊ አመራር መተካካት ውስጥ የቀጣዩ ጉዞ መሀንዲስ በሚለው እንዲካተት ተደርጎ የኢኮኖሚና ፉይናንስ ምክትል ሚኒስትር ሆነ። በሚቀጥለው የኢህአዴግ ዘመን ሶፊያን አህመድ ጠቅላይ ሚኒስትር አሊያም አምባሳደር ሲሆን በሙሉ ሚኒስትርነት ዶክተር አብርሀምን እናገኛለን። ኢኮኖሚውም በህውሀት ሁለተኛ ትውልድ ቁጥጥር ስር ይውላል። ከፊት መስመር ገለል ያለው አርከበ ከኋላና ከጮን ሆኖ የመደገፍ ስራ እንደሚሰራ ይጠበቃል።

የቦሌ ከንቲባው ሀ/ ስላሴም ቢሆን በጉንጭ አልፉው ግምገማ አልተገኘም። አርከበ አስቀድሞ አርቆታል። የትግራይ አንዲት ዞባ አስተዳዳሪ በማድረግ። የቀረው ገ/ ተንሳይ ነው። ገሬ ደግሞ የዘመነ ካፒታሊዝም ምክሩንና ቀልዱን አልጨረሰም። የህውሀት የምንግዜም ባላንጣ ተደርገው የተፈረጁት የአዲስ ከተማ ከንቲባ ሉልሰገድ እና የቦሌ ምክትል ከንቲባ ሊሻን እየተቀባበሉ ገሬን አስጨነቁት።

መጀመሪያ የጠየቀው ሊሻን ነበር፣

"ገ/ተንሳይ ልጅህ በወሰደው መሬት ተጠያቂ ነህ!"

ሉልሰገድ ቀጠለ፣

"ገበረተንሳይ በአንድ ሳምንት ውስጥ ተወርውረህ የሚሊየነሮች ጮራ ተቀላቀልክ።"

ገሬ መልስ ሰጡ፦

"ሉልሰገድም ሆነ ሊሻን የህውሀት ጠላት እንደሆናችሁ ፀሀይ የሞቀው ነው።የህውሀት የበላይነት አለ ብላችሁ ስታቀነቅኑ ነበር። ዳር ድንበራችን ቀይ ባህር ነው። ቅንጅት አዲሳባን መረከብ አለበት ብላችሁ ስትከራከሩ ነበር።"

በረከት ጣልቃ ገቡና፣ "ገ/ተንሳይ ያልበላህን አትከክ! የተጠየቅከውን ብቻ መልስ።"

ገሬ አሳማኝ መከራከሪያ አቀረበ፣

"እነ ተወልደና ስዬ የድርጅታችንን ሊቀመንበር ለማባረር ስለ ወንድሙ ኒቆዲሞስ ዜናዊ ጠይቀውት ነበር። አሱም ኒቆዲሞስ ከ18 አመት በላይ ስለሆነ እና በእኔ ቁጥጥር ስር አይደለም፣ የፈለጋችሁትን ልታደርጉት ትችላላችሁ

አላቸው። እኔም ከዚህ ውጭ መልስ የለኝም።" ብሎ ወደ ኋላ በመሄድ ታሪክ አጣቅሶ ተናገረ። በአቶ መለስ ዙሪያ ያልተጠናውን ገፅ ገላለጠ።

ግምገማው ገሬን ወደ ስራና ከተማ ልማት ከመሄድ አላገደውም። ልጁንም የጠየቀ የለም። በተቃራኒው የክፍለ ከተማው ምክትል ከንቲባና ነባር የብአዴን ካድሬ ሊሻን "ሁለት መሬት ወስጃለሁ፣ አንዱን ሸጬዋለሁ የተቀረውን ለመመለስ ፍቃደኛ ነኝ "ቢልም ከድርጅትና መንግስት ስራ ከመባረር አላመለጠም።

***

ግርማጺዮንና ሚደቅሳ

የሁሉ ደነቀውና ሚደቅሳ ጓደኛሞች ናቸው። የሁሉ ከባህርዳር የመጣ የብአዴን ጓድ ሲሆን ሚደቅሳ ደግሞ አባዱላ ከአርሲ (አርሴናል) የላከው ነው። ሁለቱ ካድሬዎች የካ ክፍለ ከተማ በመመደባቸው ምክንያት ከካድሬነት ያለፈ ጥብቅ ቁርኝት ፈጥረዋል። ብዙ ሚስጥሮች አብረው ሰርተዋል... ብአዴኑ የሁሉና ቁመተ ሎጋው ሚደቅሳ...

ከእለታት በአንዱ ቀን በክፍለከተማቸው እየተካሄደ ያለ ወንጀል ጥቆማ ይደርሳቸዋል... ሁነኛ ሰዎች አሰማርተው መከታተል ይጀምራሉ። በአጭር ጊዜ ውስጥ መረጃው እጃቸው ይገባል። የእነሱ ፍላጐት ከወንጀሉ በስተጀርባ ያሉትን ማወቅና በቁጥጥር ስር ማዋል ነበር።

ታሪኩ እንዲህ ነበር።

በምርጫ 97 ማግስት አራሷን "ገነት" ብላ የምትጠራ ግለሰብ እንደ ድሮ ባላባት ባዶ መሬት እየመተረች እየቸበቸበች እንደሆነ መረጃ ይደርሳቸዋል። ከብዙ ጥረት በኋላ ሞባይል ስልኳ እጃቸው ላይ ይገባል። እናም ይደውሉና አራት ቪላ ቤቶች ለመስራት የሚያስችል መሬት እንደሚፈልጉ ይነግሯታል። እሷም አስተዳደሩ ባስቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት የመገንባት አቅም ካላቸው የባንክ ተቀማጭ ማየት እንደምትፈልግ፣ በካሬ ሜትር መንግስት ከሚሸጥበት ሩብ ዋጋ ቅናሽ እጅ በእጅ እንደምትሸጥላቸው ትገልፃለች። ይስማማሉ። እናም ቀጠሮ ይይዛሉ።

በወቅቱ አዲሳባ በሰባት ማዘጋጃ ጣቢያ የተከፈለች ሲሆን ያንን ጣቢያ የሚመራው የክፍለ ከተማው ከንቲባ የነበረው ግርማጺዮን ነበር። ግርማጺዮን በህውሀት ከፍፍል ወቅት አቶ መለስን የታደገ ሲሆን፣ አቶ መለስ "የህውሀት የቁርጥ ቀን ልጅ!" እያለ ከሚያሞካሻቸው ታጋዮች አንዱ ነው።

(የአቶ መለሰን ሞት ተከትሎ ህውሀት በለቀቀው ሚስጥራዊ ቪዲዮ ላይ እነ ተወልደ መድረክ ረግጠው ሲወጡ "በሰጋ ሰውአት ይዘናችኋል አትውጡ!" እያለ ሲጮሁ ከነበሩት አንዱ እሱ ነበር። የድሮዎቹ ዝሆኖች ከወጡ በኋላ

እያለቀሰ የተናገረው ንግግር የእነ ተወልደን ህውሀታዊ ሞት እንዳፋጠነ ይታመናል።

አቶ መለስ ግርማጺዮንና የአቅም ግንባታ ቢሮ ሀላፊው ተክለብርሀን ወደ አዲሳባ ያመጣው አርከበን እንዲቆጣጠሩት በማሰብ ነበር። ሁለቱም ካድሬዎች ከአርከበ ጋር ተሰማምተው አያውቁም። ተክለብርሀን ጊዜና ቦታ ሳይመርጥ አርከበን ይሞልጨዋል። ግርማጺዮን በበኩሉ በውስጠ ድርጅት ስብሰባ ከልታይ ባይነት አልወጣህም በማለት ደጋግሞ ዘልፎታል።)

ከዚህ ነባራዊ ሀቅ በመነሳት እነ የሁሉና ሚደቅሳ በእንጥልጥል ላይ ያለውን ክትትል ለግርማጺዮን ያጫውቱታል። እንደሚያግዛቸውም ተስፉ ያደርጓሉ። ከሰአታት በኃላ ቢሮው ጠርቶ ሌላ አካል እየተከታተለው ስለሆነ በአስቸኳይ እንድታቋርጡ ታዛቸኋል ይላቸዋል። የተባሉትን ያደርጋሉ።

እነሆ! በረከት በሚመራው ጉንጭ አልፉ ግምገማ የአርከበ ሂስና ግለሂስ እየተሰማ ነው። ሎግላጋው ሚደቅሳ አርከበ እስኪጨርስ መታገስ አቅቶታል። ይህን የተመለከተው በረከት ቅድሚያ ይሰጠዋል። ሚደቅሳ ቋጥሮ የከረማትንና በእንጭጩ የተቀጨውን የክትትል ታሪክ ያነሳል።

በጥያቄው የተደናገጠው አርከበ መጀመሪያ፣

"አንድ ሰው በሊዝ የወሰደውን መሬት መሸጥ ይችላል። ወይዘሪት ገነትም ያደረገችው ይህንኑ ነው። የሰራችው ወንጀል የለም።" የሚል አስተያየት ይሰጣል።

የእሱን ምላሽ ተከትሎ ከግራ ቀኝ "ባዶ መሬት መሸጥ መለወጥ አይቻልም! ኢ - ህገ መንግስታዊ ነው። ህገ መንግስቱን በመጣስ ያስጠይቃል። " በሚሉ አስተያየቶች ተዋከበ። መልሱ እንደማያዋጣው የተገነዘበው አርከበ አክሮባት በመስራት፣

"እኔ አጠቃላይ በሆነ ነገር አስተያየት ሰጠሁ እንጂ ሚደቅሳ ስለሚያነሳው ጉዳይ የማውቀው ነገር የለም።" ብሎ ይሸመጥጣል።

የታሪኩ ባለቤት ግርማጺዮን ደግሞ በጉንጭ አልፉው ግምገማ እንዳይሳተፍ አስቀድሞ የአራት ታዳጊ ክልሎች ፕሬዝዳንቶችን እንዲቆጣጠር በመሾሙ ወደ ቤኔሻንጉል ክልል ሄዷል። እናም የማጣራቱ ስራ በይደር እንዲቆይ ተወሰነ... ሳይጣራ ቀረ። ግርማጺዮን ከሄደበት ሲመለስ የጠየቀው የለም። ይልቁንስ በህውሀት ሁለተኛ ትውልድ ታቅፎ ታዳጊ ክልሎችን ይበልጥ እንዲያሳድግ አደራ ተሰጠው።

ሚደቅሳ የዱከም ከንቲባ ሆነ። በአመቱ በምግብ መበረዝ በድንገት ህይወቱ አለፈ። ጓደኛው የሁሉ ደነቀው የኢትዮጵያ መዳኒትና ቁጥጥር ስራ አስኪያጅ ሆነ።

በሚደቅሳ አሟሟት ዙሪያ በርካታ ሀሜቶች ይራገባሉ። አባዱላ አቃቂ

ላይ ሹፌሮቹንና ጠባቂዎቹን መህንዲስ አስመስሎ መሬት ያሸነሸነው በወቅቱ ከክፍለከተማው ከንቲባ ከነበረው ተክለጻዲቅ ሬባ ጋር በመሰማጠር እንደሆነ ያጋለጠው እሱ ነበር። ተክለጻዲቅ ላደረገው ውለታ በቲቲአይ ሰርተፍኬት የኦሮሚያ ስራና ከተማ ልማት ቢሮ ሀላፊ መደረጉን እንደ እማኝ አቅርቧል። ርግጥም የመሬት አስተዳደር ግንዛቤ የሚጠይቅ ቦታ በምርጫው ማግስት አንጠልጥሎ በመውሰድ የካቢኔ አባል ማድረግ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል?

በነገራችን ላይ የአባዱላ ጠባቂዎችና ሹፌሮች መህንዲስ ሆነው አቃቂ ላይ መሬት እንደሸነሸኑ ከ60 በላይ የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለከተማ ካድሬዎች በግምገማ ላይ አጋልጠዋል። የግምገማው ቃለ ጉባኤ በክፍለከተማው ድርጅት ጽ/ቤት ይገኛል። በመከራ ውስጥ የሚገኘው ድፍን የአቃቂ ህዝብም ይህን ያውቃል።

አባዱላ ሚደቅሳ ያነሳበትን በመስማቱ ከማናቸውም ምደባ ውጪ አደረገው። ኢህአዴግ ቢሮ ቅሬታ በማቅረቡ የየካ ክፍለከተማ ድርጅት ጉዳይ ሀላፊ እንዲሆን ተደረገ። ሁኔታው የማያዛልቅ እንደሆነ ሲገነዘብ አባዱላ ጋር ሽማግሌ በመላክ ይቅርታ ጠየቀ። ይህን ተከትሎ የዱከም ከንቲባ አደረገው።

ወቅቶች አለፉና አቶ መለስ የባለስልጣናትን የሌብነት ደረጃ የሚያጠና ቡድን አቋቋመ። የቡድኑ ሰብሳቢ ሐይለማርያም ደሳለኝ እንዲሆን አደረገ። አጥኚ ቡድኑ መረጃ ለማሰባሰብ ከያዛቸው ዝርዝሮች ውስጥ ሚደቅሳ በቅድሚያ ተመረጠ። ስለ ወይዘሪት ገነት፣ ከግርማጺዮን ጋር ስለነበረው ቃለ ምልልስ፣ የአባዱላ ሹፌሮችና የተክለጻዲቅ ምደባ ማብራሪያ እንዲሰጥ።

ይህ መረጃ እስከዛሬም ግልፅ ባልሆነ ሁኔታ እነ አርከበና አባዱላ ጆሮ ደረሰ። በዛ ሳምንት ውስጥ በዋለች አንዲት ቅዳሜ ሚደቅሳ ሆቴል በመሄድ ምሳውን በላ። ማታውኑ በምግብ መመረዝ ታሞ ጦርሀይሎች በድንገተኛ ገባ። ቁመቱ ሎግላጋው ሚደቅሳ ሞተ።

በመቃብሩ ላይ ከተገኘነው ካድሬዎች መጽናናት ያቃተው የልብ ጓደኛው የሁሉ ደነቀ ነበር። ከእኔ ጋር የቅርብ ግንኙነት ስለነበረን ላጽናናው አጠገቡ ሄድኩኝ። በድሬደዋ የዩንቨርስቲ ተማሪዎችን በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ለማጥመቅ ሁለት ወር አብረን ሰንበተናል። በምርጫው ማግስት የየካን መሬት ሸንሽና ስለቸበቸበችው ወይዘሪት ገነት ለእኔና በወቅቱ ለነበርነው ሁለት ከፍተኛ ካድሬዎች ለሊቱን ሙሉ አጫውቶናል። እነዚህ ካድሬዎች በፓለቲካው መድረክ አሁንም ይገኛሉ። የሁሉ ባላንጣዎቹ ግርማጺዮንና አርከበ በመከራ ጊዜ እንዴት እንደተጣመሩ ሲነግረን አስደማሚ ነበር።

እናም! በጓደኛው መቃብር ላይ ላጽናናው አጠገቡ ሄድኩኝ። ወደ ጆሮዬ ጠጋ ብሎ፣ "ጓደኛዬ ሚደቅሳ ሳያውቅበት በምላሱ ጠፉ" አለኝ።

ሚደቅሳ ቢሞትም በውስጡ ያመቃቸው ሚስጥሮች በየሁሉ ደነቀ እጅ ይገኛሉ። የሁሉም ቢሆን ያፈሰሰው እንባ የሚደርቀው የንጹህ ደም አፍሰዋል ብሎ የሚያስባቸውን ሲፋረድ ብቻ ነው።

***

"ህላዌ ነብሴ!"

ህላዌ ዮሴፍ አንድ መሬት በራሱ ወስዷል። ሚስቱ የመከላከያ ሰራተኛ ስለሆነች በጅምላ መሬት ሲታደል ደርሷታል። በግለ ሂሱ ላይ አርከበ ጉድ እንደሰራው ጨምሮ ገልጿል። አንዱን መሬት ለመመለስ ፎርም ከሞሉት ካድሬዎች የመጀመሪያው እሱ ነበር። እንዲያም ሆኖ የበረከት ዘለፋና ስድብ ከማንም ካድሬ በላይ ጠንክሮ የነበረው ህላዌ ላይ ነበር። ዘወትር "ህላዌ ነብሴ!" እያለ የሚጠራው በረከት ለምን እንደጨከነበትና መልጭ አድርጐ ለመስደብ የተነሳሳበት ምክንያት ለብዙዎቻችን ግልፅ ነበር። ህላዌም ይህን በመገንዘብ ይመስላል ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ። እኔንና አጠገቤ ተቀምጣ የነበረችው አሽዛ የምትባል የህውሀት ነባር ታጋይ አጅበነው። አልቅሶ አስለቀሰን።

ህላዌ ስሜቱ አፍንጫው ስር ብትሆንም ቀላል ሰው ነው። ራሱን ማጨናነቅ አይወድም። ቀሪ ህይወቱን ዘና ብሎ ማሳለፍ ብቻ የሚፈልግ ነው። ቢያንስ በወር አንዲት ቅዳሜ እኔን፣ፀጋዬንና ካሚልን እቤቱ ምሳ ይጋብዘናል። እስከ ምሽት የቆጥ የባጡን እናወራለን። ሚስቱ በልተን የማንጠግብ የሚመስላት ደግ ናት... ስሟም ደጊቱ ነው።

ህላዌን እስከማውቀው ድረስ በግለሰብ ደረጃ ይህ ነው የሚባል ንብረት የለውም። የውጭ ህክምና ወጪውን የሚሸፍንለት በበረከት ጥያቄ ሼህ አላሙዲ ነው። ልጁን አሜሪካ ለእረፍት የወሰዱለት ጓደኞቹ ናቸው። መሉ ልብስ እየገዛ የሚያመጣለት ሰለሞን ተቀባ ነው።

ህላዌ እንደ "ዋልዋ "ሁሉ የዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት አስረኛ ነው። ኢህአዴግ አይደለም። ሆኖም አያውቅም። የደርግን ግፍ መቅመስና አስከፊው ስርአት እንዲወገድ ግንባርን ለጥይት ሰጥቶ መታገል በራሱ ኢህአዴግ አያደርግም። ኢህአዴግነት ርእዮተ አለም ነው። አብዮታዊ ዲሞክራሲ ሀይማኖት ነው። ሲበላም፣ ሲጠጣም፣ ሲኬድም ፣ ሲተኛም የሚታሰብ። ሀይል አሰላለፍና ወገንተኝነት የሚጠይቅ፣ የህላዌ ህይወት ይህን አያሳይም። ኢህአዴግነት በዘር ማንዘር ማሰብ ይጠይቃል፣ ህላዌ ለይቶ የቆመለት ዘር የለውም። ኢህአዴግነት ጨቋኝና ተጨቋኝ ብሔር መኖሩን አምኖ መቀበል ይጠይቃል። በዚህ ስሌት ከተሰላ ምንአልባትም ከእሱ ይልቅ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ለኢህአዴግ ቅርብ ነው፣ ዶክተር መራራ ደግሞ የቅርብ ቅርብ።

የህላዌ ውሎ ኢህአዴግ ማህበራዊ መሰረቶቼ አይደሉም ብሎ

ከሚያስባቸው ጋር ከሆነ ውሎ አድሯል። ህላዌ ውስጡ የማያምንበትን መንገድ እየተጓዘ ያለው ይህን መለየት አቅቶት ነው። ሲያዩት የተምታታበት የሚመስለው በዚህ ምክንያት ይመስላል።

ይህ ባይሆን ኖሮ እሱን የምናገኘው ሌላ ቦታ ነበር። ምንአልባትም ትላልቅ የስነ ጽሁፍ ሰዎቻችን ብለን የምንዘክራቸው ኢትዮጵያውያን ጐራ ይሰለፍ ነበር። ምንአልባትም በዘረኛ የኢህአዴግ ካድሬዎች ነቀፌታ የደረሰበት" የአፄ ቴድሮስ ሙዚቃ አዘል ተውኔት" ድርሰት የህላዌ ዮሴፍ ተብሎ ይጻፍ ነበር። እቤቱ መሳቢያ ውስጥ የቆለፋቸው የግጥም መድብሎች ከአንድ መጽሐፍ በላይ ሆነው ህዝብ ያነባቸው ነበር። (ኢህአዴግ ከበረሀ ጀምሮ ለመቀስቀሻነት የሚጠቀምባቸው "እንዳያልፉት የለም"፣ "እልፍ ሆነናል" የሚሉት መዝሙሮች ባለቤት የህላዌ ነብሴ መሆኑን ልብ ይሏል።)

ህላዌ ነብሴ ጊዜውን ማሳለፍ የሚፈልገው ከአርቲስቶች ጋር ነው። ከኢህአዴግ ካድሬዎች በተለየ ሁኔታ የተሻለ ግንኙነት ፈጥሯል። ስራቸውን ለህዝብ ከማቅረባቸው በፊት እንዲገመግም ያሳዩታል። የቀይ ስህተት ደራሲ አርቲስት ቴዎድሮስ ተሾመ ፊልሙን ከማቅረቡ በፊት ህላዌ ጋር ሲመላለስ ነበር። እነ ደግአረገና ሀመልማል አባተ "ጋሼ! ታላቅ ወንድማችን!" ብለው ሲጠሩት በተደጋጋሚ ተመልክቻለሁ።

አንዳንድ አርቲስቶች በተለያየ ጊዜ ወደ ቢሮው እየመጡ ያለባቸውን ችግር ያወያዩታል። አንድ ጊዜ የሀገር ፍቅር ስራ አስኪያጅ የነበረችው አርቲስት መንበረ ታደሰ ቢሮው መጣች። እንባዋን እየዘራች፣ "መስራት አልቻልኩም፣ አላሰራም አሉኝ። እኔ የቅንጅት ደጋፊ አልነበርኩም።" በማለት የውስጧን ብሶት ዘረገፈችለት። በሁኔታው የተበሳጨው ህላዌ ከወራት በኃላ የኢትዮጵያን ፓርላማ ቀላቀላት። ከአስፈፃሚነት ወደ ህግ አውጭነት ተመነጠቀች። ጠላቶቿን ቁልቁል አየቻቸው። አፍታም ሳትቆይ ፀጥ ያለው ሸንጐ ሳይመቻት ቀርቶ ይሆን ፣የወይዘሮ አዜብና ምንጅላቶቿ እርግጫ በዝቶባት ሀገር ጥላ ተሰደደች።

የህላዌ ነብሴ የመጨረሻ መጀመሪያ...

በረከት የቦርድ ሰብሳቢ የሆነበት የኢትዮጵያ ቴሌቭዥን መለወጥ እንዳለበት በማመኑ ህላዌን በስራ አስኪያጅነት ለመሾም አዘጋጀው። በኢህአዴግ ቢሮ የህላዌ ወደ ኢቲቪ መሄድ ብዙ ተወራ። ትልቅ ተስፋ ተጣለበት። በተባረር የሰሙ የግል ፕሬሶች መረጃውን አወጡ። እኛም የሽኝት ፕሮግራም አዘጋጅተን ለሊቱን ሙሉ አብረነው ስንጨፍር አደርን። መልካም የስራ ዘመን ተመኘንለት።

የሴጣን ጆሮ ሰማ።

እንደሚታወቀው በሚዲያው አካባቢ የበላይነቱን የተቆጣጠሩት የህውሀት ካድሬዎች ናቸው። የዜና አገልግሎት(ኢዜአ) ዋና ስራአስኪያጅ ታጋይ ሀዱሽ፣ የሬዲዮ ፉናው ታጋይ ወልዱ ይመስል፣ የዋልታው ታጋይ ብርሀነ ማእረት... እነዚህ ካድሬዎች ወደ እመቤታቸው ወ/ሮ አዜብ በመሄድ "ብአዴን ኢህአዴግ ቢሮን ሙሉ ለሙሉ ከተቆጣጠረ በኃላ ፊቱን ወደ ሚዲያ ተቋማት

አዙሯል" የሚል ቅሬታ አቀረቡ። ወይዘሮ አዜብ በእኔ ጣሉት ብላ ብርታት ሆነቻቸው።

ከቀናቶች በኃላ አቶ መለስ የሰጣቸው ሁለት ትላልቅ ሹመቶች በኢቲቪና ሬዲዮ ተደመጡ። የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቭዥን ዋና ስራ አስኪያጅ ዘርአይ አስግዶም... ምክትሉ ደግሞ ህላዌ ዮሴፍ... ሹመቱ የአዜብን የሁልግዜም አሸናፊነት አረጋገጠ። ከተማ ቀመሱ ህላዌ አዘነ። አንገቱን ደፉ። አንድ ሀሙስ የቀራት ነፍሱ ተበሳጨች። "ህላዌ ነብሴ!" አያለ የሚጠራው የድርጅቱ እስትራቴጂስት መሸነፉን በውስጡ አመነ።

***

ምእራፍ ሃያ አንድ

የህዝብ መድረኮች

"ኢህአዴግ ከምንም ነገር በላይ ህዝቡን ያከብራል፣ይፈራልም። ሁሌም እንደሚለው ከህዝብ ውጭ ሌላ ጌታ የለውም።"
በረከት ስምኦን (የሁለት ምርጫዎች ወግ)

የመዲናይቱ ወኪሎች

ከምርጫ 97 ግርግር ረገብ ማለት በኋላ የአዲሳባን ህዝብ መውቀት መለካት ያስችላሉ የተባሉ ውይይቶች እንዲጀመሩ ከአቶ መለስ ጋር በሚኖረን ሳምንታዊ ስብሰባ ተወሰነ። ውይይቱ ነዋሪዎች፣ ሴቶችና ወጣቶች በሚል አንዲከፉፈልና ሶስት መድረኮች እንዲሆኑ አቶ መለስ አሳሰበን።

የተወያየኮች ዋነኛ መመዘኛ በግልፅ ተመዝግበው ከሚንቀሳቀሱ የተቃዋሚ አባላት ውጪ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል የሚወክሉና ነዋሪው "ወኪሎቼ ናቸው"ብሎ ከሚያምንባቸው ጋር ብቻ እንዲሆን አቅጣጫ ተቀመጠ። ይህም ከዚህ በፊት ሲሰራበት የነበረው ሰዎችን በብሔር ማንነታቸው የመከፋፈልና ማወያየት ስራ አዲሳባ ላይ እንዲቋረጥ፣ በምትኩ በማህበራዊና እድሜ አደረጃጀታቸው ብቻ እንዲሆን ተደረገ።

ከአቶ መለስ ጋር በተሰበሰብን ወቅት የብሄር አዘል ስብሰባ ይሻላል የሚል አስተያየት በአርከበ እቁባይና በረከት ስምኦን ቀርቦ የነበረ ሲሆን ፣አቶ መለስ ንዴት በተቀላቀለበት ሁኔታ፣

"ወደድንም ጠላንም የብሔር ፓለቲካ አዲሳባ ላይ አፈር ልሶ የማይነሳበት ደረጃ ላይ ደርሷል" የሚል አስገራሚና ያልተጠበቀ አስተያየት ሰጠ።

በስብሰባው ማጠቃለያ ለማወያያ የሚሆኑ ሰነዶችን የከተማው ኢህአዴግ ከንፍ እንዲያዘጋጅ፣መድረኮቹን በበቃት ሊመሩ የሚችሉ ሚኒስትሮችንና ከፍተኛ ባለስልጣናትን የመለየት ስራ በተመሳሳይ እንድንፈጽም ተሰማምተን ስብሰባው ተፈጸመ። ውሳኔውን ተከትሎ የነዋሪዎችን ማወያያ ሀላቄ፣የወጣቶችን ፀጋዬ፣ የሴቶችን ደግሞ እኔ እንድናዘጋጅ ተስማማን። ስራው ተቀናጅቶ እንዲፈፀም በማሰብ የዞን ቋሚ ምድብተኛ ካድሬዎችን ጠርተን

አዲሱን የኢህአዴግ አቅጣጫ አረንቴሽን ሰጠን። ብዙዎቹ ካድሬዎች የብሄር ፓለቲካ በአዲሳባ በመቅረቱ ደስተኞች ሆኑ።

ህዝቡን ሊያወያዩ የሚችሉ ሚኒስትርና ባለስልጣናትን ካሚል ለይቶ እንዲያመጣ ተወሰነ። ይህን ያወቀው በረከት የለያቸውን ባለስልጣናት ስም ዝርዝር ይዞለት እንዲመጣ አደረገው። ካሚል ከበረከት ቢሮ ሲመለስ ሳቁን አልጨረሰም ነበር። ወፍራም እና ረጅም ሳቅ። ወትሮም እንደሚያረገው ቢሮው ጠርቶኝ የተሰረዘና የተደለዘ ወረቀት ወረወረልኝ።

(ካሚል ሁልጊዜም እንደ ታናሽ ወንድሙ በሰስት ያየኝ ነበር። የምግብ ሰአቴን እንኳን እየተቆጣጠረ ካልበላሁ ይቆጣኝ ነበር። እኔም ቢሆን እንደታላቅ ወንድሜ እወደዋለሁ። ዛሬም።)

እንዳያወያዩ የተሰረዙ ባለስልጣናትን ስም ዝርዝር ማንበብ ጀመርኩ። ከግርምት ውስጥ ሳልወጣ ፣

"ሽፈራው ጃርሶ ለምን ተሰረዘ?" ብዬ ጠየኩት።

"እንኳን ህዝብ ፓርላማም ተጽፎ የተሰጠውን ማንበብ አቅቶታል በማለት እንድሰርዘው ነገረኝ።"

"ካሱ ኢላላስ?"

"እየሳቀ አጐትህ ጠንካራ የህዝብ መድረክ መምራት ይቸግረዋል አለኝ።"

"ሚኒስትር ሶፊያን?"

"በህዝቡ ጥያቄ ሊደናገጥ ይችላል።"

"አርከበ እቁባይ?"

"መድረኩን ወዳልተፈለገ አቅጣጫ ይመራዋል። ከንዴት እና የበቀል ስሜት ስላልወጣ ህዝቡን ሊሳደብ ይችላል አለኝ።"

"ኮሚሽነር ወርቅነህ ገበየሁ?"

"የምንሰበስበው የአዲሳባ ህዝብ እንጂ መለዮ ለባሽ አይደለም አለኝ።"

"ስዩም መስፍን?"

"በጠዋት ሀጢያት አታናግረኝ አለ።"

***

የከተማው ኢህአዴግ ከንፍ ሰነድ ከማዘጋጀት በተጨማሪ ቀበሌዎች በምን መልኩ ምልመላ እያካሄዱ እንደሆነ ለማወቅ እንዲያስችለን ተከፋፍለን ወደ ታች ወረድን። እኔ የካ ክፍለ ከተማ የምትገኝ አንዲት ቀበሌ ሄድኩኝ። ያጋጣሚ ነገር ሆኖ የቀበሌው ምድብተኛ ካድሬ (ቢኒያም ይባላል) ጋር በመከላከያ ሚኒስቴር ውስጥ የሚገኙትን ወታደራዊ መኮንኖች አስተምረናል። ቢኒያም በባህሪው ሰዎችን ቶሎ የመፈረጅና በተለይም ኢህአዴግን ከተቀላቀለ በኃላ ድርጅቱን እንዳይጠቅ የማድረግ ባህሪ እንዳለው አውቃለሁ። ሆኖም

ከምርጫ 97 በኃላ ብዙዎቹ ካድሬዎች መሻሻል ስለታየባቸው የቢኒያምንም ተስፉ አድርጌ ነበር። ቀበሌው አዳራሽ ስደርስ አባላትን ሰብስቦ ጠብቆኛል። እያንዳንዱ አባል አስር አስር ነዋሪዎች፣ ወጣቶችና ሴቶችን ለይተው እንዲመጡ አድርጓል።

ስብሰባው ተጀመረ።

ማስታወሻ ደብተሬን ገልጬ መጻፍ ጀመርኩ። አባላት ህብረተሰቡን ይወክላሉ የሚሏቸውን መግለጽ ጀመሩ።

እንድ አባል: "ከነዋሪዎች ውስጥ አቶ አያሌው መልምያለሁ። በአካባቢያችን የሚገኘው ትልቁ አድር ሊ/መንበር ናቸው።"

ካድሬ ቢኒያም: "መአድ መልምለህ ና አልተባልክም!"

ሌላ አባል: "ከወጣቶች ያሬድ ተፈራ... ወጣቱ በፓለቲካል ሳይንስ ከአዲሳባ ዩንቨርስቲ የመጀመሪያ ዲግሪውን አግኝቷል። በአካባቢው ወጣቶች ዘንድ ከፍተኛ ተሰሚነት ያለው ሲሆን በአንድ የግል ትምህርት ቤት የስነ ዜጋ አስተማሪ ነው።"

ካድሬ ቢኒያም: "ሲቪክስ የሚያስተምር ሁሉ ጤነኛ ያደረገው ማነው? በአሁን ሰአት ቅንጅት መልምለህ መጥተህ ተሰሚነት የለውም ብትለኝ ኖሮ ይገርመኝ ነበር።"

ሌላ አባል: "ከሴቶች ወይዘሮ አረጋሽ ጋዲሳ... ሴቶች ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት እንዲደራጁ ከፍተኛ የቅስቀሳ ስራ ሰርተዋል። ኢህአዴግ በሚጠራቸው ስብሰባዎች ሁሉ አይቀሩም።"

ካድሬ ቢኒያም: "አኢሴማና ኢሰፓ እንደነበረች አታውቂምና ነው?"

ሌላ አባል: "ከነዋሪዎች ዶክተር ዋቅቶላ ... በአካባቢያችን በከፈተው ክሊኒክ ገንዘብ የሌላቸውን ነዋሪዎችን የነፃ ህክምና ይሰጣል። በጤና ዘርፍ በምናደርገው እንቅስቃሴ በየመድረኩ በመገኘት የጤና መከላከል ፓሊሲውን ያስተምራል።"

ካድሬ ቢኒያም: "ሰዎችን እንደሚረዱ አውቃለሁ... ግን ደግሞ መርዳትና አነግነት የተለያዩ ናቸው።"

ሌላ አባል: "መምህር ተክላይን መልምያለሁ። በመከላከያ ሚኒስቴር ውስጥ ሰራዊቱንና ታጋዮችን በማስተማር የዜግነት ግዴታውን ተወጥቷል።"

ቢኒያም ፈገግ አለ።ዞር ብሎ በኩራት አጠገቡ የተቀመጥኩትን የቀድሞ ሰራ ባልደረባው ገልመጥ አደረገኝ። አፍታም ሳይቆይ እጅን ወደ እኔ እየጠቆመ፣

"እኔም ሆንኩኝ እሱ የመከላከያ መምህር ነበርን። ሰራዊቱን የማብቃት ሰራ አመለካከትና ስነ - ምግባር ጥሩ ካልሆነ የሚቻል አይደለም። እነ ጀነራል ፍስሀ መንጁስን፣ እነ ወዲ መድህንን አስተምረን አሁን ለደረሱበት ደረጃ አስተዋጽኦ አበርክተናል። ተከላይም ተመሳሳይ ባህሪ የነበረው ነው። ዛሬም ቢሆን ይህ አብዮታዊነቱ የአላማ ጽናቱ አልተቀየረም። እንዲወያይ መልምላችሁ መምጣታችሁ የሚያስመሰግን ነው።"

ተመልምለው ከመጡት ሀምሳ ሰዎች አምስት ብቻ በቢኒያም ይሁንታ አለፉ። የቀበሌው ህዝብ በሙሉ በዚህ መልኩ የሚፈረጅ ከሆነ መጨረሻውን ማወቅ አያዳግትም። የቀበሌው አባላት ይዘው የመጧቸው በሙሉ በሾኬ እየተመቱ ሲያስቸግራቸው ተስፉ ቆረጡ። እኔም መጨረሻውን ማወቅ ስለፈለኩ ምንም አስተያየት ሳልሰጥ መመዝገቤን ቀጠልኩ።በመጨረሻ አንድ ተንኮለኛ አባል እጁን አውጥቶ እንዲህ በማለት ተናገረ።

"ከአካባቢው አዛውንቶች አቶ እከሌን ጠቁሚያለሁ። የቀጠናችን የልማት አስተባባሪ ናቸው። የውስጥ ለውስጥ መንገዶችንና ድልድዮችን አሰርተዋል። በቤተክርስቲያን አካባቢም በሚያደርጉት በጐ አስተዋጽኦ ይታወቃሉ።"

የአባሉ ተንኮል ስለገባኝ ካድሬ ቢኒያም ከመናገሩ በፊት እንዲህ በማለት አስተያየት ሰጠሁ፣

"አሁን የጠቀስካቸው አዛውንት ወዳጄ ናቸው። ቢኒያምም ይህን ያውቃል። ስለዚህ እኔ ባለሁበት ስትወስኑ ተጽእኖ ከማሳድርባችሁ በኋላ ላይ ወስኑ።" አልኳቸው።

ቢኒያም ከአፌ ተቀብሎ፣ "ይሻላል! ጥሩ አስተያየት ነው። ሌላ ጊዜ በደንብ አጣርተን እንወስናለን።" አለ።

***

የከተማው ኢህአዴግ ከንፍ አባል የሆነው ካሚል አህመድ ደግሞ ወደ ኮልፌ ቀራንዮ የቀድሞ ወረዳ 24 ቀበሌ 14 በመሄድ ሪፓርቱን ይዞ መጣ። በኢህአዴግ ቢሮ ሳገኘው ከአግርሞት አልወጣም። ህብረተሰቡ ይወክሉኛል ብሎ የሚያስባቸው ተብለው በቀበሌው ካድሬና አባላት የተመረጡት ሰዎች ማንነትና የኋላ ታሪክ አስደንግጦታል። ካሚልና ኢህአዴግ ብረት አንስተው የታገሏቸው ናቸው። ብዙዎቹን ኢህአዴግ "ህዝቡን በድላችኋል" ብሎ ተህድሶ ለመስጠት ጠላይ አጉሯቸው የነበሩ ናቸው። እነዚህ ከድል በኋላ በደል የተፈፀመባቸውና ፓርቲው ያራቃቸው ዜጐች በተቃራኒው ነዋሪው እኔን የሚወክሉኝና ከማንም በላይ ያሉትን የማዳምጠው እነሱን ነው ብሎ ማቅረብ እንቆቅልሽ ሆኖበታል።

ካሚል የሄደባት ቀበሌ በቅርብ አውቃታለሁ። ተወልጄ ያደኩበት በመሆኑ ብዙዎቹን ነዋሪዎች አውቃቸዋል። የሰጠኝ ወረቀት ላይ ግንባር ቀደም ወኪሎች በሚል የ50 ሰዎች ስም ዝርዝር ሰፍሯል። ሙሉ ነጥብ ያገኙትን የመጀመሪያዎቹ ሁለት ሰዎች አነበብኩ።

"**ኮረኔል ሞረዳ ዳዲ**፡ የቀድሞ አብዮታዊት ኢትዮጵያ ሰራዊት ከፍተኛ መኮንን የነበሩ። በጠላት ወረራ ወቅት ለሀገራቸው ከፍተኛ መስዋዕትነት የከፈሉ። የሀገርና የህዝብ ፍቅር ያላቸው። አጥፊ ወጣቶችን መካሪና የሀገር ሽማግሌ።"

"**ማስተር ቴክኒሻን አበራ ጆቴ**፡ የቀድሞ ኢትዮጵያ አየር ሀይል ከፍተኛ ሙያተኛ። በደርግ ዘመን የቀበሌው ሊ/መንበር በመሆን በቅንነት ያገለገሉ።በአሁኑ ሰአት ለህብረተሰቡ ቀድሞ ደራሽና በህዘን ጊዜ አጽናኝ።የእድር አመራር።በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚያስተባብሩ።"

በአጠቃላይ "ግንባር ቀደም" ተብለው ከተጠቀሱት ውስጥ 70% የሚሆኑት የቀድሞ ሰራዊት አሊያም የደርግ ካድሬ ሆነው ያገለገሉ እንደሆነ ይገልጻል። በጉጉት ሲጠባበቅኝ ለነበረው ካሚል የቀበሌው ካድሬና አባላት የሰጡት መረጃ ትክክል መሆኑን አረጋገጥኩ። የተጠቀሱት ሰዎች በትክክልም ህብረተሰቡ የሚወዳቸው፣ ወጣቶች የሚስሟቸውና የማስተባበር አቅማቸውን ከፍተኛ መሆኑን በእርግጠኝነት ነገርኩት።ሌሎች አካባቢዎችም እሱ እንደሄደበት ቀበሌ በትክክል ቢሰሩ ውጤቱ ተመሳሳይ እንደሚሆን ደግሜ አሳወኩት።

የካሚል ፊት ተለዋወጠ። የሰጠኝን ወረቀት እየተቀበለ፣

"ኢህአዴግ የሰበሰበው የህዝብ ጭራዎችን መሆኑን ዛሬ በሚገባ አረጋግጫለሁ።" ብሎ ተጨማሪ ሳይናገር ጥሎኝ ሄደ... ደርግን ለመጣል ብረት አንስቶ የታገለው ታጋይ ካሚል!!

ከቀናት በኋላ ከቀበሌዎች ተሰብስቦ የመጣው መረጃ ካሚል ከሄደበት ቀበሌ ጋር ተመሳሳይ ነበር። እንደ የካ ክፍለ ከተማ ካድሬ ቢኒያም የሰሩ ጥቂቶች ነበሩ። አብዛኞቹ የቀበሌ ካድሬዎቻችን በትክክል ህብረተሰቡ የሚቀበሏቸውን ሰዎች የትላንትና የኋላ ታሪክ ሳይመለከቱ መልምለው ነበር። በኋላ በውይይትም የተረጋገጠው ህዝቡን የሚወክሉ ሰዎች መገኘታቸው ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ ካድሬዎቻችን የሚያስመሰግናቸውን ስራ ሰርተዋል። ያገኟትን ሽንቁር እድል ተጠቅመው ህቁን በማውጣታቸው ርግጥም ይመስገኑ!

ወላፈኑ የሚገርፍ ሙቀት!

የመዲናይቱን ህዝብ ይወክላሉ ከተባሉት ወጣቶች፣ ሴቶችና ነዋሪዎች ጋር ውይይት ተጀመረ። በኢህአዴግ አስቀድሞ የተቀረፀው የመወያያ አጀንዳ በአራት ነገሮች ላይ እንዲያጠነጥን ታሳቢ የተደረገ ነበር። እነዚህም ከከተማው ህዝብ ኢህአዴግን የመረጠው ለምን እንደመረጠ?፣ ያልመረጠ ለምን እንዳልመረጠ?፣ ህዝቡ ይፈታልኝ ብሎ የሚያስበው የልማትና የመልካም

አስተዳደር ችግር ምን አንደሆነ እና በቀጣይ ተቀራርቦ ለመስራት ከእያንዳንዱ ባለድርሻ አካል ምን ይጠበቃል? የሚል ነበር።

መድረኩ ሲከፈት ከህዝቡ የሚቀርበው ውርጅበኛ እንደ ጐርፍ ሆነ። ከህዝቡ አፍ የሚወጣው ነበልባል ወላፈን በእሳት እንደመለብለብ ነበር። በእንዳንድ መድረኮች በውይይቱ ለመቀመጥ የታሰሩት የቅንጅት አመራሮች ይፈቱ የሚል ቅድመ ሁኔታ እስከመቀመጥ ደረሰ። ይህ የማይቻል እንደሆነ ሲገለጽ በሺዎች በተንጠባጠበ መልኩ መድረክ ረግጠው ወጡ። ለሁለት ሙሉ ቀናት ከተቀሩት ነዋሪዎች ጋር የተካሄደው የተካረረ ውይይት መጀመሪያውና መጨረሻው አንድ ሆኖ ተጠናቀቀ።

መድረኩ ከተፈፀመ በኋላ ለእኔና ፀጋዬ ታይለማርያም የ100ዎቹንም መድረኮች ቃለጉባኤ ተቀብለን በፈርጅ በፈርጁ እንድናስቀምጥ ተወሰነ። አንድ ሳምንት ሙሉ ከሁለት ሺህ በላይ የህዝብ ብሶትና አቋሞችን በይዘታቸውና ብዛታቸው በመለየት ባለ አርባ ገፅ ሪፓርት አዘጋጀን። በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ በነዋሪው የቀረቡት ሀሳቦች በብዛትና ክብደታቸው ሲመዘኑ በስድስት ተከፍለው ሊታዩ የሚችሉ ናቸው። እያንዳንዱ ጥያቄዎች የነበረውን ሁኔታ ገለጥለጥ አድርገው ስለሚያሳዩ ይህን ወደ መተረክ እንሸጋገር።

"ኢህአዴግ ይቅርታ ያድርግልን። አጥፍተናል!!"
የአዲሳአባ ህዝብ

የመጀመሪያው እና በሁሉም መድረኮች ልዩ ትኩረት ያገኘው የህዝብ ጥያቄ፣ "ኢህአዴግ ይቅርታ ያድርግልን፣ አጥፍተናል" የሚለው ነበር። ህዝብ መንግስትን ይቅርታ የጠየቀበት መድረክ። ምንአልባትም በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያው ክስተት። ኢህአዴግ ተቃዋሚዎችን ብቻ ሳይሆን ህዝብንም ይቅርታ ካላስጠየቀ እንደማይረካ የታየበት አጋጣሚ። በመገለጫነት ከህዝቡ የቀረበው ደግሞ፣

"እንኳን የለሽ ምርጫ እያላችሁ ጆሮአችንን ስታደነቁሩት እውነት መስሎን ነበር፣ በውስጣችሁ የከፉት መንፈስ እንዳለ አናውቅም ነበር። እኛ ስልጣን ላይ እስከሌለን ድረስ ኢትዮጵያ ምናባቷ እንደምትሉ አናውቅም ነበር። የኢትዮጵያን እጣ ፋንታ ከኢህአዴግ ህልውና ጋር አጣብቃችሁ የምታዩ አይመስለንም ነበር። በህዝብ ምርጫ እንደማትወርዱና የቀልዳችሁን እንደሆነ ብናውቅ ኖሮ እጅና እግራችንን ሰብስበን እንቀመጥ ነበር። የልጆቻችን ደም በከንቱ እንዳይፈስ አስቀድመን እናስጠነቅቃቸው ነበር። እናንተም በጠራራ ፀሀይ አትገድሉብንም። ከእንግዲህም እስከ እድሜያችሁ መጨረሻ ምርጫ ቅርጫ የሚባል እቃቃ ጨዋታ ሳታመጡ እንድትገዙን ፍቃዳችሁ ይሁን።

እባካችሁ! አጥፍተናል ፣ይቅር በሉን! ከእንግዲህም አይለመደንም" የሚል ነበር።

"የታሰሩት መሪዎቻችን ፍቱልን፣ እምቢተኛ ከሆናችሁ በእነሱ ፉንታ እኛን እሰሩ።"

የአዲሳአባ ህዝብ

ሁለተኛው የህዝብ ጥያቄ፣ "የታሰሩት የቅንጅት አመራሮች (መሪዎቻችን ይሏቸዋል) መንሰኤው እኛ ስለሆንን ፍቱልን፣ እምቢተኛ ከሆናችሁ በእነሱ ፉንታ እኛን እሰሩ" የሚል ነበር። በዚህ ዙሪያ እንደ መገለጫ የቀረቡት ደግሞ፣

"ከልብ የመነጨ ድጋፍ ሰጥተናቸው ከተደላደለ ህይወት ወደ እሳት የመራናቸው እኛ ነን። ለህዝብ ዘላቂ መብትና ጥቅም መስዋእት የሆኑ መሪዎቻችን ታስረው ዝም የምንልበት ህሊና የለንም። ተስፋችን ታስሮ የሚያርፍ ልቦና የለንም። እኛ የሰጠናቸውን የሚሊየኖች ድምፅ በጉልበተኛ ስለተነጠቁ ነው ህዝባዊ ጥሪ ያስተላለፉት። ታንክና መትረየሱ እናንተ ጋር እንጂ እነሱ ከብእር ውጭ ሰላማዊ ታጋዮች ናቸው። እነሱን ፍቱና እኛን እሰሩን!" የሚል ነበር።

የታሰሩ የቅንጅት አመራሮች ይፈቱ የሚለው ጥያቄ ለሁለት አመታት ተጠናክሮ የቀጠለ ሲሆን ከስብሰባ አዳራሾች ውጭ በተገኙት አጋጣሚዎች ሁሉ ይስተጋባ ነበር። ህዝብ ላይ የተጣበቀ የጠዋት እዳ ነበር። በዚህ ምክንያት በጥቃቅን ቡድኖችና ግለሰብ ደረጃ የገነባነው የጭቃ ካብ ህዝብ ሰብሰብ ባለ ቁጥር ይናድ ነበር። ሌላው ቀርቶ ስንዴ ሊገዛ ቀበሌ የተሰለፈ ረሀብተኛ ሳይቀር፣" መሪዎቻችን ይፈቱ!" እያለ መቆሚያ መቀመጫ አሳጥቶናል። በታላቁ ሩጫ የተሳተፈው ህዝብ ከጫፍ አስከ ጫፍ ያነገበው መፈክር "መሪዎቻችን ይፈቱ!"፣ "ልደቱ ባንዳ (ይሁዳ!)"፣ እና "ኢህአዴግ ሌባ!" የሚል እንደነበር የአደባባይ ሚስጥር ነው። ይህ ጩኸት ከህዝብ አልፎ በኢህአዴግ ካድሬዎች ዘንድ አነጋጋሪና ተስፉ አስቆራጭ ሆኖ ሰንብቷል። ታላቁ ሩጫ ይከልከል የሚል ጥያቄ በሰፊው ተነስቶ ነበር። አንዳንድ የተሰላቹ ካድሬዎች የህዝቡን ጥያቄ መልሰን ለምን ይህን አጀንዳ አንዘጋውም እስከማለት ደርሰው ነበር።

(ለአቶ መለስ በየሳምንቱ በምናቀርብለት የህዝቡ ምን ይላል ሪፓርት ላይ "ነዋሪው ታላቁ ሩጫ ይቅር፣ ለዳግም ብጥብጥ ይዳርገናል" እያለ እንደሆነ ገለጽንለት። እሱም አልዋጥለት ስላለው "ህዝቡ ብሶቱን የሚተነፍስባት አንዲት መድረክ እንዴት ይቅር ሊል ይችላል?" የሚል ጥያቄ ካነሳልን በኃላ "ታላቁ ሩጫ የህዝቡን ሙቀት ለመለካት ከምንጠቀምበት ቦታ እንደ አንዱ አድርገን መውሰድ

ይኖርብናል። ባይሆን የህይል ሚዛኑን ወደ እኛ እንዲያጋድል የውስጥ ሰራችሁን አስቀድማችሁ ስሩ!" የሚል አስተያየት ሰጠን። ከዛን በኋላ ታላቁ ሩጫ በአዲሳአባ ኢህአዴግ ከንፍ አመታዊ እቅድ ውስጥ ተካተተ። ለሩጫው አለት ሊስተጋቡ የሚገባቸው መፈክሮች አስቀድመው መዘጋጀት ጀመሩ። የወጣት(የሴት) ሊግና ፎረም አባላት የሩጫውን ትኬት አስቀድመው እንዲገዙ ጥብቅ መመሪያዎች ተላለፉ። በቡድን በቡድን ተደራጅተው ሩጫውን እንዲሳተፉ መደረግ ተጀመረ። ታላቁ ሩጫም የተመሰረተበት አላማ ቀርቶ "ታላቁ መሪ የሚወደስበት" ወደ ኢህአዴግ ሰላማዊ ሰልፍነት ተቀየረ። በፀረ-ኢህአዴግነት ተፈርጀ ከትትል ሲደረግበት የነበረው የድርጅቱ ባለቤት አትሌት ሀይሌ ገብረስላሴም በተጠመደለት የአይጥ ወጥመድ ተይዞ ኢህአዴግ ጫማ ስር ወደቀ።

እንደ እውነቱ ከሆነ የሀይሌን አግር ከሚያከብሩት ሰዎች አንዱ ነኝ። ራሱን የቻለ መዚየም ተሰርቶለት ለዘለአለሙ በክብር ቢቀመጥ ምኞቴ ነው። ይገባልም። ይሁን እንጂ የሀይሌን አድርባይ ጭንቅላት ለጠላቴም አልመኘውም። በታሪክ አጋጣሚ አለም አቀፍ ኩነቶች ጋር ተያይዞ ሀይሌ የተናገራቸውን ንግግሮች ለማውገዝ ከተቋቋሙት ኮሚቴዎች ውስጥ አባል ነበርኩ። ከቤጂንግ አሎምፒክ ጋር ተያይዞ በሰጠው አስተያየት እኔ፣ ሴኮቱሬ ጌታቸው እና በንቲ የሚባል ካድሬ የቻይና ኤምባሲ የእራት ግብዣ ተጠርተን በመሄድ የቻይናን መንግስት ይቅርታ ጠይቀናል። ሀይሌን ለማውገዝ የክልልና አዲሳባ ወጣቶች ማህበር ፕሬዝዳንቶችን በመምራት ወደ ቻይና ቤጂንግ አቅንቼ ነበር። ከዚህ በተጨማሪም በፊረንጆቹ 2008 የአሜሪካው ፕሬዝዳንት ባራክ አባማ ባህለ-ሲመት ምሽት ሀይሌ በህዝብ የለውጥ ግለት ተነሳስቶ የሰጠው አስተያየት ፍዳውን እንዲቆጥር አድርጐታል። የአቶ መለስ ሞትን በማስመልከት በተዘጋጁት የሀዘን እንጉርጉሮዎች ውስጥ አንዲት እናት በመስቀል አደባባይ ደረታቸውን እየደለቁ ሲያነቡ ይታያል። በብዙ ኢትዮጵያውያን ዘንድም ተቀርጾ ቀርቷል። ታሪክ ራሱን ይደግማል እንደሚባለው እኛሁ ልጃቸውን በቀይ ሽብር ያጡ እናት ከአምስት መቶ በላይ የቀይ ሽብር ሰማእት ቤተሰቦች በተሰበሰቡበት "ልጄ ሀይሌ ገብረስላሴ በጀርባዬ አረደኝ!" ብለው በተመሳሳይ መልኩ ደረት ደልቀዋል። አንባቸውንም አረጭተዋል። ሸመልስ ከማል ሀይሌ ላይ ይዞ የነበረውን ቂም በዚህ መልኩ ተበቅሎታል። የቪዲዮ ካሴቱም በእሱ እጅ ይገኛል። የሀይሌ ጉድ በዚህ ብቻ አያባራም። ታሪክ ሊዘከረው ይገባልና "**እንቁ አግር፣ አድርባይ ጭንቅላት**" በሚል ርዕስ ተጽፏል። በሚቀጥለው ማስታወሻ ራሱን በቻለ ምእራፍ ለንባብ ይበቃል።)

በአጠቃላይ መልኩ እስከ አዲሱ የኢትዮጵያ ሚሊኒየም ዋዜማ ድረስ የአዲሳባን ፓለቲካ ምህዳር የሸፈነው የቅንጅት መሪዎች ይፈቱ የሚለው ነበር።

ይህን ጥሬ ሀቅ መካድ ያቃተው በረከት ስምአን በሁለት ምርጫዎች ወግ መጽሐፍ ምእራፍ ስድስት "በሚሊኒየም ምንም የለም ወይንስ..." በሚለው ርእስ ስር፣

"... የቅንጅት መሪዎች ከእስር መፈታት የአዲስ አበባን ህዝብ ከሀሊና ሽክም ገላገለው።" በማለት ይገልፀዋል። በሌላ በኩል ድፍን የአዲሳባ ህዝብ "የቅንጅት መሪዎች አላጠፉም፣ ጥፋት ከሆነም የጥፋቱ መንስኤ እኛ ስለሆንን እኛን እሰሩን!" ማለቱን የስምአን ልጅ መቀበል አልፈለገም። ሊቀበልም አይችልም። ይህን አምኖ መቀበል ማለት በእራስ ላይ እባብ እንደመጠምጠም ይቆጠራል። ስለዚህም ሽምጥጥ አድርጎ መካዱ አማራጭ የለውም። ለዚህ አማኝ እንዲሆን የሁለት ምርጫዎች ወግ፣ "የሁለት አመቱ ማራቶን እንዴት ይቋጭ?" በሚለው ርዕስ ስር የሚከተለውን አስፍሯለች፣

"... እንዲህም ሆኖ ነገሮች እየተቀዛቀዙ ቢሄዱም የአዲስ አበባ ህዝብ ግን በዚህ ወቅት ከኢህአዴግ ጋር ሙሉ በሙሉ አልታረቀም ነበር። በተለይ የወጣቱ ቅሬታ ሰፋ ያለ ነበር። የታሰሩት የቅንጅት መሪዎች ቢፈቱ የሚል ሀሳብ የሚሰነዝረው የህዝብ ክፍልም ቁጥሩ ትንሽ አልነበረም። በህዝቡ ዘንድ የቅንጅት መሪዎች ይፈቱ ዘንድ ግፊት ከማድረግ በዘለለ "አላጠፉም፣ ንፁህን ናቸው" ብሎ የሚሟገት ብዙ ድምፅ አልነበረም። ህዝቡ በደፈናው ይፈቱ የሚል ጥያቄ ከማቅረብ አልፎ አላጠፉም የሚል የምስክርነት ቃልና የህሊና ፍርድ ሊሰጥ አልፈቀደም።"

እንደ እውነቱ ከሆነ ሀቁ በረከት በጻፈው መልኩ ቢሆን ኖሮ እጅግ ከሚደሰቱት ኢህአድጋውያን አንዱ እኔ እሆን ነበር። ወደኋላ ሄጄ የግለሰብ አቋሜንም አልፈትሸም ነበር። ርግጥም ስህተት ሰርተዋል፣ የኢትዮጵያን ህዝብ ሊያስጨርሱ ነበር የሚል እምነቴ ይጠናከር ነበር። በኢህአዴግነቴም እንደፀናሁ እኖር ነበር። ለስምአን ልጅ ግን ራሱ የጻፈውን ቅቡል አድርጌ አንድ ጥያቄ ላንሳ። ህሊናህ ተሸክሞ የሚዞረው ነገር ህሊናህ ፍርድ የሰጠበትን አይደለም እንዴ?

ከዚህ የህዝብ ጥያቄ ሳልወጣ አንድ ሊሰመርበት የሚገባ ቁምነገር ያለ ይመስለኛል። ስለ ህዝብ አመፅ እየተቀዛቀዘ መሄድ በተመለከተ። በረከት በመጽሐፉ እንደገለፀው በትክክልም የህዝብ ይፉ ተቃውሞ እየተቀዛቀዘ ሄዶ ነበር። ይህ የሆነበት ምክንያት ነዋሪው ከኢህአዴግ ጋር ለመታረቅ ፍላጐት ስላለው አልነበረም። ኢህአዴግና የአዲሳባ ህዝብ ላይታረቁ ተጣልተዋል። የመርህ ጉዳይ ስለሆነ። ታዲያ በግላጭ የሚታይ የአዳራሽ እና አደባባይ ተቃውሞ ለምን ተቀዛቀዘ? ለዚህ ምላሽ እንዲሆን በአንድ ወቅት ከአቶ መለስ ጋር በነበረን ስብሰባ የተናገረውን ላንሳ። አቶ መለስ እንዲህ ነበር ያለው፣

"የአዲስ አበባ ህዝብ አሁን ባለበት የኢኮኖሚ ሁኔታ የተራዘመ አመፅ

ማስተናገድ አይችልም። ታስታውሱ እንደሆነ የአመፁን የመጀመሪያ ፊሽካ የነፉት የታክሲ ባለቤቶች፣ የታክሲ ሹፌሮች፣ ወያላዎችና ተራ አስከባሪዎች ነበሩ። የታክሲ የስራ ማቆም በተደረገ በቀናቶች ውስጥ ሹፌሮች፣ ወያላዎችና ተራ አስከባሪዎች የሚልሱት የሚቀምሱት አጡ። መዋቅራችን ጋር እየመጡ ስራ መጀመር እንደሚፈልጉና የታክሲ ባለቤቶች ላይ እርምጃ እንድንወስድ ተማፀኑ። በሌሎች ዘርፎች ያለውም ተመሳሳይ ነው።"

ይህን የአቶ መለስን ሀሳብ እጋራለሁ። ርግጥ ይህ ሀቅ በአዲሳአባ ህዝብ ላይ ብቻ ሳይሆን በመላ ኢትዮጵያ ከተሞች የሚገኘው ህዝብ መገለጫ ነው። የራሱ መንስኤዎችም አሉት። በአንድ በኩል ከቀድሞዎቹ አስከፊ ስርአቶች ጋር ተያይዞ በደረሰበት በደል የፀረ ዲሞክራሲ ተሸካሚ መሆኑ ሲሆን በሌላ በኩል ከዜሮ በታች በሆነ ፍፁም የድህነት አረንቋ ውስጥ መዘፈቁ ነው። ስቸጋር የሚገረፍ ህዝብ (ፀረ - ዲሞክራሲው እና ጨዋነቱ ተጨምሮ) ረዘም ያለ አመጽ ለማድረግ ይቸግረዋል። ከፀረ - ዲሞክራሲ አንፃር እስከአሁንም ድረስ (በሂደት እየተዳከመ ቢሄድም) "ንጉስ አይከሰስ ሰማይ አይታረስ" የሚለው ብሂል ቁጥሩ ቀላል በማይባል የህብረተሰብ ክፍል ተቀባይነት አለው። በፀረ ዲሞክራሲ ውስጥ የተወለደው ደርግም የፈፀማቸውን ግፎች ከመናገር ይልቅ የኢትዮጵያዊነት ካባ እንዲጠልቅለት የሚፈልጉ ብዙዎች ናቸው። ምንአልባትም በአለም ደረጃ የነበረው የሶሻሊስት ካምፕ ባይፈራርስ ኖሮ የደርግ እድሜ ረጅም ሊሆን ይችል እንደነበር የሚመኙ እና የሚከራከሩም አሉ። ይህን ለታሪክ ምሁራን እንተወውና ወደ አቶ መለስ ምሳሌ እንመለስ።

የኢትዮጵያ ህዝብ የተራዘመ አመጽ ማስተናገድ አይችልም በማለት በምሳሌነት ስለገለፀው፣ አቶ መለስ እንዳለው በምርጫ 97 ሁከትና ብጥብጥ ምክንያት ታክሲዎች ለቀናት ስራ አቁመው ነበር። በአምስተኛው ቀን አበበ የሚባል የአዲሳባ ታክሲ ተራ አስከባሪዎች ማህበር ፕሬዝዳንት የነበረ በላይ የሆነ የተራ አስከባሪዎችና ወያላዎች ስምና ፊርማ የያዘ ማመልከቻ አራት ኪሎ ኢህአዴግ ቢሮ ይዞ ይመጣል። በማመልከቻውም ተራ አስከባሪዎችና ወያላዎች ስራ መጀመር እንደሚፈልጉ፣ ከኢህአዴግ ጋር እንደሚተባበሩና ዋነኛ ጠላቶች የታክሲ ባለቤቶች እንደሆኑ የሚገልጽ ነበር። አበበ የታክሲ ባለቤቶች ለሳምንታት የሚዘልቅ ቀለብ እቤታቸው አስቀምጠው እኛን በረሀብ ገደሉን በማለት በማመልከቻው ይከሳቸዋል። ይህ አጋጣሚ ለኢህአዴግና በረከት ልዩ ፈንጥዝያ የፈጠረ ነበር። ዘመን ተሻጋሪው ካድሬ (ታጋይ ይሳቅ ቆሬጥ) ልዩ ሀላፊነት እንዲሸከም ተደረገ።በሶስት ሳምንት ውስጥ የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ በሁለት ሺህ ወጣቶች አቶ መለስ በተገኘበት በጠቅላይ ሚኒስትር አዳራሽ ተመሰረተ። ከእነዚህ ውስጥ ሀምሳ በመቶው ለቀናት በረሀብ አለንጋ የተገረፉት ተራ አስከባሪና ወያላዎች ነበሩ። እነዚህ ወጣቶች ከወራት በፊት የህዝብን

እምቢተኝነት ተጋርተው መንግስትን ፉታ የነሱ ናቸው። ብዙም ሳይቆዩ የህዝቡን የለውጥ መንፈስ ቢገነዘቡም አማራጭ አልነበራቸውም። ነገን የማያውቀው ሆድ የማያቋርጥ ጥያቄ አቀረበ። ከረሀብ እና ደባል ሱስ ጋር ተያይዞ የሚመጡ ስቃዮች ከህዝቡ በተቃራኒው እንዲቆሙ አስገደዳቸው።

(ስለ ረሀብ አደገኝነት ሳስብ ካፒቴን ተሾመ ተንኮሉ ኢሳት ከሚባለው ሳተላይት ቴሌቪዥን ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ ፊቴ ይደቀናል።)

***

"እባካችሁ! ቂም ያዘለ በቀላችሁን በልክ አድርጉት! የሲኦል ኑሮ ይብቃ!"

የአዲሳባ ህዝብ

በሙቀት መለካቱ ስብሰባ **ሶስተኛው** የህዝብ ጥያቄ፣ "እባካችሁ! ቂም ያዘለ በቀላችሁን በልክ አድርጉት!" የሚል ነበር። ይህ ተማጽኖ አዘል ጥያቄ በዝርዝር ሲታይ እንደሚከተለው ይመስላል፣

"የፈለጋችሁትን ምረጡ ብላችሁ የፈለግነውን ስንመርጥ በከተማ ችጋር ተበቀላችሁን። አካላዊ ጉስቁልና እና ተስፉ እጦት የዘወትር ህይወታችን ሆነ። የኑሮ ውድነቱ ወገባችንን እንዲያጎብጠው አደረጋችሁ። በየቀኑ እየናረ የሚሄደውን የዋጋ ግሽበት መቋቋም አቅቶናል። ኢትዮጵያ በምግብ እራሷን እንደምትችልና በቀን ሶስቴ እንደምንበላ ቃል ገብታችሁ አንድ ጊዜም አታተን። በህፃናት ልጆቻችን የዳቦ ቁራሽ ጥያቄና የረሀብ ልቅሶ ጭንቅላታችን ዞረ!፣ ታረዝን! የለበስነው ልብስ በላያችን ላይ ነተበ።" የሚሉ ነበር።

***

"በምርጫው ማግስት የተዘረፉ የህዝብ ንብረቶች ይመለሱ። ዝርፊያውን የፈፀሙና ያስፈፀሙ ባለስልጣናት ለፍርድ ይቅረቡ!"

የአዲሳአባ ህዝብ

አራተኛው የህዝብ ጥያቄ "በምርጫው ማግስት የተዘረፉ የህዝብ ንብረቶች ይመለሱ። ዝርፊያውን የፈፀሙና ያስፈፀሙ ካድሬዎች ለፍርድ ይቅረቡ!" የሚል ነበር። ህዝቡ የሰጠው መረጃም የሚያሳየው ነገር ቢኖር ከህዝብ የተደበቀ አንድም ነገር አለመኖሩን ነው። ርግጥ በነዋሪው የቀረቡት የዝርፊያ መረጃዎች ከበረከት ጀምሮ እያንዳንዱ ካድሬ ያውቃቸዋል። በአዲሳአባ ታሪክ ውስጥ መቼም ያልተፈፀመ ስለሆነ። ኢትዮጵያ ባስተናገደችው በየትኛውም ስርአት የቀበሌና መንግስታዊ ጽ/ቤት ተሰብሮ ወደ መኖሪያ

ቤትነት የተቀየረበት ሁኔታ አላጋጠመም። በምርጫ 97 ማግስት ግን ከ30 በላይ የቀበሌ ጽ/ቤቶችና መንግስታዊ ተቋማት በኢህአዴግ ካድሬዎች፣ በፌደራል ፓሊስና ደህንነቶች ተሰብረውና በቃይዚቲ ተከፉፍለው ወደ ግለሰብ መኖሪያነት ተቀይረዋል። በቀበሌ የሚገኙ ሱይሎችና ሰነዶች ሰርቆ በማውጣት የመንግስት ቤት ወደ ግለሰብ እንዲዞር ተደርጓል።

ይህን እውነት መቀበል ያልፈለገችው የሁለት ምርጫዎች ወግ፣ "የጐዳና ላይ ነውጥ እንዳይቀሰቀስ የተካሄደ ትግል" በሚለው ርእስ ስር፣

"...ኢህአዴግ ከምርጫ 97 ማግስት በከተሞች የተከተለው አቅጣጫ ከከተማው ህዝብ ጋር ለመግባባት መልካም እድል አስገኝለት።" በማለት ትገልጻለች። ታላቅ ወንድሜ በረከት በምትወዳት ትንሿ ልጅህ (ህሊና) ይገፍሀለሁ ይህን ህሊናህ አምኖበት ነው የጻፍከው?" በምርጫው ማግስት የህዝቡን ቅሬታ ያባባሱ ጥፋቶች" ብለህ ያዘጋጀኸውን ሰነድ ረሳኸው? ...የቀበሌ ጽ/ቤቶች ተሰብረው ወደ መኖሪያ ቤት መቀየራቸውን ስትሰማ በንዴት ውስጥ ሆነህ "ወሮበላ ሁላ!" ብለህ የተናገርከውንስ?...

***

"ባለአደራ እና ኢህአዴግ የአንድ ሳንቲም ሁለት ግልባጮች ናቸው!"

የአዲሳአባ ህዝብ

አምስተኛው የህዝብ ጥያቄ፣ "ባለአደራ የሚባል ቀልድ አቁሙ!" የሚል ነበር። ይህ አስተያየት ተጨምቆ ሲታይ ይዘቱ አንደሚከተለው ነበር፣

"ባላደራ የሚል ቃል ያመጣችሁት ከተጠያቂነት ለመሸሽ ፈልጋችሁ ነው። ባላደራን የመለመለው ማነው?፣ በባላደራ ስም ማሊያችሁን ቀይራችሁና አይናችሁን በጨው አጥባችሁ ከማዘጋጃ ቤት እስከ ቀበሌ ድረስ ያለውን አስተዳደራዊ ስልጣን ተቆጣጠራችሁት። ከልባችሁ አደራ የሚጠበቅ ሰው የምትፈልጉ ከሆነ ህዝቡን ሰብስቡና ራሱ ይምረጥ። በመረጥነው እንጂ የኢህአዴግ ውስጥ ልብስ ባጠለቁ ካድሬዎች መተዳደር አንፈልግም።"

ርግጥም ከከተማ እስከ ቀበሌ የተቋቋመውን የባለ አደራ አስተዳደር የሰው ሀይል እንዲመደብ ያደረገው እኛን ነበርን። ባለአደራው በኢህአዴግ ደጋፊዎች፣አባላትና ካድሬዎች እንዲሞላ አድርገናል። በተለይ ካሚል አህመድ ልዩ ሚና ነበረው። በከተማው ባላደራ ካቢኔ ውስጥ የኢህአዴግ አባላት መሆናቸውን እያወቅን ገለልተኛ ናቸው ብለን እንዲሾሙ አድርገናል። ሽሪፍ የሚባለው የከንቲባ ጽ/ቤት ሀላፊ የደኢህዴን አባል፣ የሚኒስትሮቹ ሬድዋን ሁሴንና ሲራጅ ፈርጌሳ የቅርብ ጓደኛ ነው። ምስጋናውና ይትባረክ የሚባሉት

የማስታወቂያና ኢንዱስትሪ ቢሮ ሀላፊዎች የደኢህዴን፣ህጐስ የሚባለው የትምህርት ቢሮ ሀላፊ ደግሞ የህውሀት አባላት ናቸው። በክፍለ ከተማና ቀበሌም ተመሳሳይ ነበር። በአርከበ ዘመን የትምህርት መምሪያ ሀላፊ የነበሩ የኢህአዴግ ደጋፊዎችና አባላት የባላደራው ካቢኔ ሆነዋል። ከቀበሌ ስራ አስኪያጆች 90% በላይ በአርከበ ዘመን የኢህአዴግ ካድሬ የነበሩ ናቸው። በክፍለ ከተማና ቀበሌ የካቢኔ አባላት ስልጣን አንድ ላይ ተጨፍልቆ የስራ አስኪያጁን አያከልም። ዋና ስራ አስፈጻሚውንና ሊቀመንበሩን ጨምሮ ትእዛዝ የሚቀበሉት በስራ አስኪያጅነት ከተመደቡት የኢህአዴግ ካድሬዎች ነበር።

(የስራ አስኪያጆቹን ምደባ በተመለከተ የሲቪል ሰርቪሱን ህግ በመጻረርና በህግ በሚያስጠይቅ መልኩ የሰራው አርከበ እቁባይ ነበር። ይህን የፈፀመው በምርጫው ማግስት ነበር። ያደረገበትም ምክንያት ቅንጅት ስልጣኑን ከተረከበ ሰራ አስኪያጅነት የፓለቲካ ሹመት ሳይሆን የሲቪል ሰርቪስ መደብ በማድረግ በካድሬዎች ለማስያዝ ነበር። ይህን ነውረኛ ተግባር በማየት ለምን ህግ ይጣሳል ብሎ የጠየቀውን የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ኮሚሽነር አበባየሁ እንዲንሳፈፍ አድርጐት ነበር። በመጨረሻም አከርካሪ የሚሰብር የበቀል ዱላ አሳረፈበት።)

ከጊዜያቶች በኋላ በተግባርም የታየው ህዝቡ የተናገረው ነበር። ባላደራው ትእዛዝ የሚቀበለው ከኢህአዴግ በተለይም ስራና ከተማ ልማት ከተመደበው አርከበ እቁባይ ነበር። የመልካም አስተዳደር እጦቱም ይበልጥ ተስፋ አስቆራጭ ደረጃ የደረሰበት ሆነ። የኢህአዴግ የቅጣት በትር በእጅ አዙር ተግባራዊ ሆነ። በህዝቡ ሮሮና ልቅሶ እነ አርከበ እና በእሱ ኔትወርክየታቀፉ ካድሬዎች ደስተኞች ነበሩ። "ማን ቅንጅትን ምረጡ አላቸው! በገዛ ውሳኔያቸው ተቀጡ!" የሚሉ ቃላትን መስማት ህሊና ያደማ ነበር። በመጨረሻም የባለአደራው ሚና ብዙ የህዝብ ገንዘብ ወሮ ለበላው የኢህአዴግ ፎረም በጀት መመደብ ሆነ። ፎረሙ የኢህአዴግ የመመካከሪያ መድረክ ቢሆንም በሀያ ሚሊዮኖች የሚጠጋውን የስብሰባ፣የምሳና ትራንስፓርት ወጪ የሸፈነው ባላደራው ነበር።

ይህን ህዝብ እና የኢህአዴግ ካድሬዎች በአደባባይ የተናገሩትን እውነታ የሁለት ምርጫዎች ወግ መቀበል አልፈለጉችም። እንዲህ በማለት ለታሪክ የሚቀመጥ ቅጥፈት በገጽ 188 -189 ላይ ከትባለች፣

"የኢህአዴግ ፍላጐት ተቃዋሚዎች ህግን አክብረው ፓርላማ እንዲገቡ፣ አዲስ አበባንም ተረክበው እንዲያስተዳድሩ ነበር። ርዕሰ ከተማዋን የማስተዳደር ሀላፊነታቸውን እንዲወስዱ ለማግባባት ያደረገው መከራ ሳይሰምርለት ቀረ

እንጂ። ኢህአዴግ ህግ እንዲከበር ያደረገው ተደጋጋሚ የማግባባት ሙከራ ሳይሰምር በመቅረቱ ገሚሱ ተቃዋሚ ወደ ዘብጥያ ወረደ። ከፊሉ ደግሞ በተበታተነ አኳኋን ወደ ፓርላማ ገባ። ከዚህ በኃላ የአዲስ አበባን የሚያስተዳድር የባለአደራ አስተዳደር ማቋቋም ተገቢ ሆነ። በዚህ መሰረት በአቶ ብርሀኑ ደሬሳ የተመራና በህብረተሰቡ ተቀባይነት ባላቸው ገለልተኛ ሰዎች የተዋቀረ የባለአደራ አስተዳደር ተቋቋመ። ቅንጅቶች የአገሪቱን ዋና ከተማ ለወራት አመራር አልባ አድርገዋት ሲቆዩ ፣ኢህአዴግ እኔ እተካቸዋለሁ የሚል ጥድፊያ ውስጥ አልገባም። በሩቅም ቢሆን ፈጽሞ የመግባት ሀሳብ አልነበረውም። ይህም ድርጅቱ ለህዝብ ድምፅ ካለው አክብሮት የመነጨ ነው። ባልተመረጣችሁበት ሰልጣን ብትጋሩም ምንም አይደለም ከሚለው የአውሮፓ ህብረት የታዛቢዎች ቡድን ግልብ የዲሞክራሲ አስተሳሰብ የላቀና የጠለቀ የህዝብ መብት አክባሪነቱን ያሳየው ኢህአዴግ፣ በአዲሳአባ ከፓለቲካ ነፃ የሆነ የቴክኖክራቶች አስተዳደር እንዲመሰረት አደረገ። ይህም ለከተማዋ መረጋጋት የራሱን መልካም አስተዋፅኦ አበረከተ። የባለአደራ አስተዳደር መቋቋም ቅንጅት የፈጠረውን የአስተዳደር ክፍተት እንዲሞላ አደረገው። ኢህአዴግም ከአዲስ አበባ አስተዳደራዊ ሰልጣን ርቆ ሙሉ በሙሉ በፓለቲካና ድርጅታዊ ስራው ላይ እንዲያተኩር እድል አገኘ።"

አቶ በረከት በመጽሐፉ መቅድም ላይ ደጋግሞ የገለፀው ቃል "ተጨባጭ ሀቆችን ሳያዛቡ ማቅረብ"፣ ..."እውነታውን ሳያዛቡ ማቅረብ"፣ ..."እውነቱን ለህዝብና ለታሪክ ባልተዛባ አኳኋን ማቅረብ" የሚሉ ቃላቶችን ነው። እስቲ እኔም ሆንኩ ኢህአድጋውያን የምናውቀውን እውነታ ለስምአን ልጅ በረከት በጥያቄ መልክ ላቅርበው። ምንአልባት ረስቶት ከሆነ እንዲያስታውሰው...

አቶ በረከት ሆይ!

የኢህአዴግ ፍላጐት ተቃዋሚዎች አዲሳአባን ተረክበው እንዲያስተዳድሩ እንደሆነ ገልፀሀል። ለማግባባትም ጥረት እንደተደረገ። እንደ እውነቱ ከሆነ የከተማዋን ቋት ባዶ ለማድረግ የተወሰዱት እርምጃዎች የሚያግባቡ ነበሩ? ...ኢህአዴግ ለሽንፈቱ ተጠያቂ ያደረገውን የአስተዳደሩ ሰራተኛ ፍቅር ተቃጥሎ ነበር አርከበ ወደ መዲናይቱ ከመጣ ጀምሮ ለሶስት አመት ተቋርጦ የነበረውን የመደበኛ ደሞዝ ጭማሪ በምርጫው ማግስት እንዲፈቀድ የተደረገው?... ከምርጫው አንድ አመት በፊት የተጠራቀመ የኪራይ ገቢ ግብርን፣ የንግድ ስራ ፍቃድን፣ የውጪ ማስታወቂያን ወደ ዜሮ እንዲወርድ የተደረገው ኢህአዴግ በሁለት ቢላዋ በልቷል ብሎ ያሰበውን ነጋዴ ለመጥቀም ነበር? ...መዲናይቱ አንድም ጦሙን ያደረ መሬት ሊኖራት አይገባም ተብሎ የተካሄደው ወረራ በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶ ይታወቃል? ...በመስተዳድሩ ስር

የነበሩ ተቋማትን (ትራንስፓርት፣ ውልና ማስረጃ፣ አንበሳ አውቶብስ...) በምርጫው ማግስት መውሰድ ማግባባት ነበረ ማለት ነው? አቶ መለስ "ከመኪና ጋር ተያያዥ ያላቸውን እንደ ሊብሬ ያሉ አገልግሎቶች የወሰድነው የቅንጅት ፈረሶች የሆኑትን ታክሲዎች ልክ ለማስገባት ነው" ብሎ የተናገረውን አብረን ነበር ያዳመጥነው። ...የኦሮሚያ ከተማ ከአዳማ ወደ አዲሳአባ የመጣበት ሂደት የሚያግባባ ነው? አባዱላ የኦህዴድ ካድሬዎችን ሰብስቦ" በኦሮሞ ህዝብ እና በቅንጅት መካከል ፈንጂ ቀበርን!" ማለቱን አልሰማህም?...

አቶ በረከት ሆይ!

የባለአደራ አስተዳደሩን ከንቲባ ብርሀኑ ደሬሳን ያመጣው ማነው? አባይ ፀሀዬ አይደለም?፣ ...ከከተማ እስከ ቀበሌ የተዋቀረውን ካቢኔ የመለመለውና የመደበው ታጋይ ካሚል አህመድ እና እኛ ኢህአዴግ ቢሮ ተቀምጠን አይደለም?፣ ...የምልመላ ሂደቱ ምን ደረሰ? ዝርዝሩን ሳላይ እንዳትመድቡ ስትል የነበርከው አንተ አይደለህም እንዴ?... ገለልተኛ የምትለን ከከንቲባው ውጭ የካቢኔ አባላቶቹ የኢህአዴግ አባላት አይደሉም?... ስለ ሀገሱ ኢህአዴግነት አፍንጫህ ስር ያለው ሚኒሊክ ትምህርት ቤት ገራ በልና አንድ መምህር ጠይቅ። እውነቱን ይነግርሀል። የምስጋናውንም ቢሆን ወረድ ብለህ ውጭ ጉዳይ ተራ ሰራተኛ መጠየቅ በቂህ ይሆናል። ...በህረተሰቡ ተቀባይነት ያላቸው የምትለን ፣ነዋሪው የት አውቆአቸው በምን መዝኗቸው ነው? (እነ እከሌ የቀን ውሎአቸው ከእነ እንቶኔ ጋር ጫት እየቃሙ ነው የሚለውን ለመግለጽ የማስታወሻዬን ደረጃ ስለሚያወርደው ትቼዋለሁ እንጂ እስከዛ ድረስ መዝለቅ ይቻል ነበር።)...

አቶ በረከት ሆይ!

ኢህአዴግ ከአዲሳአባ አስተዳደራዊ ስልጣን ርቆ ነበር የምትለው የመዲናይቱን የልማት ስራዎች ሪፓርት አንተም ሆንክ እኛ ባለንበት አቶ መለስ ቢሮ በየሳምንቱ የሚያቀርበው አርከበ አቁባይ አልነበረም እንዴ? ...የብርሀኑ ደሬሳን ካቢኔ በየሁለት ሳምንቱ ቢሮው እየጠራ የሰራ ትእዛዝ የሚሰጠው፣ በጀት የሚደለድለው፣ መሬት መስጠት በታገደበት ሁኔታ ከስራና ከተማ ልማት እየተንደረደረ መሬት የሚሰጠው አርከበ አልነበረም? ...የኢህአዴግ የፓለቲካና ድርጅት ስራ የተፈፀመው ባላደራው ከህዝብ ከሰበሰበው ግብር አይደለም? እስቲ! ወደ ማዘጋጃ ቤት ወጣ በልና በባለአደራው ዘመን ለኢህአዴግ ፎረሞች ስንት ሚሊዮን ብር ወጪ እንደተደረገ ጠይቅ። ... የወጣቶች ፎረም ፕሬዝዳንት የነበረውን ወጣት ሀብታሙ አያሌው ጠይቅ (ይቅርታ ለካስ የአንድነት ኮሙዩኒኬተር ሆኗል!) ...ቴክኖክራቶች የምትለው ከአዲሳባ መቶ ቀበሌዎች ከዘጠና በላይ የሚሆኑት ስራአስኪያጆች በአርከበ ጊዜ ካድሬ የነበሩና አብዛኞቹ ለስራ አስኪያጅነት የማይመጥኑ እንደሆኑ የዘወትር ሪፓርትህ አልነበረም? ...

***

"በምርጫው ማግስት ከአዲሳባ ህዝብ የተነጠቁ ተቋማት ይመለሱ!"
የአዲሳአባ ህዝብ

ስድስተኛው የህዝብ ጥያቄ የአዲሳባን ቁመና ለማዳከም ወደ ፌደራል የተወሰዱ ተቋማት ይመለስ የሚል ነበር። እንዲህ ነበር ያሉት፣

"የአዲሳአባ መንገዶችና ትራንስፓርት፣ እንደ ቅርስ የምንቆጥረው የአንበሳ አውቶብስ ተነጥቀናል። ነዋሪው ሊቆጣጠረው የሚገባ የፓሊስ ሀይል ተነጥቆ ወደ ፌደራል መሄዱ አግባብ አይደለም። አስተዳደሩን ለማዳከም የወጡ መመሪያዎች በስራ ላይ እንዳይውሉ። ይህን ሁሉ እርምጃ የወሰዳችሁት ቅንጅት እንዳይረከብ ለማድረግ ነው። አስፈላጊ ከነበረ ከምርጫው በፊት ለምን አላደረጋችሁትም ነበር? ህዝብን እየናቃችሁ እስከ መቼ ትዝልቃላችሁ? ከጫንቃችን ላይ ውረዱ!።"

ይህን ትንፋሽ የሚያሳጥር የህዝብ ጥያቄ የሁለት ምርጫዎች ወግ ልታልፈው አልፈለገችም። በአንድ በኩል "ኢህአዴግ ከምንም ነገር በላይ ህዝቡን ያከብራል፣ይፈራልም። ሁሌም እንደሚለው ከህዝብ ውጭ ሌላ ጌታ የለውም።" ትሰናለች። በሌላ በኩል ለህዝብ ጥያቄ የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያክል ክብር እንደሌላት ለማሳየት " ከንቲባነት በቆረጣ" በሚለው ርእስ ስር፣

"... ሌላ ጊዜ ፌደራል መንግስት የአንበሳ አውቶብስና የአዲስ አበባ ህግ አስከባሪ አካላትን ተጠሪነት ለፌደራል ማድረጉን ሽፉን በማድረግ ያዙኝ ልቀቁኝ ይባላል።" በማለት የንቀቷን የትየለሌነት ትግተናለች።

***

የሚኒስትሮቻችን ሪፓርት

እኔና ፀጋዬ ሀይለማርያም ከቃለ ጉባኤ ከምናጠናቅረው ሪፓርት በተጨማሪ ወደ ቀበሌ ወርደው ህዝቡን ያወያዩት ሚኒስትሮችና ከፍተኛ ካድሬዎች ትዝብታቸውን በሪፓርት መልኩ የሚልኩትን እንድናጠናክር ትእዛዝ ተላልፎ ነበር። እጅግ በጣም የሚገርመው ነገር ከእነዛ ሁሉ ቱባ ባለስልጣናት የተሰማቸውን በወረቀት ላይ አስፍረው የላኩት ሁለት ሚኒስትሮች ብቻ ነበሩ። በወቅቱ የጤና ጥበቃ ሚኒስትር የነበረው ዶክተር ቴዎድሮስ አድሀኖምና የትምህርት ምክትል ሚኒስትሩ ዶክተር አድሀኖም። ሌሎቹ በተደጋጋሚ ቢጠየቁ

ዛሬ ነገ እያሉ ሳይልኩ ቀሩ። በስልክ አግኝቼው የነበረው ሚኒስትር ግርማ ብሩ "ደሀ ዘመም (pro poor) መሆናችን ሰላልገባው አስገራሚ ህዝብ ምን እጽፉለሁ?" አለኝ። አባዱላ ደግሞ ስሜን እየጠራ "መድረክ ላይ አጠገቤ የተቀመጥከው አንተ ስለሆንክ በአዲሳባኛ ጻፈው!" በማለት አሳስቆ ስልኩን ዘጋው። አባዱላ እውነቱን ነበር! አዲሳአባኛ ይቸግረዋል።

እነዚህ ከፍተኛ የኢህአዴግ አመራሮች ትዝብታቸውን ያላኩበት ምክንያት ግልፅ ነበር። ከህዝቡ የተነሱት ጥያቄዎች በምንም መልኩ ህዝቡ በምርጫ 97 የሰጠው ድምፅ በመርህ ላይ የተመሰረተ እንጂ የተቃውሞ ድምፅ (Protesting vote) እንዳልሆነ ተገንዝበዋል። በተደጋጋሚ የቅንጅት አመራሮች አላጠፉም፣ ንፁህን ናቸው የሚል የማያወላዳ አቋም የህዝቡ እንደሆነ ተረድተዋል። ከዛም አልፎ ህዝቡ በእነሱ ፉንታ የኢትዮጵያን ህዝብ ሰብስባችሁ እሰሩ ሲል እንደነበር ጆሮአቸው እስኪተላ አዳምጠዋል። ...ህዝቡ ወደ ምርጫ መውጣቱና የልቡን በመምረጡ እንደተፀፀተና በሚያስደነግጥ ሁኔታ ኢህአዴግ ይቅርታ ያድርግልን እንዳለ ተመልክተዋል። ..."ለገሰ ዜናዊ የእግዜር ታናሽ ወንድም የዛሬን ማርልኝ የነገን አልመርጥም!" የምትል ስንኝ በየአዳራሹ እንደ መንፈስ የተበተነ እስኪመስል ተደጋግሞ ሲሰተጋባ እንደነበር አይተዋል።... ነዋሪው በምርጫ ማግስት የተዘረፈው የህዝብ ንብረት ይመለስ፣ ወንጀለኞችም ለፍርድ ይቅረቡ ማለቱን ሰምተዋል። ይህቺ ህዝቡ የወረወራት ጦር ከአቶ መለስ ጀምሮ እያንዳንዳቸውን እንደሚነካ ጠንቅቀው ያውቁታል።

የትምህርት ምክትል ሚኒስትሩን ሪፓርት ሀላቄ አንገቱን እየነቀነቀና እየሳቀ ለእኔና ለፀጋዬ አንድ አንድ ኮፒ ሰጥቶን ሄደ።

በተሰቀለው!!

ዶክተር አድሀኖም እውነት ዶክተር ነው? የትምህርት ሚኒስቴር የሚመራው በእንደዚህ አይነት በህልሙ በሚያየው ቅዠት የሚኖር ሰው ነው? የዶክተርነት ማእረግ የሚገፈፍ ቢሆን እምዬ ኢህአዴግ ስንት ታጣ ነበር? ...እኔና ፀጋዬ የዶክተር አድሀኖምን ሀያ ገጽ ምልከታ እየሳቅን፣ እየተናደድንና አያዘንን አነበብነው።

እነሆ! የፈላስፉው ዶክተር ጥናታዊ ጽሁፍ ማጠቃለያ እንዲህ ይላል፣

"... በአዲሳባ ህዝብና ኢህአዴግ መካከል ያለው ግንኙነት በሁለት እጅግ በሚዋደዱ ፍቅረኞሞች (ኢያጐና ዴዝዲሞና) መካከል እንዳለው ግንኙነት ሊመሰል ይችላል። አንዱ ያለሌላኛው መኖር አይችልም። አንዱ ለሌላው የደስታ፣ ሀሴትና ህልውና ምንጭ ነው። እጅግ በሚዋደዱ ፍቅረኞሞች መካከል እርኩስ መንፈስ ለመግባት ጥረት ማድረጉ አይቀርም። ይህ እኩይ መንፈስ ትንሿንም ክፍተት እየተጠቀመ ተገንበቶ የቆየውን ፍቅር ጭላሽት

ለመቀባት ይፍጨረጨራል። በምርጫ 97 የሆነው ይህ ነው። ቅንጅት የሚባል የኢያጮ መንፈስ የአቴሎን ፍቅር፣ ጽናትና ታማኝነት (የአዲሳባ ህዝብ መሆኑ ነው!) አወናብዶ የተሳሳተ ውሳኔ እንዲወስን አድርጐት ነበር። የኢያጮ መንፈስ ከፍተኛ ጉዳት ሳያደርስ በእንጭጩ ቢቀጭም።"

***

የቤተ መንግስቱ ስብሰባ

የነዋሪዎች ውይይት በተካሄደ ሁለተኛው ሳምንት መድረኩን የመሩት ሚኒስትሮችና ከፍተኛ ካድሬዎች በተገኙበት ከአቶ መለስ ጋር ለመገምገም ጥሪ ተላለፈ። እኔና ፀጋዬ ሌላ ህሊና ከሚፈትን ድርጊት ጋር ተቆጠጥን። ያዘጋጀነውን ባለ አርባ ገጽ ሪፓርት በረከት ጋር ሲደርስ ግልብጥብጡ ወጥቶ ወደ ሁለት ገጽ አጠረ። ከመለስ ጋር በሚኖረው ስብሰባ ህላዌ ሁለት ገጿን እንደሚያቀርብ ተነገረን። አስቀድሞ ለመለስ እንደተላከለት ሰማን።

ቀኑ ደርሶ ቤተ መንግስት ሄድን። ከህወሀት ዶክተር ቴድሮስ አድሀኖም፣ ዶክተር አድሀኖም እና አርከበ እቁባይ ተገኝተዋል። ከአህዴድ አባዱላ፣ ግርማ ብሩ፣ ጁነዲን ሰዶ፣ኩማ ደመቅሳና አስቴር ማሞ ተገኝተዋል። ከብአዴን በረከት፣ህላዌ፣ ታደሰ ጥንቅሹ እና አዲሱ ለገሰ፣ ከደኢህዴን ደግሞ ሀይለማርያም፣ ተሾመ ቶጋና ሞፈርያት ታድመዋል። አቶ መለስ የስብሰባውን አጀንዳ ከተናገረ በኋላ ሪፓርቱን ቢያነበውም መነሻ ሀሳቦች የከተማው ኢህአዴግ ከንፍ እንድናቀርብ እድል ሰጠን።

ህላዌ አፉን በመሀረቡ እየጠራረገ፣

"በመጀመሪያ ከሪፓርቶቹ ማረጋገጥ የቻልነውና የገመገምነው በስብሰባው የተገኙት ሰዎች ነዋሪውን የሚወክሉ መሆናቸውን ነው።" በማለት የመጀመሪያውን ድምዳሜ አስቀመጠ። ባለስልጣናትም ድምዳሜውን የሚያጠናክሩ አስተያየቶችን ሰጡ። በዚሁ ውሳኔ ተጠናቀቀ።

ህላዌ በድጋሚ ጉሮሮውን ስሎ፣

"ሁለተኛው ድምዳሜ ከስብሰባው ማረጋገጥ የተቻለው የአዲሳአባ ህዝብ ተቃዋሚን የመረጠው ኢህአዴግ ላይ ያለውን ቅሬታ ለመግለጽ እንጂ (protesting vote) ለተቃዋሚዎች በመርህ ላይ የተመሰረተና ከልብ የመነጨ ድጋፍ ስላለው እንዳልሆነ ተረጋግጧል። ህዝቡ ኢህአዴግ ላይ ያሳረፈው የተቃውሞ ካርድ እንጂ ለቅንጅት በተሰጠ የድጋፍ ድምፅ አይደለም።" በማለት ተናገረ። አስከትሎም ባለስልጣናት የህላዌን ሀሳብ የሚያጠናክሩ አስተያየቶች ሰጡ። እነዚህም ነዋሪው በህገመንግስቱ፣ በህዝቦች ያልተገደበ መብት ላይ፣ በምንነነባው የዲሞክራሲያዊ ስርአት፣ በፓሊሲና ስትራቴጂዎቻችን ላይ ልዩነት

አላነሳም የሚሉ ቁምነገሮችን የሚዳስሱ ነበሩ። አቶ መለስም ቢሆን የተለየ ሀሳብ አላነሳም። የሚያሳዝነው ነገር ከህዝቡ ጋር በተደረገው ውይይት የህገመንግስትም ሆነ የፓሊሲ ጥያቄዎች በአጀንዳነት አልተያዘም። በጣም እርግጠኛ ሆኖ መናገር የምችለው ለአዲሳአባ ህዝብ "አንቀፅ 39 ከህገመንግስቱ ይውጣ" የሚል ጥያቄ ቢቀርብለት 90% ድጋፍ ይሰጣል። በካድሬነት ዘመኔ ያሳለፍኳቸው የነዋሪ፣ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ ተማሪዎች፣ መምህራን መድረኮች ይህን ስለሚያሳዩ።

ሶስተኛውን ማጠቃለያ ህላዌ እንዲህ በማለት ተናገረ፣ "የታሰሩ የቅንጅት መሪዎች ጥፋት እንደሰሩ ብናውቅም የገፉናቸው እኛ ስለሆንን ይቅርታ አድርጋችሁላቸው የህሊና ረፍት ስጡን የሚል እንደሆነ አይተናል። የአዲሳባ ህዝብ የቅንጅት መሪዎች ይፈቱልን ሲል ወንጀል አልሰሩም ከሚል ሳይሆን መንስኤው እኛ ነን ከሚል የሚመነጭ ነበር።"

በዚህ ዙሪያ ብዙዎቹ ባለስልጣናት ተመሳሳይ አስተያየት ሰጡ። ከሁሉም የተለየው ጁነዲን ነበር። ሞገደኛው ጁነዲን እድል ሳይሰጠው፣

"እኔ በመራሁት መድረክ ህላዌ እንደሚያቀርበው አይደለም። መሪዎቻችንን ያለ ቅድመ ሁኔታ ፍቱልን ብለውኛል" በማለት እውነተኛ የህዝብ ስሜት ተናገረ። አቶ መለስ አስተያየት ሳይሰጥ ህላዌን እንዲቀጥል ምልክት ሰጠው። ህላዌ እንዲህ በማለት ተናገረ፣

"በአራተኛ ደረጃ በኑሮ ውድነቱ የከተማው ህዝብ ተጐድቷል። ድጋፍ ከመንግስት ይፈልጋል የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሰናል።" የሚል አስተያየት አቀረበ። ከዚህ አንፃር በአመራሮቹ መካከል ልዩነት አልነበረም። አቶ መለስም ይህን ተቀብሎ መፍትሄው ከካናዳ በሚገዛ ስንዴ ረገብ ማድረግ እንደሆነ አስረዳ። የዛኑ እለት ከመቶ ሚሊዮን ብር በላይ በአስቸኳይ ወጪ ሆኖ ስንዴ እንዲገዛ ውሳኔ ተላለፈ።

ህላዌ የመጨረሻውን ማጠቃለያ በሚከተለው መልኩ አቀረበ፣

"በመጨረሻ ከሁሉም የቀበሌ ኮንፍረንሶች ሪፓርት ማየት የተቻለው ህዝቡ ባላአደራ እና ኢህአዴግን ነጥሎ ማየት አልፈለገም። በአንድ በኩል አዲስ ምርጫ እስኪካሄድ ኢህአዴግ እንዲቆጣጠረው የመፈለግ፣ በሌላ በኩል የባላደራውን ብቃት የመጠራጠር ሁኔታ ታይቷል።"

የህላዌን ማጠቃለያ ተከትሎ አቶ መለስ እንዲህ በማለት አስተያየት ሰጠ፣

"ለአጭር ጊዜ ባላአደራን እና ኢህአዴግን ነጣጥሎ ያለማየት ችግር ማጋጠሙ አይቀርም። ከመካከለኛ እና ረጅም ጊዜ አኳያ ይህ አመለካከት መስበር ይኖርበታል። እነ ህላዌ አንዱ ስራችሁ ይህ ሊሆን ይገባል። ኢህአዴግ

በመደበኛ ስራቸው ጣልቃ እንደማይገባ፣ ለበጐም ሆነ መጥፎ ስራቸው ሀላፊነቱን የሚወስዱት እነሱ እንደሚሆኑ ማሳየት ያስፈልጋል። ድርጅታዊ ተጠያቂነት የሌለው አካል አዲሳአባን እየመራ የመልካም አስተዳደር እጦት ማጋጠሙ አይቀርም።"

ርግጥም አቶ መለስ እንዳለው እስከ ምርጫ 2000 ድረስ የከተማው ኢህአዴግ ክንፍ ከቀረጻቸው መልእክቶች ውስጥ፣

"ኢህአዴግና ባላአደራ አንድ አይደለንም። የአዲሳአባ ነዋሪዎች እንደሌሎች የሀገራችን ከተሞች የመልካም አስተዳደር መሻሻል ያላሳየው ድርጅታዊ ተጠያቂነት በሌላቸው ቴክኖክራቶች በመመራቱ ነው። በቀጣዩ ምርጫ ድርጅታዊ ተጠያቂነት እና ቁርጠኝነት ያለው ፓርቲ ከመረጣችሁ ችግሩ ከስሩ ይነቀላል።" የሚል ነበር። ይህ ቃል ኢህአዴግ ለምርጫ 2000 ከተጠቀመበት መቀስቀሻ አንዱ የነበረ ሲሆን መልእክቱ የሚተላለፈው ደግሞ በባላደራ ወጪ ነበር።

ክፍለ ሰድስት: ምርጫ 2000

ምእራፍ ሃያ ሁለት

የ2000 ምርጫ አቅጣጫዎች

"በኢትዮጵያ የመድበለ ፓርቲ ዴሞክራሲ ተስፋ የለውም።"
ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ

በ2000 ዓ.ም በአዲሳባ ዳግም ምርጫ እንደሚካሄድ ከመታወጁ አንድ አመት በፊት በኢህአዴግ ቢሮ ምርጫውን ለማሸነፍ የሚያስችሉ ዝግጅቶች ተደረጉ። እነዚህ ቅድመ ዝግጅቶች ሁለት የተሳሰሩ አላማ ነበራቸው:-በምርጫ 97 ለምን ተሸነፍን፣ እንደዛ አይነት መጥፎ ታሪክ እንዳይደገም ምን ማድረግ ይኖርብናል የሚል እና ቀጣዩን ምርጫ በመቶ ፐርሰንት ለማሸነፍ ምን ማድረግ ይጠበቅብናል? የሚሉ ምላሾችን የሚሰጡ። አላማዎቹን ለማሳከት የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችን ነድፈው እንዲመጡ ሁለት ቡድኖች ተቋቋሙ።

የመጀመሪያው ቡድን በአቶ ካሚል የሚመራ ሆኖ በአባልነት እኔና ፀጋዬ ተጨመርን። ቡድኑ ምርጫ 97 በፓርቲው ላይ ያሳረፉትውን መጥፎ አሻራዎች ለማስቀረት ምን መደረግ አለበት የሚለውን እንዲያጠና ተደረገ። ባለፈው ምርጫ በኢህአዴግና በመንግስት ተከስተዋል የተባሉ ድክመቶችን በመለየት ይዘን እንድንመጣ ተነገረን። የጥናቱ ዳራ ከቅድመ እስከ ድህረ ምርጫ 97 እንዲሆን ተደረገ።

ሁሉን አሚጦ የሚወስደውን ስትራቴጂ የሚቀይሰው ደግሚ በህላዌ የሚመራ ሆኖ የኢህአዴግ ቢሮ ፕሮፐጋንዳ ካድሬዎችን የሚያቅፍ እንዲሆን ተደረገ። ጥናቱን በአንድ ወር አጠናቀን ለአቶ መለስ ከማቅረባችን በፊት ከበረከት ጋር ለመገምገም የሁለት ሳምንት ቀጠሮ ያዝን።

እነሆ! ቀኑ ደረሶ አቶ በረከት ቢሮ ሄድን።

በዚህ ስብሰባ የተወሰኑት ውሳኔዎች በመዲናይቱ ብቻ ሳይሆን በመላ ኢትዮጵያ የሚካሄደውን የዲሞክራሲ ስርአት ግንባታ የማይሞከርበት ደረጃ አደረሱት። የመድበለ ፓርቲ ስርአት ያበቃለት የሞኝ ለቅሶ ሆነ። የሲቪል ሰርቪሱ ገለልተኝነት የወረቀት አንበሳ ሆኖ ቀረ። መንግስትና ድርጅት የማይነጣጠሉበት ሁኔታ ተፈጠረ። ውሳኔዎቹ በፓርቲ ደረጃም ኢህአዴግ

የይዘት ለውጥ እንዲያመጣ አድርገውታል። ፓርቲው የመርህና የአስተሳሰብ ቀውስ አጋጥሞታል። የድርጅቱ ምሰሶ የሆነው "አብዮታዊነት" ጓዙን ጠቅልሎ ከኢህአዴግ ተሰናብቷል። የድርጅቱ ርእዮት ለሶስተኛ ጊዜ መሰረታዊ በሆነ መንገድ ተገላብጧል። የፓርቲው የፓለቲካና ፕሮፓጋንዳ ስራ በ80% ቀኝ ወደ ኃላ ዞሯል። የኢህአዴግ ጉዞ፣ አላማና የመጨረሻ ግብ እንኳን ለካድሬው ለፈጣሪዎቹም ግራ የሚያጋባ ሆኗል።

ወደ አባላት ከተወረደ ደግሞ ሁኔታው እየከፉ ይሔዳል። በአንድ ፓርቲ ውስጥ እርስ በራሱ የሚጣረሱ ሶስት አይነት አባላት ተፈጥረዋል። የአባላት ተልእኮ ፀረ ኢህአዴግ ሰዎችን ከመከታተልና ገንዘብ ከማሰባሰብ በላይ የማይዘልበት ደረጃ ደርሷል። በእነዚህ አባላት አማካኝነት ድርጅቱ በተዘዋዋሪ መንገድ በየአመቱ ከሁለት ቢሊዮን ያላነሰ ገንዘብ ከመንግስትና ህዝብ የሚወስድበት ስርአት እንዲገነባ አድርጓል።ኢህአዴግ በአለም ውስጥ ካሉ ሀብታም የቢዝነስ ኮርፖሬት ድርጅቶች በመጀመሪያዎቹ ረድፍ እንዲሰለፍ ሆኗል።

ይህ ሁኔታ በኢህአዴግና በተቃዋሚዎች መካከል ያለውን የሰው ሀይል የውቅያኖስና የኩሬ ያህል ልዩነት እንዲኖረው አድርጓል።ገዥው ፓርቲ ከ6.1ሚሊዮን በላይ አባላት በመያዝ በአለም ተወዳዳሪ የሌለው ድርጅት ሆኗል። ከገንዘብም አንፃር ኢህአዴግና ተቃዋሚ ፓርቲዎች ልዩነታቸው የትየለሌ ሆኗል። አውራ ፓርቲው በቢሊዮን የሚጠጋ ብር አውጥቶ የስልጠና፣ ባህልና ሙዚየም ሊያስገነባ እየተጋ ባለበት ሁኔታ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ለጽህፈት ቤታቸው ኪራይ መክፈል አቅቷቸው ይንገታገታሉ። አንዳንዶቹ መስመራቸውን "ታማኝ ተቃዋሚ" በሚል አስተካክለው ከኢህአዴግ በሚወረወርላቸው መና ይግተረተራሉ። ጉርና ሆዱ ኢህአዴግ ምርጫ ቦርድ የሚሰጠውን ገንዘብ በመናቅ ለታማኝ ተቃዋሚዎቹ ለሚላቸው እስከ ማከፋፈል ደርሷል (በምርጫ 2002 ምርጫ ቦርድ ለፓለቲካ ፓርቲዎች ከመደበው 90% ኢህአዴግ መውሰዱን ልብ ይሏል።)

አርቆ ለተመለከተው ከላይ የተጠቀሱት ውጤቶች የኢህአዴግን የማይቀረውን የተፈጥሮ ሞት እያፋጠኑት መሆኑን ይሆናል። ድርጊቶቹና ውጤታቸው ፓርቲው ወደመቃብር በፍጥነት እየተወረወረ መሆኑን የሚያመላክቱ ናቸው። በማግበስበሱ ምክንያት ወደ ማሰሮ ሆድነት የተቀየረው የኢህአዴግ መዋቅር ትንሽ ሽንቁር ሲያጋጥመው የሚከሰተው አደጋ አስከፊ ሊሆን ይችላል። እንደ ፀሀፊው እምነት አደጋውም ከውስጥ ወደ ውጭ ይፈሳል። ከድርጅት አልፎ የሀገሪቱ ህልውና ላይ የሚያንጣበብ ይሆናል። በተግባርም እየታየ ያለው ይህ ነው።

ወደዚህ ሀገራዊ አደጋ የሚያመጣ የኢህአዴግ ነጫጭ ዝሆኖች ታሪክ ከመግባታችን በፊት በአቶ ካሚል መራሹ ቡድን የጥናት ውጤትና በአቶ በረከት በተጻፈው የሁለት ምርጫዎች ወግ መጽሐፍ መካከል ያለውን ተቃርኖ ወደ መመልከት እንሸጋገር።

የምርጫ 97 ሽንፈት ምክንያቶች፣

የህላዌና የካሚል ቡድን አባላት የጥናት ውጤታችንን ይዘን አቶ በረከት ቢሮ ተገኝተናል። ቅድሚያ የተሰጠው በካሚል ለተመራው የእኛ ቡድን ነበር። ጥናቱን የሰራነው ለአባላት መጠይቆችን በማውረድ፣ በየቀበሌው የቡድን ውይይቶችን በመክፈት፣ ልማታዊ ምሁራንና ባለሀብቶችን በማሳተፍ እንደሆነ ገለጽን። ከቀረቡት አስተያየቶች በመነሳት ኢህአዴግ በምርጫ 97 የፈፀማቸውን ጥፋቶች በሶስት በመክፈል አቀረብን። በምረጡኝ ዘመቻ ፣በምርጫ ምልክትና ሌሎች ቴክኒካል ጉዳዮች በሚል።

በምርጫ ክርክር ወቅት ኢህአዴግ ባልተዘጋጀበት ሁኔታ በሩን መበርገድ አልነበረበትም። ግንቦት ለሚካሄድ ምርጫ መስከረም ጀምሮ የሚዲያ ክርክር መካሄዱ ጥፋት ነበር። በክርክሩ ወቅት ኢህአዴግን ወክለው የቀረቡ ካድሬዎች ደካማ የፓለቲካ ብቃት ማሳየታቸው ሳያንስ ሲጠቀሙባቸው የነበሩት አደገኛ ቃላት ("ኢንተርሀምዌይ" ልብ ይሏል!) የምርጫው ውጤት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድረዋል። በምረጡኝ ዘመቻ ወቅት ኢህአዴግን ምረጡ ብሎ በሙሉ ወኔና ፍላጎት የተንቀሳቀሰ አጩና አባል አልነበረም። በምርጫው ዋዜማ ሚያዝያ 30 የተካሄደው የተቃዋሚዎች የድጋፍ ሰልፍ መፈቀድ አልነበረበትም... የሚሉ ቁምነገሮች ላይ መነሻ ሀሳብ አቀረብን።

አቶ በረከት ጥናቱ ትክክል መሆኑን ለማሳየት በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ አሰደማሚ መገለጫዎችን አቀረበ።

አፉቸንን አስከፈተን!...

ጉድ ሳይሰማ እንዲሉ ግምገማው የተጻፈበት ብእር ሳይደርቅ ተገላበጠ "የሁለት ምርጫዎች ወግ" በሚል በመጽሐፍ መልክ ተዘጋጀ። ለህዝብም ይፉ ሆነ። ከአቶ በረከት ጋር አብረን የነበርን ካድሬዎች ይህንን ሲፅፍ ምን ያህል ከራሱ ህሊና ጋር እንደተጣላ ለመገመት አንቸገርም። በታሪኩ ውስጥ ያለፉና አብረውት ያሉ ሰዎችም ቢሆኑ "ኧረ እዚህ ጋር ያለው ሀቅ ተዛብቶ ቀርቧል" አለማለታቸው አሳዛኝ ነው። ህዝብ እውነትን የማወቅ መብት እንዳለው መገንዘብን ለጊዜው እንተወው። ነገር ግን የትላንትና ታሪካችን ውስጥ ይህ ድክመት ነበረብን ብሎ መናገር ምን ያህል የህዝብ ከበሬታን እንደሚያስገኝ

አለመረዳት እንዴት ያቅታል? በታሪኩ ውስጥ አብረውን ያሳለፉ ሰዎች አንድ ቀን እውነቱን ሊያወጡብን ይችሉ ይሆናል ብሎ አለማሰብስ ምን የሚሉት ንቀት ነው? በዝምታ ውስጥ መኖር አላዋቂነት አይደለም። እንደዚህ አይነት አርምሞን የሚነካ ሀሳብ ተጽፎ ዝም ማለት ደግሞ ሌላ የህሊና ሸክም ይፈጥራል። እውነትን እስክ መቼ ሸሽተናት እንኖራለን የሚል ጥያቄ ያስነሳል። ያውም አንዳንዶቹ ፀሀይ የሞቃቸው ሆነው።

***

የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጾች፣

አቶ በረከት በመራው ግምገማ ቅድሚያ ትኩረት ያገኘው የምርጫ ክርክሩ ነበር። በክርክሩ ወቅት በሚያስደነግጥ ሁኔታ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ስዩም መስፍን " ኢንተርሀምዌይ " የምትል መርዘኛ ቃላት ወጣች። ይህ ሀገር የሚያጫርስ ቃላት ያውም ከአንድ የውጭ ጉዳይ የበላይ ካድሬ መመንጨቱ ሆን ተብሎ የታሰበበት መሆኑ መነገር ተጀመረ።በዚህም ህዝቡ ቁጣውን ገልፀ። የኢህአዴግ ቱባ ባለስልጣናት ገመና ተዘረገፈ። በተከታታይ ፓለቲካዊ ክርክር ሳይሆን በስድብ የታጨቁ ዛቻዎችን በማሰማታቸው ህዝቡ ናቀን። ሁኔታው ከህዝቡ አልፎ የድርጅቱ ደጋፊዎችን ሳይቀር የሚያሸሽ ሆነ።

አቶ በረከት በግምገማው ወቅት፣

"እንደዚህ አይነት ህዝብን የሚያስኩርፉ አላስፈላጊ ቃላት መጠቀም አልነበረብንም። ኢህአዴግን ከሚደግፉ ዲፕሎማቶች ሳይቀር መሳሳታችንን ነግረውናል። የምርጫ 97 የመሸነፍ አንዱ ምክንያትም ራሳችንን መሸጥ አቅቶን የማይረባ የቃላት ጨዋታ መጫወታችን ነው" ብሎ ተናገረ።

ከዓመታት በኃላ የወጣችው "የሁለት ምርጫዎች ወግ" ይህንን ሀቅ መቀበል አልፈለገችም። እንደተለመደው የማላከክ አመክንዮ ተጠቅማለች። እንዲህ በማለት፣

"...የአቶ በድሩ ንግግር እንደተላለፈ ኢህአዴግ ወደኋላ ተመልሶ የቅንጅት መሪዎችን አስተሳሰብ ለማሳየት የተጠቀመበት አገላለፅ ትክክል እንደነበር ለማመላከት ሞከረ። ኢህአዴግ በምረጡኝ ቅስቀሳ ሂደት ይህን አስተሳሰብ በሚወክሉ አገላለጾች በመጠቀም ጉዳዩን ለማስገንዘብ ጥረት አድርጉ የነበረ ቢሆንም የሚሰማው ግን አላገኘም ነበር።" ይላል።

በዚህ አርፍተ ነገር ውስጥ ብዙ የታጨቁ ቁምነገሮች አሉ። በመጀመሪያ የሚታየው አቶ በረከት ስህተትን በስህተት በማረም ራስን ነፃ የማውጣት አካሄድ መከተሉን ይሆናል። የገሎ መዳን ስትራቴጂ... አቶ በድሩን

ገሎ፣ ኢህአዴግን ነፃ ማውጣት።

አቶ በድሩ አደም ቀድሞ ከኢህአዴግ ጋር ያላቸው ቅርርብ የአደባባይ ሚስጥር ነው። ሰውየው በኦሮሚያ ዞኖች ለምርጫ ሲወዳደሩ በአቶ መለስ ቀጥተኛ ትእዛዝ ወንበር ይለቀቅላቸዋል። ያለ ኢህአዴግ ተወዳዳሪ አሊያም በደካማ ተፎካካሪ ይቀርባሉ። በምርጫ ጣቢያው ያሉ የኢህአዴግ አባላት እሳቸውን ለማስመረጥ ይሰራሉ። ፓርላማ በግል እጩነት ከገቡም በኃላ የፓሲሲ አጀንዳ ስለሌላቸው ከገኑ ድጋፍ ይደረግላቸዋል። ሸንጐውን ያሞቁታል። በእሳቸው ሊቀርቡ የሚገባቸው የአፈጻጸም ግድፈቶችና መመታት ያለባቸው የኢህአዴግ ባለስልጣናት ዶሴ አውቀውትም ሆነ ሳያውቁት እንዲደርሳቸው ይደረጋል። እሳቸውም የግለሰብ አጀንዳና ቅሬታ ሳይቀር የተከበረው ፓርላማ ድረስ ይዘው ይገባሉ። አቶ በድሩ በመጨረሻው የፓርላማ ዘመናቸው ወደ ግለሰብ ጉዳይ አስፈጻሚነት ተንሸራተው ነበር። በወቅቱ እኔ በነበርኩበት ዞን ከአንዴም ሁለቴ የግለሰብ ፉይል ይዘው መጥተው ተጨቃጭቀዋል።

በምርጫ 97 ዋዜማ ሚያዝያ 30 በተካሄደው ሰላማዊ ሰልፍ፣ "ግንቦት ሰባት ቀን ኢህአድጐችን ወደ መጡበት እንመልሳለን!" በማለት መርዛማ ንግግር አደረጉ። ይህ ሾላ በድፍኑ የሆነ ቃል ምንም አይነት ምክንያት ሊቀርብለት የማይችል አባባል ነበር።

እኔ ኢህአዴግ ነበርኩ። ያውም እውነቱ እስኪገለጥልኝ ድረስ በእምነት የምተጋ ካድሬ። ከራሴ አልፌ በአስር ሺዎች የሚጠጉ የዩንቨርስቲ ተማሪዎችን በአብዮታዊ ዲሞክራሲ በማጥመቅ ኢህአዴግ አድርጌያለሁ። ብዙዎቹ በመንግስትና ድርጅት ስልጣን ላይ ተቀምጠዋል። እነዚህ ሺዎች የአቶ በድሩ ልጆች አሊያም የልጅ ልጆች ናቸው። እናስ ወዴት ይሂዱ? የተፈጠሩት እሳቸው ከተፈጠሩባት ኢትዮጵያ ከምትባል ሀገር ነው። የኔ ቢጤዎቹ ደግሞ እትብታችን የተቀበረው ያቺ መከራዋ በማያልቅ ባለቤት የሌላት (ነዋሪ አልባ!) ከተማ ነው... ወዴት እንሂድ?...

አቶ በድሩ ከአፍ ወለምታ በዘለለ ተሳስተዋል። የአንድ ፓለቲካ መሪ ብቃት ከሚለካበት ነገር ዋነኛው ሰውንና አመለካከትን የመለየት ባህሪው ነው። ርግጥ የኢትዮጵያ ፓለቲካ ጨፍልቆ የሚያይ ስለሆነ እሳቸው ተለይተው ላይፈረድባቸው ይችላል። ይህም ሆኖ የግለሰቡ ስህተት በምንም መልኩ ኢህአዴግ "ኢንተርሀምዌይ" ብሎ የገለፀውን ቃል ትክክለኛነት የሚያሳይ አይደለም። በኢህአዴግ ውስጠ ድርጅት ግምገማ "ልክ አልነበረንም! ይህ አባባላችን የሩዋንዳውን እልቂት እንደመገፋት ይቆጠራል" በማለት ድምዳሜ

ላይ ተደርሷል። ውሳኔው ለኢትዮጵያ ህዝብ በይፋ ቀርቦ ይቅርታ መጠየቅ ነበረበት።

በነገራችን ላይ አቶ በረከት ህሊናው ያላመነበት ነገር እንደፃፈ የሚያስታውቀ ነገር ከመጽሐፉ ለማየት ይቻላል። ይህቺን "ኢንተርሀምዌይ" የምትል መርዘኛ ቃል በመጽሐፉ ላይ አንድም ቦታ አልአሰፈረም። በደምሳሳው "የተቃዋሚን አስተሳሰብ በሚወክሉ..." የሚል ቃላትን ለመጠቀም ተገዷል። የኢንተርሀምዌይ መዘዝ ብዙ ነው። በተለይ ታሪካዊ አመጣጡን ዞር ብሎ ለተመለከተው እጅ የሚቀሰረው ማን ላይ እንደሚሆን ግልጽ ነው።

በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ቀጥሎ የምናገኘው ቁምነገር አቶ በረከት ህዝቡ መሳሳቱን በተዘዋዋሪ የተናገረበትን ሁኔታ ነው (የሐመሩ(ሐ) ፓለቲካ።) ህዝቡ ትክክል እንዳልነበረና "ብንነግራችሁ አልሰማን አላችሁ" በማለት የገለፀበትን ሁኔታ እናገኛለን።

ሁሉም እንደሚያስታውሰው የኢትዮጵያ ህዝብ ሰላማዊ የምርጫ ውድድር ማየት እንደሚፈልግ ደጋግሞ ተናግሯል። በሁሉም ወገኖች የምርጫ ክርክሩን ወደ አስደንጋጭና አስፈሪ መድረክነት የሚገለብጡ ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ አሳስቧል። የእምነት ተቋማት ሳይቀሩ የትምህርታቸውን ማሳረጊያ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ከቃላት ጦርነትና መገታተር ወጥተው ለሀገር በሚበጅ መልኩ እንዲፎካከሩ ተማጽነዋል። የሀይማኖት አባቶች "ኢንተርሀምዌይም" ሆነ "ወደ መጡበት እንመልሳለን" የሚሉት ቃላት በጋራ መስራትንና መከባበርን ስለማያመጡ ህዝቡ እንዲያወግዛቸው ጥሪ አስተላልፈዋል። አቶ በረከት ይህንን እውነት እንዳላለፈበት ሁሉ የኢህአዴግን የሁልጊዜም ትክክለኛነት ለማሳየት "ሰሚ ጆሮ አላገኘንም" በማለት ህዝቡን ይወቅሳል።

አቶ መለስ የሁለት ምርጫዎች ወግ ከመታተሙ በፊት አስተያየት እንደሰጠው በረከት በምስጋና ክፍሉ ነግሮናል። የአቶ መለስ አስተያየት ከዘነጋቸው ነገሮች አንዱ በግንቦት 1997 ለአብዮታዊ ዲሞክራሲ ልዩ እትም የሰጠውን መግለጫ ነበር። በዚህ እትም አቶ መለስ፣ "... በምርጫው ክርክር በነበሩን አንዳንድ አቀራረቦች (ኢንተርሀምዌይ) ላይ ስህተቶች እንደነበሩብን ተገንዝበናል" በማለት ስህተቱን አምኖ ነበር።

***

ሌላው በቡድኑ ጥናትም ሆነ በአቶ በረከት አስተያየት የቀረበው የኢህአዴግ ከፍተኛ ካድሬዎች በምርጫ 97 ክርክር ወቅት ያሳዩት ደካማ ብቃት ነበር። በሚዲያ ክርክር ወቅት ኢህአዴግን ወክለው የቀረቡ ባለስልጣናት

ያሳዬት አሳፉሪ የፓለቲካ ብቃት ምርጫውን በዝረራ እንድንወጣ አስተዋጽኦ አበርክቷል የሚል ነበር። አቶ በረከት ካድሬዎች የብቃት ማነስ ብቻ ሳይሆን በአቀራረብ ደረጃ በጣም አሰልቺና የህዝብን ፍላጐት ማእከል ያላደረጉ በመሆኑ መራጩ ህዝብ ፊቱን ከኢህአዴግ እንዲያዞር አስተዋጽኦ አድርጓል በማለት የወቅቱን ሁኔታ በሰፊው አብራርቷል። በመሆኑም በምርጫ ክርክሩ መሸነፋችን የቅድሚያ ውጤቱን የሚያመላክቱ ነበር ብሏል። በተቃራኒው ከሶስት አመት በኃላ በሁለት ምርጫዎች ወግ መጽሐፍ ላይ የክርክሮቹን ፉይዳ በማሳነስ እንደሚከተለው ሰፍሮ እናገኛለን፣

"...በአገራችን የሚካሄዱ የምርጫ ክርክሮች ነገር ከሚሚቅ ባለፈ የምርጫ ውጤትን የሚወስኑበት ደረጃ ላይ የደረሱ አይደሉም። በመሆኑም በምርጫ 97 የክርክሮች ፉይዳ የምርጫውን ውጤት አስከመወሰን የደረሰ ነበር ሊባል አይችልም።"

***

ታታሪዋ ንብና የህዳሴው ቾቦ!!

የአቶ ካሚል ቡድን ቀጥሎ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ኢህአዴግ ለረጅም ዓመታት ሲጠቀምባት የነበረችውን የምርጫ ምልክት "ንብ" የተመለከተ ነበር። በምርጫ 97 ቅስቀሳ ወቅት ህዝቡ የኢህአዴግ አባላትና አጨዎችን በተመለከተ ቁጥር "ዝንቦቹ መጡ!" በማለት በግልፅ ተናግሯል። በሚያዝያ 30 በተደረገው ሰላማዊ ሰልፍ "ዝንብ! ዝንብ! ዝንብ!" የሚሉ በዜማ የታጀቡ የተቃውሞ ድምጾች ጐልተው ተሰምተዋል። ከምርጫው ውጤት በኋላ ለምን ተሸነፍን የሚለውን በተደራጀ መንገድ ለማወቅ በመላ ሀገሪቱ የአባላትና ካድሬ ስብሰባ ተደርጐ ነበር። እናም ታታሪዋ ንብ እጅ ተቀሰረባት።

አቶ በረከት የምልክት አመራረጣችን ችግር እንደነበረበት አረጋገጠ። ለቀጣይ ምርጫዎች ኢህአዴግ በሌላ ምልክት እንደሚቀርብ ተናገረ። ውሳኔውን ተከትሎ በሚሚያ፣ አካባቢና አዲሳባ ዳግም ምርጫ የኢህአዴግ የምርጫ ምልክት ወደ "ቾቦ" ተቀየረ። ለቾቦ ምልክትም የተለየ ትርጉም ተሰጠው። ይህም ሀገራችን ወደ አዲሱ ሚሊኒየም በታላቅ መንፈስ እየገባች ያለችው በመሪ ድርጅቱ ኢህአዴግ አማካኝነት እንደሆነና የህዳሴው ቾቦ በማይጠፉ መልኩ መለኮሱን ለማብሰር የሚል ነበር። የተለኮሰው ቾቦ እንደ አሎምፒክ ሁሉ በቅብብሎሽ ለዘላለም ይበራል በማለት የፓርቲው ምልክት ቾቦ ሆኖ ለሚቀጥሉት ረጅም አመታት ይቀጥላል የሚል ውሳኔ ተላለፈ።

በምርጫ ውድድሩም ኢህአዴግ ቾቦን ይዞ ብቅ አለ። በመንግስት ሚዲያዎችና የግል ፕሬሶች የኢህአዴግ የመወዳደሪያ ምልክት መቀየሩ የተለያዩ

መላምቶች ተሰጥተውበት ተዘገበ። አንዳንድ የተቃዋሚ አመራሮች "ምልክት በመቀየር ውስጣዊ ባህሪ አይቀየርም! "የሚሉ አስተያየቶችን ሰጡ። ልክ በሰገሌ ጊዜ "ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም" እንደተባለው። ምንም እንኳን ተቃዋሚዎች ራሳቸው በጐንዮሽ የቀድሞው ቅንጅት ምልክት የሆነችውን የጣት አርማ እንዲሰጣቸው ለኢህአዴግ ተማጽኖ ቢያቀርቡም። አቶ በረከት ይህንን ወደ ተግባር የተለወጠ እውነት እያወቀ በመጽሐፉ ላይ የ2000 ምርጫ በገለፀበት "ታሪክ ራሱን ደገመ ወይስ...?" በሚለው ርእስ ስር የሚከተለውን አስፍሮ እናገኛለን፣

"...ኢህአዴግ ለፈረንጆቹ በተናዳፊነት፣ ለኢትዮጵያውያን ደግሞ በታታሪነት የምትታወቀውን ንብ ይዞ ፣ተቃዋሚዎች ደግሞ መልኩ ቢለያይም የተለመደችውን ጣት ይዘው ቀርበዋል።... ንብም ሆነ ጣት፣ ፈረስም ሆነ መጽሐፍ የምርጫ 97 ተፎካካሪዎች የተጠቀሙባቸውን አልባሳት እንዳልቀየሩ አመላካች ነበር" ይላል።

መቼም የአዲሳባ ህዝብ ኢህአዴግ ላይ መቀለድ አያቆምና በአዲስቷ ምልክት "ችቦ" ላይም ተፊዘባታል። እስቲ አንዷን ብቻ ላውጋችሁ።

እንዲህ ነበር የሆነው፣

ለአባሎቻቸን የኢህአዴግ ምልክት ከእንግዲህ በኃላ "ችቦ" መሆኑን በመንገር የተለያዩ ፈጠራዎችን ተጠቅማችሁ አስተዋውቁ ብለን ስምሪት ሰጠን። የአጋጣሚ ነገር ሆኖ ምርጫ ቦርድ አሰርቶ የሰጠን ችቦ የአይስክሬም ቅርጽ የሚመስል ነበር። እናም ለፈጠራ የተፈጠሩት አባሎቻችን የምርጫው እለት ቅስቀሳቸው "አይስክሬሚን ልሳችሁ ውጡ!" የሚል ሆነ። በቂርቆስ የሚቀሰቅስ አንድ እሳት የላሰ ካድሬ በየቤቱ እያንኳኳ፣" የምርጫ ስአት እያለፈ ነው። ወጥታችሁ ኢህአዴግን ምረጡ!" እያለ ይቀሰቅሳል። አንድ እናት በአጠገቡ ሲያልፉ ጠጋ ብሎ፣

"ማዘር! እንዳይረሱ አይስክሬሚን ነው ልሰው የሚወጡት" ይላቸዋል። ማዘርም ዋዛ አይደሉምና፣

"አይ ልጄ! በባዶ ሆድ አይስክሬም? ቀኑን ሙሉ ከሚያስመልሰኝ እንደለመድኩት ጦሜን ብውል ይሻለኛል" አሉት። ጦም ውላ ያደረች የምርጫ ወረቀት ሳጥኑ ውስጥ አኑረው ሄዱ። ይህ ተግባር የአስር ሺህ እናቶች ሆኖ ዋለ።

***

የኃልዮሽ ጉዞ ...

በህላዌ ዮሴፍ የተመራው ሁለተኛ ቡድን የከተማው ብሎም የሀገሪቷን ምርጫ የሚመራበትን ስትራቴጂ በመንደፍ ለውይይት አቀረበ። ቡድኑ

ከእንግዲህ የሚካሄዱ ምርጫዎችን ሙሉ ለሙሉ አሸንፎ ለመውጣት የሚያስችል ግብ አስቀመጠ። ይህን ለማሳካት እንዲረዳ ሁለት የተቀናጁ አቅጣጫዎችን ቀረፀ። እነዚህም የህዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎ ማስፋት፣ በህብረተሰቡ ዘንድ ተሰሚነትና ተቀባይነት ያላቸውን አጩዎች መመልመልና ከምርጫው ሂደት ይልቅ ውጤቱ ላይ ማተኮር የሚሉ ነበሩ። እነዚህን አቅጣጫዎችና አፈጻጸማቸውን ጠለቅ ብሎ ለመረመራቸው የኢትዮጵያ ዲሞክራሲ ጉዞ በብዙ አመታት የኋሊት እንደተንሸራተተ መመልከት ይችላል። ኢህአዴግም ቢሆን ማንነቱን ያጣበት ሁኔታ የፈጠረ ነበር።

የኢህአዴግ ዲሞክራሲ ግንባታ በቅርጽ ሲታይ የታዋቂው ሳይኮሎጂስት አብርሀም ማስሎ የፍላጐት መሰላልን ይመስላል። በታችኛው ትሪያንግል ቀጥተኛ ዲሞክራሲ የሚል ስያሜ የተሰጠውን ባህሪያት የሚያሰፉ ሆኖ ወደ ላይ በተወጣ ቁጥር የግለሰቦችን ዘላለማዊነት የሚያረጋግጥ ይሆናል። የአንድ ፓርቲ የበላይነት በሰፈነበት ሁኔታ እንዲህ አይነት ስርአት መዘርጋት በህዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎ ስም በታችኛው መዋቅር የህዝብ ጩኸት የሚታፈንበት ይሆናል። ይህንን እንደ መደላድል በመውሰድ የፒራሚዱ ጫፍ ላይ ያሉት ሰዎች ራሳቸውን ወደ ጎኸ መደብ በመቀየር ፈላጭ ቆራጭ የሚሆኑበት ሁኔታ ይፈጥራሉ።

የህላዌ ቡድን "የህዝቦች ቀጥተኛ ተሳትፎ" የሚለውን ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ በማጣቀስ በመካከለኛና ዝቅተኛ እርከን ያሉትን የምክር ቤቶች አባላት ብዛት ለማሳደግ የሚያስችል ፕሮፖዛል አዘጋጀ። ፕሮፖዛሉ የወረዳ ምክርቤት አባላት ከ50 ወደ 200፣ የቀበሌ ደግሞ ከ50 ወደ 500 እንዲሆን ሀሳብ አቀረበ። የሚገርመው ነገር በመነሻ ሀሳቡ ላይ ረቡዕ በኢህአዴግ ቢሮ ውይይት አድርገንበት ሀሙስ ጠዋት በፓርላማ በአስቸኳይ አጀንዳነት ቀርቦ እንዲፀድቅ ተደረገ። እድሜ ለአባይ ነብሱ፡ የሸንጐው ቁልፍ ካድሬ!

የፓርላማው አዋጅ የአዲሳባ ምክርቤት አባላትን የሚወስን ብቻ ሳይሆን በከተማዋ ምርጫ የሚካሄድበትን ቀን በታቀደና በተጠና መንገድ የቀየረ ሆነ። ወትሮ የከተማዋ ምክርቤት ምርጫ ከፊዴራልና ክልሎች ጋር አብሮ የሚካሄድ ነበር። በቡድኑ ጥናት መሰረት እነዚህ ውድድሮች በተመሳሳይ ጊዜ በመካሄዳቸው ምክንያት የአዲሳባ ምርጫ በፓርላማው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሯል የሚል ነበር። የፊዴራሉን አስቀድሞ በሁለት አመቱ የአዲሳባ ቢሆን የከተማው ህዝብ በፊዴራል ደረጃ ኢህአዴግ መንግስት ሆኖ እያየ ከተማዋን እንዲያስተዳድሩ ተቃዋሚዎችን የመምረጥ ፍላጐት አያድርበትም ተባለ። በመዲናይቱ የሚኖሩ የኢህአዴግ አባላትም በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት፣ "የፊዴራል መንግስት ኢህአዴግ በሆነበት ሁኔታ ለከተማዋ መስተዳድር ተቃዋሚዎችን

ብትመርጡ ልማቱ ወደኋላ ይቀለበሳል...አዲሳባ የሁከትና ብጥብጥ ከተማ ትሆናለች" የሚሉ ቃላቶችን በመጠቀም የህዝቡ አሰላለፍ ከኢህአዴግ ጋር እንዲሆን ያደርጋሉ አሊያም ህዝቡ ተስፉ ይቆርጣል የሚል ነበር። እንደተገመተው በምርጫ 2000 ይህ ቃል ገሸር መቀስቀሻ ሆኖ ከረመ።

የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ከ4.2 ሚሊዮን በላይ፣ መዲናይቱ ደግሞ ወደ 55ሺህ ያህል የምክር ቤት አባላት ይገኙባታል። ይህ ለማመን የሚያስቸግር ቁጥር የሚያመላክተን ነገር አለ። የህዝቦች ቀጥተኛ ተሳትፎ በማለት በህገመንግስቱ የተቀመጠውና በፓርላማ የፀደቀው ፀረ ዲሞክራሲ አዋጅ እስካለ ድረስ በመላ ሀገሪቱ የሚካሄዱ የአካባቢ፣ የአዲሳባና ድሬደዋ የምክር ቤት ምርጫዎች የተበሉ አቁቦች እንደሆኑ ይቀጥላሉ። ከእንግዲህ በእነዚህ አካባቢዎች የሚካሄደው ምርጫ ጉንጭ አልፉ ከመሆን አይዘልም። የሚገርመው የኢትዮጵያ የምክር ቤት አባላት እንደ አንድ ሀገር ህዝብ ቢቆጠሩ በአፍሪካ እነ ላይቤሪያ፣ ጋቦን፣ ናሚቢያንና ቦትስዋናን በመቅደም ከአፍሪካ ሀገሮች 39ኛ ደረጃ ላይ ይቀመጡ ነበር።

የቁጥሩን አስደንጋጭነት ወደ ጐን ትተን በህገ መንግስቱና በአቶ መለስ የዲሞክራሲ ስርአት ግንባታ በኢትዮጵያ የሚለውን መጽሐፍ ላይ እንደሰፈረው እነዚህ የምክር ቤት አባላት እውን የህዝብን ቀጥተኛ ተሳትፎ ያረጋግጣሉ ወይ? የሚለውን ጥያቄ ማንሳቱ ተገቢ ይሆናል። መነሻችን አዲሳባ በመሆኑ በመዲናይቱ ስለሚገኙት ከ55 ሺህ በላይ የቀበሌ ምክር ቤት አባላት ስልጣንና ተልእኮዎች በማንሳት እንጀምር።

እነዚህ የዝቅተኛ ምክር ቤት አባላት የአንድ ፓርቲ የበላይነት በሰፈነበት ሁኔታ የዲሞክራሲ ማፈኛ ተቋማት ሆነው በማገልገል ደረጃ የጐላ ሚና ይጫወታሉ። ዋነኛ ስራቸውም የአካባቢያቸውን ፀጥታ በመጠበቅ ስም የነዋሪውን ኩቴ መከታተል ነው። በአንዲት ቀበሌ ውስጥ ከ500 ያላነሱ የምክር ቤት ህጋዊ ካባ ያጠለቁ አባላትና ካድሬዎችን ማሰማራት ነዋሪው ውስጥ ምን ያህል መረበሽና በነፃነት ያለመናገር ሁኔታ ሊፈጥር እንደሚችል መገመት አያዳግትም። በእንቅርት ላይ እንዲሉ በእነዚህ እርከኖች ቡበዛት የሚሰማራው ካድሬ ህገ መንግስቱን እንኳን በአግባቡ ያላነበበና የንቃተ ህሊና ችግር ያለበት በመሆኑ እያንዳንዷን የተቃውሞ ቃላት "በፀረ - ህዝበኝነት "የመፈረጅ ባህሪው የተለመደ ነው። አንድ የምክር ቤት አባል በሚኖርበት ሰፈር ውስጥ በእድር አሊያም በለቅሶ ቤት ተገኝቶ አንድ ግለሰብ ከኢህአዴግ የተለየ አቋም ይዞ ከተመለከተ መጀመሪያ ጠላት፣ ለተከታታይ ቀናት ካራመደ ደግሞ በሽብርተኝነት ገራ እንዲሰለፍ ያደርጋል።

እነዚህ የምክር ቤት እና የድርጅት አባላት ከቁጥጥር ባሻገር ለምርጫ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ፉይዳ አላቸው። የኢህአዴግ 2001 እቅድ የአራተኛውን ሀገር አቀፍ ምርጫ ኢህአዴግ የሚያሸንፍበትን አቅጣጫ አስቀምጠ ነበር። በታላም የ2002 የምርጫ ስተራቴጀ ላይ በሚከተለው መልኩ እንዲሰፍር ተደርጓል፣

"... ከኢትዮጵያ ህዝብ ውስጥ 50% በላይ የሚሆነው ከ18 አመት በታች በመሆኑ የመራጩ ህዝብ ቁጥር ከ30 ሚሊዮን በላይ ሊሆን እንደማይችል ይገመታል። ከዚህ ውስጥ ቢያንስ 4 ሚሊዮን የድርጅት አባላት ናቸው። እያንዳንዱ አባል በቀላሉ ሊቀበላቸውና ሊያሳምናቸው የሚችል ቢያንስ 4 ወዳጆችና ዘመዶች እንዳሉት ቢታሰብ በድምሩ 20 ሚሊዮን ይሆናል። በእዚህ ብቻ 2/3 ኛውን ድምፅ ማግኘት ይቻላል።"

በአጠቃላይ ሲታይ ኢህአዴግ ለ90 ሚሊዮን ህዝብ ከ6ሚሊዮን በላይ አባላትና የምክር ቤት ካድሬዎችን በማሰማራት በአባላት ብዛት በአለም ተወዳዳሪ የሌለው ፓርቲ ሆኗል። በሌላ በኩል ኢህአዴግ ልምድ የወሰደበት የቻይና ኮሙዩኒስት ፓርቲ ለ1.4 ቢሊዮን ህዝብ ያሰማራው የአባል ብዛት 4 ሚሊዮን አካባቢ ነው። በመሆኑም ከዚህ በኋላ የልምድ ልውውጡ ተገልብጦ ጓድ Xi Jinping ወደ አዲሳባ በመምጣት ከጓድ በረከት ጋር ይመክራሉ።

***

"አብዮታዊነት ድሮ ቀረ!"

በህላዌ የተመራው ቡድን በሁለተኛ ደረጃ ለውይይት አቅርቦት የፀደቀው የእጩ ምልመላ መስፈርት መለወጥ በተመለከተ ነበር። ከዚህ በፊት ኢህአዴግ ለምርጫ ውድድር የሚመለምላቸው እጩዎች በድርጅቱ መርሆዎች ላይ በመመስረትና የፓርቲው ማህበራዊ መሰረቶች ከሚባሉት ላይ ነበር። መስፈርቶቹም: አብዮታዊነት (ወገንተኝነት)፣ የአላማ ጽናትና የብሄር መብቶችን እስከመገንጠል በእምነት የሚቀበል የሚል ነበር። ከእነዚህ ውስጥ አብዮታዊነት 90% ያህል ድርሻ ይኖረዋል። በመሆኑም የኢህአዴግ ማህበራዊ መሰረት ያልሆኑት ከፍተኛ ምሁራን ፣ባለሀብቶችና ከቀድሞ ስርአት ጋር ንክኪ ያላቸው ሰዎች በእጩነት እንዳይመለመሉ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያደርግ ነበር።

የኢህአዴግ የውስጠ ድርጅት መመሪያ ከፍተኛ ምሁራንን በሁለት ጐኑ የተሳሉ ቢላዋ በማለት በንኡስ ከበርቴነት ጐራ ይመድባል። በጀማሪ ካፒታሊዝም ውስጥ የምሁራን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሰረት ለጥገኛ ዝቅጠት የተመቸ እንደሆነና ከፍተኛ መደላድል እንደሚፈጥር ያሳስባል። በመሆኑም የምሁራን አሰላለፍ በንኡስ ከበርቴ ደረጃ በመሆኑ በህዝብ ውስጥ

የሚካሄደው ትግል ሲፋፋም በመጀመሪያው የንቅናቄ መስመር በማሰለፍ ግንባራቸውን ለጥይት እንደሚሰጡ፣ ትግሉ ሲቀዛቀዝ ደግሞ ከሌላው የበለጠ ተስፋ የሚቆርጡና የሚያስቆርጡ፣ ይባስ ብሎም ለግል ጥቅማቸው የሚሯሯጡ ሆዳሞች ይሆናሉ ይላል። በመሆኑም ድርጅቱን የሚቀላቀሉ ምሁራን አብዮቱን የመምራት ሀላፊነት ስለሚሸከሙ በመርፌ ቀዳዳ ማለፍ የሚችሉ ሆነው ከአጠቃላይ ተመልማዮች ከ1% መብለጥ እንደሌለባቸው ያብራራል።

የውስጠ ድርጅት ምልመላ መመሪያው ባለሀብቶችን በተመለከተ ምሁራን ላይ ከተቀመጠው መመዘኛ በከበደ ሁኔታ እንዲሰፍር ተደርጓል። በተቻለ መጠን ባለሀብቶች ድርጅቱን እንዳይቀላቀሉና ድጋፍ እንዳያደርጉ መከላከል ይኖርብናል ይላል። ኢህአዴግ ከባለሀብቶች ራቅ በማለት ነፃነቱን ጠብቆ መኖር እንዳለበት በማስገንዘብ።

ከምርጫ 97 በኃላ በምሁራንና ባለሀብቶች ላይ የተቀመጠው ጥብቅ መመዘኛ ባልተጻፈ መልኩ የተቀየረ ቢሆንም የእነ ህላዌ ቡድን ይዞ የመጣው መደበኛ አሰራር ሆኖ እንዲፀድቅ በማሰብ ነበር። ቡድኑ አብዮታዊነትን ከቁልፍ መመዘኛ በማሰናበት በፉንታው በህብረተሰቡ ዘንድ ታዋቂነት ያላቸውን ምሁራንና ባለሀብቶችን በእጩነት መመልመል ጊዜው የሚጠይቀው እንደሆነ አመላከተ። ቡድኑ የምርጫ 97 ሽንፈትን ተከትሎ ባለአደራ አስተዳደሩ ስልጣኑን በተረከበ ወቅት ኢህአዴግ በከተማዋ ላሰማራቸው ከ150 በላይ የሙሉ ጊዜ ምድብተኛ ካድሬዎች ደሞዝ የከፈሉትን ባለሀብቶች በምሳሌነት በማንሳት የድርጅቱ የጀርባ አጥንት እንደሆኑ አስታወሰ። በተለይም የሼህ መሀመድ አልአሙዲ ሸሪክ የሆኑት አቶ አብነት ገ/መስቀል ለዞን ሶስት ኢህአዴግ ጽ/ቤት ግማሽ ሚሊዮን ብር በመስጠት ከ30 በላይ ለሚሆኑ ካድሬዎች ለአንድ አመት ያህል ወርሀዊ ደሞዛቸውን በመቻላቸው የድርጅቱ የቁርጥ ቀን ተደርገው መወሰድ እንዳለባቸው በምሳሌነት ተነሳ። አቶ አብነት ከዚህ በተጨማሪም ዞኑ በሸራተን አዲስ ባዘጋጀው ገቢ ማሰባሰቢያ ሙሉ ወጪውን በመሸፈን ከ200 ሺህ በላይ ኢህአዴግን መታደጋቸው ተገለፀ።

"አብዮታዊነትን" አሰናብቶ በምትኩ ታዋቂነትን የተካው አዲሱ የምልመላ መስፈርት ኢህአዴግን በቅርፅና አደረጃጀት ባይቀይረውም ይዘቱን ሙሉ በሙሉ በሚባል መልኩ ቀይሮታል። የቀድሞ ወታደር የከፍተኛ ማእረግ መኮንኖች፣ ለኢህአዴግ ከፍተኛ ጥላቻ ያላቸው የእድር አመራሮች፣ የሀይማኖት መሪዎች ፓርቲውን ወክለው በየደረጃው በሚገኙ ምክር ቤቶች ውስጥ መሪ ተሳታፊ ሆነዋል። አንዳንዶቹ በከፍተኛ አመራርነት ሳይቀር ተሹመው እያገለገሉ ነው። ለአብነትም ያህል ቀድሞ በኢህአዴግ ካድሬዎች በአከራሪነት ሲፈረጅ የነበረው የአዲሳባ እስልምና ምክር ቤት ፀሀፊ ሼህ ኤሊያስ ሰይድ የከተማው

ምክትል አፈ ጉባኤ በመሆን ተሹሞ ነበር። ሼሁ የተመለመለበት ዋነኛ ምክንያት በወጣት ሙስሊሞች ዘንድ ተቀባይነት አለው ከሚል መነሻ ነበር። ከዛው ሳንወጣ የአፈ ጉባኤ ፅ/ ቤት ዋና ሀላፊ እንድትሆን በምክር ቤቱ የተሾመችው ወይዘሮ ነገደ ለማ የኢትዮጵያ ሰራተኛ ማህበር ኮሚሽን ከፍተኛ አመራር የነበረችና በቀይ ሽብር ዘመን ተባባሪ በመሆን የገዛ ወንድሟን በማስገደል የወቅቱ የደርግ "አብዮት ልጇን ትበላለች" መፈክር በተግባር ያረጋገጠች እንደሆነ ተጨባጭ መረጃ ቀርቦ ነበር። ይህ ሴትየዋ ፈፅመችው የተባለ ግፍ በአንድ የግል ፕሬስ ሙሉ ገጽ ሽፋን አግኝቶ ነበር። የግል ፕሬሱ የኢህአዴግ ጠላት ስለሆነ ሆን ብሎ ሊከፉፍለን ነው በማለት ሳይጣራ እንዲቀር ተደረገ።

የኢህአዴግ የይዘት ለውጥ በአዲሳባ ደረጃ ብቻ የተወሰነ አይደለም። በመላ ሀገሪቱ የድርጅቱ አፅም (Skeleton) ሳይለወጥ በየቀኑ እየመነመነ በሄደ አጥንቱ ላይ የሚለጠፍበት ስጋ ከሸክም በላይ ሆኗል። ይህንን ከአቅም በላይ የሆነ ስጋ የተሸከመ አጥንት በጋንግሪን እየተጠቃ መሄዱን ላስተዋለ ደግሞ ድርጅቱ እንደ ጉማ ሲጠቀለል ከምርጫ ባሻገር በሀገሪቱ ሊከሰት የሚችለውን አደጋ ለመገመት ያስቸግራል።

በአንድ ወቅት ከስምንት ሺህ በላይ የአዲሳአባ ካድሬዎችን እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎችን በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ለማጥመቅ ዝዋይ ህፃናት አምባ (አላጌ) ለወራት ከተምን። አጥማቂዎቹ ጠቅላይ ሚኒስትር ሀይለማርያም፣ በረከት ስምኦን፣ ሬድዋን ሁሴን፣ ካሚል አህመድ እና እኔ ነበርን። የአጋጣሚ ነገር ሆኖ እኔ፣ ሬድዋን እና ካሚል የተዘጋጀልን ማደሪያ የጋራ ሳሎን ያለው ነበር። እናም ማታ ማታ ጫት የሚቅመው እየቃመ፣ ቢራ የሚወደው እየጠጣ ጨዋታችን እስከ እኩለ ለሊት ይዘልቃል። ከእለታት በአንዷ ምሽት "የኢህአዴግ መዋቅር ወዴት እየሄደ ነው? ይህን ተከትሎ ሊከሰት የሚችለው አደጋ ምን ሊሆን ይችላል?" የሚል የደራ ክርክር ይነሳል። ምሽቱ በጨመረ ቁጥር አይኑ እንደ ስጋ ቤት አንፓል እያበራ የሚሄደው ሬድዋን ሁሴን፣

"አንድ ጊዜ መጣሁ!" በማለት ወደ መፀዳጃ ቤት ይሄዳል። ሬድዋን ሲመለስ አንድ ባልዲ የሚያክል ውሀ የተሞላበት ኮንደም ተሸክሞ መጣ። ኮንደም ያን ይህል ውሀ እንደሚይዝ ለመጀመሪያ ጊዜ ተመለከትኩ። ውሀ የሞላውን ኮንደም ከፍ ዝቅ እያደረገ፣

"ኢህአዴግ ወደዚህ ማሰሮ ሆድነት ተቀይሯል። ትንሽ ስንጥር (መርፌ) የወጋው አለት ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት አያዳግትም" አለን።

***

ጉዞ ወደ መድብለ ፓርቲ ቅስቀሳ!

በየጊዜው የሚጸፉ የኢህአዴግ ሰነዶችን በዝርዝር ለመመልከት እድል ያገኘ ሰው ፓርቲው በተደጋጋሚ የመርህና አቋም ለውጦችን እያደረገ መሄዱን

ለመረዳት ጊዜ አይወስድበትም። ርግጥ አንድ ተቋም ወይም ድርጅት የውስጡን፣ አገር አቀፍና የአለም ሁኔታን በማጥናትና ከተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር በማጣጣም እየተገላበጠና ልብሱን እየቀየረ ቢሄድ የሚያስከፋ አይደለም። እንዳውም ህይወት ካለው ድርጅት የሚጠበቅ እርምጃ ነው። ከዚህ አንፃር ኢህአዴግን የተለየ የሚያደርጉት ባህሪያት አሉት፦

በመጀመሪያ ደረጃ ልብሱን የሚቀይሩት በጣት የሚቆጠሩ ካድሬዎች ናቸው። ሌላው ከፍተኛ ካድሬ በዲሞክራሲያዊ ማእከላዊ መርህ በመጠርነፍ ቃር ቃር እያለውም ቢሆን ይቀበላል። አብዛኛው የድርጅት አባል ደግሞ አልባሳቱ መቀየራቸውን እንኳን ስለማያውቁ በተምታታ አዙሪት ውስጥ ይዳክራሉ። በተለይም ከትጥቅ ትግሉ ጀምሮ ታጋይ የነበሩ ካድሬዎች የአይዲኦሎጂ ለውጦች በይፋ ስለማይነገራቸው ትላንትና ይዘውት ከነበረ አስተሳሰብ ጋር ተቸንክረው ይቀራሉ።

በሁለተኛ ደረጃ ኢህአዴግ የተለየ የሚያደርገው ተቀባይነት ያላቸውን ነገሮች በመተው የራስን ፍቺ መስጠት ነው። በአለም አቀፍ ደረጃ ስምምነት የተደረሰባቸው ትርጉሞችን ወደ ጐን ትቶ ኢህአዴግአዊ ትርጉም ይሰጣል። ከዚህ አንፃር ፓርቲው "መድብለ ፓርቲ" በተመለከተ በየጊዜው የሚሰጠውን ትርጉም ማየት በቂ ይሆናል።

ኢህአዴግ ከ1993 ዓ.ም እና ከዛ በፊት ባወጣቸው የውስጠ ድርጅት ሰነዶች ላይ የመድብለ ፓርቲ ስርአት ግንባታን አምኖ የተቀበለው ሳይሆን አሁን አለም የምትገኝበት ነባራዊ ሁኔታ አስገድዶት እንደሆነ ይገልፃል። ተቃዋሚዎች በዲሞክራሲ ስርአት ግንባታ ምንም አይነት አስተዋጽኦ የሌላቸውና በተቃራኒው አሉታዊ ተጽእኖ በማሳደር የአብዮታዊ ዲሞክራሲን የአስተሳሰብ ልእልና (Hagimony) እንዳይሰፍን የሚያደርጉ በማለት ይፈርጃቸዋል። በመሆኑም በዲሞክራሲያዊ መሳሪያዎች (Democratic Instruments) በመጠቀም ማዳከም አብዮቱ እደርስበታለሁ የሚለውን የመጨረሻ ግብ ያለአንዳች እንቅፋት እንዲመታ ያደርገዋል ይላል።

በተቃራኒው በረከት ጽፎ ባስነበበን የሁለት ምርጫዎች ወግ መጽሐፍ ላይ "የሚያዝያ ሰልፎች" በሚለው ርእስ ስር ከላይ የተቀመጠውን ሀቅ በመግልበጥ፡

"... ኢህአዴግ ከሀያ አመታት በፊት የመድበለ ፓርቲ ስርአት ግንባታን የመረጠበት ምክንያት ዲሞክራሲያዊ ምርጫ የህዝብ መብት ከመሆኑ መሰረታዊ ጉዳይ የተነሳ ብቻ አልነበረም። የተቃዋሚ በተለይም ህገ መንግስቱን ተቀብሎ በፓሊሲ ልዩነት ዙሪያ ተወዳድሮ ለመመረጥ የሚሻ ጠንካራ ታማኝ ተቃዋሚ መኖር ለዲሞክራሲ ስርአት ጤንነት የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ ስላለው ጭምር ነበር።" ይላል።

እነ በረከት በኢትዮጵያ የመድበለ ፓርቲ ስርአት (Multi-party system) አለ ብለው እየተከራከሩ ነው። የአለም ህዝብ ተቀብሎ እያደረበት ያለው የብዙሀን ፓርቲ ስርአት ደግሞ የራሱ የሆነ ቅድመ ሁኔታዎችና

መመዘኛዎች አሉት። የመድብለ ፓርቲ ስርአት የተለያዩ ፓርቲዎች በተናጠልና በጋራ መንግስታዊ ስልጣን ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ በምርጫ ውጤታቸው መሰረት የሚይዙበት ስርአት ነው። በዚህ ስርአት ውስጥ የሚኖሩ የፓለቲካ ፓርቲዎች ብዛት (effective number of parties) ከሁለት ያላነሱና ከአስር ያልበለጡ መሆን እንደሚገባቸው በዚህ ሙያ ላይ ያሉ ምሁራን ያስገነዝባሉ።

በአብዛኛው የመድብለ ፓርቲ ስርአት በገነቡ ሀገሮች ያለው የምርጫ ስርአት ከአብላጫ ድምፅ ይልቅ የተመጣጣኝ ውክልና አሰራር ማእከል ያደርጋል። የተመጣጣኝ ውክልና አሰራር በምርጫው የተወዳደሩ ፓርቲዎች ያገኙት ድምፅ ተቆጥሮ ባገኙት ፐርሰንቴጅ ልክ የምክር ቤት መቀመጫዎችን የሚከፋፈሉበት ስርአት ነው። ለአብነት ያህል አንድ ፓርቲ ከአጠቃላይ መራጩ 30% ድምፅ ቢያገኝ ከምክር ቤቱ መቀመጫዎች 30% ይወስዳል። ይህ የምርጫ ስርአት ብራዚልን ጨምሮ ከ80% በላይ የደቡብ አሜሪካ ሀገራት፣ ከአውሮፓ ደግሞ ጀርመን፣ ኔዘርላንድ፣ ኖርዌይ፣ ራሺያ፣ ስፔንና ሌሎች በርካታ ሀገሮች፣ እንዲሁም አስራኤልና ደቡብ አፍሪካን የመሳሰሉ ሀገራት የሚሰራበት ነው።

በሌላ በኩል የአብላጫ ድምፅ ስርአት (first past the post) በሚከተሉ ሀገሮች ከተወዳዳሪ እጩዎች መካከል የመራጩን ህዝብ አብላጫ ድምፅ ያገኘ ህዝቡንና ፓርቲውን ወክሎ የምክር ቤቱን መቀመጫ ይወስዳል። ይህ የምርጫ ስርአት እንደ ተመጣጣኝ ውክልና ሁሉ ዲሞክራሲያዊ ቢሆንም ውጤታማ የሚሆነው ሁለትና ሶስት ፓርቲ ስርአት ባለባቸው እንደ አሜሪካና እንግሊዝ የመሳሰሉ ሀገሮች ላይ ይሆናል። በአሜሪካን ሀገር ያሉት ሁለት ግዙፍ ፓርቲዎች በመሆናቸው የምርጫ ፉክክሩ በእነሱ መካከል ይሆናል። በዲሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ የኖረው የአሜሪካን ህዝብም በፓርቲዎቹ መካከል የእርስ በራስ ቁጥጥር ለማምጣት ህግ አውጭውን ለአንዱ፣ አስፈፃሚውን ለሌላ፣ አሊያም በተቀራራቢ ቁጥር እንዲወከሉ በማድረግ የዳበረውን የዲሞክራሲያዊ ስርአት ያስጠብቃል።

የፓርላሜንት ስርአት የምትከተለው እንግሊዝ ሶስት ታላላቅ ፓርቲዎች የሆኑት ኮንሰርቫቲቭ፣ ሌበርና ሊብራል ዲሞክራቶች የሚፎካከሩባት ሀገር ናት። የቅርብ ጊዜውን እንኳን ብንወስድ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ2010 የተካሄደው ሀገር አቀፍ ምርጫ እነዚህ ሶስት ፓርቲዎች ከአጠቃላይ 650 ወንበር ውስጥ 622 ያህሉን አሸንፈዋል። በዚህ ምርጫ አብላጫውን (23%) ያገኙት ሊብራል ዲሞክራቶች ቢሆኑም መንግስት ለመመስረት የሚያስችል ተጨማሪ 10% ስለሚያስፈልጋቸው ከኮንሰርቫቲቭ ጋር ጥምረት በመፍጠር መንግስት መስርተዋል።

ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው በኢትዮጵያ የመድብለ ፓርቲ ስርአት አለ ለማለት ከላይ የተቀመጡት መስፈርቶች መሟላት ይኖርባቸዋል። በመጀመሪያ ደረጃ በሀገራችን የፓለቲካ ፓርቲ መመስረት የመንደር ሱቅ ከመክፈት በላይ ቀላል ሆኗል። ጠቅላይ ሚኒስትር ሀይለማርያም እንደገለፀው በአሁን ሰአት ከዘጠና ዘጠኝ በላይ የፓለቲካ ፓርቲዎች ይገኛሉ። ይህም ሆኖ ከገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ በስተቀር ጐልቶ የወጣ ይህ የሚባል የፓለቲካ ፓርቲ የለም። ለሀይል

ሚዛን ተስፉ ተጥሎባቸው የነበሩትም በራሳቸውና በኢህአዴግ የዜሮ ድምር ጨዋታ ምክንያት በተወለዱ ማግስት ሰላሳ ቦታ ተሰነጣጥቀዋል። በመሆኑም መድበለ ፓርቲ ስርአት ለመመስረት ከሁለት እስከ አስር የፖለቲካ ፓርቲዎች መገኘትን እንደ መሰረታዊ ነገር የተቀመጠው በኢትዮጵያ የሚሰራ አይደለም።

ከሁሉም በላይ ኢህአዴግ የሚመራበት አብዮታዊ ዲሞክራሲ ርእዮተ አለም የተፈጥሮ ባህሪው መድበለ ፓርቲን የሚያበረታታና የሚፈጥር አይደለም። ዜጐች ሲነሱና ሲቀመጡ፣ ሲበሉና ሲተኙ በህልማቸው ሳይቀር ስለአንድ ነገር ብቻ እንዲያስቡ ማድረግን እንደ ግብ የሚወስድ ፍልስፍና የተለየ አማራጭን ሊቀበል የሚችል ተክለ ሰውነት ሊኖረው አይችልም። ይህ አስተሳሰብ ገዥ ሆኖ የበላይነት ካላረጋገጠ በስተቀር ሀገሪቷ የመበታተን አደጋ ሊያጋጥማት ይችላል፣ ከዚህ በፊትም ኢትዮጵያ አጋጥሞት የነበረውን መስቀለኛ መንገድ በድል የተሸጋገረችው በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ነው ብሎ የሚያምን ድርጅት አብዛህነትን ሊከተል የሚችል መተክል አይኖረውም።

***

ኢህአዴግ እንደ መድበለ ፓርቲ ሁሉ አብዮታዊ ዲሞክራሲን አስመልክቶ የሚሰጠው ትርጉምና መፃኢ እድል ከሁኔታዎች ጋር የሚለዋወጥና ከዘመን ዘመን የሚለያይ ነው። ኢህአዴግ ባጋጠመው የውስጠ ድርጅት ቀውስና የአለም አቀፍ ሁኔታ መቀያየር ምክንያት አብዮታዊ ዲሞክራሲ ለሶስት ያህል ጊዜያት ሙሉ ልብሱን ቀይሯል። በዚህም ምክንያት የኢህአዴግ ትርጉም፣ መርሆዎች፣የጉዞ አቅጣጫና ቀጣይ እጣ ፋንታ በተመሳሳይ መልኩ ግልብጥብጡ ወጥቷል። ከ1993 ዓ.ም በፊት፣ ከ1993 -1998 እና ከ1998 ዓ.ም በኋላ ያለው ኢህአዴግና አብዮታዊ ዲሞክራሲ አንድ አይነት አይደሉም።

ከ1993 ዓ. ም በፊት ...

በዚህ ወቅት የነበረው አብዮታዊ ዲሞክራሲ በአብዮታዊ ምሁራን የሚመራ ሆኖ ለመላው አርሶ አደር፣ለላብአደርና ለከተማው ጭቁን ህዝብ ቆሚያለሁ የሚል ነበር። የዚህ ስርአት የመጨረሻ መዳረሻው ዲሞክራቲክ ሶሻሊዝምን መገንባት ነበር። ዲሞክራቲክ ሶሻሊዝም በህብረተሰቡ ውስጥ በሚካሄድ ንቅናቄ የሚመጣን መዋቅራዊ ለውጥ እንደ መሰረት በመውሰድ ያልተማከለ ፖለቲካል ኢኮኖሚ መፍጠርን የመጨረሻ ግቡ ያደርጋል። ከ93 በፊት የነበረው ኢህአዴግና አብዮታዊ ዲሞክራሲ የመጨረሻ ግቡ ዲሞክራቲክ ሶሻሊዝም ተብሎ ቢጠቀስም በየትኛው አቅጣጫ? ለምን ያህል ጊዜ ተጉዞ መዳረሻው ላይ ይደርሳል የሚለው በዝርዝር አልተቀመጠም።

ከፓርቲ አመራር አንፃር ከ93 በፊት የነበረው አብዮታዊ ዲሞክራሲ በድርጅቱ ቁንጮ ላይ የተቀመጡትን ካድሬዎች አምባገነን እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። የሁሉ ነገር አድራጊና ፈጣሪ ቁንጮዎቹ ነበሩ። የተቀረው አባል እነሱ የሚወስኑትን ውሳኔ በዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት መርህ የመቀበል ግዴታ አለበት። የጐረበጠውና ለመቀበል ህሊናው ያልፈቀደለት ያለው ብቸኛ አማራጭ ድርጅቱን ለቆ መውጣት ይሆናል። በመሆኑም በዚህ ወቅት የነበረው ስርአት

አይደለም ከውጭ በፓርቲው ውስጥ እንኳን ልዩነትን የሚያስተናግድ ባህሪ አልነበረውም። በተግባርም እንደታየው እነዚህ ካድሬዎች በሂደት ራሳቸውን ወደ ገዥ መደብነት በመቀየር ዋነኛ የስልጣን ምንጭ ሆነው ነበር። ርግጥ በእነዚህ ገዥ መደቦች መካከል የጥቅም ግጭት መነሳቱና የስልጣን ሽኩቻ መካሄዱ ነባራዊ ሀቅ በመሆኑ ጊዜውን ጠብቆ ተከስቷል። በወቅቱ የተፈጠረው የእርስ በራስ መጠላለፍና መጠፋፋት ከድርጅቱ አልፎ ጦሱ ለሀገሪቱ ተርፎ ነበር። በተለይ በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ወቅት ልዩነቱ ይፋ የሆነበት ነበር።

ከ1993-1998 ዓ.ም...

በዚህ ወቅት የነበረው አብዮታዊ ዲሞክራሲ ከበፊቱ በተለየ መንገድ ዘርዘር ባለ ሁኔታ የተብራራ ነበር። ስለ አብዮታዊ ዲሞክራሲ በውስጠ ድርጅት ሰነዶች የተገለፀውና ወደ መንግስት ስትራቴጂዎች የተተረጎመው ለየቅል ቢሆንም ፓርቲውን ለመገንዘብ የተሻለ እድል ሰጥቷል። ስርአቱ እንደ ከዚህ ቀደሙ የሚመራው በአብዮታዊ ምሁራን (ንኡስ ከበርቴዎች) ሆኖ ወገንተኝነቱ ለሀብታም አርሶአደሮችና ጥገኛ ያልሆኑ የሚል ቅፅል ለተጨመረላቸው ባለሀብቶች እንደሆነ ተገለፀ።

ይሄኛው አብዮታዊ ዲሞክራሲ የሚገነባው የካፒታሊዝም ስርአት ሲሆን የመጨረሻ እጣ ፋንታው ሊበራል ዲሞክራሲ ሊደርስበት የሚችለው ጫፍ ማድረስ እንደሚሆን ተገለፀ። በመጨረሻው ሰአት አብዮታዊ ዲሞክራሲ ራሱን በራሱ በመብላት የሚከስም ሲሆን በኢህአዴግ ውስጥ ያሉ አባላቶች ለሁለት እንደሚከፈሉ ያስረዳል። የመጀመሪያዎቹ ሀብት የማካበት እድል ያጋጠማቸው ሲሆኑ እነዚህ ሀይሎች ሁሉንም ነገር ለገበያ ለሚሰጠው ነጭ ካፒታሊዝም መመስረት ይተጋሉ። የተቀሩት በተለይም ተራማጅ አስተሳሰብ ያላቸው ለዝቅተኛው ማህበረሰብ ማህበራዊ ዋስትና መረጋገጥ የሚታገሉ ሶሻል ዲሞክራቶች እንደሚሆኑ ያስረዳል። ይህም የኢህአዴግና የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ግብአተ መሬት የሚፈፀምበት ይሆናል።

ከፓለቲካል ኢኮኖሚም አንፃር ይሄኛው ኢህአዴግ የመንግስትና የግሉን ከፍል ለይቶ የሰራ ድርሻ የሚሰጥ ነበር። የመንግስት ጣልቃ ገብነት በተለይም በተመረጡ ፣ ትስስር በሚፈጥሩና ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ በሚያስችሉ ቦታዎች ላይ መኖር እንደሚገባው ያስገነዝባል። የኢኮኖሚ ልማቱ አንቀሳቃሽ መንግስት ቢሆንም ሞተሩ የግል ባለሀብቱ በመሆኑ ባለሀብቱን መደገፍ ዋነኛ የኢኮኖሚው አቅጣጫ እንደሚሆን ያስገነዝባል። ፍትህዊ ስርጭትን ለማረጋገጥ እንደ ቴሌና መብራት የመሳሰሉ ተቋማት በመንግስት እጅ መሆን እንደሚገባቸው በግልፅ ተቀምጧል።

ከ1998 ዓ. ም በኋላ ...

በዚህ ወቅት ያለው አብዮታዊ ዲሞክራሲ የመለወጡ መሰረታዊ ምክንያት የውስጠ ድርጅት ሽኩቻ ሳይሆን የአለም አቀፍ የፓለቲካል ኢኮኖሚው በመቀየሩ ምክንያት የመጣ ነበር። ከአለም አቀፍ የኢኮኖሚ ቀውሱ ጋር ተያይዞ በተለይም በሀገረ አሜሪካ የኒዮ ሊብራል ጐራው ከፉኛ መመታት

ለአቶ መለስ ከፍተኛ ደስታ የፈጠረና ወደ አዲስ የፍልስፍና መስመር የወሰደው ነበር። ይህም ኢህአዴግና አብዮታዊ ዲሞክራሲ ለሶስተኛ ጊዜ ለመገላበጥ መልካም አጋጣሚ የፈጠረ ሆነ። በመሆኑም ፓርቲውና አብዮታዊ ዲሞክራሲ በ50 አመታት ውስጥ እድገታቸውን ጨርሰው የማይቀርላቸውን ግብአተ መሬት ይፈጽማሉ ተብሎ የተገለፀው ተገለበጠ። በምትኩ ኢህአዴግ የአስተሳሰብ እድገት አምጥቷል በማለት አብዮታዊ ዲሞክራሲ እንደ አንድ የዲሞክራሲ አማራጭ ለዘላለም ይኖራል ተባለ። አዲሱ አስተሳሰብ በኢህአዴግ የንድፈ ሀሳብ መጽሐት በሆነችው "አዲስ ራእይ" ላይ እንዲወጣ ተደርጐ በበላይ ካድሬ ደረጃ ስልጠና ተሰጠበት። ቀጥሎም ፓርቲው ለዘላለም የሚኖርባቸው ስትራቴጂዎች ተቀርፀው መተግበር ተጀመሩ። ከእነዚህ ውስጥ ዋነኛው አቶ መለስ የፃፈው "የልማታዊ መንግስት" ፍልስፍና ነበር።

ልማታዊ መንግስት የኒዮሊብራል ጊዜያዊ ውድቀቶችን በሰፊው በማጉላት ከሱ በተቃራኒ የሆነውን የመንግስት ሁሉንም የልማት ዘርፎች የመቆጣጠር አላማ ገቢራዊ የተደረገበት ነበር። ይህ አይዲኦሎጂ የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ከጫወታ ውጪ በማድረግ መንግስት የሁሉም ነገሮች አድራጊና ፈጣሪ እንዲሆን ያደርጋል። ይህ አስገዳጅ በሆነ መልኩ ልማት ማምጣትን በመገፋፋት የሚፈፀም ስትራቴጂ የግለሰቦችን ነፃነትና ዲሞክራሲያዊ መብቶች በመደፍጠጥ የሚተገበር ነው።

የልማታዊ መንግስት ፍልስፍና ከዲሞክራሲ ይልቅ ልማትን በማስቀደም የተቃኘ በመሆኑ ዜጐችን እንደ አንድ የልማት መሳሪያ ብቻ ይመለከታል። ዜጐች በመንግስት ጫማ ስር እንዲወድቁ፣የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ከጨዋታ ውጭ እንዲወጣ፣ የመንግስት ኢንቨስትመንት የትየለሌ እንዲሆን ያደርጋል። በተግባርም የሆነው ይህ ነው። በ2005 ዓ.ም የአለም ባንክ አጥንቶ ይፉ ባደረገው ሪፓርት ኢትዮጵያ ከአለማችን ሀገሮች የመንግስት ኢንቨስትመንት ከሚካሄድባቸው ሀገሮች በሶስተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች። ሁኔታው በዚህ ከቀጠለ የግል ባለሀብቱ እየከሰመ መንግስት የሁሉም ነገሮች አድራጊ እንደሚሆን አለም ባንክ አስጠንቅቋል።

***

ኢህአዴግና አብዮታዊ ዲሞክራሲ ለሶስት ያህል ጊዜያት ሲገላበጡና የአስተሳሰብ እድገት ሲያሳዩ በሁለት ነገር ላይ ግን ተመሳሳይ አቋም ነበራቸው። በመድበለ ፓርቲ ስርአት ግንባታና ተቃዋሚ ድርጅቶች ላይ። በሁሉም ወቅቶች የወጡት የድርጅቱ ሰነዶች ተቃዋሚ ድርጅቶችን በተፎካካሪ ሳይሆን በጠላትነት የሚፈርጁ ናቸው። ከዛም አልፎ ፀረ-ሰላምና የጥፉት ሀይሎች በሚሉ ቃላት በመግለጽ ኢህአዴግ ለፓርቲዎቹ ያለውን ጥላቻ የሚያሳይበት ሁኔታ እንመለከታለን።

ከ1993 ዓ.ም በፊት ኢህአዴግ ይመራ የነበረው ከጫካ ይዞት በመጣው ህግና አመለካከት በመሆኑ ፓርቲዎቹን ፀረ ዲሞክራሲያዊና አስተዳደራዊ በሆነ መንገድ ለማከሰም ተንቀሳቅሷል። በተለይም የመድበለ

ፓርቲ ስርአት መስፈን እውን ለማድረግ ተቃርቦ የነበረው የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (አነግ) ከመድረኩ ተገዶ መውጣቱ ለዚህ ጥሩ ማሳያ ይሆናል። ርግጥ የአብዛኛው ኦሮሞ ህዝብ ፍላጐት አነግ ከሚያራምደው አቋም የተለየ ቢሆንም ቁጥሩ ቀላል በማይባሉ የኦሮሚያ ዞኖች ፓርቲው ሰፊ ተቀባይነት ነበረው። ግንባሩ ይህንን ድጋፍ ተጠቅሞ የአቋም ለውጥ ሳያደርግ ቢንቀሳቀስ ኖሮ በፌዴራል ፓርላማ ከፍተኛ ቁጥር በመያዝ በህግ አውጭነት የሚሳተፍበት በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ደግሞ የጥምር መንግስት አካል የሚሆንበት እድል ይፈጠር ነበር። የኦሮሞ ህዝብን የኢትዮጵያዊነት ግንድ መሆንን ዛሬ ተገንዝቦ የአቋም ለውጥ ባደረገበት ሁኔታ የኢትዮጵያ ፓለቲካ መድረክ ላይ ተገኝቶ ቢሆን ኖሮ በእነ እንግሊዝ ያየነው ጥምር መንግስት በሀገራችን እውን ይሆን ነበር። ምንአልባትም የኦሮሞ ወጣቶች ስደትና የእስር ቤት መታጐር ይቀንስ ነበር።

ከ1993 ዓ.ም በኃላ በኢህአዴግ ከፍተኛ ካድሬዎች ተነስቶ አከራካሪ የነበረው "ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለዲሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ አስተዋጽኦ አላቸው/የላቸውም?" የሚለው ነበር። ይህ ክርክር የመጨረሻውን ድምዳሜ ባይለውጠውም ኢህአዴግ የስልት ለውጥ ያደረገበት ነበር። ይህም ተቃዋሚዎች በተዘዋዋሪ መንገድ ለዲሞክራሲ ግንባታ አስተዋጽኦ አላቸው የሚለው ነበር። በተዘዋዋሪ መንገድ ማለት ሀሳባቸውን በመግለፃቸው ምክንያት ፀረ-ህዝብና የጥፋት ሀይሎች መሆናቸው ይጋለጣል የሚል ነበር። በዚህ ምክንያት የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ትክክለኛነት ይረጋገጣል የሚል ነበር። ከዚህ በተቃራኒው የመታፈን እድል ካጋጠማቸው ግን የአብዮታዊ ዲሞክራሲ የተሻለ አማራጭነት አብሮ ይታፈናል፣ ተቃዋሚዎችንም እርቃናቸውን ማስቀረት አይቻልም የሚል ነበር። በምርጫ 97 ኢህአዴግ በሩን በልበ ሙሉነት ገርበብ አድርጐ የከፈተበት ዋነኛ ምክንያት ምንጩ ይሄ ነበር። ተቃዋሚዎችን ህዝቡ አይቀጡ ቅጣት በመቅጣት የአብዮታዊ ዲሞክራሲን ትክክለኛነት ያፀናል በሚል... ውጤቱ በተቃራኒው ቢሆንም።

ምእራፍ ሃያ ሶስት

እውን ታሪክ ራሱን ደገመ ?

"ታሪክ ራሱን ይደግማል፣ መጀመሪያ ላይ አሳዛኝ፣ ቀጥሎም ቧልት ሚመስል መንገድ።"

በረከት ስምኦን (የሁለት ምርጫዎች ወግ)

የህሊና ሸክም!

በአቶ በረከት የሁለት ምርጫዎች ወግ መጽሐፍ ላይ በ2000 ዓ.ም የተካሄደውን የማሞያና አካባቢ ምርጫ በማስመልከት "ታሪክ ራሱን ደገመ ወይስ***?" በሚለው ርእስ ስር የሚከተለው ተፅፎ እናገኛለን፡ -

"...የምርጫው ሂደትና ድምፅ ቆጠራው በሰላም ተጠናቆ ውጤቱ ሲገለፅ ብዙዎች እንደገመቱት ኢህአዴግ በአዲስ አበባ ምርጫ ሙሉ በሙሉ አሸናፊ ሆነ። ከመቶ ሰላሳ ስምንት ወንበር መቶ ሰላሳ ሰባቱን በማግኘት። በነገራችን ላይ ቅንጅትም በ97 ምርጫ በመቶ ሰላሳ ስምንት ጣቢያዎች ያሉትን ወንበሮች ሁሉ አሸንፎ የነበረ ሲሆን፣ አንድ የእነርሱ ተመራጭ በሆነ ምክንያት በመጓደሉ ተከታዩን ድምፅ ያገኘው የኢህአዴግ ተወካይ የአዲስ አበባ ምክር ቤት አባል ሆኖ ቅንጅት በሚመራው ምክር ቤት ሊሳተፍ ተዘጋጅቶ ነበር። በማሞያ ምርጫ ላይ የሆነው ተመሳሳይ ነበር። ታሪክ ራሱን ይደግማል፣ መጀመሪያ ላይ አሳዛኝ፣ ቀጥሎም ቧልት በሚመስል መንገድ።"

አቶ በረከት በዚህ ጽሁፉ የአዲሳባን ዳግም ምርጫ ባልተጠበቀ ሁኔታ በታሪክ ደጋሚነት እሳቤ መጠናቀቁን ገልጿል። ካርል ማርክስ የሚታወቅባትን "ታሪክ ራሱን ደገመ፣ መጀመሪያ አሳዛኝ ቀጥሎ ቧልት በሚመስል መንገድ" የሚለውን በመጠቀም።

ከዚህ አንፃር ሊነሳ የሚገባው ትልቁ ጥያቄ እውን ታሪክ ራሱን ደግሟል? አሳዛኙና ቧልተኛ ታሪኮች የትኞቹ ናቸው? የሚሉት ይሆናል። የኢትዮጵያ ፓለቲካ የዜሮ ድምር ጨዋታ በመሆኑ አንዱ ቡድን ደማቅ ታሪክ ብሎ የሚገልፀው ለሌላው አሳፋሪና አንገት የሚያስደፋ ይሆናል። በግለሰብም ደረጃ ተመሳሳይ የሚሆንባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው። አልፎ አልፎም

ቡድኖቹ ግለሰቦችን በመጨፍለቅና በእነሱ ላይ በመረማመድ ታሪክ መስራታቸውን ያውጃሉ። ለዚህ አባባል ግልፅ ማሳያ የሚሆነው በአቶ በረከት ከላይ የተገለፀው አሳዛኝ ታሪክ ይሆናል።

በዚህ አሳዛኝ ታሪክ ወስጥ እኔን ጨምሮ አቶ በረከት፣ ህላዌ ዮሴፍ፣ አዜብ መስፍን፣ አያት የመኖሪያ ቤት ስራ ድርጅትና አዲስ ነገር ጋዜጣ ተሳታፊ ሆነናል። ከላይ የተጠቀስነው በሙሉ በአንድ ግለሰብ ላይ የተረባረብን ቢሆንም ያነገብነው አላማ ለየቅል ነበር።

አቶ በረከት ቧልት የተባለውን ታሪክ ለመስራት፣ ወይዘሮ አዜብ እና አያት የነበራቸውን የጥቅም ትስስር በላቀ ደረጃ ለማሳደግ፣ አዲስ ነገር ጋዜጣ ከውስጥ ድርጅት የተገኘ አዲስ መረጃ በመሆኑ ቅድሚያውን በመውሰድ ትኩስ ዜና ለህብረተሰብ ለማድረስ። ጋዜጣዉ ፓለቲካውንና የጥቅም ትስስሩን ሚስጥር ባለመረዳት በተገኙዉ ሰው ላይ ያሳረፈው በትር ግለሰቡ ከህብረተሰቡ እንዳይቀላቀል ፣የእጅ መጠቋቆሚያ እንዲሆንና ተሸማቆ እንዲኖር አድርገዉታል።

ወደዚህ የህሊና ሸክም ወደ ሆነ ታሪክ ከመግባቴ በፊት ከላይ በአቶ በረከት የምርጫ 97 የአዲሳባ ውጤትን አስመልክቶ በቀረበው ወግ ላይ ተዛንፈው የቀረቡ ታሪኮች በትክክለኛው ገፅታው በማስቀመጥ ልጀምር።

"አንድ ለእናቱ"

ምርጫ 97 ሊካሔድ የሁለት ሳምንት እድሜ ሲቀረው አራት ኪሎ የሚገኘው የኢህአዴግ ቢሮ በሽብርና ጭንቀት ተዋጠ። የአዲሳባን ምርጫ እንድናስተባብር የተመደብን ሀያ ከፍተኛ ካድሬዎች በየቀኑ ማታ ማታ ከአቶ በረከት ጋር ግምገማ ማካሄድ ጀመርን። የከተማው ነዋሪ ከኢህአዴግ በተቃራኒ መሰለፉን ያልተገነዘበው አቶ በረከት አህያ የማይሸከመው ስራ በየቀኑ መቆለሉን አጠናክሮ ቀጠለ። እነዚህን እንኳን ለመፈፀም በወረቀት ላይ ለማስፈር የሚከብዱ እቅዶች ላይጀመሩ መውደቅ ጀመሩ።

ይህንን ተከትሎ በአቶ በረከት የሚቀርበው ዘለፋና ስድብ ለጆሮ የሚሰቀጥጥ ሆነ። ካድሬዎቹም ኢህአዴግ ቢሮ በየምሽቱ መምጣት ምድራዊ ሲኦል ደርሶ እንደመመለስ ቆጠሩት። በተለይም እውነቱን ከመናገር ወደኋላ የማይሉ ጥቂቶች ይህ የመከራ ጊዜ የሚያጥርበት ቀን በጉጉት እየተጠባበቁም ቢሆን የህብረተሰቡን ተጨባጭ ፍላጐት ከማንፀባረቅ ወደኋላ አላሉም ነበር። ከእነዚህ ካድሬዎች አንዱ ተከሌ ይባላል።

ተክሌ በአዲሳባ አባላት ዘንድ በቅንነት የሚታወቅ ሎግላጋ ወጣት ነበር። በቅርብ ለምናውቀው ሰዎች ደግሞ በቀላሉ የማይሸበር መንፈሰ ጠንካራና የህዝብ ቅሬታዎችን በአደባባይ የሚናገር ሰው ነበር። በአንድ ወቅት እሱ ተወልዶ ባደገበት አቃቂ አካባቢ የሚካሄደውን የአርሶ አደሮችን የማፈናቀል ስራ በመቃወም ምክንያት አቶ አሊ አብዶ የአነግ ታጔላ ለጥፎበት ለረጅም አመታት ከድርጅት ካድሬነትና የመንግስት ስራ አባሮታል።

አሊ አብዶ በተራው ውርደት ተከናንቦ ከአዲሳባ ጓዙን ጠቅልሎ ሲወጣ በግፉ የተባረሩ ካድሬዎች እንዲመለሱ በተወሰነው መሰረት ተክሌ ድርጅቱን በድጋሚ ተቀላቀለ። የልደታ ክፍለ ከተማን የፓለቲካ ስራ በበላይነት እንዲመራ ስልጣን ተሰጠው።

በምርጫ 97 ለአዲሳባ ምክር ቤት ኢህአዴግን ወክለው በልደታ ከቀረቡ እጩዎች አንዱ ተክሌ ሆነ። በዚህ ሳይወሰን የክፍለ ከተማው ምርጫ ስራ በበላይነት እንዲያስተባብር ተመደበ። በዚህም ምክንያት እንደሌሎቻችን ሁሉ ማታ ማታ ኢህአዴግ ቢሮ እየመጣ ለአቶ በረከት ተስፉ አስቆራጭ ሪፓርት ማቅረብ ይቀጥላል። በወቅቱ ከነበረው ሀቅ ጋር ፊት ለፊት መጋፈጥ ውርደት የመሰለው በረከት ከፍ ዝቅ አደረገው፣

"ልደታ ላይ ብንሸነፍ ተጠያቂው አንተ ነህ!" በሚል ማስፈራሪያ ጭምር አስጠነቀቀው።

ተክሌ ዛቻውን ከቁብ ሳይቆጥር ልደታ ላይ የማሸነፍ እድላችን ከሀምሳ ፐርሰንት አይበልጥም በማለት መከራከሩን ባለማቆሙ ከስብሰባ ታገደ። በምትኩ ከትግራይ አርከበ ይዞት የመጣውና የልደታ ምክትል ከንቲባው ዘሩ እንዲሳተፍ ተደረገ። ዘሩ ከምርጫ በኃላ ተክሌን እንዲያባርረው ተልእኮ ተሰጠው። ዘሩ የአራዊት ባህሪ ያለው፣ በጫካ ህግ የሚመራና እንቁራሪትን ዝሆን የሚያሳክል ሰው ነው።

የግንቦት ሰባቱ ምርጫ በልደታ ያልተበቀ ነገር ይዞ ብቅ አለ። በደህንነቶች ማስፈራራት ምክንያት ከምርጫው ራሱን እንዳገለለ በተነገረው የቅንጅት እጩ ምክንያት ስድስት የኢህአዴግ እጩዎች እርስ በራስ ተፋጠጡ። ብዙዎቻችን በኢህአዴግ ነባር ታጋይነቱ ለሚታወቀው ም/ከንቲባ ህላዌ ዮሴፍ ግምታችንን ሰጠን። በተቃራኒው የልደታ ህዝብ አምስት የቅንጅት እጩዎችን ከመረጠ በኃላ ቀሪዋን ወንበር ለተክሌ ሰጠ።

በአዲሳባ ደረጃ ከነበረው 138 የምክር ቤት ወንበር ውስጥ አንዷን ብቻ

ኢህአዴግ በተክሌ አማካኝነት አገኘ። ሌሎቻችን በዝረራ ወጣን። ስም ከማውጣት ቦዝኖ የማያውቁት ካድሬዎች ተክሌን "አንድ ለእናቱ" አሉት።

ምርጫው በተጠናቀቀ በሳምንቱ ኢህአዴግ ደጃፍ እንዳይደርስ ተብሎ ተወስኖበት የነበረው ምስኪኑ ሰው የተለየ ክብር ተሰጥቶት ለሌላ ትልቅ ስራ ተጠራ። ቅንጅት ስልጣን ከተረከበ በኋላ የሚካሔዱ ህገ - ወጥ ተግባራትን እየተከታተለ በምክር ቤት ጉባኤዎች ላይ የማጋለጥ ስራ እንደሚሰራ ተነገረው። ከደህንነት ቢሮ በየጊዜው ወቅታዊ መረጃዎችን የሚያገኝበት ሁኔታ ተመቻቸለት። አፍታም ሳይቆይ በሚስጥር የተያዙ መረጃዎች ይቀርብለት ጀመር። ከእነዚህ ውስጥ በእንባ ጠባቂ ኮሚሽን የሚመራ "የአዲሳባ ህዝብ ቅሬታ ማስተናገጃ ጽ/ቤት " እንደሚቋቋምና እሱ የበላይ ሀላፊ እንደሚሆን የሚጠቀሱ ናቸው።

የቅሬታ ማስተናገጃው ቢሮ የህዝብ ሮሮዎችንና በተደራጀ መንገድ እንዲያስተናግድ የታሰበ ነበር። በየቀበሌው ሊመደቡ የተዘጋጁት ቋሚ ምድብተኛ ካድሬዎች ቁልፍ ስራ የህዝብ ብሶቶችን በማሰባሰብ ተክሌ ለሚመራው ቢሮ ማስተላለፍ እንደሚሆን ተገለፀ። ከዚህ በተጨማሪም ከጐበልስ ቲዎሪ አንዱ የሆነውን "ኩነቶችን በመሪ ቃል መምራት "በሚለው መሰረት "ቅንጅቶች ቃላችሁን ጠብቁ "የሚሉ አስተዳደሩን የሚያስጨንቁ ግፊቶች እንደሚደረጉ፣ ለዚህ ስራ ግብአት እንዲሆኑ ቅንጅት በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት አሰራቸዋለው ብሎ ቃል የገባቸው እቅዶች ዶከመንት መደረግ ተጀመሩ።

ጉራማይሌው ቅንጅት እንኳን ሊፈፅማቸው በአፍ ወለምታ ሊናገራቸው የማይገባ ቃሎች ባለቤት ነበር። ለተፃራሪ ወገን መልስ ለመስጠት በሚል ብቻ ነባራዊ ሁኔታውን ከግምት ሳይገባ የማይፈፀሙ እቅዶችን መናገር ከግምት ይከታል። "በአምስት አመት ውስጥ ግማሽ ሚሊዮን ቤት ገንብቼ የመዲናይቱ ህዝብ ከቤት እጦት አላቅቃለው" በሚለው ቅስቀሳ መካከልና "ወተት በቧንቧ" በሚለው መካከል ልዩነቱ ምንድነው?

እናም ተክሌ "ቅንጅቶች ቃላችሁን ጠብቁ!" ለሚለው መፈክር እንዲዘጋጅ ተነገረው። ይህንን ተከትሎ ለከፍተኛ ጭንቀት ተዳረገ። ከእሱ ጋር ቅርበት ከነበራቸው ካድሬዎች ጋር ተማከረ። አፍታም ሳይቆይ መስከረም ሳይጠባ የሚወዳትን ሀገር ጥሎ ወደ አውሮፓ ተሰደደ።

የተክሌ መኮብለል በኢህአዴግ ውስጥ ከፍተኛ መደናገጥ ፈጠረ። እሱን ማዕከል ተደርገው የተቀረፁ እቅዶች ደራሽ ውሀ ወሰዳቸው። በአዲሳባ ምክር ቤት "አንድ ለእናቱ" ተብላ የተሰየመችው የኢህአዴግ መቀመጫ ባዶዋን ቀረች።

ሀቁ ይህ ሆኖ ሳለ አቶ በረከት ጽፎ ባስነበበን ወግ ላይ፣

"...የኢህአዴግ ተወካይ የአዲሳባ ምክር ቤት አባል ሆኖ ቅንጅት በሚመራው ምክር ቤት ሊሳተፍ ተዘጋጅቶ ነበር ... " ብሎናል።

የግንቦቱ ምርጫ በተጠናቀቀ በወራት ውስጥ ሀገር ጥሎ የወጣን ሰው ምክር ቤት ሊገባ ተዘጋጅቶ እንደነበር የተገለፀበት ምክንያት ግልፅ ነበር። ኢህአዴግ በተሸነፈበት ሁኔታ የህዝብ ድምፅ እንደሚያከብር፣ በተቃራኒው ተቃዋሚዎች ሙሉ በሙሉ ባሸነፉበት ሁኔታ የህዝብን ድምፅ ወደ ጐን ትተው አስተዳደሩን ለመረከብ አምቢተኝነታቸውን ለማሳየት ነበር...

ለጋራ ድል ያልታደለው የኢትዮጵያ ፓለቲካ!

***

አሳዛኙ ታሪክ

በምርጫ 2000 ኢህአዴግ ሁለት የተቀናጁ ስትራቴጂዎችን ቀርጾ በተግባር ላይ አውሏል፡ - የህዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎ ማስፋትና ከምርጫው ሂደት ይልቅ ለውጤቱ ትኩረት መስጠት የሚሉ። እነዚህ ስትራቴጂዎች ኢህአዴግ ይዘቱን ቀይሮ ቅርፅን ብቻ ይዞ እንዲቀር አድርገውታል።

በመሆኑም ዲሞክራሲው ወደ 300 አመተ አለም ቁልቁል በመምዘግዘግ ማረፊያውን ግሪክ አቴንስ አድርጓል። አብዮታዊነት ጦሴን ጥንቡርሳሴን በማለት ጓዙን ጠቅልሎ ከኢህአዴግ ተሰናብቷል። የመድብለ ፓርቲ ስርአት ግንባታ ወደ "ላም አለኝ በሰማይ..." ተቀይሯል። ኢህአዴግ ቻይናን ተከታይ አድርጐ በአለም ተወዳዳሪ የሌለው አባላትና ካድሬ ብዛት በመያዝ ጊነስ ቡክ ላይ እንዲሰፍር ጫፍ ላይ አድርሶታል።

በሌላ በኩል እነዚህ አዲስ አቅጣጫዎች ከአጭር ጊዜ አኳያ ኢህድግን ጠቅመዋል። ምርጫ ከመካሄዱ አስቀድሞ ኢህአዴግ ሁሉን አሟጦ እንዲወስድ በማድረግ አሸናፊነቱን አረጋግጧል። በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ከመንግስት ካዝና ወደ ድርጅቱ እንዲገባ አድርጓል። ተቃዋሚዎች የተሰፉ መቁረጥ ጉዞን እንዲጀምሩ በር ከፍቷል።

ይህ የአዲሳባን ብሎም የአገሪቷን መፃኢ እድል ያጨለመ ታሪክ "የኢህአዴግ ነጫጭ ዝሆኖች" በሚል ርዕስ በሌላ ማስታወሻ ላይ በሰፊው ይተረካል። ያለጊዜው የተነሳው በአጋጣሚ ሳይሆን የ "አሳዛኙ ታሪክ " መነሻ ስለሆነ ነው።

አሳዛኙ ታሪክ የግለሰብ ታሪክ ቢሆንም። በድርጅቱ ከፍተኛ ካድሬዎች በደል የደረሰበት ምስኪን

ጉዳዩ እንዲህ ነው።

አሳዛኙ ሰውና የዚህ ታሪኩ ባለቤት ይችላል ፈንታ ይባላል። ይችላል በአዲሳባ አስተዳደር መሬት አስተዳደር ውስጥ ከፍተኛ ሙያተኛ ነበር። በሰራ ትጋቱና ቅንነቱ ምክንያት በሰራተኞች ተቀባይነት በማግኘቱ ባለስልጣን ሆነ። የኢህአዴግ አይን አረፈበት። ለድርጅት አባልነት ቢጠየቅ "በየትኛውም ፓርቲ ውስጥ ገብቼ የመንቀሳቀስ ፍላጐት የለኝም" በማለት አሻፈረኝ አለ። ምርጫ 2000 ሲመጣ የአዲሳባ ምክር ቤት አባል ሆኖ ህዝቡን እንዲያገለግል የቅርብ ጓደኛው በሆነው ካህሳይ የሚባል ካድሬ ተለመነ። ካህሳይ የአዲሳባ ትራንስፓርት ባለስልጣን ም/ዴሬክተር ሲሆን የኢህአዴግ የመንግስት ተቋማት አደረጃጀት ሀላፊ ነበር።

ይችላል ከጓደኛው የቀረበበትን ግፊት መቋቋም አቅቶት ኢህአዴግን ወክሎ ለምክር ቤት ለመወዳደር ፍቃደኛ ሆነ። ለአዲሳባ ካቢኔ አባልነትም ምርጫው ሳይካሄድ ታጨ።

የ2000 የአዲሳባ ዳግም ምርጫ ኢህአዴግ ሙሉ ለሙሉ እንደሚያሸንፍ በመረጋገጡ ምክንያት ፓርቲው ያቀረባቸውን እጩዎችን ለህዝብ ለማስተዋት አቀረበ።ከእነዚህ ውስጥ ይችላል አንዱ ነበር።

ይችላል በሶስት ቦታዎች ለግምገማ ቀረበ። የመንግስት ሰራተኞች መድረክ፣ በሚኖርበት ክፍለ ከተማና ቀበሌ ። በሶስቱም መድረኮች ኢህአዴግ እሱን ይዞ በመቅረቡ ተወደሰ። ይችላልን የመሰለ ሀቀኛና ትጉህ ሰው ፓርቲው በማምጣቱ ምስጋና ቀረበለት። ይህን ተከትሎ ይችላል ራሱን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም በከፍተኛ ድምፅ ይዞ መውጣት እንደሚኖርበት ተልእኮ ተሰጠው። እሱም ወደ ህዝቡ እየወረደ፣

"እኔን ብቻ ብትመርጡ ዋጋ የለውም። የምትመኙት ልማት እንዲመጣ ጓደኞቼንም ምረጡ" በሚል ከራስ የዘለለ ምርጫ ቅስቀሳ ተጠመደ።

የምርጫ ቦርድ እጩ ምዝገባ ተጠናቆ ምርጫው ሁለት ሳምንት ሲቀረው አስደንጋጭ ነገር ተከሰተ። የቅርብ አለቃዬ ህላዌ ዮሴፍ ቢሮው ጠርቶኝ " ችላል ላይ የሚነሱበት ነገሮች ስላሉ በሁለት ቀን ውስጥ አጣርተህ ና!" የሚል ትእዛዝ ሰጠኝ።

በሁለተኛው ቀን ከመሬት አስተዳደር ሰራተኞችና የቀበሌ ካድሬዎች

አጣርቼ የመጣሁትን ሪፓርት አቀረብኩ። የግለሰቡ ተቀባይነት እያደገ መምጣቱንና በእሱ ምክንያት ሌሎች እጩዎቻችን ይሁንታ እንዳገኙ ነገርኩት።

"ይህቺ አዜብ መስፍን የምትባል ሴትዮ ከየት አምጥታ ነው የምትዘላብደው? መቼ ይሆን ሰከን ብላ ማሰብ የምትጀምረው? ሰውየውን አቃጥላ ልትገለው ነው!" አለኝ።

"ደግሞ ምን አለች?"

"እኔ እኮ ግራ የሚገባኝ የእሷ መረጃ ምንጭ ከሌላው የተለየ የሚፈበርክበት ምክንያት ነው! ልማታዊ ባለሀብቶችን አላሰራ በማለት ደንቃራ ሆኗል፣ በሙቶ ሺዎች ጉቦ ይጠይቃል ትላለች። ለማንኛውም ዝርዝሩን ለበረከትና መለስ ነግሬያቸዋለሁ ስላለች ካሚልና ፀጋዬን ይዘሀቸው በረከት ቢሮ እንገናኝ" አለኝ።

ከሰአታት በኃላ ተጠራርተን ወደ በረከት ቢሮ አመራን።

በምርጫ 97 ዋዜማ የነበረውና በተመሳሳይ ወቅት በምርጫ 2000 ያለው በረከት ስምኦን የተለያዩ ናቸው። አንፃራዊ በሆነ መንገድ መረጋጋት ይታይበታል። አስቀድመው የተወሰዱት እርምጃዎች ሀሳቡን አውርደውታል። ርግጥም ከምርጫ ውጤት አንፃር የሚያሳስብ አልነበረም። አስቀድሞ ውጤቱ ታውቋል።

የተበላ እቁብ!

በረከትን የጨነቀው አንድ ነገር ብቻ ነው። ይህ ለኢህአዴግ ታማኝ ያልሆነ ህዝብ ወደ ምርጫ በመውጣት ይመርጣል ወይ? የሚለው ጥያቄ ፉታ ነስቶታል። በየሁለት ቀን ከእሱ ጋር በሚኖረን ስብሰባ ማረጋገጫ የሚፈልገው ህዝቡ በነቂስ እንዲወጣ ምን እንደሰራን ማወቅ ነበር። እኛም በየቀኑ በነበረን ዳታ ላይ አስር ሺህ እየደመርን እንመጣለን። እሱም የሞባይሉን ካልኩሌተር የየቀበሌውን በመደመር ፉታ ይነሳታል።

ተጠራርተን በአስቸኳይ የተሰባሰብነው ከወትሮ የተለየ ኢንፎርሜሽን ስለመጣ እንደሆነ በረከት ገለፀልን፣ "አንዳንድ ጓዶች ይችላል በሚባለው እጩ ላይ ችግሮች እያነሱ ስለሆነ እንዲሰረዝ ማመልከቻ ለምርጫ ቦርድ እንድታስገቡ አዘጋጅቼያለሁ" ብሎ ወረቀቱን ሰጠን። ጉዳዩን ለውይይት ክፍት ማድረግ እንዳልፈለገ ተረዳን።

ከወይዘሮ አዜብ የመጣ ትእዛዝ ላይ ክርክር ማድረግ ውሀ ቢወቅጡት እንደሆነ ከልምዳቸን እናውቃለን። በምርጫ ቦርድ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እጩ የመቀየሪያ ጊዜ ስላለፈ ምን ማድረግ እንዳለብን ፀጋዬ ጠየቀ። ፀጋዬ የምርጫውን አስተዳደራዊና ህግ ነክ ጉዳዮች ይከታተላል።

ህላዌ የበረከትን ምላሽ ሳይጠብቅ፣

"የምርጫ 97 ታሪክ በተገላቢጦሽ ይደገማል!" ብሎ ተናገረ። በረከት ግራ ገባው። ምርጫ 97 በህይወቱ የማይረሳቸውን ትላልቅ ትዝታዎች የህይወት ማርግዳው ላይ ጽፎ ስላለፈ ይህንን መለስተኛ ክስተት ቢዘነጋው የሚገርም አልነበረም። ይህንን የተረዳው ህላዌ ታሪኩን ወደ ኋላ ተመልሶ ተረከለት።

ባልተጠበቀ መልኩ በረከት ከአዳማጭነት ወጥቶ በደስታና ስሜት በተቀላቀለበት ሁኔታ የካርል ማርክስን፣ "ታሪክ ራሱን ይደግማል፣ በመጀመሪያ ላይ አሳዛኝ፣ ቀጥሎ ቧልት በሚመስል መንገድ!" ብሎ ጮኸ። ቀጥሎም የዚህን ጥቅስ ታሪካዊ አመጣጥ አስረዳን።

ካርል ማርክስ ይህንን ጥቅስ የተናገረው በ19 ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ጀምሮ በፈረንሳይ መካሄድ በጀመረው አብዮት አዲስ ገዥ መደብ የተፈጠረበትን ሁኔታ ለማሳየት እንደሆነ፣ በሉዊ ቦናፓርት ቤተሰባዊ የስልጣን ቅብብሎሽ ተመሳሳይ ታሪክ በመፈፀሙ ያንን ለመግለፅ እንደሆነ አስተማረን። በረከት በፈረንሳይ አብዮትና ካርል ማርክስ ፍልስፍናዎች ላይ የተሻለ እውቀት አለው። ከመፅሀፍቶቹ የሚያገኘውን ቁምነገር ከወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር በማጣጣም ወደ ተግባር ይመነዝራቸዋል።

የአሁኑ ተረኛ ይችላል ሆነ!

ይችላልን ከእጩነት እንደሰረዝነው ለህዝብ መግለፅ እንደሚገባን፣ በመግለጫችን ላይ ኢህአዴግ በመርህ ደረጃ የሰናፍጭ ቅንጣት የምታክል ቅሬታና የሌብነት ጥቆማ የቀረበበትን ሰው እጩ አድርጐ ለማቅረብ ፍላጐት እንደሌለው፣ የይችላል ውሳኔ ከዚህ የእምነት ማእቀፍ የሚነጨ እንደሆነ መግለፅ እንዳለብን አሳሰበ። መግለጫውን ደግሞ እኔ እንደምሰጥ፣ ለየትኛው የሚዲያ ተቋም የሚለውን ከደቂቃዎች በኋላ እንደሚያሳውቀኝ ተነግሮ ስብሰባው ተጠናቀቀ።

በየቀኑ ጆሮ የሚያደነቁር የሌብነት መረጃ የሚነሳባቸው እነ መላኩ ፋንታ ለከንቲባነት እጩ በሆኑበት ሁኔታ በመልካም ስሙ የሚታወቀውን ግለሰብ ያልሆነ ስም ለጥፊ ለመናገር መዘጋጀቴ አበሳጨኝ።

(በመላኩ ፋንታ ድጋፍ በእግዚአብሔር የሚባል የቅርብ ጓደኛው በአጭር ጊዜ ውስጥ ከአርከቴክትነት ወደ ሚሊየነር መቀየሩ በሰፊው ይነገር ነበር። ይህ ግለሰብ ሩብ ሚሊዮን የሚያወጣ የወጣቶች ማእከል ግንባታ ዲዛየን በመስራት ለመንግስት በነፃ አበርክቷል። ልማታዊ ባለሀብት ተብሎ ከአቶ መለስ

ሽልማት ያገኘ ሲሆን ፣ከሀገር ከወጣሁ በኃላ የህዳሴው ግድብ አስተባባሪ ሆኖ በድጋሚ ሽልማት ተቀብሏል።)

እነዚህ መሬት ላይ የተፃፉ ሀቆች ናቸው። በረከትም ሆነ ህላዌ ያውቋቸዋል። ታዲያ ለምን እኔ ተለይቼ መግለጫውን እንድሰጥ ተደረገ ? ለምን ህላዌ? ለምን ካሚል?ለምን ፍሬህይወት?

ከደቂቃዎች በኋላ የኢህአዴግ የህዝብ ግንኙነት ሀላፊ ሴኮቱሬ ጌታቸው በኢንተር - ኮም ደወለልኝ። በረከት ያዘጋጀው የሚዲያ ተቋም አዲስ ነገር እንደሆነና ጋዜጠኛዋ ጽዮን ግርማ እንደምትባል ነገረኝ። ኢንተርኮሙ ሳይዘጋ ስልኬ ጮኸ። የአዲስ ነገር ጋዜጠኛዋ ጺዮን ነበረች።

በስብሰባ የወሰነውን ቃል በቃል ነገርኳት።

"አቶ ይችላል ከእጩነት የተቀነሰው የአያት መኖሪያ ቤት ስራ ድርጅት በሙስና አስቸግሮኛል የሚል ቅሬታ ስላቀረበ ነው የሚባለው እውነት ነወይ?" ብላ የማለውቀውን ጥያቄ ጠየቀችኝ። ለጊዜው በግለሰብ ጉዳዬ ላይ በዝርዝር መናገር እንደማልፈልግና ተጣርቶ ለህዝብ ይፉ እንደሚሆን ገልጬ ተሰናበትኳት።

አቶ በረከት ከግል ፕሬሶች አምርሮ የሚጠላውንና ከትሮይ ፈረሶች ጐራ የቀላቀለውን አዲስ ነገር ጋዜጣ የመረጠበት ምክንያት ለረጅም ጊዜ እንቆቅልሽ ሆኖብኝ ነበር። ኮሙዩንኬሽን ጽ/ቤት የእሱ ምክትል ሆኖ ስመደብ የሚስጥሩ ቁልፍ ተገለፀልኝ።

በንጋታው ቅዳሜ አዲስ ነገር ጋዜጣ ዜናውን በፊት ገፅ ይዛ ወጣች። የይችላል ከኢህአዴግ እጩነት መሰረዝ ምክንያት አያት ባቀረበበት ቅሬታና የሙስና ጥቆማ እንደሆነ እኔን እንደ ቃል አቀባይ በመግለፅ አቀረበች። በወቅቱ ስለምርጫው ከተዘገቡትና ከተነበቡት ዜናዎች ትልቁ ሆነ።

እነ መላኩ ፉንታን የመሳሰሉ በሙስና የተጨማለቁ እጩዎች በየደረጃው በቀረቡበት ሁኔታ በጥቆማ ብቻ እጩን ማግለል በር ግጥም ትልቅ ዜና ነበር። የኢህአዴግ ሁሉን አሟጦ የመውሰድ ግብ የተቀየረበት ሁኔታም መኖር በተጨማሪ ሊያነጋግር ይችላል።

ጋዜጣዋ በወጣች እለት ባለው ከሰአት የመንግስት ቢሮዎች ሀላፊው ታጋይ ካህሳይና ይችላል ቢሮዬ መጡ። ቀጠሮ ስላልነበረንና ያልጠበኩት ስለሆነ ደነገጥኩኝ። ሁለቱም አዲስ ነገር ጋዜጣ በሁለት እጃቸው ይዘዋል።

ይችላል በጋዜጣው ላይ እሱን በተመለከተ የሰፈሩትን ቁም ነገሮች በቀይ ብእር ያሰመረበት ከርቀት ይታያል። ከንዴቱ ብዛት እጁ ይንቀጠቀጣል፣ አይኖቹ ደም ለብሰዋል።

ለደቂቃዎች ዝምታ ወረሰን።

ይችላል ገነፈለ። ሲቃ እየተናነቀው ስለ እሱና አያት የመኖሪያ ቤት ስራ ድርጅት ያለመግባባት ምክንያት አስረዳኝ። ኢህአዴግና መንግስትን እያታለለ የሚኖር ድርጅት አንደሆነ፣ ህገ መንግስቱን በመፃረር ባዶ መሬት እያጠረ እንደሚቸበችብ፣ በሲኤምሲ እና በአየር ጤና አካባቢ ለታይታ የሚሆኑ ትናንሽ ሰርቪስ ቤቶችን እያሰራ ባዶውን ቦታ በመቶ ሺዎች እንደሚሸጥ፣ ከዛም አልፎ የግንባታ ደረጃው ለባንክ ብድር የማያበቃው ሆኖ ሳለ የተሳሳተ መረጃ እንዲሰጥ አማላጅና ጉቦ ልኮለት እንደነበር፣ በመሬት አስተዳደር ውስጥ ከአያት ጋር ተመሳጥረው የሚሰሩ ሙያተኞችና መሀንዲሶች መኖራቸውን በማስረጃ አስደግፎ አቀረበ።

እንባው በጉንጮቹ መስመር ሰርተው ፈሰሱ። ሲቃ አስቸግሮት መናገር አቆመ።

ካህሳይ በበኩሉ የህውሀት/ኢህአዴግ አመራሮች በተለይም ወይዘሮ አዜብና ትግራይ ልማት ማህበር (ትልማ) በአያት ጉዳይ እንደተሳሳቱ ገለፀ። በፓርቲው ሰነድ ውስጥ እንደተጠቀሰው ከባለስልጣናት ጋር በመሞዳሞድ ተጨማሪ እሴት ሳይጨምሩ ሀብት ከሚያግበሰብሱት ዋነኛው ሀያት መሆኑን በተቆርቋሪነት ስሜት ውስጥ ሆኖ ተናገረ። ከጨለማው ዘመን ንጉስ አሊ አብዶ ጀምሮ አያት እንዴት ኪራይ እንደሰበሰበ አስረዳን።

ለሁለቱም የምሰጠው መልስ አልነበረኝም። አንደበቴ ተሳሰረ ። ለራስ ያላመኑበትን ነገር እንደመናገር ህሊና የሚጐዳ ነገር የለም። የአበዮታዊ ዲሞክራሲ ምሰሶ ደግሞ ይህ ነው። የበላይ አካል እስከወሰነ ድረስ ተጻረህ መቆምም ሆነ የምታምንበትን መናገር አትችልም።

የት ነው ያለሁት ? ይችላል ላይ የተሰነዘረ ዱላ ነገ ወደእኔ እንደማይዞር ምን ዋስትና አለ? ... እራሴን እያታለልኩት እንደሆነ ተሰማኝ። ቢያንስ በንግግሬ እንዳልረከስ ዝም አልኩ። ገብቶአቸው መሰለኝ ለመሄድ ተነሱ። ይችላል ተሰናብቶኝ ሲወጣ የነበረው ፊት ፣ሲያገኘኝ ከነበረው ጋር ተመሳሳይ ነበር።

***

ቢልተኞቹ ታሪኮች

ከምርጫ 2000 ጋር በተያያዘ በርካታ አቧፊ ታሪኮችን ማንሳት

ይቻላል። ከእነዚህ ውስጥ ኢህአዴግ ብቻውን ሮጦ አሸነፈ እንዳይባል የተፈጠሩት የፓለቲካ ፓርቲዎች፣ ድምፅ አልባ ድምፀኞች በማንባር ቀደምትነት ሊነሱ የሚችሉት ናቸው።

"ባንክና ታንክ"

የ2000 የአዲሳባ ዳግም ምርጫ የመቶ ፐርሰንት የማሸነፍ ግብን ለማሳካት ከሂደቱ ይልቅ ለውጤቱ ትኩረት በመስጠት መፈፀም ተጀመረ። የምረጡኝ ዘመቻውና ውድድሩ የሚዲያ ትኩረት ተነፈገው። በውስጣቸው ምንም አባላት የሌላቸው ብቻ ሳይሆኑ የአንድ ቤተሰብ ዘመዳሞች ተሰብስበው የፓለቲካ ፓርቲ መሰረቱ። አንዳንድ ድርጅቶች የተመሰረቱበት አማባብ የፓለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ በሚፃረር መልኩ ነበር።

በአዋጁ አንቀፅ አራት ንኡስ አንቀፅ ሶስት ላይ አንድ የአገር አቀፍ የፓለቲካ ፓርቲ ህልውና የሚኖረው፡-1500 መስራች አባላት ሲኖሩት፣ ከእነዚህ መስራች አባላት ውስጥ አርባ በመቶ የማይበልጡት የአንድ ክልል መደበኛ ነዋሪዎች ሲሆኑ፣ የተቀሩት መስራች አባላት በኢትዮጵያ ከሚገኙት ክልሎች ውስጥ ቢያንስ በአራቱ ክልሎች መደበኛ ነዋሪዎች ሲሆኑ እንደሆነ ይደነግጋል።

በአቶ አርከበ እቁባይ የጥፋት ዘመን የአዲሳባ አማካሪ ምክርቤት አመራር የነበረ መሳፍንት ሽፈራው (ይህ እንደ ማያ የሚቀያየር ሰው በምርጫ ሁለትሺህ መጠሪያ ስሙ መስፍን ነበረ) የሚባል በአራዳ ክፍለ ከተማ የሚኖር ግለሰብ መላዉ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ንቅናቄ (መኢብን) የሚባል የቤተሰብ ድርጅት አቋቋመ። ድርጅቱ አይደለም ሀገር አቀፍ፣ የክልል ህልውና ሊኖረው የማይችለው መኢብን ምርጫ ቦርድ የሀገር አቀፍ ፓርቲነት እውቅና ሰጠው። በ12 ወረዳዎች ላይ እህቶቹን፣አማቾቹንና ሌሎች የስጋ ዘመዶቹን በእጩነት አቀረበ። ለአስራ ሁለት የፓርላማ መቀመጫ እየተወዳደሩ ያሉትን ቤተሰቦች ዝርዝር ምርጫ ቦርድ ላከልን። ስለ ግለሰቡ ማንነት የሚያሳይ መረጃ ደግሞ ከደህንነትና ካድሬዎቻችን አሰባሰብን።

እንደ ጭራሮ ደርቀው የቀሩት የአየለ ጫሚሶ ቅንጅትና የልደቱ ኤዴፓ ኢህአዴግ ባዘጋጀላቸው እጩ ለውድድር ተዘጋጁ። የጫሚሶ ቅንጅት እንደ መኢብን ሁሉ የሀገር አቀፍም ሆነ የክልል ህልውና የሚያረጋግጥ አልነበረም። የልደቱ ኤዴፓ በድሮው መዝገብ ስለሚንቀሳቀስ የቁጥር ችግር አላጋጠመውም። ኢህአዴግም አዳዲስ አባላት ጨምሮለታል።

ከምርጫው በፊትና በኋላ የልደቱ ፓርቲ በድርጅቱ የወደፊት አቅጣጫ ላይ ለመወሰን በሜክሲኮ መብራት ሀይል አዳራሽ የጠራውን ስብሰባ አጀንዳ የቀረጽነው፣ ተሰብሳቢዎችን ለይተን ያስገባነው እኛና ደህንነት በመቀናጀት

ነበር። ልደቱ በጠራራ ፀሀይ በመብራት ሀይል አዳራሽ በዝማ የመራውን ስብሰባ እኛ ማታ ከቃለጉባኤ እናነባለን። ተጨማሪ መረጃ ካስፈለገን ተልእኮ ተሰጥቷቸው በስብሰባው ከተሳተፉት የኢህአዴግም ኤዴፓም ጥምር አባላት እንወስዳለን። ይህንን ተከትሎ ኢዴፓ ብዙም ሳይቆይ በፓርቲ ደረጃ እንደማይወዳደር ግን ደግሞ ግለሰቦች እንወዳደራለን የሚሉ ከሆነ መብታቸው እንደሆነ የሚያሳይ አስቂኝ መግለጫ አወጣ።

ከ "ባንከና ታንክ" የመቀስቀሻ ማእከላዊ መልእክት ጋር የቆረበው ህብረት እስከ መጨረሻው የምርጫ ቀናት እየተንገዳገደ ቆየ። በአስራአንደኛው ሰአት ከምርጫው ሂደት አቋርጦ እንደወጣ ይፉ መግለጫ አወጣ። በወቅቱ በከፍተኛ ጥቅም ላይ ውላ የነበረችው "ባንከና ታንክ" የፈጠራት አቶ በረከት "አደገኛ ቃላት ከመፈብረክ የማይቦዝነው የጠባቦች ንጉስ" ብሎ የሚጠራው ዶ/ር መራራ ጉዲና ነበር። ዶክተሩ ተራ በተራ የፓርቲውን ካድሬዎች በዝህች ምትህተኛ ቃል አደቁኖበታል። በተለይም መምህር ወንድሙ የሚባሉ የፓርላማ አባልና የህብረት ከፍተኛ አመራር በምርጫ ክርክር በቀረቡ ቁጥር አልፉና አሜጋቸው "ባንከና ታንክ" ሆኖ ነበር።

የአጋጣሚ ነገር ሆኖ እኔና የስራ ባልደረባዬ የነበረው ፀጋዬ ሀ/ማርያም የአዲሳባ ኢህአዴግን ወክለን፣ መምህር ወንድሙ ደግሞ ህብረትን ወክለው ለሶስት ያህል ጊዜያቶችና ቦታዎች (አፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን፣ ባህል ማእከልና ማዘጋጃ ቤት) የምርጫ ክርክር አድርገን ነበር።

ታዲያ በማዘጋጃ ቤት በተካሄደው የመጨረሻ ክርክር ወቅት እኔና ፀጋዬ በመኢብኑ የቤተሰብ ፓርቲ ፕሬዝዳንት አቶ መስፍንና መምህር ወንድሙ ላይ ተንኮል አዝለን ወደ መድረክ ወጣን። የተከበሩ መምህር ወንድሙ ለመከራከሪያ ያዘጋጁት ሰነድ ቀድሞ የደረሰን በመሆኑ በጋራ ተመልክተነዋል። በእያንዳንዱ አንቀፅ ላይ ይቺ እንደ ጅብ ቆዳ ተጣብቃ የቀረችባቸው ቃል በመሸጋገሪያነት ተቀስራለች።

የማዘጋጃ ቤቱን ክርክር እንዲመራ የኢህአዴግ አባል የሆነ ፕሮፌሰር አደረግን። ፕሮፌሰሩ በአዲሳባ ዩንቨርስቲ የሚዲያና ኮሙዩኒኬሽን ፉክልቲ መምህርና ሀላፊ ነው። የፕሮፌሰሩ ባለቤት ደግሞ (ወ/ሮ ስንቅነሽ አጣለ ትባላለች) ኢህአዴግን ወክላ ለአዲሳባ ክልል ምክርቤት ትወዳደራለች። ሴትየዋ አፈጉባኤ እንደምትሆን አስቀድሞ ተነግሯት ነበር። በተግባርም ለሁለት አመታት መዶሻ ተሰጣት። እንግዲህ ባል አከራካሪ፣ ሚስት ተከራካሪ የሆነበት ቧልተኛው የኢህአዴግ ፓለቲካ ይህን ይመስላል።

በክርክሩ የድልድል ሰአት የመጀመሪያ ዙር ቅድሚያውን ኢህአዴግ እንዲወስድ ተስማማን። የሁሉም ፍላጐት ስለነበር በቀላሉ ተሰጠን። ፀጋዬ ንግግሩን ገና ሲጀምር በቀልደኛ አንደበቱ እንዲህ በማለት ተናገረ፣

"የተከበሩ የፓርላማ አባል መምህር ወንድሙ ባለፉት ሁለት ክርክሮች

መምህርነታቸው አገርሽቶ ባንክና ታንክ ነዐ (ባታ -ነዐነ) እና ባታ -ነዐ2 ኮርስ ሰጥተውን ነበር። ከሚገባው በላይ ገብቶናል። ኢህአዴግ ለእሳቸውና ድርጅታቸው የኮፒ ራይት መብት ይገባቸዋል ብሎ ያምናል። ይህቺን ወደ ስልጣን የምታመጣ ምትሀተኛ ቃል ሌላው መጠቀም ከፈለገ ከኦርጅናል ባለቤቶቹ ፍቃድ መጠየቅ ይኖርበታል።"

የተከበሩ መምህር ወንድሙ የመናገር ተራቸው ደርሶ ገና "ባንክና ታንክ" የሚለውን ቃል ሳይጨርሱ በአዳራሹ የተሰበሰበው ህዝብ በሳቅና ሁካታ ግራ አጋባቸው። የሚናገሩት ጠፍቶአቸው ሲንዘባዘቡ ዋሉ።

የሞኝ ለቅሶ እንዲሉ ከአምስት አመታት በኃላ በስደት ባለሁበት ሀገር በሚተላለፈው ኢሳት የሚባል ቴሌቭዥን ላይ በእንግድነት የቀረቡት የቀድሞው ህብረት የአሁኑ መድረክ ከፍተኛ አመራር የተከበሩ አቶ ገብሩ ገ/ማርያም ሳይበረዝና ሳይደለዝ ሌጋሲውን በጠበቀ ሁኔታ "ባንክና ታንክ" ሲሉ ሰማሁ። በመጥፎ ትዝታ ባህር ተሻገርኩ። እናንተዬ! ለካስ ይሄ ሌጋሲን ሳይበረዝና ሳይቀነስ ማስቀጠል የሚለው አባባል በተቃዋሚዎቻችንም ዘንድ አለ !!

***

"የአቶ መለስና ሚስታቸው ዙፋን!"

ወደ ማዘጋጃ ቤት ክርክር ተመልሰናል።

ከተከበሩ መምህር ወንድሙ ቀጥሎ እድሉን ያገኙት የመኢብኑ ፕሬዝዳንት አቶ መሳፍንት ሽፈራው ነበሩ። የአቶ መሳፍንት መተዳደሪያ ስራ ድለላ የነበረ ሲሆን በ1995 በጊዜያዊነት በተቋቋመው የከተማው አስተዳደር አማካሪ ምክርቤት ውስጥ በመልካም አስተዳደር ቋሚ ኮሚቴ ውስጥ አገልግሏል። በሁለት ሳምንት አንድ ጊዜ በማዘጋጃ ቤት በመገኘት የሚያደርገው ስብሰባ ራሱን እንደ አስፈጻሚ እንዲቆጥር አድርጐታል። በተለይም በወቅቱ ከንቲባ የነበረውን አቶ አርከበ በማዳነቅና በማሞገስ የሚናገር ስለነበረ ሰፊ የሚዲያ ሽፋን አገኘ። ይሄ አጋጣሚ የቀድሞ ስራውን በመተው ወደ "ጉዳይ አስፈጻሚነት" አሸጋገረው። በአራዳ በሚኖርበት የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ውስጥ ጉዳይ ማስፈፀሙን ቀጠለበት። አስገራሚ ማስታወቂያዎችን በየመሸታ ቤቱ መናገር ጀመረ። ከእነዚህ ውስጥ፣

"ከቡር ከንቲባው ጋር ቀርቦ የሚፈፀም ጉዳይ አለዎት? እንግዲያውስ የአማካሪ ምክርቤት አመራሩን መሳፍንት ሽፈራው ቀርበው ያማክሩ !" የሚለው አንዱ ነበር። ግፍና መከራ ወገቡን ያጐበጠው ህዝብ ያገኛትን ቀዳዳ ሁሉ ለመጠቀም መኳተኑ አይቀርምና በርካታ ማመልከቻዎች ለአቶ መስፍን ደረሰው። በዛው ልክ ኪሱ መሙላት ጀመረ።

የግንቦት 97 ማእበል የአቶ አርከበን የነቀዘ ገሸር መደብ ጠራርጐ ከከተማዋ ሲያባርር የአቶ መሳፍንት ጥገኛ ጥቅም አብሮ ተቋረጠ። ወደ ሌሎች አማራጮች ተሸጋገረ። ባለአደራ አስተዳደሩ ውስጥ ለመግባት ያደረገው ጥረት ሳይሳካ ቀረ። ለገሾዎች ማደግደግና አጠገባቸው መንጐዳጐድ የሚያስገኘውን

ጠቀሜታ በተግባር ያረጋገጠው የአራዳው ጩልሌ "መኢብን" የሚባል ፓርቲ መስርቻለሁ ብሎ ብቅ አለ። ለድህረ ምርጫ 97 ሁከትና ብጥብጥ ተጠያቂዎች አክራሪ ተቃዋሚዎች ናቸው የሚል መግለጫ በማውጣትና መኢብን የኢህአዴግ ታማኝ ተቃዋሚ ሆኖ እንደሚቀጥል በኢቲቪ ቀርቦ መግለጫ ሰጠ።

አቶ መሳፍንት በማዘጋጃ ቤቱ ክርክር ሰአት ለኢህአዴግ ያለውን ታማኝነት አረጋግጦ የዘንድሮ የአዲሳባ ምርጫ ብርቱ ፉክክር የሚደረገው በመኢብንና ኢህአዴግ መካከል ብቻ እንደሚሆን፣ ሌሎቹ ተቃዋሚዎች ህዝቡ አንቅሮ እንደተፋቸውና እዚህ ለክርክር ከተቀመጡት ውጪ ሌላ አባል እንደሌላቸው በኩራት ተናገረ። አጠገቤ የተቀመጡት የቅንጅቱ አየለ ጫሚሶ የግንባራቸው ደም ስር ወጣ ገባ መስመር ሰራ። ከእሳቸው የተቀመጡበት ወንበር ገዝፎ ታየ።

ርግጥም አቶ መሳፍንት እውነቱን ነበር። የጫሚሶ ቅንጅት በኢህአዴግና ምርጫ ቦርድ አማካኝነት ከቀድሞ ቅንጅት የአልጋ ወራሽነት ያገኘው አቶ መለስ የቆረጧትን የሁለት ጣት አርማ ብቻ ነበር።

በሁለተኛው ዙር የክርክር ሰአት ኢህአዴግን ወክዬ እንድናገር ለእኔ እድሉ ተሰጠኝ። ቀጣይ ትኩረት ያደረግነው አቶ መሳፍንት በመሆኑ በ12 የተለያዩ ወረዳዎች መኢብን ያቀረባቸውን ሰዎች እስከ አያት አነበብኩ። መኢብን በለስ ቢቀናው የኢትዮጵያ ፓርላማ ደርዘን የሚሞሉ የአንድ ቤተሰብ አካላት በመያዝ ታሪክ ይሰራ እንደነበረ ተናገርኩኝ። ከአዳራሹ ጩኸት በላይ የአቶ አየለ እንባ ያዘለ ሳቅ ጆሮዬን ሰቀጠጠው። የጫሚሶ አንጀት ቅቤ ሲጠጣ አየሁት።

አቶ መሳፍንት ያልጠበቀው ስለሆነ ተወራጨ። ተራው ሳይደርስና ሳይፈቀድለት፣

"ኢህአዴግ የራሱን ጉድ በጉያው ሸሽጐ ስለሌላ ያወራል። አቶ መለስና ሚስታቸው የተቀመጡበት የፓርላማ ዙፋን ክብደት ሁሉም የሸንጐ አባላት ተጨፍልቀው አይደርሱበትም" በማለት ጮኸ። በአንድ ግዜ ታማኝ ወዳልሆነ ተቃዋሚ ተሸጋገረ። የክርክሩን ማሳረጊያም የአቶ መለስና ሚስታቸው ዙፋን ግዝፈት ማሳየት ሆነ።

ማምሻውን ኢቲቪ የተካሄደውን ክርክር የዜና ሽፋን ሰጠው። የአዲሳባ ፕሮግራም ደግሞ በልዩ ፕሮግራም እንደሚያቀርበው ገለፀ።

በንጋታው ጠዋት የሆነው ግን ሌላ ነበር። የከተማው ኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ በረከት ቢሮ አስቸኳይ ስብሰባ ተጠራን። እኔና ፀጋዬ ክርክሩን ወዳልሆነ አቅጣጫ መምራታችንን ተነገረን። የመኢብኑ አቶ መሳፍንት ኢህአዴግ ቢሮ መጥቶ ቅሬታ ማቅረቡ ተነገረን። የድርጅት ጉዳዮን ለሚመራው ካሚል ደውሎ የመደራደሪያ ሀሳብ እንዳቀረበ ሰማን። ይህም ኢህአዴግ ከዚህ ቀደም ለአቶ በድሩ አደም እንደሚያደርገው አንድ ወንበር ከለቀቀለት ።

ቤተሰቦቹን ከእጩነት እንደሚሰርዝ የሚገልፅ ነበር።

በረከት በተቃራኒው ድርጅቱ አዲስ አቅጣጫ ማስቀመጡን ነገረን። አዲሱ ስትራቴጂ በምርጫው ውጤት ላይ ለውጥ የማያመጡ ፓርቲዎች በውድድሩ እንዲሳተፉ ማበረታታት እንደሆነ ገለፀ። ይህም በአንድ በኩል በምርጫ ቦርድ በኩል የሚመደበውና ለፓርቲዎች የሚከፋፈለው ገንዘብ በእጩ ብዛት እንዲሆን፣ ኢህአዴግ ድርሻውን ውድድር ለሚገቡ ፓርቲዎች እንደሚያከፋፍል ነገረን። በመንግስት የተያዙት የሚዲያ ውጤቶች ለተቃዋሚዎች ሰፊ ሽፋን እንዲሰጡ አቅጣጫ መቀመጡን አስረዳ።

የዚህ ሁሉ ምክንያቱ ኢህአዴግ ብቻውን ሮጦ አሸናፊ ሆነ ከሚለው ወቀሳ ለመዳን መሆኑን ማብራሪያ ሰጠ። ውሳኔውን ተከትሎ በሀገር ደረጃ ለአካባቢና ማሟያ ምርጫ ከሰላሳ ፓርቲዎች በላይ ተመዝግበዋል የሚለው መልእክት የምርጫውን አብዝሀነት ማሳያና በኢትዮጵያ መድብለ ፓርቲ ስርአት የማይቀለበስበት ደረጃ መድረሱን ማሳየት የቀጣይ ቀናት ቁልፍ ስራችን ሆኖ ተቀመጠ።

ኢቲቪም በመስተዳድሩ ፕሮግራም አቀርበዋለው ያለውን የፓርቲዎች ክርክር ሰርዞ ለመወዳደር የተመዘገቡ ፓርቲ አመራሮችን በተናጠል በመጋበዝ የመድብለ ፓርቲ ስርአቱ ይበልጥ እየተጠናከረ መሄዱን አበሰረ። እኛም ጓዛችንን ጠቅልለን መድብለ ፓርቲን ማሰስ ጀመርን... ላም ባልዋለበት!!

***

ድምፅ አልባ ድምፀኞች!

የ2000 ዓ.ም የአዲሳባ ዳግም ምርጫ እየተካሄደ ነው። ኢህአዴግ ከከተማዋ ምክር ቤት ወንበሮች ውስጥ አንዱን ለቆ መመረጥ ጀምሯል። ይችላል የተቀነሰባት ወንበር ለአየለ ጫሚሶ ቅንጅት ተሰጥታለች። አለበለዚያ የታሰበው "ዳግማዊ ታሪክ" ምልዑ አይሆንም።

እናም የኢህአዴግ ካድሬዎችና አባላት የአቶ አየለ ቅንጅትን ወክላ የቀረበችውን እጩ(ዶክተር ናት) እንደራሳቸው በመቁጠር ቅስቀሳ አደረጉላት። መድረክ እያዘጋጁ አስተዋወቋት። እሷም በተጠራችበት ሁሉ በመገኘት የሞተው ቅንጅት አክራሪው እንጂ የኢህአዴግ ታማኝ ተቃዋሚው ይበልጥ እየተጠናከረ መሄዱን፣ ድርጅቷ ከገነባው ፓርቲ ጋር የፕሮግራም ልዩነት እንደሌለው፣ ለቀጣይም እጅ ለእጅ ተያይዞ እንደሚሰራ አበሰረች።

እሁድ (የድምፅ መስጫው ቀን) ሂደቱን ለመምራት ኢህአዴግ ቢሮ ለሁለት ተከፈለ። በመላ ሀገሪቱ የሚካሄደውን ለማስተባበር በታደሰ ካሳ (ጥንቅሹ) ቢሮ እሱን ጨምሮ ታይለማርያም ደሳለኝ፣ አሸቱ ደሴ እና ሞፈሪያት

ተመደቡ። የአዲሳባን ክንፍ ህላዌ፣ ካሚል፣ ፀጋዬ፣ ፍሬ፣ ይሳቅ ቆሪጥና እኔ ተደለደልን። ሴኮቱሬ የሁለቱ ቡድን ጆከር በመሆን በየሰአቱ መርጦ የወጣውን ብዛት እየመዘገበ ለምርጫ ቦርድ ያስተላልፋል። ምርጫ ቦርድ የእኛን ቁጥር መሰረት አድርጐ በየሁለት ሰአቱ ለኢትዮጵያ ህዝብ መግለጫ ይሰጣል። የኢህአዴግና ምርጫ ቦርድ መደጋገፍ እስከዚህ ድረስ ይዘልቃል።

በአዲሳባ የዘረጋነው ኔትወርክ አንድ መራጭ ድምፅ ሰጥቶ ሲወጣ የምናውቅበት ነበር። ለዚህ እንዲረዳ ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ በማውጣት የሞባይል ካርድ ገዝተን አከፋፈልን። በከተማዋ ከ500 ያላነሱ ምርጫ ጣቢያዎች ሲኖሩ በእያንዳንዱ ጣቢያ 20 አባላት እንዲመደቡ ተደርጓል። አባላት በምሳ ሰበብ ጣቢያቸውን ለቀው እንዳይሄዱ ተመሳሳይ መጠን ያለው የምሳ አበል ወጪ ተደረገ። እነዚህ አባላት አንድ ሰው መርጦ በወጣ ቁጥር ቀበሌ ላይ ላለው ኮሚቴ በሞባይል SMS መልእክት ያስተላልፋል። የቀበሌው ካድሬ መቶ ሲሞሉለት ለክፍለ ከተማ ያስተላልፋል። ክፍለ ከተሞች በየ20 ደቂቃው ደምረው ለእኛ ይደውላሉ። አቶ በረከት በየግማሽ ሰአቱ ወደ እኛ እየመጣ ይወስዳል።

እስከ ረፉዱ ድረስ ምርጫ ጣቢያዎች የመራጭ እጦት አጋጠማቸው። እርቃናቸውን ቀሩ። ሁላችንም ደነገጥን። በረከት መረጋጋት አቃተው። የተለያዩ ፈጠራዎችን አባላችን እንዲጠቀም አሳሰበን።

ይህቺ ቃል ወደ ታች ስትወርድ እንዴት እንደምትተረጐም እያወቅን "ፈጠራ ተጠቀሙ " ብለን አስተላለፍን። አባሎቻችን እያንዳንዱን ቤት እያንኳኩ ማስፈራራት ጀመሩ..." ያልመረጠ የቀበሌ አገልግሎት አያገኝም!"፣ "ኮንዶሚኒየም ለማግኘት መምረጥ ይኖርባችኋል! "፣ "ያልመረጠ የቅንጅት ደጋፊ ነው!" የሚሉ ቃላቶች በጥቅም ላይ ዋሉ። በአለቱ እየተካሄዱ ያሉ እድር ሰብሰባዎች እንዲቋረጡ ተደረገ። አባሎቻችን ቤተክርስትያን ደጃፍ ቆመው የሚወጣውን ምእመን በቀጥታ ወደ ምርጫ ጣቢያ ወሰዱ። ህዝቡ መፈናፈኛ ሲያጣ ወደ ምርጫ ጣቢያ መትመም ጀመረ። ሰልፎች መታየት ጀመሩ።

የሰምኦን ልጅ በረከት እፎይታ አገኘ። ፀሀይ ማዘቅዘቅ ስትጀምር ትንሽ ቆይቶ እንደሚመጣ ነግሮን ሔደ። በፉንታው ሽማግሌው ሰብሀት ነጋ ተቀላቀለን። ሽማግሌው ጠጥቷል። ህላዌ ትንሽ እናስቀባጥረው ብሎ ጠርሙስ ውስኪ አሰጨበጠው።እንዲህ በማለት ጠየቀው፣

"ስማ አስኪ ሰብሀት! አንተን የከንቲባው ልዬ አማካሪ ልናደርግህ አስበናል?።"

"ህላዌ! እንኳን አርጅቼ ድሮም የሴት ቀሚስ ተከትዬና አልብሼ

አላውቅም!"

"ከአረጁ አይበጁ ሆንክ እኮ!... ማሞ ሌላ መታወቂያው ሌላ!"

"ህላዌ በሚገባ ሰምቸሀለሁ! አበሳጭቶኝ ነው። በምን አይነት መለኪያ አስቴር ማሞ ከንቲባ ልትሆን ትችላለች?... በል መልስልኝ?... እናንተስ ብትሆኑ የአዜብን ሀሳብ ዝም ብላችሁ ትቀበላላችሁ? መተጋገል የሚባል ነገር ጠፉ እንዴ? እኔ ሰሞኑን በጠቅላላ ስከራከራት ነበር። የምትሆንበትን ምክንያት አሳምኝኝ አልኳት። ከሷ ውጭ የተሻለ የለም... ትሆናለች! ትሆናለች! አለችኝ።"

ህላዌ እንደ ሎጥ ሚስት ደርቆ ቀረ። ሁላችንም እርስ በራስ ተያየን። ሽማግሌው ቀጠለ፣

"ህላዌ! እውነቴን ነው የምልህ። ይህችን ሴት ወደ ከንቲባነት ማምጣት ህዝብ እንደ መናቅ ነው። እነ መላኩ ፈንታ ባሉበት እንዴት አስቴር? በደንብ ልታስቡበት ይገባል። ባይሆን አርከበን አሳትፉት። የከተማ አመራር ሊሆን የሚችሉ ሰዎች ምርጫ ላይ ሊረዳችሁ ይችላል"

ሽማግሌው እንዳልሰከረና ሽፍጥ አንግቦ እንደመጣ ገባን። ያለማቋረጥ ጠዘጠዘን። ጥይቱን ሲጨርስ ጠባቂዎቹን ተደግፎ በቁመ እያንከራፉ ወደ መጣበት ሄደ።

ፍሬ የሰማችውን ሚስጥር ነገረችን። ለካስ ከወራት በፊት የህውሀት ከፍተኛ ካድሬዎች በአጀንዳ ይዘው ተነጋግረውበታል። በሽማግሌው ስብሀት (አርከበ እቁባይ) እና በወይዘሮ አዜብ መካከል ማን ከንቲባ ይሁን በሚለው ዙሪያ ተጨቃጭቀዋል። አዜብ በጉን በኩል ድጋፍ ለማግኘት ዘመቻዋን አጠናክራ ቀጠለች። የኦህዴድ ጽ/ቤት ካድሬዎች በሷ መስመር እንዲሰለፉ አደረገች። አስቴርን ለከንቲባነት መለስ ስለመረጠሽ ተዘጋጂ ብላ ነገረቻት።

ህላዌ በስጋት ውስጥ ሆኖ፣ "ሴትየዋ በእጅ አዙር አስተዳደሩን ሳትረከብ አንድ ነገር ማድረግ አለብን! "ብሎ ተናገረ። ፍሬ በበኩሏ፣ "ጓዶች! እንደተለመደው በተባበረ ክንዳችን እቴጌን ጉድ እንስራት! "አለች። ካሚልና ፀጋዬ ወደ እኔ ተመለከቱ።

ምሽቱኑ ሴራ ጠንስሰን አደርን።

***

ከምሽቱ አራት ሰአት አካባቢ በረከት ስምኦን፣ ተፈራ ዋልዋና ባለቤቱ አይኔ ጽጌ ተያይዘው መጡ። ሞቅ እንዳላቸው በማየት የስታውቃሉ። ተፈራ ጨርቅ ሆኗል። "ተፈ ግርግር" ደርዘን ማርቲኒ ይዞልን መጥቷል። አይኔ ደግሞ መጠጫ ብርጭቆዎች።

በረከት ፊቱ ፀሀይ ሆኗል። ለመምረጥ የወጣው ህዝብ ከገመተው በላይ ነው። የኢህአዴግ የአየለ ጫሚሶ እጩዎች አብላጫ ደምፅ እንደሚያገኙ አልተጠራጠረም። እናም መጠጣትና መጫወት ብቻ ነው የፈለገው። ከኢህአዴግ ካድሬዎች ከመለስ ቀጥሎ ተጫዋችና ተራቢ በረከት ነው። ከፓለቲካ ውጭ የሚያመጣው ጨዋታ ሁለገብነቱን ያሳያል፣... ስለ ስፓርት፣ ሙዚቃ፣ ፊልም፣ መጽሐፍ ቢነሳ አብሮ መጠረቅ ይችላል። የእንግሊዙ አርሴናል ቀንደኛ ደጋፊ ነው። ስለ አርሰን ቬንገር የአመራር ብቃትና ደፋር ውሳኔ ሲናገር በምርጫ 97 ምክንያት ያጣነውን የስፓርት ጋዜጠኛ ፍስሀ ተገኝን ያስንቃል።

የሁላችን ሞቅታ እየጨመረ ሲሄድ በረከት ዋልዋን ማብሸቅ ጀመረ። ህላዌና አይኔም ተጨመሩ። መለያው የሆነችውና ተጣብቆ የቀረባት "የዋልዋ ኮት" ተነሳች።

"የዋልዋ ኮት" ታሪክ ዘትረካ በረከት እንዲህ ነበር።

"...አቶ መለስ ለኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ የአስተሳሰብ አድገት መጥቶባቸዋል ያላቸውን ጉዳዮች ይዞ ይመጣል። ውይይቱ ሲካሔድ ነባር ታጋይ የነበሩ ካድሬዎች አልዋጥላቸው ይላል። ከሌላው በተለየ ተፈራ አዲሱን ሀሳብ ደግፎ ይናገራል። በሌሎቻችን የተበሳጨው አቶ መለስ አዳዲስ አስተሳሰብ እየፈራን እስከ መቼ እንደምንኖር አይገባኝም። ይህ ተፈራን አይመለከትም። ዋልዋ የተቸነከረችበት ኮቱ ብቻ ናት። አሁንማ መርካቶ 'የዋልዋ ኮት' የሚል ባጅ ሊጀመር እንደሆነ ሰምቻለሁ" አለ። ሁላችን ፈገግ አለን።

በረከት ቀጠለ፣

"ከመለስ ንግግር በኋላ ተፈ ግርግር የአለባበስ አድገት አመጣ። ኮቱን እርግፍ አድርጐ በመተው አዲስ ቢጫ ቆዳ ጃኬት ለበሰ። እነሆ ላለፉት ሁለት አመታት ያቺን ጃኬት የሚያስወልቀው ተናጋሪ ታጣ!"

ህላዌ፣ " የኢህአዴግ ባህል ማእከል ተገንቡቶ ሲጠናቀቅ በሚኖረው ሙዚየም ሁለቱንም በክብር እናሳርፋለን"

በረከት፣ "እስከዛ ለምን ብሄራዊ ሙዚየም ከሳሞራ የኑስ አጠገብ እንዲቀመጥ አንወስንም?"

ተፈራ፣ "አቤት ብአዴን! መቼ ይሆን ቅናት የሚለቅሽ?"

***

የተፈራ ሚስት አይኔ ደርባባ ናት። የብአዴን ካድሬዎች ደግነቷን ይመሰክራሉ። ቤቷን "የአብርሀም ቤት" ይሉታል። ድስትና መሶብ የሚገለበጥበት ቤት። ቅዳሜ ከሰአት የዋልዋ ቤት ትደምቃለች፣ ብአዴኖች የበረሀና የስልጣን ህይወታቸውን ያወጋሉ። በአዘቦት ቀንም ቢሆን ምሳ መብላት

የፈለገ "እየመጣሁኝ ነው" ብሎ መደወል በቂው ነው። እኔም አንዲት አርብ ከህላዌ ጋር ሔጂ ድንኳን ሰብሬያለሁ።

በደግነት የተሞላችው አይኔ የምታሳልፈው ህይወት አልጋ ባልጋ አይመስልም። የዜሮ ድምር ጨዋታ የሆነው የኢትዮጵያ ፖለቲካ በርካታ የህይወት ጠባሳ አሳርፎባታል።

ወንድሟንና የቅርብ ዘመዶቿን በቀይ ሽብር አጥታለች። የተፋራጅ ኮሚቴ ውስጥ አመራር ሆና ሰርታለች። የቀይ ሽብር ሰማእታትን ለመዘከር መስቀል አደባባይ የተሰራው ማእከል በእሷ ያላሰለሰ ጥረት ነው። የሰማእታቱ አፅም በክብር የተቀመጠ እለት ባሏን ተደግፉ ያነባችው እንባ ጭንቅላቴ ላይ ተቀርጾ ቀርቷል።

ያ! ከፉ ዘመን አልፎም አይኔ እፎይ አላለችም። ቀድሞ በአንድ መስመር የነበሩት ባሏና ወንድሟ አንዳርጋቸው ጽጌ ከዓመታት በኋላ በተቃራኒ ተሰልፈዋል። በወንድሟ የሚመራው ግንቦት ሰባት ሁሉን አቀፍ ትግል ብለው የሚጠሩትን ፀረ ኢህአዴግ ዘመቻ አጠናክሮ ቀጥሏል። ወንድሟ ዱር ቤቴ ብሎ ኤርትራ ከትሟል።

የ70 አመት አባቷ የገዛ ባሏንና ጓደኞቹን ለመግደል በማሴር ተጠርጥረው ማዕከላዊ ወርደው ነበር። አባቷ ላይ የደረሰውን ኢ -ሰብአዊ ድርጊት ረፍት ቢነሳት "የፍትህ ያለህ! አባቴ የደም ብዛትና ስኳር በሽተኛ ነው። መዳኒት በየሰአቱ መውሰድ አለበት" በማለት ጮህለች። ለሚዲያ አጋልጣለች። በድጋሚም አንብታለች።

ባለቤቷ የብአዴን ማእከላዊ ኮሚቴ ሲመረጥ አሻፈረኝ አለ። ለወጣቶቹ መልቀቅ አለብን ብሎ ተከራከረ። ካድሬው "ያለ አንተ ብአዴን..." ብሎ ጥያቄውን ውድቅ አደረገበት። የአንድ ሳንባ ብቻ ሳይሆን የማይድን በሽታ እያሰቃየው እንደሆነ ለጉባዔው ነናገረ። ጓደኞቹ "በቃ አታስጨንቁት! " ብለው ተማፀኑ። ተሰብሳቢው ተላቀሰ።

ለቀበቶ አልባው... "ዋልዋ!"... "ተፈ ግርግር!"... የዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት እስረኛ!!

***

እኩለ ለሊት ሲቃረብ በረከት፣ ተፈራና ሚስቱ ጥለውን ሔዱ። የመርካቶና የካ ካድሬዎች አለቃ የሆኑት ሺሰማና ፈለቀ ተቀላቀሉን። ሁለቱ ጓዶች በከተማዋ ተካሂዶ የነበረውን "ጉራጌ መራሽ አብዮት" ከጠነሰሱት

መካከል ግንባር ቀደሞቹ ናቸው። የአብዮቱ ሴራ ከታወቀ በኋላ ሂሳባቸውን አወራርደው የቅልበሳው መሪ ተዋንያን ሆነዋል። ለዚህ ውለታቸውም የአዲሳባን ካቢኔ እንዲቀላቀሉ ተደርጓል።

እነ ሺሰማ በዛ እኩለ ለሊት ሲመጡ የምስራች ይዘው አልነበረም። ቆጠራው አስደንጋጭ ውጤት ይዞ እየመጣ መሆኑን አረዱን። የአዲሳባ ህዝብ ለሶስተኛ ጊዜ ቀለደብን አሉን... ምርጫ 92፣ ምርጫ 97፣ ምርጫ 2000 ።

የቆጠራ ሂደቱን በአካል ተገኝቶ ለማየት ወጣሁ። አራት ኪሎ አቅራቢያ ወደሚገኙት አምስት ምርጫ ጣቢያዎች ተራ በተራ ሄድኩኝ። አይንና ጆሮዬን ማመን አቃተኝ።

የምርጫ ጣቢያ ሀላፊዎች ድምፅ የተሰጠባቸውን ወረቀቶች በመፈታታት ለታዛቢዎች ተራ በተራ ያሳያሉ። ለማን እንደሚመዘገብ ይናገራሉ። የምርጫ ታዛቢዎች ወረቀቱ ላይ የሰፈረውን ምልክት በማየት በሶስት ጐራ ይመዘግባሉ:- ኢህአዴግ ፣ተቃዋሚና ድምፅ አልባ በማለት። የተቆጠሩት ወረቀቶች በሶስቱ ፈርጅ ተለይተው ይደረደራሉ።

በሄድኩባቸው ጣቢያዎች የኢህአዴግ ታዛቢዎች የመዘገቡትን ውጤት ወሰድኩኝ።በአምስቱም ጣቢያዎች የሚመራው "ድምፅ አልባ" የሚለው ነበር። ከተቆጠሩ አንድ መቶ ወረቀቶች ውስጥ ከሀምሳ በላይ ድምፅ አልባ ነበር።

እየገረመኝ በደምፅ አልባ ወረቀቶች ላይ የሰፈረውን ጽሁፍና ምልክት ወደ መመዝገብ ተሸጋገርኩ...ሌላ ጉድ!!

"ኢህአዴግ ሌባ!"... "ኢህአዴግ ዘረኛ "... "የደም ስልጣን " ..."ሆዳም!"...

በመላ አዲሳባ ያለውን ለማወቅ ጉጉት ስላደረብኝ ወደ ቢሮ ተመለስኩ። ከሁሉም ክፍለ ከተማ እውነቱን ሊነግሩኝ ይችላሉ ብዬ የማስባቸውን ካድሬዎች አሰማራሁ። የሚገርም ነበር። በሁሉም ጣቢያዎች እየመራ ያለው ድምፅ አልባ ቀጥሎ ኢህአዴግ መሆኑን ነገሩኝ። ስድበቹም ተመሳሳይ ናቸው። የተጓጉትም ልቅም ባለ አማርኛ ስለነበር ፀሀፊዎቹ ወጣቶችና የተማሩ ሰዎች እንደሚሆኑ ጥርጣሬያቸውን ነገሩኝ።

ኢህአዴግ ሌባ!፣ ኢህአዴግ ዘረኛ፣ የደም ስልጣን፣...

ይህ ጥሬ ሀቅ የተደበቁ እውነቶችን ፍንትው አድርጐ ያወጣ ነበር። በአንድ በኩል ነዋሪው በተለይም ወጣቱና የተማረው ክፍል በድጋሚ ኢህአዴግን እንደማይፈልግ አረጋግጧል። በተጨማሪም ህዝቡ ከኢህአዴግ በላይ ለምርጫ የቀረቡትን ተቃዋሚዎች እንደሚጠላ አሳይቷል። በሌላ በኩል

እኛ ኢህአድጎች ከአስር ሚሊዮን ብር በላይ አውጥተን ከዘረጋነው ኔትወርክ በላይ ውስጥ ለውስጥ የተደራጀ ህቡእ መንፈስ መኖሩን አመላክቷል። ይህ ውስጥ ለውስጥ የተደራጀ መንፈሳዊ ኔትወርክ በከተማዋ ገጠር ቀበሌዎች ሳይቀር የተዘረጋ ሲሆን፣ በከተማው አርሶ አደር አካባቢ "ኢህአዴግ ሌባ"፣ "ሆዳም!" ተብሎ የተጻፈበት ወረቀት ማግኘት ምን ያህል ወደ ህብረተሰቡ ዘልቆ የገባ መሆኑን የሚያሳይ ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ በምርጫ 97 የነበረው ቅንጅት ሳይሆን መንፈሱ፣በኢትዮጵያ ህዝብ ውስጥ ያለው የለውጥ ፍላጐት ነው። ይሄ መንፈስ ዛሬም በኢትዮጵያ ምድር አለ።

***

ምርጫው በተካሄደ በንጋታው ሰኞ የሁሉም ምርጫ ጣቢያዎች ውጤት እጃችን ገባ። በ2000 ዓ.ም የተካሄደውን ዳግም ምርጫ አሸናፊው "ድምፅ አልባ" የሆነው የከተማው ነዋሪ ሆነ። ሁለተኛ ኢህአዴግና የአየለ ጫሚሶ ዶክተር ሆኑ።

በደስታ ብዛት አመሻሽ ላይ የቀበሌና ክፍለ ከተማ ካድሬዎችን ኢህአዴግ ቢሮ የምግብና ሙዚቃ ድግስ ጠራን። ግቢውን በእንኳን ደስ አላችሁና ባንዲራ አሸበረቅን። ካድሬዎቻችን የሰሰት አመት ልፋት ውጤታቸውን በጋራ ለማክበር ተጠራርተው መጡ። አራት ኪሎን የሚያንቀጠቀጡ የማጉሊያ እስፒከሮች በአራቱም አቅጣጫዎች ተተክለው መጮህ ጀመሩ።

ሁሉም መገኘቱ ሲረጋገጥ ህላዌ የደስታ መግለጫ ለማስማት ወደ መድረክ ወጣ። ብርጭቆአችንን እንድናነሳ ጠየቀ። አነሳን። እንዲህ በማለት ባስራቱን ተናገረ፣

"በምርጫ 97 ከ138 ወንበር 137 ቅንጅት አሸንፎ ነበር። አሁን ደግሞ ታሪክ ራሱን ይደገማል እንዲሉ በተቃራኒው ኢህአዴግ ከ138 ወንበር 137 ሲያሸንፍ ቅንጅት አንድ ወንበር ብቻ አገኘ። ለዚህ ታሪክ ደጋሚ ድል ዋንጫችንን እናንሳ።"

ብርጭቆአችንን አጋጭተን የተቀዳልንን ወይን ጨለጥን።

ደም የጠጣሁ ያህል ዘገነነኝ። የይችላል ያልደረቀ እንባ ፊቴ ላይ ድቅን አለ። የድምፅ አልባ ወረቀቶች ድምፅ ህሊናዮን ረፍት ነሳው። ጩኸታቸው አንዳልረጋጋ አደረገኝ።

ኢህአዴግ ሌባ... ዘረኛ... የደም ስልጣን...ሆዳም!

የሙዚቃ ድግሱ ሊጀምር ሲል የከተማው ኢህአዴግ ከንፍ በአስቸኳይ አቶ በረከት ቢሮ ተጠራን። ሄድን። የበረከት የትላንትና ደስታ ብንን ብሎ ጠፍቷል። ጠረጴዛው ላይ የማጠቃለያ ውጤቱን የሚያሳይ ሪፓርት ብቻ

ተቀምጧል። በሰንጠረዥ መልኩ አዘጋጅተን የሰጠነው እኛ ነበርን።

ሁላችንም መምጣታችንን ሲያረጋግጥ አጭር ማሳሰቢያ ሰጠን፣

"ከዛሬ ጀምሮ በከፍለ ከተማና ቀበሌ ሊካሄዱ የታሰቡ ተሀድሶዎች እንዳይካሄዱ። ያልመረጠን ህዝብ ብዙ ስለሆነ ዳንኪራ ባዘጋጀን ቁጥር የባሰ ቂም ይይዝብናል። ድምጻችንን አጥፍተን ልማታዊ መንግስት መሆናችንን እናሳያለን። ከእንግዲህ ያለን የመጨረሻ አማራጭ እሱ ብቻ ነው። ይህን በመመልከት ድርጅቱ ሁሉም ነገር ወደ አዲሳባ እንዲሆን ወስኗል።" አለን።

እቤቴ ስደርስ በማስታወሻዬ ላይ "ድምፅ አልባ ድምፀኞች" በሚል አሰፈርኩት። አቶ በረከት ደግሞ ከሶስት አመት በኃላ ሀቁን በመገልበጥ፣ "ታሪክ ራሱን ይደግማል፣ መጀመሪያ አሳዛኝ፣ ቀጥሎም ቧልት በሚመስል መንገድ" ብሎ በመጽሐፍ መልክ አዘጋጅቶ ለንባብ አበቃው።

አሳዛኙ፣ዳግማዊውና ቧልተኛው ታሪክ የትኛው ነው?

አያት አክሲዮን ማህበር ህገ ወጥ በሆነ መንገድ የተገኘን ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ በመስራት፣ በአራጣ ማበደር ፣ያልተፈቀደ የባንክ ስራ መስራት፣ የ ገቢ ግብርና ታክስ ህግ መተላለፍ፣ ከቀረጥ ነፃ እቃዎች እንዲገባ በማታለል ... አጠቃላይ በ21 ክሶች ጥፋተኛ ተባለ። ከፍተኛው ፍርድ ቤት ለጥፋቱ 176 ሚሊዮን ብር በላይና የ12 አመት እስራት ተፈረደበት። የሚገርመው ነገር በክሱ ውስጥ ህገ መንግስቱን በመጻረር የከተማዋን ሲሶ መሬት መሸጥ መለወጡ የአንበሳ ድርሻ ይዞ አልተነሳም። ይህ ቢሆን ኖሮ ህገ መንግስቱን በጠረባ የመቱት አሊ አብዶና አባይ ፀሀዬ እግረ መቅ ተገጥሞላቸው የፍርድ ቤት ሳጥን ውስጥ እናገኛቸው ነበር።

ከራሳቸው፣ ቤተሰባቸውና ኢህአዴግ ቆጥቦ ከሰጣቸው አባላት ውጭ ምንም አባላት የሌላቸው እነ አየለ ጫሚሶና መሳፍንት የኢትዮጵያን መድብለ ፓርቲ ስርአት በማይነቃነቅ ደረጃ ተከሉት። እነሆ!ላሚ እበቷን ጥላ ኩበቱ መለቀም ጀምሯል። መስፍን መሳፍንት ሆኖ፣ አየለ ጫሚሶ ደግሞ ስማቸውን ሳይለቁ የተወዳጁ ኢቲቪ የዘወትር ሙሽራ ሆነዋል። ዘመኑ የአባይ ግድብ ነውና ኢቲቪ፣" ተቃዋሚዎችና የአባይ ግድብ" ብሎ ባዘጋጀው ዶክመንተሪ ላይ ጫሚሶና መስፍን (ይቅርታ መሳፍንት!) መሪ ተዋንያን ሆነዋል። አዲሱ ነገር" ዘንድሮ ምን ወጣት አለና ስልጣኔን አስረክባለው!" በሚል አሳፋሪ ንግግራቸው የሚታወቁት ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ በፊልሙ መካተታቸው ነበር።

የአዲሳአባ ህዝብ ምርጫ ካርድ በምትባል ምትሀተኛ ወረቀት ዳግማዊ

ሳይሆን ሳልሳዊ ቧልት ሰራ። ምርጫ 92፣ ምርጫ 97፣ ምርጫ 2000። ለኢህአዴግና የመድብለ ፓርቲ ስርአቱን የላቀ ደረጃ ላደረሱት ተቃዋሚዎች ግልጽ መልዕክት አስተላለፈ። ከሳጥን ውስጥ ተጣጥፉ የተገኘችው ወረቀት ድምፅ አልባ ብትባልም ያነገበችው ጩኸት ዘመን ተሻጋሪ ሆነ።

ምስኪኑ ይችላል አያትን ከመሳሰሉ ሌቦች ጋር አልደራደርም በማለቱ አንገቱን እንዲደፋ ተደረገ። ህሊናው እንዲቆስል ተፈረደበት። ባደረበት ብስጭት ለረጅም ጊዜያቶች አልጋ ላይ ወደቀ። ይህ መከራ ብቻውን ይበቃው ነበር። የሁለት ምርጫዎች ወግ በሌላ መርዘኛ ጦር ወጋው። በረከት ስምኦን የፓለቲካ ጢባ ጢቤ ተጫወተበት።

ይችላል በህይወት ይኑር፣አልጋ ላይ ይቅር፣ ሀገር ጥሎ ይሸሸ የማውቀው ነገር የለም። ከአለበት ለኢትዮጵያ ህዝብ ድምፅን ለማስማት መጮህ እንዳለበት ይሰማኛል። እውነቱን መግለጽ ይጠበቅበታል። ከዚህ በላይ የሚመጣ ግለሰባዊ ውርደት የለም። እንባዎቹ የሚደርቁት ይህን ሲያደርግ ብቻ ነው። በዚህ አሳፋሪ ታሪክ ውስጥ የነበርን ሰዎች ደግሞ ጉዳቱ በራሳችን ላይ ቢደርስ ብለን በማሰብ ይቅርታ መጠየቅ ይኖርብናል... እነሆ! አሳዛኙ ታሪክ ያንተ ነውና ይህ ምእራፍ ማስታወሻነቱ ላንተ ይሁን!!

ምእራፍ ሃያ አራት

የበቀል ጅራፍ

"የኢህአዴግ አመራር ሌላው ባህርይ ሁሌም ለመማር ዝግጁ መሆኑ ነው።"
በረከት ስምኦን (የሁለት ምርጫዎች ወግ)

ዳግም ንቅለ ካድሬ

በምርጫ 97 አዲሳአባን በተመለከተ እንደ አንድ የመሸነፍ መንስኤ ተደርጐ የተቆጠረው ከህብረሰቡ ጋር ትስስር የሌላቸውን ካድሬዎች ከየቦታው ለቃቅመን በማምጣት መመደባቸው እንደነበር ተገምግሞ ነበር። የአዲሳአባ ህዝብ በራሱ ልጆች የመተዳደር ህገ መንግስታዊ መብቱን ጨፍልቀናል የሚሉ አስተያየቶች ሳይቀር ተደምጠው ነበር። ከአቶ መለስ ጋር በነበረን መደበኛ ስብሰባ፣

"እስከ ምርጫ 2000 የሚኖራችሁ ቁልፍ ስራ የነዋሪው ልጆች የሆኑ የተማሩ ወጣቶችን መልምላችሁ ለአመራር ብቁ እንዲሆኑ ማድረግ ነው። ከተማዋን ማስተዳደር ይኖርባቸዋል።" ብሎን ነበር። እኛም ነዋሪውንና ወጣቱን በሰበሰብን ቁጥር ራሳቸውን ዝግጁ እንዲያደርጉ ወተወትን። የቁርጥ ቀን ሲመጣ ግን የሆነው ሌላ ነበር። ሌላ ዙር ህዝብ መናቅ!! ሌላ ዙር ሽፍጥ!!

ምርጫ 2000 በተካሄደ ማግስት እነ አባዱላ አህዴድን ተገን አድርገው የአዲሳአባ ካቢኔ ውስጥ መወከል አለብን የሚል ጥያቄ ያነሳሉ። አህዴድን ማስቀየም ያልፈለገው አቶ መለስ ሲናገር የከረመውን በማጠፍና ቃልአባይ በመሆን ሌሎች የብሄር ድርጅቶችም ካድሬዎች አዋጥተው አዲሳአባ ዳግም በመዋጮ እንድትመራ ትእዛዝ ያስተላልፉል። ብዙዎች ካድሬዎች (እኔን ጨምሮ) አቶ መለስ የወሰደው እርምጃ መንስኤ አህዴድን ለማባበል የሚለው አሳማኝ አልነበረም። ይልቁንስ በምርጫ 2000 የሚስጥር ድምፅ መስጫ ወረቀቱን ድምፅ አልባ ያደረገውና ኢህአደግን የሚያዋርዱ ጽሁፎችን ያሳረፈው ወጣቱ ሀይል በመሆኑ ተበሳጭቶና ተስፉ ቆርጦ እንደሆነ የሚለው ሀሳብ ሚዛን ደፍቶ ነበር።

በዳግም ምርጫ 2000 ዓ.ም ኢህአዴግ መዲናይቱን በተቆጣጠረ ወቅት አቶ በረከት ቢሮ ውስጥ እኔ፣ህላዌ፣ካሚል፣ፀጋዬና ፍሬህይወት ተሰብስበን ከንቲባ፣ ስራ አስኪያጅ ፣የካቢኔ አባላት እየመለመልን ነበር። ስብሰባው እንደ ተጀመረ ከቤተ መንግስት የአቶ መለስ ስልክ ተንጫረረ። አርከበ ለስራ አስኪያጅነትና ካቢኔ የሚሆን ይዞ እየመጣ ስለሆነ ተቀበሉት የሚል አጭር

ትእዛዝ ሰጠ። ስልኩ ሲዘጋ ሀላቂ፣

"Welcome ሀይሌ ፍስሀ!...Welcome መኩሪያ ሀይሌ! " ብሎ በዜማ ቅላፄው ዘፈነ። ካሚል ከጣራ በላይ ሳቀ። ፀጋዬ አንገቱን ነቀነቀ። እኔና ፍሬሀይወት በአይናችን አወራን። ስብሰባውን ጨርሰን ስንወጣ ፍሬሀይወት የምትፅፈውን ግጥም ለማንበብ ጓጓሁ!

በረከት እንደተለመደው፣

"ሀይሌም ሆነ መኩሪያ ወደ አዲሳባ የሚመጡት እኔና አርከበ ቦታ ስንቀያየር ነው ። ቡምስላግ! እስስት!" በማለት ጥርሱን ነከሰ። አፍንጫውን ፈተገ።

ወቅቱ ለአርከበ ወሳኝ ነውና በድል አድራጊነት ሰሜት ውስጥ ሆኖ የምንግዜም ባላንጣው ቢሮ ተገኘ። ጊዜ ሳያጠፉ፣

"መለስ የካቢኔ አባላትና ስራ አስኪያጅ መልምለህ ስጣቸው ባለኝ መሰረት ሳምንቱን ሙሉ ቁልፍ ስራዬ አድርጌ ስባዝን ነበር። ለካቢኔ አባላት የሚሆኑትን የሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ፕሬዝዳንት ዶክተር ሀይለሚካኤል በጣም አግዞኛል። እነ ህላቄ ደውላችሁ አመስግኑት። ኮሌጁን ባዶ አድርገሙ ነው መምህራኖቹን እየሰጠን ያለው።"

ትንፋሽ ወሰዶ፣

"...በዚህም መሰረት ለትምህርት ቢሮ ሀላፊነት የደኢህዴን ጠንካራ ካድሬ የሆነውን የኮሌጁ መምህር ዴንታሞ መርጫለሁ። የቅንጅት መንፈስ ያለቀቀውን የትምህርት መዋቅር ግልብጥብጡን ያወጣዋል። ለፉይናንስና ኢኮኖሚ ደግሞ የህውሀት ታጋይና የኮሌጁ መምህር በላይነሽ የመጀመሪያ ምርጫዬ ሆናለች። ለንግድና ኢንዱስትሪ እንዝርት የሆነውን የጉራጌ ካድሬ ፍፁምን መልምያለሁ። ብአዴኗ ዶክተር አፀደ የትም ቦታ ብትቀመጥ እንደምትመጥን ዶክተር ሀይለሚካኤል እምነት አለው።"

በድጋሚ ትንፋሽ ወሰዶ ወደ ዋናው ተልእኮ ገባ፣

"...ስራ አስኪያጅ የሚሆኑ ሁለት ጠንካራ ካድሬዎች ይገ መጥቻለሁ። የመጀመሪያ ምርጫዬ መኩሪያ ሀይሌ ነው። የደኢህዴን ሊቀመንበሩ ሀይለማርያምን አስተያየት ጠይቄው ደቡብን ባዶ ተደርግብናለህ እንጂ ሁነኛ ሰው መርጠሀል ብሎኛል። በሁለተኛ ደረጃ ሀይሌ ፍስሀ ቢሆን የሚል አስተያየት አለኝ። የህውሀት ቢሮ ለመስጠት አንገራግረው ነበር ግን አዲሳባ ላይ ጠንካራ ሰው መመደብ ወሳኝ መሆኑን ነግሬያቸው ፍቃደኛ ሆነዋል። እናም መኩሪያ የመጀመሪያ ምርጫዬ ቢሆንም ደኢህዴን ካለበት የሰው ሀይል እጥረት አኳያ ሀይሌ ፍስሀ ቢሆን ይሻላል..." አለ።

የፍርዬ ቁንጥጫ አጥንቴን ዘልቆ ተሰማኝ።

አርከበ ማቆም አልፈለገም። በረከትን በአሸናፊነት መንፈስ እየተመለከተው፣

"ለከንቲባነት ማንን አጫችሁ?" ብሎ ጠየቀው።

በረከት በበኩሉ፣

"ከንቲባ በኢህአዴግ ስራ አስፈጻሚ ይመደባል።" አለው።

አርከበ እየሳቀ፣

"ጥሩ ነው። አስቴር ማሞ የሚባል ሰምቼ እጅግ ደንግጬ ነበር። መቼስ ኢህአዴግ ቢሮ የተሰራውን የድርጅትና ፓለቲካ ስራ ወደ ጎላ መመለስ ካልፈለገ በስተቀር አስቴርን ከንቲባ አያደርግም። ውስብስብ የሆነችውን አዲሳአባ በአስቴር አቅም የሚያዛልቅ አይመስለኝም። ብአዴን ካልሰሰተ በስተቀር መላኩ ፋንታ ቦታውን ይመጥናል።" የከተማው ኢህአዴግ ክንፍ አባላት አንገታችንን ከታች ወደ ላይ በመነቅነቅ ለአርከበ ድጋፍ ሰጠን።

በረከት መልስ መስጠት አልፈለገም። አርከበ ተልኮውን በመጨረሱ ተሰናብቶን ሄደ። አፍታም ሳይቆይ በረከት ማስታወሻውን እየገለጠ፣

"ከከንቲባ፣ ምክትል ከንቲባ፣ አቅም ግንባታ፣ ከንቲባ ጽ/ቤት ፣ ስራና ከተማ ልማት፣ ትምህርትና ጤና ቢሮ ውጪ ባሉት የካቢኔ አባላት ላይ ሊመደቡ ይገባል የምትሏቸውን አቅርቡና በዝርዝር እንመልከታቸው።" በማለት ጠየቀን።

ህላዌ በጥርጣሬ እየተመለከተው፣

"ከላይ የተቀስካቸው ለምን አንመለከትም?" በማለት ጠየቀው።

"በቀጣይ በከተማው የሚሰራው ስራ ወጣቱ የሚያገኦበጥ በመሆኑ ከክልሎች ጠንካራ ካድሬዎችን ማምጣት እንዳለብን ተስማምተናል። በዚህ መሰረት አህዴድ ዳባ ደበሌን ለአቅም ግንባታ፣ አብድላዚዝን ለከንቲባ ጽህፈት ቤት፣ ዶክተር አህመድ ለጤና ቢሮ መድቧል። ብአዴን ጌታቸው ህይለማርያምን ለስራና ከተማ ልማት፣ ደኢህዴን ደግሞ ሬድዋን ሁሴንን መድቧል።"

ሁላችንም ደነገጥን። ህላዌ በንዴት ውስጥ ሆኖ፣

"አይ ኢህአዴግ! ሲፉጅ በማንኪያ ሲቀዘቅዝ በእጅ ሆኖ አረፈ። ደሞ ከንቲባስ የሚሆነው ማነው? ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባ?" በማለት ተናገረ።

በረከት ፊቱን አጨማዶ፣

"ከንቲባ አስቴር ማሞ፣ ምክትሏ ደግሞ ከፍያለው አዘዘ እንዲሆኑ ተወስኗል።" በማለት እቅጩን ነገረን። በረከት ጉዳዩ ከእሱ አቅም በላይ እንደሆነ ያስታውቃል። እኛንም ለስብሰባ የጠራን ሊነግረን እንጂ ሊያሳምነን አልነበረም። ያላመኑበት ነገር እንዲፈፀም ከመናገር በላይ የሀሊና ቁስል ይኖር ይሆን? የቀዳማዊ አመቤት አዜብ መስፍን ጉልበት የበረከትን አንገት እስከመቅላት ይዘልቃል። ከመፉዘዝ መውጣት ስላቃተን ስብሰባውን መቀጠል አልተቻለም።

ለሳምንት ቀጠሮ ይዘን ተለያየን።

እንደ እውነቱ ከሆነ አየተሰራ ያለው ስራ እጅግ ያሳዝናል። ትላንትና ከየክልሉ በመዋጮ ማምጣት አልነበረብንም ብሎ የኮነነ ምላስ፣ ዛሬ በተመሳሳይ መልኩ እንድትተዳድር ሲወስን የጤነኝነት ጥያቄ ያስነሳል። በዛ ላይ ከብሄር ድርጅቶቹ ወገብ ለሚያጎብጥ ስራ ብቃት ያላቸው የተባሉትን ካድሬዎች ማንነት የሚያውቅ ሰው እድሜ ልኩን ከግርምት አይወጣም።

አቅም ግንባታን ይመራል ተብሎ ከአህዴድ የተመደበው ዳባ ደበሌን ማንነት ሩቅ ሳይሄዱ ዶክተር ነጋሶን መጠየቅ ብቻ በቂ ይሆናል። ነጋሶ መድረክ ረግጠው ሲወጡ የተናገረው አሳፋሪ ንግግር ኢቲቪ ደጋግሞ በማሳየቱ በዛ ምክንያት ብዙ ሰው ያስታውሰዋል። ዳባ ከሻይ ቤት ባሬስታነት ያለምንም ትምህርት የኦሮሚያ ዞን አስተዳዳሪ እንዲሆን የተደረገ ካድሬ ነበር። ይህ በግል ጋዜጦች ሳይቀር የወጣ ሀቅ ነው። ቢጤውን የሚሰበስበው አባዱላ በነቀምት የአህዴድ ጉባኤ በማእከላዊ ኮሚቴነት ዳባ እንዲጠቆም ሲያደርግ አዳራሹ በሙሉ ሳቀበት። ከአንድ ሺህ በላይ ከነበረው ጉባኤተኛ የአስር ሰዎች ድጋፍ ብቻ አግኝቶ ወደቀ። ዳባ አንዲት ገጽ አስተካክሎ አማርኛ መጻፍ አይችልም። እንግዲህ ይህ ካድሬ ነው ከ50 ሺህ በላይ የሆነውን የአዲሳአባ ሲቪል ሰርቪሱ አቅም ይገነባል ተብሎ ወገብ ለሚያጎብጥ ስራ የተመደበው። (በአርከበ ዘመን የአቅም ግንባታ ቢሮ ሀላፊ የነበረው ተክለብርሀን" የተቸነከረው ታጋይ "ልብ ይሏል። የአዲሳአባ አቅም የሚገነባው በእንደዚህ አይነት ካድሬዎች ነበር። እነሆ! ታሪክ አሳዛኝና ቧልተኛ በሆነ መንገድ ራሱን ደገመ።)

የደኢህዴኑ መኩሪያ ወደ አዲሳአባ መምጣት ላይም ቢሆን የደኢህዴን ከፍተኛ ካድሬዎች ቅሬታቸውንና የመኩሪያን ሌብነት የሚያሳዩ መረጃዎች በግልጽ አቅርበው ነበር። በተለይም የድርጅቱ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ የነበረው አማኑኤል አብርሀ (በአሁኑ ሰአት የፓርላማ አባልና የኢህአደግ ቢሮ አደረጃጀት ሀላፊ) እና የኢህአዴግ ፉይናንስ ሀላፊው ተፈሪ በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ ናቸው። አማኑኤል አፍ አውጥቶ ለእኔና ፀጋዬ ሀይለማርያም፣ "አዲሳአባ ከጥቁር ጅብ ወደ ነጭ ጅብ ሽግግር አደረገች።" በማለት ነግሮናል። ይህም ሆኖ መኩሪያ ሀይሌ ስራ አስከከያጅ ሆነ!... በረከትና አርከበ ቦታ ሳይቀያየሩ ቀረ። መኩሪያ ሚኒስትር ሲሆን ደግሞ በቅብብሎሽ ህግ መሰረት ለሀይሌ ፍስሀ አወረሰው!

አርከበ ለሸፉን ይዞ የመጣቸው የሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ መምህራንም ከሹመት በኃላ ሲጣራ የተገኘው ነገር አስገራሚ ነበር። የደኢህዴን ጠንካራ ካድሬ የተባለውና የትምህርት ቢሮ የተሾመው ዲንታሞ ከምርጫ 97 ውጤት በኋላ ኢህአዴግነቱን በይፉ ትቷል። ለሶስት አመት ወርሀዊ መዋጮ አልከፈለም። ኢህአዴጐችን ሲያይ ይሸሽ ነበር። እንዝርት ተብሎ ለንግድና

ኢንዱስትሪ የተመደበው ፍፁም መንፈቅ ሳይሞላው በአቅም ማነስ ከካቢኔ ተባረረ። አፈ ጉባኤ የነበረችው ዶክተር አፀደና የኢኮኖሚና ፉይናንስ ሀላፊዋ በላይነሽ ዘግየት ብለው የካቢኔ ሻንጣቸውን ሸክፈው እብስ አሉ።

እልህ የተጋባው የከተማው ኢህአዴግ ከንፍ የተሳካለት አስቴርን ከከንቲባነት ማስቀረት ብቻ ነበር። በከተማዋ ለተደራጁት የነዋሪዎች፣ ወጣቶችና ሴቶች ፎረም መረጃው በሚስጥር እንዲደርሳቸው አደረግን። የፎረሙ አባላት በሙሉ ተቃውሞአቸውን አሰሙ። የግል ሚዲያዎችም ቀጣዩ ከንቲባ ኩማ ደመቅሳ እንደሚሆን ይጠበቃል የሚሉ መረጃዎችን መጻፍ ጀመሩ። ለአቶ መለስ "ህዝቡ ምን እያለ ነው?" በሚለው ሪፓርታችን ላይ ሰፊ ሽፋን ሰጥተን አሳወቅነው። ቅርቃር ውስጥ የገባው አቶ መለስ የሚስቱን ፍላጐት ሽሮ ኩማ ደመቅሳን ከንቲባ እንዲሆን አደረገ። በረከትንም ከገባበት ጭንቀት ገላገልነው።

ኩማ ደመቅሳ ከንቲባ እንደሆነ የተነገረው ምክርቤቱ ሊሰበሰብ ሶስት ቀን ሲቀረው ነበር። እስከአዛ ድረስ የሚያውቀው ነገር አልነበረም። ለካቢኔ ከተመለመሉት ውስጥ በአካልም ሆነ በስም የሚያውቃቸው የአህዴድ ካድሬዎቹን ዳባ ደበሌንና ለጤና ቢሮ የተመደበውን ብቻ ነበር። የከተማዋ ቻርተር ከንቲባው የካቢኔ አባላትን በመለየትና ለምክርቤቱ በማቅረብ ያፀድቃል ይላል። ለኩማ ደመቅሳ ይህ ህግ አልሰራም (ለነገሩ ለከንቲባ ድሪባ ኩማም እንዳልሰራ በብዙ ሺህ ማይሎች ከሀገሬ ርቄም መታዘብ ችያለሁ።)

ምክርቤቱ ተጠራ። ባልተለመደ ሁኔታ የምክርቤቱ ስብሰባ በቀጥታ የቴሌቪዥን ስርጭት ለኢትዮጵያ ህዝብ እንዲሰራጭ ተወሰነ። የሀገሪቷ ሚኒስትሮች በሙሉ በክብር እንግድነት እንዲገኙ ተደረገ። ሚኒስትር መላኩ ፉንታ ኩማ ደመቅሳ ከንቲባ እንዲሆን ኢህአዴግ እንደመረጠው አሳወቀ። እኔ ደግሞ አፈ ጉባኤ፣ ምክትል አፈጉባኤና የ ጽ/ቤት ሀላፊዎችን በማቅረብ ሹመቱ እንዲፀድቅላቸው አደረኩ። ኩማ ደመቅሳ በረከት ጽፎ የሰጠውን የአምስት አመት እቅድ በሚያስታውቅ መልኩ እየተንተባተበ አቀረበ። በረከት የኢህአፓና ሰሜንኛ ቃላቶችን ሞጅሮ አዲሱን ከንቲባ ከጅምሩ ግምት ውስጥ እንዲገባ ያደረገበት ምክንያት ራሱ ብቻ የሚያውቀው እንቆቅልሽ ሆነ። ቀጥሎም የማያውቃቸውን ካድሬዎች "የከተማውን ልማትና ዲሞክራሲ ጉዞ የሚመሩ" በማለት የካቢኔ አባላትን እንዲፀድቁለት አቀረበ። የኢህአዴግ ጽ/ቤት አዲሳባ ከንፍ ስራ አስፈጻሚ የሆነው እኔና ፀጋዬ ሀይለማርያም መንግስታዊ ሹመት ተጨመረልን። ፀጋዬ የፍትህ ቢሮ ሀላፊ ሆነ። እኔ ደግሞ የከንቲባው አማካሪና የመንግስት ዋና ተጠሪ የሚል ሹመት ተሰጠኝ።

***

ቀዝቃዛ በቀል

አዲሱ የኩማ ደመቅሳ ካቢኔ ስራ ሲጀምር ከኢህአዴግ ማእከል

የተሰጠን አቅጣጫ የከተማዋን ሲቪል ሰርቪስ (ቢሮክራሲ) ከስራ ውጭ ማድረግ ነበር። የኢህአዴግ አዲሱ አቅጣጫ ሰራተኛ ማባረር ሳይሆን ሽባ ሆኖ እንዲኖር ማድረግ ስለነበር በአርከበ ዘመን እንደተደረገው የለውጥ ሀይል የሆነ ያልሆነ የሚል ማባረሪያ መንገድ አልተከተልንም። ከዛ በተቃራኒው ሰራተኛው ወደ ስራው መጥቶ ምንም ሳይሰራ ወደ ቤቱ እንዲመለስ የሚያደርግ አቅጣጫ ነበር።

በመሆኑም ከከተማ እስከ ወረዳ ድረስ ቁልፍ የቢሮክራሲው የስልጣን ቦታዎች እንዲጠኑ ተደረገ። ጥናቱ 3,800 ያህል የስራ መደቦች ወሳኝ ቦታዎች እንደሆነ አመላከተ። ይህን ተከትሎ 4,000 የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው የኢህአዴግ አባላት የሆኑ ወጣት ምሩቃን በአንድ ጊዜ እንዲቀጠሩና ወሳኝ መደቦችን ከነባሩ ቢሮክራሲ እንዲቀሙ ተወሰነ።

እንደ እውነቱ ከሆነ የከተማው ኢህአዴግ ከንፍ አባላት በውሳኔው በጣም ደስተኛ ነበርን። በተለይ እኔ። ከ1998 አመተ ምህረት ጀምሮ እስከ 2000 ምርጫ ድረስ የአዲሳባ ልጆች ሆነው በከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚማሩ ተማሪዎችን የማደራጀት፣ የማሰልጠንና ስምሪት የመስጠት ሀላፊነቱን የወሰድኩት እኔ ነበርኩ። በዚህ ምክንያት ለሶስት አመታት ከአራት ሺህ በላይ ተማሪዎችንና ተመርቀው ስራ ያጡ ወጣቶችን ስከታተል ቆይቻለሁ። በተለይ በከረምት ወራት ውሎዬ በሚኒሊክ ትምህርት ቤት አዳራሽ ከእነዚህ ወጣቶች ጋር ሆኖ ነበር።

እነዚህ ወጣቶች በምርጫ 2000 ኢህአዴግ እንዲመረጥ ካደረጉ በቀጥታ ስራ እንደምናሲዛቸው ቃል ገብተንላቸው ነበር። በዚህ ምክንያት ለአመታት ስራ አጥተው ወደ ተስፋ መቁረጥ የገቡት ወጣቶች በየቤቱ እየሄዱ " ኢህአዴግ ከተመረጠ ስራ ሊያሲዘን ቃል ስለገባ እባካችሁ ምረጡት" ወደሚል ተማጽኖ ገቡ። ወጣቶቹ ይህን በማድረጋቸው የሚፈረድባቸው አልነበረም። የመኖርና ያለመኖር የህልውና ጥያቄ ፊታቸው ተደቅኖ ከዚህ ውጪ በተቃራኒው ሊቆሙ አይችሉም። ለእኛም የደስታ ምንጭ የነበረው ይህን ችግር መፍቻ አጭር መንገድ ማግኘታችን ነበር።

የቅጥር ውሳኔውን ተከትሎ የሆነው ግን ቆሽጥ የሚያደብን ነበር። ሸፍጡን የሰማሁ እለት የቢሮዬን በር ዘግቼ ስቅስቅ ብዬ አልቅሻለሁ። እኔ ብቻ ሳልሆን የከተማው ኢህአዴግ ከንፍና በዞን ያሉ ካድሬዎቻችን እጅግ አዝነዋል። የእነ ዳባ ደበሌ ወደ አዲሳባ የመምጣትና ሲቪል ሰርቪሱን እንዲመሩ የመደረጉ ሚስጥር ወለል ብሎ የታየኝ በዚህ ወቅት ነበር።

እንዲህ ነበር የሆነው፣

የወጣቶቹ ቅጥር የምዝገባ ሂደት መንግስታዊ ቅርጽ እንዲኖረው ፒያሳ በሚገኘው ማዘጋጃ ጽ/ቤት እንዲሆን ተደረገ። በተስፋ ሲጠብቁ የነበሩት የመዲናይቱ ወጣቶች ማዘጋጃ አቅም ግንባታ ቢሮ ሄደው እንዲመዘገቡ ወደ ታች ላሉ ካድሬዎቻችን መመሪያ አስተላለፍን። ፒያሳ ተጥለቀለቀች።

የምልመላውን ሂደቱ በኢህአዴግ ቢሮ እንዲከታተል ካሚል አህመድ ተመደበ። ማታ ማታ መዝጋቢዎቹን እየጠራ መገምገም ጀመረ። በሶስተኛው ቀን ዳባ ደበሌ 2,000 ሰም ዝርዝር ያለበት ወረቀት ይዞ ኢህአዴግ ቢሮ መጣ። የአህዴድና ህውሀት ጽ/ቤት ፉክስ እንዳደረጉለት፣ ከአቶ መለስ ጋር ድርጅቶቹ እንደተነጋገሩ እና የተላኩት ወጣቶች ቅድሚያ እንዲሰጣቸው መወሰኑን ገለፀ። በዚህ እልህ የተጋባው ካሚል ወደ ደኢህዴንና ጉራጌ ዞን በመደወል የ500 ወጣቶች ዝርዝር አመጣ። ጠባብነት ጠባብነትን ይወልዳል እንዲሉ ካሚል ባልተጠበቀ ሁኔታ የመረተኛ ወቅት ሲመጣ ወደ ጐጆው በመሄድ ታሪካዊ ስህተት ሰራ።

እናም አዲሳባን ረግጠዋት የማያውቁ፣ አንዳንዶቹም ህብረተሰቡ የሚጠቀምበትን ቋንቋ በቅጡ የማይረዱ፣ ጥቂቶቹ ደግሞ አማርኛን መናገር ቢችሉም መናገር በማይፈልጉ ጫፍ የረገጠ ዘረኝነት በተጠናወታቸው ወጣቶች አዲሳአባ ተጥለቀለቀች። መሄጃ የሌላቸውና የተሰፉ እንጀራ ሲቀለቡ ከከረሙት የመዲናይቱ ወጣቶች ሩብ ያህሉ ብቻ የመመልመል እድል አገኙ። ስም ዝርዝር ማዘጋጃ ቤት የተለጠፈ እለት የመዲናይቱ ወጣቶች እንባ ፈሰሰ። የአዲሳአባ ኢህአዴግና የዞን ስራ አስፈጻሚዎችን ስም እየጠሩ ልካቸንን አቀመሱን። ሌባና ከሀዲ የሚል ማእረግ አለበሱን። አዲሳአባ የእነሱ ብቻ ሳይሆን የእኛም አይደለችምና ውርጅብኙን ተቀበለን ኖርን።

***

ክፍል ሰባት: የአርማጌዶን ጦርነት

ምእራፍ ሃያ አምስት

የሐመሩ(ሐ) ፓለቲካ

"ዘርአይ አስግዶም የሚባል ቁጥር መደመርና መቀነስ የማይችል ሰው ኢቲቪ ሀላፊ አደረጋችሁ!"

አቡነ ሳሙኤል

ሲኖዶሱና አዲሲቷ ኢትዮጵያ

ሚያዝያ፣ ሁለት ሺህ አንድ...

ከፀጥታው ምክር ቤት አባላት ከፊሎቻችን የፓትሪያርኩ ጽ/ቤት ተገኝተናል። ለአስቸኳይ ስብሰባ። መሪያችን አባይ ፀሀዬ ሲሆን ዶክተር ሽፈራው፣ ኩማ ደመቅሳ፣ ኢሳያስ ወ/ጊዮርጊስ፣ ኮሚሽነር ወርቅነህ ና እኔ በኢጋፉሪነት ተሳትፈናል።

ወደ ስብሰባ አዳራሹ ስንገባ ፓትሪያርኩ የሲኖዶሱ አባላት በሙሉ ሰብስበው እኛን ይጠብቃሉ። የአዳራሹ ሞገስ ቢማርከኝም በውስጥ ያለው ድባብ ከብዶኛል። የጳጳሳቶቹ ጥቁር አልባሳትና ቆብ ወከክ ያደርጋል። ለካስ ጥቁር ውበት ነው። ውበቱን አጣጥሜ ሳልጨርስ ከራሴ ጋር የገጠምኩት መግት ፊት ለፊቴ ተደቀነ።

ሊለቀኝ ያልቻለ መግት...

እኛ በህዝብ ተመረጥን ፣አልተመረጥን በታሪክ አጋጣሚ መንግስት ሆነናል። ሀገሪቷን በህገመንግስቱ መሰረት የመምራት ግዴታ በእኛ ላይ የተጣለ ነው። ማንኛውም አካል ሆነ ቡድን (የሀይማኖት ተቋማትን ጨምሮ) የህገሪቷን ህገ መንግስት የማክበርና በህግ የበላይነት መመራት ይኖርባቸዋል። ይህንን አላከብርም የሚል ካለ በህጉ መሰረት መንግስት ይመለከታቸዋል የሚባሉ አካላትን ጠርቶ የመመካከርና እርምት እንዲወስዱ የማስደረግ ሀላፊነት አለበት። ከዚህ ካለፈም ህጋዊ እርምጃ መውሰድ የመንግስት ስራ ነው። ሀላፊነቱን የሚሸከም አሊያም ይሁንታ ሊሰጠን የሚገባ አካል ስናፈላልግ መኖር የለብንም። እንዲህ አይነት የወረደ ስራ ውስጥ እንዲገባ የሚገደድ መንግስት ወይ በህዝብ አልተመረጠም፣ አሊያም በህዝብ አመኔታ ስለሌለው ተቋማት ጉያ ውስጥ ተሸሽጐ እነሱን እየተለማመጠ እድሜውን የሚያራዝም ነው።

በመሆኑም እኛ የመንግስት ካባ ያጠለቅን የአባይ ፀሀዬ ደቀመዝሙራን

ለአመታት እያደረግን ያለነው ከላይ የተጠቀሰውን ነው። ሁከትና ግጭት በተፈጠረ ቁጥር ሲኖዶሱንና መጅሊሱን ወደ መለመን እንገባለን። በህገ መንግስቱ የተቀመጠውን የመንግስት ከሀይማኖት ነፃ መሆን በመጋፋት ተከፋፍለን ወደ ተቋማቱ እንሄዳለን።

ስምሪቱ በራሱ አስገራሚ ነበር። ከጅከሮቹ አባይና ዶክተር ሽፈራው ውጭ ወደ ሲኖዶስ ሲመጣ ከላይ የተጠቀስነው እንሆናለን። ወደ መጅሊሱ ሲኬድ ደግሞ እነ ሬድዋን፣ ሲራጅ ፈርጌሳና ካሚል ከፊት መስመር ይሰለፉሉ። ስምሪቱ ብቻ ሳይሆን የምናቀርበው ተማጽኖ በዛው ልክ ሀይማኖታዊ ይዘት ያለው ይሆናል።

ከሲኖዶሱ ጋር በተገናኘን እለት ዶክተር ሽፈራው ሳት ብሎት፣

"ጌታ እኮ ግራህን ሲመታህ ቀኝህን ስጠው ብሏል" ብሎ ለማስተማር በመሞከሩ የደረሰበት የቅብብሎሽ ዱላ የማይዘነጋ ነው። በስብከቱ የተበሳጩት አንድ ጳጳስ "ወንድሜ እሱን ተወውና ወደ መጣህበት ተመለስ!" በማለት አስቁመውታል። ርግጥም አንድ የሌላ እምነት ተከታይ የሆነ ካድሬ ለጳጳሳት ሀይማኖት ነክ ትምህርት ለማስተማር መሞከር እንደ ንቀት ሊያስቆጥር ይችላል። ይህንን እንኳን መገንዘብ ተስኖኛል።

ምንአልባትም ጳጳሳቶቹ በእኛ ላይ ያላቸው ንቀት አንዱ ምክንያት ይህ ሳይሆን አልቀረም። በግልጽ የሚነበብ ጥላቻ ይታይባቸዋል። አንዳንዶቹ በሙሉ አይናቸው ሊያዩን እንኳን የፈቀዱ አይመስልም። በእጃቸው በያዙት ትላልቅ መስቀል ግንባራቸውን አስደግፈዋል።

የስብሰባችን ምክንያት በከተማዋ በሚገኙ ሶስት ቤተክርስትያኖች ውስጥ በተነሳ ተቃውሞ በፓሊስና ህዝቡ መካከል ግጭት በመፈጠሩ ነበር። በዚህም ብዙ ሰዎች ጉዳት ደርሶባቸዋል። በተለይም በልደታ የተነሳው ብጥብጥ አልበረደም ነበር። የግጭቱ መንስኤ በቤተክርስትያኑ አካባቢ "አንድ ጥምቀት - አንድ ሀይማኖት" የሚል ቲሸርት የለበሱ ሶስት ወጣቶች የፈጠሩት ትንኮሳ በመስፋፋቱ ነበር። እነዚህ ወጣቶች በቤተክርስትያኗ ደጃፍ የሚያልፍ የሙስሊም ልብስ የለበሰ ሰላማዊ ግለሰብ በመተናኮል ጉዳት አደረሱ። በተመሳሳይ ሰአት ሌሎች ሁለት ወጣቶች የእስልምና መለያ ባርኔጣ ያጠለቀ የታክሲ ሹፌር ከጭንቅላቱ ላይ ኮፍያውን በግንሳት መሬት ላይ ረጋገጡ። በዚህ የተበሳጨው ሹፌር ከታክሲው በመውረድ አንዱን በስለት ወጋው።

ጥፋት አስከትሎ የሚመጣው ራሱን በመሆኑ ይህ ድርጊት በተፈፀመ በማግስቱ ሌላ የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ ቤተክርስትያን በመግባት "አላህ አክበር" ብሎ ጮኸ። ይህ ጠብ አጫሪ ድርጊት በአንዳንድ የህገሪቷ ክልሎች በመደገሙ አጀንዳው ወደ ህገራዊ ውጥረት ተቀየረ።

የፀጥታ ሀይሎች እነዚህን በጣት የሚቆጠሩ አጥፊዎች በቁጥጥር ስር አውለዋል። ቃላቸውን ተቀብለው ለህግ ቀርበዋል። አንዳንዶቹ ፍርዳቸውን

ይጠባበቃሉ። የተቀሩት ውሳኔ ተሰጥቷቸው ወህኒ ወርደዋል።

እኛ ደግሞ በጐንዮሽ የህግ የበላይነት ወደ ጐን ትተን ዘላቂ መፍትሄ በማያመጣ መልኩ ደጅ ልንጠና ፓትሪያርኩ ጽ/ቤት ተገኝተናል። በሰልስቱ ወደ መጅሊሱ እንሄዳለን። ለማስፈራራት እንዲረዳን ደግሞ የተለያዩ መረጃዎችን ይዘናል። በተለይ የደህንነት ሹሙ ኢሳያስ በርካታ ሲዲዎችን፣ የታተሙ ሀይማኖት ነክ መጻህፍትንና የተቀዱ ስብከቶችን ተሸክሞ መጥቷል። የክንዱን ውፍረት በያዛቸው መረጃዎች ማሳየት ፈልጓል።

ስብሰባው ተጀመረ...

ፓትሪያርኩ እንዲህ በማለት ተናገሩ፣

"የመንግስት ሀላፊዎች ሊያናግሩን እንደሚፈልጉ ገልፀውልኛል። አስቀድመን እድሉን እንስጣቸውና የሚሉትን እናዳምጥ ..."

ጳጳሳቱ አቋርጠዋቸው፣

ሳይፈቀድላቸው መናገር ጀመሩ። በማከታተል ኢቲቪ ላይ ውርጅብኝ አዘነቡ። ውሸታም፣ ቀጣፊ በማለት ተሳለቁበት። ባለፉት ጊዜያቶች ከስምምነታችን ውጭ የሆነ መልእክት ስላስተላለፈ አዳራሹን ለቆ መውጣት አለበት አሉ። ከብዙ ጭቅጭቅ በኃላ አባይ ፀሀዬ ለተፈፀመው ስህተት ይቅርታ ጠይቆ፣ ለቀጣይ በምንስማማባቸው ጉዳዮች ላይ ብቻ መግለጫ እንደሚሰጥ ቃል ገባ። ሀላፊነቱም ወደ እኔ ተወረወረ።

በማስከተል የጉዳዩ ዋነኛ ባለቤት ዶክተር ሽፈራው የተለመደችውን "የመቻቻል" ዲስኩር ካሰማ በኃላ፣

"...በአሁኑ ሰአት ይህንን የመቻቻል ባህላችንን የሚሸረሽር ድርጊት ሀይማኖትን ሽፋን ባደረጉ ፀረ ሰላም ሀይሎች በመፈፀም ላይ ይገኛል። በመንግስት እምነት አክራሪነት ከፊታችን የተደቀነ አደጋ ሆኗል። ይህ አደጋ በሁሉም የሀይማኖት ተቋማት ውስጥ አየተዛመተ ነው። አክራሪነትና ጽንፈኝነት ለሽብርተኝነት መፈጠር ለም መሬት ሆኗል። ሽብርተኝነት ግልጽና ተጨባጭ አደጋ ሆኖ ፊትለፊታችን ተጋርጧል። እናም ዛሬ የመጣነው በችግሮቹና መፍትሄው ላይ ለመወያየት ነው። መንግስት ሁሉም የሀይማኖት ተቋማት የአክራሪነት አደጋ እየተፈታተናቸው መሆኑን አውቀው ከእነሱ የሚጠበቀውን ሀላፊነት እንዲወጡ ይፈልጋል ። አዲሲቷ ኢትዮጵያ የሁላችንም እንደመሆኗ መጠን እከሌ ከእከሌ ሳይባል ሁላችንም ሀላፊነት አለብን።" በማለት ተናገረ።

ምነው አግሬን በሰበረው...

የጳጳሳቱ ዱላ በብረት ሰንሰለት እንደመገረፍ ነበር። እየተቀባበሉ ወረዱብን...

አንደኛው ጳጳስ ንቀትና እልህ አዋህደው እንዲህ ሲል ተናገሩ፣

"ስማ ወንድሜ! ለመሆኑ የምትናገረውን ታውቀዋለህ? አክራሪነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ታውቃለህ? አክራሪነት በሁሉም ሀይማኖት አለ ብለህ የምትለው ከየት አምጥተህ ነው? ስለ ኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ

ቤተክርስቲያን ምን የምታውቀው ነገር አለ?፣ በተቆጣጠራችሁት ራዲዮና ቴሌቪዥን ህዝቡን የምታደናግሩት ሳይበቃ እኛን ልታደናቁር ትመጣለህ። ስም ከመለጠፍ በፊት ማወቅና መገንዘብ ይጠይቃል። ይህቺ ቤተክርስትያን በባዶ ጫጫታ የምትፈርስ ከመሰላችሁ ተሳስታችኋል።"

ጳጳሱ ማቆም አልፈለጉም፣

"...በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን አስተምህሮ አከራሪነት የሚባል ነገር ቦታ የለውም። አስገድደን ተዋህዶ ኦርቶዶክስ የምናደርግበት ስርአትም ሆነ አሰራር የለንም። ታሪክ የምታውቅ ከሆነ የሌሎች ሀይማኖት ተከታዮች ባህር አቋርጠው ሲመጡ ተቀበልናቸው እንጂ አስገድደን የእኛን ተቀበሉ አላልንም።"

በሁኔታው የተደናገጡት አባይ ፀሀዬና ዶክተር ሽፈራው አንሾካሾኩ። አፍታም ሳይቆይ ዶክተሩ ማስታወሻ ጽፎ አቀበለኝ። ስገላልጠው የሚከተለው መልዕክት ጽፎበታል፣ "ሁሉም ጋዜጠኞች ካሜራቸውን ይዘው ይውጡ። ስብሰባው እስኪያልቅ ማረፊያ ክፍል እንዲጠብቁን አድርግ" የሚል ነበር። ለጋዜጠኞቹ ቡድን መሪ ጠርቼ በጆሮው ሹክ አልኩት። ሁሉም ወጡ።

የጳጳሳቱ ቁላ ተጠናክሮ ቀጠለ። ኢህአዴግን ኖራ የተቀባ መቃብር አደረጉት። አንድ ከሁሉም ጐልማሳ የሆኑ ጳጳስ መናገር ሲጀምሩ፣ አጠገቤ የተቀመጠዉ ኢሳያስ ማስታወሻዬ ላይ፣ "ቀንደኛ መአድ ነበር። በአይነ ቁራኛ እየተከታተልነው ነው " ብሎ ጻፈ።

የጐልማሳውን ጳጳስ ንግግር ወደ መክተቡ ተሸጋገርኩ፣

"ወንድሜ ይህቺ አዲሲቷ ኢትዮጵያ ያላችኋት የትኛዋ ናት? ኢህአዴግ አዲስአባን ከተቆጣጠረ በኃላ የፈጠራችኋት ናት? ...ቤተክርስትያን የተቃጠለባት፣ ክርስትያኖች እንደ በግ የታረዱባት፣ እምነታችንንና ስርአታችንን ጠብቀን እንሄዳለን የሚሉ በአክራሪነት የተፈረጁባት ...በፔትሮሊየም ዶላር ሰክረው ሀገር የሸጡት እነ አሊ አብዶ የነገሰቡት አዲሲቷ ኢትዮጵያ! ... እስቲ ልጠይቅህና መልስ ስጠኝ?"

ጐልማሳው ጳጳስ ትንፋሽ ወስደው ቀጠሉ፣

"...አሊ አብዶ በአጭር ጊዜ ውስጥ በመዲናይቱ 98 መስኪዶችን እንዳስገነባ ታውቃለህ? በአዲሳባ የመስኪዶች ቁጥር ከአብያተክርስትያናት በ42 የበለ ልቆ እንደሚገኝ መረጃ አለህ? እንግዲያውስ ልንገርህ! በአዲሳባ ብቻ 180 መስኪዶች ይገኛሉ። ከላይ ከተጠቀሱት መስኪዶች መካከል 130 ያህሉ ባለፉት 15 አመታት የተሰሩ ናቸው። በዚህ ወቅት የተሰሩት አብያተክርስትያናት አራት ብቻ ናቸው። የእናንተ አዲሲቷ ኢትዮጵያ ይህን ትመስላለች። ለዚህ ምላሽ አላችሁ?"

አዳራሹ በቁጭት ጉምጉምታ ታጀበ።

"... ታሪክ ለመስማት ፍላጐት ካለህ የሀገራችን ታሪክ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ታሪክ ነው። ሂድና ታሪካችንን ለማጥፋት የባህል ሚኒስትር ያደረጋቸሁትን ሰው በብራና ላይ የተጻፉ አዲሷ የምትላት ኢትዮጵያ የማትክዳቸውን፣ ዘመን የማይሽራቸውን ቅርሶች ጠይቅ። እዚህ የተቀመጥነው የአባቶቻችንን ርስት አሳልፈን ለመስጠት እንዳይመስልህ።"

አዲሲቷ ኢትዮጵያ እያየኋት የእንቧይ ካብ ሆነችብኝ። ታሪኳም ጤዛ ወረረው።

የደህንነት ሹሙ ኢሳያስ የጻጻሱን ንግግር አቋርጠ፣ "የአባቶቻችንን ርስት!... ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት! ... አንድ ሀገር አንድ እምነት! ...አንድ ጌታ አንድ ሀይማኖት አንዲት ጥምቀት! የሚል ቲሸርት ለብሶ መሄድ ፀብ አጫሪነት ነው። ቲሸርቱ ተሰርቶ የተሰራጨው እዚህ ውስጥ ካላችሁት አንደሆነ መረጃዎች በእጃችን ላይ ይገኛል" ብሎ በእጁ የያዛቸውን መጽሐፍትና ካሴቶች ከፍ አድርጐ አሳየ።

ቀጣዩ ተረኛ አቡነ ሳሙኤል ሆኑ። እንዲህ በማለት ንግግራቸውን ጀመሩ፣

"...አቶ ኢሳያስ አጃምለህ ያቀረብከው ልክ አይደለም። አንድ ሀገር አንድ አምነት የሚል ቲሸርት አሰርቶ ያሰራጨ የለም። እንደዚህ አይነት መልእክት የያዘ ቲሸርት የለበሱ ካሉ ከእኛ ውጪ ያሉ ሰዎች ናቸው። የዛትከውን ማድረግ ትችላለህ። ነገር ግን የአንድ ጌታ፣ ሀይማኖት፣ ጥምቀት የአምላክ ቃል ነው። ወደ ኤፌሶን ሰዎች 4:5 ላይ አንድ ጌታ፣ አንድ ሀይማኖት፣ አንዲት ጥምቀት ይላል። እኛም እየሰበክን ያለነው ይህንኑ ነው። ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ናት ስንል ጥንት በሕገ አበው (በህገ ልቡና) ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በሕገ ወንጌል በጠቅላላው ከ3000 አመታት በላይ ኢትዮጵያ ከአምልኮተ እግዚአብሄር አልተለየችም ማለታችን ነው። ይህንን በማድረጋችንና ሀይማኖቱ የሚፈቅደውን በመፈፀማችን የሚያሳስረን ከሆነ ለመታሰር ዝግጁ ነን። በተጨማሪም አቶ ኢሳያስ ከፍ አድርገህ ያሳየሽውን መጽሀፍ የጻፍኩት እኔ ነኝ። በዚህ ምክንያት ልታስሩኝ ከፈለጋችሁ ከእናንተ በላይ እኔ ደስተኛ መሆኔን ልነግርህ እወዳለሁ።"

ኢሳያስ በድጋሚ ማስታወሻ ደብተሬ ላይ፣

"የሲአይኤ መልእክተኛ መሆኑን ደርሰንበታል። ማህበረ ቅዱሳንን የሚያሸከረክረው እሱ ነው።ይሄን ወህኒ የሚያስወርደውን መጽሐፍ የጻፈው እሱ ነው" በማለት መጽሐፉን ገፉ አደረገልኝ።

ርዕሱን ሳየው "እውን በኢትዮጵያ የሀይማኖት መቻቻል አለን?" ይላል።

ትልቅ ርእስ ነው። ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሊወያይበት የሚገባና ለማንበብ ቀልብ የሚስብ ነው። ፀሀፊው መቻቻል አለ፣ የለም ብለው የመጻፍ ህገ መንግስታዊ መብት አላቸው።ርግጥም ሀሳቡ በነፃነት በመገለጹ ቃሊቲ የሚያስወርድ መሆኑ አልዋጥልኝ አለ።

አቡነ ሳሙኤል ድምጻቸውን ከፍ አድርገው የመጨረሻ ጥይታቸውን ተኮሱ፣

"... በአሊ አብዶ! አብዱ! የግራኝ መሀመድ መልእክተኛ ዘመን እምነታችንን ለማጥፋት ተንቀሳቀሳችሁ። ዛሬ ደግሞ ዘርአይ አስግዶም የሚባል ቁጥር መደመርና መቀነስ የማይችል ሰው ኢቲቪ ሀላፊ አደረጋችሁ። የአዲሳባ ስቱዲዮም ምን ያህል ሰዎች የመያዝ አቅም እንዳለው የማያውቅ! እባካችሁ! ባለስልጣን ከማድረጋችሁ በፊት መሰረታዊ የሂሳብ ስሌት አስተምሩ።"

ፓትሪያርኩ ተወራጭተው አቋረጡት፣

"የሰው ስም ማንሳቱ ደግም አይደል። ቅሬታችንን በአግባቡ ማቅረብ ይሻላል። የመንግስት ሀላፊዎች ምላሽ እንዲሰጡ እድል መስጠት ይኖርብናል" ብለው ተናገሩ።

በማስከተል የቀረቡትን አስተያየቶች ሀሊናን ያደማሉ። አቅምና ሞራል ያላሸቃሉ።አለም ያወቀው ፀሀይ የሞቀው ሀቅ በመሆኑ መላወሻ ያሳጣሉ። ሌላው ቀርቶ በእብሪት ተወጥሮ የነበረው ኢሳያስ እንዳንቀላፉ አውራ ዶሮ ከአንገቱ ያጎበጡ ነበሩ። የማይቀር እዳ ነበረና እየተናነቀን ተጋትነው።

በእውነቱ የነበረው ወቀሳ የኢህአዴግን የቤት ውስጥ ቀጋ መሆን የሚያመላክቱ ነበር። የሰነፎች መንገድ እየተጓዝን እንደሆነ ተሰማኝ። እንኩን የለሽ ህገ - መንግስት፣ አዲሲቷ ኢትዮጵያ፣ ምናምንቴ እያልን የምንዘምረው ራሱ ምናምንቴ ሆኑብኝ። የህዝቦች እኩልነት፣ የሀይማኖት ነፃነት፣ አንድ እግር በመሬት እያልን እንደ ፈረስ ስናናፉ መኖራችን ወለል ብሎ ታየኝ። ከአለት የጠጠረ ልብ ተሸክመን፣ ስህተቶቻችንን በጉያችን ደብቀን ጣታችንን ወደ ሌላ እየቀሰርን እንደሆነ ተገነዘብኩ።

የሰብሰባውን የውሳኔ ሀሳብ ለመቅረጽ ለግማሽ ሰአት ረፍት ተሰጠ። ሁሉም አዳራሹን ጥሎ በመውጣት በቡድን ተከፋፍሎ መመካከር ጀመረ። ኢሳያስ ቀንደኛ መአድ ብሎ ወደፈረጃቸው ወጣቱ ጳጳስ ሄድኩኝ። እንዲህ በማለት ጠየኳቸው፣

"አባቴ!የእርሶ ሀሳብ ተስማምቶኛል። በኮሙዩኒኬሽን ጽ/ቤት በሀይማኖት ዙሪያ ያሉትን ችግሮች ለመቅረፍ የሚያስችል መወያያ ጽሁፍ እያዘጋጀን ነው። በመላ ሀገሪቱ የሚሰራጭ ነው። በአንዳንድ ነጥቦች ላይ

የእውቀት ችግር አጋጥሞናል። ለምሳሌ መሰረተ እምነትና ስርአት የተባለውን ቢያብራሩልኝ።"

በደስታ ውስጥ ሆነው እንዲህ በማለት አስረዱኝ፣

"...መሰረተ እምነት (ዶግማ) በአምላክ ቃል መሰረት ብቻ የቆመ፣ የሚጨመርበትና የሚቀነስለት ወይም እንደ ሁኔታው ቷይቶ የሚሻሻል ነገር የሌለበት ዘላለማዊ ነው። ቀኖና ደግሞ አምልኮተ እግዝአብሔርን ለማካሔድና ወንጌልን ለማሰራጨት ሲባል የሚወጣ ስርአት ነው። ስርአት ሊቀየር ይችላል። ስርአት ባህርይው ቋሚነት የሌለው፣ ከህዝቡ የኑሮ ደረጃና የአስተሳሰብ እድገት፣ ከአለም ስልጣኔ አንፃር እየተሻሻለ፣ አያደገና እየተለወጠ የሚሄድ ነው። አለም አቀፍ ሁኔታው ተጠንቶና ከክርስትና ቀኖና ጋር ተመሳክሮ መታረም ያለበት ጉዳይ ቢስተካከል የተሻለ ይሆናል።"

አንገቴን በመነቅነቅ እንደገባኝ አሳየሁ። አስከትዬ እንደሚከተለው ጠየኳቸው፣

"ህገ ልቦና፣ የክርስቲያን ደሴት የሚባለው ሀይማኖታዊ መሰረት አለው?"

ከጥቂት ዝምታ በኃላ እንዲህ በማለት መልስ ሰጡኝ፣

"በሚገባ። ህገ-ልቦና ማለት ህገ-አሪትና ህገ- ወንጌል ከመመስረታቸው በፊት ሰዎች አምላካቸውን የሚከተሉበት ነው። የተጻፈ ህግ አይደለም።ርግጥ የክርስትያን ደሴት የሚለው ምን ማለት እንደሆነና፣ ምን ማለት እንዳልሆነ የመረዳት ችግር አለ። ከሲኖዶሱ ይጀምራል። የክርስቲያን ደሴት ማለት ክርስቲያን የሆነ ብቻ የሚኖርባት ሀገር ማለት አይደለም።"

አጀንዳ መቀየር ስለፈለኩ፣

"በሀገር ጉዳይ ላይ ተቀራርበን መስራት ይጠበቅብናል። ይህ ክፍተት የተፈጠረ ይመስለኛል።" አልኳቸው።

"...እናንተ ከማን ጋር እየሰራችሁ እንደሆነ አታውቁም። ፓትሪያርኩ አምባገነን ሆነዋል። አፍ አውጥተው ልጆቼ እያሉ ማንም አይነቀንቀኝም ብለዋል። እናንተ ሙስና! ሙስና! ትላላችሁ። ትልቁ ምዝበራ የተንሰራፋው እዚህ ነው።"

"በረከት ስምአን አጫውቶኛል።" አልኳቸው።

በረከት ፓትሪያርኩ ላይ ያለውን አቋም አውቃለሁ። ቢኖሩም የማይጠቅሙ፣ ባይኖሩም የማይገዱ (Good for nothing) ብሎ ከሰየማቸው እነ ሽማግሌው ስብሀት ነጋና አማቹ አለቃ ፀጋዬ፣ ልደቱ አያሌው፣ ሊቀ ትጉሀን አስታጥቄና ፕሬዝዳንት ግርማ ጐራ ፓትሪያርኩን ከጨመራቸው ቆይቷል።

"...ከማን ጋር እየመከራችሁ አንደሆነ ማወቅ አለባችሁ። መንግስት አንደመሆናችሁ መጠን የአርቆ ተመልካችነትና የብልሆች መንገድ ልትከተሉ ይገባ ነበር። የሀይማኖቱን ነፃነት ሳትጋፉ ከህዝበ ክርስቲያኑ ጋር ተቀራርባችሁ መስራት ትችሉ ነበር። ይህ እድል በራሳችሁ ጥፋት እያመለጣችሁ ነው። በተለይም ለሀይማኖቱ ቀናኢ የሆነው ወጣቱ ትውልድ ከእጃችሁ ከወጣ ቆይቷል።"

ከጳጳሱ አፍ የሚወጣው ቁምነገር መሬት ጠብ አይልም። መአድ እንደሳቸው የሚያስብ ከሆነ ከኢህአዴግ መዶ እጥፍ እንደሚሻል አሰብኩ። መአድ መሆን አማረኝ። አመስገኜ ወደ መቀመጫዬ ተመለስኩ። ሌሎቹም ተሰባሰቡ።

ዶክተር ሽፈራው የተስማማንባቸው በማለት ሶስት የውሳኔ ሀሳቦችን እንደጻፈ ገለፀ። አንዲህ በማለት አነበበ፣

"ሀ፡- በሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች ሀይማኖትን ሽፋን በማድረግ የተፈጠሩ ግጭቶችን እናወግዛለን። ለ፡- ህገ መንግስታዊ ድንጋጌዎችንና የህግ የበላይነት እንዲከበር፣በሀገራችን ያለውን የሀይማኖት መቻቻል ተጠናክሮ እንዲቀጥል ድርሻችንን እንወጣለን። ሐ፡- ህገ ወጥ አላማቸውን በሀይል ያራመዱ፣ ህዝብ ለህዝብ የሚያጋጩ ድርጊቶችን የፈፀሙ በህግ እንዲጠየቁ ተስማምተናል።"

ሌላ ዙር ውርጅብኝ...ሐመሩ(ሐ) ፈረደባት።

ሐመሩ(ሐ) አፍ አውጥታ መናገር የምትችል ቢሆን ኖሮ ኢህአዴግ ከኢትዮጵያ ፓለቲካ እስኪወገድ ድረስ ከመዝገበ ፊደል ሰርዙኝ በማለት ማመልከቻ ታስገባ ነበር። ምን ያደርጋል! ተስፉ ገ/ስላሴ ዘብሄረ ቡልጋ ለዘላለም ካንቀላፉ አስርተ አመታት አስቆጠሩ።

(የሐመሩ(ሐ) ፓለቲካ...

የኢህአዴግን ፓለቲካ በቅርበት የተከታተለ የሐመሩ(ሐ)ን ሮሮ ምክንያት በቀላሉ ይደርስበታል። ፓርቲው ከሌሎች አካላት ጋር ተወያይቶ የውሳኔ ሀሳብ ይዞ ከመጣ ሶስት መሰረታዊ ነጥቦች እንዲካተት ያደርጋል። ከእነዚህ ውስጥ ሶስተኛው ተቃዋሚዎች በህዝቡ የሚጠሉበትና ኢህአዴግ ውሉን መሰረት አድርጎ እነሱን የሚመታበት ሀሳብ መካተቱን ማረጋገጥ ይሆናል። ውስጥ አዋቂ ካድሬዎች "የሐመሩ(ሐ) ፓለቲካ" ብለን እንጠራዋለን። የሐመሩ(ሐ) ፓለቲካ ከኢህአዴግ የዘሮ ድምር ጨዋታ ህግጋት አንዱ ነው።

ከዚህ አንፃር በህዳር ወር 1999 ዓ.ም ወደ ሱማሊያ የኢትዮጵያ ጦር እንዲገባ ለፓርላማ የቀረበው የውሳኔ ሀሳብ የሚጠቀስ ነው። በፓርላማው አቶ መለስ እጅቹን እያወራጨ ደጋግሞ "ሐመሩ(ሐ)" እያለ የሚዝትበት ፊልም እስከ አሁንም በማህበራዊ ድህረ ገጾች ተለጥፎ ይገኛል። ውሳኔውን ተከትሎ በእነ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ፣ በእነ አቶ ተመስገንና ቡልቻ ደመቅሳ ላይ ከፍተኛው የነበረው የሀገር ክህደት ዘመቻ እስከአሁንም አላባራም።

በረከት በሁለት ምርጫዎች ወግ መጽሐፉ ይህንን አስመልክቶ ራሱን በቻለ ምእራፍ ጽፎታል። እነ ቡልቻ ደመቅሳን ለሀገር ደህንነትና ብሄራዊ ጥቅም ያልቆመ፣ኢትዮጵያ ላይ የተቃጣውን አደጋ ለማስወገድ የሚደረገውን እንቅስቃሴ ለማደናቀፍ የተንቀሳቀሱ፣ የኤርትራ መንግስት ለማስደሰትና የልብ ልብ እንዲሰማው በማድረግ አሰላለፉቸውን ከሻእቢያ ጋር ያደረጉ ብሎቸዋል።)

የሐመሩ (ሐ) ፓለቲካ አንደ ፓርላማው ሁሉ አባ ጳውሎስ ቢሮ አልሰራችም። የሲኖዶስ አባላት ደምጽ ብልጫ የሚባል ዲሞክራሲ አያውቁም። ውሳኔ የሚያሳልፉት በመግባባት (Consensus) ላይ በመመስረት ነው።

ጳጳሳቱ ቅኔ ዘረፉብን።

አባይ ፀሀዬ በድጋሚ ይቅርታ ጠየቀ። ሐመሩ(ሐ) ተሰረዘች። ፊደሊቷ ጮቤ ስትረግጥ ታየኝ። ለእሷ እኔም ደስ አለኝ።

ስብሰባው ጨርሰን ስንወጣ የሰላ ትችት ሲያቀርቡ የነበሩት ሁለት ጳጳሳት ወደ እኔ መጡ። ወጣቱ ጳጳስ ጐተት አድርገው አስቀሩኝ። "አደራህን ልጄ! ባጠለቅከው ማህተብ ይገፍሀለሁ። የተስማማንባቸውን ብቻ ተናገር። የማሰር ፍላጐት ካላችሁ እኛን እሰሩ። ወጣቶቹ ለእምነታቸው ተቆርቋሪ በመሆናቸው እኛ አድርጉ ያልናቸውን አድርገዋል። ደግሞም አትርሳ ወንድሞችህ ናቸው።"አሉኝ። ከልቤ ቃል ገብቼ ተሰናበትኩ።

ውጭ በራፉ ስደርስ የአባይ ደቀ መዘምራን ተሰባስበዋል። አንድም ትንፍሽ ሳይል አቀርቅሮ ሲያዳምጥ የነበረው ኩማ፣ "ሁለተኛ የቤት ስራችንን ጊዜ ሰጥተን ሳንሰራ እንደዚህ አይነት ወራዳ ስራ ውስጥ መግባት የለብንም " አለ።

ኮሚሽነር ወርቅነህ በበኩሉ፣

"እንዲታሰሩ የለየናቸውን አስቀድመን በማሰር አጀንዳውን ወደ ፍቱልን ተማጽኖ እናሸጋግረው ነበር። የህይል ሚዛኑ ወደ እኛ ይሆን ነበር" ብሎ በቁጭት ተናገረ። "ከማሰሩ ይልቅ የጀመርነውን የመከፋፈል ስትራቴጂ አንድ ደረጃ ማድረስ ነበረብን" በማለት ኢሳያስ ተቃወመ። አባይ ዝም አለ... ዝምታ

አይነቅዝም በሚመስል መልኩ። በተሸናፊነት ውስጥ ሆነን ተለያየን።

ወደ ቤቱ ገብቼ ኢቲቪ ከፈትኩ። የሁለት ሰአት ዜና ሊጀምር መሸጋገሪያ ሙዚቃ እያሰማ ነው። ጓደኛዬ መሰለ ገ/ ህይወት ከነግርማ ሞገሱ ዜና ሊያነብ ብቅ አለ። መሰለ በእኔና ፍሬህይወት አያሌው ሲመራ የነበረው የመዲናይቱ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ነው። ግንኙነታችን የአለቃና ምንጅላት ሳይሆን የጥሩ ጓደኝነት ነበር። በምርጫ 97 ማግስት የተከራየበት የግለሰብ ቤት ባለቤቶች " እንደዚህ አይነት ነጭ ውሸት ያዘለ ዜና እያነበብክ እቤታችን እንድትኖር አንፈቅድም " ብለው አስለቀቁት። እኔና ፍሬ ተሯሩጠን አንዲት ክፍል የቀበሌ ቤት አሰጠነው። ሀገር ጥዬ ከወጣሁ በኃላ በአውጫጭኝ ተንገላቶ እንደነበር ሰማሁ። አዝናለሁ!

መሰለ የመጀመሪያውን ዜና እንደሚከተለው አነበበ፣

"...በመንግስት ከፍተኛ ሀላፊዎች የተመራ ቡድን ከኢትዮጵያ ተዋህዶ አርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስ ጋር ገንቢ ውይይት በማድረግ ባለ ሶስት ነጥብ የአቋም መግለጫ ማውጣቱን የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ጽ/ቤት ሀላፊው ገለጹ። አነዚህም: ሀ:- በሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች ሀይማኖትን ሽፋን በማድረግ የተፈጠሩ ግጭቶችን እናወግዛለን። ለ:- ህገ መንግስታዊ ድንጋጌዎችንና የህግ የበላይነት እንዲከበር፣በሀገራችን ያለውን የሀይማኖት መቻቻል ተጠናክሮ እንዲቀጥል ድርሻችንን እንወጣለን ። ሐ:- ህገ ወጥ አላማቸውን በሀይል ያራመዱ፣ ህዝብ ለህዝብ የሚያጋጩ ድርጊቶችን የፈፀሙ በህግ እንዲጠየቁ ተስማምተናል።..."

ጭንቅላቴን ይገፍ ጮህኩ።

የዜናው ክፍለ ጊዜ ሲያልቅ ለመሰለ ደወልኩለት። ወደ ዜና ማንበቢያው ስቱዲዮ ሊገባ ሲል ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ፉክስ እንደተደረገና ዘርአያ እየሮጠ መጥቶ እንደሰጠው ነገረኝ። ለካስ የአባይ ፀሀዬ ዝም ያለው እየቋጠረ ነበር።

ለሊቱ ተጋመሰ...አልተኛሁም።

ወፍ ተንጫጫ...ነጋ... አልተኛሁም።

ጭንቅላቴ የሰው እስኪመስል ከበደኝ። ጆሮዬ ጭው በሚል የማያቋርጥ ድምፅ ተበከለ። የናወዘ ገላዬን በቀዝቃዛ ውሀ ነክሬ ወደ ቢሮ ሄድኩኝ። በደመነፍስ።

ነፋሻማው የሲኤምሲ አየር ጭንቀትና ነፃነትን ያነፍሳል። የጭንቀቱ ቀን እያጠረ ነው...ሀገሬን ለቅቄ ለመሰደድ የወራት እድሜ ቀርቶኛል...መሸቷል... እየነጋም ነው። ስደት ንጋት የሆነባት አዲሲቷ ኢትዮጵያ!!

***

የኢህአዴግ ከንፍ የሆነው መጅሊስ

በሶስተኛው ቀን...

ከኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት (መጅሊስ) ጋር ለመወያየት ቀጠሮ ይዘናል። ረፍት ያጣው ህሊናዬ አጥር ላይ ተቀምጧል። ሁለት ምርጫዎች ፊት ለፊቴ ተጋርጠዋል። ዳግም ብሶት ላለመስማት መቅረት፣ አሊያም ለታሪክ ማስታወሻ እንዲሆን መገኘት። ርግጥ እንደ ሲኖዶሱ እንደማይከብድ አውቃለሁ።

የኢህአዴግ የፓለቲካ ቁማር አንገቴ ጋር ደርሷል። ንቅዘት የነገሰበት ስርአት ማገልገል ሰልችቶኛል። በተቻለ መጠን አስገዳጅ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር መሸሽ አማራጭ አድርጌዋለሁ። ህሊናዬ አሸንፎ ቀረሁ። በእኔ ስር የነበረውን ካድሬ ላኩት። ሰለሞን ይባላል። ሰለሞን የኮሙዩኒኬሽን ጽ/ቤትየሰው ሀይል ልማት ዲያሬክተር ነበር።

ሰለሞን ከስብሰባው ሲመለስ ፊቱ ፀሀይ ሆኗል። ሳልጠይቀው እንዲህ በማለት መናገር ጀመረ፣

"ኢህአዴግ ለብሔር ብሔረሰቦችና ሀይማኖት እኩልነት ጠንክሮ እንደሰራ የሚያመላክት ስብሰባ ነበር። ከመጅሊሱ ጋር የተደረገው ውይይት የውስጠ ድርጅት ህዋሳት ስብሰባ ያህል ቀላል ነበር። የመጅሊሱ አባላት አክራሪዎች በጉያችን አሉ፣ በውስጣችን ተሰግስገዋል፣ ጥቂቶች ስለሆኑ ከመንግስት ጋር በመተባበር ለህግ እናቀርባቸዋለን ብለዋል። ህዝበ ሙስሊሙ ከመንግስት ጐን እንዲቆም ጥሪ እንደሚያስተላልፉ ቃል ገብተዋል።"

ሰለሞን ገራገር ትዝብቱን እየነገረኝ ወደ አራት ኪሎ ኢህአዴግ ቢሮ በሀሳብ ሄድኩኝ።

ወደ ትግል ጓደኞቼ ...

መኩታር ከድር...ሬድዋን ሁሴን ... ካሚል አህመድ ።

የፌደራሉን መጅሊስ ጠፍጥፈው የፈጠሩት መኩታር፣ ሬድዋንና ዶክተር ሽፈራው ናቸው። ከኦሮሚያ ወደ መጅሊሱ ተለይተው የሚመጡትን መኩታር ይለያል። የኢህአዴግ ቢሮ ሀላፊ እያለ ኦሮሚያን ወክለው ስለመጡት አዛውንት ያቀረበው ሪፓርት አስደማሚ ነበር። ስለ አባቱ ምስክርነት የሚሰጥ ይመስል ነበር። ሬድዋን ደግሞ ደቡብና ሀረሬን ወክለው ለሚመጡ የመጅሊሱ አባላት ሀላፊነት ይወስዳል። የፌደራሉ ምርጫ ከመካሄዱ በፊት የሁሉም

ከልሎች የፀጥታ ቢሮ ሀላፊዎች በፌደራል ጉዳዮች ጠሪነት አዲሳባ ይመጣሉ። መጅሊሱ ውስጥ ሊገቡ የሚችሉ ሙስሊሞችን እጩ በዝርዝር ያቀርባሉ። የሀገር ውስጥ ደህንነት በበኩሉ የኋላ ታሪክ ያጣራል።

በአዲሳባ ከቀበሌ እስከ ከተማ ያለውን ደግሞ ሬድዋንና ካሚል አህመድ። ጠርዝ የረገጠ የሊብራል አስተሳሰብ ያለው ሬድዋን ብዙ ቦታ ጆከር ነበር። በአዲሳባ ከቀበሌ እስከ ከተማ ምርጫ ከመካሄዱ አንድ ሳምንት በፊት ዝርዝሩ ለካሚል ይደርሳል። ሙስሊም ለሆኑ የፓርቲው አባላት ተለይተው አረንቴሽን እንዲወስዱ ይደረጋል። አስመራጮች፣ ሊቀመንበር፣ ምክትሉና ፀሀፊው አስቀድመው ይለያሉ። የቀበሌው ካድሬ የአዳራሽ ዝግጅቱንና ጥሪውን ያከናውናል። ሙስሊም ሆነም አልሆነ በታዛቢነት በስብሰባው ይገኛል።

(ሁልጊዜም የሚገርመኝ ነገር ቢኖር የእስልምና የምክር ቤት ምርጫ ለምን በወረዳና ቀበሌ አዳራሽ እንደሚከናወን ስመለከት ነበር። የእድር አባላት ነፃነታቸውን ለመጠበቅ አመራራቸውን በተቋማቸው የሚመርጡበት ሁኔታ ባለበት ሁኔታ ህዝበ ሙስሊሙ አዳራሽ እንዲሰበሰብ ማድረግ በርግጥም አስገራሚ ነው። መልስ የሚፈልግ ጥያቄ!)

በመሆኑም በየደረጃው ያለው ምክር ቤትና መጅሊሱ ለሙስሊሙ ማህበረሰብ ፍላጐት ውጪ በኢህአዴግ ተፅዕኖ የተመረጠ በመሆኑ ተገዥነቱ ለመረጠው አካል መሆኑ አይቀርም። የሚያስተላልፈው መልእክትም ከዚህ ውጪ ሊሆን አይችልም።

ይሄ አሳፋሪ ሀቅ በአቶ መለስ፣ በረከትና እንከን የለሹ ህገ መንግስት እውቅና የሚፈፀም ነው። ሁሉን ከመቆጣጠር አባዜ የሚመነጭ። በእነ ሬድዋንና መኩታር ብቻ ማላከክ ልክ አይደለም። ሁሉም በየደረጃው ተርመጥምጧል። የህግና ሞራል ጥያቄው ለሁሉም የኢህአዴግ ቁንጮዎች መወርወር ይኖርበታል። መጅሊሱን የኢህአዴግ ክንፍና ልሳን ያደረጉት ሁሉም ስለሆኑ።

ምእራፍ ሃያ ስድስት

የአክራሪነት ጫካ

"... አክራሪነት ሌላ ቦታ ሳይሆን በውስጣችን የመሸገ መሆኑ የማይታበል ሀቅ ነው።"
ም/ጠ ሚኒስትር መኮንን ከድር

"...እነ ሬድዋን፣ መኮንን፣ ደመቀ፣ አብድላዚዝ ፣ጁነዲን የከርስቲያን ስብእና የተላበሳችሁ መሪዎች ተበሎ ማስተርስ ሲሰጣችሁ ምን ተሰማችሁ?"
ተፈሪ (የኢህአዴግ ቢሮ ፋይናንስ ሀላፊ)

የህሊና ጥያቄዎች...

እንደ እውነቱ ከሆነ የሀይማኖታዊ ይዘት ባለው ርእስ ላይ ማስታወሻ ለመጻፍ ሳስብ በአእምሮዬ የተመላለሰው ጥያቄ "እኔ ማነኝና ይህንን ትልቅ አጀንዳ የምነካካ? "የሚል ነበር። ከብዙ ማወላወል በኃላ ፍልስፍናን ከሰማየ ሰማያት እንዳወረደ የሚነገርለት ሶቅራጥስ ተናግሮታል ተበሎ የሚገለፀው አባባል ጭንቅላቴ መጣ... "አለማወቄን ማወቄ ነው"። እናም ምንም እንደማላቅ እያወኩ የሚከተሉትን በህሊናዬ ዘወትር የሚንከላወሱ ጥያቄዎች አነሳሁ።

...አክራሪነት ምን ማለት ፣ ምንስ ማለት አይደለም ? ፣ አስኳሉስ የት ነው ያለው?... እውን በአዲሳአባ የሀይማኖት ተቋማት (በተለይ መስኪዶች) በዝተዋል?... የቤተክርስቲያኖችና መስኪዶች መበራከት በራሱ የሀይማኖት ነፃነትን ያመጣል?፣ ... በአጠቃላይ መልኩ የሀይማኖት ጉዳይ የኢትዮጵያን የፓለቲካ ምህዳር የሚያናውጥ ተግዳሮት ለምን ሆነ ?፣ ችግሮቹ ወደተወሳሰበ ምእራፎች ለምን እየተሸጋገሩ ሄዱ?

***

እንዴት እንመካከር?

ቀደምቶቹ የስነ ልቦና ፈላስፋዎች ሀይማኖትን ከሞት መፍራት፣ ከሞት በኃላ ያለ ህይወትና ሞራሊቲ ጋር ተያይዞ ከሚመጣ ፍላጐት አንፃር ይመለከቱት ነበር። በአሁን ዘመን ደግሞ ሀይማኖት የስልጣን፣ ነፃነት፣ ተቀባይነት፣ ህብረተሰባዊ ግንኙነትና እሴት የመሳሰሉ በርካታ ፍላጐቶች ውህደት መሆኑን መተማመን የተደረሰበት ሆኗል።

በመሆኑም የመጀመሪያው ጉዳይ የሀይማኖቱ ተከታይ ለእምነቱና የእምነቱ ስርአቶች ቀናኢ፣ስሱና ተቆርቋሪ መሆኑን ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። በዚህ ዙሪያ የሚፈፀም የግለሰብ ጠብ አጫሪነት በአጭር ጊዜ ውስጥ ተዛምቶ አገር አቀፍ ነውጥ ሊፈጥር ይችላል።

በማስከተል የተገራ አንደበት መያዝን ግድ ይላል። ይህ ማለት ተከድኖ ይብሰል እንደማለት አይደለም። ችግሮች መኖራቸው እየታወቀ አኳኩሎና ቀባብቶ ማቅረብም አይደለም። ይልቁንስ ስሜትን አውጥቶ መነጋገር የጥላቻና ቁርሾ መነሻን ለማስወገድ ይረዳል። በተረጋጋ ሁኔታ ነገሮችን በሰከነ መንፈስ መወያየት ሰላማዊ ልቦናን ያጎናጽፉል። ይህም ሆኖ ከጠብ አጫሪዎች መራቅ ስለማይቻል ፣ እንደዚህ አይነት አጋጣሚ ሲከሰት ራስን መግራትና ምክንያታዊ መሆን ያስፈልጋል።

በመሆኑም በአደጋ ላይ ያለ ሁኔታ ላይ ጋዝ የሚያርከፈክፍ አካሄድ መከተል በራሳችን ቁስል ላይ እንጨት እንደመስደድ ይቆጠራል። በኋላ ቀርነትና መረጃ እጥረት ውስጥ የሚዳክረውን ምስኪን ህብረሰብ በፍርሀትና ተስፉ መቁረጥ ውስጥ መክተት ግፍን አለመፍራት ይሆናል።

***

ኢትዮጵያና ሐይማኖት፣

ተግራሪ አመለካከቶች አደባልቆ መጓዝ ከየትኛውም የአለም ሀገሮች በላይ ለኢትዮጵያ እጅግ አደገኛ እና አስፈሪ ይሆናል። ከዚህ አንፃር ሀገራችን ከሌሎች ሀገሮች የምትለይበትን ሁኔታ ማጤን ያስፈልጋል። የሀገራችን ጂኦ - ፖለቲካል አቀማመጥ፣ ከስድስት ደርዘን በላይ ብሔረሰቦች መገኘት፣ የክርስትና እና እስልምና ሀይማኖት ተከታዩ ቁጥር መቀራረብ ዋነኞቹ ናቸው። ይህ በራሱ መታደልም፣ ስጋትም ነው።

ስጋቱ በዚህ ዙሪያ የሚነሳ ግጭት የሀገሪቱን ህልውና አደጋ ላይ የመጣል አቅሙ ነው። ለማይበርድ ደም መፋሰስና እልቂት ከመዳረጉም ባሻገር ወደ ብሔር ግጭት ሊሄድ ይችላል። በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የብሔርና ሀይማኖት ጥያቄዎች የሚዛመዱበት ሁኔታ ሰፊ ነው። የሱማሊያ፣አፋር ፣ስልጤ ፣ሐረሬ የመሳሰሉ ብሔረሰቦች ማንነት ጥያቄ ውስጥ የእስልምና ሀይማኖት አንዱ ገጽታ ነው። ከዚህ ውጭ ማሰብ ግንጥል ጌጥ ከመሆን አያልፍም።

መታደሉ ደግሞ ህብሩና ውበቱ ነው። የኢትዮጵያ ህዝቦች አንዱ ወሳኝ ገጽታቸው የባለ ብዙ ባህልና እምነት መተባበር የፈጠሩት ህብር ነው።ያለ ልዩነት ሕብረት፣ ያለሕብረት ደግሞ ሕይወት ዘበት እንደሆነና በፍፁም ውህደት

ሰው አድርገው ያቆሙን እልቆ መሳፍርት ሴሎች መልካም አርአያ ናቸው። ከአንድነታቸው የተነሳ ተለይይተው መኖር አይችሉም። ኢትዮጵያዊያን ነን።

በሀገራችን ያሉ ሀይማኖቶች የሚታወቁት በኢትዮጵያዊ ታሪክ ፣ ባህልና ትውፊቶች ላይ የጋራ አንድነት ፈጥረው መኖራቸው ነው። የኢትዮጵያ ሀይማኖቶች ዘር ሳይለያቸው አንድነትን የጋራ እሴት አድርገው የያዙ ናቸው። የአለም አቀፍ ማህበረሰብ የሀይማኖት ተከታዮቹ ቁጥር መቀራረብና የጋራ ፍቅር በማየት የሀይማኖቶች መቻቻል ተምሳሌት ያደረገን በዚህ ምክንያት ነው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በማህበረሰባችን ውስጥ ለሀይማኖታዊ ስርአቶች ፍፁም ተገዢ መሆንና ፅንፈኝነትን አደባልቆ የማየት ችግር ይስተዋላል።

በሀይማኖት አስተምርሆዎች መመራት ፣ የሌላን ሳይጋፉ የራስን እምነት አጥብቆ መያዝ፣ ለሀይማኖት ነፃነት መታገልና አክራሪነት ሆድና ጀርባ ናቸው። መጾም ፣መፀለይ፣ እምነቱ የሚያዘውን አልባሳት መልበስ የሚከበር እንጂ በፅንፈኝነት አያስወነጅልም። የእምነቱ ተከታዮች የሌላውን ሳይነኩ ለእምነታቸው ከብረት ግንብ የጠጠረ ተገዥነት ማሳየታቸው በምንም መመዘኛ አክራሪነት ሊሆን አይችልም። ቤተክርስትያኖች እና መስኪዶች እንዲበራከቱ ገንዘብና ጉልበትን መስዋት ማድረግ ሊበረታታ የሚገባው እንጂ በአክራሪነት የሚያስፈርጅ አይደለም። ሊሆንም አይገባውም።

በተቃራኒው አክራሪነት የእኔን በግድ ካልተቀበልክ እገድልሀለው ፣ አጠፋሀለው የሚሉ ናቸው። አክራሪነት በማስገደድ ተከታይ እንድትሆን የሚደረግበት ስርአት ነው። የአክራሪዎች የመጨረሻ አላማ የእነሱ ተከታይ ያልሆነውን ክፍል በሀይል እነሱ በቀደዱት ቦይ ብቻ እንዲፈስ መጫን ነው። ከዚህ ውጭ የሄደውን የሀይማኖቱን ህልውና በመታደግ ስም እስከመግደል ይሔዳሉ። አክራሪዎች ሌላዉ እውነተኛ አይደለም በማለት የሚያጥላሉና የሚያሳድዱ ሲሆኑ በመዝገበ -ቃላታቸው ውስጥ በልዩነት ውስጥ መኖር ፣ መከባበር፣ መቻቻል የሚል የለም። መጨረሻውም የከፉ ነው።

***

የሀይማኖት ተቋማት መብዛት ስጋት ወይስ እድል?

ከዚህ አኳያ በብዛት ወቀሳ የሚያቀርቡት የኦርቶዶክስ አምነት አመራሮች ናቸው። ይህም በአዲሳባ ከተማ የኦርቶዶክስ አማኙ ቁጥር ልቆ በሚገኝበት ሁኔታ የመስኪዶች ብዛት ከአብያተ ክርስትያናት በዝቶ ይገኛል፣ ባለፉት አስራ አምስት አመታት መስኪዶች በ72% ሲጨምሩ አብያተክርስትያናት በ3% ብቻ ጨምረዋል የሚሉት ዋነኞቹ ናቸው። ይህ

ተቃውሞ አርቆ ላስተዋለው ሰው ውሀ የሚቋጥር አይደለም።

አዲሳባ እንደስፉቷና መለጠጧ አንፃር በርካታ ቤተክርስትያኖችና መስኪዶች ያስፈልጓታል። አንድ ነዋሪ ወደ እምነት ተቋሙ ለመሔድ ትራንስፓርት መያዝ አሊያም ወንዝ መሻገር ግዴታው መሆን የለበትም። አሁን ባለው ህዝብ ብዛት ከተሰላ ስርጭቱ አንድ መስኪድ ከ5 ሺህ በላይ ለሆኑ የእስልምና ተከታይ ይሆናል። ስርጭቱ ፍትሀዊ ቢሆን ኖሮ በአንድ ቀበሌ በአማካይ የሚኖረው መስኪድ ከሁለት አይበልጥም። በአንድ ቀበሌ ከደርዘን በላይ መቆመሪያና ጫት ቤቶች በተንሰራፉበት ሁኔታ የመልካም እሴቶች መገንቢያ የሆኑ መስኪዶችን በዝተዋል ብሎ መከራከር የተሸዋረረ አመለካከት ከመያዝ የሚመነጭ ነው።

ርግጥ መስኪዶቹ የተገነቡበት ሁኔታ ውሱንነት ያለበት መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም። ይህንን ማስተካከል ከኢትዮጵያ ሙስሊሞች የሚጠበቅ ይሆናል። በተለይም ተቋማቱ በውጭ እርዳታ የሚያገኙትን ገንዘብ እየፈጠረ ያለውን ተጽእኖ ማጤን ተገቢ ይሆናል።

ከውስጥ አቅም ይልቅ በውጭው ሀይል ላይ ጥገኛ የሆኑ ናቸው። በሳውዲው ልኡል፣ በእንቶኔው ሀገር ንጉስና ፕሬዝዳንት ድጋፍ የተገነባ መባሉ የተለመደ ነው። የአለም በዳኔ፣ የጅማ ነጋዴዎች፣ የአላሙዲን መስኪዶች የሚባሉት ሳይቀሩ የአረብ ሀገራት እጃቸውን ያስገቡባቸው ናቸው። አንዳንዶቹ መስኪዶች ተገንብተው ወደ አገልግሎት ሲገቡ አስተዳደራዊ ወጪያቸውን የመሸፈኑን የአንበሳ ድርሻ የውጭ ሀይሎች እንደሚወስዱ ሲደመጥ ደግሞ ሩቁን መዳረሻ በጥርጣሬ መታየቱ አይቀሬ ይሆናል።

የትኛውም የውጭ ሀይል እንደዚህ እጁን ዘለግ አድርጎ ሲደግፍ ከጀርባው ምን ሊኖር እንደሚችል መገመት አያዳግትም። በሀይማኖቱ ህግጋትና አስተምሮ ላይ መመጋገቡ የማይቀር ቢሆንም በግንባታና የአለት ተአለት አስተዳደራዊ ወጪዎች ላይ እንዲሳተፉ መጋበዝ እጅ ለመጠምዘዝ አስቀድሞ ፍቃደኛ መሆንን ያመላክታል። የመስኪዱን ኢትዮጵያዊ ጣእም የሚያሳጣው ይሆናል። እዛው ሳለ የኢትዮጵያዊውን ሙስሊም ማህበረሰብ አቅም የሚያኮላሽና ወደ መና ጠባቂ እንዲወረወር የሚያደርግ ይሆናል።

በማስከተል መመለስ ያለበት ጥያቄ የቤተክርስቲያኖችና መስኪዶች መበራከት በራሱ የሀይማኖት ነፃነትን ያመጣል ወይ?፣ለእኩልነት አስተማማኝ ዋስትና ይሰጣል ወይ? የሚለው ይሆናል።

እንደሚታወቀው በብዙዎቹ የአለማችን ሀገራት ከኢትዮጵያ ተቃራኒ የተለያየ ሀይማኖት ተከታዩ ቁጥር ተቀራራቢ አይደለም። የአንደኛው ሀይማኖት ተከታይ ከሌላኛው በላቀ ቁጥር ይበልጣል። ይህንንም ተከትሎ የሀይማኖት ማምለኪያ ተቋማት ብዛትና ስርጭት በተከታዮቹ ብዛት የሚወሰንበት ሁኔታ ያጋጥማል።

የኤሜሪካን መዲና በሆነችው ዋሽንግተን ዲሲና አካባቢዋ በየመንደሩና ጉራንጉሩ አንድ ቤተክርስትያን ይገኛል። በተቃራኒው የመስኪዶች ብዛት በጣት የሚቆጠሩ ናቸው። ይህም ሆኖ በዲሲ የሚኖረው የሙስሊም ማህበረሰብ ሀይማኖቱን በነፃነት ያራምዳል። እድሉን አግኝቶ በመስኪዶቹ የተገኘ አሊያም በአጠገቡ ያለፈ ሰው አህጉርና ቀለም ሳይለይ ህዝበ ሙስሊሙ በህብር አምላኩን ሲያመሰግን፣ ከፀሎት በኃላ ደግሞ አንዱ ሌላው ያዘጋጀውን ምግብ በጋራ ሲቋደሱ ይመለከታል፣... ኢትዮጵያዊው ከኤርትራው...ካሜሮኑ ከናይጄሪያው... ህንዱ ከፓኪስታን... አሜሪካዊው ከኢራኑ...ጋር ሲጫወትና ሲበላ ማየት ልዩ ስሜት ይሰጣል።

ይህ የሚያሳየን የሀይማኖት ማምለኪያ ቦታዎች መብዛት በራሱ የሀይማኖት የነፃነት ማረጋገጫ አለመሆናቸውን ይሆናል። በጣት የሚቆጠሩ መስኪዶች ያሉባት ዲሲ የአለም ሀገራት ሙስሊሞችን ከራሷ ዜጐች እኩል ሀይማኖታቸውን በነፃነት እንዲያራምዱ ፈቅዳለች። በተቃራኒው ከመቶ በላይ ቤተክርስትያንና መስኪዶች ያለባት ሀገራችን በነፃነት እጦት እየታመሰች ትገኛለች። በተቋማቱ ላይ የሚደርሰው ጫናና ጣልቃ ገብነት የሀገሪቷን ህልውና በመፈታተን ላይ ይገኛል።

***

አብዮታዊ ዲሞክራሲና ሌሎች ሀይማኖት

አብዮታዊ ዲሞክራሲ ለብዙዎቹ የህውሀት ታጋዮች ምድራዊ ሀይማኖት ነው። ከኢትዮጵያ ውጭ በየትኛውም ሀገር የሌለ። በታሪክ አጋጣሚ ደግሞ መንግስታዊ ሀይማኖት ሆኗል። ይህን ሀይማኖት የፈጠሩት ሰዎች ተከታዮቻቸው ሲበሉም፣ ሲጠጡም፣ ሲተኙም (በህልማቸው ሳይቀር) እንዲያስቡት አድርገው ቀርፀውታል። ሌላው ቀርቶ የግል ህይወት ውስጥ ችግር ሲያጋጥም፣ ሀዘን ሲደርስ፣ ትዳር ሲመሰረት እንኳን በዛ ቅኝት መሆኑን ማረጋገጥ ይፈልጋሉ። ለዚህ መከራከሪያ እሩቅ መሄድ ሳያስፈልግ ብዙዎቹን የህውሀት ታጋዮች ጠጋ ብሎ፣ "ሚስትህን እንዴት አገባሀት?" ብሎ መጠየቅ በቂ ይሆናል። ታጋዩም ሳያቅማማ፣" አብዮታዊነቷና የአላማ ጽናቷ ማርኮኝ!" የሚል ምላሽ ይሰጣል።

ከእለታት በአንዱ ቀን የኢህአዴግ ቢሮ የስራ ባልደረባዬ ታጋይ ይሳቅ ቆሪጥ (ዘመን ተሻጋሪው ካድሬ) ቢሮዬን ከፍቶ ሲገባ ደስተኛ ያልሆነ መልኬን ተመለከተ። ለምን እንደተበሳጨሁ አጥብቆ ጠየቀኝ። ከሚስቴ ጋር አለመግባባት ተፈጥሮ መበሳጨቴን ነገርኩት። ታጋይ ይሳቅ ለአንድ ቀን ሙሉ መልእክተ ዜናዊን ምእራፍ በምእራፍ እየገለጠ አስተማረኝ። ትምህርቱን እንዲህ በማለት አጠቃለለ፣

"... ችግር ያጋጠመህ ትዳርህን አብዮታዊ ዲሞክራሲ ባስቀመጠው ትእዛዝትና ቅኝት ስላልመራኸው ነው። እኔና ሚስቴ ተሳስበን በፍቅር የምንኖረው አብዮታዊ ዲሞክራሲ ባስቀመጠልን መስመር ስለምንሄድ ነው። አለመግባባት እንኳን ቢፈጠር አብዮታዊ ዲሞክራሲ ያስቀመጠልንን የችግር መፍቻ አቅጣጫዎች እንጠቀማለን። በየሳምንቱ እሁድ ጠዋት ልጆቻችን አስቀምጠን በሀዲዱ ላይ መጓዛችንን እናረጋግጣለን። ለዚህ ያደረሱን መስዋዕቶች ዘላለማዊ ክብር እናጐናጽፋለን።"

ይህ የይሳቅ ምክር የመቶሺዎች ነው። የህውሀት ታጋዮች አብዮቱን የሚያወድስ አታሞ በተደለቀ ቁጥር አቅላቸውን ስተው ይወድቃሉ። በእንባ ይራጫሉ። በትጥቅ ትግሉ የሞቱ ጓዶቻቸውን ስም እየጠሩ ስማእትነታቸውን ይዘክራሉ። አስተሳሰቡ የበላይነት እንዲያገኝም ተግተው ይሰራሉ።

እንግዲህ ይህ አመለካከት ነው በትጥቅ ትግል አሸንፎ መንግስት የሆነው። መንግስት ሆኖም መሰረታዊ ባህሪው የሆነው የዜሮ ድምር ጨዋታ አልተቀየረም። በመሆኑም በኢትዮጵያ ምድር አብዮታዊ ዲሞክራሲ እያለ ስለ ክርስትና እስልምናና ሌሎች ሀይማኖቶች እኩልነትና ነፃነት ማሰብ የማይቻል መሆኑን ነው። አብዮታዊ ዲሞክራሲ ከመሰረታዊ ባህሪው በመነሳት ሌሎቹን ለማጥፋት አሊያም ለማዳከም መንቀሳቀሱ አይቀርም። ርግጥ ሌሎቹ ሀይማኖቶች ከአብዮታዊ ዲሞክራሲ በፊት የተፈጠሩ በመሆናቸውና የብዙሀኑ የህይወት መመሪያ በመሆናቸው ሊያጠፉቸው አይችልም። ያለው ብቸኛ አማራጭ መንግስታዊ ስልጣኑን ተጠቅሞ ማዳከምና ችግር መፍጠር ይሆናል።

በመሆኑም አብዮታዊ ዲሞክራሲ መራሹ መንግስት የሚፈጥራቸው ችግሮች መጠነ ሰፊ ናቸው። ከእነዚህም ውስጥ... ለአንዱ ሀይማኖት ወገንተኛ መስሎ መታየት፣ ተቋማቱ እርስ በራስ ተራማጅ ያልሆነ ፉክክር ውስጥ እንዲገቡ ማድረግና በፓርቲ ውስጥ የሚታዩትን የጽንፈኝነት ችግሮች ውጫዊ ማድረግ የሚጠቀሱ ናቸው።

የሀይማኖት ተቋማት እርስ በራስ በጠላትነት እንዲተያዩና የጡንቻ ፍተሻ ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ በቀዳሚነት የሚነሳ ነው። ይህ የሚፈፀመው

የህይማኖት ተቋሞቹ በውስጣቸውና ከሌሎች ጋር የሚናቆሩበት የከፉፍለህ ግዛው መረብ በመዘርጋት ነው። አንደኛው ሌላኛውን እንደ ስጋት እየቆጠረና እየተጠራጠረ እንዲሄድ፣ በተቋማቱ መካከል መተማመን እንዳይኖር የሚያደርግ ነው። ይህ የተንኮል መረብ በትክክልም የሚፈልገውን የሚያጠምድበት ጊዜያቶች በሰፊው ይስተዋላሉ። የህይማኖት ተቋማቱ የተዛባው ፕሮፓጋንዳ ሰለባ በመሆን በተዘጋጀላቸው የጥፋት ወጥመድ ሰተት ብለው ይገባሉ። ይህ የማይታበል ሀቅ ነው።

ቀጥሎ ያለው ነገር ኢህአዴግ ችግሮቹን ውጫዊ ለማድረግ እየሄደበት ያለው መንገድ ይሆናል። ዋነኛው የአክራሪነት ሀርድ ኮር ያለው በፓርቲው አባላት ውስጥ መሆኑን እያወቀ ላም ባልዋለበት አካሄድ መከተሉ ነው። ጽንፈኝነት በኢህአዴግ ውስጥ እንደ ሰደድ እሳት እየተዛመተ መሆኑ ፀሀይ የሞቀው ቢሆንም ፓርቲው የማላከክ አቅጣጫ ተከትሏል። የኢህአዴግ አባላት በአወቅኩሽ ናቅኩሽ ፣ካድሬዎች ደግሞ የራሳቸውን አፍቅሮ ንዋይ ለመሸፈን አክራሪነትን እንደ ሽፋን እየተጠቀሙ መሆኑ ግልፅ በሆነበት ሁኔታ የበሬ ወለደ ፕርፓጋንዳ እየተሰራጨ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

በሶስተኛ ደረጃ የቡድን መብት ጠበቃ ነኝ ብሎ የሚያስበው ኢህአዴግ ህይማኖት ጋር ሲደርስ መሸብረኩ ይሆናል። አንዳንዶች ፓለቲካና ህይማኖት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጾች ናቸው ሲሉ፣ ኢህአዴግ ይህ የሚሆነው በእንከን የለሽ ህገ መንግስቱ መቃብር ላይ ነው ይላል። ኢህአዴግ ህይማኖት በመንግስት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፣ መንግስትም በህይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም በማለት ሌሎችን ያስጠነቅቃል። እንደዚህ አይነት መከራከሪያ የሚያቀርቡት የተሸዋረረ አረዳድ ስላላቸው ነው በማለት ይከሳቸዋል። በኢህአዴግ ውስጥ በቡድንና ብሄር አስተሳሰብ ላይ የተመሰረተ የፓለቲካ አወቃቀር ባለበት ሁኔታ ህይማኖትና ፓለቲካ ሊነጣጠሉ ይችላሉ? ህገር የጋራ ህይማኖት የግል ሊባል ይችላል? የአፋር፣ ሱማሌ፣ ህረሬ፣ ስልጤ ብሄረሰብ ...አወቃቀር፣ ባህልና ማንነት ከእስልምና ውጭ ሊታሰብ ይችላል?

ኢህአዴግን የሚመለከቱ ችግሮች የሚዲያ፣ የማህበረሰብ ድህረ ገጾችንና የህትመት ውጤቶችን አጨናንቀዋል። በመሆኑም በካድሬነት ዘመኔ ካጋጠሙኝ ነገሮች ውስጥ ከላይ ለተጠቀሱት ሶስት መሰረታዊ ችግሮች መገለጫ ወደሚሆኑት ወገኖች ወደ ማንሳት እንሸጋገር።

***

ከእለተታ በአንድ ቀን እንዲህ ሆነ፣
በኮሙዩኒኬሽን ጽ/ቤት ከሸመልስ ከማል ጋር የጠዋት ስራችን

ሀገራችንና አለም እንዴት እንዳደረች ለማወቅ ሚዲያ ሞኒተር የምናደርግበት ነበር። ይህን እየሰራን እያለ ፀሀፊዬ በኢንተርኮም ደውላ ከአዲሳባ ሀገረ ስብከት የተላኩ ሰዎች ሊያናግሩኝ እንደሚፈልጉ ገለፀች። እንድታስገባቸው ነገርኳት። ሁለት ጐልማሳ እድሜ ላይ ያሉ ሰዎች ገብተው ተቀመጡ። አፍታም ሳይቆዩ የአዲሳባ ሀገረ ስብከት ስራ አስኪያጁ አቡነ ሳሙኤል ወደ ኢቲቪና ኮሙዩኒኬሽን ጽ/ቤት አቤቱታ እንዲያቀርቡ እንደላኳቸው ነገሩን።

ታሪኩ እንዲህ ነበር፣

ከሁለት ቀን በፊት የእስልምና እምነት ተከታዮች በአላቸውን ለማክበር በአዲሳባ ስቴድየምና በዙሪያው ተገኝተው ነበር። በስፍራው የተገኘው የመንግስት ጋዜጠኛ በዜና ዘገባው ከ1.6 ሚሊዮን በላይ ሙስሊሞች እንደተገኙ ገለፀ። በወቅቱ የስታስቲክስ ኤጀንሲ የአዲሳባ ህዝብ 2.7 ሚሊዮን እንደደረሰ የተናገረበት ወቅት ነበር። ከእነዚህ ውስጥ የክርስትና እምነት ተከታዩ ከሰማንያ ሁለት በመቶ በላይ እንደሆነ ኤጀንሲው አሳውቋል።

በመሆኑም ሁሉም የእስልምና እምነት ተከታዮች ወደ ስቴዲዮም ወጥተዋል ቢባል እንኳን ከግማሽ ሚሊየን አይበልጥም። በዛ ላይ እንደ አቃቂ ያሉ ክፍለ ከተሞች የሚኖሩ ሙስሊሞች በአላቸውን የሚያከብሩት በአቃቂ ስቴዲዮም ላይ በመሰባሰብ ነው። በአዲሳባ ዙሪያ ያሉ የኦሮሚያ ልዩ ዞኖች በተመሳሳይ በአካባቢያቸው ያከብራሉ።

ሁለቱ መልእክተኞች ይዘው የመጡት አቤቱታ ተጨምቆ ሲታይ ይህን የሚያመላክት ነበር። ርግጥም አላስፈላጊ ፉከክር በተገባበት ሁኔታ እንደዚህ አይነት ዜና መልቀቅ ተገቢ አልነበረም። በየትኛውም መንገድ ቢሆን የስህተቱ ምንጭ መንግስት መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም። አንድም የአዲሳባ ህዝብ ብዛት ተብሎ የተገለፀው ልክ አይደለም፣ አሊያም በስቴዲየም ተገኘ የተባለው ተጋኖ ቀርቧል።

ቅሬታ አቅራቢዎቹ ያነሱት ጥያቄ ተገቢነት ያለው መሆኑን ገለጽን። አጣርተን ምላሽ እንደምንሰጥ ቃል ገብተን አሰናበትናቸው።

እየሰራን የነበረውን ሚዲያ ሞኒተሪንግ አቋርጠን የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት (ኢዜአ) ስራ አስኪያጅ ገ/ሚካኤል በአስቸኳይ ጠራነው። የሀገሪቱ ዋነኛ የዜና ምንጭ የሆነው ኢዜአ በኮሙዩኒኬሽን ጽ/ቤት ውስጥ በዳሬክቶሬት ደረጃ እንዲዋቀር ተደርጓል። እናም የኢዜአ ሀላፊውን የጠራንበት ምክንያት ከአዲሳባ ሀገረ ስብከት የመጣው ቅሬታ በጉያችን ያለው ኢዜአ የፈጠረው መስሎን ነበር። የህውሀት ካድሬው ገ/ሚካኤል ከፒያሳ እየከነፈ

መጣ። ሽመልስ እንደገመተው ምንጩ ኢዜአ ሳይሆን ኢቲቪ ሆኖ ተገኘ።

ከስሜት ሳልወጣ ቆሞ ለቀረው ዘርአይ ደወልኩለት። እንደገመትኩት አንድ አይነት ቋንቋ ማውራት አልተቻለም። እንደዚህ አይነት ዜና ማስተላለፍ የሚፈጥረውን ስሜት አስረዳሁት። ስህተቱ ሳይታሰብ የተፈጠረ ከሆነ የማረሚያ ዜና መስራት እንደሚገባ ነገርኩት። የቀረበውን ጥሬ ሀቅ ከመቀበል ይልቅ አቡነ ሳሙኤል ላይ ዛቻ ደረደረ፣

"እየገነባን ያለነውን ዲሞክራሲያዊ ስርአት እያመሰ ያለው እሱ ነው። ሰውዬው ቆብ ያጠለቀ የአሜሪካ ፓለቲከኛ ነው። የትግራይን ህዝብ ከድቶ ከትምክህት ጐራ ተቀላቅሏል። የኢህአዴግ ጠላት የሆነውን ማህበረ ቅድሳን የሚያሸከረክረው እሱ ነው። በቅርብ ቀን ልኩን እናሳየዋለን..." በማለት ሲንዘባዘብ አቋረጥኩት፣

"ዘርአይ! ዲሞክራሲያችን በአንድ ሰው የሚንገዳገድ ከሆነ ስራ እየሰራን አይደለንም፣ አሊያም ዲሞክራሲው ችግር አለበት። የእኛ ጥያቄ ለጊዜው እሱ አይደለም። የቀረበው መረጃ በተራ መደመርና መቀነስ ቢሰላ ይጣረሳል። ከሁለት አንዱ ትክክል አይደለም። ማሳመኛ ነጥብ ካለህ ንገረን። አለበለዚያ እንድታርመት እንፈልጋለን" አልኩት።

"የሐመሩ(ሐ) ፓለቲካ እንደማይቀለበስ እያወቅክ እንዴት እርማት አድርጉ ትሉኛላችሁ?" በማለት ፍቃደኛ ሳይሆን ቀረ።

ሽመልስ ስሜት ውስጥ ሆኖ፣

"ይሄን ባዶ ገረዊና ከምንገፉ በረከት ጋር እንሂድ" አለኝ።

ተያይዘን በረከት ጋር ሄድን። የተፈጠረውን በዝርዝር ነገርነው። በግል የሚዲያ ተቋማት ቢወጣ አሳፋሪ እንደሚሆን ገለጽን። ስህተት መፈጠሩ አግባብ እንዳልሆነ ነገረን። አስከትሎም፣

"በዜና መልኩ ወደ እርምት መስጠት ብንገባ የፓለቲካ ስራችን ይበላሻል። በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ በእሱ ያለምንም ችግር በመቶ ሺዎች ወጥተው ማከበራቸው፣ ይህም በእንከን የለሹ ህገ መንግስት የተገለፀው የህይማኖት ነፃነት እውን መሆኑን የሚያሳይ እንደሆነ የሚያመላክት ጽሁፍ እንላክላቸው። የቅዳሜ የኢቲቪ ህትመት ዳሰሳ በዚህ ላይ ሰፊ ትኩረት እንዲሰጥ አቅራቢዎቹን ጠርታችሁ አረንቴሽን ስጧቸው። ደጋግመው በመቶ ሺዎች በተገኙበት እያሉ ይናገሩ" አለን።

እነሆ! የስምአን ልጅ በረከት ያዘዘንን አደረግን። አዲስዘመን መቶሺዎች በተገኙበት በድምቀት እንደተከበረ የጻፍንላትን ለህትመት አበቃች። የህትመት ዳሰሳ ቋሚ ተሰላፊ የሆነውና የደኢህዴን ካድሬው ሚዛን ከአሸበር ጋር ሆነው መቶሺህ ሲሉ ዋሉ።

ይህም ሆኖ በሚዲያና ማህበራዊ ድህረ ገጾች መብጠልጠሉ ግን እስከአሁንም አላባራም። ኢዜአና ዘርአይም ከታሪክ ሽሚያ አልተላቀቁም። የህውሀቱ ቁንጮ ዘርአይ ኢቲቪን ባለአዋቂ ሳሚነት እየጨመጨመ ነው።

***

ጊዜው ሚያዝያ 2001 ነበር፣

የሀይማኖት ጉዳዮችን የምንከታተል የፀጥታው ምክር ቤት አባላት አስቀድመን ካርታ ስራ ድርጅት ተገናኝተናል። የስብሰባውን አካሄድ ለመወሰን። ቀስ በቀስ የተንጣለለው አዳራሽ ከአፍ እስከ ገደፉ በኢህአዴግ ሚኒስትሮችና ከፍተኛ ካድሬዎች ጥቅጥቅ አለ። ከአንድ ሺህ በላይ ካድሬዎች ተገኙ።

የፊደራል ጉዳዮች ሚኒስትሩ ዶ/ር ሽፈራውና የትምህርት ምክትል ሚኒስትሩ ዶ/ር አድሀኖም መድረኩን እንዲይዙ ተደረገ። ሁለት ቀን ፕሮግራም የተያዘለት ስልጠና አጀንዳ በአዲስ ራእይ ላይ የወጣውና አንገብጋቢ በሆነው የሀይማኖት ጉዳይ ላይ ለመወያየት ነበር። ጽሁፉን ያዘጋጀው በረከት ስምኦን ነበር።

(አዲስ ራዕይ ከሁለት እስከ ሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ የምትዘጋጅ የኢህአደግ ነድፈ ሀሳብ ትንታኔ መጽሄት ናት። መጽሄቷ ቀለም ቀመስ ለሆኑ ካድሬዎች የምትዘጋጅ ሆና በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የድርጅቱን አቋም የምታሳይ ናት። አልፎ አልፎም ፓርቲው የመርህና አይዲኦሎጂ ለውጥ ሲያመጣ በግልጽም ባይሆን "የአስተሳሰብ እድገት መጥቷል" በሚል ይፉ ታደርጋለች። ለበርካታ አመታት "አብዮታዊ ዲሞክራሲ ሊብራል ዲሞክራሲ የሚደርስበት ጫፍ በማድረስ ግብአተ መሬት ይፈጽማል" የሚለውን የብሉ ኪዳን መልእክተ ዜናዊ በመቀየር "አብዮታዊ ዲሞክራሲ እንደ አንድ የዲሞክራሲ አማራጭ ለዘላለም ይኖራል" የሚለውን የአዲስ ኪዳን መልእክተ ዜናዊ ብስራት ያመጣችልን አዲስ ራዕይ መጽሄት ነበረች። ዘላለማዊነታችን በመረጋገጡ ያልተደሰተ አልነበረም!! በተለይ ሩቅ አሳቢ ካድሬዎች" ኢትዮጵያ ለዘላለሙ በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ውስጥ ትኖራለች!!" የሚል መፈክር ብጤ አሰምተው ነበር።)

የሀይማኖት አጀንዳ የኢህአዴግን አመራር የከፉፈለ በመሆኑ ወቅታዊ ሆኖ በአዲስ ራዕይ መጽሄት ላይ መቅረቡ የሚያጠያይቅ አልነበረም። ካድሬውና ባለስልጣናቱ በየሀይማኖቱ ተከፋፍሎ ጣቱን መቀሳሰር ጀምሯል። ድምፅ አልባው ተቃዉሞ ድርጅቱን አደጋ ውስጥ ከቶታል። ሀይማኖት በጐተተው መገታተር አብዮታዊ ዲሞክራሲና ካድሬው ዱባና ቅል መሆን ጀምረዋል። የአስተሳሰብ ልእልና እክል አጋጥሞታል። ይህን የተገነዘበው በረከት ስንዴውን

ከእንክርዳዱ የማይለይ ጽሁፍ አዘጋጀ። ይህ የሰላ ትግል ይካሄድበታል ተብሎ የተዘጋጀ ሰነድ ብዙ ነገሮችን ጐልጉሎ አወጣ።

የበረከት የመከነ ብእር ችግሩን ለሌላ በመስጠት የማላከክ ግብ ቢያስቀምጥም የእክራሪነት አስኳል ኢህአዴግ ውስጥ መሆኑን ሰብሰባው አረጋገጠ። ኢህአዴግ በሲኖዶስና መጅሊስ የሚደረገው እርባና ቢስ ምልልስ የእብድ ገላጋይ ስለሆነ ነው ተባለ። አክራሪነት እያቆጠቆጠ እና ስር እየሰደደ ያለው ቅጥ ካጣ ጣልቃገብነት፣ ሁሉን ለመቆጣጠር ከሚመነጭ አባዜ፣ ስልጣንን ለማቆየት ከሚካሄድ ሩጫና ሌብነትን ለመሸፈን ከሚካሄድ ዘመቻ መሆኑ መተማመን ላይ ተደረሰ። አንዳንድ ከፍተኛ ካድሬዎች ያቀረቧቸው አስተያየቶች መሬት የሚወድቁ አልነበረም።

የኢህአዴግ ቢሮ ሀላፊው ሙክታር ከድር እንዲህ በማለት ተናገረ፣ "... በኢህአዴግ ቢሮ ባለው ስታስቲክስ መሰረት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከሚማሩ ተማሪዎችና መምህራን ሰማንያ በመቶው የድርጅታችን አባላት ናቸው። በተለይም እንደ ባህርዳር ያሉ ዩንቨርስቲዎች እስከ ዘጠና በመቶ ይደርሳል። በተቃራኒው በሀይማኖት ጉዳዮች እየታመሱ ያሉት እነዚህ ተቋማት ናቸው። በተቋማቱ በተፈጠረ ሁከት ምክንያት መስታወትና ወንበር የሰባበሩ ተማሪዎች በቁጥጥር ስል ውለው ማጣራት ሲካሄድ ከሀምሳ ውስጥ አርባ ሁለቱ የእኛ አባላት ናቸው። እናም አክራሪነት ሌላ ቦታ ሳይሆን በውስጣችን የመሸገ መሆኑ የማይታበል ሀቅ ነው።"

በኢህአዴግ ቢሮ አህዴድን በመወከል የውጭ ግንኙነት ላይ የሚሰራ በንቲ የሚባል ካድሬ ቀጥሎ እድሉን ወሰደ። ይህ ካድሬ በደቡርነቱ የሚታወቅ ነበር። ከደህንነቶች ጋር በጥምር ስለሚሰራ የተፈፀሙ ሌብነቶች በቀላሉ ይደርሰዋል። በአንድ ወቅት ግርማ ብሩ የፈፀማቸውን ሌብነት በመረጃ አስደግፎ ለኢህአዴግ በማቅረብ የእስር ትእዛዝ ለማስቆረጥ ተንቀሳቅሶ በአቶ መለስ እምቢ ባይነት እንዲቋረጥ ተደርጓል። ግርማ ብሩ ቢሮ ድረስ በመሄድ "እየፈፀምክ ካለኸው ወንጀል ተቆጠብ" ብሎታል። የበንቲን ድርጊት የሰማነው በረከት ቢሮ ለስብሰባ ተቀምጠን ነበር። የስምኦን ልጅ ተንተክትኮ ከመሳቅ ውጭ የባሌም የበሌም አልተናገረም... አምባሳደር ግርማ አቶ መለስ አሊያም አባይ ፀሀዬ፣ ራቅ ካለም አዲሱ ለገሰ አይደለምና!!

በንቲ በአሮሚያ ያለውን ችግር እንዲህ በማለት አስረዳ፣

"እኔ የምናገረው በአህዴድ ካድሬዎች ዘንድ ውስጥ ለውስጥ የሚቀርበውን ሀሜት በአደባባይ አውጥተን እንድንነጋገርበት ፈልጌ ነው። በአህዴድ ካድሬዎች ዘንድ መጀመሪያ አካባቢ ወደ ስልጣን ለመምጣት

አርሴናል መሆን አለብህ የሚል ሀሜት ነበር። አርሴናል ማለት አርሲ ማለት ነው። ቀጥሎ ከአርሴናል ወደ MA ወደሚል ተቀየረ። MA ማለት ሙስሊም አርሲ ማለት ነው። ይህም ሆን ተብሎ የእስልምና ተከታዮች የሆኑ ካድሬዎችን ወደ ስልጣን ለማምጣት የተካሄደ ሩጫ እንደሆነ እየተነገረ ይገኛል። ነዋሪው አርቶዶክስና ፕሮቴስታንት የሚበዛበት ሳይቀር ካድሬዎቹ ሙስሊሞች ናቸው። ህዝቡ ይህን በማየት ምስለኔ ብሎ ይጠራቸዋል። የቢሮክራሲው ቅጥር ላይ አንዳንድ ዞኖች ስም በማየት ብቻ ቅጥር መከናወኑን እነ አባዱላ ያውቃሉ። ጀማል አሊያም መሀመድ ከሆነ ስምህ ትቀጠራለህ። በተቃራኒው ሚካኤል ወይም እስጢፋኖስ ከሆነክ አትቀጠርም። በጅማ የተቃጠሉት ቤተክርስትያኖች ላይ የአህዴድ ባለስልጣናት አለበት የተባለበት ምክንያት ለዚህ ነው..."

በመቀጠል በኢህአዴግ ቢሮ ካድሬ ለነበረው ተፈሪ ተሰጠው። ተፈሪ የአዋሳ ከንቲባ ነበር። በታማኝነቱ ምክንያት በተዝረከረከ ብጥስጣሽ ወረቀት በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ የሚያንቀሳቅሰው ኢህአዴግ ፉይናንስ ሀላፊ ተደረገ። ይህን ታማኝነት ጠብቆ በመቆየቱ የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ስራ አስኪያጅ ሆነ። ታማኝነቱን አጎደለ መሰል ወደ ማይቀረው ከርቸሌ ተወረወረ። እስከማውቀው ድረስ ተፈሪ ፕሮፌሽናል፣ ጨዋና ግልጽ ካድሬ ነበር። ወደ ኪራይ ቤቶች ተመድቦ ሲሄድ ደስተኛ አልነበረም። መንግስታዊ አሰራር የማያውቀው ኪራይ ቤቶች እነ በረከትን፣ አባዱላንና አርከበን ያፋጠጠ ተቋም ነበር። በአንድ ወቅት አቶ መለስ የአውራ ዶሮ ጨዋታ መጫወት ፈልጎ የኪራይ ቤቶችን ተጠሪነት ለአርከበ፣ የቦርድ ሰብሳቢውን ለአባዱላ፣ ቤት አከፋፋዩን ደግሞ ኢህአዴግ ጽ/ቤት (በረከት) አድርጎ ነበር። ይህን ተከትሎ ነበር በረከት ታማኙን ተፈሪ ከኢህአዴግ ፉይናንስ ወደ ኪራይ ቤቶች የሰደደው። የስምአን ልጅ በአቶ መለስ፣ አባይ ፀሀዬና አዲሱ ለገሰ ላይ ካልመጡበት በስተቀር የአህያ ባል ነው። ለዚህም ይመስላል ተፈሪን ከጅቡ ማስጣል የተሳነው።

ተፈሪ እንዲህ በማለት ንግግሩን ጀመረ፣

"የሀይማኖት አስተማሪዎች በድርጅታችን ውስጥ አባል መሆን ቢችሉም አመራር ደረጃ መምጣት እንደሌለባቸው መመሪያው ይደነግጋል። ፓርላማ የሀገሪቱና የድርጅቱ ከፍተኛ አመራር የሚስጥበት ቦታ ነው። ነገር ግን የፓርላማ አባሎቻችን ውስጥ ጥምጣምና ኮፍያ አውልቀው የተቀላቀሉ ብዙ ናቸው። ሩቅ መሄድ ሳያስፈልግ ከአዲሳባ ጉለሌን ወክለው ፓርላማ የገቡት ሰባኪ ቄስ ናቸው። የመዲናይቱ ምክትል አፈ ጉባኤ ሼህ ኤልያስ የአዲሳባ እስልምና ጽ/ቤት አመራር ነው።"

ተፈሪ ቀጠለ፣

"የደቡብ ቁልፍ ካድሬ ለመሆን ቅድመ ሁኔታው የፕሮቴስታንት አማኝ

ተከታይ መሆን ይጠይቃል። የካቢኔ ስብሰባ በፀሎት የተጀመረበት ወቅት አስታውሳለሁ። ደቡብ ክልል ሚሊኒየሙ በጋራ ደስታ እንዳይከበር ልዩነት የፈጠረው ሽፈራው ሽጉጤ አይደለም? ሽፈራው የዋዜማው እለት ምንድነው ያደረገው? የእንኳን አደረሳችሁ መግለጫ ሲያነብ ጌታ እየሱስ ይመስገን ብሎ ተናግሯል። በዚህ ምክንያት ህዝበ ሙስሊም ቅር መሰኘቱ በሰፊው ታይቷል። ሚሊኒየሙ የሙስሊሙ አይደለም ወይ የሚል ሰፊ ጥያቄ አስነስቷል።"

ስለ ትምህርት ተነስቶ በነበረው ላይ ደግሞ እንደ ማፌዝ ባለ ድምፀት፣

"ትምህርት ሴኩላር ነው እንላለን። እኛ ጋር ሲደርስ ግን አይሰራም። የኢህአዴግ ፓሊት ቢሮ አባላት ኃይለማርያም፣ ኩማ፣ ሬድዋን፣ ሽፈራው ሽጉጤ፣ አስቴር ማሞ፣ ካሳ ሸሪፎ፣ ደመቀ፣ ገዱ፣ ሙክታር፣ አብድላዚዝ፣ ጁኒዲን፣ ደግፌ ቡላ... ደቡብ፣ አማራና አዲሳባ ከፍተኛ ካድሬዎች የተማራችሁት ማስተርስ የክርስቲያን ሊደርሺፕ ነው። አስተማሪዮቻችሁ ሰባኪ ፓስተሮች ነበሩ። ከኬንያ መጥቶ ስለ ግጭት አፈታት ያስተማራችሁ ፓስተር ያኪሩ የራሱ ቤተክርስቲያን አለው። በቀን አራት ጊዜ አይናችሁን እያስጨፈነ ይፀልይላችሁ ነበር። የወሰዳችሁት እያንዳንዱ ኮርስ የመጨረሻ ግብ ክርስቲያናዊ ባህሪ መላበስ ይላል። አነዚህን ባህሪያት ወደ ተቋማችሁ እንድትተገብሩ ግፊት ተደርጓል። በየተርሙ የምትሰሩት ጥናት ያንን መሰረት ያደረገ ነው። አንድ ጊዜ ስሙን መጥራት የማልፈልገው የአስልምና እምነት ተከታይ ሚኒስትር እየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረ ሰአት ሰርቫንት ሆኖ የሰራቸውን ተግባራት በሶስት ገጽ ጻፍልኝ ብሎ ጽፌለታለሁ። በጣም ስለከነከነኝ ለምን እንደሆነ ጠየኩት። ሰርቫንት ሊደርሽፕ ለሚባለው ኮርስ ተርም ፔፐር እንደሆነ ገለፀልኝ።" ቤቱ በሳቅ ተሞላ። አስከትሎ ሞቅ ያለ ጭብጨባ።

"... አፍረጥርጠን መነጋገር ይኖርብናል። እነዚህ የክርስቲያን ተቋማት አምነታቸውን ለማስፋፋት የቀየሱት ስትራቴጂ አመራሩን አስቀድሞ በመረብ ውስጥ ማስገባት የሚል እንደሆነ ታውቃላችሁ። እንደ ድሮው ስኳርና ሳሙና ይዘ መምጣት እንደማያዋጣ ገብቷቸዋል። ሌሎቻችሁ ይሁን እነ ሬድዋን፣ ሙክታር፣ ደመቀ፣ አብድላዚዝ፣ ጁኒዲን የክርስቲያን ስብእና የተላበሳችሁ መሪዎች ስትባሉ ምን ተሰማችሁ? የጁኒዲን ይባስ! በኢቲቪ ዜና ላይ ቀርቦ ክርስቲያናዊ ምስክርነት ሰጠ። አፍረጥርጠን መነጋገር ይኖርብናል! ነገ ከኢራን አሊያም ፓኪስታን የሚገኝ አስላማዊ ግብ ያለው ዩንቨርስቲ ቢመጣ የመንግስት ባለስልጣናትን ያውም በመንግስት በጀት እንዲያስተምር ይፈቀድለታል?፣ የኢህአዴግ ጽ/ቤት ሀላፊው ሙክታር ለዚህ መልስ እንድትሰጠኝ እፈልጋለሁ።

ለተፈሪ ከድርጅቱ ባህል ባፈነገጠ ሁኔታ ተጨበጨበለት።

በማስከተል ሚሊዮን አሰፉ (የቴዲ አፍሮ ጠበቃ) እንዲህ በማለት

አስተያየት ሰጠ፣

"በሀይማኖት ተቋማት መካከል ያለው አንዱ ችግር ከተማዋን በድምፅ መረበሽ ነው። በዚህ ዙሪያ ተቋማቱ እርስ በራሰ ፉክክር የገቡ ይመስል በአራቱም ማእዘን ትላልቅ ስፒከሮችን በመክፈት ከሚገባው በላይ ያጮህሉ። አንድ ሰው የማይፈልገውን ድምፅ መስማት አይገደድም። ከእንቅልፉ መቀስቀስ የለበትም። ይህ የኃላ ቀርነት ምልክት ነው..."

"... በአንድ ወቅት በኮልፌ ቀራንዮ በሚገኝ አካባቢ ህዝቡ ተሰባስቦ በመሄድ ከአንድ አዲስ የተቋቋመ የሀይማኖት ተቋም ውስጥ ምልክትና ድምፅ ማጉያ ነቅለዋል። ድርጊቱ ህገ ወጥ ቢሆንም የሚያስተምረን ነገር አለ። ለኮንደሚኒየም ቤቶች ቡና መውቀጥ፣ ጠላ መጥመቅ፣ የሬዲዮ ድምፅ ምናምን እያልን መመሪያ አውጥተናል። በሀይማኖት ተቋማት ላይም የድምፅ ብክለት ህግ ማውጣት ይኖርብናል። ይህ አዲስ ነገር አይደለም። ብዙ ሀገሮች እንደዚህ አይነት ህግ አላቸው። በአሜሪካን ሀገር የሚገኙ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ማይክራፎን ውጪ መትከል አይችሉም። በኢትዮጵያም የማይደረግበት ምክንያት የለም።"

የመጨረሻው ተናጋሪ ዶክተር ሽፈራው ነበር። ዶክተሩ እንዲህ በማለት ንግግሩን ጀመረ፣

"... በሀይማኖት ሽፋን የሚደረጉ ወንጀሎችን ለመከላከል የሚያስችል አዲስ የሀይማኖት ህግ እያዘጋጀን ነው። ይዘቱ ከመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅት አዋጁ ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም ጫጫታ እንዳይፈጠር በመመሪያ ደረጃ እንዲታጠር አድርገነዋል። ለጊዜው "የሀይማኖት ድርጅቶችንና ማህበራት ለመመዝገብና ተዛማች አገልግሎቶችን ለመስጠት..." የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል። ይህ ጥብቅ ቁጥጥርን መሰረት ያደረገ መመሪያ የሀይማኖት ተቋማቱ በእግራችን ስር እንዲወድቁ ያደርጋል። ከእንግዲህ እኛ ሳንሆን እነሱ ወደ እኛ መጥተው ይለማመጡናል። መመሪያው ለፌደራል ጉዳዮች ከፍተኛ ስልጣን ይሰጣል። ለምሳሌ ሀይማኖት ድርጅቶቹ የሚያቀርቡትን ደንብ እንዲያሻሽሉ አስተያየት እስከ መስጠት ይዘልቃል። አስተያየቱን መቀበል ካልቻሉ የመመዝገብ እድል ላይኖራቸው ይችላል። መመሪያው ማንኛውም ቡድን ሆነ ግለሰብ ህጋዊ የምዝገባ ፍቃድ ሳያገኝ ህዝበን መጥራት፣ በአደባባይ መስበክ ፣ ሀይማኖትን ሽፋን ያደረገ የፓለቲካ አጀንዳ ማራመድ በህግ የሚያስጠይቅበት ሁኔታ ይፈጥራል። በህግ ከተፈቀደ ማምለኪያ ቦታ ውጭ ለሚካሄድ ስብከት ከመንግስት አካላት ፍቃድ ሳይገኝ ማከናወን አይቻልም ..."

ዶክተር ትንፉሽ ወስዶ ቀጠለ፣

"...መመሪያው በተግባር ላይ ሲውል የሀይማኖት ሰባኪ ነን ባዮች በወፍ

ዘራሽ የሚመጡ ሳይሆን በሀይማኖት ድርጅቶቹ እውቅና የተሰጣቸው ብቻ ይሆናሉ። አርቶዶክስ ነኝ ያለ ሰባኪ ያለ ሲኖዶሱ አሊያም ሲኖዶሱ በሚያዋቅረው አደረጃጀት ውስጥ ካልታቀፈ መስበክ አይችልም። የእስልምናውም ፕሮቴስታንቱም ተመሳሳይ ነው። በየጉራንጉሩ የሚካሄዱ ፖለቲካ አዘል ስብከቶች ድምጥማጣቸው ይጠፉል።"

"... መመሪያውን ለመፈፀም የሚያስችል ክፍል በፌደራል ጉዳዮች ተቋም ይደራጃል። ጠንካራ ካድሬ በምክትል ሚኒስትር ማእረግ ይመደባል። ሁኔታዎች በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ቁጥጥር ስር እስኪውሉ ድረስ የተቋሙ ቁልፍ ስራ ይህ እንዲሆን ድርጅቱ ወስኗል። እመኑኝ! ይህን መመሪያ መተግበር ስንጀመር እንደ ፊኛ የተነፉው ሲኖዶስ ተንፍሶ በእግራችን ስር ይወድቃል። ሲኖዶሱ በተቃዋሚዎች የሚናጥ በመሆኑ በሂደት እንደ መሸሸጊያ እኛን መጠቀሙ አይቀርም። ከመጅሊሱ ጋር ተመሳሳይ ይሆናል። እደግመዋለሁ! እኛ ሳንሆን እነሱ ወደ እኛ በመምጣት ደጅ መጥናት ይጀምራሉ።"

በዚህ መልኩ ለሁለት ቀናት የተካሄደው ስልጠና ዋናው ችግር ውስጣችን እንደሆነ መተማመን ላይ ተደረሰ። የአክራሪነት አስኳል ኢህአዴግ ውስጥ መኖሩ ተረጋገጠ። ኢህአዴግ የሚመራው መንግስት ህገ መንግስቱን እየጣሰ እንደሆነ ተገለፀ። የአቶ መለስ የቁጥጥር አባዜና "የአሳ ግማቱ ከጭንቅላቱ" ተረት ተረት መደምደሚያ ሆነ። ይህን ተከትሎ ኢህአዴግ ራሱን ማጥራት እንዳለበት ስምምነት ተደረሰ።

የውህ ቅዳ ውህ መልስ መህንዲሶቹ እነ አባዱላ እንደተለመደው ከአምስት ሺህ በላይ የአህዴድ ካድሬዎችን ጠራርገው አባረሩ። ለተባራሪዎቹ "የአመለካከት ጥራት መጓደል" የሚል ታርጋ ተለጠፈባቸው። የአባዱላ የበቀል ጅራፍ በሚኒስትር ጁነዲን ሳዶ ላይ እርምጃ በመውሰድ ወደ ሌላኛው ምእራፍ ተሸጋገረ።

***

አንድ ምሽት ከአሊሴሮ ጋር...

በሀገሪቱ የምንገኝ ቁልፍ የኢህአዴግ ካድሬዎች ለሁለት ወር አዳማ ከትመናል። ምክንያቱ ደግሞ አቶ መለስ የጻፈው የልማታዊ መንግስት ፅንሰ ሀሳብ ላይ ስልጠና ለመውሰድ ነበር። ይህንን ስልጠና ያልወሰደ በከፍተኛ የአመራር ደረጃ መቀመጥ አይችልም በመባሉ የቀረ ካድሬ አልነበረም። በህመም ምክንያት ውጭ ሀገር በመሄዱ ያልተሳተፈው አርከበ እቁባይ ብቻ ነበር።

ስልጠናው አቶ መለስና በረከት በሚሰጡት ገለጻ ይጀመራል። በየምእራፉ በመከፋፈል መነሻ ሀሳቦች ያቀርባሉ። በማስከተል ለተራዘመ ቀናት በቡድን በመከፋፈል ክርክር ይካሄዳል። በመጨረሻ አቶ መለስ ለማጠቃለያው ተመልሶ ይመጣል።

እኔ በነበርኩበት ክፍል የቡድን መሪዋ ወይዘሮ አዜብ መስፍን ነበረች። የቡድኑ አባላት ከሁሉም ብሔር ድርጅቶችና አጋር ፓርቲ ካድሬዎች እንዲሰባጠር የተደረገበት ነበር። የአፋር እና ጋምቤላ ፕሬዝዳንቶች እኛ ቡድን ነበሩ።

የአዜብ ንግግር እጅግ የወረደና እንጨት እንጨት የሚል ነበር። እርባና የሌለው ነገር እያነሳች ቀኑን ሙሉ እንደ ክላሽ ትንተከተካለች። አንዳንድ ግዜም ሁሉን ታውቃለች እንድትባል አስደንጋጭ ሚስጥሮችን ትዘከዝካለች። የምትናገራቸው ሚስጥሮች በህገሪቱ የሚናፈሱ ወሬና ግምቶችን አውነትነት ያፀና ነበር።

በኢትዮ-ኤርትራና ኢትዮ-ሱማሊያ ጦርነት ከ120ሺህ በላይ የሀገራችን ወጣቶች ማለቃቸውን በይፋ የሰማነው ከእሷ አንደበት ነበር። በዶረና ግንባር በተካሄደው ጦርነት፣ በአሰብ በረሀ ውሀ ጥማት የረገፈው ወታደርና የደረሰው እልቂት ስታብራራ የብዙዎቻችን አይን ላይ እንባ አቅሮ ነበር። ተጠያቂነቱን ደግሞ እንደ ባሏ ሁሉ ወደ እነ ስዬ አብርሀ ወርውራለች። ጦርነቱን መለስ ቢመራው ኖሮ ይህን ያህል ኪሳራ አይደርስም ነበር በማለት በቁጭት ተናዛለች። ባሌ ለረጅም አመታት አቁሞት የነበረውን ሲጃራ አስጨሱት፣ በሽተኛም አደረጉብኝ የሚል ክስ አቅርባለች። በባሏ ህመም ላይ እሷ ሌባ ጣቷን ወደ እነ ስዬ ትጠቁማለች፣ እነ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደግሞ ወደ እሷ አቅጣጫ የታጠፉ ሶስት ጣቶቿን ያመላክታሉ።

አዜብ በምርጫ 97 ባለቤቷ የወሰደው እርምጃ ህገ መንግስቱን ያልተከተለ ቢሆንም ኢህአደግን መታደጉን በኩራት ነግራናለች። ከአዲሳባ ህዝብ የተነጠቁት ተቋማት ተገቢ ባይሆንም ከበጣም መጥፎ፣ መጥፎ ይሻላል በሚል እሳቤ የተደረገ መሆኑን አስረድታለች።

አዜብ ካድሬዎችን ለመዘርጠጥ ህጋዊ ስልጣን የተሰጣት ይመስል እያንዳንዱን እየጠራች አፈር ከድሜ አስግጣለች። አንዳንዶቹን ሚኒስትሮች ዘራቸውን እየጠራች "የብሄር ታፔላ ያጠለቁ የተዋጽኦ ሚኒስትሮች" በማለት አዋርዳለች። በሌብነትም ከሳለች። "የእያንዳንድሽ የሙስና ፉይል እጃችን ይገኛል" በማለት አስፈራርታለች።

እመቤታችን የምትናገረውን እንደ በቀቀን እየተቀበሉ ከሚያስተጋቡት መካከል የአፉሩ ፕሬዝዳንት እስማኤል አሊሴሮ፣ ያረጋል አይሸሹምና ዘመን ተሻጋሪው ታጋይ ይሳቅ ቆሪጥ በቅድሚያ የሚጠቀሱ ናቸው።

አሊሴሮ ንግግሩን ሲያጠቃልል፣

"አማራ በሀይል ገዝቶን ነበር። አማራ ሙስና አስተማረን..." የሚሉ እድሜ ጠገብ ታሪኮች ይናገራል። ለአሊሴሮ አማራ ማለት የደጋና መሀል አገር ሰው ባጠቃላይ ነው...፣ ወላይታው፣ ጉራጌው፣ አሮሞው፣ አማራው፣ ክርስትያኑ በሙሉ አማራ ነው። ለነገሩ ፕሬዝዳንት መንግስቱ ኃይለማርያም የቴድሮስን ሽጉጥ ሊጠጣ በተቃረበ የመጨረሻው ሰአት የአፉር ጐሳ መሪዎች የሰጡትን ሻሞላ እያሳየ አማራ ማለት በተራራ ላይ የሚኖር ህዝብ ማለት እንደሆነ ሌክቸር ሰጥቶን አልነበር? በቆራጡ መሪያችን ስሌት ከተሄደ ደግሞ ተራራ ላይ የሚኖር አፉር፣ ዙምባብዌ፣ አፍጋኒስታን አማራ ይሆናል። ይሄ አማራ ፈረደበት!!

አሊሴሮ ደፉርና ግልጽ ሰው ነው። አለማወቅ ደፉር ያደርጋል። በተለይ ለቡድን መወያያ እንዲሆን የተሰጠች ጥያቄ ላይ ያቀረበው ማብራሪያ ደፉርነቱን የሚያሳይ ነበር። ለዚህ ጽሁፍም መነሻ የሆነው ይህ ማብራሪያ ነበር።

እንዲህ ነበር የሆነው።

ከኢህአዴግ ስልጠና ማእከል ለሁሉም ቡድኖች ከተበተኑት ጥያቄዎች አንዱ አንዲህ የሚል ነበር፣

"በክልላችሁ ካሉ ቢሮዎች ውስጥ በእቅድ የሚመራ፣ ባስቀመጠው ጊዜ የሚፈጽም፣ በጀቱን በአግባቡ የሚጠቀም፣ የሙስና ችግር የሌለበት፣ ተገልጋዩና ማህበረሰቡ ደስተኛ የሆነበት ተቋም በመለየት ውይይት አድርጉበት" ይላል።

ወይዘሮ አዜብ መጀመሪያ ተቋማቱን የመምረጥ ስራ ተከናውኖ ውይይቱ በንጋታው እንደሚጀመር አሳሰበች። ኢምግሬሽን ጽ/ቤት፣ ከአዲሳባ ወደ ፌደራል አቶ መለስ ቀምቶ የወሰደው ውልና ማስረጃ፣ የትግራይ ትምህርት ቢሮ፣ የደቡብ ኢንቨስትመንት ቢሮ ወረፉ አስያዙ። የአሊሴሮ እጅ ተራ ለማስያዝ ተቀሰረ። ተሰጠው፣

"በአፉር ክልላዊ መንግስት ከላይ የተጠቀሰውን ፀባይ የሚያሞላው የጨረቃ ምርምር ቢሮ ብቻ ነው።" በማለት ለጨረቃ ምርምር ቢሮ ወረፉ አስያዘ።

ግራ ገባኝ። በፌደራል ደረጃ የሌለ የጨረቃ ምርምር ቢሮ ወደ ኋላ የቀሩ ክልሎች በሚባለው አፉር ውስጥ በተቋም ደረጃ መቋቋሙ የሚገርም

ነበር። ከምድር በታች ኢትዮጵያን ያስጠሩት የእነ ድንቅነሽ (ሉሲ)፣ የአርታሌ እሳተ ገሞራ አገር በጨረቃ ምርምር ላይም የተሻለ ስራ በጊዜና በሰአቱ ሰራ ሲባል ልብ የሚያቆም ነበር። የዋልዋ ልጅ ይሄን ቢሰማ ኖሮ ለሆቢው ያቋቋመው የጠፈር ምርምር ተቋም ልምድ እንዲወስድ አፋር ይልከው ነበር።

በእራት ሰአት አሊሴሮ ፈልጌ ጐኑ ተቀመጥኩ። እንዲህ በማለት ጠየኩት፣

"ፕሬዝዳንት አሊሴሮ ስልጠናውን እንዴት እያየህ ነው?"

"በጣም ጥሩ ነው። ዲፕሎማው እስኪሰጠን ቸኩያለሁ። ቢሮዬ አናት ላይ ስቅዬ ጠላቶቼን አፍ አዘጋለሁ። አልተማረም ምናምን እያሉ ለአባይ ፀሀዬና ለመለስ ዜናዊ የሚያቃጥሩ አሉ።"

"ጥሩ ሀሳብ ነው አሊሴሮ።"

"እኔ የምለው እናንተ አማሮች እንደአርታሌ መንተክተክ የምታቆሙት መቼ ነው። አንተም ሲያዪህ ልጅ ብትመስልም ሚጥሚጣ እንደላሰ ሰው ትንጣጣለህ። ደግሞ ሴትየዋ ማቆሚያ የላትም እንዴ? እሷም ባሏም እሳት ከሆኑ ልጆቻቸው ምን ሊሆኑ ነው?"

"አዜብን ማለትህ ነው? " እየሳቅኩ ጠየኩት።

"ታዲያ ሌላ ማንነው? የምትናገረው በጣም ጥሩ ነው። ባልና ሚስት በአንድ ወንዝ ይወርዳሉ። እውነቴን ነው የምልህ መሬት አይወድቅም። ስብሰባው ጥሩ ሆኖ ሳለ አንዳንድ ደስ ያላሉኝ ነገሮች አሉ።"

"በስልጠናው አንስተህ እንዲስተካከል ማድረግ ትችላለህ አሊሴሮ!"

"በስብሰባ የሚነገር ቢሆንማ ምን ችግር ነበረበት። እናንተ አማሮች የሚስቶቻችሁን አለባበስ እንዲቀይሩ መቆጣት አለባችሁ። እውነቴን ነው የምልህ ሀጢያት ነው! አላህ አይወደውም!።"

ንግግሩን አቋርጦ በጥርጣሬ ተመለከተኝ። ወደ ጆሮዬ ጠጋ ብሎ፣

"ባሷ ግን ራቁቷን ስትሄድ ለምን አይቆጣትም። ንግስት እመቤት፣ ቀዳሚ እመቤት እያላችኋት እንዴት የውስጥ ሱሪዋ ይታያል? ወላሂ ነው የምልህ በማደሪያ ክፍላችን ወሬው ይህ ብቻ ሆኗል። ቅድም የአፋር የድርጅት ጉዳይ ሀላፊው መሀመድ ከሌላ ቡድን መጥቶ የሄደው ለምን ይመስልሀል? ማታ ተወራርደን ሊያረጋግጥ ነበር የመጣው።" ሳቄን ማቆም አልቻልኩም።

"ምንድነው የሚያስቅህ? ወንድ ልጅ እኮ ነን!"

እንባዬ ፈሰሰ። ለደቂቃዎች መናገር አልቻልኩም። ለጠየቀኝ መልስ ሳልሰጠው ወደ ሌላ ጥያቄ ተሻገርኩ፣

"አሊሴሮ! ሳምንቱን ሙሉ ስለ ዳጉ ያስረዳኸን ተመችቶኛል። በሌሎች አካባቢ ቢስፉፉ ጥሩ ይመስለኛል" አልኩት።

"እናንተ አማሮች እኛን እንዳልሰለጠነ ትቆጥሩናላችሁ። አፋር የሰው ልጅ ብቻ ሳይሆን የግንኙነት (የኮሙዩኒኬሽን) መሰረት ናት። ዳጉ የሚባለው

ስርአት የአፋር ብሔረሰብ ከጥንት ጀምሮ የሚጠቀምበት የመረጃ ልውውጥ ባህል ነው። አንድ አፋር በመንገዱ ላይ ሌላ አፋር ካገኘ መረጃ ሳይለዋወጡ አይተላለፉም። የግጦሽ መሬት ፣ውሀ በምን ያህል ርቀት እንደሚገኝ...ሽፍታ ያለበት አካባቢ....የጎሳ መሪዎችና መንግስት ያስተላለፈውን መልእክት ተለዋውጠው ይተላለፉሉ። "አለኝ።

መልስ ሳልሰጠው ትንሽ ቆየሁና በልቤ የያዝኩትን ጠየኩት፣

"የአፋር ብሔረሰብ እጅግ በጣም ብዙ ያልተጠኑ ገጾች አሉት። አርአያ እንደሆነ የገለጽከው የጨረቃ ምርምር ቢሮ ራሱ በሚዲያ ቀርቦ ሌላው ትምህርት ሊወስድበት ይገባል። እንዴት አዋቀራችሁት? ዋና ስራው ምንድነው?"

አሊሴሮ ኮራ ብሎ፣

"የጨረቃ ምርምር ቢሮ የካቢኔ አባል ነው። ከክልሉ ከፍተኛ በጀት ከሚመደብላቸው ተቋማት አንዱ ነው። ትልቁ ስራው የአፋር ህዝብ እስልምና ሀይማኖቱን ጠብቆ እንዲኖርና ለስርአቱ ተገዥ እንዲሆን ማስተማር ነው። መስኪዶች እንዲገነቡ ድጋፍ ያደርጋል። የካቢኔ አባላትን፣ ተማሪዎችን፣ ዳዋ የሚወጡ ወጣቶችን ያሰለጥናል። ረመዳንን የመሳሰሉ ትላልቅ በአላት የሚከበሩበትን ቀን ለህዝቡ ያሳውቃል፣ ድግስ በማዘጋጀት ህዝበ ሙስሊሙን ያበላል። ሀይማኖቱ ከሚያዘው ውጭ የሄደ ካለ እርምጃ እንዲወሰድበት ድጋፍ ያደርጋል። በአጠቃላይ መልኩ የክልሉ አስተዳደር የእስልምና ሀይማኖት በሚያዘው መሰረት እንዲመራ የሚያደርገው ይህ ቢሮ ነው።" ለሰጠኝ ማብራሪያ አመሰግኘ ተሰናበትኩት።

በንጋታው በተካሄደ የቡድን ውይይት ህገ መንግስቱን በኬሻ የጠቀለለው የአሊሴሮ "የጨረቃ ምርምር ቢሮ" ተሞክሮውን አቀረበ።

ወይዘሮ አዜብ የኢሴሮን ተሞክሮ አዳንቃ አንጨብጭቡ አለች። አንጨበጨብን። አሊሴሮ እንደ ቅሪላ ተነፉ። አለማወቅ ደፋር ያደርጋል። አሊሴሮ፣ ወይዘሮ አዜብ፣ የገመዳ፣ የሸጉጤ፣ የጐበዜ ልጆች፣ አለቃ ፀጋዬ፣ እኔ፣ ኢህአዴግ ...ደፋሮች ነን።

(ከስልጠናው መጠናቀቅ በኃላ በኢህአዴግ ቢሮ ለበረከት ነገርነው። መጀመሪያ ከት ከት ብሎ ሳቀ። ትንሽ ቆይቶ ደነገጠ። በሳምንት ውስጥ ቆመን ያንጨበጨብንለት የጨረቃ ምርምር ቢሮ በሚስጥር ፈረሰ። እስከ ፈረሰበት ቀን ድረስ ለፈፀመው ኢ - ህገመንግስታዊ ተግባር ግን የተጠየቀ የለም።)

***

ክፍል ሰምንት: የጎብልስ ትእዛዛት ማጠንጠኛ - "The Big Lie Theory"

" Make the lie big,make it simple,keep saying it, and eventually they will believe it "

Joseph Goebbeles

ምእራፍ ሃያ ሰባት

ያልሞተው እሰሰት

"ለምን እንደሆነ ባይገባኝም መለስ ስለትላልቅ ፕሮጀክቶች መስማት አይፈልግም። ዛር እንደያዘው ሰው ያንቀጠቅጠዋል።"
አምባሳደር አሊ አብዶ

ሸራተን አዲስ ...

የካቲት 2001፣

የጨለማው ዘመን ነጉስ ከነበረው አሊ አብዶ ጋር በሸራተን አዲስ አራት እየበላን ነው። የተገናኘነው ከስምንት አመታት በኃላ ነበር። እሱ የሱዳን አምባሳደር ሆኗል፣ እኔ ደግሞ የበረከት ስምኦን ምክትል። ያገናኘን ምክንያት የኢትዮ-ሱዳን የጋራ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ኢትዮጵያን ወክዬ በሚዲያና ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ላይ እንድደራደር በመወከሌ ነበር።

አሊ ቀኑን ሙሉ በነበረው ድርድር አንገቱን አቀርቅሮ ዋለ። በሙሉ አይኑ ሊያየኝም አቅም አነሰው። ሌላው ቀርቶ በስብሰባው ወቅት በሚኖረው የሻይ ሰአት ደጋግሞ ሲሸሸኝ ተመለከትኩ። በየጊዜው የወረወረብኝ ጦሮች ያደረሱትን ጉዳት እንዳልረሳው ያስታውቃል። የወጋም አይረሳም! እኔም ብሆን ለእሱ ያለኝን የወረደ አመለካከት አመታት አልፈውም መቅረፍ አልቻልኩም። በተለይ በአዲሳአባ ህዝብ ላይ የፈፀማቸው ወንጀሎች የህሊናዬ ግርግዳ ላይ ተለጥፈው ቀርተዋል።

በዚህ ስሜት ውስጥ እያለን ነበር ለፕሮቶኮል የተዘጋጀ የእራት ጠረጴዛ ያገናኘን። አጠገባችን ተቀምጠው የነበሩትን በኢትዮጵያ የሱዳን አምባሳደር ጥቂት ካወራናቸው በኃላ እኔና አሊ ተፋጠጥን።

ከረጅም ዝምታ በኃላ ስሜን እየጠራ እንዲህ ሲል ተናገረ፣

"ይገርምሀል እንደዚህ አይነት አጋጣሚ ይፈጠራል ብዬ አስቤ አላውቅም። በአንዳንድ ነገሮች ቅር እንደተሰኘህብኝ አውቃለሁ። ርግጥ ስህተቶች ነበሩ። የሚቆጩ ናቸው። እዚህ ደረጃ ደርሰህ ሳይ ደግሞ እጽናናለሁ። ከሁሉም በላይ ግን በወቅቱ አብረውኝ የነበሩት ሰዎች የማያሰሩ እንደሆነ

ታውቃለህ?"

በመገረም እያጤንኩት፣

"እውነቱን ንገረኝ ካልክ በህይወቴ ካዘንኩባቸው ሰዎች አንዱ አንተ ነህ። እስከዛሬም በተለያየ ጊዜ እየተከታተልክ ለምን እንዳጠቃኸኝ አይገባኝም? በተለይ የከለከልከኝ የውጭ ሀገር የትምህርት እድል ልረሳው አልቻልኩም።" አልኩት።

ዘመን ተገልብጧል...

ትላንትና አበሻቅጠ፣ "ቀስ ብለህ እደግ!" በማለት ከቢሮው አስወጥቶኛል። ተወዳድሬ ያገኘሁትን የውጭ ሀገር የትምህርት እድል ለሌላ አሳልፎ ሰጥቷል። ከትልቅ ስብሰባ ውሰጥ አንተን አይመለከትም ብሎ አባሮኛል። ሶስት ቀንና ለሊት መስኪድ አሳድሮኛል። በአርከበ ዘመን ምደባ ሲካሄድ የአመለካከት ችግር አለበት፣ ኦሮሞን አይወክልም፣ አህዴድ እውቅና አልሰጠውም በማለት ከምደባ ውጭ አድርጎኝ ነበር። ዛሬ ደግሞ እኔ የኢትዮጵያ መንግስትን ወክዬ እደራደራለሁ። እሱ ደግሞ ድግሱ እንዳማረላት ሴት ወረቀት ያመላልሳል። ከኃላዬ ቆሞ የምፈርመውን ሰነድ እየገለበጠ ይሰጠኛል።

ግንባሩን አየፈተገ፣

"እንድታውቅ የምፈልገው ግን የኔዘርላንዱን የትምህርት አድል ከአንተ ነጥቆ ለሙለሜ ረሺድ እንዲሰጥ ያደረጉት ሌሎች ሰዎች ናቸው።"

"እነማን?" በጥርጣሬ ተመለከትኩት።

"ጉዳዩ ከእኔና ከአንተ አይለፍ እንጂ ካሊድ፣የመከላከያ ሚኒስትሩ ሲራጅ ፈርጌሳና የስልጤ ዞን አስተዳዳሪው ናቸው።"

"ለምን? ከካሊድ ውጭ ሌሎቹ አያውቁኝ፣ አላውቃቸው?"

"ታስታውስ እንደሆነ በዛን ሰሞን የአንተን እድል የወሰደችው ወይዘሮ ሙለሜ ረሺድ የደኢህዴን ማእከላዊ ኮሚቴ ተመርጣ ነበር። የስልጤ ፓሊት ቢሮም ሆና ነበር። እናም የማእከላዊ ኮሚቴ የተመረጠ ሰው እያለ ከዛ በታች ያለ ካድሬ መሄድ አይችልም ብለው ተከራከሩ "

በከፊል አመንኩት። ሴትየዋ በእያንዳንዱ ንግግሯ የደኢህዴን ማእከላዊ ኮሚቴ እና የስልጤ ፓሊት ቢሮ መሆኗን ለማሳየት ትጥር ነበር። በተለይ ሲራጅ ፈርጌሳና የስልጤ ዞን አስተዳዳሪው የወሬ ማጣፈጫዋ ሆነው ከርመዋል። " የስልጤ ጉራጌ አይደለም" መፈክር ያቀነቀነው ቡድን አመራር ነበረች። አንድን ህዝብ ለሁለት የሰነጠቀው ህዝበ ውሳኔ በበላይነት ካስፈፀሙት የስልጤ ካድሬዎች አንዷ ነበረች።

"የትምህርቱ እንዳልከው ይሁን። ግን ለምንድነው በአርከበ ዘመን የምደባ ወቅት ጠብቀህ እንዳልመደብ ጥረት ያደረከው?"

በወቅቱ ከነባሩ ካድሬ ውስጥ ተመርጦ ምደባ ሲካሄድ በቁጥር አንድ እኔ እንዳልመደብ አንድ ጊዜ "የአመለካከት ችግር አለበት" ፣ሌላ ጊዜ " የብሄር ጥያቄ ላይ የጠራ አቋም የለውም" ብሎ ሲከራከር የነበረው እሱ ነበር። ይህ ሁሉ አላዋጣው ሲል በደፈናው "አህዴድ አልፈቀደም" ብሎ ከምደባ ውጭ አደረገኝ። በሳምንቱ በ28 ወረዳዎች በተካሄደ ስብሰባ የእኔን በአሊ አብዶ መገፋት የሰሙ ከ5 ሺህ በላይ የአዲሳባ አባላት ተቃውሞ አሰሙ። ወደ ካድሬነት ያመጡኝ መከላከያ መኮንኖች ጣልቃ ገቡ። በወታደሮቹና በአባሉ ግፊት የአርከበ ዘመን ካድሬ ሆንኩ።

ለዚህም ወቀሳ ሌላ ሰበብ አለው፣

"በህቅ ንገረኝ ካልክ ብዙ የማታውቃቸው ነገሮች ነበሩ። አህዴድ በተለይም አባዱላና ጁነዲን የአዲሳባ አህዴድ አባላትን እንደ አባል አይቆጥሯቸውም። የገበና ዳጩ ልጆች ይሏችኋል። የትምክህት ሰለባ ናቸው ብለው ያምናሉ። በዛ ላይ ጠንካራ የአህዴድ ህልውና በፌንፌኔ ማረጋገጥ አለብን የሚል እምነት አላቸው። ይህን እውን ለማድረግ ከአዲሳአባ ልጅ ውጭ ያሉ ካድሬዎችን እንዲመደቡ መመሪያ ሰጥተውን ነበር።"

ሆዴ ውስጥ ከሚቀር ብዬ እንዲህ ብዬ ጠየኩት፣

"በተህድሶ ጊዜ መለስ የአህዴድ ካድሬዎችን በሰበሰበ ሰአት እኔን ብቻ መርጠህ ለምን አይመለከትህም ብለህ አባረርከኝ። በወቅቱ ከእኔ ጋር በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የነበሩ የዞን ካድሬዎች እንዲሳተፉ ተደርገው ነበር።"

"ለዚህ እንኳን ከጊዜያቶች በኋላ መሳሳቴን ተገንዝቤያለሁ። በወቅቱ በህቡዕ የሚካሄድ የፓለቲካ ሻጥር ነበር። ታስታውስ እንደሆነ እነ ኩማ፣ ሽፈራው ጃርሶና አንዳንድ የአህዴድ ፓሊት ቢሮ አባላት ፀረ - መለስ አቋም ይዘው ነበር። በመሆኑም የመለስን ሀሳብ ሊደግፉ ይችላሉ የተባሉ ካድሬዎች እንዳይሳተፉ ውስጥ ለውስጥ መልእክት ተላልፎ ነበር። መለስ አያወያየንም፣ ስብሰባው በአሮምኛ ብቻ መካሄድ አለበት፣ ህውሀት አህዴድንና የአሮሞ ህዝብን ይቅርታ ይጠይቅ የሚሉ መልዕክቶች ተሰራጭተው ነበር። አንተም በዛ ስሌት ነበር ከስብሰባው እንድትወጣ የተደረገው።"

ከግለሰብ እሰጣ ገባ መዉጣት ስለፈለኩ፣

"አንተ ከለቀቅክ በኃላ የአዲሳባን ለውጥ እንዴት አየኸው? "አልኩት።

"እሱንማ አንተ ልትነግረኝ ነው የሚገባው። በሁለቱም ዘመን የነበርከው አንተ ነህ?"

በውስጡ ያዘላቸውን ቅሬታዎች ስለማውቅ፣

"በአሸዋ ላይ የተሰራ ቤት ነበር፣ በሬ የወለደበት ዘመን!፣ ዘረኝነት አግጦ የወጣበት!፣ ግለሰቦች ከድርጅቱ በላይ ራሳቸውን የሸጡበት" አልኩት።

የአጋር ልጅ አሊ ደስ አለው።ጭንቅላቱን ላይ ታች በመነቅነቅ እንዲህ ሲል በረጅሙ አወጋኝ፣

"... እውነትህን ነው። መለስ ለአርከበ ያደረገለትን ድጋፍ ለእኔም ቢያደርግ ኖሮ የእሱን ያህል መስራት አያቅትም ነበር። አርከበ እንዲፈጽም የተሰጠውን እቅድ ሙሉ ለሙሉ የጻፈው መለስ ነበር። የእቅዱ ማስፈፀሚያ ገንዘብ የተመደበው ከፌደራል መንግስት በመለስ ልዩ ትእዛዝ ነበር። ታስታውስ እንደሆነ እኔ ፕሬዝዳንት በሆንኩበት እያንዳንዱ አመታት የምንሰበስበው ገቢ ከ2 ቢሊዮን አይበልጥም ነበር። ፌዴራል መንግስት አይን የሚገባ ድጎማ አያደርግልንም። እንደውም ብዙ የገቢ ምንጮችን ይወስድብን ነበር። ለሰራተኛ ደሞዝ ከፍለን የምትቀረን ገንዘብ በጣት የሚቆጠሩ ፕሮጀክቶችን ለመስራት ብቻ የሚያስችል ነበር። እንደዚህም ሆኖ አርከበ አፍ አውጥቶ አይናገራቸው እንጂ የቀለበት መንገዱ፣ የድሬ ከርሰ ምድር፣ የአካባቢ ልማት ስራዎች ህዝቡ በበገሙ የሚያነሳቸው ናቸው።

ትንፋሽ ወስዶ በቁጭት ቀጠለ፣

"... በተቃራኒው ፌደራል መንግስት ለአርከበ ገና እንደመጣ ብረትና ሲምንቶ መግዣ ብቻ ስንትና ስንት ብር ድጋፍ አድርጓል። ከእኔ በላይ እንደምታውቀው በመጀመሪያው አመት የአርከበ አስተዳደር የሰበሰበው ገቢ አነስተኛ ነበር። በተለይ መርካቶ ከፍተኛ አጣብቂኝ ውስጥ በመግባቱ የተሰራው ወንጀል የሚዘገንን ነው። ለልማት የህብረተሰቡ መዋጮ ዝቅተኛ ነበር። በእኔ ዘመን ለአካባቢ ልማት ስራዎች ህዝቡ የተሻለ አዋጥቷል። የውስጥ ለውስጥ መንገዶችና መፀዳጃ ቤቶች በህዝብ ገንዘብ የተሰሩ ናቸው። ተሞክሮ መውሰድ አለባችሁ ተብሎ ከትግራይና አማራ ክልል ካድሬዎች መጥተው ገመቺተዋል። በአርከበ ዘመን ይህ ተግባር ተዳክሞ ሁሉንም ነገር የሚሰራው መንግስት ሆኖ ነበር... ያውም ፌዴራል መንግስት" አለ።

አሊ ሮሮውን ማቆም አልፈለገም። ጥርሱን እያንቀጫቀጨ፣

"...ታስታውስ እንደሆነ የቀለበት መንገድ ግንባታው ግማሽ ላይ ተቋርጦ ነበር። የተጠየቀው ካሳ ከፍተኛ በመሆኑና በበጀት እጥረት ምክንያት። በዛን ሰአት የፌደራል መንግስቱ ድጋፍ እንዲያደርግልን መለስ ጋር ሄድን። በፍፁም ባልጠበቅነው ሁኔታ ተበሳጭቶ የህገሪቷ የልማት አቅጣጫ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ላይ ገንዘብ ማፍሰስ አይደለም በማለት ተናገረ። መለስ ቁጣውን የገለፀበት ሁኔታ አልረሳውም።"

አቋርጬው "ምን አላችሁ?" ብዬ ጠየኩት።

"ለአባይ ግድብ፣ ለማዕድን ቁፋሮ፣ ለቀለበት መንገድና ለትላልቅ መስኖዎች ገንዘብ ማውጣት ጥገኛ አስተሳሰብ የወለደው ነው። የአብዮታዊ

ዲሞክራሲ የልማት አቅጣጫ ካለመረዳት የሚመጣ። አባይም ግንዱን ይዞ ይዙር፣ ቀለበትም ሳይጠለቅ ይቅር። ሁለቱም ነጫጭ ዝሆኖች ናቸው አለን። ለምን እንደሆነ ባይገባኝም መለስ ስለትላልቅ ፕሮጀክቶች መስማት አይፈልግም። ዛር እንደያዘው ሰው ያንቀጠቀጠዋል።" ትንሽ ረፍት ወስዶ፣

"... የሚገርምህ በምትተርፈን ገንዘብ ሲኤምሲ ፣ፈረንሳይ ፣ሳር ቤትና ቃሊቲ ከንደሚኒየሞችን መገንባት ጀምረን ነበር። ይህም እንዲቆም የተደረገው በመለስ ምክንያት ነበር። የቤት ልማት መከናወን ያለበት በማህበር በሚደራጁ ግለሰቦችና የሪል ስቴት ባለቤቶች እንጂ በመንግስት በጀት መሆን የለበትም ብሎ በድጋሚ ገሰጸን። ለልመና ሄደን የግማሽ ቀን የአቅም ግንባታ ስልጠና ወሰደን ተመለስን።"

"ምን አሰለጠናችሁ?"

"ረጅም ሰአት ነው ገለጻ የሰጠን። ሰነዶቹ የገጠር ልማትና የኢንዱስትሪ ስትራቴጂውን ነበር። መለስ ደግሞ ደጋግሞ የግብርና ልማታችን በበሬ ግንባር በምታከለው የአርሶ አደር ማሳ ላይ የሚፈፀም ሲሆን፣ ኢንዱስትሪውና ከተማው ደግሞ የግብርና ምርትን እንደ ግብአት በሚወስዱ የጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ላይ ያተኩራል አለን።"

ከጥቂት ደቂቃ ዝምታ በኃላ የጥያቄ መአት አዥጐደጐደ። የአንዳንዶቹን መልሶች ራሱ ያውቃቸዋል። እንዲህ በማለት ጀመረ፣

"... እውን አርከበ "ተወዳጅ" መባል የሚገባው መሪ ነበር ? የፈፀማቸው ተግባራት ይህንን ዘመን ተሻጋሪ ማእረግ የሚያጐናጽፉት ናቸው ? የአርከበ አመራር (Leadership) ጥራትና ስብእና በዚህ ደረጃ ሊያስፈርጀው የሚችል ነው?... በመርህ ደረጃ አንድ መሪ ታላቅና ተወዳጅ ሊሆን የሚችለው ምን አይነት ባህሪያት ሲላበስ ነው? አንተ ሊደርሺፕ ተምረሀል። እውነቱን እንነጋገር?"

እንዲህ በማለት መልስ ሰጠሁት፣

"አሊ! ተገቢ ጥያቄ ያነሳህ ይመስለኛል። በዚህ ጉዳይ ላይ ሁሉም ሰው አለም በተስማማበት ሚዛን ላይ ተቀምጦ መመዘን ይኖርበታል። ለታሪክም ሳይዛባ ማስተላለፍ ያስፈልጋል። አንድ የፓለቲካ መሪ ታላቅና ተወዳጅ ለመሆን ማሚላት ያለበት መሰረታዊ መርሆዎች፣ እሴቶችና ባህሪያት አሉ። ከእነዚህ ውስጥ፡ ህበረተሰቡን ወደተሻለ አቅጣጫ ሊመራ የሚችል ራዕይ ያለው፣ ለህዝብ የተለየ ፍቅርና አክብሮት ያለው ፣ህዝብ ተበድሏል ብሎ ሲያስብ በጽናት የሚታገልና እስከ መጨረሻው ድረስ መስእዋት የሚሆን፣ የህግ የበላይነትና ተጠያቂነት ለማምጣት የሚተጋ፣ በዘር፣ በሀይማኖትና በመሳሰሉት ላይ ተመስርቶ አድሎ የሌለበት፣ ስልጣኑን ለግል ጥቅም የማያውል... መሆን ይኖርበታል።"

በቁጭት ውስጥ ሆኖ እንዲህ ሲል ጠየቀኝ፣

"ስልጣንን ለግል ጥቅም አለማዋል ካልከው እንነሳ። የባለስልጣናትን ሙስና ደረጃ ለማጣራት በኃይለማርያም ደሳለኝ የሚመራው ኮሚቴ ተጨባጭ የሌብነት መረጃ ያገኘው በሸማግሌው ስብሀትና አርከበ ላይ አይደለም... ይህን አታውቅም?"

"በደንብ አውቃለሁ አሊ! ራሱ ኃይለማርያም በዝዋይ ህፃናት አምባ ካድሬዎችን ልናሰለጥን በገባን ወቅት ለእኔ ፣ሬድዋንና ካሚል ነግሮናል። ልጆቻቸውን ከአንድ ቻይና ኩባንያ በሚሊዮን ብር ምልጃ ተቀብለው እያስተማሩ እንደሆነ በከትትል እንደደረሱበት አጫውቶናል። ልጆቹ የሚማሩበት የቻይና ኮሌጅ ድረስ የሚያጣራ ሰው ተልኮ መረጃው ትክክል መሆኑን አረጋግጧል። የእነ አርከበ አለመታሰር ለኃይለማርያም የእግር እሳት ሆኖበታል።"

እየጋለና ስሜታዊ እየሆነ ሄደ። ካርቱም ቁጭ ብሎ የሰበሰበውን ብሶት በሸራተን ቶኒክ ዘረገፈው። እንደፈቀደ እንዲተነፍስ በር ከፈትኩለት። እንዲህ በማለት ቀጠለ፣

"... ህሊናችንን የህቅ ሚዛን ላይ የምናስቀምጥ ከሆነ እንደ አርከበ ጐጠኛ አለ? እንደ አርከበ በደምና አጥንት የሚያምን አለ? እንደምታውቀው አዲሳባ ተዘዋውሮ ሲመጣ ይዞ ከመጣቸው የህውሀት ካድሬዎች ውስጥ አራቱን የከፍለ ከተማ ከንቲባ ሲያደርግ በተቀሩት አምስት ክፍለ ከተሞች ደግሞ ምክትል ከንቲባ እድርጐ አልሾመም። አዲስከተማንም ቢሆን ከንቲባው ሳይሆን እሱ ከትግራይ ይዟት የመጣው ሮማነ ነበር እንደፈለጉች ያሾረችው።"

በድጋሚ ራሴን ላይ ታች፣ ታች ላይ ነቀነቅኩ።

የቀረበለትን ቡና እየጠጣ ትረካውን ቀጠለ፣

"...የትምህርት መዋቅሩ ከላይ እስከ ታች ያለው ሙያዊ አመራር በህውሀት ካድሬዎች እንዲያዝ አድርጓል። ሶስት አመት ሙሉ ትምህርት ቢሮን *"ቢሮ ሀበሬታ ትምህርቲ!"* ብላችሁ ስትጠሩት እንደነበረ ሰምቻለሁ።"

መልስ መስጠት አልፈለኩም። በቁጭት ውስጥ ሆኖ እንዲህ አለኝ፣

"...ቅድም ከተወዳጅ መሪዎች የጋራ ባህሪያት አንዱ ለህዝብ የተለየ ፍቅርና አክብሮት ያለው ፣ህዝብ ተበድሏል ብሎ ሲያስብ በጽናት የሚታገልና እስከ መጨረሻው ድረስ መስእዋት የሚሆን ብለኸኝ ነበር። ትክክለኛ አስተሳሰብ ይመስለኛል። ይህን እስቲ ከአርከበ ስብእና ጋር አዛምደን እንመልከተው። በምርጫ 97 ማግስት የተቋቋመው ሰባት ማዘጋጃ ጣቢያ የፓለቲካ ዘርፉን በሙሉ እንዲይዙት ያደረገው የህውሀት ካድሬዎችን ነበር። ተመጣጣኝ እርምጃ አልወሰደም የሚባለውን የፓለቲካና ፀጥታ ጥምር ኮሚቴ የሚመራው እሱ ነበር። በወቅቱ ለነበረው ነውጥ ተጠያቂው ማንም ይሁን ማን የህዝብ ልጆች

ወድቀዋል። በአመጹ የሌሉ ንጹሀንና ህፃናት ተገለዋል። አርከበ የመዲናይቱ እንደራሴ እንደ መሆኑ መጠን ይቅርታ መጠየቅ ነበረበት። ከመሬት ስር ለዋሉት ህፃናት ተጠያቂ ነው። እሱ ያደረገው በተቃራኒ ነው። በጥምር ኮሚቴ ሰብሳቢነቱን ተጠቅሞ ህፃናቱ ባንክ ሊዘርፉ ሲሉ ተገደሉ የሚል ዜና እንዲነበብ አድርጓል።"

ትንፋሽ ሰቦ ቀጠለ፣

"...ከግድያውና ዝርፊያው በኋላ አርከበ ወደ ስራና ከተማ ልማት ሲሄድ ይዟቸው ከሄዱት 18 ካድሬዎች ውስጥ 15 ያህሉ የህውሀት ካድሬዎች ናቸው ። ራስህ መፍረድ ትችላለህ እነማን አጅበውት እንደሄዱ። በረከት ስምኦን በመራው ግምገማ ላይ እንዳይገኙ ለምን አሸሻቸው? ከተገኙት ውስጥ ጀሮ የሚሰቀጥጥ ሌብነት የፈፀሙ ካድሬዎች አሁን የት ነው ያሉት?"

የአጋር ልጅ አሊ ብሶት አዘል ጨዋታ ጨምሯል። አቶ መለስ ላይ ቂም ቋጥሯል። በተለይም በየጊዜው ለአዲሳባ የሰጠውን በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ አንገብግቦታል። ሱዳን ተቀምጦ የአዲሳባ ካቢኔ በየሳምንቱ ከአቶ መለስ ጋር ተሰብስቦ ያነሳቸውን አጀንዳዎች በዝርዝር ያውቃቸዋል። ታላቁ መሪ በዘር ላይ የተመሰረተ አድልኦ ፈጽሟል የሚል እምነት አለው። የህውሀት ካድሬዎች ከሌላው ገዝፈው እንዲታዩ የተደረገው በዚህ መልኩ በሚፈፀም ኢ - ፍትሐዊነት እንደሆነ ጥርጣሬ የለውም። በአርከበ ዘመን የተፈፀሙ ወንጀሎችን በጭንቅላቱ መዝግቦ ይዟል። ከአዲሳባ ካርቱም የዘረጋው ኔትወርክ ሳያቆራርጥ መረጃ እንዳደረሰው ያስታውቃል። በተለይም የአዲስ ከተማ ከንቲባ የነበረው ሉልሰገድ በትክክልም የአሊን ውለታ መመለሱን የሚያመላክት ነበር።

በመለያያችን ሰአት ላይ በትካዜ ውስጥ ሆኖ እንዲህ ሲል ጠየቀኝ፣

"ይሄ ሁሉ ቅሌትና ወንጀል ፈጽሞ ሲያበቃ አርከበ እቁባይ ለምን ከሌሎቻችን በተለየ ተወዳጁ ከንቲባ የተባለ ይመስልሀል?"

"አምባሳደር አሊ! ጀርመናዊው ሚ/ር ጆሴፍ ጐብልስ ኢትዮጵያ ከከተመ ዘመን ተቆጠረ!" አልኩት።

"ደግሞ እሱ ማነው? ከጀርመን ተራድኦ ድርጅት (GTZ) ጋር ለኮንደሚኒየም ግንባታ መጥቶ ነው? ጀርመኖችን ማመን ቀብሮ ነው!" በጉጉት ጠየቀኝ። በማያቋርጥ ሳቅ ውስጥ ሆኜ፣

"Make the lie big, make it simple, keep saying it, and eventually they will believe it" ብዬ መልስ ሰጠሁት።

ክቡር አምባሳደር አሊ አብዶ ስለምን እንደምናገር አልገባውም። እንደሱ ሁሉ ብዙዎች ግራ ተጋብተዋል...

ቀጣዩ ክፍል ለዚህ የአጋር ልጅ ልቅሶ አዘል ጥያቄ ምላሽ መስጠት እንደሚኖርባት ይጠበቃል። ርግጥ ትግሉ ቀላል አይሆንም። የተደጋገመው ኩሸት ህዝቡን ወደተፈለገው አቅጣጫ ይዞት ነጉዷል። እልፎችን አስልፉል። የአባባሉ ዋነኛ አቀንቃኝ ምስኪኑ ህዝብ ብቻ ሳይሆን ከመልእክተ ዜናዊ ተቃራኒ የተሰለፉትም እስከ መሆን ደርሷል። ከሀገሬው ህዝብ አልፎ አንደ አፍሪካ ብሮድካስቲንግ የመሳሰሉ ተቋማት "የአፍሪካ ከንቲባ!" የሚል ማእረግ እስከ ማጐናፀፍ ደርሰዋል።

ምአራፍ ሃያ ስምንት

ጐብልስ በአዲሳአባ

"አርከበ! አድሜ ልክህን የፓለቲካ ደሀ ሆነህ ትኖራለህ?"
ተፈራ ዋልዋ

የኢህአዴግ ፕሮፓጋንዳ የሚመራባቸው መርሆዎች በአብዛኛው የሚመነጩት ከጀርመናዊው ፕሮፓጋንዲስት ጆሴፍ ጐብልስ ነው። ጐብልስ በዘመነ ሂትለር የተለያዩ መርሆዎችን በመቅረጽ በተግባር ላይ አውሏል። ከእነዚህም ውስጥ ፕሮፓጋንዳ በታቀደ መልኩ በአንድ ተቋም፣ በተመረጠ መሪ ቃል መመራት እንዳለበትና ተደጋጋሚ በሆነ መንገድ (አሰልቺም ቢሆን) መገለጽ እንዳለበት ያስገነዝባል። የጐብልስ ፕሮፓጋንዳ ማጠንጠኛ "The big lie theory" በመባል ይታወቃል። የሀገራችን ሰው "ውሸት ሲደጋገም እውነት ይሆናል" እንደሚለው።

ኢህአዴግ በተለያዩ ጊዜያት እነዚህን መርሆዎች በጥቅም ላይ አውሏል። አንዳንዶቹ ፓርቲው በተለየ ሁኔታ እንዲታወቅ ያደረጉ ሲሆን የህብረተሰብ ገዥ አስተሳሰብ እስከመሆን ደርሰዋል። ከሀገሬው ህዝብ አልፎ አለም አቀፍ ተቋማትም ተቀብለውት አስተጋብተውታል።

ኢትዮጵያዊው ጐብልስ ሰስት ገጾችን አጣምሮ የያዘ ነው... እዉነት... እውነትና ውሸት...ውሸት።

ከእነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ "የኢህአዴግ ስልጣን የዛፍ ላይ እንቅልፍ ነው"፣ "ባለ ሁለት አህዝ እድገት"፣ "የህዝቦች ተጠቃሚነት"፣ "ተወዳጁ አርከበ"፣ " አዲሲቷ ኢትዮጵያ"፣" የትራንስፎርሜሽኑ መሀንዲስ"፣ "የአርሶአደር ፍቅርና ድጋፍ ያተረፈ ድርጅት"፣ "መተካካት"... የሚባሉት ቃላቶች በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የዘውትር ህይወት ላይ ባይፈልግ እንኳን የሚያዳምጣቸው ናቸው። በሚዲያ ተቋማትና በኢህአዴግ ካድሬዎች በተደጋጋሚ ተንኳኩተዋል። በዚህ ምክንያት አንዳንዶቹ የህብረተሰቡ መሪ አመለካከት እስከመሆን ደርሰዋል።

***

"የኢህአዴግ ስልጣን የዛፍ ላይ እንቅልፍ ነው!"

ኢህአዴግ አዲሳባን ከተቆጣጠረ ጀምሮ በስልጣን ላይ ያሉና ሀገራዊ ጥፋት መፈፀማቸው የሚታወቅ አያሉ" የኢህአዴግ ስልጣን የዛፍ ላይ እንቅልፍ ነው" በሚል ይገለጻል። በረከትም በሁለት ምርጫዎች ወግ መጽሐፉ ላይ ይህን አባባል ተጠቅሞበታል። ይህ መፈክር እውነትና ቅጥፈት የተጐራረሱበት ነው።

በኢህአዴግ የስልጣን ማማ በታችኛው እርከን ያለው ካድሬ የሚራገፈው እንደ 77 የኢትዮጵያ ድረቅ ነው። በአንድ ወቅት አባዱላ ገመዳ ከ10 ሺህ በላይ የወረዳና ቀበሌ ካድሬዎችን አባሮ እንደጀግና የተቆጠረበት ጊዜ ነበር። "ሺቫ አባዱላ!" የተባለበት ዘመን። አዲሳባ ደግሞ መስከረም በጠባ ቁጥር አዲስ የቀበሌ ሊቀመንበር ይኖራታል። እያንዳንዱ የከተማ ነዋሪ በሚኖርበት ቀበሌ የኢህአዴግ ዘመን ሊቃነመናብርት ቁጠር ቢባል የሁለቱም እጆቹ ጣቶች አይበቁትም። አንዳንዶቹንም ከነመፈጠራቸው አያውቃቸውም። ካድሬዎቹ የሚራገፉበት የግምገማ ነጥቦች ለተመለከተ ደግሞ ለብዙ ቀናት ከአግርሞት አይወጣም... "የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ጋዜጣ እዳ አለብህ፣ የአባላት መዋጮ በሰአቱ አላስገባህም፣ ከተቃዋሚ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች ጋር ሻይ ቡና ጠጥተሀል..." የሚሉ ናቸው። ጠንከር ያለ ከሆነ ደግሞ "የቀበሌ መታወቂያ ሰጥተሀል"፣ "ደሀ ያልሆነውን ደሀ ብለህ ለጤና ጣቢያ የነፃ ህክምና ወረቀት ጽፈሀል"፣ "የቀበሌ ቤት ይሰጠኝ ብለህ ጠይቀሀል፣ አጥርህን ገፉ አድርገህ አጥረሀል..." ይሆናሉ።

በተቃራኒው የላይኛው የኢህአዴግ የስልጣን እርከን ፓርቲው ላይ ስጋት እስካልተፈጠረ ድረስ በስፖሪንግ ፍራሽ ላይ ተደላድሎ እንደመተኛት ነው። ያውም በየጊዜው የሚቀየር ፍራሽ። የአቶ መለስ ስልጣን እስከ ህልፈቱ ዘልቋል። አቶ ስዩም መስፍን ጀሮው መስማት ተስኖትም የሶስት ሚኒስትሮችን ያህል ስልጣን ተሸክሞ ቤጂንግ ከትሟል። እነ አባይ፣ በረከት፣ አዲሱ ዛሬም በስልጣን ላይ አሉ። አባዱላ የሸንጐውን መዶሻ እየደበደበ ነው። አባይ ነብሶ የሸመልስ ከማልና ሚሊዮን አሰፉ ሳንባ ተገጥሞለት አሁንም የፓርላማው አስትንፉስ ነው። የኢቲቪ ገረዊና ዘርአይ አስግዶም ወሬ ያሳመረ መስሎት "...ሬዲዮኑ፣ ቴሌቭዥኑ፣ ስልኩ፣ ኢንተርኔቱ..." እያለ በተከበረው ፓርላማ ይለፉደዳል። የአማራ ክልሉ ገዱ እውነትም ገደኛ ነው። አንድ መጽሐፍ ሳያነብ ፓስተር ባደማና በዙሪያው የሰበሰባቸው ኤክስፐርቶች ባለ ማስተርስ አድርገው የባህርዳር ቆንጆዎቹ ሆኗል። አለ አብዶ ናይጀሪያ፣ ግርማ ብሩ አሜሪካ ነግሰዋል። አርከበ

እቁባይ ጥናታዊ ጽሁፎች የሚያዘጋጁለት ፕሮፌሽናል ሙያተኞች ከጐኑ አስቀምጦ ዶክትሬቱን እየሰራ ነው። ትምህርቱን ሲጨርስ በአማካሪነት አሊያም በቦርድ አባልነት ኢኮኖሚውን ይዘውራል። ዶ/ር አብርሀም የኢኮኖሚያችን ዋልታ ሆኗል። ሀይሌ ፍስሀ ከከንቲባው በላይ የመዲናችን ቁልፍ ሰው ነው። የህውሀት አባላት ለቀበሌ ካድሬነት ብቁ አይደለም የሚሉት አለቃ ፀጋዬ የደህንነቱ አስኳል ሆኗል።

***

"ባለሁለት አሀዝ!"

ባለ ሁለት አሀዝ እድገት በኢትዮጵያ ተገኝቶ እንደነበር የሚያጠያይቅ አይደለም። ከዚህ አንፃር ትልቁ ጥያቄ እድገቱ ፍትሀዊ የሀበት ስርጭትን በሚያረጋግጥ መልኩ የተገኘ ነበረ ወይ የሚለው ይሆናል። ከዚህ በተጨማሪም እንደዚህ አይነት የባለ ሁለት አሀዝ እድገት በዘላቂነት ቀጥሎአል ወይ የሚለውን ማንሳት ይቻላል።

ይህም ሆኖ በብዙ ኢትዮጵያውያን ጭንቅላት ውስጥ 11.2% እድገት ተቀስራ ቀርታለች። አለም አቀፍ ተቋማትም አሰልቺ በሆነ መንገድ የተነገረውን በመቀበል አስተጋብተውታል። ይህን በተመለከተ በረከት በሁለት ምርጫዎች ወግ መጽሐፉ ገጽ 190 ላይ የሚከተለውን አስፍሮ አናገኛለን፣

"...ሚዲያው ኢትዮጵያ በልማት ገሃና እንደገሰገሰች ለሰስተኛ ጊዜ ባለሁለት አሀዝ እድገት አንዳመጣች ገለፀ። ሚዲያው ፊቱን ወደ ልማት አጀንዳ አዙሮ ጉዳዩ የህዝብ መነጋገሪያ መሆን ሲጀምር አለም አቀፍ ሚዲያውም እግር በእግር ተቀብሎ አስተጋባው። አለም የአገሬው ህዝብና መንግስት የሰጡትን ሊቀበል እንደሚችል ታየ። ስለራሳቸን መጥፎ በነገርነው ቁጥር ይህንኑ እንደ ገደል ማሚቴ ሊያስተጋባ፣ ጥሩ ስንነግረውም ያንኑ ሊቀበል እንደሚችል አረጋገጥን።"

ይህን የበረከት መልእክት በጥሞና አንብቦ የተረዳ ሰው የሁለት ምርጫዎች ወግ መጽሐፍ ማጠንጠኛ እንዳገኘ ይቆጠራል። ከዛም አልፎ የኢህአዴግን ፕሮፐጋንዳ መርሆዎች ምንጭ ይገነዘባል።

***

"ተወዳጁ አርከበ"

,

ይህ መፈክር የመነጨውና የተስፋፋው በተለያዩ ምክንያቶች ነው። የመጀመሪያው ከፓርቲው የገሎ መዳን ስትራቴጂ የሚመነጭ ነበር። አሊ

አብዶን ገሎ ኢህአዴግን በአርከበ አማካኝነት ማዳን። በምርጫ 97 የኢህአዴግን አሸናፊነት ማረጋገጥ። በዚህም ምክንያት ኢህአዴግ ከፀሀይ በታች በአዲሳባ የሰራቸው ስራዎች አርከበ ከመጣ በኋላ እስኪመስል ድረስ ተሰበከ። አርከበ የኢትዮጵያ ቴሌቭዥንን ሚስቱ አደረገው። አጥራ ዊንፍሬን ጨምሮ አለም አቀፍ ታዋቂነት ያላቸው ሰዎች በመጡ ቁጥር የአዲሳባን ቁልፍ ማበርከት ጀመረ። በከተማው የሚካሄዱ ትላልቅ ስብሰባዎች መክፈቻ የእሱ ቃለ ቡራኬ ሆነ። የአፍሪካ መሪዎች በተገኙበት ኪኖት አቅራቢ ሆነ። ይህ ድርጊቱ እያደር በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ወደመሆን ተሸጋገረ።

ከዚህ አንፃር ስየ አብርሀ "ነፃነት እና ዳኝነት በኢትዮጵያ" ብሎ በጻፈው መጽሀፍ በገጽ 185 ላይ የምርጫ 97 ስሌት በገለፀበት ክፍል የሚከተለውን አስፍሮ እናገኛለን፣

"ኢህአዴግ መቼም ቢሆን እንደሚሸነፍበት በመገመት የሚሰጋበት አንዱ እና ትልቁ ከተማ አዲስ አበባ ነው። ከተመረጠበትና ከተመደበበት የትግራይ ብሄራዊ ክልል አቶ አርከበን በማምጣት በአዲስ አበባ ከንቲባነት ሲያስቀምጥም በአጭር ጊዜ ለውጥ በማምጣት የመሸነፍ ስጋቱን ይቀርፍልናል ከሚል ተስፋ ነበር። ለዚህም ሲባል አዲስ አዋጅ ወጥቶለት፣ ሰፊ ስልጣን ተሰጠው። ብዙ ገንዘብ ተመድቦለት የራሱ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ከፍቶ አዲሳባን እየለወጥኩ ነው ብሎ እንዲናገርም ተደረገ። ዳሩ አቶ አርከበ አመል ሆኖበት ቴሌቪዥኑን እንደ መስታወት ራሱን ለማየት ሲጠቀምበት የአቶ መለስ ዘለፉ ሰለባ ሆኖ አረፈው እንጂ።"

(ስየ ልክ ነበር። በነካካ እጁ "ኢህአዴግ መቼም እንደሚሸነፍበት በመገመት የሚሰጋበት አንዱ እና ትልቁ ከተማ አዲስ አበባ ነው።" ብሎ የገለፀውን ወደ ኋላ ሄዶ ትንሽ ፈታ ቢያደርጋትና እሱም ዝሆን በነበረ ወቅት የተፈፀሙ ጥፋቶችን ቢነካካ ጥሩ ነበር። ፀፀቱም የተሟላ ይሆናል።)

ሁለተኛው ምክንያት ህውሀትን በልዩ ሁኔታ ለመሸጥ በአቶ መለስ የታቀደ ነበር። ከፊዴራል መንግስት በተመደበው ከፍተኛ በጀትና ድጋፍ ምክንያት በመዲናይቱ ለውጥ መምጣቱ ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አልነበረም። " የሁሉም ነገር ወደ አዲሳአባ" ነጋሪት በከተማዋ ታይቶ የማይታወቁ ህንፃዎች፣ መንገዶችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንደ እንጉዳይ እንደሚያፈላ የሚያጠራጥር አይደለም። አቶ መለስ ሰገሬን እንቁላሏን እንደምትከታተለው አይኑን አዲሳአባ ላይ ተክሏልና መንግስታዊ አገልግሎት አሰጣጡ ወደ ተሻለ ደረጃ መሸጋገሩ የማይቀር ይሆናል። የተገዱ የህብረተሰብ ክፍሎች በማለት ሴቶች፣ አረጋውያን፣ አርበኞች፣ አካል ጉዳተኞች ... እየተባለ የኮንደሚኒየም ቤቶች እንደሚታደሉ አስቀድሞ የተቀየሰው ወደ ተግባር በመቀየር ተአምር

እንደወረደ መቆጠሩ የማይቀር ሀቅ ነው።

ከዚህ አንባር ትልቁ ጥያቄ የውጤቱን ውለታ (ክሬዲት) ማን ይውሰደው? በለውጡ ፉና ወኒነት የትኛው ፓርቲ ስሙን ይትከል? የአዲሳአባን የልማት እድገት አብሳሪ ማን ይሁን? የሚሉት ይሆናል። ይህንን ጥያቄ ታሳቢ በማድረግ ታላቁ መሪ አርከበን የማዋረድ ግብ በልቡ ይዞ በአፉ "ተወዳጁ አርከበ" እንዲቀነቀን አደረገ። በክፍለከተማም የህውሀትን የልማታዊ ፉኖነት ለማጽናት ከንቲባና ምክትሎችን በሙሉ የህውሀት ካድሬዎች አደረገ። "ብረት አንግቦ ተራራ ያንቀጠቀጠው ትውልድ የልማት አርበኝነቱን አስመሰከረ።" የሚሉ ግጥሞችና መዝሙሮች ተቀነቀኑ።

ሶስተኛው ምክንያት ከውስጠ ድርጅት የተገኘው መረጃ በአቶ መለስና አርከበ መካከል ልዩነቶች መከሰታቸው በሰፊው በህዝቡ ዘንድ በመሰራጨቱ ነበር። አቶ መለስ የቅናት ዛር ይዞት አላሰራው አለ የሚባሉ ወሬዎች ተዛመቱ። በዚህ ምክንያት ህዝቡ አቶ መለስ ላይ ያለውን የመረረ ጥላቻ አርከበን በመውደድ አሳየ። ሁለት ተቃራኒ የሆኑ ነገሮችን በተመሳሳይ የመውደድ አመክንዮ ስለማይሰራ። አልፎ ተርፎም አርከበ ኢህአዴግን ትቶ ተቃዋሚን እንዲቀላቀል ተማጽኖ መቅረብ ጀመረ። ህዝቡ አርከበን ከኢህአዴግ ማእቀፍ አውጥቶ ማሰብ ጀመረ።

አራተኛው ምክንያት አማካሪ ምክርቤት ተብለው የተደራጁት የህብረተሰብ ክፍሎች፣ የአርበኞች ማህበር አመራር የሆኑት እነ ሊቀ ትጉሀን አስታጥቄ፣ በአሊ አብዶ ላይ የመረረ ጥላቻ ያላቸው የሲኖዶስ አባላት "ተወዳጁ አርከበ" መፈክር ባገኙት አጋጣሚ አስተጋብተዋል። በፀረ ኢህአዴግነታቸው ዝርዝራቸው ተይዞ ክትትል የሚደረግባቸው እነ አርቲስት ችሮታው ከልካይ በአማካሪ ምክር ቤት የተወዳጁ አርከበ ድራማ መሪ ተዋንያን ሆነው ነበር። በደርግ ዘመን የአዲሳባ ከንቲባ የነበሩት አምባሳደር ዘውዴ አርከበ የልማት አርበኛ ተደርጐ እንዲሳል ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። በአማካሪ ምክርቤት ስብሰባ ወቅት በአምባሳደሩና አርከበ እቁባይ መካከል የሚካሄደው መሞጋገስ ሰፊ ሰአት ይወስድ ነበር። በንግግራቸው ማሳረጊያ የሚሰማው ጭብጨባ መንግስቱ ኃይለማርያም የኢሰፓአኮ መሪ ሲሆን የተደረገውን የሚያስንቅ ነበር። በዚህ ብስጭት ያለው ህላዌ ነብሴ በውስጠ ድርጅት ስብሰባ ላይ "አሁንስ በዛ! የስልጣን ሽግግሩ ከአምባሳደር ወደ አርከበ የተካሄደ አስመሰሉት" ብሎ ተናገረ።

በአጠቃላይ መልኩ የአርከበ ተወዳጅነት የመነጨው ኢህአዴግ ቀርጾ በተደጋጋሚ ባስተላለፈው መልእክት፣ ህዝቡ ለአቶ መለስ ከነበረው ጥላቻ እና ምላሳቸው ረጃጅም የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ደጋግመው በመጮህቸው

ምክንያት የመጣ ነበር።

***

አርከበ በካድሬዎች አይን፣

በጉንጭ አልፉው ግምገማ ላይ በረከት አርከበን እንዲህ ሲል ጠየቀው፣

"በአዲሳባ ታቅደው ከተሰሩ ስራዎች ውስጥ አንዲት የድርጅቱ ሳይሆን የእኔ ፈጠራ ናት የምትላትን እንድትነግረን እፈልጋለሁ?"

አርከበ እንዲህ በማለት ምላሽ ሰጠ፣

"በዚህ ጉዳይ ላይ ሁለታችንም የምንለያይ አይመስለኝም። ድርጅቱ ከሚነግረን ውጪ ዝንፍ እንደማንል ልቦናህ ያውቀዋል።" አለው።

በረከት አፍንጫውን እየጐተተ፣

"እሱን የእኔ ግምገማ ሲቀርብ ትናገራለህ። አንተ ግን ድርጅቱ ቃል በቃል ነግሮህ እንኳን በአግባቡ መፈፀም አትችልም ነበር። የሚያሳዝነው የድርጅቱን ውጥኖች የራስህ ፈጠራ አስመስለህ ግለሰባዊ ስብእናህን ስትገነባ መክረምህ ነው።" በማለት እቅጩን ተናገረ።

"በረከት የእኔና የአንተ ችግር የዛሬ ሳይሆን ከበረሀ ጀምሮ ነው።" አርከበ ከዚህ ውጭ ምላሽ አልነበረውም።

ከዓመታት በኋላ ይህንን ድምዳሜ ለታሪክ ማስቀመጥ አስፈላጊ በመሆኑ በሁለት ምርጫዎች ወግ መጽሐፍ " ማሚሻ ወግ "በሚለው ርእስ ስር፡

"... አዲሱ አመራር ኢህአዴግ ያስቀመጠለትን አቅጣጫ ተከትሎ በከፍተኛ ተነሳሽነት ሰራ በጀመረ ማግስት በብዙ መስኮች የቆየውን አዝጋሚ አካሔድና አሰራር የሚቀይር በኢትዮጵያ አዲስ የከተሞች አድገት ምእራፍ መክፈቱን የሚያበስር ሰፊ እንቅስቃሴ ተቀጣጠለ።" በማለት የፈጠራውን ባለቤት ለኢህአዴግ (አቶ መለስ) ይሰጣል።

የውስጠ ድርጅቱ ግምገማ ግልፅ ነው። ለህዝቡ በሁለት ምርጫዎች ወግ የተገለፀበት አግባብ ደግሞ ውስጠ ወይራ። አርከበን በተመለከተ የድርጅቱ ከፍተኛ ካድሬዎች ያላቸው አመለካከትና ለህዝቡ እንዲሰርፅ ያደረጉት አስተሳሰብ ተቃራኒ ናቸው። ከአቶ መለስ ጀምሮ ሌሎቹ ካድሬዎች በውስጠ ድርጅት ስብሰባ የአርከበን የፓለቲካ ድህነት፣ መርህ የሌለው መሆኑን፣ ውግንናው ኢህአዴግ ቆሜለታለሁ ከሚለው ማህበተሰብ በተቃራኒ እንደሆነ፣ የራሱን ገፅ ሲገነባ መክረሙን በግልጽ ይናገራሉ። የተለያየ ስያሜ ይሰጡታል። አቶ መለስ "ቀለም ቀቢው"፣ ሚስቱ ደግሞ "የሳሎን ውሻ" ብለው ይጠሩታል። በረከት "የዛፍ ላይ እባብ "ይለዋል። ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም " እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል!" በማለት ይገልፀዋል። የዋልዋ ልጅ " የፓለቲካ ደህ" በማለት ይወርፈዋል።

እስቲ ስላንዳንዶቹን ዘርዘር አድርገን እናውጋ፦

"የሳሎን ውሻ"

አርከበ ወደ አዲሳባ በመጣ ሩብ አመት ሳይሞላው "ኤች አይ ቪ ኤድስን ለመከላከል የቆረጠ አመራር" በሚል ዝናው እንዲሰራጭ ይደረጋል። አፍታም ሳይቆይ የኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያ ሴክሬተሪያት ዲያሬክተር ለነበረው ዶክተር አሸናፊ ትእዛዝ በመስጠት ቢልቦርድ እንዲዘጋጅ ያደርጋል። ቢልቦርዱ ከሀምሳ ሺህ ብር በላይ የወጣበት ሲሆን ፣አርከበ ኤድስ ሲመረመር የሚያሳይ ነበር። ይህ ግርማ ሞገስ ያለው ታፔላ መህል ፒያሳ ላይ እንዲተከል ተደረገ።

ተመሳሳይ ቁመና ያላቸው ተጨማሪ ቢልቦርዶች በከተማው አራት ዋና ዋና ቦታዎች እንዲተከሉ ዶክተሩን በድጋሚ ያዘዋል። ገ*ን ለገ*ን በትላልቅ ፓስተሮች በማሰራት በየጤና ጣቢያው፣ ትምህርት ቤቶችና የአስተዳደሩ ጽ/ቤቶች እንዲለጠፍ ያደርጋል።

ከእለታት በአንዱ ቀን ወይዘሮ አዜብ በፒያሳ አለፍ ስትል አይኗ ያየውን ማመን ያቅታታል። ስልኳን አንስታ በበረከት መጽሐፍ ላይ ስቅስቅ ብሎ ለሚያለቅሰው ለአሊ ሲራጅ ትደውላለች። ከፍ ዝቅ አድርጋ በመሞላጭ "ይህን የሳሎን ውሻ" ብላ የጠራችውን ታፔላ በአስቸኳይ እንዲያነሳ ታዘዋለች። ትእዛዙ የእመቤቱ ነውና በተባለው እለት ግብረሀይል አሰማርቶ ያስነቅላል። በየተቋሙ የተለጠፉትን ፓስተሮች መቅደድ የሳምንቱ ቁልፍ ስራው አድርገ* ይከርማል። ሽቅርቅሩ አርከበና እጁን ሰርጉዳ የያዘችው ቆንጅዬ ነርስ ተቀዳደው ተጣሉ። አርከበ ውርደቱን ዋጥ አድርገ* ኖረ።

ይህ መጥፎ አጋጣሚ ባለፈ በወራት ውስጥ ወይዘሮ አዜብ የኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከል አውራ ሆነች። እነ አባዱላ የክልል ፕሬዝዳንትነት ስራቸውን ትተዋል እስኪባል ድረስ ጭራዋን እየተከተሉ አንዴ የአሩሲ ፣ሌላ ጊዜ የጅማዋን ወይዘሮ ቀሚስ ሲያለብሱ ከረሙ። ሽፈራው ሽጉጤና አያሌው ጎበዜ በካድሬው የሀሜት ምላሽ እስኪለበለቡ ድረስ አብረዋት በአዳራሽ መገ*ለት ቀጠሉ። የረገጠቻቸው ዞኖች የእሷን ምስሎች በያዙ ፓስተሮች ተጥለቀለቁ። እነ ዘርአይ ፣ወልዱ፣ ብርሀነ ማእረት ኢቲቪን ፣ሬዲዮ ፋናንና ዋልታን በእመቤታቸው ዜናና ዲስኩር አጨናነቁት። ይህን ተከትሎ ወይዘሮ አዜብ በአፍሪካ ቀዳማዊ እመቤቶች ዙሪያ አድናቆት ተቸራት። እሷም የሀገራችንን ቁርጠኝነት ለማሳየት የአክሱም ሀውልት ያለበት የአንገት ሀብል መሸለም ስራዬ አድርጋ ተያያዘችው። ለዚህ ጠንካራ ስራዋ የአለም አቀፍ ሽልማት ባለቤት ሆነች።

***

"ቀለም ቀቢው"

አርከበ በወራት ውስጥ የተሰጠውን በጀትና አቅጣጫ ተጠቅሞ ለውጥ ያመጣል ብሎ ያሰበው አቶ መለስ የጠበቀውን ማግኘት አልቻለም።

አርከበ አስሩንም ጣቶቹን የተለያየ ቦታ ነክሮ ሲዳክር ተመለከተው። በዚህ ድርጊቱ በመናደድ አርከበንና ካቢኔውን አስቸኳይ ግምገማ ጠራ። እንዲህ በማለትም ዘለፈው፣

"አርከበ ጣድ ያልተባልከውን ዘጠኝ ድስት ጣድክ። ከፊሉን ማመሲያ ሳታዘጋጅ አጐረናኸው፣ የተቀረውን ድንክዬ ማመሲያ አዘጋጅተህ በእጅህ ገባህበት።"

አርከበ ባልሞት ባይ ተጋዳይነት ሊፍጨረጨር ሞከረ። አቶ መለስ የመጨረሻውን ውርጅብኝ አከናነበው፡

"አርከበ እድሜ ልክህን ቀለም ቀቢ ሆነህ ትኖራለህ። መቼ ይሆን ከዚህ ስራ የምትገላገለው?" አለው።

ባለቤቱ ወይዘሮ አዜብ ይህን ዱላ ቀረሽ ስድብ ህዝቡ እንዲሰማ ስለፈለገች ለሪፓርተር ጋዜጣ ባለቤት አሳልፋ ሰጠችው። በዛው ሳምንት ሪፓርተር በርእሰ አንቀጹ "ክቡር ከንቲባ ከቀለም መቀባት ስራ እንላቀቅ" በማለት ጻፈ።

***

"የፖለቲካ ደሀ..."

በ97 ምርጫ ዋዜማ አርከበ ጥሩ የሰራ መስሎት የታክሲ ሹፌሮችን ሰብስቦ የቅጣት ምህረት አደረገ። የነጋዴዎችን ውዝፍ ግብር በተመሳሳይ እንዲነሳ አደረገ። ድርጊቱን የአዲሳባ ምርጫ የምናስተባብር ካድሬዎች ኢህአዴግ ቢሮ በሚኖረን የምሽት ስብሰባ ላይ በድል አድራጊነት ውስጥ ሆኖ ተናገረ። አጠገቤ የነበረው ተፈራ ዋልዋ ከመቀመጫው ተቆናጥሮ በመነሳት፣

"አርከበ! እድሜ ልክህን የፖለቲካ ደሀ ሆነህ ትኖራለህ። መቼ ነው አዙረህ መመልከት የምትጀምረው? እርግጠኛ ነኝ የታክሲ ሹፌሮቹ የማዘጋጃ ቤቱን አዳራሽ ለቀው ሲወጡ በጣታቸው የድል ምልክት አያሳዩ መሆን አለበት። ነጋዴዎቹም ቢሆን ቅንጅትን እያመሰገኑ ይሆናል። መሸነፋችንን አስቀድመህ ባወጅክበት ስብሰባ መሳተፍ አልፈልግም" በማለት ስብሰባውን በጠበጠ። የስኒ ማእበል አስነሳ።

የዋልዋ ግምት ትክክል ነበር።

ከምርጫው በኋላ አቶ መለስ ታክሲዎችንና ሹፌሮቹን " የቅንጅት ትሮይ ፈረሶች" ብሎ ሰየማቸው። እነሱን ከመዲናይቱ ጠራርጐ ሳያወጣ እንቅልፉን እንደማይተኛ ዛተ። የአዲሳባን ትራንስፓርት ወደ ፌደራል በመውሰድ ጊዜ ጠብቆ የሚፈነዳ ፈንጂ ቀበረ።

***

"ቡምስላግ"

የ2000 ዓ.ም የአዲሳባ ዳግም ምርጫ እየተካሄደ ነው። የአዲሳአባ ኢህአዴግ ክንፍ ስራ አስፈጻሚዎች ካሚል ቢሮ ተሰባስበን መርጦ የወጣውን ህዝብ በስልክ ከዘኖች እየተቀበልን ነው። ትልቁ ፍራቻችን ህዝቡ ሊወጣ አይችልም የሚለው ሆኗል። አቶ መለስና በረከት ጭንቀት አርግዘዋል።

ቀትር አካባቢ ላይ የህላዌ ስልክ ላይ አርከበ ደወለ። በየምርጫ ጣቢያው ምንም ሰው ዝር አይልም ፣ ሶስት ዓመት ሰራን ያላችሁት የፓለቲካ ስራ የታለ ብሎ ህላዌን አላገጠበት።

ህላዌ በረከት ሲመጣ ጠብቆ ቃል በቃል ነገረው። በረከት፣ "ይሄ ቡምስላግ!" እያለ ደጋግሞ ተሳደበ። ህላዌም ይቺኑ ቃል ደገማት። ቃሏን በጭንቅላቴ መዝግቤ ወደ ኮምፑዩተር በመሄድ ጐለጐልኩ። ደነገጥኩኝ። የአፍሪካ አደገኛ እባቦች የሚለው ዝርዝር ውስጥ የዛፍ ላይ እባብ (Boomslang) የሚል አገኘሁኝ። ይህ የውጭ ቀለሙ የሚያብረቀርቅ የእባብ ዝርያ በሳብ ሰሀራን ሀገሮች የሚገኝ ሲሆን ጊዜንና ሁኔታን አስልቶ ጉዳት የሚያደርስ ነው።

ስያሜው ገርሞኝ ወደ ካሚል ቢሮ ስመለስ አቶ መለስ ከበረከት ጋር በስልክ ይጨቃጨቃል... እውነትም ቡምስላንግ!!

***

እውን አርከበ ተወዳጅ መሪ ነው?

በመርህ ደረጃ አንድ መሪ ታላቅና ተወዳጅ ሊሆን የሚችለው ምን አይነት ባህሪያት ሲላበስ ነው? እነ ማርቲን ሉተር ኪንግ፣ ኔልሰን ማንዴላ ፣ ማልኮሚክስ፣ ማህተመ ጋንዲ ለምን ተወዳጅ ሆኑ? ምን አይነት ጠንካራ ጐን ነበራቸው? ታሪክ ዘለአለሙን ለምን ይዘክራቸዋል? ... የእነዚህ ጥያቄ መልሶች አንድ መሪን ታላቅ ወይም ተወዳጅ ለማለት ከስሜት በፀዳ መልኩ ትክክለኛውን ስእል እንድንጨብጥ ያደርጋል።

የተወዳጅና ጥሩ መሪዎች ባህሪ ህዝብ ሲበደልና ግፍ ሲደርስበት በግንባር ቀደምትነት መታገላቸው ነው። ይህም ለህዝብ ካላቸው አክብሮትና ፍቅር የሚመነጭ ነው።በተለይም በወሳኝ ወቅቶች ትግሉ የሚጠይቀውን መስዋእትነት እስከ መጨረሻው ድረስ በመሄድ ይከፍላሉ። ተወዳጅ መሪዎች ከቂም በቀል ይልቅ በይቅር ባይነት ይታወቃሉ። ከላይ የተጠቀሱት መሪዎቹ የዚህ ባህሪ ባለቤቶች ናቸው።

ተወዳጁ አርከበን ቁንጽል አብነቶችን በማንሳት በዚህ መነጽር እንመልከተው፣

በዘር የታመመ ...

በመጀመሪያ ደረጃ አርከበ ጐልቶ የሚታይበት ጐጠኝነቱ ነው። አሊ አብዶ እንዳጫወተን አርከበ ወደ አዲሳባ ተዘዋውሮ ሲመጣ ይዞ ከመጣቸው የህውሀት ካድሬዎች ውስጥ አራቱን የክፍለ ከተማ ከንቲባ ሲያደርግ በተቀሩት አምስት ክፍለ ከተሞች ደግሞ ምክትል ከንቲባ እድርጐ ሾሟል። ይህም ሰውየው ከጅምሩ ዘረኝነት የተጠናወተውና ለነዋሪው አክብሮት የሌለው

እንደሆነ የሚያሳይ ነበር።

በዚህ ማስታወሻ ላይ ለአብነት የተነሳው ትምህርት ቢሮ አርከበን በወንጀል የሚያስጠይቀው ነው። የምሁራን መናኸሪያ በሆነ ቦታ ላይ ከአስሩ ስምንቱ ከፍለከተማ የህውሀት ካድሬዎችን የበላይ ሀላፊ ማድረግ በትግራይ ህዝብ ላይ ኢንተርሀምዌይ ማወጅ ነው። ይህን አይን ያወጣ ሰንኮፍ እያየ ዝም የሚል ህሊና አይኖርም። መምህራን በምርጫ 97 ያደረጉት ይህንኑ ነው።

በመከራ ጊዜ አዲሳአባ በሰባት ማዘጋጃ ጣቢያ ስትከፈል የሰባቱም ጣቢያ መሪዎች እንዲሆኑ ያደረገው የህውሀት ካድሬዎችን ነበር።

የሌብነት አውራ...

ቀጥሎ የሚመጣው ነገር የፈፀማቸው ወንጀሎች ናቸው። ከምርጫ 97 በኃላ የተካሄዱት መንግስታዊ መሬት ዝርፊያዎች ከአቶ መለስ ቀጥሎ ተጠያቂው አርከበ እቁባይ ነው። በረከት የመሬት ወረራውን አስመልክቶ "ውሻ በቀደደው..." የሚለውን አባባል የተጠቀመው የአቶ መለስ ጥፋትን ለማሳየት ነው። "ጅብ ይገባል" ደግሞ ለአርከበ እቁባይ። ሁለቱ ባይገራረሱ ኖሮ አዲሳአባ ራቁቷን አትታይም ነበር።

በዝዋይ ህፃናት አምባ ከህይለማርያም ደሳለኝ ጋር ካድሬዎችን ለማሰልጠን በገባን ወቅት ስለ አርከበ እቁባይ ሌብነትና ህገወጥ አሰራሮች ኃይለማርያም ሲነግረን አፍ ያስከፍት ነበር። መንግስታዊ አሰራሮች ሙሉ ለሙሉ ተጥሰው በሚሊዮን ገንዘብ የሚገዙ ቁሳቁሶች ያለ ጨረታና ፐርፎርማ ይገዙ ነበር። ከከንቲባነት ከወረደም በኃላ በአርከበ ቀጥተኛ ትእዛዝ መሬት ይሰጥ ነበር። ግብር መክፈል አለባቸው ተብሎ በገቢዎች ኤጀንሲ ጥናት የተደረገባቸው ድርጅቶች እንዳይከፍሉ አድርጓል። ከዚህ አንፃር በተለይም በጂቲዜድ ውስጥ ያለ አትራፊ ድርጅት እንዲከፍል ቢወሰንበትም ጥናቱን የሰሩትን ቢሮው በመጥራት አስፈራርቷል። ግለሰቦቹም ሀገር ጥለው ተሰደዋል።

በዝዋይ ህፃናት አምባ (አላጌ) በነበረን ቆይታ ከተነሱ የአርከበ ሌብነቶች መካከል ትልቅ ቦታ የያዘው ከምርጫ 97 ማግስት የተሰጡ ሪል ስቴቶችን የተመለከተው ነበር። ይህ አስቀድሞ ህጋዊ ሽፋን የተሰጠው ሌብነት በርካታ ነገሮች ን መዘ አውጥቷል። የአርከበን ማንነት በግልጽ ያጋለጠ ነበር።

የአላጌ ጨዋታችን እንዲህ ነበር፣

አቶ ሀይለማርያም ደሳለኝ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከደቡብ ክልል ፕሬዝዳንትነት ተነስቶ በሚኒስትር ማእረግ የጠቅላይ ሚኒስትሩ

የአደረጃጀት አማካሪ ሆኖ ይመደባል። የኢህአዴግ ቢሮ ምክትል ሀላፊ ይሆናል። አቶ መለስ በመጀመሪያ እንዲሰራለት የሰጠው የሚስጥር ተልእኮ የባለስልጣናትን የሌብነት እና ህገ ወጥ ድርጊት እንዲያጠና ማድረግ ነበር። ይህን ተከትሎ ኃይለማርያም አቢይና ንኡስ ኮሚቴ ያደራጃል። የአዲሳአባ ኢህአዴግ ክንፍ በአቢይ ኮሚቴ እንዲሳተፍ በመወሰኑ ምክንያት ፀጋዬ ሀይለማርያም(በአሁን ሰአት የአዲሳአባ ፍትህ ቢሮ ሀላፊ) እንዲካተት በሙሉ መስማማት ተወሰነ። እስከማውቀው ድረስ ፀጋዬ የመንደርተኝነት ስሜት ያለው ቢሆንም ፀረ - ሌባ ነበር። በተለይም አርከበ እቁባይ የፈፀማቸውን ዝርፊያዎች በአደባባይ ከመናገር ወደ ኋላ የሚል አልነበረም። በተለይ እለቱን በውል በማላስታውሰው አንዲት ቀን ከአቶ መለስ ጋር በነበረን የጋራ ስብሰባ ላይ አርከበን ፊትለፊት እየተመለከተ" የአዲሳአባ ህዝብ ትናንሾቹ አሳዎች እንጂ ትላልቆቹ እየተጠመዱ አይደለም እያለ ነው!" በማለት ተናግሯል። አርከበ ስለእሱ እና ግብረአበሮቹ እየተናገረ መሆኑን በማወቁ የሚይዘው የሚጨብጠው ጠፍቶት ነበር። እኛም ብንሆን ፀጋዬን አቢይ ኮሚቴ ውስጥ እንዲገባ ያደረግነው ይህን ስለምናውቅ ነበር።

እነሆ! የካድሬ ሰራዊት ለማሰልጠን በአላጌ ኮሌጅ ኃይለማርያም ደሳለኝ፣ ሬድዋን ሁሴን፣ ካሚል አህመድ፣ ፀጋዬ ሀይለማርያምና እኔ ተገኝተናል። በየእለቱ ከስልጠና በኋላ የምናደርገው የምሽት ጨዋታ ደርቷል። ሁሉም የልቡን ይናገራል። በወጋችን መካከል ዘለግ ተደርጉ የተተረተረው ከምርጫ 97 ማግስት በአዲሳአባ የተካሄደው የመሬት ወረራ ነበር። በተለይ አስቀድሞ ህጋዊ ሽፋን የተሰጣቸው ፓለቲካዊ ካልሆነ በፀረ ሙስና ህገወጥ ሊባሉ የማይችሉትን ለይተን የተጫወትንበት ነበር። በወጋችን ወቅት ፀጋዬ ሀይለማርያም ማስታወሻውን እየገላለጠ በሚስጥር እንዲያጣራ የተሰጠውን ስራ ይተርክልን ነበር።

ፀጋዬ የሚያነሳቸውን በብዛት የማውቃቸውም ቢሆን በዝርዝር ሲገለጹ ሀሊና ያደሙ ነበር። በእርግጥም "ተወዳጁ ከንቲባ" አዲሳአባን ለማጥፋት ቆርጦ የሰራ መሆኑን የሚያሳዩ ነበር። የተከተለው መንገድ እጅግ ነውረኛ እና በቂም በቀል የታጨቀ እንደነበር ወለል ብሎ ያመላክት ነበር። በተለይም "ሪል እስቴት" የሚባለው የልማት አቅጣጫ ውስጡ ሲፋቅ የከተማው አርሶአደር ላይ የዘር ማጥፋት የተፈፀመበት ነበር። በሪል ስቴት ስም በምርጫው ማግስት መሬት የተረከቡት ግለሰቦች አብዛኞቹ የአንድ አካባቢ ሰዎች የነበሩና ቤሳቤስቲን ሳንቲም ያልነበራቸው ነበሩ። እነዚህ ሪል ስቴቶች መሬቱን ከወረሩ በኃላ ህገ መንግስቱን በጣሰ ሁኔታ እየሸነሸኑ ይሸጡ ነበር። ለመስማት ቢዘገንንም ከምርጫ 97 ማግስት "ሪል እስቴት" በሚባለው የጥፋት አቅጣጫ ከ3 ሚሊዬን ካሬ ሜትር በላይ የህዝብ መሬት ተዘርፉል።

የሪል እስቴት ዝርፊያው በተለይ በቦሌ፣ የካ፣ ኮልፌና ንፋስ ስልክ ክፍለከተማ የተፈፀመው ወንጀል ለቀጣዩም ትውልድ የሚሸጋገርና ጊዜ ጠብቆ ሂሳብ የሚወራረድበት መሆኑ አይቀሬ ይሆናል። እዚህ ጋር ልብ ሊባል የሚገባው ከላይ በተጠቀሱት ክፍለከተሞች ዝርፊያውን የመሩት ካድሬዎች አርከበ እቁባይ ከትግራይ ይዟቸው የመጡትና አዲሳአባ በሰባት ማዘጋጃ ጣቢያ ስትከፈል ግንባር ቀደም መሪ የነበሩት ናቸው (የካ - ግርማጺዮን፣ ቦሌ - ሀይለስላሴ፣ ኮልፌ - ነጋ፣ ላፍቶ - ሀይሌ ፍስሀ)።

የተሰጠውን የስለላ ስራ ከልቡ በእልህና ቁጭት የፈፀመው ፀጋዬ ሀይለማርያም በሪል ስቴት ስም የተፈፀመውን ሌብነት በወራሪዎቹ የድርጅት ስም፣ ወረራው በተፈፀመበት ቀን፣ የቦታው ስፋት እና አድራሻ በግልጽ በሚያሳይ መልኩ አዘጋጅቶ ነበር። በአላጌው የእሳት ዳር ጨዋታችን ወቅት ያቀረበልንም በዛው መልኩ ነበር። የፀጋዬ አቀራረብ አስደማሚ ስለነበር ኃይለማርያምን ጨምሮ ሁላችንም ከአድናቆት ባሻገር ለፀረ ሙስና ኮሚሽነርነት አጭተነው ነበር።

(ኃይለማርያም ከመስሎ አዳሪነት ተላቆ በህግና ህገ መንግስቱ የተሰጠውን ስልጣን መጠቀም ሲጀምር ፀጋዬ ኮሚሽነር ሱሊማንን ተክቶ እናየው ይሆናል።)

ፀጋዬ ሀይለማርያም በአላጌው የእሳት ዳር ጨዋታችን ካቀረበውና በማስታወሻዬ ካሰፈርኳቸው እጅግ በጣም ጥቂቶቹ የሚከተሉትን ይመስላሉ።

በመጀመሪያ ደረጃ ፀጋዬ ያቀረበልን ከምርጫ 97 ማግስት በቦሌ ክፍለከተማ በሪል ስቴት ስም ለመኖሪያ ቤት ግንባታ ህጋዊ ሽፋን ተሰጥቷቸው የወሰዱትን ነበር። በዚህ ክፍለከተማ አስቀድመው ለኮንደሚኒየም ግንባታ፣ ለወጣቶች ማእከል፣ ለአረንጓዴ መናፈሻ የተያዙ ቦታዎች በሙሉ አርከበ እቁባይ በመስክ ላይ በመገኘት ያዘረፉቸው ናቸው። በዚህ መልኩ የተወረረው መሬት ከ1.5 ሚሊዮን ካሬ ሜትር በላይ ነበር። በሪል ስቴት ስም መሬቱን ከተቀራመቱት መካከል ከ50,000 ካሬ ሜትር በላይ ለእያንዳንዳቸው የደረሳቸው ድርጅቶች ከ12 በላይ ናቸው። ከእነዚህም ውስጥ አድሮም ትሬዲንግ፣ ጋድ ኮንስትራክሽን፣ ካንትሪ ክለብ፣ ገ/ሚካኤል ሪል ስቴት፣ ተክለብርሀን አምባዬ፣ ሙሉነሽ ሪል ስቴት፣ ጌታቸው ወልዳይ ሪል ስቴት ይገኙበታል። ከሁሉም የሚያሳዝነው ሀገራችንን በአለም መድረክ በማስጠራቱ የምንወደው ሀይሌ፣ በአስታራቂ ሽማግሌነቱ የምናመሰግነው ሀይሌ፣ በአለም አደባባይ አልቅሶ ያስለቀሰን ሀይሌ "ሀይሌና አለም ሪል ስቴት" በሚል የድርጅት ስም በመስከረም 7/1998 በቦሌ ክፍለከተማ ቀበሌ 18 ውስጥ 50,000 ካሬ ሜትር ህጋዊ ሰውነቱ በነዋሪው ድምፅ ከተገፈፈው አርከበ እቁባይ እጅ

ወስዷል። መቼም ታላቁ ሯጭ እየተካሄደ ያለው ውንብድና አዲሳአባን ማጥፋት እንደሆነ ሳይገባው ቀርቶ አይመስለኝም።

ፀጋዬ በሁለተኛ ደረጃ ያቀረበልን በሀይሌ ፍስሀ (በአሁን ሰአት የአዲሳአባ ስራ አስኪያጅ) መሪ ተዋንያንነት በንፋስ ስልክ ላፍቶ የተፈፀመውን የሪል ስቴት ወረራ ነበር። በዚህ ክፍለከተማ ከምርጫ 97 ማግስት የተዘረፈው መሬት ከ300,000 ካ.ሜ በላይ ነበር። እያንዳንዳቸው ከ50ሺህ በላይ ካ.ሜ ከወሰዱት መካከል ሮማናት፣ ዩቴክ ኮንስትራክሽን፣ ፔትራም፣ ትራኮን ኮንስትራክሽን፣ ማጅኮን ኮንስትራክሽን ይገኙበታል።

ጨዋታ የሚያውቀው ፀጋዬ ከወትሮው በተለየ ፊቱን ቅጭም አድርጎ በሶስተኛ ደረጃ የነገረን የታጋይ ግርማዊዬን ልዩ ግዛት ስለነበረችው የካ ክፍለከተማ ነበር። በየካ ክፍለከተማ ከምርጫ 97 ማግስት በሪል ስቴት ስም የተወረረው መሬት ከፍተኛ የአርሶአደር መፈናቀል ያስከሰተ ሲሆን በአጠቃላይ 450,000 ካሬ ሜትር የገበሬው መሬት ተወሯል። እያንዳንዳቸው ከ50ሺህ ካሬ ሜትር በላይ ከወሰዱት ውስጥ አሴር፣ ፓስራክሲንክ፣ ሰሙ ተክሌ... ይገኙበታል።

እነዚህ እንግዲህ በወፍ በረር ከፀጋዬ ማስታወሻ ላይ የለቀምኳቸው ናቸው። ማንም ያገባኛል ባይ መሬት ወርዶ ሊያጣራቸው የሚችል። እነሆ! ተወዳጁ ምድብ ከንቲባ የእነዚህ ህገወጥ ተግባራት ባለቤት ነው።

ቂምና በቀለኛ...

በሶስተኛ ደረጃ በአርከበ ላይ የሚታየው ባህሪ ቂምና በቀልን አጣምሮ የያዘ ሰው መሆኑ ነው። በተለይ ከምርጫ 97 በኃላ በአዲሳባ ህዝብ ላይ ቂም በመያዙ ምክንያት ለመበቀል ያላደረገው ጥረት የለም። በተለይም ደህውን የአዲሳባ ህዝብ ከሚኖርበት ለማፈናቀል ተግቶ ሰርቷል። አካባቢን መልሶ ማልማት በሚል ስም ነባር ነዋሪውን ከቦታው እያስነሳ ለባለሀብቶች ሸጧል። በተለይ ለሸራተን ማስፋፊያ ቦታ ለማስለቀቅ ሲንቀሳቀስ የነበረው እንደ አንድ የአላሙዲን ጉዳይ አስፈጻሚ እስኪመስል ነበር። ይህን የተገነዘበው አቶ መለስ በእኛ ፊት ምን ብሎ እንደሰደበው ከሁላችንም ህሊና የሚጠፉ አይደለም።

በመዲናይቱ ተከስቶ የነበረው ሁከትና ብጥብጥ ከተረጋጋ በኃላ የህዝቡን ሙቀት ለመለካት የሚያስችሉ መድረኮች በየቀበሌው ተከፍተው ነበር። መድረኩን መምራት የሚችሉ ሚኒስትሮችና ሌሎች ባለስልጣናት በሚለይ ወቅት አርከበ እንዳይገባ መግባባት ላይ ተደርሶ ነበር። እንዳያወያይም

ተደርጓል። ምክንያቱ ደግሞ ህዝቡ በመሳደብ መድረኩን ወዳልተፈለገ አቅጣጫ ይመራዋል በሚል ነበር።

የስልጣን ጥመኛ...

አርከበ ከስልጣን እርከኑ ውጭ ያለን ነገር ጠቅልሎ መያዝ የሚፈልግ ሰው ነው። ለዚህ ማስረጃ እንዲሆን በባለአደራ አስተዳደሩ ወቅት ሲያደርግ የነበረውን መመልከት በቂ ይሆናል።

በአሻንጉሊቱ ባላደራ አስተዳደር ወቅት የመሬት አስተዳደሩን በቀጥታ ይመራ የነበረው አርከበ እቁባይ ነበር። ባላደራው በውስጥ የኢህአዴግ መመሪያ መሬት እንዳይሰጥ የተከለከለ ቢሆንም አርከበ ከስራና ከተማ ልማት እየተወረወረ ለሚፈልጋቸው ባለሀብቶች ይሰጥ ነበር። የባላደራው ካቢኔ (ከክንቲባ ብርሀነ ዴሬሳ) ውጪ ተጠያቂነታቸውን ለአርከበ አድርገው ነበር።

ከቀናቶች በኃላ የውስጥ ሴራው የደረሰበት ክንቲባ ብርሀኑ ደሬሳ እያንዳንዱን የካቢኔ አባል እየጠራ፣ "ከአቶ አርከበና ኢህአዴግ ጋር እየተመሳጠራችሁ እንደሆነ ደርሼበታለሁ። ከእንግዲህ ብሰማ እያንዳንድሽን አባርራለሁ" ብሎ አስጠነቀቀ። የሰውየው ንግግር ኢህአዴግና አቶ መለስ ቢሮ ድረስ ተሰምቶ ቁጣን ቀሰቀሰ። አንዳንዶቻችን በእሳት ዳር ጨዋታችን ወቅት ለክንቲባ ብርሀነ ያለንን አክብሮት አንስተን አወጋን፣ በተለይ" ኢህአዴግ ክንቲባ ሊያደርጋቸው አይገባም ነበር "የሚል ጭቅጭቅ በኢህአዴግ ቢሮ ስንሰማ ስለሰውየው ይዘን የነበረው አመለካከት የተዛባ መሆኑን አረጋገጥን። ምንም እንኳን የአርከበ ድርጊት እስከመጨረሻ ባይቋረጥም።

ርግጥ አቶ መለስ ባላደራ የሚል አስተዳደር መስርቶ ሲያበቃ የከተማዋን የልማትና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ሪፓርት ከአርከበ መስማት አልነበረበትም። ከአቶ መለስ ጋር በየሳምንቱ በሚኖረን ስብሰባ የመዲናይቱን የልማት አፈጻጸም ሪፓርት ከአርከበ እናዳምጣለን። ከከተማ እስከ ቀበሌ የተቋቋመውን የባለ አደራ አስተዳደር የሰው ሀይል እንድንመደብ ያደረገው እኛን ነበር። በተለይ ካሚል አህመድ ልዩ ሚና ነበረው። በከተማው ባላደራ ካቢኔ ውስጥ የኢህአዴግ አባላት መሆናቸውን እያወቅን ገለልተኛ ናቸው ብለን እንዲሾሙ አድርገናል። ሸሪፍ የሚባለው የክንቲባ ጽ/ቤት ሀላፊ የደህዴን አባል፣ የሚኒስትር ሬድዋን ሁሴንና ሲራጅ ፈርጌሳ የቅርብ ጓደኛ ነው። ምስጋናውና ይትባረክ የሚባሉት የማስታወቂያና ኢንዱስትሪ ቢሮ ሀላፊዎች የደኢህዴን፣ህገ-ስ የሚባለው የትምህርት ቢሮ ሀላፊ ደግሞ የህውሀት አባላት ናቸው።

ዋሸና ቀጣፊ...

በረከት ባካሄደው ጉንጭ አልፉ ግምገማ ላይ አርከበ ከግራ ከቀኝ የስንግ ሲያዝ ተደነባብሮ " የማውቀው ነገር የለም" ማለቱ ተገልጿል። " ወይዘሪት ገነት በሊዝ የወሰደችውን መሬት ሸንሽና የመሸጥ መብት አላት!" ባለ አንደበቱ በረከትና ካድሬዎች ህገመንግስቱን ጥሰሀል ብለው ማንቁርቱ ላይ ሲቆሙ፣" እኔ አጠቃላይ ነገር አነሳሁ እንጂ ስለ ወይዘሪት ገነት የማውቀው ነገር የለም።" በማለት። ከበረሀ ጀምሮ በቅርበት የሚያውቋት ታጋዮች ይህን ባህሪውን ጠንቅቀው ያውቃሉ። አቶ መለስ እንደ ቅሪላ የሚጫወትበት ይህን ስለሚያውቅ እንደሆነ ይናገራሉ።

ለዚህ ማሳያ እንዲሆን የቀድሞ የትግል ጓዱ ስዬ አብርሀ " ነፃነትና ዳኝነት በኢትዮጵያ" ብሎ በጻፈው መጽሀፍ ውስጥ ከገጽ 163 -165 የሰፈረውን ሳይበረዝ እንደወረደ ማቅረብ መርጫለሁ። ስዬ " የአቶ አርከበ አቋባይ ምስክርነት" በሚለው ርእስ ስር የሚከተለውን አስፍሯል፣

የመጀመሪያ ቅጥፈት...

"... አቶ አርከበ እኔ የትእምት/ EFFORT ዋና ስራ አስኪያጅ ሆኜ እሰራ በነበረበት ጊዜ አብረውኝ ይሰሩ ከነበሩት ምክትል ስራ አስኪያጆች አንዱ ነበር። ትራንስ ኢትዮጵያ መኪና ሲገዛ ድርድር ውስጥ በቀጥታ የተሳተፈ በመሆኑ ስለጨረታው ሂደት ፣ ስለድርድሩና ውሉ በዝርዝር ያውቃል። ትራንስ ኢትዮጵያ ለገዛቸው መኪኖች ሻጭ ኢቪኮ እንደነበረም ያውቃል። በጽሁፍ የሰፈረ ነገርም ነው።

"አቶ አርከበ ምስክርነት ሲሰጥ፣ ትራንስ ኢትዮጵያ ለገዛቸው መኪኖች ሻጭ ማን ነበር ተብሎ ሲጠየቅ "አምቼ ኢቪኮ" ነበር ያለው። አምቼ ኢቪኮ የሚባል ድርጅት አለ ወይ ብለው የእኛ ጠበቆች ሲጠይቁት "የለም" አለ። "ታዲያ የሌለ መሆኑን እያወቅክ ለምን አምቼ ኢቪኮ ትላለህ? ሻጩ ማነው? ተባለ። እንደገና "አምቼ" አለ። አንደኛው የአቶ አርከበ ሀሰት ይህ ነበር።"

ሁለተኛ ቅጥፈት...

"... ኢቬኮ ለትራንስ ኢትዮጵያ በሰጠው ዋጋ ጥቁር አባይ ለሚባል ባለቤትነቱ የቢ.አ.ዴ.ን ለሆነ ድርጅት በተመሳሳይ ዋጋና በተመሳሳይ ውል

ተጠቃሚ እንዲሆን ተደርጓል። ይህን እሱም እኔም እናውቃለን። ታዲያ በዚህ ዋጋና በዚህ ውል ተጠቃሚ የሆነ ሌላ ድርጅት ነበረ ወይ ብለው ቢጠይቁት" አልመልስም" አለ። መልስ ብለው ዳኞች ሲይዙት "አዎ አንድ ድርጅት ነበር" አለ። ማን ነው? ተብሎ ሲጠየቅ "ጥቁር አባይ" በማለት ገለፀ። እኔ እስከማውቀው ድረስ ትራንስ ኢትዮጵያ በገዛበት ዋጋና በዚያ ውል ተጠቃሚ የነበረው ይህ ጥቁር አባይ የተባለ ድርጅት ነው። ከዚያ ሌላ በዚያ ዋጋና በዚያ ውል ተጠቃሚ የሆነ ድርጅት አልነበረም።

"... ቀጥሎ የነበረው ጥያቄ ምህረተአብ ስለገዛቸው 5 መኪኖች ምን ታውቃለህ የሚል ነበር። አቶ አርከበ ሲመልስ "ስየ ለትራንስ ኢትዮጵያ በተሸጠው ዋጋ ለወንድሜ እንዲሸጥለት አምቼን ጠይቅልኝ አለኝ። ይህ ለስምህ ጥሩ አይደለም ብዬ መለስኩለት። ለትራንስ ኢትዮጵያ የተሰጠ ጥቅምም ለሌላ የሚተላለፍ አይደለም አልኩት። ይህን ጥያቄ ለአምቼ ስራ አስኪያጅ አላስተላልፍም አልኩት" አለ። ከዚህም ባሻገር " ትራንስ ኢትዮጵያ ያገኘው ጥቅም ለሌላ አይተላለፍም የሚል ነገር ተናግሬያለሁ" አለ። ለጥቁር አባይ እንደተላለፈ ግን እኔም እሱም እናውቃለን። ዉሉ ላይ ጥቅምን ለሌላ ማስተላለፍን የሚመለከት ምንም ነገር የለውም። ዝም ብሎ ያመጣው እውነት ያልሆነ ንግግር ነበር።

ሶስተኛ ቅጥፈት...

"አምቼን ጠይቅልኝ ብሎህ አምቢ ስትለው ምን አለህ? ተባለ።" እንግዲያው አንተ ካልፈቀድክ ለፀሀይ ነጋሽ ንገርልኝ ፀሀይ ነጋሽ መልእክቱን ለአምቼ ያድርስልኝ ብሎኛል" አለ። አርከበ እኔን አለቃውን እምቢ ሲለኝ ሌላ አማላጅ እንዲልክልኝ አርከበን ጠየቅኩት ማለቱ ነው። ከዚያ በኋላስ? ሲሉት፣ "ከዚያ በኃላማ ፀሀዬን ጠራሁትና ስየ ይህን ጥያቄ ጠይቆኛል ብሏል፣ እኔ ግን አላመንኩበትም። ይህ ከትእምት ስራ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። የግል ጉዳይ ነው ብዬ ነገርኩት" አለ። የግል ጉዳይ ነው፣ ከትምእት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፣ ይህን ነገር አላምንበትም እያለ በሌላ በኩል ግን የማያምንበትን ነገር አስተላለፍኩ እያለ ነው።"

አራተኛ ቅጥፈት...

"ከዚያ በኃላስ? ሲሉት፣" ሁኔታውን አልተከታተልኩም፣ ግን ምሕረተአብ ለትራንስ ኢትዮጵያ በተሸጠለት ዋጋ መኪኖችን እንደገዛ ሰማሁ" ነበር ያለው። ሰማሁ እንጂ አወቅኩ ብሎ የተናገረው ነገር የለም።"

እንግዲህ አቶ አርከበ ከንቲባ በተመደበ በማግስቱ ፍርድ ቤት ቀርቦ እንዴት እንደ ዋሸ ከስዬ መጽሐፍ ማየት ይቻላል። ይህ በፍርድ ቤት የተመዘገበ መረጃ ስለሆነ ሊስተባበል የሚችል አይደለም። ባይሆን ትልቅ ጥያቄ ሆኖ መነሳት ያለበት አቶ መለስ አርከበን ከንቲባ በሾመ በቀናት ውስጥ ምስክር እድርጌ ለምን ላከው የሚለው ይሆናል። ማንም ትንሽ አዙሮ ማየት የሚችል ሰው በፍርድ ቤት ከተካሄደው አሰጣ ገባ አንድ ነገር መዘ ማውጣት ይችላል። በስየ አብርሀ ወንድም (ምህረተአብ) የመኪና ግዥ ውስጥ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የአርከበ እጅ አለበት። አርከበ ሰምቶ ዝም ማለቱ ብቻ በወንጀለኝነት ያስጠይቀዋል። እነሆ! የአቶ መለስ የካርድ መዘዛና ቅርቃር ወደ ተግባር ሲለወጥ ይህን ይመስላል።

የግርጌ ማስታወሻ

1. የሁለት ምርጫዎች ወግ፣ በረከት ስምኦን 2003 ዓ. ም
2. የኢፌዲሪ ህገ መንግስት
3. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር፣ 1995 ዓ. ም
4. የማስፈፀም አቅም ማንባታ ስትራቴጂ፣ 1994 ዓ.ም
5. ነፃነት እና ዳኝነት በኢትዮጵያ፣ ስየ አብርሀ፣ 2002 ዓ.ም
6. አለም ጠፍጣፉ ናት፣ ጆን ፍሪድማን፣ እ.ኤ.አ 2006
7. የእነ ህላዌ ዮሴፍ የይቅርታ ደብዳቤ፣ 1997 ዓ.ም
8. የነጋሶ መንገድ፣ ዳንኤል ተፈራ፣2003 ዓ.ም
9. መልካም አስተዳደር ፣ ፍራንሲስ ፉኩያማ ፣እ.ኤ.አ 2004
10. ሪፓርተር ጋዜጣ ፣2003 ዓ.ም
11. የደራሲው ማስታወሻ፣ ተስፉዬ ገበረአብ፣2002 ዓ.ም
12. ዲሞክራሲና ሁለንተናዊ ልማት በኢትዮጵያ፣ ዶክተር ብርሀኑ ነጋ እ.ኤ.አ 2013
14. የተሻሻለው የኢትዮጵያ የምርጫ ህግ፣ አዋጅ ቁጥር 532/2007
15. የዲሞክራሲ ማንባታ ጥያቄ በኢትዮጵያ፣ 1994 ዓ. ም
16.ዲሞክራሲና ዲሞክራሲያዊ አንድነት በኢትዮጵያ፣ 1998 ዓ.ም